አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ተፈጥሮን መናቅና ሥጋን ማክበር፤ ለክፉ ዐይን አጋላጭ ክስተት በምሥራቅ ጎጃም በሚገኘው የኅዛምን ማኅበረሰብ እምነት

በ

ዋልተንጉሥ መኮንን

መጋቢት፣ 2007 ዓ/ም

አዲስ አበባ

ARABA UNIVERSITY
LIBRARIES
BOX 117

ተፈጥሮን መናቅና ሥጋን ማክበር፤ ለክፉ ዐይን አጋላጭ ክስተት በምሥራቅ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማኅበረሰብ እምነት

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለፎክሎር የፒ.ኤች. ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ዋልተንጉሥ መኮንን

2007 ዓ/ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ተፈጥሮን መናቅና ሥጋን ማክበር ለክፉ ዐይን አጋላጭ ክስተት በምሥራቅ ጎጃም በሚገኘው የኅዛምን ማኅበረሰብ እምነት

በ

ዋልተንጉሥ መኮንን

2007 ዓ/ም

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም	ፊርማ
ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር)	----------
የውስጥ ፈታኝ ስም	ፊርማ
ሀብታሙ ወንድሙ (ፕሮፍሰር)	----------
የውጭ ፈታኝ ስም	ፊርማ
ተስፋዬ ዳኘው (ዶ/ር)	----------

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

አጠቃሎ

ይህ ጥናት በጎዛምን ሰዎች አስተሳሰብ፣ ዕውቀትና ባሕርይ ውስጥ ክፉ ዐይን የያዘውን ሰፊ ትርጉምና ግዝ ቦታ የፎክሎር ጉዳዮችን በመያዝ የመረመረ ነው፡፡ የጎዛምን ወረዳ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ የዞን መስተዳድሮች መካከል አንዱ በሆነው የምሥራቅ ጎጃም ዞን ውስጥ የሚገኝ አስተዳደራዊ ቦታ ነው፡፡ ይህ ወረዳ በአጠቃላይ በ25 የገጠር ቀበሌዎች፣ በአንድ ንዑስ ታዳጊ ከተማ እና በአንድ የከተማ አስተዳደር የተዋቀረ ሲሆን፣ በጥናቱ የተካተቱት ግን በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ሰባት ቀበሌዎች ናቸው፡፡

ይህን ጥናት ለማካሄድ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከቀዳማይና ከካልኣይ ምንጮች ነው። ቀዳማይ ምንጮች በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይትና ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችን በማሳተፍ የተገኙ ሲሆን፣ በመረጃ ምንጭነት በአጠቃላይ 15 ሴት እና 34 ወንድ በድምሩ 46 ሰዎች ተሳትፈውበታል፡፡ መረጃው ከሚያዚያ10፣ 2003 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 26፣ 2006 ዓ/ም ባለው ጊዜ የተሰበሰ ሆኖ፣ አራት ዙር ምልልስና የስምንት ወር ቆይታ ተደርጎበታል፡፡

በጥናቱ የተሳፉ ሰዎች የተመረጡት በዓላማ ተኮር (purposive sampling)፣ በጠቋሚ ናሙና(Snowball Sampling) እና አልፎ አልፎ በአመች ንጥና (Convenience Sampling) ስልቶች ሆኖ፣ በከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ (Semi structured Interview) እና በኢመደበኛ ቃለ መጠይቆች (Informal interviews) መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡ ቃለ መጠይቁ በዲጅታል መቅረጸ ድምጽ የተቀረጸ ሲሆን፣ በድንገት የተገኙ አስተያየቶችና ምልከታዎች በማስታወሻ ደብተር ተገልብጠዋል፡፡ ደጋፊ መረጃዎች በዲጅታል ፎቶ ካሜራ ተይዘዋል፡፡ በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትክክለኛነት በመስክ ላይ በተካሄደ ምልከታ፣ ከቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ጋር በተደረገ ውይይት እንዲሁም በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት ከተደረጉ የጋራ ውይይቶችና መግባባቶች በመነሳት ትክክለኛነታቸው ተመዝኗል፡፡ በአጠቃላይ ሦስት ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምድብ ሰባት፣ በሦስተኛው ደግሞ ስምንት ሰዎች ተሳትፈዋል፡

እያንዳንዱ ፍጡር ሚዛንና ልክ ካላቸው ባሕርዮች እንደተገኘ ይታመናል፡፡ ከዚህ ልክ የሚያወጣ አድራጎት መሥራት፣ በባሕርዮች መካከል አለመስማማትን ይፈጥራል፡፡ በሥጋ ባሕርያት መካከል ሚዛንና መመጣጠን ሲጠፋ በመካከል ያለ ትስስር ይላላል፡፡ ከፍጥረቶች መካከል ይሽን መነባት ጠባይ ያደረጉ ከሰው፣ ከእንስሳትና ከተክሎች ወገን የሆኑ ፍጥረቶች አሉ፡፡ በእነዚህ ፍጥረቶች ውስጥ ያለ ዐመል ግላዊነት፣ በልክ አለመኖር፣ ገፊነት፣ ተሻሚነት፣ መራቨርነት፣ ደም መጣጭነት፣ ሙት ፈላጊነት፣ አፍላሽነትና የመሳሰሉ የራስ ወዳድነት ስሜቶች ናቸው፡፡ እንደዚህ ያሉ ጠባዮች በፍጥረቱ ላይ ሞት፣ ዕልቀት፣ ባዶነት፣ ድካም፣ ህመምና ስንፍና ይተክላሉ፡፡ ይህ ጠባይ ራስ

ማዘዙን ነስቶ ፍጹም ተግዥ ያደርጋል። ፍጥረቱ በአካሉ ላይ የማዘዝ መብቱን ያሳጣዋል። ይኸን ውድቀቱን በመጠቀም የሚተክሉ፣ በድክመትና በስስት የሚገቡ፣ በመጋለጡ የሚጠቀሙ መልካም ያልሆኑ ኃይሎች ክፉ ዐይኖች ይባላሉ። በመሆኑም፣ ስስታምና ስግብግብ የሆኑ፣ ራሳቸውን አብዝተው የሚወዱ፣ ለሥጋ ፈቃዳቸው የሚገዙ ፍጥረቶች ላይ ይኸ ኃይል ተግላጭ ነው።

በመሆኑም፣ በነዛምን ለክፉ ዐይን የሚያጋልጡ አውዶች ከጊዜ ጨለማና ክረምት፣ ከሽግግር ሥርዓቶች ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት፣ ከዕድሜ ሽምግል፣ ከተክሎች ህይወት የአመድ ዘመን፣ ከሰብሎች የዕድገት ወቅት የአውድማ ጊዜና የማዕድ ሥርዓት፣ የአተላና የአምቡላ ወቅቶች ዋነኞች ናቸው። በመሆኑም፣ ከዚህ ጥቃት ለማምለጥ ዋነኛ የመከላከያ መንገድ የሚሆነው ህይወትን በምላኔና በልክ ማኖር፣ ማካፈልን መልመድ፣ ትርፍ ከመያዝ መቆጠብ፣ ሥጋ እንደመራና ስሜት እንዳዘዘ አለመሆን፣ ራስን በዕውቀትና በማስተዋል ማስተዳደር፣ የሰውን መፈለግንና መመኘትን ማነወር፣ ተፈጥሮውን መጠበቅ፣ ራስን ለተለያዩ ፍላጎቶችና ስሜቶች አለማጋላጥ፣ ለጥንካሬው ምልክቶች ዋጋና ክብር መስጠት፣ ከመጤና እንግዳ ጠባዮች ጋር ሳይዳቀሉና ሳይበረዙ መኖር፣ የተለየና አዲስ የሆነን ጠባይ አለመልመድ፣ ነባሩን ማክበር። በተጨማሪ፣ አጥፍቶ ለመመለስ፣ ተመክሮ ለመቀበል፣ አዳምጦ ለመረዳትና ለመገራት፣ ለመቅናት፣ ለመልዘብና ለመመለስ ታጣቂ መሆን፣ ናቸው

ይኸንን ሁሉ አልፎ መጋለጥ ቢመጣ ንስሐን ከባሕርይ ሙላላነፍ አውጥቶ ወደ ቀደመ የተፈጥሮ ሚዛን እና የሰብዕና ስፍር መመለሻና ማስተካከያ መንገድ ይሆናል። በግብር የተጣሉትን ባሕርዮች እንዲታረቁ፣ እንዲስማሙና እንዲመጣጠኑ በማድረግ ተጠቂውን አካል ከክፉ ዐይን ማዳን ይቻላል። ሥጋን በመቅጣትና በማስተካከል፣ ነፍስን ወደቦታዋ ለመመለስ በሚደረገው ሥርዓት ውስጥ አራት ዘዴዎች አሉ። እነሱም ጸሎት፣ ምጽዋት፣ ጾምና ስግደት ናቸው። የእነዚህ ማስተካከያ ዘዴዎች ዋና ተግባር ሥጋ የሰበሰበውንና ያጠራቀመውን የሚበትኑ፣ የሚቀንሱ፣ የሚጠርጉና የሚያራቁቱ፣ በዳይ በጸጸት፣ ራስን በመውቀስ ፈቅዶና ወዶ ወደራሱ ነባር እንዲመጣ የሚያደርጉ ተፈጥሮን ማግኛ መንገዶች ናቸው።

ታህሳስ፣ 2007 ዓ/ም

አዲስ አበባ

አበርክቶ

ይህ ሥራ መታሰቢያነቱ

ለእናቴ ለእማሆይ ማናዬሽ ፍካሬ፣

ለባለቤቴ ለኤልሳቤጥ ፀጋዬ፣

እንዲሁም ለልጆቻችን

ለካሌብ እና ለኢያሱ ይሁንልኝ።

ምስጋና

ይህ ጥናት ለፍሬ የደረሰው በርካታ ግለሰቦችና ተቋማት አስተዋጽኦ አድርገው ነው፡፡ በመጀመሪያ ከርዕስ መረጣ ጀምሮ እስከፍጻሜ ድረስ አቅጣጫ በመስጠት፣ የጥናት ወረቀቱን በማረምና በማስተካከል፣ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ለዶ/ር ፈቃደ አዘዘ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ከሁሉም በላይ የጥናቴ ፈርጦች የመረጃ አቀባዮቼ ናቸው፡፡ ሳይሰለቹና ሳይታክቱ የጠየቅኳቸውን ሁሉ በመመለስ፣ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ዕውቀታቸውንና ልምዳቸውን ያካፈሉኝን የትዛምን አካባቢ የጥናት ተሳታፊዎች ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ያለእነሱ መልካም ፈቃድና ትብብር ይኸ ሥራ የትም አይደርስም ነበርና፡፡ በመቀጠል፣ የመስክ ቆይታዬን የተመቸና የተደላደለ ላደረጉልኝ፣ ከሰዎች ጋር በማገናኘት አብረውኝ ለደከሙት ለአቶ ተዘራ አስማረና ለአቶ ጥላሁን ውሃቤ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በተለይ፣ አብሮኝ ደጋውንና ቆላውን ሲረግጥ፣ ሥራውን ትቶ ሲለፋና ሲደክም ለነበረውና ድንገት ታምሞ መስከረም 16 ፣ 2007 ዓ/ም በሞት ለተለየኝ ለወንድሜ ቀረዓለም ሙሉቀን፣ “አምላክ ነፍስህን በክብር ያኑራት” እላለሁ፡፡ በአካባቢው ያለምንም የጸጥታ ችግር መረጃ እንድሰበስብ፣ በሂድኩባቸው መሥሪያ ቤቶች የፈለኩትን መረጃ እንዳገኝ የረዱኝ የዞንና የወረዳ መሥሪያ ቤቶች፣ ባለሙያዎች፣ ኃላፊዎች አመሰግናቸዋለሁ፡፡

እናቴ እማሆይ ማናዬሽ ፍካሬ በማስታወስ ችሎታሽና ነገሮችን በመመርመር ብቃትሽ በጣም ተገርሜያለሁ፡፡ ምናልባት ለውጤት እንድበቃ ባለሽ ጉጉት አእምሮሽን ከሚገባው በላይ ያስጨነቅሽው ይመስለኛል፡፡ ዕድሜና ጤና እንዲሰጥሽ እመኛለሁ፡፡ ያለ አባት አሳድገሽኛል፣ አላንደልሽብኝም፡፡ ምናልባት በዚህ ባስደስትሽ ብዬ ፀሎቴና ልመናዬ ሁሉ መጨረሻዬን እንድታይ ነበር፡፡ ሊሳካልኝ ነው መሰል፡፡

ባለቤቴ ኤልሳቤጥ ፀጋዬ፣ ልጆቻችን ካሌብና ኢያሱ ለትግስታችሁ፣ የልጅነት ዘመናችሁን ስለተጫንኩት ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ ለሁሉም ነገር ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ እህቶቼ ባሳገነው መኮንን፣ ዓለሚቱ መኮንን፣ አጸደ መኮንን፣ ይደነቁ መኮንን፣ ወንድሞቼ ውብሸት መኮንን፣ ምስክር መኮንን፣ ይልቃል መለሰ፣ ዘመኑ ከፋለና አለሰው ይግባው ላደረጋችሁልኝ ትብብር ሁሉ አምላክ ዋጋውን ይክፈላችሁ፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የግንዘብ ድጋፍ ስላደረገልኝና የትምህርት ዕድል ስለሰጠኝ አመሰግነዋለሁ፡፡ መቐለ ዩኒቨርስቲ ከሁለተኛ ዲግሪ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ላደረገልኝ የግንዘብ፣ የማቴሪያልና ልዩ ልዩ ድጋፍ ስላደረጉልኝ በጣም ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በሃሳብ ከጎኔ ሆናችሁ ለመከራችሁኝ፣ መጽሐፍ ላዋሳችሁኝና ለሰጣችሁኝ የሥራ ባልደረቦቼና የክፍል ጓደኞቼ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ በደረጃ ማበልጸጊያ ወቅት ትኩረቴን በመሰብሰብና አካሄዴን በማረቅ ጥናቴን መስመር ላስያዙልኝ ለዶ/ር ጉዳይ እምሬና ለዶ/ር ስርግው ገላው የከበረ ምስጋና አለኝ፡፡

የገጽ ማውጫ

ማውጫ---------- ገጽ

አጠቃለሎ----------I

አበርክቶ----------III

ምስጋና----------IV

የገጽ ማውጫ----------V

1. የ ጥናቱ መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 4

1.2. የጥናቱ ዓላማ 10

1.3. የጥናት አካባቢ ምርጫ 11

1.4. የጥናቱ ወሰን ወይም ገደብ 13

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ 14

1.6.የጥናት ጽሑፉ አደረጃጀት 15

2. የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት፣ ትውራዊ አቀራረቦች፤ የጽንሰ ሐሳብ ማዕቀፎችና የመተንተኛ ሞዴል 17

2.1. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት 17

2.1.1. የሃገር ውስጥ ጥናቶች 17

2.1.2. ከኢትዮጵያ ውጭ የተደረጉ ጥናቶች 23

2.2. ትውራዊ አቀራረቦች 32

2.2.1. የስነአእምሮ እይታ ክፉ ዐይንን ለማጥናት 32

ተግባራውያን አቀራረብ 38

2.2.2. የተግባራውያን-መዋቅራውያን አቀራረብ 43

2.2.3. መዋቅራውያን 51
2.3. ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ 55
2.4. የመተንተኛ ሞዴል 58
3. የምርምር ስነዘዴና የመስክ ተሞክሮ 61
3.1. የመስክ ልምድ ሁኔታ 61
3.1.1. ካልአይ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ 68
3.1.2. የቀዳማይ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ 68
3.2. የመረጃ መተንተኛ ስልት 73
3.2.1. የቀዳማይ መረጃዎች አተናተን 73
3.2.2. የካልአይ መረጃዎች አተናተን 74
3.3. የመስክ ላይ ተሞክሮዎች 74
4. መልክዐምድራዊ፣ ማህበራዊ ፣ ታሪካዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በምሥራቅ ጎጃም 85
4.1. የመልክዐ ምድራዊ ገጽታ ማስተዋወቂያ 85
4.2. የጎጃም ሰዎች የአሰፋፈር ታሪክ 86
4.3. የማህበራዊ ማንነት አገነባብ 90
የጋራ ልምዶች 91
ራስን መቻል 95
የመልክዐምድራዊ ገጽታ አስተዋጽኦ 98
4.4. ከጎላምን አካባቢ ከተሰበሰቡ መረጃዎች የተገኙ እሴቶች 101
መብዛትን ማክበር 102
የቀደመውን መጠበቅ (Originality) 103
ዘር መቁጠር 107

VI

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA

ጅግናን ማክበር 109
4.5. የዝምድና መፍጠሪያ መንገዶች 111
5. የክፉ ዓይን እሳቤና የማደሪያ አካሎች ምንነት 117
5.1. የክፉ ዐይን መንፈስ ምንነት 117
5.2. የክፉ ዐይን ባሕርይ 125
5.3. የክፉ ዐይን ወኪሎች 126
5.3.1. ሰዋዊ የክፉ ዐይን ወኪሎች 127
5.3.3. የክፉ ዐይን ማደሪያ እንስሳት 146
6. ተጋላጭነትና አጋላጭ አውዶች 149
6.1. የሰብአዊነት አደካከም 149
ጋብቻ 149
እርግዝና 154
እርጅና 159
መካንነት 161
6.2. የጊዜ ዕልቀት አውዶች 167
ጨለማ 168
አርብ 171
ክረምት 174
6.3. የሰብለሎችና የተክለሎች አስሳሰም 178
የእህል አደካከም 178
ማዕድ 181
አመድ እና አተላ 182
7. የክፉ ዐይን መከላከያ መንገዶች 186

7.1. ፍትሃዊ መሆን 186
7.2. መከላከልን ማጥበቅ 204
ቀንድ 205
ራስ 207
የፊት እግር 210
ቆዳ ወይም ቁርበት 216
7.3. ንጽሕናን ማክበር 223
7.4. ታጣቂ መሆን 230
8. ሥርዓተ ንስሐ፤ የመፈወሻ መንገድ 238
8.1. ሥርዓተ ንስሐ 238
8.2. የባሕርይ ማስታረቂያ ግብሮች 241
ምጽዋት 244
ጸምና ስግደት 248
ፀሎት 253
8.4. የማስፈጸሚያ ስልቶች 264
የ7 ቁጥር ሚና 265
የ3 ቁጥር ሚና 272
9. ማጠቃለያና ይሁንታ 280
9.1. ማጠቃለያ 280
9.2. ይሁንታ 290
ዋቢ መጻሕፍት 293
1. አባሪ
1.1. በቃለመጠይቅ የተሳተፉ አባላት ግላዊ መረጃ መዘርዝር

1.2. በአካባቢው እሴቶች፣ የዝምድና መፍጠሪያ ስልቶችና ታሪኮች ላይ በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሳተፉ

1.3. በሽሽግግር ሥርዓት ልማዶች ውስጥ ስለተከለከሉና ስለተፈቀዱ ነገሮች ከሴቶች ጋር የተደረገ የተተኳሪ የቡድን ውይይቶች

1.4. በንጽሕና፣ በርክሰት፣ በነፍስና ሥጋ ባሕርይ፣ በመፈወሻ ዘዴዎች ዙሪያ

1.5. መዳዩ ቃላት

1.6. የአማራ ክልል ካርታ

1.7. የምሥራቅ ጎጃም ዞን ካርታ

1. የ ጥናቱ መግቢያ

ክፉ ዐይን በአብዛኞቹ የዓለማችን ክፍሎች ከታሪክ ንጋት ጀምሮ በሰፊው የሚታወቅና ረጅም ዘመን የቆየ (was born on Olympus)፣ ከዘመን ጋር ራሱን እያስማማ የኖረና የሚኖር እምነት ነው (Berry, 1968, 250)[1]። እምነቱ በሁሉም የዓለማችን ክፍሎች ባይታወቅም፣ በተለይ ከሕንድ እስከ አየርላንድ፣ ከሰሜን አሜሪካ እስከ ሰሃራ አፍሪካ ባሉ አካባቢዎች ባህል የሆነ ነው ይሉታል (Dundes, 1971, 259)። በኢንዶ-አውሮፓና በሴም ሕዝቦች ውስጥ ደግሞ የአይዲዎሎጅ መፍለቂያና የማንነት መግለጫ ነው ብለው ይናገሩለታል (Vallee, 2010, 209)[2]።

በክፉ ዐይን ምንነት ላይ ጥናት ያካሄዱ አንዳንድ ምሁራን እንደሚያስረዱት፣ እምነቱ፣ "ማህበረሰባዊ ዝምድናን አመላካችች" indexes of social relations ነው በማለት ያስረዳሉ (Marwick,1952,122)። ሌሎቹ እንዲሁ እሴታዊ ሥርዓቶችን ለማጽናት የሚያስችልና ማህበራዊ ተቋምን ለማስጠበቅ የሚረዳ ኃይል ነው as forces supporting the system of values, and hence sustaining the social structure በማለት ይገልጹታል (Marwick,1952,122)። ፍትሃዊነትን መጠየቂያና አድሏዊነትን መሚገቻ መሳሪያ አድርገው የሚረዱትም እንዲሁ በርካቶች ናቸው። ይህ እምነት አለመግባባቶች በበዙባቸው፣ ውጥረቶች በጠነከሩባቸው፣ ጭንቀቶች ባየሉባቸው ቦታዎች የሚታይ በመሆኑ፣ በጎ ያልሆኑ ስሜቶች የሚገለጽበትና ብሶት የሚወጣበት የስነአእምሮ ገጽታ አለው እያሉ የሚበይኑትም አሉ (Sanders, 2001,6) ።

በዚህ ምክንያት የማህበራዊ ጭንቀትና መታወክ መምጫ ምንጮችን ለማወቅ፣ የምሬትና የበደል የግፍና የአድልዎ አይነቶችን ለመረዳት፣ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ትብብርንና መተጋገዝን የሚያዳክሙ ሁኔታዎችን ለማስረዳት ሲፈልግ ክፉ

---

[1]ጽሑፉን ያቀረቡት የውጭ ዜጎች ከሆኑ ስማቸውን ተከትሎ የሚመጣው ዓመተ ምህረት በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር የተገለጸ ሲሆን፣ የጽሑፍ አቅራቢዎች ኢትዮጵያውያን ከሆኑ ስማቸውን ተከትሎ የሚመጣው አቆጣጠር በኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር ይሆናል።

[2]Alan Dundes እንደ ቡዳ ያለ ጠንካራ ጉልበት ያለውና በሁሉም ቦታ የሚገኝ ሌላ ሃገረሰባዊ እምነት አለ ብሎ ማሰብ ይከብዳል ይላሉ it is difficult to think of a more pervasive and powerful folk belief than the evil eye (p,259)።

ዐይንን የምርምር ጭብጥ እያደረጉ ብዙ የትምህርት ዘርፎች ያጠኑታል (Strathern, 2004, ix) ።።

አንዳንድ ተመራማሪዎች፣ የክፉ ዐይንን እምነት፣ የሰው ልጅ በጥንታዊ ታሪኩ የሚያገኘውና ተሻግሮ የሚያልፈው፣ በቀዳሚ የአስተሳሰብ ዕድገት ደረጃው ላይ የሚያጋጥመው፣ በስልጣኔ መስፋፋት በትምህርት መዳረስ የተነሳ እየተዳከመና እየጠፋ የሚሄድ የጥንታዊ ማህበረሰቦች ባህል ነው ብለው የሚያስቡ ተመራማሪዎች ነበሩ (Malinowski, 1945, 94)። ከአብርሆት (Enlightment) ዘመን ጀምሮ፣ ከስልጣኔና ከትምህርት መስፋፋት፣ እንዲሁም ከሚስዮናውያን እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ይዳከማል የሚል እምነት ቢኖርም፣ ከመጥፋት ይልቅ ጉልበቱ እየበረታና እየተስፋፋ፣ ከዘመን ጋር ራሱን እያዛመደና ልዩ ልዩ ፍቺና እሳቤ እየያዘ የመጣ ቁልፍ ሰዋዊ ጉዳይ ሆኗል (Malinowski, 1945, 94)።

እምነቱ በተወሰኑ ማህበረሰቦች ውስጥ ባህል ሆኖ እንዲገለጥ ሰበብ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች አሉ። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፣ በማኅበራዊ አደረጃጀታቸው ውስጥ ልዩ ልዩ ዘውጎች ካሉባቸው ማኅበረሰቦች ይልቅ፣ አንድ የዘር ዘውግ ባላቸው ማህበራዊ ሥርዓቶች ውስጥ ይህ እምነት ጠንክሮ ይገለጣል የሚሉ ጥቆማዎች አሉ (Douglas, 1970,117)። ውጫዊ ድንበራቸውን ለሌላ እንግዳና መጤ ማኅበረሰብ ዝግ ባደረጉና ውስጣዊ አደረጃጀታቸው ላይ ብዙ ችግሮች በበዙባቸው ማህበረሰቦች ይህ እምነት የተንሰራፋ ነው የሚሉ የጥናት ውጤቶች አሉ (Douglas, 1970,118)። Malinowski (1945, 94) ምንም እንኳ በአንድ ዘር መያዝና አለመያዝ ከክፉ ዐይን ጋር ያለውን ግንኙነት ባይገልጹም፣ "የኢኮኖሚ ቀውስ፣ የማህበራዊ ውጥረት፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ጭቆና መንሰራፋት እንዲሁም የምግባር ጥሰት ለክስተቱ መቀስቀስና መኖር አሳይ ምልክት ነው ይላሉ።

የክስተቱን መኖር ከማህበራዊ ህመሞች መባባስ ጋር አነጻጽረው የሚገልጹ አንዳንድ አጥኝዎች፣ ለክፉ ዐይን እምነት ያላቸው ስሜት በጎ ነው። ማህበራዊ እሴቶችን ለመጠበቅና ሰብዕናን ለማረጋጋት፣ አዳዲስና እንግዳ ሃሳቦች ገብተው እንዳያውኩ ለመገደብ፣ ነባሩን ለማጽናትና አዲሱን ለማራቅ፣ ወግና ልማድን ማስከበሪያ

ማህበራዊነትን መቆጣጠሪያ (social control)፣ ተሰሚነትን ማግኛና እሴትን ማስጠበቂያ መንገድ ነው በሚል ይደግፉታል (Moore, 2004, 7; Marwick,1965; Turner, 1964)። Douglas (1970: xxi) ፡፡ "አላስፈላጊ መቀራረብን ለመከላከል (as an instrument for breaking off relations) ማህበራዊ ዝምድናን ለማጎልበት (to strengthen a society) መተኪያ የለውም" በማለት የክስተቱን መኖር በአዎንታዊ ጎኑ ይመለከቱታል። አንዳንዶቹ ግን የኃይሉ ምንጭ ስነ አእምሯዊ ይሁን "ማጅካዊ"፣ ጉዳቱ ሆን ተብሎ ይፈጸም ከቁጥጥር ውጭ በሆነ አጓጊን ያለ ዕውቀት ይምጣ፣ ውርሰቱ በዘር ይሁን በትምህርት በበጎ መታየት የለበትም ብለው የሚሞግቱም አሉ (Vallee, 2010, 209)።

በክፉ ዐይን ላይ የተካሄዱ አንዳንድ የዳሰሳ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የአብዛኛዎቹ ጥናቶች ትኩረት፣ ለማህበራዊ ግንኙነትና ዝምድና መሻከር ሰበብ የሆኑ ችግሮችን ለመንቀስ፣ ለስነልቦና መናጋት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ችግሮችን ለመቅረፍ፣ ማህበራዊ ውቅሮችን ለማስጠበቅ፣ እሴቶችን ለማጽናት፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ለመጠገን (social maintenance) (Herzfeld, 1981,562) ፤ ለዕድል፣ ለሰብዕና፣ ለተጠያቂነት፣ ለሰበብና ለሌሎችም መልካም ላልሆኑ አጋጣሚዎች (misfortune) መፈጠር ምክንያት ሆኖ ነው (Evans-Pritchard, 1937, 99-106) ፡፡ አጥኝዎችም በብዛት የስነአእምሮ፣ የስነሰብዕና የስነማህበረሰብ ተመራማሪዎች ናቸው።

ነገር ግን፣ ጥናቶቹ እምነቱ በሰዎች የማንነት አቀራረጽ፣ በአንድ ጎብረተሰብ ባህል፣ አስተሳሰብ፣ ልማድ፣ የተፈጥሮ እሳቤ በአጠቃላይ ህይወት ውስጥ ያለውን ቦታና ትርጉም በአግባቡ የመረመሩ አይደሉም። መሠረቱን እየተው ምልክቶችን በመግለጽ፣ ውስጡን ከመመርመር ይልቅ ተጓዳኝ ጥቅሞቹን በማጥናት ላይ ትኩረት ሲያደርጉ ይታያል። በተለይ፣ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመያዝ ምንነቱን ለማወቅ የተደረገው ሙከራ መጠነኛ ነው። ክስተቱን በመመርመር ሌሎች ችግሮችን ለመንቀስና የመረጃ ምንጭ አድርጎ ከመጠቀም ባለፈ እምነቱን ራሱን ለማጥናት የሚደረገው መከራ ያነሰ ነው።

ከጥናቶቹ የተገኙት አስተሳሰቦች፣ ጽንሰ ሐሳቦችና እሳቤዎች በክስተቱ ላይ ግንዛቤን በመፍጠሩ ረገድ ያስገኙት ዋጋ ሲመዘን ቀላል የሚባል ባይሆንም፣ እስካሁን ድረስ

ያልተተረጎመ፣ ክፍተት የፈጠሩና ሊታወቁ የሚገባቸው በርካታ መረጃዎች ስለመኖራቸው ማወቅ ይገባል። ቀደምት ጥናቶች በጽንሰ ሐሳቦቹ ዙሪያ ያነሷቸው ውስብስብ፣ አሻሚና ተለዋዋጭ ገጽታዎች ከየማህበረሰቡ እሳቤ ጋር እየተዛመዱ የታዩ አይደሉም። በኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱት ሁሉም ጥናቶች በአይሁድ ሃይማኖትና በክርስትና መካከል የነበረውን ልዩነት ለማሳየት የተካሄዱ ማስረጃዎች ነበሩ (Uhlig, 2003, 634) ።

በመሆኑም፣ ክፉ ዐይን የቀረበው በአይሁድና በክርስትና ባህል መካከል ያለውን አለመግባባት አሳይ ሆኖ ነው። በጉዳዩ ዙሪያ ያልተሰበሰቡ መረጃዎችን ለቅሞ በመያዝ በጉዳዮቹ አይነት፣ መንስኤ ነገር፣ የመጠቂያ አጋጣሚ፣ የህመም ምልክቶችና ስሜቶች ላይ ተናጠላዊ ምርመራ በማድረግ የክስተቱን አካባቢያዊ እሳቤና ምንነት በሙሉ ገጽታው ለመረዳትና ማህበራዊ ትርጉም ለማወቅ መሞከሩ ተገቢ ነው። ይህንን ሃሳብ ከዳር ለማድረስ በአማራ ክልላዊ መንግስት፣ በምሥራቅ ጎጃም መስተዳድራዊ ዞን፣ በጎዛም ወረዳ ላይ ይህንን ጥናት ለማድረግ አስፈልጓል።

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ርዕስ መርጬ እንዳጠና በርካታ ገጠመኞችና የህይወት ልምዶች ሰበብ ሆነውኛል። ከእነዚህ ሰበቦች መካከል አንዳንዶቹ በግል ያጋጠሙኝ፣ አንዳንዶቹ ሲወሩ የሰማኋቸውና ሌሎቹም ሳነብ ያገኘኋቸው ናቸው። አብዛኛው የሥራ ልምዴ በማስተማር ዙሪያ ያጠነጠነ ነው። የሰራሁባቸው ቦታዎችም እንዳጋጣሚ ሆኖ ከተወለድኩበት አካባቢ የራቁ ነበሩ። ልዩ ልዩ ባህልና ያኗኗር ዘይቤ ካላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር ኖሬአለሁ። በሄድኩባቸው አካባቢዎች እንዳጋጣሚ ሆኖ እኔ ከተወለድኩበት አካባቢ ተወልደው በሥራ ምክንያት አብረውኝ ይሰሩ የነበሩ በርካታ የሥራ ባልደረቦች ያጋጥሙኝ ነበር። እነዚህን መምህራን ጨምሮ ሁላችንም በባህርያችን ውስጥ ነገሮችን የማጥበቅ፣ አንድን ነገር ጠንከር አድርጎ የመያዝ ልምድ ስለነበረን ቸልተኛ ከሆኑና ነገሮችን አቅልለው ከሚያዩ የሥራ ባልደረቦች፣ የሥራ ሃላፊዎችና ተማሪዎች ጋር በተደጋጋሚ እንጋጭ ነበር።

በተለይ ፈታኝ ሆነን በክፍል ስንመደብ፣ የዩኒት አስተባባሪ፣ ምክትልና ዋና ሃላፊ ሆነን የአመራር ቦታ ስንይዝ አይቶ ማለፍ እያቃተን፣ መክሮና ገስፆ መመለስ አልሆንልን እያለ ያጋጨን ነበር። በዚህ ጠባያችን የተነሳ ስማችንን ከክፋትና ከተንኮል ጋር እያያያዙ ይገልጹት ነበር። ሁልጊዜ፣ ለምን ጠባያችን ተመሳሰለ? በአስተዳደጋችን ውስጥ በዚህ በተለየ እንድንታሰብ ያደረገን ምን የጋራ ህይወትና ልምድ አለ? የሚለው ጥያቄ ሁልጊዜ ያሳስበኝ ነበር።

አንድ ሁለተኛ ድግሪውን ጎንደር በሚኖሩ ቤተ እስራኤሎች "የቡዳ እምነት" ላይ የሰራ ተማሪ፣ መረጃ አቀባዮችን ስጠይቃቸው፣ "ምነው ጎጃምን ዘለህ እኛ ጋ መጣህ?" ብለው ጠየቁኝ ብሎ ሲናገር በተቋቁሞው ላይ ሰምቸዋለሁ (ሙሉቀን፣ 2006)[3]። ከጎጃም ውጭ ባሉ አብዛኞች አካባቢዎች "ልጅ" ወይም "አራስ" ሴት ስትታመም ጎጃሜ ካለ ከሌላው ሰው ተለይቶ እሱ እንደሚጠረጠር ይነገራል። አንድ ጎጃሜና ጎጃሜ ያልሆነ ሰው ሲጣሉ ጎጃሜ ያልሆነው ጎጃሜውን የሚሰድበው "ቡዳ" ብሎ ነው።

ስድስት ኪሎ አካባቢ ትዳር መስርቶና ልጅ ወልዶ ከአንድ ግቢ ውስጥ ቤት ተከራይቶ የሚኖር አንድ ያጎቴ ልጅ ነበር። አንድ ቀን ከወሬ ወሬ አንስቶን ወደ እሱ ጉዳይ እንገባለን። ከዚያም፣ ስለመጀመሪያ ሚስቱ አንዳንድ ታሪኮችን እየጫወተኝ ሳለ፣ በመካከለ ግን ለምን ፈታሃት? የሚል ጥያቄ ድንገት አነሳበታለሁ። እሱም ይሸንን ይመልስልኛል።

> ከተከራየሁበት ግቢ አንዲት ህፃን ልጅ በጠና ትታመማለች። ወላጆቿም ቡዳ የበላት መስሏቸው የተለያዩ መድሃኒቶችን ሲያጠጧትና ሲያሸቷት ይውላሉ። ሥራ ውዬ ሀገር አማን ነው ብዬ ማታ ቤት ስገባ የልጅቷ ቤተሰቦች ተከትለውኝ ከቤቴ ገብተው፣ ሰው ሁሉ እንትና እንትና እያለባት ስለሆነ፣ አንተም እንደዚያው አድርግ ይሉኛል። ያኔ በጥያቄአቸው በጣም እናደዳለሁ። ለመማታት ሁሉ ተጋበገኩ። ከሌለብህ ለምን አትተፋባትም ምን ችግር አለው? እያሉ ይጠይቁኛል። አላደርገውም ብዬ ዱላ ስመዝ ወጥተው ይሄዳሉ። ከዚያ ሲጨንቃቸው ወደ ሃኪም ቤት ይዘዋት ሄደው ስትመረመር

[3] ሙሉቀን ሁለተኛ ድግሪውን የሰራው በቡዳ ላይ ሲሆን፣ በተቋቁሞ ፕሮግራሙ ላይ ተካፍዬ ነበር። የመመረቂያ ወረቀቱን ከዲፓርትመንትና ከቤተ መጻሕፍት አፈላልጌ ላገኘው ባለመቻሉ ለማካተት አልቻልኩም።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

'ታይፎድ' መሆኑ ይረጋገጣል። ያኔ ሳጣራ ሁሉም ሰው ባለቤቴን ጨምሮ እንዲተፋባት አልተጠየቁም ነበር። ከግቢው ውስጥ ጎጃሜው እኔ ብቻ ስለነበርኩ ሌላውን ሁሉ ነጻ አድርገው ጥርጣሬው ያረፈው እኔ ላይ ነበር። ባለቤቴም ከእነሱ ጋር አብራ አስቀየመችኝ። (ቀረዓለም ሙሉቀን፣ 2002 ዓ/ም ግንቦት 10፣ ያጫወቱኝ) ።

ይኸው ሰው አንድ ቀን ራሱን ይታመምና ከሥራ ቀርቶ ከቤቱ ይተኛል። በአጋጣሚ የባለቤቱ እህት ከእህቷ ጋር ለመጫወት ፊልጋ ወደ ቤት ጎራ ትላለች። ዕድሜዋ አራት ዓመት የሞላት ልጁ፣ ቤት ውስጥ ስትጫወት ምንጣፍ ይጠልፋትና ትወድቃለች። እናት በልጇ መውደቅ ደንግጣ የወደቀችበትን ቦታ በዱላ ትመታዋለች። የአባትን መተኛት ልብ ያላለችው እህት ድግሞ የፌዝ ሳቅ እየሳቀች፣ "እሷንም በዳ ይበላታል እንዴ?" እያለች ታሽሟጥጣለች። አልጋ ላይ የተኛው አባት ይኸንን ሽሙጥ ሲሰማ ተናዶ ይነሳና በዱላ ይመታታል። ዱላው የጠናባት እህት አ! አ! ብላ ትጮሃለች። በጩኸቷ ጎረቤት ይሰበሰባል። ባሏም ከቤት ስለነበር ዱላ ይዞ ወጥቶ ከዚህ ልጅ ጋር ይገጥማል። እሱንም ይፈነክትና ልጁን ይዞ ወጥቶ በዚያው ይቀራል። በዚህ ምክንያት ከሚስቱ ጋር ተለያይቶ ይኖራል።

ክልላዊና ሃገራቀፋዊ የስፖርት ፌስቲቫሎች በተለያየ ጊዜ እንደሚካሄዱ ይታወቃል። የምሥራቅ ጎጃም ዞንም እንደሌላው አካባቢ ሁሉ የአካባቢውን ወጣቶች መልምሎ ያሳትፋል። እነዚህ ልጆች አካባቢያቸውን ወክለው ከሌሎች አካባቢ ከመጡ ቡድኖች ጋር በሚጫወቱ ጊዜ የተቃራኒ ቡድን ደጋፊዎች አጥንት ወደ ሜዳ እንደሚወረውሩባቸው ይናገራሉ። ሜዳ ውስጥ እንደ ጅብ እየጮኹ ስሜታቸውን ለመጉዳት መከራ እንደሚያደርጉ የተሳተፉ ስፖርተኞች ሲያወሩ አድምጫለሁ።

ይህ ስም ለምን ከጎጃም ጋር ተያያዘ? በዳ በሌሎች አካባቢዎችስ አለ አይደል ብዬ የጠየኳቸው አንዳንድ የአካባቢው አባቶች፣ በአካባቢው መታሰብ ላይ ልዩ ግምት እንዲኖር የጎጃም ስም ከዚህ ክስተት ጋር እንዲያያዝ አፈ ታሪኮችና የግድል ጥቆማዎች ሚና አላቸው በማለት ይናገራሉ (አቶ ቅሩብ፣ 2002 ዓ/ም፣ ግንቦት 7፣ በጨዋታ መካከል የነገሩኝ)። እነዚህ ታሪኮች በአካባቢው መታሰብ ላይ

ማጠናከሪያና አሳማኝ ተደርገው የሚያዙ ሐሜቶች ገዝፈውና እውነት መስለው እንዲታዩ የሚያደርጉ ተረኮች ናቸው፡

ጎጃሜ ቡዳ ነው አም ቡዳ ነው፣

ቢበላ አይደለም ወይ ቀዩ ያለቀው፡፡ ይባላል፡፡

በተጨማሪም የቅዱስ ላሊበላ ታሪክ እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ነው፡፡ ቅዱስ ላሊበላ፣ ጎጃም ውስጥ የሃይማኖት ትምህርት ሲማር በትጋቱና በአቀባበሉ የተነሳ መምህሩ ከሌሎቹ ተማሪዎች ሁሉ ለይተው ይወዱት፤ ከጓደኞቹ መርጠው ያገዙት፤ አቅርበው የተለየ መልካም ፊትና ፍቅር ያሳዩት ነበር ይባላል፡፡ ከመውደዳቸው የተነሳ ወጥ ሠርቶ እንዲያበላቸው የሚያዝዙት እሱን ነበር እየተባለ ይነገራል፡፡ እንግዳው ላሊበላ፣ ከመምህሩ ያገኘው ፍቅርና ልዩ አክብሮት ተማሪዎችን ያስቀናቸው ነበር፡፡ በዚህ ድርጊት ይናደዱ የነበሩ አንዳንድ ተማሪዎች፣ ቅዱስ ላሊበላ ተበሳጭቶ እንዲጠፋ፣ ባዕድነት እንዲሰማውና እንዲናደድ የተለያዩ ነገሮችን እያደረጉ ሆድ ያስብሱት ነበር ይባላል፡፡

አንድ ቅናቱ ያየለበት ተማሪም ላሊበላን ከመምህሩ ጋር ለማጋጨት አስቦ አንድ ተንኮል ይጠነስሳል፡፡ ወደ መቃብር ቦታ ይሄድና፣ ከትኩስ አስከሬን ላይ የአንድ ሕጻን ልጅ እጅ ቆርጦ ቅዱስ ላሊበላ በአዘጋጀው ምግብ ውስጥ ያስቀምጣል፡፡ አይነስውሩ መምህር፣ ሊበሉ እጃቸውን ወደ ማዕዱ ሲሰዱ የሰው እጅ ያገኛሉ፡፡ ይህንን ያየው ላሊበላ ደንግጦ ወጥቶ ይሸሻል፡፡ ከዚያ በጎጃሞች ተንኮል ተናድዶ አይደለም ጎጃምን ወደ ጎጃም አቅጣጫ እንኳ ማየትን ጠልቶ ኖሮ ሞተ እያለ የሚያወሩ ወገኖች አሉ በማለት አቶ ቅሩብ አጫውተውኛል (አቶ ቅሩብ አንተነህ፣ 2002 ዓ/ም፣ ግንቦት 7፣ በጨዋታ መካከል የነገሩኝ)፡፡

ሌላኛው አፈታሪክ ደግሞ የሃይማኖት አባቶችን ዋቢ በማድረግ የሚነገር ነው፡፡ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ከግብፅ ተነስተው፣ አባይን ተከትለው ኢትዮጵያ ይገባሉ፡፡ በዐባይ በረኻ ውስጥ ብዙ ድንቃድንቅ ተአማራትን ሲሰሩ ቆይተው ወደ ሸዋ ሊሻገሩ ሲሉ አጋንንት አስቸገራቸው ይላሉ፡፡ ይህንን ያደረጉት ጎጃሜዎች ናቸው ብለው ስላሰቡ ጎጃምን አጠፋዋለሁ ብለው ይዝታሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ተማጽኖው ስለበዛባቸው

ምልክት ይሆን ዘንድ ዐባይን መቀነቱ አድርጌ አስቀምጨዋለሁ ብለው አስነገሩ እየተባለ በገድሉ የሌለ ታሪክ ሲወራ ይሰማል (አቶ ቅሩብ፣ 2002 ዓ/ም፣ ግንቦት 7፣ በጨዋታ መካከል የነገሩኝ) ።።

የውጨ ሰው ጎጃምን በዳ ነው የሚልበት መንገድ ምንም እንኳ የተለየ ቢሆንም፣ ራሱ ጎጃሚውም እርስ በርሱ በዳ ይባባላል።። የተወሰነውን በድን ለይቶ "በዳ"፣ "ጠንፋፊ" እና "ቁመኛ" እያለ ሲያማና ሲያገል ይታያል።። በዘሩ ውስጥ እንዳይገቡ በጥንቃቄ የሚይዛቸው፣ በመብልም ሆነ በማህበራዊ ግንኙነት እንዳይጠጉት አግልሎ የሚያያቸው ሰዎች አሉት።። እናቶች፣ "ልጄን በዳ እንዳታስበይው ሽፋፍኝው" ይባባላሉ።። ልጆችንና የቤት እንስሳትን ከግቢ አታስወጧቸው በዳ ይበላቸዋል እያሉ ያስራሉ፤ ከቤት አያስወጧቸውም።። "ልጄን በዳ በልቶት ጤና አዳም፣ ነጭ ሽንኩርት ካላችሁ እባካችሁ ስጡኝ" ብለው በግልጽ ከጎረቤት ይለምናሉ።። እንግዳ ሰው ሲመጣ ቀድመው እህል ያቀምሱታል፣ እሱም ጠረጠሩኝ ሳይል ልማድ አድርጎት ቆርሶ ይጎርሳል።። "አብሮህ የሚመጣው አይታወቅም" ይባባላሉ።። እከሌ በዳ ስለሆነች/ስለሆነ በመንገድ ስታገኟት/ኙት አስደንግጧት/ጡት እየተባልን ነው ያደግን።። በልጆች፣ በከብቶች፣ በአዝመራ ላይ የተለያዩ መከላከያዎች በግልጽ ይደረጋል።።

አንድ ጊዜ ሴት አያቴ ሞታ የአርባ መታሰቢያ የሚሆን ጸበለ ጻድቅ ከቤታችን ተዘጋጅቶ ፍተሃት ፀሎት ሲያደርጉ ለዋሉ ሰዎች እህል ውሃ ልታቀምስ፣ እናቴ ታላቅ እህቴንና እኔን ይዛ ቤተክርስቲያን ትሄዳለች።። የእናቴ ትውልዷና ዕድገቷ በዚያ ደብር አካባቢ ስለነበር፣ በቡድነት የሚጠረጠር አንድ ቂስ መኖሩን ታውቅ ነበር።። እኛን ከጓዳ እንዳትንቀሳቀሱ ብላ አስጠንቅቃ አስቀምጣ ማስተናገድ ትጀምራለች።። በመሃሉ እቃ ረስታ ታላቅ እህቴን እንድታቀብላት ትጠራታለች።። እህቴም ዕቃውን ይዛ ወደ አዳራሽ ትገባለች።። በዚያን ሰዓት እናቴ የሰራችው ስህተት ትገ ሲላት፣ "ተመለሽ ተመለሽ እያለች" ከሰው መሀል ቆማ ስትጮኽ፣ እህቴ ደንግጣ ትመልሳለች።። ካበሉና ካጠጡ በኋለ ወደቤታችን እንመለሳለን።። ምሽት ላይ የተፈራው ደርሶ እህቴ ታማ ትቸጋገራለች።። እናቴም እያለቀሰች፣ "ያ መናጢ ሰራልኝ፣ ወይኔ በገዛ እጄ፣ እጄን ቆረጥኩት" እያለች ማለቃቀስ ትጀምራለች።።

የእናቴ ታላቅ ወንድም የቡዳ መድሃኒት አዋቂ ስለነበር ጥራው ተብዬ ወደ ገጠሯ መንደር እላካለሁ። ከቤት ደርሼ ሁኔታውን ለአጎቴ ሳስረዳው፣ በእናቴ ተግባር በእጅጉ አዝኖ፣ "ለምን ሰው በተሰበሰበበት እናንተን ይዛ መጣች?" ብሎ ወቀሳት። አመሻሽ ላይ እህል ሳይቀምስ መድሃኒቱን ይዘን ደንግጦ ከእኔ ጋር እየሮጠ ይመጣል። በመንገድ ላይ፣ "እውነት እሱ ከሆነ ገና ከቤት ስገባ ይጮኻል" ታያለህ እያለ እያጫወተኝ ከቤት ደረስን። ነገር ግን፣ ስንገባ የነገረኝ ነገር አልሆነም፤ እህቴ የተለየ ነገር አላሳየችም። የያዘውን መድሃኒት ደጋግሞ አሸተታት፤ ተናገር እያለ አስጨንቆ ጠየቃት። እሷም አላመመኝም፣ ተወኝ እባክህ እያለች አጎቴን ለመነችው። "እይ፣ እሱ ቢሆን ኖሮ ይሸን ያህል አይቆይም ነበር" ብሎ ማሸተቱን ይተዋል። እሷም እንደተቸገረች አደረች። በነጋታው ግን "የኮሶ ትል" ኖሮ ሽሯት ሰላሚ ተመለሰላት። ይሸን ታሪክ እያነሳን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከእህቴ ጋር እንሳሳቅ ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ፣ በእኛ ቤት ውስጥ የተፈጠረ አንድ ሥር ያለው አሳዛኝ ታሪክ አለ። ይህ ታሪክ በቤተሰቡ ህይወት ላይ ተጽእኖ የፈጠረና የስነ ልቦና መናጋትን ያስከተለ ነው። በኃይለስላሴ ዘመን መንግስት የኮሌጅ ትምህርቱን የተከታተለ፣ አንድ የእናቴ የአጎቷ ልጅ የሚሆን ተማሪ ነበር። ይሽ ልጅ ተመርቆ ወደ ደብረማርቆስ በመምጣት ላይ እያለ፣ ዐባይ በርሃው ውስጥ የተሳፈረበት መኪና ተገልብጦ ከታሳፋሪው ሁሉ ተለይቶ እሱ ይሞታል። በጊዜው የእናቴ ዘመዶች ገጠር ስለነበሩ፣ በቅርብ የተገኘው አባቴ መርዶውን ሰምቶ ድርጊቱ ወደ ተፈጸመበት ቦታ በመሄድ አስከሬኑን ቄኖ ይወስዳል። አስከሬኑ ከመጣ በኋላ፣ "ልጄ ማለት አይደል ብሎ ተው እያልነው ከቤት አስገባው" ይላሉ የእናቴ ዘመዶች።

ከዚያ በኋላ፣ ሶስት ሴቶችና ሶስት ወንዶች እህቶቻችንና ወንድሞቻችን እንደዕድሜያቸው ተከታትለው ይሞታሉ። ሁኔታው በጣም አስደንጋጭ ነበር። አጎቴ በሁኔታው አዝኖ፣ "በኔ ልጆች ለውጥ፣ ለውጥ ብሎ አለቀሰ" እያሉ ሲያወሩ ሰምቻለሁ። አባቴም ይሽ ዓለም በቃኝ ብሎ ገዳም ገብቶ አንድ ዓመት ከቆየ በኋላ "ዘር አለህ" ተብሎ ተመልሶ ነው የወጣ እያለች እናቴ ነግራኛለች። በምን ምክንያት ነው የሞቱ? ብዬ እናቴን ስጠይቃት፣ "መኪናው ሲገለበጥ ሲደነግጥ በዚያው ከበርሃ

ያለ የቡዳ መንፈስ አደረበት። አባትህ ባለማወቁ ሞትን ከቤቱ አስገባ። ልጆቻችንንም ያ መናጢ አከታትሎ ወሰደብን" ብላ በፀፀት ነገረችኝ። የአባቴ ወንድም ከአካባቢው ዘወር ይበል ብሎ አንዱን ወንድሜን ሐረር ይዞት ሄዶ ነበር ይባላል። እርቆ ቢሄድም የአስራ አንደኛ ክፍል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ሞተ ይላሉ። አንቴ ግን እሱን የገደለው "የጉበት ህመም" ነው ብሎ ነግሮኛል። እናቴና ሌሎች ዘመዶቻችን እስካሁን የሚያምኑት "ቡዳው" መሆኑን ነው።

በተለይ የአንዱ ሚች ወንድማችን ስም "በጊዜው መኮንን" ነበር። በስም አወጣጡ የተደነቀ ሌላ "መኮንን" የተባለ የአካባቢው ነዋሪ ወንድ ልጁ ሲወልድ ስሙን "በጊዜው" ብሎ ያወጣለታል። ያም ልጅ ብዙ አልቆየም ሞተ እያለ ሁኔታውን ከእኛው ክስተት ጋር አዛምደው ሲናገሩ እሰማለሁ። ሁኔታው ከቤታችን አልፎ አካባቢያዊ ስጋት ሆኖ የስነልቦና መናጋትን ፈጥሮ እንደነበር ለማወቅ ይቻላል። ከዚያ በኋላም ለተረፍነው ልጆች ዘመዶቻችን ስም ያወጡት፣ "ፈራውህ"፣ "ሞት ባይኖር"፣ "ውብሊቀር"፣ "አስረሳሽኝ"፣ "ደግፋቸው" በማለት ነበር። ለወንዶቹ የሴት ስም፣ ለሴቶች የወንድ ስምና ልብስም እያቀያየሩ እንዳሳደጉን ትዝ ይለኛል። እስኪ "አታሞ[4] ይጨኸበት ሞት ይውጣ" ተብሎ ታላቅ እህታችንን በ14 ዓመቷ ድረዋት ነበር። እሷም የተጽእኖው ጋብቻ ህይወቷ ላይ አሉታዊ ጫና አሳድሮ ሦስት ወልዳ በልጅነቷ ተቀጠፈች።

በዚህ የተነሳ የዚህን እምነት እሳቤ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ትርጉም፣ በአካባቢ ማህበረሰብ ስነልቦና ውስጥ ያለውን ቦታ ለመመርመር ሁልጊዜ አስብ ነበር። ከዚያም በኋላ የቀጠሉ ጸጸቶች፣ ግጭቶች፣ ጥንቃቄዎች፣ ሥጋቶች ሁሉ በእኔም ሆነ በቤተሰቦቼም ላይ የቀጠሉ ስለነበር ሁኔታውን በማጥናት ለማወቅ በእጅጉ ተነሳሳሁ።

1.2. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት፣ በምስራቅ ጎጃም አካባቢ የሚገኘው ማኅበረሰብ በክፉ ዐይን እምነት ላይ ያለውን እሳቤና እምነቱ እንዲከሰት ያደረገውን ምክንያት በመግለጽ ላይ ያተኮረ ነው። ክስተቱ በማኅበረሰቡ አስተሳሰብ፣ ዕውቀት፣ ክህሎትና ባሕርይ ውስጥ

[4] እንደ ክበሮ ያለ ከቆዳ የሚሰራ ለዘፈን ማድመቂያነት የሚያገለግል የሙዚቃ መሳሪያ ነው።

የያዘውን ሰፊ ትርጉም የፎክሎር ጉዳዮችን በመያዝ መርምሯል። ይህ አመለካከት በሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ልምዶች ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ ያብራራል። በዚህም፣ ያ ማኅበረሰብ በርዕዮተ ዓለሙና በማንነቱ ተለይቶ የሚታወቅበትን ነገር ይገልጻል። ጥናቱ በእነዚህ ዋና ዓላማዎች ላይ ተመስርቶ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ይመልሳል።

1. የክፉ ዐይንን እሳቤ ፣ ምንነት፣ ባህርይና ያለውን ማህበራዊ ፍቺ በበቂ ሁኔታ ለመግለጽ፤
2. የክፉ መንፈስ ወኪል በመሆን ስለሚያገለግሉ ፍጥረቶች ባሕርይ ለማስረዳት፣
3. ክፉ ዐይን የሚከሰትባቸውን አውዶችና የመጠቂያ አጋጣሚ ለማብራራት፣
4. የክፉ ዐይን መንፈስን ለመከላከል የሚያገለግሉ ዘዴዎችን ለመግለጽ፣
5. በክፉ ዐይን የተያዙ ፍጥረቶችን ለመፈወስ የሚያገለግሉ የማንጫ መንገዶችን ለማስረዳት ናቸው።

1.3. የጥናት አካባቢ ምርጫ

የዚህ ጥናት አካላይ የሆነው የምስራቅ ጎጃም ዞን፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ከሚገኙ ከአሥራ አንድ የዞን መስተዳድሮች መካከል አንዱ ነው። የዞኑ የቆዳ ስፋት በካሬ ሜትር 14,004.47 የሚገመት ሲሆን፣ በዚህ አካባቢ ከ2,311,390 ሕዝብ በላይ ሰፍሮ ይኖርበታል። ከነዚህ ሰፋሪዎች መካከል የሴቶች ብዛት 1,166,933 ሲሆን፣ ቀሪው 1,144,457 ደግሞ የወንዶች ቁጥር ነው። ከአጠቃላይ ነዋሪው መካከል 100% አማርኛን በአፍ መፍቻነት የሚናገር ሲሆን፣ 90.08% በእርሻ ሥራ የተሰማራ የገጠር ነዋሪ ያለበት ሥፍራ ነው (CSA,2007[5]) ።

በተለያዩ ጊዜያት ጎጃም በተለየ የወሰን አከላለል ሲመደብና ሲጠራ ቆይቷል። ዘመነ መሳፍንት ተብሎ በሚታወቀው የኢትዮጵያ ታሪክ ወቅት ለማዕከላዊ አስተዳደር እንዲያመች ታስቦ የአሁኑ ምሥራቅ ጎጃምና ዳሞት በአንድ ላይ ተጠቅልለው እንደነበር Yehenew ይጠቅሳሉ (1996, 21) ። በአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ደግሞ የጎጃም ጠቅላይ ግዛት የሚል አስተዳደር ተፈጥሮ በሥሩ ሰባት አውራጃዎችን ማለትም አገው ምድርን፣ ባህርዳርን፣ ብቸናን፣ ደብረማርቆስን፣ ቆላደጋዳሞትን፣

[5] CSA= Central Statistical Agency

ሞጣንና መተከልን ዋና ዋና የሚያደርግ የአስተዳደር ሥርዓት ተዘርግቶ ነበር (CSO, 1966) ። ይህ አመዳደብ እስከ ደርግ ዘመነ መንግስት ቆይቶ፣ በዘመነ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.፣ ምሥራቅና ምዕራብ በሚሉ የዞን መስተዳድሮች እንደገና ሊከፋፈል ችሏል።

የሃገር ሽማግሌዎች የጎጃም ድንበር ከጅበላ እስከ ቆለላ፣ ከበላያ እስከ ጉበያ ድረስ ነው[6] ብለው ይናገራሉ (ዮሴፍ፣ 1997)። እነዚህን ቦታዎች "የጋፋት" ልጆች ማለትም "ሰረቤ" እና "ደረቤ" እንደተካፈሏቸው ይነገራል። የምሥራቅ ጎጃም ቅድመ አያት እንደሆነ የሚነገርለት "ደረቤ" አምስት ልጆችን ማለትም ጎዛምንን፣ አነደድን፣ ጥላትግንን፣ አዋበልን፣ ውድሚትን አምስት ይወልዳል (አለቃ ተክለ-ኢየሱስ፣ ግርማ በተረጎመው፣ 2003፣ 43)። ጎዛምን የደረቤ የመጀመሪያ ልጅ ሲሆን፣ እሱም በተራው ሌሎች አራት ልጆችን "ተጎዘምን"፣ "የሸምሸምን"፣ "ተፈሥፅምን" እና "የረስን" ይወልዳል። ተጎዘም ደግሞ በረትግምንና ልትማመግን ወልዷል (አለቃ ተክለ-ኢየሱስ፣ ግርማ እንደተረጎመው፣ 2003፣ 43)። ተጎዘም እንደ አባቱ ጎዛምን የመጀመሪያ ልጅ በመሆኑ የልቅና መሬት ከሶስቱ ወንድሞቹ መልካም መልካሙን መስክ እየመረጠ ወስዷል። እስከ ዛሬ መሬቱ በየብራጌና በግምጃቤት በማርቆስ ውስጥ በረት ገን ተብሎ ይጠራል (አለቃ ተክለ-ኢየሱስ፣ ግርማ በተረጎመው፣ 2003፣ 61)።

በመሆኑም፣ የደብረማርቆስ ከተማና ዙሪያው እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ሲጠራ የቆየው በአባቱ በጎዛምን ስም ሲሆን፣ በቅርብ ጊዜ በወጣው ከተማዎችን በልዩ የማስተዳደር ፖሊሲ ምክንያት ዙሪያው በጎዛም ሲጠራ፣ ከተማው ተለይቶ ደብረማርቆስ የከተማ አስተዳደር ተብሏል። በዚህ ጥናት ግን "ጎዛምን" ሲል የአሁኑን የጎዛምንን ወረዳና የደብረማርቆስን ከተማ ያጠቃልላል።

---

[6] ጅበላ ከደብረማርቆስ ከተማ በስተምዕራብ በእግር የ6 ሰዓት መንገድ ተጉዞ የሚገኝ ቀበሌ ነው። ቆለላ ደግሞ ከሞጣ ከተማ በስተሰሜን የሚገኝ አበያ የተባለ ወንዝ የሚያዋስነው ሞቃታማ ቦታ ነው። ከጅበላ እስከ ቆለላ ማለት ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ ጫፍ ማለት ነው። ከበላያ እስከ ጉበያ ደግሞ ከሰሜን እስከ ደቡብ ጫፍ ያለውን ቦታ ያመለክታል። ጉበያ ከደጀን ከተማ በስትደቡብ ዐባይ ወንዝ የሚያዋስነው ቦታ ሲሆን፣ እንጅባራ ደግሞ አሁን የአዊ ዞን ማዕከል የሆነች ከተማ ነች (ዮሴፍ)።

የጎዛምን ወረዳ በአጠቃላይ በ25 የገጠር ቀበሌ፣ በአንድ ንዑስ ታዳጊ ከተማ እና በአንድ የከተማ አስተዳደር የተዋቀረ የአስተዳደር ቦታ ነው። በጎዛም ወረዳ እምብርት ላይ የምትገኘውና የዞኑ ዋና ከተማ በመሆን እያገለገለች የምትገኘው የደብረማርቆስ ከተማ ከአዲስ አበባ በ300 ኪ/ሜ ከክልሉ ዋና ከተማ ባህርዳር ደግሞ በ265 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። ጥልቀት ያለው የኢትኖግራፊ ጥናት ለማካሄድ እንዲመች በዚህ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ ሰባት ቀበሌዎች ማለትም "የጥጃን"፣ "ሸበልማ"፣ "ወንቃ"፣ "እነራታ"፣ "ቀቢ"፣ "የቦ አርጀና"፣ "የጋግና" እና "ፅምቦርድ" እና አንድ የከተማ አስተዳደር ማለትም የደብረማርቆስ ከተማ ተመርጠዋል። ይህ ወረዳና ቀበሌዎቹ ሲመረጡ ብዙ ነገሮች ታሳቢ ተደርገዋል።

የጥናት ቦታዎቹን ለመምረጥ መስፈርት የሆኑት ጉዳዮች 1/ በአካባቢው ለቀዳሚነትና ለነባር ቦታዎች ክብር መሰጠቱ ታሳቢ ተደርጎ ነው። ጎዛምን የደረቤ የመጀመሪያ ልጅ ነው ተብሎ ዘር ይቆጠራል። በመጀመሪያ ልጅነቱ ትልቅ ተብሎ ለልቅናው የተሻለ ቦታ እንዲይዝ ተደርጓል። ክፉ ዐይን እንዲነቃ የተሻለ ነገር መነሻ ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን አጋጣሚው በጎ ያልሆነ ስሜት ሊያሳስብ ይችላል ብዬ በማሰቤ። 2/ ከከተሞች መስፋፋትና ከማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጋር ተያይዞ ክስተቱ የተለያዩ ጠባዮችን እያሳየ ስለመጣ፣ በዞኑ ውስጥ ካሉ ወረዳዎች ከተማንና ገጠርን በንጽጽር ሊያሳይ የሚችለው ቦታ ይኸ ነው ብዬ በመገመቴ። 3/ መረጃ ለማግኘትና እንደልቤ ለመንቀሳቀስ ከሌሎች ቦታዎች በተሻለ ሊያግዙኝና ሊረዱኝ የሚችሉ ሰዎችን በብዛት አገኝበታለሁ ብዬ በማመኔ 4/ በዞኑ ውስጥ ካሉ ወረዳዎች ለዋና ከተማዋ ለደብረማርቆስ ጥግ የሆነ አካባቢ በመሆኑ፣ የአሰፋፈር ጥግግቱ የሚያሳየው አንድ ነገር ሊኖር ይችላል ብዬ በመጠርጠሬ ነው። ማህበራዊ ችግሮች፣ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራዎችና ባህላዊ ግጭቶች በበዙባቸው አካባቢዎች ክፉ ዐይን በብዛት ይከሰታል የሚሉ ተመራማሪዎች ስላሉ ይህ ተለዋውጦ ጉዳዩን ይበልጥ ሊያሳይ ይችላል ብዬ በማሰቤ ነው (Malinowski, 1945, p. 94)።

1.4. የጥናቱ ወሰን ወይም ገደብ

የዚህ ጥናት ትኩረት በክፉ ዐይን ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። ከድግምት፣ ከአስማትና ከሥራይ በተያያዘ ያሉ ባህሎች የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት አይሆኑም። ክፉ ዐይን አስበውና ፈቅደው የሚያጠቁት፣ በዓላማ ሆን ብለው የሚያደርሱት ጉዳት ሳይሆን፣ በማያውቁትና ባልጠበቁት መንገድ የሚሰነዘር ነው። በመሆኑም፣ በዕውቀትና በዕቅድ የሚሰነዘር የመናፍስት ጥቃት የዚህ ጥናት ትኩረት አይደለም። ዛርና ውቃቤ እንደ ክፉ ዐይን ሁሉ በዘር ግንድ የሚጋቡ ናቸው። ከፍርድና ክጥበቃ ጋር ተያይዞ በመልካም የሚታሰቡ በመሆኑ፣ እነሱም የጥናቱ አካል አይሆኑም። በተጨማሪም፣ ጥናቱ በንዛሆን አካባቢ ያለውን የክፉ እምነት እሳቤ የፎክሎር ጉዳዮችን ማለትም፣ እምነት ነክ፣ ምሳሌያዊ ንግግር፣ ተረኮችንና አባባሎችን በመሰብሰብ የሚያጠና ይሆናል።

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ክፉ ዐይን ርዕሰ ጉዳይ ተደርጎ በመጠናቱ በርካታ ጥቅሞች ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው።

- ✓ የአካባቢው ህብረተሰብ ህይወቶች ስለሚመሩባቸው ደንቦች፣ ትውፊታዊ ስርዓቶች ስለቆመባቸው ህጎች፣ ባህርያዊና ድርጊታዊ ልምዶች ስለተፈቀዱና ስለተከለከሉባቸው ሁኔታዎች መረጃዎችን ይሰጣል።
- ✓ የንዛሆን ሰው ስለ ዓለማቱ አፈጣጠር፣ ስለተፈጥሮ ሥርዓት፣ በተፈጥሮ ውስጥ ስላሉ ፍጥረቶች ባህርይ፣ የአፈጣጠር፣ የአደረጃጀት፣ የአሰረጣጨትና የአስተዳደር ዕውቀት ይጠቁማል። ይህ እምነት፣ በአስተዳደር፣ በፖለቲካ አመለካከትና በኢኮኖሚ አስተሳሰብ ላይ ያለው አንደምታ ምን መልክ እንዳለው ለማገናዘብ ይጠቅማል።
- ✓ ስለአካባቢው ሰው ማንነት፣ ማህበራዊ ፍላጎቶችና ስሜቶች ያስረዳል።
- ✓ ስለአካባቢው ማህበረሰብ የዕውቀት ሁኔታ፣ ፍልስፍናና ሃይማኖታዊ ድንጋጌ ይጠቁማል።
- ✓ ማህበረሰባዊ ህጎችና ትውፊታዊ እሴቶች ከየት እንደመጡ መልስ የሚሰጡ፣ ለባህል መሰረት የሚያቆሙና ለማህበራዊ ደንቦች ሁሉ የድንጋጌ ምንጭ በመሆን የሚያገለግሉ መነሻ ልምዶችን ለማወቅ ይጠቅማል።

- ✓ ይህን ርዕሰ ጉዳይ መርጠ ለማጥናት መሞከሩ በፖለቲካው፣ በስነልቦናዊና በኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ለሚካሄዱ ጥናቶች ብዙ መጋቢ መረጃዎችን ያስገኛል። በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ለሚከናወኑ የማደረጃና የማጠናከሪያ እንቅስቃሴዎች ልምድ ለመቅሰም፣ እንዲሁም ለሌሎች የፍልስፍና፣ የታሪክና የስነ ቅርስ ጥናት መስኮች የመረጃ ምንጭ በመሆንም ይጠቅማል።
- ጥናቱ ከእነዚህ ጥቅሞች በተጨማሪም ሌሎች ቀጥተኛ ያልሆኑ ፋይዳዎችም ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል። ከእነዚህም መካከል፣
- ✓ በተለይ በሃገረሰባዊ እምነቶች ላይ በቀጣይ ለሚካሄዱ ምርምሮችና በሃይማኖት ዙሪያ ለሚሰጡ ትምህርቶች፤ ግብዓት ይሆናል። ከጤና ጋር ተያይዘው ለሚነሱ የአመጋገብ፣ የንጽሕና፣ ቅድመ መከላከል እክሎች ጠቋሚ ሃሳብ ይኖረዋል።
- ✓ ዕያችን ለተለያዩ መፈወሻ ተግባራት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል መረጃ ያቀብላል። ከትምህርት፣ ከግብርና፣ ከግጭት አፈታት፣ ከማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ ጋር ተያይዘው ለሚከናወኑ የተግባራዊ ፎክሎር (Applied folklore) ስራዎች መነሻ ሃሳቦችና በርካታ ጭብጦች ያስገኛል።
- ✓ በቀጣይም በጥልቀት መጠናት፣ መተንተንና መጣራት ስላለባቸው ባህላዊ ዕውቀቶች ክፍተት ይጠቁማል። ጥናቱ የሚከተለው የአተናተን አቅጣጫ በቀጣይ በዘርፉ ላይ ለሚካሄድ ምርምሮች አስተማሪ ነገር ይኖረዋል። አማራጭ የማጥኛ ዘዴን በማሳየት ዘርፉ በተለያዩ አንጻሮች የሚታይበትን ዕድል ያሰፋል።

1.6.የጥናት ጽሑፉ አደረጃጀት

ይህ ጥናት መግቢያውንና ማጠቃለያውን ጨምሮ በዘጠኝ ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው። በመጀመሪያው ምዕራፍ፣ የጥናቱን ጽንሰ ሐሳብ የሚያስተዋውቁ፣ ለዳራዊ ዕውቀት የሚያግዙ መረጃዎችን ያካተተው የጥናቱ ዳራ፣ ጥናቱ እንዲካሄድ ምክንያት የሆነው ጉዳይ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ወሰንና ጠቀሜታ ተካትቶበታል።

ምዕራፍ ሁለት፣ ከለሳ ድርሳናት የቀረበበት ክፍል ሆኖ ትውራዊ አቀራረቦች፣ ተዛማጅ ጥናቶች፣ ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፎችና የመተንተኛ ሞዴሎች የተብራሩበት ነው። በሦስተኛው ምዕራፍ፣ ለምርምሩ መረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችና የአጠናን ዘዴዎቹ ተገልጸውበታል። ምዕራፍ አራት፣ ስለጥናት አካባቢው መልክዐምድራዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች በስፋት ተዋውቆበታል።

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች፣ ከምዕራፍ አምስት ጀምሮ እስከ ምዕራፍ ስምንት ባሉት ክፍሎች ውስጥ ተተንትነው ቀርበዋል። ምዕራፍ አምስት በክፉ ዐይን እሳቤ፣ በክፉ ዐይን ወኪሎች፣ ስለክፉ ዐይን ወኪሎች ባህርይ፤ በምዕራፍ ስድስት ለክፉ ዐይን አጋላጭ ስለሆኑ አጋጣሚዎችና በተጋላጭነት ዙሪያ ስላለ አመለካከቶች፤ በምዕራፍ ሰባት፣ ክፉ ዐይንን መከላከል ስለሚያስቸሉ አስተሳሰቦች፣ ከመጋለጥና ከመጠጋት ስለሚያድኑ ዘዴዎች፤ በምዕራፍ ስምንት የመፈወሻ ስርዓት ስለሆነው ንስሓ ተተንትኗል። ምዕራፍ ዘጠኝ፤ የጥናቱ ማጠቃለያና ይሁንታ የተሰጠበት ክፍል ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

2. የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት፣ ትውራዊ አቀራረቦች፤ የጽንሰ ሐሳብ ማዕቀፎችና የመተንተኛ ሞዴል

በዚህ ምዕራፍ በክፉ ዐይን ላይ በሃገር ውስጥና ከሀገር ውጪ የተካሄዱ ጥናቶች ተዳስሰውበታል፡፡ እነዚህን ጥናቶች ለመተንተን ስላገለገሉ አንጻሮች፣ በጥናቱ ውስጥ አውራ ስለሆኑ ጽንሰ ሐሳቦች፣ የፍች ማዕቀኞችና የመተንተኛ ሞዴሎች ተብራርተው ቀርበውበታል፡፡

2.1. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

በዚህ ክፍል የቀረቡት የኢትኖግራፊና የታሪክ ጥናቶች በክፉ ዐይን ዙሪያ በኢትዮጵያና በዓለም ላይ ያለውን አስተሳሰብ የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ጥናቶቹ የየአካባቢውን ባህላዊ፣ ማህበራዊና አውዳዊ ሁኔታዎችን ትኩረት ሰጥተው ለመመርመር የሞከሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች በሃገር ውስጥ የተካሄዱና ከሃገር ውጭ የተካሄዱ በሚል ተከፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

2.1.1.የሃገር ውስጥ ጥናቶች

በኢትዮጵያ ውስጥ ክፉ ዐይንን ርዕሰ ጉዳይ አድርገው የተጠኑ ምርምሮች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች፣ ሁሉም ከአንዱ በቀር በአማራ ብሔረሰብ ላይ የተካሄዱ ናቸው፡፡ ሁሉም ጥናቶች የተካሄዱት ደግሞ በውጭ ሃገር ተመራማሪዎች ሲሆን፣ የተከተሉት የአጠናን መንገድም ተመሳሳይ ነው፡፡ ተመራማሪዎቹ በክፉ ዐይን ተሸካሚነት የሚጠረጠሩ ሰዎችን መጤና በዕደ ጥበብ ሙያ የተሰማሩ ናቸው ብለው የሚደመድሙ ሲሆኑ፣ የጥናቶቻቸው ሙሉ ትኩረት ጥቃት ያደርሳሉ ተብለው በሚጠረጠሩ ሰዎች ማንነት ላይ የተወሰነ ነው (Reminick,1974,280; Finneran, 2003, 427)፡፡ አጥኝዎች ከታሪክ፣ ከስነሰብዕና ከስነማህበረሰብ ትምህርት ክፍሎች የመጡ ናቸው፡፡

“Buda in Ethiopia” በሚል ርዕስ፣ በ1957 Kenneth Honea ያካሄዱት ጥናት አንዱ ነው፡፡ እኚህ ሰው ይቺን ጥናት መላኩ ህይወት ለተባለ በቬና የኤሌክትሪካል አንጅኒየሪንግ ትምህርታቸውን ይከታተሉ ለነበሩ ሰው ቃለመጠይቅ በማቅረብ

ያካሄዷት ነች። መረጃ ሰጪው ግለሰብ በዝቋላ አካባቢ ተወልደው ያደጉ በመሆናቸው፣ ሲወራ የሰሙትን፣ በልጅነታቸው ያዩትን እያስታወሱ የተናገሩት በመሰብሰብ የተጠና ነው። ተመራማሪው ይሽንን ጥናት ከሌሎች ጥናቶች ያገኙትን መረጃ በመጨመር በተወሰነ መልኩ ሊያዳብሩት ሞክረዋል። አጥኝው የቡዳን ቃላዊ አመጣጥ ለመመርመር የሞከሩ ሲሆን፣ ቡዳ የሚለው ቃል በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ በሚኖሩ የኮሽቲክ ሕዝቦች የተለመደ መሆኑን ገልጸው፣ ፍቺውም ክፉ ዐይን (witchery) ከሚለው ጋር የሚስማማ እንደሆነ ያስረዳሉ። የቡዳ ቃላዊ ሥር bd መሆኑን የሚጠቅሱት እኒሁ ተመራማሪ፣ ፍቺውን መውረስ፣ መቆጣጠርና መመላት በሚል ይተረጎማል በማለት ያስረዳሉ። ይህ ቃል በኦሮምኛ፣ በሳሆኛ፣ በትግርኛ እና በአማርኛ ቋንቋዎች በተመሳሳይ አጠራር እንደሚወከልም ገልጸው፣ በሶማሊያ "ቢዳ" በአፋር ደግሞ "ቡዳ" እና "ቡታ" እንደሚባም Leslauን በመጥቀስ ያስረዳሉ (Honea, 1957, 20)።

Honea ከአንድ ሰው ላይ ያገኙትን መረጃ ዋቢ በማድረግ በኢትዮጵያ በቡድነት የሚጠረጠሩት የተወሰኑ ዘሮች መሆናቸውን ያስገነዝባሉ። ቡድነት በእነዚህ ዘሮች የዘር ግንድ ውስጥ በመወለድ የሚተላለፍ ሆኖ ሊላቀቁት የማይችል ቋሚ ጠባይ ነው ተብሎ እንደሚታመን ያስረዳሉ። ነገር ግን፣ እነዚህ የህብረተሰቡ አባላት ከሌላው ነዋሪ ተለይተው የሚታወቁበት ቁመና ወይም የአለባበስ ባህል እንደሌላቸው ያስረዳሉ (Honea, 1957, 21)። በእነዚህ አካሎች የሚሰነዘረውን ጥቃት የአካባቢው ሰው የሚከላከለው ራሱን በመደበቅ፣ በመሸፋፈንና ከቡዳው ዐይን በመራቅ እንደሆነ የሚናገሩት Honea፣ በቡዳ የተጠቃ ሰውን ለመፈወስ የሚያገለግሉ የዕፅ ሥሮች መኖራቸውን ያስረዳሉ። ይህ ጥናት አንድ ሰው የሚያስታውሰውን ጠይቆ የቀረበ በመሆኑ፣ ጥናት ነው ብሎ ለመቀበል ይከብዳል።

ሁለተኛው ጥናት የተካሄደው በእውቁ የታሪክ ተመራማሪ Richard Pankhurst ነው። Pankhurst፣ "A Social History of Ethiopia" በሚል ርዕስ በ1990 ባሳተሙት መጽሐፋቸው "Belief in Buda, or possessed person and the Evil eye" የሚል አንድ ንዑስ ርዕስ አካትተዋል። ይህ ጥናት ተጓጉችና የውጭ ሃገር ጎብኝዎች እንዲሁም አንዳንድ የታሪክ ድርሳናት ስለክፉ ዐይን ያሰፈሩት ተሰብስቦ

የተዳሰሰበት ክፍል ነው። Pankhurst የዕድ ጥበብ ሙያ በኢትዮጵያ ባህል ውስጥ ያለውን ታሪካዊ አመጣጥና ማህበራዊ ሁኔታ ለመቃኘት ሲሞክሩ፣ የቡዳን እምነት ከሙያው ጋር በማስተሳሰር በእግረመንገድ ለመቃኘት ሞክረዋል። የዕደ ጥበብ ሙያ ከፈላሻዎች ጋር ተያይዞ የሚነገር በመሆኑ፣ ማህበራዊ ታሪክ ለማጥናት ሲሞክሩ ይኸንን ጉዳይ አንድ ጭብጥ አድርገው መጠነኛ ዳሰሳ አድረገውበታል።

Pankhurst የቡዳን እምነት በአብዛኛው የሃገራቱ ክልል ተሰራጭቶ የሚገኝና በሰፊው የሚታመን እምነት መሆኑን ልዩ ልዩ ድርሳናትን ምንጭ በማድረግ ይጠቅሳሉ። በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን አካባቢ በኢትዮጵያ በብረት ቅጥቀጣ ተሰማርተው የነበሩ ፈላሻዎች መሆናቸውን Henry Saltን፣ Duftonን እና Sternን በመጥቀስ ጽፈዋል (Pankhurst, 1990, 223)። እነዚህ ባለሙያዎች ልዕለ ተፈጥሮ ኃይልን መሳሪያ እንደሚያደርጉ፣ ማታ ማታም ራሳቸውን ወደ ጅብነት እንደሚቀይሩና የሰው ሥጋ እንደሚበሉ ይታመን እንደነበር ተጠቁሞ ይገኛል (1990, 223)። እነዚህ ተጓጉችም ሆኑ ጎብኝዎች ክፉ ዐይንን የጠቀሱት ፈላሻዎች በኢትዮጵያ የነበራቸውን ተቀባይነት ለማሳየት እንጅ የቡዳ እምነት በህብረተሰቡ ህይወት ያሳየውን ባህላዊና ማህበራዊ ሚና ለማሳወቅ በማሰብ አልነበረም።

ወደሃገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ እንደመጡ የሚነገርላቸው የውጭ ሃገር ተጓዡ Henry Salt በ1810 አካባቢ በጻፉት የግል ማስታወሻ፣ ቡዳ በዚያ ዘመን በከፍተኛ ደረጃ የሚታመንበትና ተፈሪ ክስተት መሆኑን በማስታወሻቸው ላይ እንዳሰፈሩት ይነገራል። Dufton and Stern በ19 መቶ ክ/ዘመን አብዛኛዎቹ ብረት ይቀጠቅጡ የነበሩት ፈላሻዎች ናቸው በማለት ስለማስፈራቸው በ Pankhurst መጽሐፍ ተገልጿል (Pankhurst 1990, 223)።

Pearce በጎብኝቱ ወቅት ከቡዳ ለመደበቅ የአካባቢው ሰው ብዙ መከራ ሲያደርጉ እንደተመለከቱ በPankhurst መጽሐፍ ተገልጿል (1990, 203) ። በሸማና በጋቢ ራሳቸውን ይሸፍናሉ። በአደባባይ ሰውነታቸው እንዳይጋለጥ ይጠነቀቃሉ። ሲበሉና ሲጠጡ ሰው እንዳያያቸው ይጋርዳሉ ብለዋል (Pankhurst, 1990, 203) ። ራስ ብሩ ለመጠጣት ብርሌያቸውን ሲያነሱ፣ እንዲሁም ሊያዛጉ አፋቸውን ሲከፍቱ አገልጋዮቻቸው በልብስ ሲጋርዷቸው ማየታቸውን በማስታወሻቸው ጽፈውታል

(Pankhurst, 1990, 203)። ጥሩ ፈረሶችና ጎበዝ ጋላቢዎች ከሌላው በተለየ ዐይን ያስፈራቸውል ተብሎ ይታመን እንደነበር ተጽፏል። ሰዎች ሲታመሙ የአብዛኛው ሰው ጥርጣሬ የሚያርፈው በጉዳ ነው በሚል ነው።

"በምሥራቅ ጎጃም ዞን በቢቡኝ ወረዳ የገነቱ ማርያም ቀበሌ የባህላዊ መቅ አሰራር" በሚል ርዕስ መኮንን ባይህ በ2002 ዓ/ም ባካሄደው ጥናት የአካባቢው ሰው የዕድ ጥበብ ባለሙያዎች ባሉበት ሰፈር ሰው በሚተላለፍ ጊዜ ጋቢ የለበሰ ጋቢውን፣ ነጠላ የለበሰ ነጠላውን፣ ጎጃም አዘነ የለበሰ ጎጃም አዘነውን ተከናንቦ ልጆች ከያዘም ለጆቹን ሸፋፍኖ ያልፋል በማለት እስከአሁን ድረስ በዚህ ሙያ በተሰማሩ ሰዎች ውስጥ እምነት እንዳለ የመስክ ተሞክሯቸውን አካፍለዋል (መኮንን ባይህ፣ 2002፣ 58) ።

በዚህ ሙያ የተሰማሩ ሰዎች እንደሚያስረዱት፣ የቤተሰብ አልበቃ ብሎ ልጆቻቸው አብረው እንዳይጫዎቱና ወጥተው እንዳይገቡ የተለያዩ ጫና እንደሚደረግባቸው ያስረዳሉ። የጨዋ ልጆች ከሚባሉት ጋር በሚጣሉበት ጊዜ ያለዕድሜያቸውና ያለደረጃቸው የጉዳና የሸማኔ ልጆች እያሉ እንደሚሰድቧቸውም አስፍረዋል። እነዚህ ባለሙያዎች ዛሬም በጋብቻ ልዩነት እንደሚደረግባቸው ይነገራል። በኑሯቸውና በስራቸው ይሳለቁባቸዋል። ቀን ቀን ሰው ይምሰሉ እንጅ አዳራቸው ከጅብ ጋር ነው እየተባሉም በማህበረሰቡ ይታማሉ በሚል መኮንን ገልጸውታል (መኮንን ባይህ፣ 2002፣ 57) ።

Ronald A. Reminick ፣ "The Evil Eye Belief among the Amhara of Ethiopia" በሚል ርዕስ፣ ከ1967-1969 ባለው ጊዜ ከመንዝ ሸዋ በሰበሰቡት መረጃ ላይ ተመርኩዘው በ1974 አንድጥናት አቅርበዋል። Reminick ክፉ ዐይን አለባቸው ተብለው የሚታሰቡት በዝቅተኛ መደብ ላይ ያሉ ሰዎች ስለመሆናቸው ያስረዳሉ (Reminick,1974, 280)። እነዚህ ሰዎች ከአካባቢው የማይወለዱና የትውልድ ቁጥር የሌላቸው በማህበራዊ መደባቸው የተለዩ ተደርገው የሚታሰቡ ናቸው ይሏቸዋል። በዚህ ጥናት አካባቢ በጉዳ የሚባሉት መሬት የሌላቸው ጢሰኞች፣ ብረቴዎች፣ ሸክለኞች፣ ሸማኔዎች መሆናቸውን ይገልጻሉ። እነዚህን ሰዎች የአካባቢው ሰው "ጠይብ" ብሎ እንሚጠራቸው ገልጸው፣ የታሉ ፍቺም ጥበበኛ ማለት እንደሆነ ይጠቁማሉ። ይኸንን ጥበብ ዲያብሎስ እንደገለጠላቸው ነው የሚታመነው። ይህ

ኃይል ልዕለ ሰብ የሆነ ችሎታን የሚያስገኝና በንግድና በሥራ ላይ ሁሉ ለየት ያለ ፈጠራ እንዲያሰጥ እንደሆነ ይነገራል። እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ አስክሬን ይበላሉ። እንዲሁም ራሳቸውን ወደ ጅብነት ይቀይራሉ ተብሎ እንደሚታመን ጽፈዋል (Reminick,1974, 283)። ሰዎችን በመንደፍ ታመው እንዲሞቱ ካደረጉ በኋላ ከተቀበሩበት አስነስተው አገልጋይ ያደርጓቸዋል እያሉም ያሚቸዋል በማለት ያስረዳሉ።

በአካባቢው ሁለት ዐይነት ማህበራዊ አወጋገን እንዳለ የሚገልጹት Reminick (1974, 283)፣ ንጹህ አጥንት አላቸው በሚል ጨዋና ባላባቶችን እንዲሁም አጥንተ ጎደሎ ናቸው በሚል መጠጦችንና ባዕዳዎችን በሌላ ምድብ ውስጥ ያስቀምጧቸዋል። በመጀመሪያ ምድብ የሚታቀፉትን ወገኖች፣ "ረጋ" ብለው ይጠሯቸዋል። ቡዳነት የሚኮነው በመወለድ በመሆኑ ሰዎች ምንጊዜም ማህበራዊ ደረጃቸውን አይለቁም ይላሉ (Reminick, 1974, 281)።

ቡዳ የሆነውን ሰው ካልሆነው ለመለየት አካላዊ መስፈርት ባይኖርም፣ ደማቸው ከጨዋው ይቀጥናል ተብሎ ስለሚታሰብ ቀጫጭኖች ናቸው። አይናቸው የተንሸዋረረና ከአይናቸው እንባና ፈሳሽ ያጎርፍ ይሉቸዋል (Reminick,1974, 281)። Reminick በአማራ ባህል ምሽት ተፈሪ ጊዜ ነው ይላሉ። በተለይ በዚህ ሰዓት ቡዳ የሚል ስም ከተጠራና ተፈሪው ሃይል ከሰማ ስለሚናደድ ከቤተሰብ አባላት መካከል አንዱን ይበላዋል ተብሎ እንደሚታመን ያስረዳሉ። ቡዳ የፈራ፣ ያዘነና የተጨነቀ ሰው ካየ ያጠቃል የሚል እምነት እንዳለ ገልጸውታል። መልከኛ የሆነ፣ ከሌላው ለየት ያለ ነገር የሚሰራ እንግዳ ሰው ቡዳ ይበላኛል ብሎ እንደሚፈራ መረጃው ይጠቁማል። ነገር ግን፣ ጥናታቸው ገለጭ በመሆኑ ለምን? የሚለውን ጥያቄ አይመልሱም (Reminick, 1974, 280)። ቡዳዎች ማታ ማታ ጅብ ይጋልባሉ፣ እንደ ጅብ ይፏኻሉ የሚለው እምነት በሰፊው አለ ይላሉ (Reminick 1974, 282)። ቡዳ በልዕለ ተፈጥሮ ነገረ እሳቤው ውስጥ የሚገኝ ኃይል ያለውና ሰውን የሚጎዳ፣ በአካል ውስጥ አድሮ ክፉ ነገርን የሚያሰራ ተደርጎ ይታሰባል።

"Ethiopian Evil Eye Belief and the Magical Symbolism of Iron Working" በሚል ርዕስ ጥናት ያካሄዱት ሌላኛው ተመራማሪ Niall Finneran ናቸው። በ1995 በአክሱም አካባቢ በጥንታዊ ቅርሶች ላይ ጥናት ለማካሄድ ቅኝት ሲያደርጉ፣ ቡዶች

ስላለበት መንደር ከሰሙት ታሪክ በመነሳት ስለቡዳ ለማጥናት እንደተነሳሱ ያስረዳሉ። Finneran በኢትዮጵያ ብዙ የክርስትና ሀይማኖት አማኞች፣ ጥቂት የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች የሚገኙበት ቦታ ነው ይላሉ። መዝሊሞች መጤዎች ተደርገው ስለሚታሰቡና የተሰማሩበትም መሪያ የእጅ ጥበብ በመሆኑ፣ በቡዳነት እንደሚጠረጠሩ ያስረዳሉ(Finneran, 2003, 428)።

በዚህ ተግባር የሚከሰሱት ሁሉም ሰዎች መጻተኞች፣ ባዕዶችና እንግዶች ናቸው። የአካባቢ ሰው ተወላጅ ሆኖ በዘሩ ቡዳ የሆነ ሰው አለ ተብሎ አይታመንም ይላሉ (Finneran, 2003, 428)። በመሆኑም፣ እነዚህ ሰዎች በመሪያም ሆነ በአካላዊ ቁመና ልዩ ተደርገው ይታሰባሉ። ቡድኑት የሥጋ ዝምድና ያላቸው ቡድኖች መታወቂያ ተደርጎ ይታሰባል(Finneran, 2003, 429)።

Finneran ከሰበሰቡት መረጃ ተነስተው፣ ቡዳዎች እንዲበሉ ዋነኛው አነቃቂ ጉዳይ ምቀኝነት(envy)፣ ጥቃቱ የሚበዛበትን ወቅት ደግሞ የምሳ ሰዓት፣ ህመም፣ እርግዝና፣ ልጅነት፣ የአዝመራ ወቅት እንደሆኑ ይገልጻሉ (Finneran, 2003, 429)። በዚህ ኃይል የሚጠቁ ሰዎች የተለየ ተሰጥኦ ያላቸው፣ ቆንጆና ወጣ ያለ ችሎታ የሚያሳዩ፣ የተትረፈረፈ ሃብት የያዙ እንደሆኑ ይናገራሉ። የዚህን ምክንያት ሲያስረዱ አካል የሚደክምበትና ኃይል የሚያንስበት ጊዜ በመሆኑ ነው ይላሉ። በምቀኝነትና በአካል መድከም መካከል ያለው ተጠየቃዊ ዝምድና አልተብራራም። በመሆኑም፣ ይህ አስተያየት ከመረጃው የተገኘ ሳይሆን ግምታዊ ለመሆኑ አሳይ ነው።

ከላይ የቀረቡት ሁሉም ጥናቶች አገሬውን ተጠቂ፣ መጤውን አጥቂ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው። ንጽጽሩ የግብርና መሪያና የዕደ ጥበብ ሥራ ሆኖ የተቃኘበት ነው። በተለይ ክርስትናና ጁዲዝም ያላቸውን ተቃርኖ ለማነጻጸር የሞከሩና በውጪኩና በውስጡ መካከል ስላለው መተሳሰብ የሚተርኩ ናቸው። በመረጃ አሰባሰብ ዘዴአቸው ላይ እንደታየው ኢትኖግራፊያዊ ምርምርን ተከትሎ የተካሄደው ጥናት አንድ ብቻ ነው። ሌሎቹ ምልከታን፣ ካልአይ ምንጭንና ማስታዎሻዎችን መሰረት አድርገው የተጠኑ ናቸው። በመረጃ ደረጃም የትኩረት ነጥብ ሆኖ የተመረመረው ይህ ጎጅ ሃይል አለባቸው ተብለው ስለሚጠረጠሩት ወገኖች ማንነት፣ ስለተሰማሩበት መሪያ፣ ለምን ክስተቱ ከዚያ መሪያ ጋር ሊተሳሰር ቻለ የሚሉት ነጥቦች ብቻ ናቸው።

በመሆኑም፣ የምርምር አንጻሩ ውስጣዊ እይታን (emic perspective) መሰረት ያደረገ አይደለም። በመከላከያ ዘዴዎቹ፣ በአጋላጭነቱ፣ በመፈወሻ ዘዴዎች ላይ ምንም አይነት ፍተሻ አልተካሄደም። ይኸ ሁሉ ባልተሟላበት ስለክስተቱ ምንነት አጠቃላይ የሆነ ትንታኔ መስጠት የሚቻል አይሆንም።

2.1.2. ከኢትዮጵያ ውጭ የተደረጉ ጥናቶች

በክፉ ዐይን ላይ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል። የተመራማሪዎች ብዛት እንዳለ ሆኖ የምርምሩ ዓላማም በዚያው ልክ ልዩ ልዩ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ ሁሉንም ማካተት ስለማይቻል አህጉራዊና አካባቢያዊ እሳቤዎችን ለማሳየት ተጠቃሽ የሆኑ ወካይ ስራዎችን በመጥቀስ እዚህ ላይ ለማቅረብ ይሞከራል።

በክፉ ዐይን ጥናት ስማቸው ተደጋግሞ የሚጠቀሱት Evans-Pritchard's (1937) Witchcraft, Oracles and Magic Among the Azande በሚል ርዕስ በናይልና በኮንጎ መካከል በሱዳን በሚገኙት በAzande ህብረተሰብ ላይ ያካሄዱት የኢትኖግራፊክ የመስክ ሥራ በብዙ ጥናቶች ውስጥ ተደጋግሞ የተጠቀሰ ታዋቂ ሥራ ነው። በተጨማሪም፣ በደቡብ ምዕራብ አሜሪካ በDine ወይም Navajo ህብረተሰብ ላይ Clyde Kluckhohn (1967) መስክ በመሄድ ከተናጋሪዎች አፍ ሰብስበው ያጠኑት ሌላኛው ተጠቃሽ ሥራ ነው። በ1960ዎቹ አካባቢ, Melford E. Spiro (1967) በደቡብ እስያ በሚገኙ የBurma ህብረተሰብ ላይ በክተሞች አካባቢ የሰበሰቡት የኢትኖግራፊ መረጃ እንዲሁ በብዙ ስራዎች ውስጥ የሚጠቀስ ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉም ጥናቶች በአቀራረባቸው፣ በትኩረታቸውና ክስተቱን በሚያዩበት መንገድ የሚለያዩ ናቸው። በሁሉም አካባቢ በዚህ ክስተት ላይ በተደረጉ ጥናቶች ውስጥ የጋራ ተተኳሪ ሆኖ የመጣው ነጥብ የጥቃት ፈጻሚዎችን ማንነት፣ ባህርይ፣ ዓላ፣ ማህበራዊ ደረጃና የውርሻ አይነት መለየት ላይ ነው። ጥቃት አድራሽ ወገኖች ጥቃቱን የሚያደርሱት ፈቅደው ነው ወይስ በማይቆጣጠሩት ሁኔታ ተገፋፍተው? የሚለው ዋነኛ ማጠንጠኛ ሆኖ በሁሉም ተዳስሷል። ጥቃት ፈጻሚ አካል ጉዳቱን የሚያደርሰው አውቆና ፈቅዶ ነው ወይስ በማያውቀውና

በማያስበው መንገድ ተገፋፍቶ በሚለው ነጥብ ላይ የተሰበሰቡ የኢትኖግራፊ መረጃዎች ሁለት መንገድ የተከተለ ነው።

ይህ ሃይል ያደረባቸው ሰዎች ጥቃት ሲያደርሱ አይታወቃቸውም፤ አስበውና አቅደው አይፈጽሙትም፣ ፈቅደውና ወደው አያደርጉትም ጉዳቱን አውቆ ከማድረስ፣ በዓላማና በዕቅድ ሆን ብሎ ከመፈጸም ጋር አይያያዝም ብለው የሚያስቡ እንዳሉም ተጠቁሟል (Vallee, 2010, 211)። ጥቃቱ የሚሰነዘረው ከጉዳት አድራሾች ዕውቀትና ግንዛቤ ውጭ ነው በሚል በሚታመንባቸው አካባቢዎች፣ ክፉ ዐይን በፈቃድ የሚሆኑት፣ ወደው የሚያቀርቡት ጠልተው የሚያርቁት አይሆንም። የሆነ ዓላማ ለማሳካት አስበው ሲያደርጉት አይታይም። ሳይፈልጉ ሲቀር የሚተውት አይነት አይደለም፣ አለማጥቃትን ፈልገው መተው አይችሉም የሚሉ ናቸው (Ibn Khaldum in Dundus, 1971, 259)።

በዳይኖች ግን ክፉ ዐይን ከቅርብ ቤተሰብ የሚወረስ ወይም የሚማሩት ነው ተብሎ ይታመናል (Kluckhohn in Vallee, 2010, 211)[7]። መውረስ ከላይኛው ጋር የሚስማማ ቢሆንም መማር የሚለውን ግን ሌላ ገጠመኝ ያደርገዋል። መማር በዚህ አገባቡ የሆነ ጥቅም ለማግኘት በዕቅድና በዓላማ የሚከናወን ማለት ሳይሆን አብሮ በማደግ ከክፉ ነገሮች ጋር በመላመድ የሚሆኑት ለማለት ነው።

በመማር ወይም በመልመድ የሚመጣ ከሆነ ክስተቱ የማንኛውም ሰው ጠባይ የሚሆንበት ዕድል አለው ማለት ነው። በተጨማሪም፣ የፊለግ የሚሆነው ያልፊለግ የማይሆነው ከሆነ ከተወሰነ ግላዊ ፍላጎት ጋር ተያይዞ የሚታሰብ ስለመሆኑ ልብ ይሏል። ነገር ግን፣ በእምነት ጥናት ውስጥ ሁለቱን ክስተቶች ለያይቶ የማየትና ለየባህርያቸውም የተለያዩ ስሞችን የመስጠት ልማድ እንዳለ የተገለጸ ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች "በክፉ ዐይን" እና "በሶሪሰሪ" መካከል ልዩነቶች ሲታዩ በሌሎች ደግሞ አንዳንዱ ቦታ ሶርሴሪ፣ በሌላ ቦታ ደግሞ ክፉ ዐይን ብቻ ተብሎ ሲገለጽ ይታያል።

[7] Among the Dine, witchcraft was something that was obtained or learned, usually from relatives'

Kluckhohn እንደጠቆሙት አንዳንድ ሰዎች ለማጥቃት ሲያስቡ ከአስከሬን ላይ የተለያዩ ንጥረ ነገሮችን ወስደው ይቀምማሉ ይሏቸዋል። ከዚያም ሊያጠቁት በፈለጉት ሰው አፍንጫና አፍ ውስጥ ይከታሉ (Vallee, 2010, 211)። ሊጎዱት ከፈለጉት ሰው አካል ላይ እንደጥፍር፣ ፀጉር፣ እና የተለያዩ ወዝ ያረፈባቸውን ነገሮች በመውሰድ በዚያ ላይ ደግመው ሰዎች የሚጎዱበትን መንገድ ያመቻቻሉ ይሏቸዋል (Douglas, 1970, II9; Leach 97I, 22-5)[8] ።

ነገር ግን፣ ይህ አካሄድ በአብዛኛው አካባቢ ከሚታመነው የክፉ ዐይን ጥቃት ጋር የሚገጥም ልማድ ሆኖ አላገኘሁትም። የክፉ ዐይን ጥቃት በአብዛኛው አካባቢ ሊቆጣጠሩት በማይችሉት ሁኔታ አምልጦ ወጥቶ ሰዎችን ይጎዳል የሚል ነው። ክስተቱ እንቅስቃሴን ከመከታተል፣ የሚያገኙበትን መንገድ ከማመቻቸት፣ የሚያጠቁ ሰዎችንም በቅድመ ሁኔታ መርጠ ከመያዝ ጋር ተዛምዶ የሚታሰብ እንዳልሆነ በአብዛኛዎቹ የኦትኖግራፊ ሪፖርቶች ላይ የተገለጸ ነው።

ይህ ጥናት በሚካሄድበት አካባቢም እንደዚህ ያለ እምነት ቢኖርም፣ በዚህ ተግባር የሚከሰሱ በደል አድራሾችን የሚጠሯቸው "እጀ ሰብ" ብለው ነው። እነዚህ አካሎች መንፈሶችን በማቅረብ ወይም የተፈጥሮ ምስጢርን በመረዳት በዓለማቱ ላይ የፈለጉትን ለመፈጸምና ለማከናወን የሚሞክሩና አቅደውና ፈቅደው ከሌሎች ኃይሎች ጋር በመተባበር ለጥቃታቸው ማስፈጸሚያነት እነሱን በአጋርነት የሚገለገሉ ናቸው (Evans-Pritchard,1935, 418)። በመሆኑም፣ ሶርሴሪ በትምህርት ወይም በመለማመድ የሚገኝ ሲሆን፣ ክፉ ዐይን ግን በውርስ የሚተላለፍ ደመነፍሳዊ ባህርይ ነው የሚለው በአብዛኛው አካባቢ የሚታመነው ነው።

የየማህበረሰቦች ልምድ እንደሚጠቁመው፣ በአብዛኛዎቹ ቦታዎች በተደረጉ ዳሰሳዎች ውስጥ የተገኘው መረጃ የሚያስረዳው፣ "ከልጅ ወደ የልጅ ልጅ የሚሸጋገርና ሊያመልጡትና ሊሸሹት በማይችሉት መንገድ በዘር ሐረግ ወርዶ የሚተከል ነው" የሚለው በአብዛኞቹ አካባቢዎች የሚታመን እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ። ለምሳሌ፡-

[8] external-controlled and internal-uncontrolled powers which involves the use of medicines for harming people

በአዛንዴ አንዳንድ ሰዎች የክፉ ዐይንን ሰብስታንስ ይዘው ይወለዳሉ ተብሎ ይታመናል (Evans-Pritchard's, 1937) ::

ይህ ሃይል በአዘንዴ mangu በሚል ስም የሚታወቅ ሲሆን ከእናት ወደ ሴት ልጅ ከአባት ደግሞ ወደ ወንድ ልጅ የሚተላለፍ ነው Mangu was transmitted from mother to daughter and from father to son :: በዘር ውርስ የሚመጣ ጣጣ ከሆነ ጉዳዩ ከተወሰኑ ማህበራዊ ቡድኖች ጋር የሚያያዝ ይሆናል:: የሃይሉ ባለቤቶች በምን መንገድ እንደሆኑ አያውቁም:: በፈቃዳቸው ያደረ እያወቁ የተማሩት፣ የሆነ ጥቅም ለማግኘት የተዋረሱት አይደለም በሚል የሚያምኑ ናቸው:: በተዋራሽ ነጻ ፈቃድ የሚመጣ ወይም በመልመድ የሚገኝ ሳይሆን፣ በውርስና በዘር ፍሬ ከአያት ከቅድመ አያት በመወለድ የሚጋባ እና ሆነውት የሚገኙት ነው በሚል የሚታሰብ ነው ::

ጥቃት አድራሾችም ፈልገውና ፈቅደው የማይሆኑት ከሆነ በዚህ የሚከሰሱት እነማን ናቸው? መርጠ የሚይዛቸውና የማይዛቸው የሰው ዘሮች አሉ ወይ? ኃይሉ ማደሪያ አድርጎ ለምን እነዚህን ሰዎች መረጠ? በማደሪያነት በሚገለገልባቸው አካሎች ዙሪያ ያለው እሳቤስ ምንድን ነው? ለመምረጫነት የሚያገለግለው መስፈርት ምንድን ነው? በእነዚህ ሰዎች ለምን? የሚሉ ጥያቄዎችን በመምዘገ የየማህበረሰቡን አስተሳሰብ ለማወቅ ቀጣይ ምርምር ተደርጓል:: በዚህ ዙሪያ ያለው አካባቢያዊ እሳቤ የተለያየ ሆኖ ተገኝቷል:: ሃይሉ በባህርይው ውስጥ መልካም ነገር ስለሌለው በማደሪያነት በሚመለመሉ ሰዎች ዘንድ ያለው አቀባበል ያልተለመደ መጥፎ ባህርይ ማሳየትና ተለይቶ መታየት ነው:: ማህበረሰቦች ጽንሰ ሐሳቡን የሚረዱበት መንገድ የተለያየ በመሆኑ፣ በማደሪያነት በሚገለገሉባቸው ሰዎች በኩል ያለው አረዳድም እንደዚያው የተለያየ ነው::

በአንዳንድ አካባቢዎች ክፉ ዐይኖች የሚባሉት በስስትና በስግብግብነት እንዲሁም በክፋትና በተንኮል የሚወቀሱ ሰዎች ናቸው (Vallee, 2010, 210) :: እነዚህ ማካፈልን የሚጠሉ፣ ብቻ መብላትንና መበልጸግን የሚወዱ፣ ተረዳድቶ ማደግን የሚያነውሩና ለራስ መሰሰትና ለግል ስሜት ማደር ላይ የሚተጉ ሰዎችን ክፉ ዐይን አለባቸው ይሏቸዋል (Kluckhohn in Vallee, 2010, 211) :: በመሆኑም፣

ማህበረሰቦች ቁልፍ ብለው ከያዟቸው እሴቶች መልካም ብለው ከሚያከብሯቸው ይጠቅሙኛል ብለው ከሚንከባከቧቸው መውጣት ይህን ስም ሲያሰጥ ይታያል።

ሌላው በክፉ ዐይንነት ለመጠርጠር ምክንያት የሚሆነው ነገር፣ "ከብዙሃኑ በአካል ቅርጹና በማህበራዊ አኗኗር የተለየ ሆኖ መታየት ነው። ልዩነቱ ከሚገለጽባቸው መካከል የዐይን ቀለም በአንዳንድ አካባቢ መሠረታዊ ሆኖ ይጠቀሳል። በሳሐራ አካባቢ ባሉ የአፍሪካ ሃገሮች ክፉ ዐይን እንዳለባቸው የሚገለጹት፣ ዐይኖቻቸው የተንሸዋረሩ ወይም የቀሉ ሰዎች ናቸው። በሜዲትራኒያን አካባቢ ደግሞ የአብዛኛው ሰው የዐይን ቀለም ጥቁር ስለሆነ፣ ሰማያዊ የዐይን ቀለም ያለው ይጠረጠራል። በሰሜን አውሮፓ ጥቁር የዐይን ቀለም ያልተለመደ ስለሆነ ተጠርጣሪ ነው። በማዕከላዊ ታንዛንያ ተመሳሳይ እምነት መኖሩን Beidelman (1963) በጥናት አረጋግጠዋል። በሰሜን ዩጋንዳ ዊቾች የሚጓዙት በእግራቸው ሳይሆን በራሳቸው ነው ተብሎ እንደሚታመን Middleton በጥናታዊ ሥራቸው ገልጸውታል። በዚህ አገባብ ደግሞ አለመመሳሰልና ልዩ ምልክት መያዝ ለመጠርጠር ምክንያት ነው።

ክፉ ዐይንን ከጨለማ፣ ከዳፍንት፣ ከቆሻሻና ከዱር እንስሳት ጋር አያይዘው የሚገለጹ ማህበረሰቦች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ (Mayer, 1954)። በጥንት ጊዜ፣ ረጅም መንገድ ተጉዘው ወደ ተለያዩ አካባቢዎች የሚሄዱ መነኩሴዎች በእንግድነታቸው ምክንያት ቡዳ ይባሉ እንደነበር በLykiardopoulos ተጽፏል (1981, 223)። ከላይ በቀረቡት መረጃዎች ውስጥ የጥርጣሬ ምንጭ የሆነው ነገር ልዩ መሆን ወይም እንግዳ ሆኖ መታየት ነው።

ሌላኛው የጥርጣሬው ምክንያት ሆኖ በማህበረሰቦች ጥናት ውስጥ የተጠቆመው ነገር፣ "ወጣ ያሉና በማህበረሰቡ የተነወሩ ባህርያትን ማሳየትና ያልተለመዱ ተግባሮችን መፈጸም ነው" (Marwick, 1965) ። አብዛኛው ሰው ነውር ብሎ ያጸደቀውን ደንብ የሚጥሱ፣ ከሥርዓትና ከደንብ ውጭ የሚሰሩ፣ ለማህበራዊ ግንኙነት የሚታሰቡ አስነዋሪ ሥራዎችንና ተግባሮችን ሁሉ የሚያከናውኑ ሲገኙ ክፉ ይሏቸዋል። ከእነዚህ መካከል በቅርብ ቤተሰብ መካከል ወሲብ መፈጸም (Lienhardt, 1951, 306)፣ የሰው ሥጋና አስከሬን መመገብ (Mair 1980, 228)፣ በሰው ፊት መሽናት፣ መዋሸት ወይም ማታለል(Vallee, 2010, 210) ይገኙበታል። በመሆኑም፣ የንጽሕና

ጉድለቶችና ማህበራዊ እርሞች በአንዳንድ ቦታዎች ተጠቃሽ የስነ ምግባር ጥሰቶች ናቸው።።

በዓለም ላይ የተካሄዱ ምርምሮች እንደሚያሳዩት ለክፉ ዐይን መንፈስ ማደሪያነት የሚጠረጠሩት ሰዎች ብቻ አለመሆናቸውን አረጋግጧል። ክፉ ዐይንነት፣ ሰዋዊ ባህርይ ብቻ ሳይሆን በእንስሳትና በተክሎችም የሚገለጥ መሆኑ የታመነ ነው። በመሆኑም፣ ማንኛውም ፍጥረት የመንፈሱ ማደሪያ በመሆን የማገልገል ዕድል እንዳለው መረዳት ይቻላል። ከተክሎችና ከእንስሳት ወገን የሆኑ አንዳንድ ዘሮች ከዚህ ሃይል ጋር በተያያዘ ስማቸው እንደሚነሳ ጥናቶች ያሳያሉ። ከእንስሳት ወገን በዚህ ሃይል ተሸካሚነት ከሚጠረጠሩት መካከል ጅብ፣ እባብ፣ ቀበሮና አንዳንድ የወፍ ዘሮች ይጠቀሳሉ። በተክሎች ምድብ ደግሞ የማግበስበስ፣ ሌላውን ተክል የመጋፋትና የማድረቅ ጠባይ ያላቸው ክፉ ተክሎች ከዚህ ስም ጋር ተያይዞ ስማቸው ይነሳል።

ክፉ ዐይን በባህርይው ከሰው ሰው በዘር ቢተላለፍም በጸታ በኩል ያለው አስተሳሰብ እንዲሁ ከአካባቢ አካባቢ እንደሚለይ ጥናቶች ያሳያሉ። ክስተቱ ጸታ ሳይለይ በሁሉም ላይ ይገለጣል የሚለው በአብዛኞቹ ጥናቶች የተጠቀሰ ቢሆንም፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የተለየ ነገር እንዳለ ለመረዳት ተችሏል። መንፈሱ፣ በማጥቂያ ቦታ ምርጫ፣ በማንቂያው ምክንያት፣ በሃይልና በአሰያየም ጸታዊ ጠባይ ያሳየባቸው ሁኔታዎች ለመኖራቸው የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ።

ጉዳዩ የዘር ውርስ ጣጣ ያለበት ተደርጎ ስለሚታሰብ በዚህ ኃይል ከሚጠረጠሩ ሰዎች እስከተወለዱ ድረስ የዝምድና ሐረግ መስመር ይዞ ይተላለፋል የሚል እምነት ያለ ቢሆንም (Lienhardt, 309)፣ በአንዳንድ አካባቢ ለምሳሌ፣ በዲንካ እምነት ከእናት ወደ ሴት ልጅ፣ ከአባት ደግሞ ወደ ወንድ ልጅ ጸታዊ ምድቡን ጠብቆ የሚጋባ ሆኖ ይታመናል ። በLugbara ዊች ሁልጊዜም (Vallee, 2010, 212) ወንዶች ሲሆኑ (Middleton, 1960, 239)፣ በNupe ደግሞ ሴቶች ናቸው (Nadel, 1952, 19)። ወንዶች የሚታሰቡት ደግሞ ከሴት ክፉ ዐይኖች ጋር ለመነጋገርና ለመወያየት የሚያስችል አቅም ያላቸውና ሴት ክፉ ዐይኖችን የሚቆጣጠሩ መልካም ኃይሎች ተደርገው ነው (Nadel, 1952, 19)።

በአንዳንድ አካባቢዎች የወንድና የሴት ክፉ ዐይኖች ስምና ግብር የተለያየ ሆኖ ይታሰባል። በጸታ ረገድ ያለውን የክፉ ዐይን እሳቤ ከጸታ ጋር በማያያዝ ለማጥናት ከሞከሩት መካከል Spiro (1967) ተጠቃሽ ናቸው። Spiro ጽንሰ ሐሳቡ ከጸታ ጋር የሚያይዘው አንዳንድ ነገር አለ ብለው የሚያምኑ ተመራማሪ ናቸው። ጥናት ባካሄዱበት፣ በBurmese ሴት ዊኞች Souns፣ ወንዶቹ ደግሞ Aulan Hsayas ተብለው መጠራታቸውን ይናገራሉ። በያታዎች መካከል ያለው ልዩነት የስም ብቻ ሳይሆን፣ የኃይል ብልጫ ጭምር ነው ይላሉ። ከያዙት ሃይል አንጻር ሁለቱ ጸታዎች ሲነጻጸሩ ሴቶቹ ከወንዶቹ ደካማ ሆነው ይታሰባሉ ባይ ናቸው። ከማጥቂያ ክልል አንጻር ያለው የያታ አመዳደብም Souns ጥቃት የሚያደርሱት በመንደራቸው አካባቢ ሲሆን፣ ወንዶቹ ግን ከመንደራቸው ራቅ ካለ አካባቢ ሄደው ነው። ለሴቶቹ የጥቃት መነሻ የሚሆነው በብዛት ክፋት፣ ተንኮልና ቅናት መሆኑ ተጠቅሷል (Valleee,2010, 212)።

ተጋላጮች

Middleton በLugbara ማህበረሰቦች ላይ ባካሄደው ጥናት ክፉ ዐይን የሚቀሰቀስበትን ትክክለኛ አውድ ሲገልጽ፣ ሰዎች በእርሻ ማሳቸው ላይ ማዕዳቸው ሞልቶ ቁጭ ብለው እየበሉ፣ ሳለ በአጠገብ የሚያልፍን ሰው እያዩት ሳያቀምሱት ሲቀር ነው ይላሉ። በጭፈራ ቦታ በባላንጋራው በዳንሱ ሴቶችና ወጣቶች መደነቃቸውን ሲያይ፤ እሱ አጥቶ ሌሎቹ በሃብት ከብረው፣ ልጆች በዝተው፣ ከብቶቹ ረብተው ሲመለከት ነው(Middleton 1960, 240)። በዚህ እሳቤ ሁሉም ሰው ክፉ ዐይን የመሆን ዕድል እንዳለው ያስረዳል።

Elworthy ደግሞ፣ በአንድ ሰው ወይም ነገር ላይ ከመጠን ያለፈ አድናቆትና ምስጋና ማቅረብ ነው ብለው የሚያስቡ አካባቢዎች እንዳሉ ይጠቁማል (Middleton 1960, 240)። በሁሉም ሃገሮች ቀደም ባለው ጊዜም ሆነ በአሁኑ ሰዓት ሕፃናት ለክፉ ዐይን መንፈስ ተጠቂ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሆነው ይታሰባሉ። ዝነኛና ታዋቂ ሰዎችም እንደ ሕፃናት ሁሉ በተጋላጭነት የሚጠቀሱ የማኅበረሰብ ክፍሎች ናቸው (Jackson, 1975, 389)። ስመጥርነትና ተሰሚነት፣ ነፍሰ ጡር መሆን፤ ወሊድ በአብዛኛው የተጠቀሱ ናቸው። ባለጠጎች ሆነው ያገኙትን መልካም ፀጋ ለሌላው

የማያካፍሉ ከሆኑ ሃብታቸው እነደሚያስጠቃቸው ተገልጿል(Jackson, 1975, 389) ::

ከሰው ልጅ በተጨማሪ በኃይሉ ከሚፈለጉ ፍጥረቶች ውስጥ የቤት እንስሳት ይገኙበታል:: ከቤት እንስሳት መካከልም ዋነኞቹ ለሰው ልጅ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ዋጋ ያላቸው ብቻ ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ ፈረስ ዋነኛው ሆኖ ቀርቧል:: ፈረስ በህንድ፣ በቻይና፣ በቱርክ፣ በግብጽ፣ በኢንግሊዝ፣ በስኮትላንድ፣ በአይርላንድ፣ በግሪክ ከሁሉም በላይ ደግሞ በጣሊያን የተጠቀሰ እንስሳ ነው:: ከእንስሳት በተጨማሪም አንዳንድ የእህል ዘሮች፣ ዛፎች፣ አበባዎች እና የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችም ጉዳቱ ያርፋባቸዋል በሚል ጥንቃቄ የሚደረግላቸው ናቸው::

በመከላከያ መንገዶች

የክፉ ዓይን ጥቃትን ለመከላከል በሚያገለግሉ መሳሪያዎች ዙሪያ በጣም የተጋነነ ልዩነት ባይኖርም ከባህል እና ከማህበረሰብ አኳያ ልዩነቶች እንዳሉ ጥናቶች ያሳያሉ:: አሳሳች ነገሮችን በማድረግ የተመልካቹን ቀልብ ለማስቀየስ የሚደረግ ሙከራ፤ ለልጁ ወይም ለዕቃው ያለንን አድናቆት ከገለጽን በኋላ ምራቅን መትፋት ወይም አለመዋጥ፣ በልጆች የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ልዩ ልዩ ጌጣጌጦችን ማድረግ፤ በአንዳንድ ባህሎች ስለ ሰዎች የጤና ሁኔታ፣ ሰላም መሆንና ደህንነት ሲጠየቁ ጥሩም ሳይሉ መጥፎም ሳይሉ አማካይ የሆነ መልስ መስጠት በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው::

በአንዳንድ የአፍሪካ ሃገሮች ይህ ሃይል አለባቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎች ከአደበታቸው የአድናቆት ቃል ከወጣ እንስሳትን ይገድላሉ፤ ዛፍን ያደርቃሉ፤ ለልጆች ሞት ምክንያት ይሆናሉ በሚል ይፈራሉ:: የግሪክ እናቶች አባቶች ልጆቻቸውን እንዳያዩ ይከለክሏቸዋል (Plut, mor. 682) :: የሮም ነርሶች ልጆች በተኙበት ክፍል እንግዳ ሰው ከገባ ወይም የተወለደውን ልጅ ካየው ፊቱ ላይ ሶስት ጊዜ እንትፍ እንዲልበት ያስገድዳሉ ይባላል (Pliny, Nat. Hist. 28.29):: አባት ከመውደድ ብዛት በልጆቹና በንብረቱ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል፣ ስለእነሱ

ጥሩነት ማሰብ የለበትም ይላሉ። ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ሁሉም ሰው በጎ የመሆን ዕድል ያለው መሆኑን ነው።

ስለዚህ፣ የዘር ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሰው በጎ የሚሆንበት አጋጣሚ መኖሩንም ማወቅ ይቻላል። በስኮትላንድ ገበሬዎች ከብቶቻቸው ወደ መስክ ሲሄዱ በብዛታቸው ወይም በአካላቸው መመላት ተማርከው በደስታ ብዛት ስለእነሱ በማሰብ እንዳይጎዷቸው መነሻ የሆነውን ማየትን ለማስቀረት ከቤት ውስጥ ይቀመጣሉ ይባላል።

ጣሊያናዊ አሜሪካኖች አድናቆታቸውን ከገለፁ በሁዋላ ምስጋና ይጨምራሉ። "እንዴት ታምራለች"፣ ካሉ በሁዋላ "እግዚአብሔር ይባርክሽ ወይም ያሳድግሽ" በማለት በቅናት አማካይነት የወጣው ምኞትና ውዴታ፣ የምስጋና ቃል በመጨመር ምቀኛቸውን ያጠፉልናል ብለው ያስባሉ(Green 1997, 120)። ይህ ነገር የሚጠቁመን ጥቃቱን የሰው ልጅ የሚያደርሰው ፈቅዶና ወዶ ሳይሆን ባላወቀው አኳኋን ተመርቶ መሆኑን ነው። ከገባበት ከፍተኛ ተመስጦ ሲነቃ የዋጠውን በመትፋት፣ ከልቡ ያስገባውን በመተው አደጋው እንዳይደርስ መልሶ ለመተው የሚፈልግ መሆኑን ነው።

በአንዳንድ አካባቢ ከዚህ ጥቃት ለማምለጥ ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ብቻን መንቀሳቀስ ይፈራል። ዊችች ለማጥቂያነት የሚጠቀመበትን የሰውነት ወዝና ከአካላቸው ላይ ተቆርጠው የሚጣሉ ነገሮችን መደበቅ ልማድ ነው። በአንዳንድ አካባቢ ደግሞ ከሚበሉት ምግብ ቀንሰው ከቤታቸው ውጭ በማስቀመጥ ማታላይ ሃይሉ ወደ ቤት ሲመጣ እንዲቀምስ በማድረግ ፍላጎቱን ለማርካት ይሞክራሉ።

በሚያደርሱት ጉዳት

እነዚህ ሃይሎች በሰዎች ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት በተመለከተ በሰዎች፣ በንብረቶችና በእንስሶች ላይ በዓይን አማካይነት የሚደርስ ጉዳት ነው(Vallee,2010, 212)። ጉዳቱም ህመም፣ ሞትና ውድመት ሊሆን ይችላል(Kearney, 1975, 247)። ጥቃቱ የደረሰው በንብረት ላይ ከሆነ የመሰነጣጠቅ፣ የመሰበር፣ የመናድ አደጋ ነው (Vallee,2010, 212)። እንስሳት ከሆነ ደግሞ ከስቶና መንምኖ ይሞታል (Kearney,

1975, 247)። የወለደች ላምን ክፉ ዐይን ከተቆራኛት የጡት መድረቅ፣ የምግብ ፍላጎትን ማጣት፣ አዝመራ ሲሆን በአበባው የመጠውለግ፣ ፍሬው በረከት የማጣት፣ በአመዳይና በትል መወረር ይገኙበታል።

"ማንጉ" አካላዊ ህመምን ብቻ ሳይሆን የአእምሮ መታወክንም ጭምር እንደሚተክል ይናገራሉ። የዊች ክራፍቱን ነፍስ ወደ ተጠቂው አካል በመላክ፣ በሃይሉ የተወጋውን አካል ነፍስ ሰልበው ከያዙ በኋላ መግደል። ነገር ግን፣ ክፉ ዐይኖች ኃይላቸውን በማንኛውም ጊዜ ማውጣት የሚችሉ ሆኖ ሁኔታው ግን በተሸካሚው ዕውቅት አይከናወንም። በአዘንዴ ዊቾች አካላዊ ጉዳትን እና ሞትን ያመጣሉ ተብሎ ይታመናል። አካላዊ ጉዳትና እስከ ሞት የሚደርስ ችግርን ያስከትላሉ።

2.2. ትውራዊ አቀራረቦች

ማህበራዊና ባህላዊ የስነ ሰብዕ ተመራማሪዎች፣ የስነ ማህበረሰብ አጥኝዎችና የስነ አእምሮ ሊሂቃን የተለያዩ የመተንተኛ አንጻሮችን ይዘው ክፉ ዐይንን ለማጥናት ሞክረዋል (Vallee, 2010, 214) ። እነዚህ ጥናቶች ከመስክ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ተመርኩዘው የተጠኑ በመሆናቸው፣ በምንነታቸው ላይ የተሰጠው መግለጫ የየአካባቢውን ልማድ ያሳያል ተብሎ ይታሰባል። ነገር ግን፣ በተመራማሪዎች የጥናት መስክ መለያየት፣ ትኩረት በተደረገበት የመረጃ አይነትና በያዙት ዓላማ ምክንያት የአመለካከት ልዩነቶች መታየታቸው አልቀረም።

በዚህ ክፍል የተለያዩ ተመራማሪዎች ስለክፉ ዐይን ምንነትና እሳቤ ያላቸው አተያይ እንዴት እንደተንጸባረቀ ተዳስሶ ይቀርብበታል። የተለያዩ ማህበረሰቦች ይሽንን እምነት እንዴት ነው የተረዱት? ባህላዊ ዳራው ምንድን ነው? እንዴት ነው ከነዋሪው ህይወት ጋር የተሳሰረው? የሰው ልጅ ለምን ይሽንን እምነት ፈጠረ? ለሚለው መልስ ይሆን ዘንድ እነዚህ ተመራማሪዎች የተለያዩ ቴዎሪዎችን ተጠቅመው ዳስሰውታል።

2.2.1.የስነአእምሮ እይታ ክፉ ዐይንን ለማጥናት

ማንኛውም አካል የሚያድገው ከመወለዱ በፊት በነበረ ባህል ውስጥ በመሆኑ፣ የባህል ውጤት ነው በማለት የኢትኖሳይንስ ምሁራን ያስረዳሉ። እያንዳንዱ ሰው ሲወለድ

ነገሮችና ሁኔታዎች መልክና ሥርዓት ይዘው ስለሚያገኛቸው አወቀ የሚባለው ከተሰራው ልማድ ጋር ራሱን ሲያስማማ ነው፡፡ ዕውቀትን ማህበራዊ የሚያሰኘው ይኸው ባህሪው ነው፡፡ ግለሰቦች የዕውቀት ምንጮች ናቸው የማይባለውም ባለው ላይ የሚቀጥሉ እንጅ ከባዶ ነገር ላይ የሚነሱ ባለመሆናቸው ነው፡፡ እያንዳንዱ አንደበቱን የሚፈታው ራሱ ባልፈጠረው ቋንቋ ነው፡፡ የሚገለገለው ባልሰራው መሳሪያ ነው፡፡ እነዚህ ገጽታዎች ዕውቀት፣ ጥበብና ሃብት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ የወል ሃብቶች ናቸው ያስብላቸዋል፡፡ እነዚህን ልዩ ልዩ ሃብቶች የምናወርሰውም ሆነ የምንወርሰው ከማህበረሰብ ነው፡፡ የእነዚህ ሁሉ ነገሮች አመንጪ ማን እንደሆነና ከየት እንዳገኛቸው ማየት ካልቻልን የራሳችን ስራዎች አይደሉም ማለት ነው፡፡

ሁሉም ሰው ማንኛውንም ስራ ከማህበረሰቡ እየተማረ ዕውቀት አድርጎ ይይዘዋል፡፡ ታይለር (2004)ባህል፣ የሰው ልጅ የህብረተሰቡ አባል በመሆኑ የሚማራቸው/ የሚለምዳቸው እውቀት፣ እምነቶች፣ ስነጥበብ፣ ስነምግባር፣ ህግ፣ ደንብ፣ ወግ እና የመሳሰሉትን ችሎታዎችና ልምዶች ሁሉ የሚያካትት፣ አንድ ሰው የህብረተሰብ አባል በመሆኑ የቀሰማቸውን ክህሎቶችና ልምዶች ሙሉ የሚያጠቃልል ውስብስብ የሆነ ውህድ ነው በማለት የሚበይኑት ይህንን ነገር ታሳቢ በማድረግ ነው (ታይለር በራስ ወርቅ፣ 2004፣3) ፡፡ የታይለር ብያኔ ባህል በዝርያ የሚወረስ ሳይሆን፣ በመኖር የሚለመድና የሚማሩት መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡

ከባህል ባሻገር እያንዳንዳችን ግላዊ የሆኑ በዘርያ የምንወርሳቸውና ከቤተሰብ የምናገኛቸው ልዩ ልዩ የህይወት ልምዶችና ትምህርቶች አሉ ይላሉ፡፡ እነዚህ ግላዊ ተሞክሮዎች በአስተሳሰባችንና በስሜቶቻችን ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩና ባሕርይን ለመተርጎም ምክንያት የሚሆኑ መገለጫዎች ናቸው በማለት ይገልጿቸዋል(7) ፡፡ Kardiner እና Linton በባህልና በባሕርይ መካከል ያለው ቁርኝት በምክንያትና በውጤት ደረጃ የሚገለጽ ነው ይላሉ፡፡ ባሕርይ በመጀመሪያ የሚያስገኙት ቀዳሚ ተቋማት የሚባሉ ሲሆን፣ በቀዳሚ ተቋማት አማካይነት የሚፈጠሩትን ካልዓይ ተቋማት ብለው አንዱ የሌላው አመጪ፣ ሌላው የአንዱ ወጤት ናቸው ብለው

ያስባለ። ቀዳማይ ተቋማት አንድን አካባቢ በመልመድ የሚገኝ ውጤት በመሆኑ፣ የሚታሰቡት ስጦታዎች ተደርገው ነው(McGee and Warms , 2008, 205)።

ሰፈሎች ደግሞ ማህበራዊ አደረጃጀቶች፣ ግብረገብ የሚያስተምሩበት (disciplining) መንገድ፣ ቴክኖሎጅዎች፣ የልጆች የአስተዳደግና የአሰላጣጠን ሁኔታ ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ የህይወት ልምዶች በልጆች የሰብዕና አቀራረጽ ላይ መሰረታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ አለባውያን ናቸው ተበሎ ይታመናል (McGee and Warms ,2008, 205)። ልጆች በሚያድጉ ጊዜ ከእነዚህ ተቋማት ጋር እየተላመዱ ስለሚሄዱ፣ በሂደቱ ለሁሉም የጋራ የሚሆን፣ ውስጣዊ ግፊትንና ጭንቀትን የሚፈጥሩ ክስተቶች ይመጣሉ ይላሉ። በዚህ ጊዜ ካልአይ ተቋማት እነዚህን መናጋቶች ለማደላደል፣ የተፈጠረውን መዛባት ለማስተካከል ይቋቋማሉ ብለው ያስባሉ (Barnard and Spencer 2002, 217)።

እነዚህ የህብረተሰቡ የመጀመሪያ ተቋሞች መሰረታዊውን የሰብዕና ውቅር ፈጣሪዎች ሲሆኑ፣ ሰብዕና ደግሞ በተራው ለስሜቱ ማደላደያ ይሆኑ ዘንድ ሁለተኛ ተቋሞች እንዲፈጠሩ ያደርጋል። እንደ ሃይማኖት ያሉ ባህላዊ ተቋሞች ሚና በስነአእምሯዊ መንገድ ሰብዓዊ ፍላጎቶች የሚረኩበትን መንገድ ለማመቻቸት የሚቋቋሙ ናቸው። በመሆኑም፣ በማህበራዊና በስነአእምሯዊ አገላለጽ፣ ተገቢ የሆኑ ባሕርዮችና የአስተሳሰብ ሂደቶች (አምክንዮ) የሚገመገመው ከባህላዊ እሴቱ አኳያ ነው ይላሉ። በባህልና በባሕርይ ላይ ቀደምት ጥናት ያደረጉት የስነልቦናና የስነሰብዕ ተመራማሪዎች የልማዳዊ አንጻራዊነት ተከታዮች እንደነበሩ ይነገራል(Barnard 2004, 99)።

ከእነዚህ መካል Spiro ይጠቀሳሉ። Spiro (1967) በአስተዳደግ ችግር ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያደርጉት እንክብካቤ፣ የሚሰጡት ፍቅር በሚቀንስ ጊዜ በልጆች ሰብዕና ውስጥ ጭንቀትና ፍርሃት፣ ብቸኝነትና ግራ መጋባት ይመጣል ይላሉ። ወላጆች ራሳቸውን ከተጠያቂነትና ከወቀሳ ለማዳን ውጫዊ ነገሮችን ሰበብ ያደርጋሉ። በቤተሰብ መካከል ግንኙነቱን ጤናማ ለማድረግ የጠባዩን ለውጥ በሌላ ነገር ያሳብቡታል። ለአጋጣሚው ስበብ የሚያደርጉት ክፉ ዐይን ነው ይላሉ።

ይህም ልጆች በወላጆቻቸው ላይ ጥላቻና የባላጋራነት ስሜት እንዳያድርባቸው በሌላ አካል የማሳበብ ስልት ነው ይሉታል (Barnard 2004, 99)።

ሰዎች አንዳንድ ጊዜ መልካም ለሆኑ ነገሮች ትኩረት ሰጥተው የመከታተል ልማድ ይታይባቸዋል። የምልክታው መነሻ የኔ በሆነ ምኞት ነው። አድናቆት ቀስ በቀስ ወደ ራስ መመኘት የሚሄድበት ጊዜ አለው። እንደዚህ አይነት ምልከታዎች ትኩረት ያረፈበት አካል ግራ እንዲጋባ፣ እንዲጠራጠር፣ ለምን የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ ያስገድዳሉ ይላሉ። ዐይን፣ በሰዎች፣ በእንስሳትና በግዑዛን ነገሮች ላይ እስከሞት የሚያደርስ ኃይል ያመነጫል የሚለው መከላከያ የተፈጠረው አብዝቶ መመልከትን ነውር ለማድረግ ነው (Erkison in Dundes,1971, 263) ።

Erikson በበኩሉ ሕፃናትን ከሚገባው በላይ አፍጥጦ መመልከት፣ መንፈስንና ቀልብን ሁሉ ሰብስቦ በእነሱ ላይ ማሳረፍ ሃላፊነት የጎደለው ተግባር በመሆኑ መግታት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ (Erikson, in Dundes 1971, 263) ። አፍጥጦ መመልከትን ለመስበር ድርጊቱን የክፉ መንፈስ ሥራ አድራጎ ማሳሰብ ነው ይላሉ። ምቀኝ ክክፉ ዐይን መንፈስ ጋር የሚያያዘው በዚህ ምክንያት ነው ይላሉ (Erikson, in Dundes, 1971, 263) ።

የዚህ ትውፊዊ ዳራ ደጋፊ እንደሆነ የሚነገርለት Summer (1960, 434)፣ እርኩስ መንፈሶች በሰዎች ስኬትና ዕድገት ለማይደሰቱ አካሎች ያምናሉ። በእርግጥ በቡዳና በቅናት መካከል የቀረበ ግንኙነት መኖሩን ከተለያዩ አካባቢዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ያስረዳሉ። በአንድ ነገር ላይ አምሮትና ፍላጎት የሚቀሰቀስብኝ ነገሩን አይተን ስንመኘው ነው። አንድን ነገር ረዘም ላለ ጊዜ በጉጉት እንድንመለከተው የሚያደርገን በነገሩ ላይ ልዩ ፍላጎትና ውዴታ ሲያድርብን ነው (Dundes,1971, 263)። ጥሩ ነገርን መመኘት ደግሞ ሰዋዊ ባህርይ ነው። ማየት በተራው ምኞትን ይወልዳል። አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነን ነገር ስናይ ውዴታችንን የምንገልጸው ከአንደበታችን በሚወጣው የአድናቆት ቃል አማካይነት ነው።

ቅናት የሚወጣው አንድም በአንደበት አለዚያም በዐይን (ወይም በሁለቱ) ነው (Schoeck 1955) ። Schoeck (1955) ከዚህ በመነሳት ቡድኑን ዓለማቀፋዊ የሆነ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA

የክፉ ቅናት መገለጫ ነው ይላሉ። ሰዎች አይተው እንዳይመኙ፣ ተመልክተው መጥፎ ነገር እንዳያስቡ ለማድረግ አትኩሮ የሚመለከትን ሰው በዳ በማለት እይታውን እንዲያቋርጥ ወይም እንዲመጥነው ማድረጊያ የመቆጣጠሪያ መንገድ ይሆናል።

የቅናት ትውር ተከታዮች ያቀረቧቸው ነጥቦች በአንድ ጎን አሳማኝና ተቀባይነት ያላቸው ይመስላል(Spooner in Dundes, 1971, 263)። ነገር ግን፣ "በጽንሰ ሐሳቡ ዙሪያ የሚሸከረከሩትን ሃሳቦች አመልቶና አቅፎ መልስ ለመስጠት የሚያስችል አቅምና ስፋት ይዟል ለማለት ግን ያስቸግራል" በማለት ይሞግታሉ (Spooner in Dundes, 1971, 263)። አንድ ትውር በአንድ ልማድ ውስጥ ያለን ጥቃቅን እውነታ ለመተንተን እስካላስቻለ ወይም ለባህርያቱ ሰብ ክፍሎች ምንነት ማስረዳት ይችል ዘንድ አቅም ካነሰው፣ ትውሩን አሳማኝና ትክክለኛ ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል በማለት ይከራከራሉ። ለምሳሌ፡- የበዳ ምልክት የሆነው ማዛጋት ምንጩ፣ ምንድን ነው? ቢባል ይህ ትውር መልስ አይኖረውም። የዛፍን ፍሬ ክፉ ዐይን የሚያደርቀው ለምንድን ነው? የላም ጡትስ ለምን ይነጥፋል? እነዚህን አስተሳሰቦች በትውሩ ውስጥ እንዴት ነው የሚካተቱት? የሚተረጉመውስ? በማለት የአንባሩን ጉድለት ይጠይቃሉ (Spooner, in Dundes, 1971, 263) ።

Spooner (in Dundes, 1971, 263) አክለውም ቅናት በአንዳንድ ገጽታው ዓለማቀፋዊ ጠባይ ያለው ነገር ሆኖ ሳለ፣ በድነት ለምን በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ተወሰነ? ብለው ይጠይቃሉ። ከዚህ መገንዘብ የምንችለው ቅናት የተወሳሰበ ገጽታ ካለው የበዳ እሳቤ ውስጥ አንዱ ክፍል እንጅ፣ ጽንሰ ሐሳቡን በተሟላ ሁኔታ የሚወክልና የሚያብራራ አለመሆኑን ነው።

በዚህ የመተንተኛ ሞዴል ላይ የሚነሱ ሌሎች ጥያቄዎችም አሉ። በመጀመሪያ፣ ጥናቱ ትኩረት አድርጎ መረጃ የሚሰበስበው የመከላከያ መንገዶች ላይ ብቻ ነው። በመሆኑም፣ አካሄዱ የክስተቱን መሉ ገጽታ እንዳያይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው ጋርዶታል ማለት ይቻላል። በተጨማሪም፣ ሰዎችን ከድንጋጤና ከግራ መጋባት ለመከላከል የተዘየደ ከሆነ ለሰብሎችና ለእንስሳት ማድረጉ ለምን አስፈለገ? ለጨቅላ ህጻናት ለምን መከላከያ የማድረጉ መከራ ባህል ሆነ? ብሎ መጠየቅ ይቻላል።

ስለዚህ፣ አትኩሮ መመልከትን ለማስቀረት የሚለው የማያ መነጽር ክስተቱን በሙሉ የሚተረጉም አይደለም የሚለው ነቀፌታ እውነትነት ያለው ይመስላል። በመሆኑም፣ ምቀን በክፉ ዐይን ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ ቦታ ቢኖረውም፣ ክስተቱን አመለካቶና አቅፎ ለመተንተን የሚያስችል አቅም ይጎድለዋል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

የፍካሬ ልቦና መስመር ተከታዮች የትንታኔ አፅንኦት በመከላከያ ዘዴዎች ላይ ያተኮረ ነው። ሕብረተሰቦች ቡዳን ለመከላከል የሚገለገሉባቸውን ነገሮች ቅርጽ በማየት ምንነቱን ለማስረዳት የሞከሩ ናቸው። የዚህ ትውር አቀንቃኞች እንደሚሉት ክፉ ዐይንን ለመከላከል ማህበረሰቦች የሚይዟቸውን መከላከያዎች እንደክታብ ያሉ ልዩ ልዩ ጥፈቶች ነው። በእነዚህ ክታቦች ውስጥ የሚጠቀለለው የወንድ ብልት ቅርጽ ያለው ነገር ነው። ይህ ቅርጽ ከሌሎች ነገሮች በተለየ መከላከያ ሆኖ ለምን ተመረጠ? በሚለው ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።

በአንዳንድ አካባቢ ሰዎች በመንገዳቸው ክፉ ዐይን ካለባቸው ሰዎች ጋር ፊት ለፊት ሲገጣጠሙ፣ ብልታቸውን ፈጥነው ይይዛሉ (Valla, in Dundes, 1971, 264) ። በአንዳንድ አካባቢ ደግሞ በክታቡ ውስጥ የወንድ ብልት ቅርጽ ያለው ቀይ ጥፈት አስጥፈው ያስቀምጡና እየሄዱ እያሉ የሚጠረጥሩት ሰው ሲመጣ በእጃቸው ያንን ጥፈት ይነካኩታል ይባላል። ይሽን የሚያደርጉት ቡዳ የውንድን ብልት ይገድላል ብለው ስለሚያስቡ ነው (Valla and Servadio, in Dundes, 1971,264)። ክፉ ዐይን ከያታ ጋር ብቻ ለመያያዝ ከታሰበ ነፍሰ ጡር ሴቶችን ያጠቃል። በአንዳንድ አካባቢ ደግሞ ጡት መጥባት የተወ አንድ ሕፃን ወደ መጥባቱ ቢመለስ ቡዳ ይበላል ይበላዋል ተብሎ ተጠቅሷል (Dundes, 1971, 264)። Dundes እንዲሁም ላሞችና ሴት ሕፃናት ከየተቃራኒ አቻዎቻቸው በበለጠ፣ በቡዳ የሚበሉበት አጋጣሚ የሰፋ ስለመሆኑ በጥናቶች ተረጋግጧል በማለት ሃሳቡን ውድቅ ያደርጋሉ። ስለዚህ፣ ወንድነትን በመነጠል ከቡዳ ጋር አዛምዶ ለመተርጎም መሞከሩ በመረጃ አሰባሰብና አተናተን ላይ ያለን ክፍተትና ዝንፈት የሚጠቁም ነው ይላሉ (Dundes,1971, 264)።

Roberts (in Dundes, 1971, 264) ከተለያዩ አካባቢዎች በተሰበሰቡና የቡዳ ባህርያትን በሚያሳዩ መረጃዎች ላይ የንጽጽር ጥናት አድርገው የጋራ የሆነ ጠባይ

ለመንቀስ ሞክረው ነበር። ድንበር ዘለል የባህል ጥናት ካደረጉ በኋላ አንድ የጋራ ነው ያሉትን ባህርይ ለማስተዋወቅ ያስባለ። ምንም እንኳን በመካከላቸው ያለውን የዝምድና ሁኔታ ለማብራራት ባይችሉም፣ ቡድነት ወተት ከማለብና ከብት ከማርባት ጋር በእጅጉ ይያያዛል ከሚል ማደማደሚያ ላይ ይደርሳሉ(1976, 241, 258) ።

ፍካሬ ልቦናውያንም (psychoanalysis)፣ አይንን ከእንስት የስነህይወት ቅርጽ ጋር በማነጻጸር እምነቱን በዚያ መንገድ እንዲታሰብ ይሞክራሉ (Reitler in Dundes, 1971, 264)። የአይን ብሌንን በሴት ብልት፣ ክዳኑን በብልት ከንፈር፣ ሽፋሽፍቱን በብልት ፀጉር መስልው ክፉ ዐይንን በዚህ አቀራረብ ለመተንተን የሄዱበት መንገድ ይጠቀሳል(Tourney and Plazak in Dundes, 1971, 264)። ስለዚህ፣ አይን ወክሎ የሚቆመው የወንድን ወይስ የሴትን ልጅ ብልት ወይስ ከሁለቱም ውጪ ያለን ሌላ ነገር? ይህ እንዴት ነው ሊመለስ የሚችለው። ይህ አስተሳሰብስ ላምን ከመጉዳትና ወተቷን ከማድረቅ ጋር እንዴት ይያያዛል? የሚለው በዚህ ሞዴል መልስ የሚያገኝ አይመስልም። በመሆኑም፣ በክስተቱ ውስን ገጽታ ላይ ብቻ በማተኮር ነገሮችን ለማየት መሞከሩ የክስተቱን ሙሉ ገጽታ ለማወቅ አያስችልም።

ተግባራውያን አቀራረብ

ተግባራውያን፣ ባህላዊ ተቋማት የአንድን ህብረተሰብ አባላት ቁሳዊና ስነልቦናዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉ መሳሪያዎች ናቸው ብለው የሚያምኑ ናቸው። የዚህ ትውር አቀንቃኝ እንደሆኑ የሚነገርላቸው Malinowski (1939,941) ፣ መሰረታዊ የሰው ልጆች ፍላጎቶች ናቸው በማለት ምግብን፣ መዋለድን፣ አካላዊ ምቾትን፣ ደህንነትን፣ መዝናናትን፣ እንቅስቃሴንና ዕድገትን ይጠቅሳሉ። የእነዚህ ፍላጎቶች ምንጭ ተፈጥሯዊው ዓለም ሆኖ መገኛውንም ከቁሳዊ ዓለም ያደርጉታል (Malinowski,1939, 941)፣ ። የባህላዊ ተቋማቱ ሚና የሚሆነው፣ እነዚህ ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ላይ ይሆናል (McGee and Warms, 2008, 161)።

መራባት ወንድና ሴት ዖታዊ ፍላጎታቸውን የሚያረኩበት፣ ዝርያቸውን የሚያበዙበትና የሚያስቀጥሉበት መንገድ ነው (Malinowski, 1939, 941)። ሰዋዊው

ፍጡር በአካላዊ ምቾቱ ንቁና ውጤታማ የሚሆነው በጤናማ የአየር ንብረት ውስጥ ሲኖሩ ነው። ለማረፍና ለመተኛት ምቹ የሆነ መኖሪያ ቦታ፣ ለመንቀሳቀስና ለመስራት የሚስማማ የአየር ሁኔታ ያስፈልጋል (Malinowski, 1939, 941)። ደህንነት ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አዳጋዎች መጠበቅ፣ ከመሬት መንቀጥቀጥ፣ ከተለያዩ ሞገዶች፣ ከማዕበል፣ ከአስፈሪ አራዊትና ከሌሎችም ጎጅ ከሆኑ ፍጥረታት ሥጋቶች ነጻ መሆን ነው።

እነዚህ ምቾቶችና ማህበራዊ ደህንነቶች ካልተጠበቁ፣ የሰው ልጅ መንፈሳዊና ቁሳካለዊ ሁኔታ አደጋ ላይ መውደቁ አይቀርም ይላሉ። ምግብ በሌለበት ስለ ህይወት አይታሰብም። ደህንነት ባልተጠበቀበት ስሜት ውስጥ ሁከትና አለመረጋጋት ይነግሳል። ጤና ይረበሻል፣ አካላዊ ጥንካሬ ጉልበት ያጣል ብለው ይናገራሉ። ስነልቦና ወደ አለመረጋጋትና መረበሽ ይሄዳል። ህይወት ወደ መመሰቃቀልና መታወክ ያመራል። እነዚህ ያልተለመዱ ክስተቶች ሲያጋጥሙ፣ ደስታ እንደሚታጣና ፍርሃት እንደሚወር ያስረዳሉ። እንደዚህ አይነት ጭንቀቶች የሚነሱት ደግሞ የተወሰኑ ፍላጎቶች ተቀስቅሰው ለማርካት የሚያስችሉ ቴክኒኮች ሲታጡ ነው ብለው ያስባሉ (Homans,1941, 166)። ይህንን ጭንቀትና ችግር ለመቅረፍ አማራጭ መፍትሄዎች የሚያደርጓቸው የእምነት ተቋሞችን ነው። እምነቶች ግለሰቦች ወደ ማህበረሰቡ ልማድና እሴት እንዲቀርቡና አክብረው ጠብቀው እንዲይዟቸው ያደርጋሉ።

በመሆኑም፣ የሰው ልጅ በእምነት ተቋማት ላይ ሙሉ እምነት የሚያሳድረው ከዚህ ጭንቀት ሊገላግለው የሚችል ሌላ አማራጭ አለማግኘቱ ነው። ፍላጎቱን በግል ጥረት ማሳካት ሳይችል ሲቀር ሊያሳካልኝ ይችላል ብሎ በሚያስበው ተቋም ላይ ጥገኛ ይሆናል። አካላዊ ፍላጎቶች እንዴት ነው ሊረኩ ወይም ሊሟሉ የሚችሉት? ተብሎ ሲጠየቅ የሚገኘው መልስ በቡድኑ እምነት ላይ መተማመን ሲፈጥሩና እርስ በርስ እየተረዳዱና እየተጋገዙ ችግሮቹን በጋራ መቅረፍ ሲሞክሩ ነው። የጎደላቸውን እየሞሉና አዳዲስ ነገሮችን እያከሉና እየፈጠሩ ሲሄዱ ነው (Malinowski, 1939, 943) ።

ተግባራውያን ክሊሎች የማህበረሰብ ትውር አቀንቃኞች የሚለያቸው ዋናው ጉዳይ ለግለሰቦች የሚሰጡት ትኩረት ነው (Malinowski, 1939, 161; McGee and Warms , 2008,161)። ተቋማት የግለሰቦችን ፍላጎት ለማርካት የሚኖራቸውን ሚናና እነዚህን ፍላጎቶች ለማርካት ባህላዊና ማህበራዊ ማዕቀፎች እንዴት እንደሚሰሩ በመመርመር ላይ ትኩረት ይሰጣሉ (Barnard and Spencer, 2002, 61)። የዚህ ትውር አቀንቃኞች፣ አስተሳሰብን ለማወቅ ስሜታዊና ዕውቀታዊ የሆነውን አእምሯዊ ሂደት ብቻ መመርመር በቂ አይደለም ብለው የሚከራከሩ ናቸው (Malinowski, 1939, 939)።

ከዚሁ ጎን ለጎን የሰው ልጅ ስነህይወታዊ ፍላጎቶች መታየት ይኖርባቸዋል ብለው የሚመክሩ ናቸው። አካላዊ ፍላጎት፣ አካባቢያዊ ተጽእኖዎች እና ለተዕእኖዎች ያለው ባህላዊ ምላሽ ሁሉ ጎን ለጎን መመርመር ይገባዋል ባዮች ናቸው (Malinowski, 1939, 940)። የሰው ልጅ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አካባቢው የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ በእንቅስቃሴው የሚደርስበት ተጽእኖ፣ ምኞትንና ፍላጎቱን ለማሳካት ወደ ትብብርና ወደ እርስ በርስ መረዳዳት የሚሄድበት መንገድ ሁሉ የጥናቱ አካል ተደርጎ እንዲያዝ ይመክራሉ (Homans, 1941,164; Malinowski, 1939, 940)። ግለሰቦችን ወደ ህብረተሰብ የሚያመጣው መቧደኛ መንገድ መነሻው የግል ፍላጎቶች የሚፈጥሩት ጭንቀትና መረበሽ ነው (Malinowski, 1939, 940)።

በመሆኑም፣ የጥናቱ ዋና ጉዳይ የሰው ልጅ ስነህይወታዊ ገጽታው በመሆኑ፣ ቁሳዊው ዓለም (the physical world) የትኩረት ጉዳይ ነው (Malinowski, 1939, 940) ። የሰው ልጅ ደህንነቱና ማህበራዊ ቡድኑን ለማስቀጠል ያለው አስፈላጊነት ሁሉ የሚታቀፈው በዚህ ውስጥ ነው ብለው ያስባሉ። ይህ ፍላጎትና ምኞት እንዲሟላ ሰው ሆኖ መፈጠር ብቻውን በቂ አይደለም ብለው ይከራከራ። ግለሰቦች እንደተወለዱ የሚያገኙት ነገር ለተፈጥሯዊ ፍላጎታቸው ምላሽ የሚሰጥ ነው። ተፈጥሯዊ ፍላጎቶች ይህ ሁኔታ ግለሰቦች ከማህበራዊ ቡድኑ ጋር በምን መልክ ተቀላቅለውና ተስማምተው መኖር እንዳለባቸው እንዲያስቡ ያስገድዳቸዋል (Homans, 1941, 161)።

በሰው ልጅ አእምሮ ከሚመላለሱ ሐሳቦች መካከል አንዱ ለምን እና እንዴት መልካም ያልሆኑ ነገሮች ይከሰታሉ? የሚለው ጥያቄ ነው። አንዳንድ አደጋዎች መሠረታዊ በሆኑ የሰው ልጆች፣ እንስሳትና ሰብሎች ዕድገት ላይ ችግር ሲፈጥሩ ይታያል። የተወሰነ ወቅትን ጠብቆ የሚመጣ ድንገተኛ ሞት፣ ህመም፣ ድርቅ፣ ረሃብ፣ ቸነፈር አለ። ያልተለመዱና እንግዳ ተፈጥሯዊ ክስተቶች እንዴት እንደሚመጡ ግልጽ አይደለም። እንደዚህ የመሰለ እንግዳ ክስተቶች ሲያጋጥሙ ለምን በዚያ ሰው፣ ወይም ቡድን፣ እንስሳ፣ ንብረት ላይ ተለይተው ደረሱ? ለምን በሌላ ላይ አላጋጠሙም? የሚል ጥያቄ ይነሳል። እንደዚህ አይነት ነገሮችን ማን ፈጠራቸው፣ ለምን ፈጠራቸው ለሚለው ምላሽ ለማግኘት ስለሚቸገር መልስ የሚሆነው "እምነት" ነው። ለማስረዳት የሚያስቸግሩ እንግዳ ገጠመኞች እንዲሁም በስሜት ህዋሶቻችን ለይተን ልናውቃቸው የማንችላቸው ከእውቀትና ከልምድ በላይ የሆኑ ክስተቶች ሲደርሱ ሰበብ የሚሆነው "ክፉ ዐይን" ነው።

የብሪቲሽ የስነ ሰብዕ ተመራማሪ የሆነው Evans-Pritchard (1937) ፣ በአዘንዴ ህብረተሰብ ላይ ያካሄደው ጥናት ከላይ ለተጠቀሰው አንጻር በምሳሌነት የሚቀርብ ነው። ጥናቱ በአካባቢው መጥፎ ዕድሎች ሲከሰቱ እንዴት እንደሚታሰቡ፣ አሻሚ፣ ግራ አጋቢ፣ እንግዳ የሆኑ፣ የማይታወቁ፣ ያልተጠበቁና ያልተገመቱ ነገሮች በሰዎች አስተሳሰብ ውስጥ ሲመጡ እንዴት እንደሚተረጉሙና ለመምጣቸው ምክንያቱ ማን እንደሆነ ያለው በዚህ ተጠቃሎ ቀርቧል (Sanders, 2001, 8) ።

በሰው ልጆች ህይወት ለምን ያልተለመዱ ነገሮች ይከሰታሉ? የሚለው ጥያቄ ሰዋዊ ነው (Evans-Pritchard, 1937)። በአዘንዴ አንድ ዝሆን አንድን አዳኝ ረግጦ ቢገድለው ለምን ይህንን ሰው ሊገድለው ቻለ? ለምን ሌላ ሰው ላይ ጥቃቱ አልደረሰም? ለምንስ ይኸ ዝሆን ይህንን ችግር አደረሰ? ለምን በሌላ ዝሆን አልሆነም? ብለው ይጠይቃሉ። በተጨማሪም፣ ለምን ዛሬ? ይኸ ድርጊት በሌላ ጊዜ ለምን አልተፈጸመም? እያሉ የክስተቱን አመጣጥ አጋጣሚያዊ አድርገው ላለመመልከት ይሞክራሉ (Evans-Pritchard Malinowski, 19376, 9-70)። በዚህ ጊዜ የክፉ ዐይን እምነት ጣልቃ ይገባል። አንድ ሰው በጤና ቆይቶ ድንገት ሲታመም፣ ጓደኞቹ ሳይታመሙ እሱ ለምን ታመመ? ብለው ይጠይቃሉ። እባብ

ጠብቆና ለይቶ አንድ ሰው ላይ ጥቃት ሲያደርስ፣ ሌሎች አዳኞች ደህና ሆነው ሳለ እሱን ለይቶ ለምን ነደፈው? ይላሉ፡፡

ሰዎች የሰውነታቸውን ምስጢር፣ በአለም ለመኖር የቻሉበትን ምክንያት ለማወቅ በተፈጥሮ ይጓጓሉ፡፡አካባቢያቸውንም በመመልከት የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ገጽታዎችና መልክአምድራዊ ቅርጾች አፈጣጠርና አመጣጥ፣ ማን እንዳስቀመጣቸው ለመረዳት ይሻሉ (ዘሪሁን፣ 1998፣ 33) ፡፡ ህይወታቸውን ለማቆየት በሚደረግ ጥረት ከተፈጥሮ ጋር ትግል ሲያደርጉ ብዙ አስደንጋጭ፣ አስፈሪና ፈታኝ ሁኔታዎች ይገጥሟቸዋል፡፡ እንዲህ ያሉት ሁኔታዎች የመጡት ከየት ነው? ብለው ያስባሉ፡፡

ለየት ያለ መልክና ቅርጽ ወይም ድርጊት ያላቸው እንስሳትና ተክሎች፣ እንዲሁም የመሬት አቀማመጦችን ሲያዩ ለምን ተለዩ? ይህንን ያደረገው ማን ነው? እያሉ ይጠይቃሉ፡፡ ለምን ተለይተው ይህን ቅርጽ ሊይዙ ቻሉ? ብለው ይመረምራሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ለምን በቅሎ መከነች? የጅብ አንድ እግሩ ለምን ተለይቶ አጠረ? የሌሊት ወፍ ተለይታ ለምን ማታ ማታ ትበራለች? የሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም፣ የክፉ ዐይን ፋይዳ የሚሆነው የሰው ልጅ በአካባቢ ያሉትን ነገሮች እና ዓለማት ኬት መጣ (origin)፣ በዙሪያ ላሉ የተዘበራረቁ ተፈጥሮዎች በፎክሎር አማካይነት ሥርዓትና ቅርጽ በማበጀት ለሕይወት ፍቺ፣ ለኑሮው መልክ፣ ለኅሊና አንጻራዊ መረጋጋትን ማግኛ መንገዶች ይሆናሉ (ፈቃደ አዘዘ፣ በሽፈራው 2004፣ 105)፡፡ መልካም ያልሆኑ ዕድሎችን እና አጋጣሚዎችን አምጪ አካል ተደርጎ ይታሰባል፡፡

የክፉ ዐይን እምነት አዋኪና የረጋውን አደፍራሽ ለማህበራዊ ውጥረት ሰበብ ሆኖ የሚጠቀስ አካል ነው፡፡ ነገር ግን፣ ይህ ውጥረት የሚወጣበት ብቸኛው መንገድ ግን አይደለም ብለው የሚከራከሩ አሉ፡፡ በምዕራቡ ዓለም እንደ ስፖርት፣ ዘረኝነት፣ ብሔርተኝነትና ጦርነት ያሉ ክስተቶች መነሻቸው ማህበራዊ ውጥረት ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ፡፡ Mary Douglas (1970) አርታኢ ሆነው በሳተሙት መጽሐፍ ውስጥ አስተዋጽኦ የነበረው Keith Thomas (1970) የአታችነት ተግባር (explanatory function) በአቀራረቡ የክፉ ዐይን እምነት ስለመኖሩ በቂ ማሳያ አይደለም ብለው ከሚከራከሩት ወገኖች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ስለዚህ፣

ከችግሮች መካከል አንዱ ከሆነ ይህ ተግባሩ ቀዳሚ አፈጣጠሩ ሳይሆን፣ እግረ መንገድ የሚያስገኘው ጥቅም ነው የሚል አቋም ያራምዳሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ድክመት በተጨማሪ፣ የዚህ ትውር አቀንቃኞች የሰውን ልጅ እንቅስቃሴ ወደ ተራ ሂደት (mechanical processes) ዝቅ አደረጉት በሚል ጠንካራ ትችት ይቀርብባቸዋል (Vallee, 2010, 215) ፡፡ ክስተቱን እንደተራና አሳማኝ ያልሆነ የማስፈጸሚያ መሳሪያ አድርገው አሰቡት ብለው ይነቅፏቸዋል፡፡ ሁለተኛው ወቀሳ፣ አንጻሩ የማህበራዊ ለውጦችን ተጽእኖ አያይም፡፡ ነገሮች ቋሚና የማይለወጡ ናቸው ብለው ያስባሉ እያሉ ይተቿቷል፡፡ አዋኪና የማይፈለጉ ማህበራዊ ክስተቶችን (ለምሳሌ እንደክፉ ዐይን ያሉ እምነቶችን ማለት ነው) አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዳላቸው አድርገው ለማሳየት ይሞክራሉ በማለት ይነቅፏቸዋል(Vallee, 2010, 215) ፡፡ እንዴት? የሚለውን ከመመለስ ባለፈ ለምን? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የላቸውም፡፡

2.2.2.የተግባራውያን-መዋቅራውያን አቀራረብ

የስነማህበረሰብ አጥኝዎች የምርምር ፈለግ እንደሆነ የሚነገርለት የተግባራውያን መዋቅራውያን አንጻር አጽኑኦቱን ቡድን ላይ ነው፡፡ የዚህ ትውር አቀንቃኞች፣ “ህብረተሰብ በሥርዓት የተዋቀረ ነው” ብለው የሚያስቡ ናቸው፡፡ እንደ Spencer ያሉ የዚህ ትውር አቀንቃኞች ከዚህ ማደማደሚያ ላይ የደረሱት ሞዴላቸውን ከህያው ፍጥረቶች ሥርዓትካር አዛምደው በማየት ነው፡፡ እያንዳንዱ ህብረተሰብ እንደሰው ልጅ ሁሉ ከልጅነት እስከ እርጅና የሚያልፍበት ተመሳሳይ ደረጃዎች አሉት ብለው ስለሚያስቡ የሰው ልጅ ስነህይወት የሚሰራበትን መንገድ ለህብረተሰብ ጥናት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ፡፡

Spencer እና Durkheim ህብረሰተብ ለአንድ ዓላማ የቆመ የተለያዩ አካሎች ያሉት ሥርዓታዊ ውቅር ነው ብለው ያምናሉ፡፡ እነዚህ ክፍሎች በሂደት የሚለዋወጡ ሆነው ውቅሩን ጠንካራና ልል የሚያደርጉት በመካከላቸው በሚመሰርቱት ዝምድና አማካይነት ነው ይላሉ፡፡ ይህ ቆየት ያለው የመዋቅራውያን ተግባራውያን አመለካከት ቀስ በቀስ በራሱ በDurkheim በኋላ የተሻሻለ ሲሆን አዝጋሚ ለውጡን

ከማየት ይልቅ ማህበራዊ ውቅሮች ያላቸውን ወቅታዊ አገልግሎት በመፈተሽ እንዴት ጤናማ ማህበረሰብ መፍጠር ይቻላል? የሚለውን ሲያጠኑ ነበር።

Brown (1935, 395)፣ እያንዳንዱ ህብረተሰብ የተለያየ ጥቅምና አገልግሎት ካላቸው ግን ደግሞ ከሚናበቡ፣ ለአንድ የጋራ ተግባርና ተልዕኮ ከቆሙና ፍጹም ውህደት ከመሠረቱ ልዩ ልዩ ብልቶች ተግጣጥሞ የተበጀ ተቋም ነው የሚለውን የSpencer እና የDurkheim አመለካከት ይደግፋሉ። ሁሉም ውቅሩን ፈጣሪ ብልቶች በግላቸው የሚሰጡት ጥቅምና አገልገሎት እንዳለም ያምናሉ። በውቅሩ ውስጥ መሠረታዊው ነገር ተዋቃሪ አካላቱ የሚኖራቸው ተናጥላዊ ጥንካሬ ሳይሆን፣ በህብረት የሚያስገኙት ውህደት ነው ብለው ያስረዳሉ። እያንዳንዱ ተዋቃሪ ከመሰል አካሎች ጋር በመሳሳብና በመዛመድ አንዱ ለሌላው በሚጥቅምና በሚመች መልኩ የሚፈጥሩት ግንኙነት ህብረተሰብን ጤናማ ከማድረግ አኳያ ያለው ሚና የላቀ ነው ይላሉ (Barnard, 2004, 66)። በማህበራዊ አደረጃጀቱ ውስጥ ወሳኝ ሚና ያላቸው ንዑሳን ውቅሩን ፈጣሪ አካሎች ግለሰቦች ሲሆኑ፣ እነዚህ ግለሰቦች ወደ አንድ ጥምር አሃድ (integrated whole) የሚመጡበት የማህበራዊ ዝምድና መፍጠሪያ መንገዳቸው ደግሞ "ሥርዓት" ነው (Jarvie, 1973). ።

በመሆኑም፣ እያንዳንዱን ማህበራዊ ውቅር ጥበቅ ወይም ልል የሚያደርገው አካሉን የፈጠሩት ልዩ ልዩ ክፍሎች ጤናማ ዝምድና መፍጠር አለመፍጠራቸው ሆኖ (Radcliffe-Brown, 1935, 396)፣ በማህበራዊ ውቅሮች መካከል ያለው ትስስር ሲላላ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተገቢ ተግባሮቻቸውን ማከናወን ይሳናቸዋል። እያንዳንዱ ተዋቃሪ አካል ለጥቅል ማህበራዊ ስራቱ የሚመችና የሚገጥም ተግባር ሲያከናውን ማህበራዊ ጤና የሚሰፍን ይሆናል። ማህበራዊ ውቅሩ ወደ ሙሉ ውህደት ባደገ ቁጥር ማህበራዊ ጤና (social health)፣ ማህበራዊ ሰላምና ቡድናዊ ትስስር እየጠነከረ ይመጣል። በሰዎች መካከል መስማማትና መተሳሰብ እየነገሰ ይሄዳል። በማህበራዊ ውቅሩ ውስጥ ባሉ ሥርዓቶች መካከል ያለው ቅንጅት የላላ ከሆነ ጤናማው አካሄድ ወደ መደነቃቀፍና መተራመስ (disorder)፣ ሥርዓት ወደማጣትና ማህበራዊ ህመም (social ill-health) ወደ ማብዛት ይገባል(Radcliffe-Brown,1935, 397)።

ማህበራዊ ሥርዓቱ የሚታመመውና ሰላም የሚያጣው እያንዳንዱ ተዋቃሪ አካል የሚገባውን ነገር በሥርዓት ማድረግ ሲያቅተው ነው። ይህ የሚመጣው ከውስጥና ከውጭ የሚነሱ ግጭቶች፣ ማፈንገጦች፣ ግፊቶች፣ ፍላጎቶችና አዳዲስ አስተሳሰቦች ሲመጡ ነው። በሽታው አይሎ ውቅሩ ተገቢውን ሥራ እንዳያከናውን ካሳሰረውና ጤናማ አካሄዱን ካናጋው በህመም አማካይነት ህብረተሰባዊ የሚነቅዝ ይሆናል። ከማህበራዊ ውቅሩ ውስጥ የተወሰነው ክፍል በታመመ ቁጥር ማህበራዊ ውቅሩ ተግባሩን በተገቢው መንገድ እንዳያከናውን ያደርገዋል።

Radcliffe-Brown (1935, 397) የማህበራዊ አወቃቀሩን ጤናማ ጉዞ ከሚያናጉት መካከል የጥቅም ግጭቶች ተጠቃሾች ናቸው ይላሉ። ይህ ግጭት በማህበራዊ ሥርዓቱ አባላት መካከል እኩል ተጠቃሚነት ቀርቶ ግለኝነት አስተሳሰብ ሲበዛ የሚፈጠር እንደሆነ ያስገነዝባሉ። ነገር ግን፣ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ህብረተሰቡ፣ ማህበራዊ ተቋማትን አቋቁሞ ልዩነቶችን በማጥበብ አንድነት የሚመጣበትን ብልሃት ከዘየደ ከንቅዘት ይታደጋዋል። በዚህ ችግር ውስጥ የክፉ ዐይን ክስ የሚሆነው በማህበራዊ ሥርዓት ውስጥ ለተፈጠረው ንቅዘትና ጤናማ ያልሆነ አካሄድ ግለኝነትን ተካይና ችግር ፈጣሪ በመሆን ነው። ለምሳሌ፣ በDinka ብዙ ሃብት የሰበሰበን ሰው ህብረተሰቡ የሚጠራው "ቡዳ" ብሎ ነው። የግል ብልጽግናን ማህበራዊ እሴቱ ያነወረው የቡድን መንፈስን ያናጋል ብሎ ስለሚፈራው ነው። ነፍስ የሚያጠፉ፣ የሰው ሥጋ የሚበላ፣ በአጠቃላይ የነውር ምግባር የሚሰሩ ሁሉ ለማህበራዊ ሰላም ጠላቶች በመሆናቸው ምድባቸው ከክፉ ዐይን ነው (Vallee, 2010, 214)

እነዚህ ሃይሎች የረጋውን ሥርዓት ወይም ተፈጥሮ ስለሚያመሰቃቅሉና ስለሚያውኩ ለረጋው ውቅር ባላንጋራዎች ናቸው። ጤናማው የሰው ልጅ አኗኗር እየታወከ በሄደ ቁጥር፣ ማህበራዊ ሥርዓቱ በአሳታፊነቱ ስለሚደክም አንድነትንና ጥንካሬን ለሚያላላው ነገር ክፉ ዐይን መጠሪያ ይሆናል። በመሆኑም፣ ማህበራዊ ውቅሩ ፍጹም ውህድ በሆነበት ሥርዓት ውስጥ የክፉ ዐይን እምነት ገቢ የሚል ሲሆን፣ በውስጣዊ አደረጃጀትና አወቃቀር ላይ ክፍተት ከበዛ ክሱ ይበረክታል።

የጸናውንና የሰከነውን በመረበሽ በኩል ማህበራዊ ለውጦች የሚያስከትሉትና የሚያስተዋውቁት ነገር አብሮ የሚጠቀስ ነው። አዳዲስ አስተሳሰቦች በነባሩ ውቅር

ላይ ለውጥን ስለሚጠሩ፣ ክፉ ዐይን በብዛት አዲስና መጤ ለሆነ ለውጥ መጠሪያ ይደረጋል። በመሆኑም፣ ከህብረተሰቡ በአኗኗር፣ በአስተዳደርና በአካል ለየት ብሎ መገኘት፣ አዳዲስ ሀሳብ ማመንጨት፣ መነጠል፣ የተለየ ሆኖ መፈጠር፣ ከተለመደው ልዩ ሆኖ መታየት ህብረተሰባዊ አንድነት እንዲላላ ያደርጋል ብለው ያስቡታል። የአካባቢው ሰው ይህንን ስም በመፍራት ከብዙሃኑ አስተሳሰብና ተግባር ላለመነጠል ሲል የነበረውን ወደ ማክበር፣ አዲስ የመጣውን ወደ መሸሽና ወደ መፍራት ይገባል። አዳዲስ ነገሮችን እየፈራና እየሸሸ በሄደ ቁጥር ከነባር እሴቶች ጋር ያለው ትስስር ይጠነክራል። በመካከለኛው አውሮፓ ከመንግስት ሥርዓትና ከቤተክርስቲያን ቀነኖ ወጣ ያለ ጠባይ የሚያሳዩ ሰዎችን ክፉ ዐይን አለባቸው ይባል የነበረው፣ ተግዥዎች አስተዳደሩን ተቀብለው እንዲሄዱ ለማድረግ ነበር። ለእነዚህ ሰዎች ይኸ ስም ይሰጣቸው የነበረው ቤተክርስትያን ከደነገገችው ልማድ የሚቃረን ድርጊት ፈጽመው ሲገኙ ወይም ለቆመው ህግና ደንብ አልገዛ ሲሉ ነው (Harris in Vallee, 2010, 214)።

በማዕካላዊ አፍሪካ በክፉ ዐይን የሚጠረጠሩት ጥሩ ኑሮ የሚኖሩና የተሻለ ማህበራዊ ቦታ የያዙ ሰዎች ናቸው (Marwick,1952; Mitchell,1956)። እነዚህን አካሎች በግለሰቦች ሞትና ህመም ተጠርጣሪዎች ናቸው። እነዚህ የህብረተሰብ አባላት ከሌላው በተለየ በዚህ ስም ያስከሰሳቸው፣ ማህበራዊ ቦታዎችን ለግል ጥቅማቸው አውለውታል በሚል ነው። ማህበራዊ ሥርዓቱ ግልጽ የሆነ የሥልጣን፣ የሃብትና የማህበራዊ ክብር ማግኛ መንገዶችን ዘርግቶ በዚያ መምራት ካልቻለ አድልዎና በደል የሚገለጸው በዚህ ስም አማካይነት ነው (Anderson, 2002; Marwick,1965)። ክፉ ዐይን ለበዳይና ለክፉ አድራጊ የተሰጠ ስም በመሆኑ፣ እሴታዊ ስርዓቱን በመደገፍ ማህበራዊ አወቃቀሩን አጠንካሪ ኃይል ሆኖ ይመጣል። ሰዎች ሰዎችን እንዳይበድሉ ከበደሉም በኋላ ለስራቸው ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ ክፉውን አስወግዶ ማህበራዊ ተቋሙ ጤናማውን ጉዞ ሲጀምር ክፉ ዐይን የሚጠፋ ይሆናል። ስለዚህ፣ ክፉ ዐይን በዚህ ቦታ ያለው ትርጉም የህበረተሰባዊ ውቅሩ ጥንካሬ ማስጠበቂያ መሳሪያ መሆን ነው (Marwick,1952)።

በአብዛኞቹ የአፍሪካ ሃገሮች በተፈጠሩ የመንግስትና የህብረተሰብ ግጭቶችና ውጥረቶች ውስጥ የክፉ ዐይን ሚና የፖለቲካና የአስተዳደር በደል መኖሩን ማሳያ ነው (Geschiere, 1988, 37) [9]። የመንግስታቱ የጨቋኝነት ባህርይ የብዙሐኑን ህዝብ ኑሮ ሲያንሳቁለው፣ ፍርድ እየተዛባ በደሎች ሲያይል፣ አደጋዊ አሰራር ነግሶ ማህበረሰቡ ጤና ሲያጣ ህብረተሰቡ፣ የፖሊተካ መሪዎችን አስነዋሪ ሥራ የሚቃወመው ለግዥዎች የክፉ ዐይን ስም በመስጠት ነበር ። በማህበራዊ ውቅሩ ውስጥ ፖለቲካ አንዱ ማህበረሰብን ፈጣሪ ተዋቃሪ አካል እንደመሆኑ የዚህ ክንፍ መንቀዝ አጠቃላይ ማህበራዊ ስርዓቱ እንዲታመምና እንዲናጋ ስለሚያደርገው ክፍተቱን ጠግኖ ጥንካሬውን ለመመለስ ንቅዘት ያየለበትን ክፍል ለይቶ ማከም ያስፈልጋል።

በመሆኑም፣ ፖለቲካዊ ስርዓቱ መልካም ነገርን ማስፈን እየተሳነው በክፉ ድርጊት ሲጠመድ፣ ለህብረተሰባዊ ውቅር መዳከም ምልክት ይሆናል። በዚህ ጊዜ የተበላሸውን ክፍል ለይቶ በማከምና ጠግኖ በማስተካከል ማህበራዊ ስርዓቱ የነበረው አገልግሎት እንዲሰራ ክፉ ዐይን ስርዓት ማስፈኛ መሳሪያ ይሆናል። በሰሜን ዩጋንዳ በተካሄደ ጥናት ላይ የተገኘው መረጃ የሚጠቁመው ይህንኑ እውነታ ነው። በህዝብ ተቀባይነት የሌላቸውን የጎሳ መሪዎች በማውረድ በተሻለ ሰዎች ለመተካት በአደረገው ሙከራ ሥርዓቱ ላይ ግፍ የሰሩ ሰዎች እንዲወርዱ ሲጠይቅ ምክንያት ያደረገው "ክፉ ዐይኖች" ናቸው በማለት ነበር (Middleton,1960)።

በመሆኑም፣ የደም ትስስር የሌላቸው ሆነው ከብዙ ብሔሮች የተውጣጡና ልል ማህበራዊ ትስስር ባላቸው ህዝቦች መካከል የክፉ ዐይን እምነት አይኖርም ይላል (Barnard, 2002, 844) ። የአንድ ጎሳ አባላት ሆነው ውጫዊ ድንበራቸው የታጠረ ከሆነ እንዲሁም በውስጣዊ ግንኙነት ውስጥ አለመረጋጋትና ሁከት ከበዛ በዚያ ማኅበረሰብ ውስጥ የክፉ ዐይን እምነት መኖሩ የግድ ነው ይላል (Douglas 1970, 118)።

[9] in many African contexts sorcery and witchcraft play a central role in the tensions between state and society።

Douglas (1970) በዚህ መንፈስ የሚጠረጠሩ ሰዎች ከተወሰኑ ዘሮችና መልክአምድራዊ አሰፋፈሮች ጋር እንደሚያያዝ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች የሚጠረጠሩት አካባቢያቸውን ትተው ወደሌሎች የመኖሪያ ክልሎች በተለያዩ ምክንያቶች ለመስፈር ሲሞክሩ ነው፡፡ ፈላሾቹ፤ የደም ትስስር ያላቸው ሰዎች ወደሚኖሩበት ክልል የሚደረግ ጉዞ ከሆነና ያ መስፈሪያ ቦታ ለም ከሆነ፣ መጤዎቹ ጥቅም ፈልገው የመጡ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ባላንጋራ ተደርገው ይቆጠራሉ ይላሉ፡፡ በመሆኑም፣ እነዚህን ሰዎች በዚህ ስም የሚያስከስሳቸው እንግድነታቸው ነው፡፡ የአካባቢው ሰው እንግዳን የሚያገለው ደግሞ በራስ ወገን ብቻ አስከብሮ መጤው እንዳይተክል ለመከልከል ነው፡፡
በመሆኑም፣ መጤውን ክፉ ነባሩን ደግሞ ምርጥ አድርገው በማስጠናት እሳታቸውን ያጠነክሩበታል፡፡ የሚፈለጉ ባህርያት እንዲበረታቱ፣ የማይፈለጉት ደግሞ እንዲነወሩ ለማድረግ የተፈጠረ ዘዴ መሆኑ ነው (Douglas, 1970, xvii) ፡፡ ስለዚህ፣ የክፉ ዐይን የህብረተሰቡን ጥቅምና ክብር ማጠናከሪያና አንድነቱን መጠበቂያ መሳሪያ ይሆናል፡፡

Krige (1947,17) ክፉ ዐይን ጭንቀትና ጉዳት ባለበት አውድ ውስጥ ይበዛል ይላሉ፡፡ በሰሜን ምስራቅ ዛምቢያና ማላዊ አካባቢ የCewa ቋንቋ ተናጋሪ በሆኑ ህብረተሰቦች ላይ ያካሄዱት የክፉ ዐይን እምነት ጥናት የሚያሳየው፣ የክፉ ዐይን ክስ የሚመጣው ማህበራዊ ዝምድና ሲሻክርና ግጭቶችና አለመተማመኖች ሲበዙ ነው (Marwick, 1965, 122)፡፡ የማይተዋወቁ ሰዎችን እንዲጣሉ የሚያደርግ የጋራ የሆነ ጉዳይ ስለማይኖር ሰዎች እርስ በርስ ሊካሰሱ አይችሉም፡፡ የቅርብ ግንኙነትና የጋራ ጉዳይ ግን ለግጭት መንስኤ ይሆናል፡፡ የሻከረ ግንኙነት፣ በመቀራረብ የሚመጣው ግላዊ ፍላጎት፣ በጋራ በሚያገ ንብረት ላይ የተወሰኑ ሰዎች ፍትሃዊ ያልሆነ ድርሻ መያዝ በክፉ ዐይን ያካስሳል (Gluckman,1965, 222)፡፡ በZulu ከአንድ አባዊ ቡድን የመጡና በተመሳሳይ ማዕረግ የተቀመጡ ዘመዳሞች በክፉ ዐይን አይተማመሙም፡፡ ወንድም ወንድሙን በክፉ ዐይን አያማውም፡፡

ግን በባዕዶቹ ማለትም በሚስቶች፣ በአማቾች፣ በዋርሳዎችና በምራቶች መካከል የሚነሳው ግጭት ስሙ ክፉ ዐይን ነው፡፡ በሰሜን Zulu የሚገኙት Swaziዎችና

Tsongaዎች በተመሳሳይ የክፉ ዐይንን መንፈስ የሚወርሱት ሚስቶች ናቸው ብለው ስለሚያምኑ፣ ከልጆቻቸው መካከል ወንዶችን ነጻ፣ ሴቶችን ደግሞ የእናቶቻቸው ወራሾች ያደርጓቸዋል (Gluckman, 1965, 222)። ይህ ክስ ከሴቶች ጋር እንዲያያዝ ያደረገው ወንዶች የሚቀናኑት በሴቶችና በመሬት በመሆኑ ነው (Gluckman ,1965, 222)።

በመሆኑም፣ Gluckman የZuluን ጎሳ "አባዊ ማህበራዊ አደረጃጀት" ለግጭት ምክንያት ያደርጉታል። አንድ ወንዱ ብዙ ሚስቶችን እንዲያገባ ማህበራዊ ልማዱ ይፈቅድለታል። ሁሉም ሚስቶች የሚኖሩት በአንድ ቤት ሆኖ፣ እንደአገባባቸው አንዷ በሌላኛዋ ላይ አዛዥ ሆኖ ትሾማለች። ይህ ስልጣን በንብረትና በልጆቻቸው የመውረስ መብት ላይ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው። ስለዚህ፣ ሚስቶች እርስ በርስ በክፉ ዐይን ሲካሰሱ የሚያጋጫቸው በሚጋሩት ባል ብቻ ሳይሆን እናጠዋለን ብለው በሚፈሩት በልጆቻቸው የውርስ መብት ላይ ጭምር ነው (Gluckman, 1965, 223)

በማህበራዊ ውጥረቶችና በክፉ ዐይን መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን ማወቅ ይቻላል (Marwic, 1952, 122) ። ለግጭት መነሻው መቀራረብና አብሮ መኖር ነው። ተራርቀው የሚኖሩ ሰዎች አንዱ በሌላው ላይ ጥላቻንና በደልን ለማድረስ የሚያስችል ምክንያት ስለማይኖረው በጎ ያልሆነ ነገር እንዲያስብ ምክንያት አይኖርም። በደሎችና ቅሬታዎች በሚተዋወቁ ሰዎች መካከል ስለሚበዙ ክፉ ዐይን ማህበራዊ ግንኙነት ለመላላቱ፣ ለመሻከሩና ውጥረትና ጭንቀት ለመንሰራፋቱ አሳይ ምልክት ይሆናል።

ከላይ በተጠቀሱት ጥናቶች ውስጥ የክፉ ዐይን ሚና ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ናቸው። ክፉ ዐይንም ለአፈንጋጮች የተሰጠ ስም ነው። የእምነቱ ሚና ህብረተሰባዊ አንድነትን ለማደርጀትና በማህበራዊ ደንቡ አባላቱ እንዲገዙ መግሪያና መመለሻ ዘዴ ሆኖ ነው። ክፉ ዐይን ክስ በዛ ማለት ማህበራዊ ቀውሶች መጨመራቸውን አሳይ ነው። ክሱ ሲቀንስ ማህበራዊ ጤና ለመኖሩ ምልክት ነው። ማህበራዊ ቀውስ ያለው በሁሉም የዓለም ክልል ሆኖ ሳለ፣ ለምን ክፉ ዐይን በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ እምነት ሆነ? የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይሆናል። በተለያዩ የመስክ ተሞክሮች እንደታየው እንግዳ ሰዎችን በክፉ ዐይን

የመክሰስ ልማድ በአብዛኛው አካባቢ ያለ ነው። መቀራረብና መራራቅ፣ መተዋወቅና አለመተዋወቅ ተጽእኖ ቢኖራቸውም ዋና የክስተቱ መገለጫ ጠባይ ሆነው ግን ይታሰባሉ ለማለት ያስቸግራል።

በእርግጥ በዚህ ጥናት አካባቢ "ቡዳ በወዳጁ ይቀድማል" በሚል ይገለጻል። በሌላ በኩል፣ እንግዳ ሰውን የመፍራት ልማድም ይታያል። የማያውቁት ሰው ወደ ቤታቸው ሲመጣ ቀድመው የበሰለ እህል ያቀምሱታል። ልጆችን፣ ከብቶችን ወደ ውስጥ ያስገባሉ። ከእንግዶች መካከል በተለየ መርጠው የሚጠረጥሯቸው አሉ። ጠብና አለመስማማት ብቻ ቡዳን ይወልዳል ብሎ ለማጠቃለል መሞከር ግን የሚቻል አይመስልም።

ይህ ክስተት በሰዎች ማህበራዊ ህይወት ላይ ብቻ ሳይሆን በእንስሳት፣ በተክሎችና ግዑዝ በሆነ ፍጥረቶች ላይ ሳይቀር እንደሚከሰት ይታመናል። ከእህል ዘሮች፣ ከተክሎችና ከዕጸዋት ወገን ቡዳ የሚባሉ አሉ። ከእንስሳትና ከአዕዋፋት እንዲሁ በመጥፎ የሚመለኩ ብዙ ናቸው። ይህ ከማህበራዊ ህይወት ጋር ምን ግንኙነት አለው? ብለን ብንጠይቅ መልስ የሚሰጥ አይመስለኝም። ክፉ ዐይን ከብርሃን፣ ከጨለማ፣ ከህይወትና ከሞት ጋር ተያይዞ ስሙ ይነሳል። ከአይነቱ አተላውን፣ ከሚጠቅመው ወዳቂውን ይመርጣል ይሉታል። ከዘመን በክረምት ይበረታል እያሉ ይናገራሉ። አዝመራ በሚያፈራበት ጊዜም መከላከያዎች ብዙ ናቸው። በተክሎች ህይወት አመድ አጋላጭ ነው። ከጠላም አተላ ይፈራል። በእንስሳት ህይወት ግልገሎች፣ አጥቢዎች ላይ ያይላል። በእነዚህ መካከል ያለው የጋራ ነገር ምንድን ነው ብሎ ማሰብ ይገባል።

አብዛኞች ጥናቶች ትኩረታቸው በሰው ልጅ ህይወት በመሆኑ ጥናቱን የማህበራዊ አደረጃጀት ችግር አድርገው እንዲያዩ እንዳስገደዳቸው ለመገመት አይከብድም። ከሰው ልጅ የህይወት ዘመን ሽግግር መካከል ይሽ ክፉ መንፈስ ጥቃት ያደርሳል ተብሎ የሚታመነውን ስናይ በተክሎች፣ በእንስሳትና በወቅቶች ላይ ካለው ጋር የተመሳሰለ ነው። በመሆኑም፣ ከማህበራዊ አደረጃጀት ከፍ ባለ ሊመረመር እንደሚገባ መረጃዎቹ ጠቋሚ ናቸው።

2.2.3.መዋቅራውያን

ተግባራውያን-መዋቅራውያንና መዋቅራውያን በነገሮችና በአካሎች መካከል ያለውን ዝምድና ስለሚፈልጉ የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖርም፣ መሠረታዊ ልዩነት እንዳላቸው ይነገራል። ተግባራውያን መዋቅራውያን ከማህበራዊ ዝምድና ውስጥ ሥርዓትን ለማውጣት ሲሞክሩ፣ መዋቅራውያን ግን የሃሳብ ውቅር (Pattern of ideas) ለማግኘት የሚታትሩ ናቸው (Barnard, 2004, 120)። የመዋቅራውያን መስራች እንደሆኑ የሚነገርላቸው Levi-Strauss ባህል የአእምሮ ውጤት ነው a product of the mind ይላሉ (McGee and Warms 2008, 324)። የዚህ ትውር ተከታዮች፣ የሰው ልጅ አንጎል በስነህይወት ተመሳሳይ ስለሆነ፣ በባህል ተመሳሳይ እንድንሆን የሚያደርግ በታህታይ ቅርጽ የተቀመጠ መዋቅር አለ ብለው ያስባሉ። በመሆኑም፣ በሰው ልጅ ዕውቀት ውስጥ ያለውን መሠረታዊ መዋቅር፣ የሃሳብ ቅጥአምባር ለይቶ በማውጣት ወቅታዊና ታሪካዊ የባህል ለውጦችን በመመርመር ሃሳቦች እየሰፉ የሄዱትን መንገድ ማወቅ ይገባል የሚል አቋም ያራምዳሉ(McGee and Warms, 2008, 324)።

በመዋቅራዊያን አተያይ፣ አንድ ጽንሰ ሐሳብ ከተሸከመው ሃሳብ ይልቅ በሃሳቦች መካከል ባለው ግንኙነት (pattern) ላይ ትኩረት ያደርጋል (Barnard, 2004, 120)። በዚህ የትንታኔ ማዕቀፍ መሰረት ትርጉም የሚገኘው ነገሮች እርስ በርስ ካላቸው ግንኙነት እንጅ በተናጥል ከሚይዙት የግል ፍች አይደለም። ሃተታ ተፈጥሮን፣ ተረቶችንና ሃይማኖትን በማጥናትና ከውስጣቸው ያለውን መንታ ተጻርሮ (Binary opposition) በመለየት፣ የሰውን ልጅ አስተሳሰብ መሰረቶችን መገንዘብ ይቻላል የሚል እምነት አላቸው (McGee and Warms 2008, 326)።

ሃሳቦቹ በብዛት ተደራጅተውና ተሰልፈው ቅርጽና መልክ በመያዝ ወደ ዕውቀትና ክህሎት መጠራቀሚያ ቋት ውስጥ ገብተው የሚደረደሩበትና የሚከማቹበት ሲመዘዙ እየተሳሰሩ የሚወጡበት መንገድ አለ። ይህ አእምሯዊ የሃሳብ ውቅር በህሊና ውስጥ የሚቀመጠው በተዘበራረቀና በተበጣጠሰ መልኩ ሳይሆን፣ በተደራጀና በተነባበ

አኳኋን ነው። ተመሳሳይ ሃሳቦች በወል የሚደራጁበት፣ ተቃራኒዎቻቸውም በትይዩ የሚቆሙበት፣ የአንዱ መጠራት ለሌላው መንቃትን፣ የአንዱ ከፍታ የሌላውን ዝቅታ የሚያስከትልበት የማደራጃና የማቀናጃ ስርዓት መኖሩን ያስረዳሉ።

ይህንን መንገድ በመከተል በክፉ ዐይን ላይ ጥናት ያካሄዱት Dundes ሲሆኑ ለጥናታቸው ርዕስ፣ "Wet and Dry" የሚል ስም ሰጥተውታል። Dundes በዚህ ሞዴል የሴምን ሕዝቦች ርዕዮተ ዓለም ለመተንተን ይረዳል በሚል ያስተዋወቁት አንድ የመተንተኛ አንጻር አላቸው (Dundes,1971, 266) ። በዚህ ሞዴል ውስጥ ዋነኛው ጉዳይ በሴም ሕዝቦች አስተሳሰብ ውስጥ "የውስን ተፈጥሮ ሃብት" እሳቤ (limited Goods)አለ የሚለው አመለካከታቸው ለሞዴሉ መቀረጽ አስተዋጽኦ ሆኗል። Alen Dundes የክፉ ዐይን እምነት ባሉባቸው አካባቢዎች፣ የህይወት መሠረት ፈሳሽ ነገር ነው ይላሉ (Dundes, 1971, 266)። የወንድ የዘር ፈሳሽ፣ ወተት፣ ደም፣ ሐሞት፣ ምራቅ፣ እና ሌሎችም እርጥበት ያላቸው ነገሮች እስትንፋስ መሰረቷን የጣለችበት አላባዎች ናቸው በማለት ያስረዳሉ (Dundes, 1971, 266)።

ስለዚህ፣ የህይወት መሰረት ፈሳሽ የመሆኑን ያህል በሰውነት ውስጥ ፈሳሽን ማጣት ደግሞ ወደ ሞት ማምራት ነው የሚል አመለካከት እንዲጨበጥ አምክንዮአቸውን ያስቀምጣሉ (Dundes, 1971, 273) ። ስለዚህ፣ መርጠብና መድረቅ በተቃራኒ የቆሙ የህይወትና የሞት ጥንድ ምሳሌዎች ያደርጓቸዋል። በመሆኑም፣ በጥናቱ ውስጥ ፈሳሽን ለህልውና፣ ድርቀት ደግሞ ለሞት ወኪል ይሆናል (Dundes, 1971, 273) ። በእነዚህ አካባቢዎች በተገኙ ሚቶች (myths) ውስጥ፣ በሁለም ነገር አሰራር ላይ የልክና የምጣኔ አስተሳሰብ ገንኖ ይታያል ይላሉ። ሁለም ነገር ከተፈቀደላት ነገር በላይም ሆነ በታች አንሶ ወይም በዝቶ አልተገኘም።

በመሆኑም፤ እንደ ሃብት፣ ጤና፣ ፍቅር፣ ሰላም የመሳሰሉት ሁሉ ከተፈቀደላቸው መጠንና ልክ በላይ ጨምረውም ሆነ አንሰው አይገኙም። ወደዚህ ሃሳብ እንዲያመራ ለነገሮች ምክንያት የሆነው ነገር የሁለም ነገር ፍጥረት በውስን ቀናት መጠናቀቁ ነው። ከዚህ ቀን በሁዋላ የተፈጠረም ሆነ፣ በተፈጠረው ነገር ላይ የተደረገ ምንም አይነት መሸሻል የለም የሚለው ነው። በዚህ ምክንያት ፍጥረቶች ሁሉ ሳይለወጡና

ሳይሻሻሉ ውሱን በሆነ ሁኔታ በጥንቱ ቅርፃቸውና መልካቸው ህልውናቸው ተጠብቆ ይገኛሉ የሚል አስተሳሰብ እንዲያዝ አድርጓል ይላሉ።።

ማህበረሰቡ ይህንን ሃብት ያለውን ዕውቀትና ጥበብ ተጠቅሞ ከፍተኛውን ድርሻ ለመውሰድ ይሞክራል።። ይህንን የተፈጥሮ ፀጋ ሁሉም ሰው የመካፈል ዕድል ቢኖረውም፣ ክፍፍሉ ፍትሃዊ ባለመሆኑ አንዱ ላይ ሲበዛ ከሌላው ላይ ማነሱ አይቀርም።። መልካም የሆኑ ነገሮች ከተፈቀደላቸው መጠንና ልክ በላይ አልፈው አይገኙም ተብሎ ስለሚታሰብና በምንም መልኩ አዲስ ነገር ሊገኝ ይችላል ተብሎም ስለማይጠበቅ ብቸኛው ምርጫ የሚሆነው ያለውን፣ የነበረውንና የሚኖረውን ነገር መካፈል ነው።።

እነዚህ ፍጥረቶች የማይባዙ ወይም የማይከስሙ፣ ከተፈቀደላቸው መጠንና ልክ በላይ አልፈው ወይም ተርፈው ወይም አንሰውና ቀንሰው የማይሄዱና ውስን ተፈጥሮ ያላቸው ነገሮች ናቸው።። ይህንን ተፈጥሯቸውንና ባህሪያቸውን ማወቅና መገንዘብ የሚቻለው በሁለት መንገድ ነው።። አንድም ራስን ለመልካም ነገር በማስገዛት፤ አንድም መልካም ካልሆኑ ሃይሎች ጋር በመተባበር፤ ሌላም ኢ-ፍትሃዊ በሆነ አግባብ በማግኘት ነው።። ስለዚህ፣ ይላሉ Dundes ፣ ይህንን ውስን ተፈጥሮ ያለውን ነገር ሁሉም ሰው በእኩል ሊካፈለው ወይም ከነበረው መጠን በላይ አራብቶ ሊያባዛው ስለማይችል፣ የሚሆነው ያለውን ተካፍሎ መጠቀም ወይም ተሻምቶ መንጠቅ ነው።።

በዚህም፣ የአንዱ ህልውና በሌላው ሰው ህይወት፣ ያንዱ ማግኘት በሌላው ማጣት፣ የአንዱ መክበር በሌላው ሰው መደህየት ላይ እንዲመሰረት ያደርገዋል።። በመሆኑም፣ አንድ ሰው በአካሉ ውስጥ የበዛ ፈሳሽ አለው ማለት በሌላኛው ሰው አካል ውስጥ ያነሰ መጠን ያለው ፈሳሽ እንዲኖር የግድ ያደርገዋል።። በአንዱ ሰው ቤት የተትረፈረፈ ሃብት ካለ በሌላው ሰው ቤት ደግሞ በዚያው መጠን ያነሰ ሃብት መኖሩን ያስከትላል በማለት ይገልጹታል።። ይህ ሁኔታ ወደ ሌላኛው የአስተሳሰብ መስመር ውስጥ እንድንገባ ይመራናል ይላሉ።። ማለትም ስስትን፣ ስግብግብነትን፣ የራስ ያልሆነን መመኘትን ማሰብን ያመጣል።። የሌለው ያለውን ወደ መመቅኘት፣

ያለው ደግሞ የሌለው የመጠራጠርና የመፍራት ተጋሪው እና ባለጋራው[10] አድርጎ የማሰብ ሁኔታን ያመጣል።

ህይወት በባህርይዋ የፍትህ ሚዛኗን የምታስተካክለው በተቃራኒ ውጥረቶች ይሆናል (Dundes,1971, 266) ። አንድ ሰው ሃብታም ከሆነ የግድ ሌላ ደሃ መኖር አለበት፤ ጤነኛ ካለ የግድ በሽተኛን ይጠራል። ጤና የራቃቸውና ሃብት የሸሻቸው ሰዎች ለከበሩና ጤናማ ለሆኑ ሰዎች የሥጋት ምንጮች ይሆናሉ። ይህ እሳቤ ደግሞ ደህና ህይወት በሚመሩ ሰዎች ላይ መልካም የሆነ አመለካከት እንዳይኖር ያደርጋል። መልካም የሆነው ነገር ያላቸው ሰዎች ደግሞ በተራቸው ሌሎቹ ሰዎች ይመቀኙናል ብለው ስለሚያስቡ፣ እነሱም በተራቸው በእነዚያ ሰዎች ላይ መልካም ያልሆነ ስሜት ይይዛሉ።

Dundes በጥናታቸው ውስጥ ተጻርሮን የተመለከቱት እርስ በርስ እንደሚጠፋፉና እንደሚተካካ ነገር እንጅ ደረጃ ባለው አዳጊ ቅርጽ አይደለም። በተፈጥሮ ውስጥ ምጣኔ አለ ብለው ካሰቡ፣ ይህ ምጣኔ በሂደት ቢያንስ ቢያንስ ሶስት ጠባዮችን ሊያሳይ ይችላል ብሎ ማሰብ ይቻላል። አንደኛው በተመጠነው ልክ የሚኖር፣ ሌላኛው ከምጣኔው አንሶ የሚገኝ እና ከምጣኔው ተርፎ የሚገኝ ነው። ለምሳሌ፣ አንድ ነጋዴ ሊከስር፣ በዋናው ሊሆን ወይም ሊያተርፍ ይችላል። በመሆኑም በማጣት ውስጥ የሚቀረው ማግኘት ብቻ ሳይሆን በዋና መገኘት ጭምር ነው። ህይወት በራሷ የሞት ወኪል ብትሆንም ህይወት በራሷ ደረጃ ያላት ነገር ነች።

በዚህ ጥናት ውስጥ የውስንነት ጽንሰ ሐሳብ ይዞት የቆመው አምክንዮ፣ ማግኘት ማጣትን፣ መኖርን አለመኖርን ወዘተ... ፈጠረ የሚል ነው። እነዚህ መነባቶች ደግሞ በተከታይ ሰዎችን ባላንጋራ ያደርጋሉ የሚል እሳቤን እንዲያስከትል ያደረገ ነው። ይህ ደግሞ፣ የአንዱ መኖር በሌላው ዕጣ ፈንታ ላይ እንዲወሰን አድርጎ ውስንነትን በማጠፋፋት ለማስተካከል የሚሞክር አስተሳሰብ ነው። ስለዚህ፣ Dundes ቀድሞ የሚደለደለው በቂ እንዳልሆነና ክፍፍሉም በፍትሃዊ መልክ አለመድረሱን ያስረዳሉ። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት መሠረታዊ ነገር፣ ሁሉም ነገር በልክ

[10] ደስታ ተክለወልድ ባለጋራን ደመኛ ጠላት ምቀኛ ከሳሽ አሳዳጅ በሐሰት በተንኮል የሌላውን ጥቅም የሚጋራ፣ የሚካፈል በማለት ይበይኑታል።

ከተፈጠረ ሌላኛው ዘንድ የሚበዛበት ዕድል እንዴት ይገኛል የሚለው ነው። ውስን በሆነው ተፈጥሮ ውስጥ ወሰን አልባነት እንዴት ሊመጣ ይችላል? የሚለው ጥያቄ ነው።

እያንዳንዱ ፍጥረት ከተሰጠው ልክ በላይ አልፎ የሌላኛውን ድራሻ የሚይዝበትን አቅም ከየት ያገኛል? የሚለው ነው። ቢያገኝስ እንዴት ይችለዋል? የት ላይ ያስቀምጠዋል? የሚለው ነው። ስለዚህ፣ ሚዛንንና ምጣኔ መኖሩን ከDundes ተቀብለን በዚህ የተፈጥሮ ህግ ሲገዙ ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ መኖርን፣ ሲያልፉ ደግሞ መጣላቱን ከክፉ ዐይን ጋር ምን ያገናኘዋል የሚለውን በሌላ መነጽር መመርመር ይገባል እላለሁ።

2.3. ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ

በዚህ ክፍል በጥናቱ ውስጥ ገዥ የሆኑ ሃሳቦችና ምርምሩን የሚመሩ ጽንሰ ሐሳቦች የሚኖራቸው አገባቢዊ ፍቺ ይብራራበታል። በትንታኔ ወቅት የሚኖራቸው አውዳዊ አገባብና አቅጣጫ ይጠቆምበታል። በመሆኑም፣ በዚህ ጥናት ውስጥ የሚከተሉት ጽንሰ ሐሳብ የሚኖራቸው ፍቺ የሚከተለው ነው።

ነፍስ

በነፍስ ምንነትና አተረጓጎም ላይ የስነ-ሰብዕ፣ የስነ-ማህበረሰብ፣ የስነ-አእምሮ፣ የስነመለኮት አጥኝዎች የሚሰጡት ትንታኔ አንድ አይደለም። እያንዳንዱ ህብረተሰብ ስለነፍስ ያለው አመለካከት እንዲሁ ልዩ ልዩ ነው። ጽንሰ ሐሳቡን ጉዳያቸው አድርገው የመረመሩ አጥኝዎች ነፍስን ከደግ ተግባር፣ ከማህበራዊ ህይወት፣ ከጤና፣ ከዕውቀትና ከመንፈስ ጋር እያያያዙ ይገልጹታል። በማህበራዊና በባህል ዘርፎች በነፍስ ዙሪያ ያለው የምርምር ባህል ጠቅለል ብሎ ሲታይ ሦስት ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ይመስላል። አንደኛው ነፍስን እንደመንፈሳዊ ኃይል የሚመለከቱ፣ እንደ ዕውቀት የሚያስቡና ነፍስ ለሥጋ ህይወትን እንደምትሰጥ አካል አድርገው የሚረዱ ናቸው።

ነፍስ በዚህ ጥናት የተሰጠው ትርጉም፣ ምድራዊ ነገር የማይጫነው፤ ለመራብ፣ ለመጠማትና ለሌሎችም ስሜቶችና ሃሳቦች ተገዥ ያልሆነ፤ የማሰብ፣ የመመርመር፣

ከፍ ከፍ የማለት፤ ለመተባበር፣ ለመተጋገዝና ለመረዳዳት ዋጋ የሚሰጥ፣ በሚዛንና በምጣኔ መኖርን እሴት ለሚያደርግ አስተሳሰብ ወሳይ የሆነ የሰብአዊነት መገለጫ ባሕርይ ነው። ነፍስ ለሥጋ ህይወትን የምትሰጥና የህልውና መሠረት የሆነች አካል ነች። ሰውን ህያው ፍጡር የምታደርገው እሷ ነች ብለው ስለሚያምኑ፣ ነፍስ እስካለች ድረስ በህይወት ይኖራል ብለው ያምናሉ።

ነፍስ መንፈሳዊ አካል ሆና ሦስት ልዩ ልዩ ተግባሮች ታከናውናለች ተብሎ ይታሰባል። የመጀመሪያው የሰው ልጅ እንዲያስብ፣ እንዲመረምርና ልብ እንዲገዛ ማድረግ፣ ሁለተኛው የእስትንፋስ መሰረት የሆነችውና ህልውናን የምታረጋግጠው ህያዊት፣ ሶስተኛዋ ደግሞ የአንደበት ክፍል የሆነችው ነባቢት ነች። ነፍስ የምትዳሰስ ተፈጥሮ ያላት ሳትሆን ረቂቅ ባሕርይን የያዘችና ተጨባጭ ያልሆነች የህይወት ክፍል በመሆኗ ሞት የለባትም።

ሥጋ

ሥጋዊ ባሕርይ ደግሞ መራብ፣ መጠማት፣ መታመምና መሞት የሚስማማው፣ ግዙፍ ውስንና ተጨባጭ የሆነ አካላዊ ባሕርይ ነው። ወደ ምድራዊ ግብርና ኃጢያት ያዘነብላል። ሥጋ ካሸነፈ በሰውዬው የሥጋ መሻቱን የሚያደርግ የኃጢያት ባሪያ ይሆናል። ሥጋ በተመቸውና ፈቃዱንና መሻቱን ለመፈጸም ኃይል ባገኘ ጊዜ ነፍስ ትደክማለች። ስለዚህ፣ ሁለቱንም አጣጥሞ ለመጓዝ ታላቅ መንፈሳዊ ትግልን መታገል ያስፈልጋል።

ነፍስ ማደሪያዋ ከሆነው ከሥጋ ስትነጠል፣ ሥጋ ይፈርስና ይበሰብሳል። ስለዚህ፣ ሥጋ ያለነፍስ ህልውና ከሌለው በሥጋ ላይ ህይወትን የምትዘራው ነፍስ መሆኗ ነው። ከአምላክ ባህርይ የተከፈለችና በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ በመለኮት እስትንፋስ አማካይነት የምትገባ ነች። በወሊድ ጊዜ የምትሰጥ ሆና እያንዳንዱን ድርጊታችንንና እንቅስቃሴያችንን ሁሉ የምትመራ መንፈሳዊ የሆነች የንቁው ህሊናችን አካል ነች። በግለሰብ ደረጃ የአንድ ሰው ጠባይና የሰብዕና መገለጫ የሆነ ከፈጣሪ የሚገኝ ነገር ነው።

ንጽሕና እና ርክሰት

ርክሰትን ወይም ሃጢያትን ከማህበራዊ ልማዶች ከማፈንገጥና ለሥርዓት ካለመገዛት ጋር አዛምደው የሚገልጹት አለ። በአንድ ቦታ ከተለመደው ወጣ ያለ ነገር ስለተሰራ ብቻ ያረክሳል፣ ያሳድፋል፣ ያቆሽሻል አይባልም የሚሉ ወገኖች አሉ። ፍንገጣ መርከስን የሚያመጣው ለማህበራዊ ቀውስ ምክንያት ከሆነ ነው ብለው የሚያስቡ ህብረተሰቦችም አሉ። Douglas (1966 161)ርክሰት የሰው ልጅ ነገሮችን ለማደራጀት የተጠቀመበት ሥርዓት መፍጠሪያ መንገዱ ነው በማለት ይገልፁታል። ቅርጽ ያልያዘው ነገር ወደ ጠበቀ ደንብ በሚገባበት ጊዜ የጸናው ስርዓት እንዳይፈርስና እሳቤውን ይዞ እንዲቀጥል ማድረግ ሲፈለግ ቃሉ የማደረጃና ሥርዓት የማስገዣ ስልት ሆኖ ይመጣል ይላሉ።

ስለዚህ፣ እያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባል ይህንን ደንብ ማክበር ሲጀምር፣ ልዩነቱን እየለየ ምደባውንም እያጸናው ይመጣል (Douglas, 161)። ርክሰት የተፈጠረው ሥርዓት አልባውን (disorder) ሕገኛ እንዲሁም ቅርጽ የለሽን (formless) ባለቅርጽ አድርጎ ለማስተካከል ነው ብለው ያስረዳሉ። በመጀመሪያ ቅርጽ የሌለው ነገር ስለነበረ የመለየት ሁነት አልነበረም ይላሉ። በመለየቱ ሂደት ነገሮች መልክ መልክ መያዝ ሲጀምሩ ንጽሕና የደንብና የሥርዓት ማምጫ ስበብ ሆኖ ይመጣል(Douglas 1966, 162)። ስለዚህ፣ አንድ ነገር ረክስ የምንለው ይኸ ቅርጽ የያዘው ነገር ተመልሶ ቅርጽ አልባ ሲሆን ነው ።

በዚህ ጥናት ውስጥ የንጽሕና አገባባዊ ፍቺ ከሕግ ጋር ተያይዞ የሚተረጎም ሆኖ፣ መጠበቅን የሚነግርና የሰው ልጅ ተፈጥሮውን በገደብና በሚዛን ለመምራት ይችል ዘንድ በቀዳሚነት ያገኘውን ባሕርይ አክብሮ መያዙን የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው። የሰው ልጅ የባሕርይ መሠረት የሆነውን ተፈጥሮውን በገደብና በሚዛን መምራት ይችል ዘንድ በቀዳሚነት ያገኘውን ባህርይ ጠበቆና አክብሮ ሲይዝ ንጹሕ ሆነ፣ ነፍስን ከሚያሳድፍና ሃጢያት ከሚሆን ነገር በመራቅ፣ በሥጋ ባሕርይቱን በመጠንና በልክ በማስገዛት የነፍስ የሆኑትን ሥራዎች ከሥጋ ባህርያት ጋር አስማምቶ ማስኬድ ነው።

ርክሰት ደግሞ፣ ባሕርያዊ ነገርን እየተው ወደ ግላዊ ስሜትና ራስወዳድነት ከሚመሩ ልዩ ልዩ ሥጋዊ ጠባዮች ጋር መተዋወቅ፤ ከተፈጥሮ ውጭ የሆነ ክልክ ያለፈ

አድራጎት ማሳየት፣ ከገደብ አልፎ ልቅ መሆን፣ ስሜትን በማዳመጥ ተፈጥሯዊ ሚዛንና ልክን ማጓደል ማለት ነው። ከተፈጥሯዊ ባሕርይ ውጪ ትርፍ ነገርን መያዝ ነው።

ክፉ ዐይን

የስነ ሰብዕና የማህበረ ታሪክ ተመራማሪዎች ክፉ ዐይንን በተለያየ መንገድ ገልጸውት ይገኛል። አብዛኞቹ የኢትኖግራፊ ጥናቶች ክፉ ዐይንን እንግዳ ለሆኑ ክፉ አጋጣሚዎች መተርጎሚያ ሆኖ ሲያገለግል ይታያል። ለማህበራዊ ውቅሮች መላላት፣ አለመጠናከር፣ ለውስጣዊ ቀውስና መታመስ ሰበብ አድርጎ የመሳል ሁኔታ አለ።

በዚህ ጥናት ፣ የክፉ ዐይን አገባባዊ ትርጉም፣ ሰው በተፈጥሮው መኖር ሲያቆምና በቀዳሚነት ከያዘው ነገር እየራቀ ሲሄድ ሌላ ጠባይ በመላመዱ ምክንያት በነፍስና በሥጋ መካከል ያለውን መጣላት ተጠቅሞ በሥጋ ላይ የሚከብርና አዛኝ የሚሆን ክፉ ኃይል ነው። የሰው ልጅ ለሥጋ መድከሙን ለነፍሱ ዋጋና ክብር አለመስጠቱን ተከትሎ ከሰብዕናው የሚያስወጣውን ሥራ የሚያሰራው ተቆጣጣሪና ወራሽ አካል ነው።

2.4. የመተንተኛ ሞዴል

በኢትኖግራፊ ጥናቶች ውስጥ የቀረቡትን መረጃዎች በማየት፣ ሌሎች ጥናቶች በተከተሏቸው የመተንተኛ አንጻሮች ውስጥ ያለውን ድክመትና ጥንካሬ በማውጣት ይህንን ጥናት ለመተንተን "ተፈጥሯዊ" የተባለ ሞዴል ተመርጧል። ለዚህ ሞዴል ስም የሰጠው አጥኝው ቢሆንም፣ ሞዴሉ ግን በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን አስተምህሮት በሰፊው የሚታወቅ ነው። ይህ ሞዴል "በመዋቅር ቴዎሪ" ውስጥ የሚካተት ሆኖ፣ በተለይ የክርስትና ባህል ባላቸው እንደ ጎዛምን ባሉ አካባቢዎች አስተሳሰብን፣ ርዕዮተዓለምንና ዕውቀትን ለመተርጎም በእጅጉ የሚረባ ሞዴል ነው ብሎ አጥኝው ያምናል።

	የሥጋ ባሕርያት			
	ነፋስ	እሳት	ውሃ	መሬት
	ብሩህነት	ብሩህነት	ጥቁርነት	ጥቁርነት
	ርጥብነት	ሞቃትነት	ሞቃትነት	ርጥብነት
ግብሮች	ቀዝቃዛነት	ደረቅነት	ቀዝቃዛነት	ደረቅነት

1. ይህ ሰንጠረዥ የሥጋን ባህርያትና ግብሮች የሚያሳይ ሆኖ፣

በዚህ ሞዴል መሠረት፣ ከመነሻው ህይወት ባላቸው በእያንዳንዱ ፍጡሮች ውስጥ በቀዳሚነት እካልን የሚያስገኙ ወይም የሚገነቡ ሥሮች ወይም መሠረቶች ተብለው አራት ባሕርዮች ተቀምጠዋል። እነዚህ የባሕርይ ስሮች ነፋስ፣ እሳት፣ ውሃና መሬት ይባላሉ። እነዚህ አራቱ የፍጥረት ሥሮች በሁሉም ነገር ውስጥ በመጠንና በሚዛን ከፈጣሪ ተሰጥተው ልካቸው ላይ ሲደርሱ የረጉ ናቸው ተብለው ይታመናሉ። በእነዚህ ላይ ሦስቱ የነፍስ ባሕርዮች ሲያድሩ ሰው የሚባል ፍጡር ይገኛል። የሥጋ ባሕርዮች ለሰዎች የተበረከቱ የፀጋ ስጦታዎች ሆነው፣ ባግባቡ ስንኖርባቸው ሰውነትን የሚያከብሩ፣ ባግባቡ ሳንኖር ስንቀር ደግሞ የሚያረክሱ ሆነው የተቀመጡ ናቸው።

እነዚህ የተፈጥሮ ሥሮች ለሁሉም ነገር ጀማሪና አዲስ እንደመሆናቸው ፋታሂነት፣ ሃይለኛነት፣ ንጹሕናና ታዛዥነት ይገኝባቸዋል ተብሎ ይታመናል። ከቀዳሚነት ባህርይ የሚያስወጣው ነገር፣ የተፈጥሮ ሥር ስፍርን አለመጠበቅ ነው። በመሆኑም፣ ከቀዳሚ ባሕርይ ይበልጥ እየራቁ መምጣት በሥጋና በነፍስ መካከል ያለውን ትስስር የሚያላላና ወደ ሞት የሚያደርስ መንገድ ይሆናል።

አራት ባሕርዮች በሰው ልጅ የዕድሜ ዘመን ውስጥ የሚሰለጥኑባቸው ወቅቶች አሏቸው። አንዱ ሲጨምር በሌላው ግብር ስለሚገደብ እንዳይጣሉና እንዳይጋጩ ይሆናል። እነዚህ አራቱ ባህርዮች እርስ በርስ ይጣላሉ፤ ይሸናነፋሉ። በዋናነት በባህርያችን ውስጥ የሚሰጡ ነገሮች እንዳሉ ነው እንጅ አራቱም ባህርያት ቦታቸውን የለቀቁበት ጊዜ የለም። አለዚያ ሰው፣ ሰው ከመሆን ውጭ ይሆናል። ነፋስነትን ቢያጣ፣ ወይም ውሃነትን፣ ወይም መሬትንትን አንዱን ቢያጣ ሰው አይሆንም። እንከን ይገጥመዋል ማለት ነው። ዋናው ነገር በጎላበት ዘመን የጎላውን

ማሳየት ነው። የባሕርይ መጠኑ ገደቡን አልፎ እንዳይሄድ ሲባል አራቱ ባህርያት የሚስማሙባቸውና የሚመጣጠኑባቸው ሦስት ሦስት ግብር እንዲኖራቸው ሆነው ተፈጥረዋል።

እነዚህ አራቱም ነገሮች በፍጥረት ጊዜ ቀድመው በተገኙ ነገሮች ቅርጽ፣ ጣዕም፣ መጠን፣ አይነት ላይ የሚገለጹ ሆነው፣ ከቀዳሚው ነገር ቀጥሎ የሚገኘው ወይም የሚመጣው ክፍል ከእነሱ ባህርይ ሙሉውን የሚቀበል ይሆናል። ከቀዳሚው ቀጥሎ የሚመጣው ደግሞ ያነሰውን ድርሻ እየወሰደ ከዚያም እየሸሸ በሄዱ ቁጥር እየደከመ የሚሄድ ነው። በቀዳሚው ነገር ውስጥ ሁሉም ነገር በአዲስ የተሞላ ሲሆን፣ ከቀዳሚው በራቁ ቁጥር ይህ የህይወት ውህደት እያጠጠ፣ እየደከመ፣ እየቀነሰ ሄዶ በመጨረሻ ተፈጥሯዊ ባህይውን የሚያጣ ይሆናል። ሰው በነፍስነት ባህርይው ለሃጢያት ተጠቂ አይደለም ተብሎ ይታሰባል። ይህ ዘመን በፍጥረት ህይወት ውስጥ በመጀመሪያው የለጋነት፣ የጀማሪነት፣ የቡቃያነት ዘመን የሚገለጽ ነው።

በመሆኑም፣ እያንዳንዱ አካል ከቀዳሚነቱ የሚያርቅ ሥራ ባከናወነ ቁጥር የመከላከል አቅሙ እየደከመና ለጥቃት የመጋለጥ ሁኔታው እየጨመረ ይመጣል ። ወደቀዳሚነት በቀረበ ቁጥር የመጋለጥ መጠኑ ይቀንሳል። በቀዳሚነት ውስጥ ያለው ጥንካሬ ተጠብቆ እንዲቀጥል ዘሩ ከያዘው ቀዳሚ ተፈጥሮ የሚያስለቅቀውን ነገር ከማከናወን መጠበቅ ይኖርበታል። በመሆኑም፣ ከባህርይው የወጣ ነገር አለማድረግ፣ ከመከለስ፣ ከመዳቀል፣ ከመቀላቀል፣ ከመበረዝ፣ ከመነካካትና ከመሳሰሉ ተጋቢ ጠባዮች መራቅ ዋነኛው ጸንቶ መገኛው መንገድ ይሆናል።

በመሆኑም፣ በዚህና በመሳሰለው ሁሉ የሚመጣውን መርከስ ማንጻት የሚቻለው ወደ ቀደመው መልክና ባህርይ በመመለስ ነው። ቀዳሚ ተፈጥራዊ መንገድ ነው። የተፈጥሮ ስርዓት የሚገዛበትን ሕግ ወይም ምስጢር ጥበባዊ በሆነ መንገድ ተረድቶ ለራስ ፍላጎትና ስሜት በሚጠቅም መልክ ለማዋል የሚደረግ ጥረት ነው። ነገሮች ሲፈጠሩ የተገኙበት መንገድ፣ እነዚያን ፍጥረቶች አስገኝው አካል በሥርዓት በመመደብና በማደራጀት ነገሮችን ያመጣበትን ስልት አውቆ በዚያው መንገድ ለውጤት የሚበቀቡበትንና ለፈለግነው ዓላማ የሚፈይዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

3. የምርምር ስነዘዴና የመስክ ተሞክሮ

በዚህ ምዕራፍ የምርምሩ አካሂድ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ የንሞና ስልት፣ አተናተን፣ የምርምር ቱምሪ ምርጫና የመስክ ልምድ ይብራራበታል።

3.1. የመስክ ልምድ ሁኔታ

ይህ ጥናት በደብረማርቆስ ከተማና በዙሪያው በሚገኙ የጎዛምን ወረዳዎች ላይ የተካሂደ ነው። ጥናቱን ለማካሂድ አራት ዙር የመስክ ላይ ምልልስና የስምንት ወር ቆይታ ተደርጓል። የመጀመሪያው ጉዞ ከሚያዚያ10፣ 2003 ዓ/ም እስከ ሰኔ 15፣ 2003 ዓ/ም ባለው ጊዜ፤ ሁለተኛው ዙር ከታህሳስ 20፣ 2004 ዓ/ም እስከ የካቲት 28 ፣ 2004 ዓ/ም፤ ሦስተኛው ዙር ከሐምሌ 5፣ 2005 ዓ/ም እስከ ጷጉሜ 5፣ 2005 ዓ/ም እንዲሁም አራተኛው ዙር፣ ከጥቅምት 28፣ 2006 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 26፣ 2006 ዓ/ም ባለው ጊዜ የተከናወነ ነው።

አስፈላጊውን ቁሳቁስ አሟልቼ፣ የትብብር ደብዳቤ ከትምህርት ክፍሉ አጽፌ ከጨረስኩ በኋላ ሚያዚያ 10 ቀን 2002 ዓ/ም ከቀኑ በስምንት ሰዓት ላይ የ300 ኪ/ሜ ጉዞ በአውቶብስ አድርጌ ደብረ ማርቆስ ከተማ ገባሁ። ለከተማው እንግዳ ባልሆንም አንዳንድ የምፈልጋቸው የመንግስት ተቋማት የት እንዳሉ ዕውቅት ስላልነበረኝ፣ ከጓደኞቼና ከቤተሰቦቼ ጋር በመሆን ለሁለት ቀን ያህል አካባቢውን ሳጠና ሰነበትኩ። ከሚያዚያ10፣ 2003 ዓ/ም እስከ ሰኔ 15፣ 2003 ዓ/ም ባለው ጊዜ፣ በአካባቢው የስነ ሕዝብ፣ የመልክዐምድር፣ የቆዳ ስፋት፣ የአሰፋፈርና የኃይማኖት ታሪክና የአየር ጠባይ መረጃ የማሰባሰብ ስራ አከናወንኩ። በሁለት ወረዳዎች ማለትም በደብረማርቆስ ከተማና በጎዛምን ወረዳ ከሚገኙ የመስተዳድር ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና የባህል ኤክስፐርቶች ጋር ተዋወቅኩ።

ለደብረ ማርቆስ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ ለማስታወቂያ ጽ/ቤት፣ ለፀጥታ ክፍል፣ ለዞንና ለወረዳ የገንዘብ መምሪያ ጽ/ቤቶች፣ ለምሄድባቸው የቀበሌ ጽ/ቤቶች፣ የፍትህ ተቋማት፣ የወረዳ ትምህርት፣ ማዘጋጃ ቤቶች፣ የግብርና ፣ የገንዘብ ጽ/ቤቶች የትብብር ደብዳቤ አጽፌ ያዝኩ። ፈቃድ ካገኘሁ በኋላ በመረጥኳቸው የወረዳው ቀበሌዎች ያለምንም ችግር ለመንቀሳቀስ ቻልኩ። ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችን

በመመልመል የቀበሌ መረጣ፣ የመረጃ አቀባይ ግለሰቦች ምልመላ በማካሄድ የቅኝት ስራ ለማከናወን ሞክርኩ። ከእነዚህ ሰዎች ጋር የት መሄድና ከማን ጋር በምን ጉዳይ መነጋገር እንዳለብኝ ምክክር አደርግኩ።

እነዚህ የትብብር ደብዳቤዎች፣ በጓደኞቼና በቅርብ ቤተሰቦቼ አማካይነት ከተዋወቋቸው ሰዎች ጋር ተጨምረው ያለምንም ችግርና መጉላላት የፈለጉትን መረጃ በጊዜው እንዳገኝ አስችለውኛል። በተጨማሪም፣ ከአንዳንድ የባህል አጥኝዎች፣ የአካባቢው ሽማግሌች፣ የቋንቋና የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን፣ የማስታወቂያ ባለሙያዎች፣ የኮሌጅና የዩኒቨርስቲ መምህራን ጋር እንድገናኝና የምፈልገውን መረጃ እንድጠቀም አግዞኛል። በእነዚህ ሰዎች ጥቆማ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ተገናኝቼ በጥናት ክልሉ አካባቢያዊ መረጃ ጠቃሚ ሰነዶችን ለማግኘት ችያለሁ። ይህ የመጀመሪያ ደረጃ የአሰሳ ቅኝቴ በአጠቃላይ ከሁለቱም ወረዳዎች 5 ሰዎችን ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቼና ሁለት የመስክ ላይ ረዳቶች አድርጌ እንድመርጥ አግዞኛል። በዚህ የመጀመሪያ የመስክ ሥራ ላይ የሚከተሉትን የምርምር ተግባሮች ለማከናወን ችያለሁ።

1. በአካባቢው ወደሚገኙ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች፣ አብያተ መጽሐፍት፣ አብያተ መዛግብት በመሄድ ስለጥናት ቦታው መልክዐምድር፣ ስነህዝብ፣ ታሪክ፣ አሰፋፈርና የአየር ንብረት የሚገልጹ መረጃዎችን ሰበሰብኩ።
2. በአምልኮት ቦታዎች በተለይም በንግስ ቀናት በመገኘት የሰዎችን አለባበስ፣ የአነጋገር ስርዓት፣ የሰላምታ አለዋወጥ፣ የአቀማመጥ ሁኔታ ቃኝቻለሁ። በማህበረሰቡ አባላት መካከል በጸታ፣ በዕድሜና በማህበራዊ ደረጃ አማካይነት ከአለባበስ፣ ከአቀማመጥ፣ ከአበላል፣ ከአጠጣጥ ጋር በተያያዘ ያሉ ልዩነቶችን ለመታዘብ ችያለሁ።
3. በጋብቻ፣ በአስተጫጨት፣ በዋዜማ ሥርዓቶች፣ በሠርግ ዕለት፣ በጫጉላ፣ በገለጣ ክንውኖች ላይ ስለሚፈጸሙ ልምዶች ቃለመጠይቅ አካሄድኩ።

4. በእርሻ ስራ ተግባራት፣ በአስተራረስ፣ በአዘራር፣ በዘር ምርጫ፣ በበሬ አሰለጣጠን፣ በአረም፣ በአጨዳ፣ በአውድማ ስርዓት ስለሚከናወኑ ተግባራት በቃለመጠይቅ መረጃ ሰበሰብኩ።

5. በዕፅ ምንነት፣ አገልግሎት፣ በቆረጣ ሥርዓት፣ በግቢር፣ በንጽሕና አጠባበቅ፣ በአቆራረጥ ስህተት፣ ስለ ዕፆች አሰዋወር፣ ግቢሩን አስተካክለህ ባለመቁረጥህ ምክንያት ስለሚደርሱ አደጋዎች በተመለከተ የዕጽ እግር ከሚያውቁ ባለሙያዎች ጋር ቃለመጠይቅ አካሄድኩ።

ሁለተኛው ዙር የመስክ ሥራ የተካሄደው ከታህሳስ 20፣ 2004 ዓ/ም እስከ የካቲት 28፣ 2004 ዓ/ም ባለው ጊዜ ነው። በዚህ የመስክ ቆይታ በመጀመሪያው ዙር የታዘብኳቸውን ነገሮች በማስፋት፣ ተጨማሪ መጥራት፣ መብራራት የሚገባቸውን በመለየት፣ በአዲስ መቃኘት የሚገባቸውን በመዳሰስ በድጋሚ ለመሰብሰብ ችያለሁ። በመሆኑም፣ የሚከተሉት መረጃዎች በሁለተኛው ዙር ተሰብስበዋል።

1. ከወሊድ፣ ከሠርግ፣ ከእርግዝና እና ከጋብቻ ጋር ተያይዘው ስለሚፈጸሙ ልማዶች ከተወሰኑ ወላዶች፣ የልምድ አዋላጆች፣ አጋቢ ሽማግሌዎች፣ ጋር ጥልቅ ቃለ መጠይቅ አካሄድኩ።
2. በዘር አመራረጥ፣ በአዘራር አያያዝ፣ በአስተራረስ፣ በአረም ምንነት፣ በአጨዳና በአውድማና ላይ ስለሚከናወኑ ስራዎችና ልማዶች በቦታው ላይ በመገኘት ቃለመጠየቅና ምልከታ አድርጌያለሁ።
3. በጨለማ፣ በሰንበት፣ በክረምት፣ በአዲስ ዘመን ላይ የሚፈጸሙ ክንውኖችን፣ ወቅቶችን የአካባቢው ሰው እንዴት እንደሚያስባቸው፣ በእነዚህ ወቅቶች፣ ጊዜዎችና ቀኖች ስለሚከናወኑና ስለማይከናወኑ ተግባሮች፣ ከእናቶች፣ ከነጋዴዎች፣ ከአራሾች፣ ከአባወራዎች ጋር ቃለመጠይቅ አካሂጃለሁ።
4. በከብቶች፣ በአዝመራና በልጆች አካባቢ የዐይንን ጥቃት ለመከላከል ስለሚያገለግሉ መከላከያዎች፣ በአካባቢው ዕውቀትና ልምዱ ላላቸው ሰዎች ሰፋ ያለ ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ።

5. በመናፍስት ምንነት፣ ባህርይ፣ በክፉ አይን እሳቤ፣ በሚያደርሰው ጉዳት፣ መንፈሱ ሰዎችን በምን አጋጣሚና ሁኔታ እንደሚያጠቃ፣ በመንፈሳዊነትና በዓለማዊነት ሃሳብና ትርጉም ላይ በአካባቢው አዋቂ ከሆኑ ሰዎች ጋር ቃለመጠይቅ በተናጥል ተካሂዷል፡፡

6. ለመንፈስ ማደሪያ በመሆን የሚያገለግሉ ሰዎች፣ እንስሳት፣ ተክሎች ባህርይ፣ በዚያ እንዲፈረጁ ስላደረገው ጉዳይ በተመለከተ የዕፅ እግር ለሚያውቁ ባለሙያዎች ቃለመጠይቅ ቀርቧል፡፡

7. እህል ተዘርቶ እስኪሰበሰብ ድረስ ስለሚፈጸሙ ልማዳዊ ክንውኖች ቃለ መጠይቅ በግብርና ሙያ ከተሰማሩ አባቶና እናቶች መረጃ ተሰብስቧል፡፡

8. ከተለመደው ውጭ የተወለዱ ወይም የተፈጠሩ ሰዎች፣ እንስሳት፣ ተክሎች ምንነት፣ ምሳሌነት ለምሳሌ፣ አካለ ስንኩላን፣ ያልወለዱ ሴቶች፣ ወፎች፣ ተሳቢ ፍጥረቶች መረጃ ተይዟል፡፡

እነዚህ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ፣ የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን የመስክ መረጃ ከመጀመሪያው ጋር በማሰናሰል በተመረጡ ይዘቶች አማካይነት የማደራጀት ስራ አከናወንኩ፡፡ በመልክ በመልክ ካስቀመጥኩ በኋላ የመተርጎምና የመግለጽ ስራ ሰርቻለሁ፡፡ የመረጃዎቹን በቅደም ተከተል አስተካክዬ አስቀምጬ፤ ትርጉም በሚሰጡበት ሁኔታ ቅርጽ እንዲይዙ አደረግኩ፡፡ በመካከላቸው ያለውን ዝምድናና ተመጋግቦ እየመረመርኩ ፋይዳቸውን ካጤንኩ በኋላ ድርሳናትን በመከለስ መረጃው የሚበለጽግበትንና መልክ የመይዝበትን መንገድ አመቻችሁ፡፡ በተጨማሪም፣ የመረጃ ክፍተት ያለባቸውን፣ በሚገባ ያልተዳሰሱትን፣ በቀጣይ መሰብሰብና መከለስ የሚገባቸው ነገሮች መኖራቸውን ለመለየት ቻልኩ፡፡ በመጨረሻም፣ መረጃዎች ትርጉም በሚሰጡበት ቅርጽ ሊደራጁ ችለዋል፡፡ ይህንን አረጋግጬ ለተቋቁሞ ቀረብኩ፡፡

በተቋቁሞው ላይ የተጠቆመ አስተያየቶችን በማካተት፣ ክለሳ ድርሳናትን በማንበብ የምርምሩን አቅጣጫ አስተካክዬ፣ መረጃውን ይበልጥ ያብራራታል፡፡ እንዲሁም፣ በተሻለ ግንዛቤ ለመፍጠር ያስችላሉ ተብሎ የታመነባቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ

ሦስተኛ ዙር የመስክ ስራ ለማከናወን ከሐምሌ 5፣ 2004 ዓ/ም እስከ ጁጉሜ 5፣ 2004 ዓ/ም ባለው ጊዜ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ጥናት ቦታዬ በመሄድ ቆይታ አደረግኩ።

1. በቀለም፣ በግራና በቀኝ አቅጣጫዎች፣ በብርሃንና በጨለማ፣ በቁጥሮች ፋይዳና አገልግሎት ለጽንሰ ሐሳቦቹ ቅርብ ከሆኑ አባቶች፣ እናቶች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ የታሪክ ዕውቀት ካላቸው አባላት ጋር ቃለመጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት አደረግኩ።

2. በንጽሕናና በርክሰት፣ በክፉ ተክሎች፣ በክፉ እንስሳት፣ በርኩስ እንስሳት፣ ለምግብ በሚመረጡ እንስሳትና ተክሎች ባህርይ፣ የመምረጫ መስፈርት ላይ፣ በህይወትና በሞት ምንነት፣ በህይወት አላባዎች፣ በሞት ማህበራዊ እሳቤ፣ ሞትን ስለሚያመጡ ሃይሎች፣ ስለዕድሜ ያለን አመለካከት፣ ከመምከን፣ ከዕድሜ ማጠር፣ ከማግባትና ካለማግባት በተያያዙ ስላሉ አመለካከቶች በቃለመጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ።

3. መንፈሱ ባረፈባቸው ሰዎች ላይ ስለሚታዩ ምልክቶች፣ በማከሚያ ወይም በመፈወሻ መንገዶች፣ መንፈሱ ወደ ሰዎች እንዳይደርስ ስለሚዘየዱ ቅድመ መከላከሎች፣ ለመከላከያነትና ለመፈወሻነት ስለሚያገለግሉ ዕፆች አይነትና ምንነት፣ ባህርይና አደራረግ፣ ስለቡዳ ማከሚያ መንገዶች ቃለመጠይቅ ተካሂዷል።

4. መናፍስቱ ሃይልና ጉልበታቸውን የሚገልፁባቸው ተፈጥሯዊ ክስተቶች ምን እንደሆኑ፣ ለምን እነሱን እንደመረጡ፣ መለኮቶችና መናፍስቶች በርከት ብለው የሚገኙባቸው ቦታዎች የትኞቹ እንደሆኑና ለምን እነዚያ ቦታዎች እንደተመረጡ በእነዚህ ጭብጦች ከሚመለከታቸው የመረጃ አቀባዮች መረጃ ተወስዷል፤

5. የዘመን መሸጋገሪያ፣ በእርሻ ስራዎች /የበራይ፣ የመኸር ወቅቶች፣ የጳጉሜ ቀናት / በጠበል ቦታዎች፣ የሽግግር ስርዓቶች /የሠርግ፣ የሞት፣ የአራስ ቤቶች፣ የመኸር ወቅቶች፣ የጠበል ቦታ፣ የባህል በሠርግ ዋዜማ፣ በሞት፣ በፅዋ፣ በምርቃት

ስርዓቶች ላይ በአካል ተገኝቶ ሥርዓቱን በመመልከት አጠቃላይ ልምዱ የሚመራበትን ደንብ ለማየት ችያለሁ፡፡

6. በእርድ ቦታ፤ በሥርግ፤ በልቅሶ፤ በዘመን ሽግግር፡ በእርሻ ተግባራት አውዶች ላይ የሚከናወኑ ልማዶችን ለማየት በአካል ተገኝቻለሁ፡፡

ከጥቅምት 28፣ 2006 እስከ ታህሳስ 26፣ 2006 ዓ/ም (የአጨዳ፣ የአይን መክላኪያ፣)

1. በእንግዳ ሰዎች፣ ነገሮችና ክስተቶች አቀባበል፣ አገላለል ዙሪያ ያለውን አስተሳሰብ፣ ስለክፉ እንስሳት፣ ተክሎችና ሰዎች ፣ በእንስሳትና በተክሎች ላይ ማህበረሰቡ ያለው አመለካከት፤ በክፉ ዐይን ስለሚጠረጠሩ ሰዎች፣ ለምን በዚህ ሊጠረጠሩ እንደቻሉ፣ ስለዘራቸው ማንነት፣ የተሰማሩበት የስራ መስክ ሁሉ በቃለመጠይቅ ተካትቷል ፡፡
2. ከጠፍ መሬት፤ ከማይተካ ዕጽ፤ ከመሰነ ከብትና እንስሳት ጋር ተያይዞ ያለውን እምነት፣ ከወቅቶች፣ ከጊዜዎች፣ ከጨለማ፣ ከክረምት፣ ከሞት፣ ከማዕድ፣ ከአውድማ፣ ከአመድ፣ ከአተላ ጋር በተያያዘ ስላለው አመለካከትና በእነዚህ ክስተቶች ላይ ስለሚፈጸም ክንውን ለእናቶች፣ ለአባቶች፣ ተጨማሪ ጥያቄ ቀርቦ መረጃ የማጠናከር ሥራ ተከናውኗል፡፡

3. በነፍስና በሥጋ በሕርያት፣ ግብሮች እና ጠባዮች፤ በቅድስናና በንጽሕና፣ በንጽሕናና በርክሰት፣ ስለሚያረክሱ እንስሳት፣ በመፈቀድና በመከልከል ዙሪያ ያለው አምክንዮ ምን እንደሆነ፣ ወደ ሰብዕና መመለሻ መንገዶች፣ ስለያም፣ ስለመጽዋት፣ ስለ ስግደት፣ ስለጸሎት ምንነት ዕውቀቱ ካላቸው አባቶች ጋር የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካሂዷል፡፡

4. በዕፅዋትና በእንስሳት ተፈጥሮ ውስጥ ስላለው የእንግዳነትና የለማዳነት፤ የግስጋሽነት ወይም የዘማችነት ወይም የወራሪነት እና የማፍለስ፤ የመምከንና የማፍራት/መዋለድና መድረቅ፤ መመሳሰልና መለያየት፤ መበርከትና በአጭር መቅረት፤ ማግለልና ማቅረብ፤ ባይታወርነትና በወገን መከበብ፤ ነጠላ መሆንና መደረብ የወገንነት መገለጫ ጽንሰ ሐሳቦች፤ ማቅረብና ማራቅ፤ መሳብና

መግፋት፤ ዘመድ ማድረግና ባዕዳ ማድረግ፤ ብዙነትና ነጠላነት ጋር ስላላቸው መመሳሰል

5. በቀደምት ታሪኮች፣ የጋራ ልምዶች፤ በአካባቢው ስለነበሩ የአስተዳደር ጉድለቶች፤ በማንነት ግንባታው ውስጥ አስተዋጽኦ ስላደረጉ አካባቢያዊ አስተዋጸዎች፤ መልክዓምድራዊ አቀማመጦች፤ በአካባቢው ዙሪያ ስለሚነገሩ አፈታሪኮችና ሚቶች በአካባቢው እሴቶች፣ ለምሳሌ ብዙ የመውለድ እሴት ጋር በተያያዘ ስለአካባቢው ታሪክ የሚያውቁ ሰዎች ጋር የተደረገ ውይይት፡፡

6. የዘር ምርጫ፤ የዘር ምርጫ ማህበራዊ እሳቤ፣ ማንነትን ስለመጠበቅ፣ ዘርን ቆጥሮ ስለመለየትና ስለመያዝ፣ ጀግንነትን ባህል ስለማድረግ፣ እህል እንዲበረክት፣ ከወሳጅ ለመከላከል በቡሃቃ፣ በጎተራ የሚደረጉ ልማዶች፤
7. መካን የሆኑ ሴቶች አራስ ቤት ሲመጡ ወይም የደረሱ ልጆችን ሲያዩ ሊጎዷቸው ይችላሉ ተብሎ ሲታሰብ ስለሚፈጸሙ ልማዶች፡፡ ስለራስ፣ ስለቀንድ፣ የወር አበባ፣ ስለእንባር፣ የወንዝ ክብር፣ ስለመጠንፈፍ፣ ስለባዶ እንስራ፣ ስለክረምት፣ ስለእንስሳት፣ ስለጅብ፣ በመብል፣ በንክኪና በፈሳሽ ስለሚያረክሱ፣ ስለ ክፉት ምንነት፣ ስለ ክፉ እንስሳት፣ መርከስ፤
8. ስለቀንድ፣ ቆዳ ወይም ቆርበት፣ ስለ ድንግልና፣ ስለየሚበሉ እንስሳት፣ የሰኮና ትርጉም፣ ከአካል መጉደልና መስዋይት ምርጫ፣ ጸታዊ ግንኙነት እና የወር አበባ፣ ስለተክሎች መደጋገፍ፣ በቅድስና እና በንጽሕና ዙሪያ ያለው አንድነትና ልዩነት፣ ንስሓ፣ እሳት፣ ፀጉር መላጨት፣ ሰንበት፣ ማምስኳ

ከዚህ በኋላ መረጃዎችን እንደየ ባህርያቸው፣ ትርጉም ሊሰጡ በሚችልበት መንገድ አደራጅቼ ተረጎምኩ፡፡

መረጃ አሰባሰብ ዘዴ፤ ካልአይና ቀደማይ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልኣይ ምንጮች የተሰበሰቡ ናቸው። እነዚህ መረጃዎች የተሰበሰቡበት መንገድና ያሰባሰቡ ሁኔታ በሚከተለው መንገድ ተከናውኗል፡፡

3.1.1.ካልአይ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ለዚህ ጥናት አጋዥ የሆኑ ካልአይ ምንጮች የተሰበሰቡት ሌሎች ተመራማሪዎች ከአሳተሟቸው የጥናት ውጤቶችና ከጻፏቸው መጻሕፍት ነው። እነዚህን ምንጮች ከቤተ መጻሕፍት፣ ከቤተ መዛግብትና ከመረጃ መረቦች የተገኙ ናቸው። ከጥናት ርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ካልአይ የመረጃ ምንጮችን ከተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ከቤተ-አምልኮቶች፣ ከግለሰቦች የግል ስብስብ፣ ከተለያዩ የመረጃ ቋቶች የተወሰዱ ናቸው። ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው። የአካባቢውን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚያስረዱ፣ በግብር፣ በርስትና በመሬት ስሪት ዙሪያ አስረጅ የሆኑ ሰነዶች፣ ስለአካባቢው ማህበረሰብ ሃይማኖት፣ ታሪክ፣ መልክአምድራዊና ስነ ልቦና ሁኔታ የሚያስገነዝቡ ጥናቶች፣ ማስታዎሻዎች፣ መዛግብት ሁሉ የመረጃ ማበልጸጊያ መንገዶች ሆነው ተሰብስበዋል።

በየገዳማቱ፣ በየአድባራቱና በግለሰቦች እጅ የተገኙ ኃይማኖታዊ ታሪካዊ መረጃዎች፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም፣ ከኬኔዲ ቤተ መጻሕፍት፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ የባህል ማዕከል፤ የታተሙና ያልታተሙ ጽሑፋዊ መረጃዎች፣ በደብረማርቆስ የዞን መስተዳድር ውስጥ ከሚገኙ የባህል፣ የትምህርት፣ የማስታወቂያ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ፣ ማዘጋጃ፣ የፍትህ መምሪያና ጽ/ቤቶች የተገኙ ሪፖርቶች፣ ጥናቶች፣ የታተሙና ያልታተሙ ልዩ ልዩ ጽሑፎች ናቸው።

3.1.2.የቀዳማይ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ይህ ጥናት፣ የሰዎችን አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ ልምድና ባህርይ ያጠና በመሆኑ የምርምሩ ስነዘዴ ዓይነታዊ ነው (Dawson, 2007,16)። አጥኝው መረጃውን ያገኘው ከሚጠናው ማህበረሰብ ባህል በመገኘት የተጠኝውን ህብረተሰብ ህይወትና ኑሮ በመኖር በመሆኑ፣ ከዓይነታዊ የምርምር ዘዴዎች መካከልም ኢትኖግራፊያዊ ጥናት ነው (Dawson, 2007,19)። በመሆኑም፣ የጥናቱ ፍልስፍና የማህበራዊ ግንባታ (Social constructivism) ሆኖ በትርጓሜ (Interpretative) ውስጥ የሚካተት ይሆናል። ለዚህ ዓይነታዊ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ (method) በመሆን፣

አሳታፊ ምልከታ፣ ጥልቅ ግላዊ ቃለመጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ከቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ጋር በተደረገ ውይይት የተሰበሰበ ነው፡፡ የእነዚህ ዓይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አጠቃቀም በሚከተለው መልኩ የተከናወነ ነው፡

ምልከታ

ይህን መረጃ አራት ጊዜ በተካሄዱ ምልልሶችና በስምንት ወር ቆይታ የተሰበሰበ ነው፡፡ ምልልሱና ቆይታው በዓላማ የተከናወነ ሆኖ፣ በተለይ የዘመን መሸጋገሪያን፣ የእርሻ ሥራ ክንውኖችን (የበራይ፣ የመኸር ወቅቶች)፣ የደግሚ ቀናትን፣ በጠበል ቦታዎች፣ የሽግግር ሥርዓቶች ፣ የንግስና ልዩ ልዩ የሽግግር ጊዜያትንና ወቅቶችን ታሳቢ ያደረገ ነበር፡፡ በመሆኑም፣ በአንድ የሠርግና የሞት ሥርዓት ላይ ተገኝቼአለሁ፡፡ የወለደች አራስ ጠይቄአለሁ፡፡ በአጨዳና ሥርዓቶች ላይ በመገኘት አውድማው ላይ በመሳተፍ ልማዳዊ እምነቱን ተመልክቼአለሁ፡፡ በጠበል ቦታ በመሄድ ስለሚካሄዱ የስብከት፣ የማከሚያ መንገዶች በመጠመቅ፣ ሥርዓቱ ፀሎቱን በመከታተል፣ አብሮ በመቆየት ለመቃኘት ሞክሬያለሁ፡፡ በባህል የሠርግ ሥርዓት፣ በምርቃት ሥርዓቶች፣ በዕጽ ቆረጣና ዝግጅት ላይ በአካል ተገኝቶ ተጀምሮ እስኪያልቅ ያለውን ሥርዓት በአሳታፊ ምልከታ ለመመልከት ችያለሁ ፡፡

በዚህ ረጅም ጊዜ ውስጥ ከሚጠናው ማህበረሰብ ጋር ጠበቅ ያለ ቅርበት ለመመስረት ችያለሁ፡፡ ቆይታው ማህበረሰቡ የሚኖረውን ኑሮ በመኖር፣ የሚሰራውን ስራ በማከናወን የአካባቢውን ሰው መሠረተ እምነት፣ ፍርሃት፣ ተስፋና ምኞት ለመረዳትና ለመጋራት አስችሎኛል፡፡ ለመስክ የቆየሁባቸው ቀናት ሁሉንም ባህላዊ ድርጊቶች ለመታዘብ፤ በየቀኑ፣ በየወሩ፣ በየወቅቱ ስለሚከናወኑ ተግባሮች ለመረዳት የሚያስችሉ ስለነበሩ የአካባቢውን ማህበራዊ-ባህላዊ ሁኔታ በሁለንተናዊ መልኩ ተገንዝቤአለሁ፡፡

በመሆኑም፣ በእነዚህ ቀናት ምልከታ የማደርግባቸውን ቦታዎችና ጊዜዎች በመለየት መንፈሱ የሚገለጥባቸውን፣ የመከላከያ መንገዶች የሚዘጋጁባቸውን፣ የታመሙ ሰዎች የሚታከሙባቸውን ቦታዎች ደጋግሜ በመሄድ ጎብኝቻለሁ፡፡ በወሊድ፣ በሠርግ፣ በቀብር፣ በእርሻ፣ በዘር፣ በአረም፣ በአጨዳና በበራይ ሰዓት ስለሚፈጸሙ ልማዶች

በአካል ተገኝቼ እንቅስቃሴውን ጎብኝቻለሁ፡፡ በተጨማሪም፣ ሰዎች በሚሰባሰቡባቸው የዓመት በዓሎች፣ ማህበሮች፣ ሰንበቴዎች ተጋብገር፣ አንዳንድ ታቦቶችን ለማንገስ ሂጀ ብዙ ነገሮችን ለመመልከች ችያለሁ፡፡

ሰዎች ሲናገሩ፣ ሲያደርጉና ሲያከናውኑ ሃሳባቸው፣ እምነታቸው፣ አመለካከታቸውና ጠባያቸው ስለሚገለጽ ትዝብቱ ጥሩ የመረጃ ምንጭ ሆኖ አገልግሎኛል፡፡ በተለይ የአካባቢው ተወላጅ በመሆኔ፣ የኔን መገኘት በሌላ መልኩ ሳይጠረጥሩ እንደ አንድ የማህበረሰቡ አባልና ተሳታፊ በማሰባቸው ያለምንም ችግር እና መሳቀቅ ባህላዊ ልምዶችን ለመቃኘት አግዞኛል፡፡ ፎቶ ካሜራ፣ በመስክ ምልከታ ወቅት የሚቃረሙ መረጃዎችን ለመያዝና በተለይ በትንታኔ ጊዜ ትውስታን ለማንቃት በእጅጉ የሚረዳ መሳሪያ ነው፡፡ በተለይ ከአቀማመጥ፣ ከአለባበስ፣ ከገጽ ተለዋውጦ፣ ከቦታና ከጊዜ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ ለሚስተዋሉና መረጃውን ለማስፋት የሚያገለግሉ ምንጮችን ቀርሶ ለመያዝ ዲጅታል ፎቶ ካመራ አገልግሏል፡፡

ቃለመጠይቅ

ቃለመጠይቅ የአንድ መስክኛ ጠቃሚ የመረጃ መሰብሰቢያ ቴክኒክ ነው (Fetterman, 2010, 40)፡፡ ቃለመጠይቅ መስክኛው ያየውን እና ያጋጠመውን ለማብራራትና ለመተንተን ያግዘዋል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ አድርጌ በቅድመ የመስክ ጉብኝቱ ላይ በመመርኮዝ 45 ሰዎችን በመረጃ ምንጭነት አሳትፌአለሁ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 15 ሴቶች ቀሪዎቹ 31 ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ከጎዛምን ወረዳ እና ከደብረማርቆስ ከተማ የተለያዩ ቀበሌዎች የተመረጡ ናቸው፡፡ ቃለመጠይቁ፣ በዓላማ ለተመረጡ የተለያዩ ወካይ አካላት የቀረበ ነው፡፡ የመረጃ ሰጪዎች ሲመረጡ ጅአግራፊያዊ ስርጭት፣ ሙያ፣ ጸታ፣ ዕድሜና የትምህርት ደረጃ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ለሴቶች ቃለመጠይቅ ሲካሄድ አንዲት ሴት የፎክሎር የዶክትሬት ተማሪን በአሳታፊነት መርጫለሁ፡፡

ቃለመጠይቁ በገጽ ለገጽ ውይይት የተካሄደ ሆኖ፣ የሥራ ሰዓትን፣ ቅርበትን፣ ምቹነትን ማዕከል ባደረገ መልኩ ተለይቷል፡፡ በመሆኑም፣ ከሴቶች ጋር ቃለመጠይቅ ያካሄድኩት በዓል በሆኑ ቀናት፣ ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመሄድ

ሲሆን፣ ወንዶችንም በመኖሪያ ቤታቸው፣ በእርሻ ማሳቸው፣ በቤተ ክርስትያንና እኔ ባመቻቸሁት ቦታ ነው።

አካባቢያዊ ዕውቀቶች፣ ልማዳዊ ድርጊቶች በተጨባጭ ብቻ የሚገለጹና በአንድ ጊዜ እይታ የሚቃረሙ ልምዶች ስላልሆኑ፣ ሁሉም ሰው በእኩል አያውቃቸውም። እያንዳንዱን የማህበረሰብ አባል በኃይማኖት ዕውቀቱ፣ በባህል ልምዱ፣ አከባበሩና ለማወቅ ባለው ጉጉት ይለያያል። በመሆኑም፣ ለዚህ ቃለ መጠይቅ አይነት የመረጃ አቀባዮች ሲመረጡ ለባህል ያላቸው ዕውቀት የመምረጫ መስፈርት ሆኖ ገብቷል። ከተጠኝው ማህበረሰብ አባላት መካከል አጥኝው በጥናቱ ላይ ጥሩና ጠቃሚ መረጃ ሊሰጡኝ ይችላሉ ብዬ ያመንኩባቸውን መረጃ ሰጭዎች በዓላማ ዘዴ (purposive sampling) መርጫለሁ። በውይይት ወቅት ሰዎቹ ይህንን ጉዳይ ከእኔ በተሻለ እከሌ ያውቀዋል። ስለዚህ፣ ነጥብ ደግሞ እከሌን ጠይቀው በማለት መረጃ ከሚሰጡ ተጠኝዎች ጥቆማ በመነሳት አንዳንድ ሰዎችን በጠቋሚ ናሙና (Snow ball Sampling) ስልት እንዲጠይቅ ስላደረጉኝ ይሽንንም ተገልግየበታለሁ። አንዳንድ ጊዜ አጋጣሚዎች አልቀና ሲሉ እና በቅርብ መረጃዎችን ማግኘት ሲያስቸግረኝ በአመች ናሙና ስልት (Convenience Samples) መረጃዎችን ለማግኘት ሞክሬአለሁ። በተለይ በዚህ የናሙና ስልት የሰበሰብኳቸው መረጃዎች መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመቅረጽ አስችለውኛል።

ከእነዚህ ሰዎች ጋር የተደረገው ውይይት በከፊል ነጻ ስልት ቃለ መጠይቅ (Semi structured Interview) የተሰበሰበ ነው። በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከቤተሰቦቼ፣ ከጓደኞቼ፣ ከዘመዶቼ ጋር በነበርኩበት ወቅት አጋጣሚዎች በሚፈጥሯቸው ውይይቶች፣ ሌሎች ሰዎች በሚያነሷቸው አንዳንድ ጥያቄዎች፣ ጨዋታዎች መካከል የሚነሱ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጉዳዮች፣ ሃሳቦችን እና ስሜቶችን በኢመደበኛ ቃለመጠይቆች (Informal interviews) ለመሰብሰብ ሞክሬአለሁ።

ሁሉም በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በዲጅታል መቅረጸ ድምጽ ተይዘው፣ ትራንስክራይብ ሆነው በጭብጥ ተደራጅተው ተቀምጠዋል። አንዳንድ ጊዜ በመንገድ ላይ ስሄድ፣ ከሰዎች ጋር ስወያይ የማገኛቸውን መረጃዎች ወዲያው

በማስታዎሻ ደብተር ገልብጫቸዋለሁ፡፡ በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትክክለኛነት በመስክ ላይ በተካሄደ ምልከታ፣ ከቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ጋር በተደረገ ውይይት እንዲሁም በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት በተነሱ ውይይቶች ትክክለኛነታቸው ሊረጋገጥ ችሏል፡፡

ተተኳሪ የቡድን ውይይት

ስለኑሃምን ሕዝብ ማህበራዊ-ባህላዊ እሴቶች ጠቋሚ መረጃዎችን ለማግኘት፣ በመናፍስቱ ዙሪያ የተሰበሰቡት መረጃዎች ትክክል መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥና አንዳንድ ሀሳቦችን ለማጥራትና ተጨማሪ ቁምነገር ለመጨበጥ ተተካሪ የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በዚህ ውይይት ላይ ለባህሉ ዕውቀት ያላቸውና ተገቢ የሆኑ ከ7 እስከ 8 የሚደርሱ ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ በአጠቃላይ ሦስት የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ምድብ፣ በአካባቢው እሴት፣ የዝምድና መፍጠሪያ ስልቶችና ታሪኮች ላይ ያነጠጣጠሩ ጥያቄዎች ቀርበው የታሪክ ዕውቀት ያላቸው፣ ባህሉን የሚያውቁና መተርጎም የሚችሉ ስምንት ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡

ሁለተኛው ቡድን በንጽሕናና በመርከስ፣ በነፍስ ምንነትና በሥጋ ባሕርይ ዙሪያ የተደረጉ ውይይቶች ተካትተውበታል፡፡ በዚህ ተተኳሪ የቡድን ውይይት በመስበክ፣ ህልም በመፍታት፣ መጽሐፍ በመተርጎም፣ ታሪካዊ ዕውቀት ያላቸው ከ7 ሰዎች ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡ በሶስተኛው ምድብ፣ ከሴትነት ጋር በተገናኘ የተፈቀዱና የተከለከሉ ነገሮችን፣ ከምግብ ዝግጅት፣ ከወሊድ፣ ከጊዜና በአጠቃላይ በሽግግር ሥርዓት ውስጥ ስላሉ እሴቶች ከቤት እመቤቶች፣ ባለሙያዎች፣ ባህሉን ከሚያውቁ ሴቶች፣ ልማዱን ከሚያደርጉ እናቶች ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡ በዚህ ተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ላይ የተሳተፉ ሰዎች 7 ናቸው፡፡ በውይይቱ ጊዜ መረጃዎቹ በመቅረጸ ድምጽ ተቀድተዋል፡፡ በተጨማሪም፣ ፍሬ ሃሳቦች በማስታወሻ ደብተር ተለቅመው ተይዘዋል፡፡

ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች

እንደ Michael and Fiona (2006, 109) ገለጻ በኢትኖግራፊክ ጥናት አንድ አጥኝ ሊጠቀምባቸው የሚገባና በጣም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሊሰጡ የሚችሉ ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች (Key Informants) በመባል ይጠራሉ። እነዚህ መረጃ ሰጭዎችን ቁልፍ ያሰኛቸው ጉዳይ በመረጃ ስብሰባው ወቅት ጥናት ስለሚደረግበት አካባቢ መነሻ እውቀት ሊሰጡ መቻላቸው፣ የት የት ቢኬድ ጠቃሚ መረጃ ሊገኝ እንደሚችል በመጠቆማቸውና ባላቸው አቅም ሁሉ ሊያግዙ በመቻላቸው ነው።

ሌላው ነጥብ በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ለረጅም ጊዜ በመኖራቸው ስለሚጠናው ጉዳይ ታሪካዊ ዳራ ሊሆን የሚችል በቂ መረጃ መያዛቸው ነው። ከሞያቸው አንጻር ለማህበረሰቡ ባላቸው ቅርበት ለአጥኝው ጠቃሚ መረጃዎችን አስገኝተዋል። በመሆኑም፣ እነዚህ ሰዎች በጥናቱ ዙሪያ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባሮች ሊያሚሉ በመቻላቸው ቁልፍ መረጃ ሰጭ አድርጌ እንደ እረዳት አጥኝ (Co-researcher) አሳትፌአቸዋለሁ።

3.2. የመረጃ መተንተኛ ስልት

Glesne and Peshkin (1992, 130) የመረጃ ትንተና (data analysis) መረጃዎችን ለትንተናና ለፍርድ እንዲመቹ ማድረጊያ የማደራጃና የመመደቢያ ሂደት ነው ይላሉ። የመረጃ ትንተና ተግባር ተመራማሪው ከአየው ከሰማው በመነሳት ጠቃሚ ፍቺዎችን፣ ቅጥአምባሮችንና ጭብጦችን መፈለጊያ መንገዱ ነው። ከቀዳማይና ከካልአይ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንዴት እንደተደራጁና እንደተተነተኑ በሚከተለው ክፍል ቀርቧል።

3.2.1.የቀዳማይ መረጃዎች አተናተን

ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን የተመረጠው ዘዴ የይዘት ትንተና (content analysis) ነው። በተሰበሰቡ መረጃዎች ውስጥ ያለውን የሃሳብ ዝምድናና የባህርይ መመሳሰል በመመርመር በተወሰኑ ይዘቶች አማካይነት መረጃዎቹ እንዲደራጁ ተደርጓል። መራጃዎቹ የክፉ ዐይንን ምንነት የሚያብራሩ፣ አጋላጭ የሆኑ አውዶችን የሚገልጹ፣ መከላከያዎችን የሚያስረዱና የመፈወሻ መንገዶችን የሚያሳውቁ በሚል ነው።

በእነዚህ አደረጃጀቶች አማካይነት ከሰው፣ ከተክሎች፣ ከእንስሳትና ከወቅቶች ጋር በተገናኘ የተሰበሰቡ መረጃዎች በአንድ ምድብ እንዲገቡ ሆነዋል። በአደረጃጀቱ ጊዜ የጋራ የሆነ ቅጥአምባር (pattern) ለማፈላለግ ተሞክሯል። በመጀመሪያ በመከላከያ መንገዶች ተዘውትረው የሚጠቀሱት እንደ ወጉር፣ ጥፍር፣ ቀንድ፣ የአካል የውስጥ ልብሶች፣ ወዮች ላይ ያለው ክፍል ጠቅለል ብሎ እንዲጠራ ተደርጓል። አጋላጭ በሆኑ አውዶች ላይ ያለው አስተሳሰብ ማለትም፣ እርግዝና፣ ወሊድ፣ ሽምግልና፣ ሞት፣ ህመም፣ አመድ፣ አተላ፣ አምቡላ፣ ጨለማ፣ ክረምት፣ አርብ፣ አውድማ፣ ማዕድ፣ በመካከላቸው ያለው የጋራ ባህርይ እንዲወጣ ሆኗል። ከዚያም ቀዳሚው መከላከያ ተከታዩን ተጋላጭ ያደረገው ነገር ምን እንደሆነ ለማጤን ተሞክሯል። በሰዎች፣ በእንስሳት፣ በተክሎችና በሁነቶች ውስጥ ያለውን ተፈጥሯዊ እሳቤ በመመርመር እነዚህ አጋላጮች የሚፈጠሩበትን እና የሚከሰቱበትን ተፈጥሯዊ ሁኔታ ለመመርመር ተችሏል።

3.2.2.የካልአይ መረጃዎች አተናተን

ከካልአይ ምንጭ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከቀዳማይ ምንጮች የተገኙትን መረጃዎች ለማጎላመስ የገቡ ናቸው። ቀዳሚ መረጃዎች የሚያብራሩት፣ የሚተነትኑትና የሚወክሉት ሃሳብ በሌሎች ጥናቶች ከተገኘው መረጃ ጋር እየተገናዘበ ምስስሎሽና ልዩነት እንዲያሳይ እይሆነ ገብቷል። በተለይ በአካባቢው ያለው የመሬት ውርስ፣ የጋብቻና ዝምድና መፍጠሪያ መንገድ፣ የውርስ ሥርዓት ቀዳማይ መረጃውዎችን በማጎልመስ በኩል ፋይዳቸው የጎላ ነበር።

3.3. የመስክ ላይ ተሞክሮዎች

እንኳን እንደዚህ ሰፋ ያለና ረጅም ጊዜ የሚወስድ ጥናት ይቅርና አጫጭርና ተራ ሥራዎችን ለማከናወን በሚደረግ መከራ ውስጥ በርካታ ተግዳሮቶች ማጋጠማቸው አይቀርም። የችግሮቹ ምንጮች ልዩ ልዩ ሆነው፣ ሁኔታውን በማክበድ ወይም በመጠኑ በማቅለል ርዕሰ ጉዳዩ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል። የመረጥኩት የጥናት ርዕሰ ምስጢር ነገሮች የበዙበት፣ አስፈሪና አስጊ ሁኔታዎች ያለበት፣ ነውርና ፀያፍ፣

ወንጀል ነክና አግላይ ታሪኮች የተካተቱበት ስለሆነ፣ የምርምር ሂደቱ በእጅጉ ፈታኝ ነበር።

በመከላከያ፣ በመለያና በመፈወሻ ዘዴዎች ዙሪያ ብዙ ረቂቅና ህቡዕ ነገሮች የተካማቹበት፣ በድብቅና ይፋዊ ባልሆነ መንገድ የሚከወኑ ሥርዓቶቹ የበዙበት በመሆኑ፣ ውስጡን ለመፈተሽ ፈተናው ቀላል አልነበረም። ቃለመጠይቅ ካደረግኩላቸው ሰዎች ጋር በግልጽ ለመወያየት ተቸግሬ ነበር። ገጠመኞቻቸውን በዝርዝር ለማውራት ሲጨነቁ፣ የሰሙትንና ያዩትን ታሪክ እየሸፋፈኑና አያለፉ ለማሳጠር ሲሞክሩ ስመለከት ክስተቱ ምን ያህል ከባድ እንደነበር ለመታዘብ ችያለሁ።

መረጃ ለመሰብሰብ ወደ አካባቢው ሄጀ የሚያግዙኝን ሰዎች መርጬ፣ ከዘመድ አዝማድ ጋር ምክር ስጀምር ገና ከመጀመሪያው የደረሰብኝ ግሰጻ፣ "አካባቢያዊ ገጽታን ያበላሻል፤ በጥሩ እንዳንታሰብ ያደርጋል፤ ሰዎች በእኛ ላይ በጎ ያልሆነ ስሜት ያሳድራሉ" እያለ የምርምር ርዕስ እንድቀይር ይጠይቁኝ ነበር። ይህ ስሜት በሂደት ቢቀንስም እስከመጨረሻው ግን ጨርሶ ያልጠፋና የተከተለኝ ፈተናዬ ነበር። ተጠንቶ ይፋ ሲወጣና ሲነበብም "ነጃም በዳ ነው" ልታስብለን ነው፣ "የመተት ሃገር ነው" ብለህ በሰው ልታሰድበን ነው የሚሉ ወቀሳዎች ይሰነዘሩብኝ ነበር። "ሊሎች የሚሉን ባላነሰ አንተ ደግሞ ጭራሽ በይፋ ልታሰድበን ነው" እያለ ቅሬታቸውንና መከፋታቸውን በተለያየ መንገድ ይገልጹልኝ ነበር።

በቃለመጠይቁ ወቅት በክስተቱ ምንነት ልምድና ዕውቀት ካላቸው ሰዎች ጋር በአንዳንድ ጉዳዮች ስወያይ መረጃውን ላለመስጠት ሆን ብለው ይጠቀሙበት የነበረው የማምለጫ መንገድ፣ "በዳ በሌለበት ስለበዳ ማውራትና የአንዳንድ የመንፈስ ስሞች እያነሱ መጥቀስ፣ ክስተቱን ይበልጥ እንዲባባስ ያደርገዋል፤ ስሙን መጥራት መከራን መጥራት ነው" የሚል ነበር። ክስተቱ እንደሌለ በመቁጠር ችላ ሲባል ጥቃቱም ሆነ ስርጭቱ ይቀንሳል፣ ዝናውን እየዘረዘሩ ማንሳት ከተጀመረ ግን የተበይው ወይም የተለካፊው ቁጥር ይጨምራል፤ እንዳበደ ውሻ ያንንም ያህንንም መለካከፋቸው አይቀርም። ስሙን መጥራት እንደነውርም ስለሚቆጠር በእሱ ዙሪያ ማሰቡ አይገባም ብለው ላለመናገር ያንገራግሩ ነበር።

ሌላው የአብዛኛው ሰው የጋራ አቋም ሆኖ ያገኘሁትና ሁሉም ሰው እንደ መፈክር ሲያቀነቅነው የሰማሁት ግን፣ "ርዕሰ ጉዳዩ ጠቃሚ ነገር የለውም፤ መልካም ነገር አይገኝበትም፤ ካልጠፋ ርዕስ እንዴት ይሆንን መረጥህ? ምን ቁምነገር አገኝበታለህ ብለህ አስበህ ነው? ለወሬስ የሚበቃ ምን ታሪክ አለው" በሚል የዘርፉን ፋይዳ አሳንሶ የማየት አመለካከት ነበር። የእንደዚህ ዐይነት አስተያየቶችን መነሻ ከአንዳንድ ሁኔታዎች ለመታዘብ እንደሞክርኩት የተነገረበት ዋናው ዓላማ ክስተቱ እንዳይታወቅ፣ ለወግና ለታሪክ እንዳይበቃ የመፈለግ ነው። በተለይ በይፋ ከሚታመነው ኃይማኖት ጋር ይጋጫል ብለው ስለሚያስቡና ከዚሁ ሃይማኖት ውጪ ያሉ እምነቶችም እንደ ጣኦት አምልኮና እንደ አጉል እምነት ስለሚቆጠሩ፣ ጉዳዩን በልባቸው እያወቁ ሲጠየቁ እንደማያውቁት መናገርና ይኸ ከወንጌል የሚቃረን አጉል ልማድ ነው። ድሮ ቀርቷል በማለት የመፍራትና ጠያቂውንም የመጠራጠር ሁኔታ ነበር።

ቤተሰቦቼና ዘመዶቼ በጣም አዘውትረው ይመክሩኝ የነበረው፣ "ይህ ርዕስ ለህይወትህ አደገኛ ነው። ከህብረተሰቡ ጋር ያጋጭሃል፤ ከሰውም ጋር ያራርቅሃል፤ ደብተራን ቀርቦ መለየት ከባድ ነው። አንድ ነገር ይሰሩብህና ዘላለም ችግር ውስጥ ትወድቃለህ" የሚል ነበር። ወደ ደፍተራ የሚሄድ፣ ከደብተራ ጋር የሚታይ፣ ስለ 'አጉል እምነት' የሚጠይቅ ሰው በአካባቢ በጥርጣሬ ይታያል። አንተም ቢሆን ውስጠ ነገሩን ለማወቅ ይከብድሃል። ብዙ የሆነ አሰራርንና አካሄድን የሚከተል የተወሳሰበ ገጽታ ያለው አደገኛ ዘርፍ ነው። አትሞክረው ይቅርብህ ብለው ከማበራታት ይልቅ እንድተወው አጥብቀው ይመክሩኝ ነበር።

ጉዳዩን ከወንጀል ጋር እያያያዙ እንድፈራና እንድተወው ይመክሩኝ የነበሩ ሰዎችም አጋጥሞኛል። ሰላይ ነህ ከሚለው ጀምሮ፣ "በአንድ በኩል አጉል ልማድ ነው ትላላችሁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እናጥናው ከውስጡ ጠቃሚ ነገር አለው ብላችሁ ትመጣላችሁ። እርስ በርሱ የሚያጋጭና የሚቃረን ነገር አትናገሩ። ይኸ ነገር ስንገምት እንደ 'እያንጓለለ'[11] ልታደርጉን ነው፣ ለምን በእንጀራችን ትመጣለህ፣ ከሰዎች ጋር ለምን ታጣላናለህ፣ ለምን አትተውንም" በማለት የሚያማርሩ ሰዎችም

[11] በወቅቱ በጥንቆላ ስሙ ተነስቶ የነበረውና የመገናኛ ብዙኃን ሳይቀሩ ጉዳዩን ያራግቡት የነበረው ታምራት ገለታ፣ እያንጓለለ የሚለው የሚዜቃ ክሊፕ ተዘጋጅቶለት ስለነበር ያንን ማለታቸው ነው።

አጋጥመውኛል። ያለ ሰዓት ስለመንፈስ አይወራም። መንፈስ የሚጠራበት ጊዜና ቦታ አለው። የተረጋጋውን መንፈስ ቀስቅሰህ አስቆጥተህ መከራ ታመጣብናለህ። በማንኛውም ቦታና ጊዜ ስለዚህ ሃይል መነጋገር አይቻልም በማለት ለቃለመጠይቅ የተመረጡ ሰዎች ለውይይት የተያዘውን ቀጠሮ ይሰርዙብኝና ለመገናኘትም ፈቃድ ይከለክሉኝ ነበር።

በተለያዩ መናፍስት ተጠቅተው ሰፊ ታሪክ ያላቸውን ሰዎች ለመጠየቅ በምሄድበት ጊዜ መረጃውን ለመስጠት ፍቃደኛ አይሆኑም። ለምን እንደምፈልገው በማስረዳት ለማግባባት ስሞክር የሚነግሩኝ አንድ ጉዳይ ነበር። የዚህ ጉዳይ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ብዙ የተዳፈነና የሚፋጅ ታሪክ ያላቸው ናቸው። አንዳንዶቹ የሚደርስባቸው ታሪክ ለሰሚው ግራ የሚያጋባ፣ ነውር የሆነ፣ ከተለመደውና ከዘውትሩ የሰው ልጆች ችግር የወጣ፣ በሰዎች ዘንድ ልዩ ግምት የሚያሰጥና ተቀባይነትን የሚያሳጣ፣ ክብርንም በእጅጉ የሚነካ በመሆኑ፣ ይህንን ገመናቸውን አሳልፈው መስጠት አይፈልጉም። ባለታሪኮቹ ይህ ገጠመኛቸው ቢወጣ ማህበረሰቡ ያገለናል፣ ይርቀናል፣ ይጸየፈናል ብለው ይሰጉ ነበር። የጉዳዩ ሰለባዎች በብዛት በሚለፈልፉ፣ ታሪካቸውን በሚናዘዙ ሰዓት ሰብአዊ ክብርን የሚነኩና በሰዎች ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት የሚያሳጡ ታሪኮች በመሆናቸው ያህንን ለመንገርም ሆነ ለማስቀረጽ ፍቃደኞች አይሆኑም። ለመናገር ቢፈልጉም እንኳ ጥንቃቄ ያበዛሉ፣ ታሪኩንም ሙሉ በሙሉ ለመተረክም ድፍረት ያጣሉ።

ሌላው ያጋጠመኝ ፈተና መረጃዎቹን የማግኘት ነው። አንዳንድ ጥበቦች በምስጢር ካልተያዙ ስለሚረክሱ በእነሱ ዙሪያ መረጃ አናወጣም የሚሉ ሰዎችም ነበሩ። ግቢሩን እየተናገሩ፣ ስለ ዕፁ አይነት አለመግለጽ፤ አንዳንድ ድግምቶቹን ደብቆ የመያዝ፤ ዕፆችን እንዴት እንደሚያዘጋጁት ለመናገር ፈቃደኛ ያለመሆን ናቸው።

መንፈስ ስበን ስለአንተ ሁኔታ ጠይቀን ፈቃድ ካላገኘን መረጃ አንሰጥህም የሚሉ ሰዎችም አጋጥመውኛል። የመንፈሱን ፈቃድ እንጠይቅ ጊዜ ስጠን፣ ስለአንተም አንዳንድ ነገር ማወቅ እንፈልጋለን ታግሰን በማለት ረጅም ጊዜ ያለሥራ እንድቆይ የተደረግኩባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ።

እነዚህን እና መሰል ችግሮች ለመፍታት ብዙ መፍትሄዎችን ለማፍለቅ ሞክሬአለሁ፡፡ ከላይ የቀረቡትን ችግሮች ምንጭ ስመረምር አንዳንዶቹ በኔ ላይ እምነት ከማጣት የሚመነጩ ናቸው፡፡ እንዲሁም እርስ በርስ ከመፈራራት፣ በጥናቴ ላይ ግንዛቤ ካለመጨበጥ፣ እከሌ ነው የነገረው ታስብለኛለህ በሚል ሚስጥር ያወጣል ብሎ ከመጠራጠር፣ የተደበቁ ምስጢሮችን ይፋ ያደርግና ግጭት ይቀሰቅሳል ብሎ ከመስጋት ነው፡፡ ይህንን ከተረዳሁ በኋላ የወሰድኳቸው መፍትሄዎችም አንዳንዶች በሂደት እየተለወጡ የሚሄዱ በመሆናቸው በአንዴ እንደማይቀየሩ ስለገባኝ ትዕግስትና ቻይነትን፣ ተስፋ ሳልቆርጥ መቀጠል እንዳለብኝ ተረዳሁ፡፡ አንዳንዶቹን ግን በሌላ መንገድ መቅረብ እንዳለብኝ ተገነዘብኩ፡፡

የመጀመሪያ ዘዴ ያደረግኩት ለእኔም ለማሰቢያ እንዲሆነኝ፣ ከማህበረሰቡም ጋር ሰፋ ያለ ትውውቅ እንዲፈጥርልኝ የቆይታ ጊዜዬን ማስረዘሙ ላይ ነው፡፡ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ከመግባት መጀመሪያ ከሰዎች ጋር መግባባት እንደሚገባ ተረዳሁ፡፡ ይህንን ለማድረግ እነዚህ ሰዎች አዘውትረው የሚገኙበትን የመዝናኛና የአምልኮ ቦታ መለየት፣ የሚቀርቧቸውን ሰዎች መግባባትና ከእነሱ ጋር አዘውትሮ መታየት ነበር፡፡ ለእዚህ ጉዳይ አስፈጻሚ በማድረግ የመረጥኳቸው ለእኔ የቅርብ ዝምድና ያላቸውንና በዘመድ ዘመድ ያገኘኋቸውን ሰዎች ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ቀስ በቀስ መንገዱን ስለከፈቱልኝ ከተወሰኑት ጋርም በአጭር ጊዜ መግባባትን ስለፈጠሩልኝ እነሱ ደግሞ በተራቸው ከሌሎቹ ጋር ቅርበት እንድፈጥር መንገዱን አመቻችተውልኛል፡፡

በተጨማሪም፣ ለሙያቸውና ለዕውቀታቸው አክብሮትና ፍቅር በማሳየት ለሌላ ነገር ያለመጣሁ መሆኔን እንዲገነዘቡ ለማድረግ ሁኔታውን አሰራሩ ላይ ከማዘውተር ይልቅ ማህበራዊ አገልግሎቱ ላይም በማተኮር ዓላመዬን እንዲረዱኝ የማድረግ ስራ እግረመንገድ እሰራ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ የነበረንን መተማመን ይበልጥ የገነባው ስለነበር በር ከፍቶልኛል፡፡ በተጨማሪም ከዳሚዎችና አንዳንድ አገልጋዮችም ዛሩን ጠይቀን ለክፋት አይደለም መልካም ሰው ነው ንገሩት አለን ብለው ስለፈቀዱልኝ አጋጣሚውን የተሳካ አድርጎልኛል፡፡

በጉዳዩ ዙሪያ መጥፎ ስዕል የሚያስይዝ ሥራ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ፍርሃት ባደረባቸው ዘርፍ ላይ ማለትም የቡዳን መንፈስ የክፉ አይን እሳቤ በሚል ርዕሰ ጉዳዩን ትንሽ "ዲፕሎማት ሆኜ" ስያሜውን ቀይሬ፣ ፈጥኜ በመስራትም ለአካባቢው ሰው ለማቅረብ እያሰብኩ ባለበት ወቅት፣ የደብረማርቆ ዩኒቨርስቲ አንደ ሃገር አቀፍ አውደ ጥናት ማዘጋጀቱን ስለሰማሁ በዚያ ላይ እንድሳተፍ ጥሩ አጋጣሚ ፈጠረልኝ። በዚያ አውደ ጥናት ላይ ጥናቱ ተመርጦልኝ በህዝብ ፊት አቅርቤው ውዴታንና አድናቆትን ስላስገኘልኝ የነበረውን ፍርሃትና ጥርጣሬ ለመቅረፍ ችያለሁ።

ይህ ጥናት በሃገረሰባዊ እምነቶች ውስጥ ያሉ ልዕለ ተፈጥሮ ሃይሎች የሚገለጹባቸውን አውዶች፣ የሚቀርቡባቸውን ምክንያቶች፣ በሚከሰኑ ጊዜ ተሚልተው ስለሚገኙ አንዳንድ ነገሮች ማወቅ እንደሚገባና ማህበረሰቡም ለምን ለምን ማህበራዊ ግልጋሎቶች እንደሚያውላቸው ለመረዳት የሚደረግ ነው። ይህን መረጃ ለማግኘት ደግሞ ከተፈጥሮ መቼቱ ላይ በአካል መገኘትን፣ ከሰዎቹ በኩል ፈቃድ ማግኘትን በቅርብ ሆኖ መከታተልን፣ ግራ ሲያጋባ መጠየቅን ሁሉ ይፈልጋል። ስለዚህ፣ አገሬው ስሜቱንና መንፈሱን ስለሚገልጽባቸው፣ በባህሉ ውስጥ ስላሉ ልዩ ልዩ እምነታዊ እውቀቶች በቂ መረጃ በመሰብሰብ ጥናቱ ምልዑ እንዲሆን ማድረግን በከፍተኛ ሁኔታ ይፈልጋል።

እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ፣ እያንዳንዱ ተመራማሪ ለጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደጥናት ክልሉ ከመሄዱ በፊት ቀድሞ ሊያከናውናቸው የሚገቡ በርካታ ስራዎችን እንዲያቅድ ያስገድዱታል። ከሚያቅዳቸውም መካከል፣ ስለአካባቢው ማህበረሰብ ባህላዊና ስነምህዳራዊ ሁኔታዎች ጋር የመተዋወቅ፣ ከአካባቢው ባህልና ልማድ ጋር ሊያላምዱ የሚችሉ ሰዎችን የማፈላለግ፣ ጥሩ የመረጃ አቀባዮችን የመመልመልና የመለየት ተግባሮች ናቸው ወዘተ...። የዚህ ጥናት ባለቤትም እነዚህን ተግባሮች ስራዬ ብሎ ቀድሞ ተዘጋጅቶባቸው መሄዱ ጥናቱ ላይ በጎ ነገርን አስገኝተውለታል። በአካባቢው ተወልዶ ያደገና ከባህሉና ከልማዱ ጋር የሚተዋወቅ መሆኑ፣ ጥሩ የመረጃ አቀባይ ሊሆኑ በሚችሉ ሰዎች ዘንድ የመታወቅንና በቀላሉ የመግባባትን ዕድል አስገኝቶለታል።

በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የተገቡ የተግባቦት ስርዓቶችን በአብዛኛው ስለተገነዘባቸው፣ ማህበረሰቡ የሚያነውራቸውንና የሚቀበላቸውን ምግባሮች ለይቶ ስለተረዳቸው፣ በዚያ ዙሪያ ችግሮች በብዛት ሳይገጥሙት የመስኩን ተግባር ጨርሶ ለመምጣት ችሏል። በመረጃ አሰባሰቡ ጊዜም ከቃላት፣ ከአገላለጽ፣ ከእንቅስቃሴና ከሌሎች የተግባቦት ስርዓቶች ጋር በተያያዘ የሚታዩ አንዳንድ ተምሳሌታዊና ታካይ ሰዋሰዋዊ (extra grammatical) ምልክቶችን ለመረዳት መቻሉ በአተረጓጎም ጊዜ በእጅጉ አግዘውታል።

ነገር ግን፣ በመረጃ አቀባዮች መረጣ፣ አሰባሰብና አተናተን ወቅት ያለው መጠነኛ እውቀት መረጃውን እንዳይጫነው፣ ተጽእኖ ከሚፈጥሩ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች የጸዳ ተግባር ለመፈጸም ቅድመ ዕውቀት ይዞ ሄዶ ነበር። ስሜታዊነትንና ግዴለሽነትን በመቆጣጠር፣ አውቀዋለሁ ብሎ ከመተው በመጠንቀቅ፣ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ ዝቅ ወይም ከፍ አድርጎ ያሳያል ከሚል የግል አመለካከት በመነሳት መረጃውን ለማካተትም ሆነ ለማግለል ባለመጣር የእይታ ዝንፈትንና አድልዎን (biase) ለመቆጣጠር ተችሏል።

እምነት በባህርይው ግላዊና አከራካሪ ጉዳዮችን የሚያስተናግድ የአመለካከት ዘርፍ ስለሆነ፣ በመረጃ አሰባሰብ ጊዜ አጨቃጫቂና አሻሚ የሆኑ መረጃዎች ሊሰበሰቡ ይችላሉ የሚል ቅድሚያ ግምት ነበር። እንደዚህ አይነት ለውሳኔ አስቸጋሪ የሆኑ መረጃዎች በሚያጋጥሙ ጊዜ ታማኝነት የሚገለጸው ለማን ነው የሚል ጥያቄ ሁሉ ነበረኝ። ነገር ግን በሂደት የተረዳሁትና የተቀበልኩት የማህበረሰቡን አመለካከት ማክበሩ ላይ ነው። በመሆኑም በዚህ ጥናት ላይ ይበልጥ ተተኳሪ የሆኑት ግለሰቦች ሳይሆኑ፣ ማህበራዊ (ባህላዊ) ቡድኑ ነው። ጥናቱ በማህበረሰቡ አመለካከትና ርዕዮተ ዓለም ላይ የሚወሰን ስለሆነ፣ ተመራማሪው የማህበረሰቡን ሃሳብና ስሜት በሚገባ አክብሯል።

ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ቅዱስ የሆኑ ባህርያትን የተላበሱ፣ ምስጢራዊነት የሚበዛባቸውና በክወና ወቅትም ስርዓቶቹ በሰዓታት፣ በቀናትና በቦታ የተገደቡ ስለሆኑ፣ በመረጃ አሰባሰብ ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮች እንደሚኖሩ መገመቱ አያዳግትም። ስለዚህ፣ በመረጃ በአሰባሰቡ ጊዜ ያለፈቃድና ያለማህበረሰቡ እውቅና

አንዳችም መረጃ በድምጽም ሆነ በምስል ለመቅዳትም ሆነ ለመቅረጽ አልተሞከረም። ይህንን ክፈተት ለመሙላት መረጃዎቹ በማስታወሻ ደብተር ተይዘዋል። መረጃ በመስጠት የተባበሩ ሰዎች ከስጋትና ከተለያዩ አመለካከቶች በመነጨ፣ ማንነታቸው በምስጢር እንዲያዝላቸው ጠይቀዋል፣ ድምጻቸው ሆነ ገጽታቸው በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ እንዳይካተት ፈልገዋል። በመሆኑም፣ ያለ እነሱ ፈቃድና እውቀት በድብቅ ምንም አይነት ስራ አልተሰራም። የፈቀዱትና ያመኑበት ነገር ብቻ የምስጢር ቁጥር ተሰጥቶትና የተለዩ የስም ኮድ ወጥቶለት እኒደቀርብ ተደርጓል።

አንድ ጊዜ ከአንድ ሴት የፎክሎር ፒ.ኤች. ዲ. ተማሪ ጋር በመሆን የአውድማ ሥርዓት ለማየት የቦ ከሚባል የገጠር መንደር ሄደን ነበር። ከአውድማ መልስ ቡና ጠጡ ተብለን ከአባወራው ቤት እንገባለን። የአባወራው ባለቤት በመልካም ተቀብለው ምሳችንን አብልተው ቡና አፍልተው፣ በቆሎ ጠብሰው ያስተናግዱናል። በአንዳንድ ጉዳዮች ውይይት አንስተን ስንጫዎት ሳይገባን ቁስል ነካክተን አባወራና ሚስት አታካራ ውስጥ ይገቡብናል። አብራኝ የነበረችው ጓደኛዬ ፈጥና ስጦታ አለኝ ብላ የያዘችውን ሻርፕ አውልቃ፣ "ይቺን ጠዋት ጠዋት ሲነሱ ፊትዎን ውርጭ እንዳይመታው ይሸፍኑበት" ብላ ስትሰጣቸው ግጭቱ ወደ ሌላ አቅጣጫ መልኩን እንደቀየረ አይረሳኝም። እኛም ተሳስቀን ሰውዬውን እንዲመርቁት በማድረግ ነገሩን በመልካም ነገር ቀየርነው።

አንድ ጊዜ ደግሞ ስንቀርጽ ውለን ከተመለስን በኋላ ሰውነታችንን ታጥበን ልብሳችንን ቀያይረን እራት ለመብላት ልንወጣ ስንል ምናልባት ሰው ብናገኝ መቅረጸ ድምጿን እንያዛት ተባብለን እኔ በኪሴ ይዜ ጉቦ እንዳርጋለን። እራታችንን በልተን ከሌላ ሰው ጋር ሳንገናኝ ወደ መኝታ ክፍላችን እንመለሳለን። ጠዋት ላይ "ቻርጅ" ለማድረግ አስቤ ኪሴን ስፈትሽ መቅረጸ ድምጿ ከኪሴ የለችም። ኪሴን ስፈትሽ ቀዳዳ እንዳለው ተረዳሁ። ማታውኑ የተንቀሳቀስንበትን መንገድ ተከትለን ብንፈትሽ ልናገኛት አልቻልንም።

በእርግጥ ሁልጊዜ የቀረጽኩትን መረጃ ፈጥኜ ወደ ላፕቶፔ የመገልበጥ ልማድ አለኝ። ነገር ግን፣ በቀጣይ መረጃ የምሰበስብበት ተጨማሪ መሳሪያ አልያዝኩም

ነበር። ከሁሉ በላይ ያሳሰበኝ የመረጃ ሰጪዎቼ ብዙ ገመናዎች ባልሆነ ሰው እጅ ይገባል የሚለው ፍርሀቴ ነበር። ሙሉ ስማቸውንና ቀበሌያቸው ሳይቀር ተቀርጸ ስለነበር፣ ሊያጋልጣቸው ይችላል ብዬ ፈራሁ። በመሆኑም፣ ቁጭ ብለን ማድረግ ስላለብን ነገር መወያየት ጀመርን። በመጀመሪያ የመጣልን ሃሳብ፣ በጠዋት ሊንቀሳቀስ የሚችለውን ሰው ለይቶ በዚያ አካባቢ እንድንፈለግ ነበር። ጠዋት ተማሪዎችና የቤተክርስትያን ሰዎች መንቀሳቀሻ ሰዓት ነው። ተማሪዎችና ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄዱ በመሆናቸው በቅርብ ወዳሉ ትምህርት ቤቶችና አብያተ ክርስትያኖች በመሄድ እንዲያፈላልጉልን ነገርን።

ይሸንን ሞክረን አልተሳካልንም። በቀጣይ ከመምህራን ጋር ስንወያይ አንድ መላ ለገሱን። "ወደ ቀበሌ ሂዳችሁ፣ በማይክራፎን እየተዘዋወሩ እንዲለፍፉላችሁ አድርጉ" የሚል ነበር። የቀበሌ ሊቀመንበሩን አግኝተን ስናማክረው ተባበረን። ከዚያም፣ ለመንግስት ሥራ ከአዲስ አበባ እንደመጣን፣ ለከፍተኛ ሥራ የሚፈለግ መረጃ የያዘ መቅረጸ ድምጽ እደጠፋብን፣ ለእነሱ ምንም እንደማይጠቅም፣ ወድቆ ያገኘ ቢመልስልን ወረታውን የምንከፍል መሆኑን ገልጸን አስለፈፍን። በተወሰኑ ደቂቃ አገኘሁ የሚል ሰው ተጠቁመን መቅረጫውን በእጃችን ልናስገባ ችለናል።

የቅርብ ዘመዴ የሆነ አንድ ሰው መረጃ ለመሰብሰብ ወደ የጥጃን ስሄድ "ወንቃ" የሚባለውን የገጠር ቀበሌ ማየት አለብኝ ብሎ አብሮኝ ይሄዳል። ቃለመጠይቅ ከማደርግላቸው ሰው ጋር የተቀጣጠርነው እሁድ ቀን ከጊዮርጊስ ቤተክርስትያን ከቅዳሴ ውጪ ነበር። በመሆኑም፣ ቅዳሴ ሳይገቡ ደርሰን የአካባቢውን ሰው መስለን ሰው የሚያደርገውን እየተከተልን ሥርዓቱን ስንፈጽም ቆየን። ከዚያም ቅዳሴው ሲያልቅ መክፈልት እየተዞረ መታደል ተጀመረና ለእኔም ለጓደኛዬም ተሰጠን።

ይሽ ልጅ ቤተክርስትያን የመሄድ ልምድ አልነበረውም እና መክፈሉን እንደተቀበለ ቆርሶ ሲጎርስ እኔና ከአጠገባችን የተቀመጡ አንድ አባት ድንገት እናየዋለን። በዐይኔ ስቆጣው እንደጎረሰው ደንግጦ ሳያላምጥ አፉን ገጠመው። ከዚያም ሰውዬው እንግዳ መሆናችን ስለገባቸው አይናቸውን መለስ ሲያደርጉ ሳያላምጥ ዋጠውና ምንም እንዳልተፈጸ ሆነ። ከዚያም፣ አቡነ ዘበሰማያት ተሰጥቶ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA

ሰው ሁሉ መቅመስ ሲጀምር አብረን እኛም ቀመስን። ሁኔታውን ለእናቴ ነግረናት "እናንተ አሕዛቦች" ብላ ሰደበችን።

ከአንድ ቄስ ጋር በንስሐ ዙሪያ ለመወያየት ቤተክርስትያን ተቀጣጥረን ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ እሄዳለሁ። ሰውዬውን ለማስደሰት አሮጌውን ማተቤን በጥሼ በወጉ ሊታይ የሚችል አዲስ ማተብ አስሬ ነበር። ማተቤ እንዲታይ አድርጌ ነበር ያደረግኩት። ከዚያ በቀጠርኳቸው ሰዓት በማግኘቴ ተደስቼ፣ ሥርዓቱን ጠበቁ ከተሳለምኩ በኋላ ለውይይት እንዲመቹን ከፊታቸው ተቀምጬ ስለጥናቱ ዓላማ እያስረዳኋቸው እያለ አይናቸውን ከማተቤ ላይ ተክለው አልነቅል ይላሉ። እኔም ግራ ተጋብቼ ብዙ ከቀባጠርኩ በኋላ አንድ አስደንጋጭ ጥያቄ ጠየቁኝ። "ማተብዎ አዲስ ነው፣ ዛሬ ወደእኔ ሲመጡ ነው መሰል ገዝተው ያሰሩት" በማለት ይጠይቁኛል። እኔም ሳልዋሽ እውነቱን ነገርኳቸው። እንዳይጠራጠሩም ብዬ የወገኖቼን ስም እየጠቀስኩ እርግጠኛ እንዲሆኑ ለማግባባት ሞከርኩ። ያመኑ ሲመስለኝ፣ ጥያቄ ማቅረብ ጀመርኩ። ለጠየኳቸው ጥያቄ ተጠንቅቀው መለሱልኝ። ግን ያመኑኝ አልመሰለኝም።

በአንዳንድ ከፍርድ፣ ከአደራረግና ሌሎችንም ተምሳሌቶች ለመተርጎም የሚያስችለኝን ቅርጽ ለማየት ፈልጌ የዛር ፍርድ በሚከናወንበት ስርዓት ላይ ለመሳተፍ ፈለጌ አንድ ያጎቴን ልጅ አማክረዋለሁ። ምንም ችግር የለም ማክሰኞ ማታ "ካሱ" ቤት ይገፍሀ እሄዳለሁ ይለኛል። እኔም ተስማምቼ ዝግጅት ሳደርግ፣ የስርዓቱን ሁኔታ ስጠይቀው ሰንብቼ ቀኑ ደረሰ። በር ላይ አውላ እየጠጣን ነው የምንገባ። አውላው የዛረ ፈረሱ እግር የታጠበበት ነው ይባላል። እና ጨለማ ስለሆነ የምትጠጣ መስለህ በልብስህ ልቀቀው ብሎኛል። ከዚያ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ወደ ካሱ ቤት ጉዞ አደረግን። በር ላይ አንዲት ሴት በትንሽ ፅዋ አውላ ይዛ ጠጡ አለችን። እኔ የሴትዬዋ እግር እጣቢ መሆኑ ትዝ ሲለኝ ሽቅብ ሊለኝ ሞከረ እንደምንም ራሴን አሳምኜ ወደ ከንፈሬ አስጠግቼ በጋበዬ ላይ ለቀቁት። ልጅቱ አይታኛለች። ግን፣ አክብራኝ ይመስለኛል ዝም አለችኝ። ዝምታዋን ተጠራጥሬው ስለነበር ቁጭ ብለን እስከምንወጣ ድረስ እንቅስቃሴዋን ሁሉ

እከተታለው የነበረው በጥንቃቄ ነበር። በሕይወቱ ዐይኔ እንደ በራች የነጋችበት ቀን ብትኖር ያች ቀን ነች።

4. መልክዐምድራዊ፣ ማህበራዊ ፣ ታሪካዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በምሥራቅ ጎጃም

በዚህ ምዕራፍ ስለጥናቱ አካባቢ መልክዐምድር፣ ታሪክ፣ ማህበራዊ ህይወት፣ እሴቶች፣ ማህበራዊ አደረጃጀቶች፣ የብሔርና የሃይማኖት ሁኔታ፣ የህዝብ ብዛት፣ አኗኗርና ሃይማኖት በሰፊው ተዳሷል።

4.1. የመልክዐ ምድራዊ ገጽታ ማስተዋወቂያ

የጎሳምን ወረዳ፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ አሥራ አንድ ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን፣ የሚገኘውም በምስራቅ ጎጃም መስተዳድራዊ ዞን ውስጥ ነው (ጎወግጽ, 2006).። ይህ ወረዳ በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ አሥራ ስምንት ወረዳዎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ በ25 የገጠር ቀበሌና በአንድ ንዑስ ታዳጊ ከተማ ተዋቅሮ ይገኛል። ወረዳውን በሰሜን ስህናንና ደባይ ጥላንት ግን፣ በደቡብ ደብረ ኤልያስ፣ በምስራቅ አነደድና ባሶ ሊበን ወረዳዎች ያዋስኑታል (ጎወግጽ, 2006) ።

እንደ ምስራቅ ጎጃም ዞን ግንዘብና ኢኮኖሚ ልማት 2004 ዓ.ም ሪፖርት፣ የወረዳው የቆዳ ስፋት 1217.8 ኪሜ ስኩዌር ወይም 121780 ሄክታር ይገመታል። መልካምድራዊ አቀማመጡ ከፍተኛው ቦታ 16%፣ ተራራማው 9%፣ ሜዳማው 74%፣ ሸለቋማው ደግሞ 1% ነው (ምጎግኢልመ, 2006)። የወረዳው አብዛኛው አካባቢ ወይና ደጋ የአየር ጠባይ የሚሰማው ሲሆን፣ ከወረዳው የቆዳ ስፋት 74% በዚህ የአየር ንብረት ዞን የተካተተ ነው። ቀሪው 9% ደጋ ፣ 16% ቆላ እንዲሁም 1% ውርጭ ጠባይ በቅደም ተከተል የሚሸፍኑ ናቸው (ጎወግጽ, 2006)።

የወረዳው የግብርና ጽ/ቤት ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ እነዚህ የአየር ንብረቶችና የቦታ አቀማመጦች የሚያበቅሏቸው ዋና ዋና ሰብሎች በቆሎ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ኑግ፣ ተልባ፣ ገብስና ማሽላ ናቸው (ጎወግጽ, 2006)። የወረዳው ዓመታዊ የሙቀት መጠን ዝቅተኛው 7.5ና ከፍተኛው 25 ዲ.ሴ. ሲሆን፣ የዝናብ መጠኑ ከ900 እስከ 1800 ሚ.ሜ. እንደሚደርስ ይገመታል (ጎወግጽ, 2006) ።

ወረዳው ከውሃ ጠለል በላይ ከ4000 እስከ 15000 ሜትር የሚደርስ የከፍታ አቀማመጥ ያለው ሲሆን፣ ይህ ገጽታ አካባቢውን የተለያዩ የአየር ንብረቶች እንዲሰሙት ያደረገ ነው። ዞኑን በመክበብ ትልቅ ስምጥ ሸለቆ የሰራው የአባይ ወንዝ እና በዞኑ በአማካይ ቦታ ላይ ደረቱን ስጥቶ የሚታየው ትልቁ የ "ሮሙቄ" ተራራ አካባቢው በአየር ንብረቱ የተለየ እንዲሆን ያደረጉ ተፈጥሯዊ ክስተቶች ናቸው። በወረዳው ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ 23 ዋና ዋና ወንዞችና ከ60 በላይ ምንጮች እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በወረዳው የአባይ ተፋሰስ የሆነውና ርዝመቱ 45 ኪ.ሜ የሚረዝመው የጨሞጋ ወንዝ በዚሁ ወረዳ ይገኛል (ጎወግጽ, 2006)።

በጎዛም ወረዳ ሰፍሮ የሚኖረው ሕዝብ 168,082 እንደሆነ ይገመታል። ከእነዚህ ሰፋሪዎች መካከል የሴቶች ብዛት 51.49% ሆኖ ተጠቅሷል (CSA, 2007)። ከአጠቃላይ ነዋሪው መካከል 1.93% የከተማ ነዋሪ ነው። የሕዝቡ ጥግግት በአንድ ስኪዌዬር ኪ/ሜ 109 ሰው እንደሆነ ይገመታል። ይህም ከዞኑ አማካይ179.96 ያነሰ ሆኖ ተገኝቷል። በወረዳው የሚኖረው ሕዝብ የአማራ ብሔር ተወላጅ ሲሆን፣ ሁሉም አማርኛን በአፍ መፍቻነት የሚናር ነው(ጎወግጽ, 2006),።

4.2. የጎጃም ሰዎች የአሰፋፈር ታሪክ

ከአሥራ አራተኛው መቶ ክ/ዘመን ቀደም ብሎ ስላለው የጎጃም ታሪክ የሚያስረዱ የታሪክ መዝገቦች ያሉ አይመስልም (Habtamu, 2003, 7)። በ13ኛውና በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ስለነበረው ሕዝብ የሚያትቱ አንዳንድ የታሪክ ሰነዶች ተገኝተዋል። እነዚህ ሰነዶች፣ በምሥራቅ ጎጃም አካባቢ ሰፍረው ይኖሩ ከነበሩ ሕዝቦች መካከል አብዛኛዎቹ የአገው ማኅበረሰቦች መሆናቸውን የሚመሰክሩ ናቸው። የዛሬው የሃገራችን ሰሜናዊ ክፍሎች የአገውኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች መኖሪያ ቦታ እንደነበሩ የሚመሰክሩ ናቸው (ባዬ ይማም፣ 2001፣ V)። በአካባቢው እስካሁን ድረስ የሚነገሩ ቃላዊ ትውፊቶችና መጠሪያዎች፣ የታሪክና የስነልሳን ማስረጃዎች አገዎች ከአማራዎች ቀድመው መስፈራቸውን የሚጠቁሙ ናቸው። "አገው ባድማ"፣ "አገው መሬት"፣"አገው በረት"፣ "አገው ካብ"፣ "አገው ምንጭ"፣ "አገው አምባ" በሚል መጠሪያ የሚጠሩ፣ ከእነሴና ከእነብሴ በስተምሥራቅ፣ ከማኽከል

በስተምዕራብ የሚገኙት እነዚህ አካባቢዎች እስካሁን ድረስ በዚሁ ስም የሚጠሩ ናቸው (Abebaw, 2002,17)።

በሌላ በኩል፣ ከጎጃም ቀዳሚ አቅኝዎች መካከል የጋፋት ትውልዶች እንደሚገኙበት የሚያስረዱ አፈ ታሪኮችም አሉ (Taddesse 1994) ። "እነዚህ አፈ ታሪኮች፣ የጋፋት አባቶች አካባቢውን አቅንተውና ርስት ጉልታቸውን መሥርተው፣ ከጥንት ጀምረው ይኖሩ እንደነበር ያስረዳሉ። አብዛኛው የምስራቅ ጎጃም ህዝብም፣ የዘር ሐረጉን ሲቆጥር የትውልድ ግንዱን ከጋፋት ይመዛል ይባላል። አለቃ ተክለየሱስ የጎጃም ትውልድ በሚለው መጽሐፋቸው ይህንን አፈታሪክ የሚያጎላምስ ነገር አስፍረው ይገኛል።

> አሥራ ሁለት ቤት ጎጃም የተባሉት አባቶች ዙሪያውን ጎጃምን ከበው የሠፈሩት ስማቸው እነማይ፣ እነሴ፣ ዳሞት፣ አገው፣ ሰብራድ፣ ጽሕናን፣ ማቻከል፣ ጎዛምን፣ አነደድ፣ ጥላትግን፣ ዋበል፣ ውድሚት ይባላሉ። እነማይና እነሴ፣ ዳሞትና አገው ጓላ ተደርበው የተሰሩባቸው። የቀሩት የጎጃም ዘሮች፣ የደረቤና የሰረቤ ልጆች ናቸው። ጋፋቶች ይባላሉ (ተክለየሱስ ዋቅጅራ በግርማ፣ 30) ።

ይህ መረጃ የሚጠቁመን የመጀመሪያዎቹ የጎጃም አቅኝዎች ጋፋቶች፣ የጋፋት ሁለቱ ልጆቹ ደግሞ "ደረቤ" ና "ሰረቤ" መሆናቸውን ነው። ከአንዳንድ ቦታዎች የተሰበሰቡ አፈታሪኮች ሰረቤንና ደረቤን ተቀብለው አባት ለተባለው "ጋፋት" ግን ዕውቅና ይነፍጋሉ። ይህ አፈታሪክ የሚያወሳው፣ "ሰረቤና ደረቤ የሚባሉ ሁለት ወንድማማቾች ከየት እንደመጡ ሳይታወቅ ዛሬ ብቸና ተብሎ በሚታወቀው አገር ይኖሩ እንደነበር ነው። በኋላ ሁለቱ ወንድማማቾች ጎጃም የተባለውን አካባቢ ለሁለት ተካፈሉ። ሰረቤ ዳሞትን ያዘና የምዕራብ ጎጃም ሕዝብ ቅድመ አያት፣ ደረቤ ደግሞ ምሥራቁን ክፍል አቅንቶ የምሥራቅ ጎጃም ሕዝብ ቅድመ አያት ሆነው ተተከሉ" የሚሉ ናቸው (Yehenew, 1996, 25)።

አንዳንድ የሃገር ሽማግሌዎች "ዛሬ ጎጃሞች ተብለው የሚጠሩት የመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከኢየሩሳሌም የመጡ ናቸው ይላሉ (Yehenew, 1996, 25) ። ግን፣ Taddese Tamrat (1988) ጋፋቶች በጎጃም ውስጥ ከአባይ

ወንዝ በስተደቡብ አቅጣጫ የሠፈሩት ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ባለው ጊዜ ነው በማለት አፈ ታሪኩን ያስተባብላሉ።

ከአክሱም ዘመነ መንግስት ጀምሮ እስከ 16ኛው መቶ ክፍል ዘመን አጋማሽ ባለው ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ግዛትን ለማስፋፋት የተደረገው እንቅስቃሴ፣ የደቡብን አቅጣጫ የተከተለ እንደነበር ይታወቃል። ስልጣን ከዛጉዌዎች እጅ ወጥቶ በድጋሚ ወደሰለሞናዊው ሥርዎ መንግስት ሲገባ፣ ይህ የማስፋፋት እንቅስቃሴ ይበልጥ ተጠናክሮ እንደነበር ታሪክ ይነግረናል። ለዛሬው የምስራቅ ጎጃም አካባቢ የክረስትና ታሪክ መሠረቱ፣ ዳግም ስልጣን ወደ ሰለሞናዊ መሸጋገሩና አፄ አምደ ጽዮንም (1314-1344) ዙፋኑን መረከባቸው እንደሆነ Abebaw ምንጭ ጠቅሰው ያስረዳሉ (2002, 18) ።

Taddese (1974, 189-190) የሥርዎ መንግስቱን ሽግግር ተከትሎ የመጣው የፖለቲካ ማዕከል ለውጥ ወደ መሃል አገር (ማለትም ከላስታ ወደ ሸዋ) መዛወርና ለመስራቅ ጎጃም አካባቢ መቅረብ፣ አካባቢው በፖለቲካው እንቅስቃሴ ውስጥ ለመግባቱ አሳይ ምልክት ነው ይላሉ። ይህንን ለማስፈጸምም ማኅበረሰቡ የክርስትናን ሃይማኖት እንዲቀበል ተደርጓል። በመሆኑም፣ ሃይማኖቱ የፖለቲካ ሚና ለመጫወት መንገድ ጠራጊ ሆኖ መምጣቱን ልብ ይሏል።

ይህ ታሪካዊ አጋጣሚ በአካባቢው የክርስትና እምነት እንዲተዋወቅ መንገድ የከፈተ ነው። በዚህ ዘመን አካባቢውን ክርስቲያን ለማድረግ ሁለት አይነት እንቅስቃሴዎች ተካሂደው እንደነበር ይነገራል። የመጀመሪያው ሙከራ፣ ወንጌላውያንን ወደ አካባቢው በመላክ በአስተምህሮትና በስብከት መመለስ የሚል ሲሆን፣ ይህ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞት ውጤት ሳያመጣ መክኖ የቀረ ነበር(Taddesse in Habtamu, 2003, 7)። ይህን ጠንካራ ተቃውሞ በዘላቂነት ለመቀልበስ የተቀየሰው ሁለተኛው አማራጭ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ክርስቲያን የሆኑ የአማራ ነገዶችን ከዛሬው ሰሜን ሸዋና አጎራባች አካባቢዎች አምጥቶ በማስፈር በነባር ሰፋሪዎች ላይ ተጽእኖ መፍጠር ነበር። Habtamu (2003, 7)በ14ኛው እና በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ በርካታ ዘውጌ ማህበረሰቦች ወደ ምሥራቅ ጎጃም እንደገቡ የሚያስረዱ ቃላዊ ትውፊቶች

መኖራቸውን ይመሰክራሉ ። ይህ ስልት ግቡን የመታና በአካባቢው ማህበረሰብ የእምነት አቀባበልና ማህበረ ኢኮኖሚ ላይ ተጽእኖ የፈጠረ አጋጣሚ ነው ይባላል (Habtamu, 2003, 8)። የአካባቢው ማኅበረሰብ ክርስትናን መቀበሉን ተከትሎ በርካታ አብያተ ክርስትያኖች ተገንብተዋል። ይህን እንቅስቃሴ ተከትለው ከተገነቡት መካከል ዲማ ጊዮርጊስ፣ ደብረወርቅ እና መርጡለ ማርያም ይገኙበታል (Habtamu, 2003, 7) ።

የክርስትና ሃይማኖትን ያመልኩ የነበሩ የአማራ ነገድ ሡፋሪዎች ወደ ጎጃም መጥተው አካባቢውን የተቆጣጠሩት ከሴማዊ ባህላቸውና ሃይማኖታቸው እንዲሁም ይተዳደሩበት ከነበረው የኑሮ ዘይቤአቸው ጋር ነበር (Habtamu, 2003, 8) ። ቀስ በቀስም ክርስትያን ያልሆነው የአገው ህዝብ በክርስትያን አማሮች እየተገፋ፣ ባህልና ልምዱ ሊላ መልክ እየያዘ፣ ቋንቋውና ይዞታው በሌላ ነገድና ሃይል ተጽእኖ ውስጥ እየወደቀ ሄዷል (Abebaw, 2002፣ 5)። ነባሮቹ ማለትም አገዎች፣ መጤው ማህበረሰብ ሲጠጋቸው ሲሸሹ፣ ሲቀርባቸው ሲርቁ ሃይላቸው እየተዳከመ ሄዶ በባህላቸውና በሃይማኖታቸው ላይ የበላይ እንደሆነባቸው ያስረዳሉ (Abebaw, 2002, 5) ።

በአካባቢው "አገው ሲነቀል ጨዋ ሲከተል"፣ "አገው ሲሰደድ፣ አማራ ሲለምድ" የሚሉት አባባሎች ይህንን እውነታ የሚገልጹ ስለመሆናቸው አበባው ያስረዳሉ (Abebaw, 2002, 7)። በአካባቢ ብዙ ነገዶች መኖርም፣ በመሬት፣ በግዛትና በሥልጣን ጥያቄ ምክንያት ባላንጣነት ተፈጥሮበት። በቦታው ላይ የሃይሎች ውዴታ እንዲያድርበት ያደረገው ስትራቴጅክ የሆነ ለምና ሰፊ ምድር በመሆኑ ነበር። በውጊያው ሲሸናነፉ የኃይል የበላይነት ያለው አካል መሬቱን በመቆጣጠር ነባር ሰፋሪውን ያፈናቅላል። ሃይል አልባው ተፈናቃይ ወገን ለእርሻ ተግባር የማይመቸውን ቦታ መርጦ በተወሰኑ መንደሮች ላይ ይሰፍራል።

ህይወቱን ለማስቀጠልም ዕደ ጥበብን መተዳደሪያ አድርጎ ይይዛል። የዚያን ዘመን በአካባቢው በዕደ ጥበብ ሙያ ተሰማርተው የነበሩ ባለእጆች የጋፋት ማህበረሰብ ርዝራዦች እንደነበሩ በአለቃ ተክለየሱስ በመጽሐፋቸው ውስጥ ተገልጸ ይገኛል (አለቃ ተክለየሱስ በግርማ፣ 2003፣ xxxiv) ። ነገር ግን፣ የክርስትና እምነት ወደ

ደቡብ (የካፊው ሽዋና) ወደ ደቡብ ሰሜን ምዕራብ ጎጃምና የጣና ሐይቅ አካባቢ የተስፋፋውና በጽኑ መሠረት ላይ እምነቱን የተከለው፣ በዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት ማለትም በ15ኛው መቶ ዓመት ላይ ነበር (ባሕሩ ዘውዴ፣ 2000፣ 7) ።

አካባቢው ክርትናን መቀበሉን ተከትሎ የተገነቡት ትልልቅ ቤተክርስቲያኖች በግራኝ መሐመድ ወራር ምክንያት ሊወድሙና ሊፈራርሱ ችለዋል። በዚህም ዘመን በተሰመዘረው ጥቃት ቤተክርስትያን አቅሟ ሊዳከምና ሃብቷ ሊጠፋ ችሏል። የግራኝ መሐመድን ወረራ ተከትሎ በርካታ ቁጥር ያላቸው የኦሮሞ እንቅስቃሴዎች ደግሞ በተራው የበለጠ ጫና ፈጥሮ ያለፈ ክስተት ነው (Habtamu, 2003, 8) ።

4.3. የማህበራዊ ማንነት አገነባብ

Guetzkow ማንኛውም ማህበራዊ ቡድን በዋናነት የሚመሰረተው የአባላቱን ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ጥቅም ለማስከበር the members of social units obtain satisfaction of their economic, cultural and poltical needs through participation in social group ነው ይላሉ (1957, 49)። አባልነትም በስሜትና በፍላጎት ከሚገጥመው ቡድን ጋር ጥቅምን ለማግኘት የሚመሰረት ቅርበት ነው ይላሉ (Tajfel,1972,292)። ይህንን ፍላጎት በሥርዓት ለመምራት ቡድኑ የሚመራበትና የሚገዛበት የመተዳደሪያ ደንብ ይቀረጻል፣ አኗኗርን የሚመራ መርህ ይዘጋጃል፣ ለግንኙነት ደንብና ህግ የሚሆን መተዳደሪያ ደንብ ይወጣል። በእነዚህ መመሪያዎች ውስጥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶችን ለማርካት የሚያስችሉ እሴቶች በውስጥ ይካተታሉ። እየተወለደ የሚያድገው እያንዳንዱ የማህበረሰቡ ክፍል የህብረተሰቡ አባል በመሆኑ እነዚህን ቀኖናዎች እየተማራቸውና እየለመዳቸው እውቀትና እምነት የሚያደርግበት መንገድ ይዘየዳል። ስለዚህ፣ እነዚህን ማህበራዊ ማንነቶች በዝርያ (ascribed identities) ከምንወርሳቸው በላይ በመኖር፣ በመልመድና በማድረግ ገንዘብ የምናደርጋቸው በሥርዓት የተደራጁ ወሳኝ ሃብቶች ናቸው።

ሰዎች በልዩ ልዩ ማህበራዊ አደረጃጀቶች ራሳቸውን ይቦድናሉ። አንዳንዶቹ በድርጅት አባልነት፣ በሃይማኖታዊ ተቋማት መሪነት፣ በጸታና በዕድሜ በሌላም

መንግድ ራሳቸውን ያዋቅራሉ (Tajfel & Turner, 1985) ። የኅዛምን ማኅበረሰብ እንደ አንድ ማኅበራዊ ቡድን እንዲታሰብ የስነልቦና ሚካፕ በመፍጠርና አንድ አይነት አመለካከት በማስገንት በኩል አስተዋጽኦ ያደረጉ የማንነት መገንቢያ መንገዶች እንዳሉት አንዳንድ በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የጋራ ልምዶች

የጋራ ገጠመኞች በሰዎች ጠባይና ልምድ ውስጥ ተጽእኖ ፈጣሪ ኃይሎች ናቸው (Guetzkow, 1957)። በአንድ አይነት የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ የጋራ ህይወትን ማሳለፍ፣ አድካሚ ወይም ምቹ ገጠመኝ መጋራት፣ የወጡ የወረዱበት መንገድ መመሳል፣ በጋራ የተደሰቱ የተቸገሩበት ሁኔታ መኖር፣ በአንድ መንገድና አይነት ሁኔታ ማሰብንና በነገሮች እና በክስተቶች ተመሳሳይ አረዳድ ማያዝንና በእይታ መቀራረብን ያመጣል ይላሉ (Hoelscher, 2003)። ማህበራዊ አኗኗር የገጠመኞች ውጤት እንደመሆኑ ለሥርዓቶች ሁሉ መነሻ የሆነ ነገር የሚገኘው በዚህ መልክ ከሚጠራቀም ልምድ ነው። የደረጁ ልምዶችና ተደጋጋሚ ገጠመኞች የሚፈጥሩት በይሆናል ከተገኙ ዕውቀቶች ሳይሆን በተግባር ከተፈተሸና ውጤታቸው ከተመዘኑ ተጨባጭ እውነታዎች ነው።

የምሥራቅ ጎጃም ሕዝብ በአንድ አካባቢ በመኖሩና በመፈጠሩ ምክንያት በህይወት ጉዞው ውስጥ የተጋራቸውና የተካፈላቸው ገጠሞኞችና ታሪኮች አሉት። በእነዚህ ባለፉ ታሪኮቹ ያገኛቸው ተሞክሮዎቹና ከተሞክሮዎቹ ፈልፍሎ ያወጣቸው እይታዎቹ በማንነቱ አገነባብ ላይ ወሳኝ እርሾዎቹ ሆነዋል ይላሉ አቶ ቻላቸው (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በዘላቂነት የሚጎዱትን ከማይጎዱት በመለየት፣ ሊያስወግዳቸውና ሊከላከላቸው የሚችሉትን በማወቅ፣ ሊላላና ሊጠብቅባቸው አነውሮና ተጸይፎ ሊይዛቸው ስለሚገቡ ነገሮች ሁሉ በመንገር ሰፊ ልምድ ሆነውታል (አቶ ቻላቸው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በዘላቂ አሳሳቢና የህይወት መስመሩንና የትውልዱን ጉዞ ያበላሸብኛል ያላቸውን ቋሚ ፈተናዎቹ እንዲለይ፣ ለይቶም ሥርዓትና ደንብ እንዲያቆምላቸው አስተምረውታል።

አብዛኛው የጎጃም መስፍን ለአካባቢው ሰው የሚመች፣ እንዳይከፋው፣ እንዳያዝንና እንዳይበደል በማለት የሚጠነቀቅ የሚያስብ እንደነበር ጎሩይ ወልደ ሥላሴ ጽፈውት ይገኛል (2001፣ 47)። ሕዝቡም ወገኖቼ ናቸው ብሎ ስላመነ በደሉን ከግለሰብ ክፋት ነጥሎ የሥርዓት ችግር አድርጎ አይቆጥረውም ነበር ይባላል (አቶ አቻምየለህ ጌታነህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) ገዥዎችም ጨዋውን ሕዝብ እንደ ባዕዳ ሳያዩ በርስትና በጉልት ተክለው፣ ወገኔ ብለው ያስተዳድሩት ስለነበረ፣ ቢበድሉት ለምዶትና ተለማምዶት ባህሉ ስላደረገው ከሚጠብቀውና ከሚያውቀው ውጭ ስለማይሆንበት ውሳኔያቸውን እንደ ነውር አይመለከተውም ነበር። ክፉ ያላላቸው በየጊዜው እየቀያየሩና እያሻሻሉ ስላላገላቱትና በለመደው መንገድ ስለገዙት ነው ይላሉ ።

አቶ ተዘራ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ የአካባቢውን ሕዝብ የፈተኑትና ክፉ የሰሩበት ከሌላ አካባቢ የመጡ ገዥዎች ነበሩ ይላሉ ። እነዚህ አካሎች እየተመላለሱ ከፍ ያለ ግፍ ፈጽመውበታል። ሃብት እንዳያፈሩ ያራቁቱት፣ ሰላምና ፋታ አግኝቶ እንዳይኖር ያውኩት፣ ሰላማዊ ህይወት እንዳይመራ ይረብሹት፣ እርስ በርስ እንዲጠቃቃና እዳይስማማ ያናቁሩት፣ አንድ እንዳይሆን ባልናጋራ ይተክሉበት ነበር ይላሉ።

በየታሪክ አጋጣሚው በተፈጠሩ የተለያዩ ችግሮች የአካባቢ ሰው ተፈትኗል። እምነቱን አንቋሸሸው፣ አቅሙን አዳክመውና ህይወቱን አስገብረው የገዙት ሰዎች በታሪኩ ውስጥ አለ። እነዚህ ሰዎች እየዘረፉ ያደኸዩት ናቸው። የላሙንና የበሬውን አንገት ሳይባርኩ ሞኑንና ሸንጡን እየነቀሉ ከአካሉ ላይ እየቆረጡ በአልለመደው መንገድ ሲበሉ፣ ዝርዝሩን እህል እያጨዱ ለርኩሶች ሲሰጡ ተመልክቷል (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ሞፍራ ሰደው አገሬውን አዘርፈውታል፣ ሚስቱንና ልጆቹን በተከታዮቻቸው አስደፍረውበታል (አለቃ ተክለየሱስ፣ ስርግው በተረጎመው፣ 2002፣ 164፣ ብላቴን ጌታ ኀሩይ፣ 1999፣173) ።

ልብሴንም ገፈፈው ለበሰው እርዘኛ፣

በሬዬንም ነዳው አረደው ነፍጠኛ፣

እህሌን ዘረፈው በላው ቀለብተኛ፣

ንጉሥ የቀረዎ ጥቂት አማርኛ፣

ምነው ሆድ አይዘርፉ አርፌ እንድተኛ።[12] እያለ ሁለ ብሶቱን ያንጎራጉር ነበረ ይላሉ። በቀደመው ጊዜ የነበሩ ነገሥታት አንዱ ለሌላው አልገብርና አልታዘዝ ሲል መከራውንና ስቃዩን ያይ የነበረው ተራው ሰው ነበር። ደጃች ደስታ ለአማቱ ለአፄ ተክለጊዮርጊስ አልታጠቅ ብሎ ሊወጋው በመዘጋጀቱ፣ አፄ ተክለጊዮርጊስ ደጃች ደስታን ሊቀጣ ወደ ጎጃም ሲመጣ በደጃች ደስታ ንዴት ደኃውን ዘርፎት ነበር። ይህንን ግፍ ያየች አንዲት የጎጃም ሴት እንዲህ ብላ እንደተቀኘች ይነገራል።

ዕውሩ በመሪ አንካሳው በምርኳዝ የተከተለዎ፣

አህል አይበቅልም ወይ ንጉሥ ባገርዎ።

አባት የለውም ወይ የመጣው ንጉሥ፣

እህል ይመት ይላል ተክለ ጊዮርጊስ። ብላ ገጠመች ይባላል (አለቃ ተክለየሱስ በስርግው እንደተረጎመው 2002፣ 137) ።

ጎጃም እሳት በላው ዐባይ እስታባይ

ንጉሡ የመጡት ሊያጠፉት ነው ወይ[13]

እንጀራ አትበል እንጅ ሥጋማ ምን ገዶ፣

የመከተሪያ ለት ድፍን ጎጃም ታርዶ።[14]

---

[12] ይህ ቃለ ግጥም አፄ ቴዎሮስ በአካባቢው ባደረሱት ቅጣትና ወታደሮቻቸው በፈጸሙት ዘረፋ ተናዳ አንድ የጎጃም አልቃሽ እንደተቀኘችው በአለቃ ተክለየሱስ መጽሐፍ የተገለጸውን ሥርግው ገላው በተረጎሙት በገጽ 128 ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

[13] በአፄ ዮሐንስ ላይ የተነገረ አለማየሁ ሞገስ ገጽ 99

[14] የድራር ዕለት ብዙ ሰው ስለተጨፈጨፈ የተነገረ አለማየሁ ሞገስ ገጽዕ፣ 98

አካባቢውን ለማስተዳደር ከሌላ አካባቢ የመጡ የግሸርው መደብ አባላት በነዋሪው ህዝብ ላይ ከፍተኛ ግብር በመጫን ጥሪት እንዳይቋጥርና አቅምና ጉልበት እንዳያገኝ ይረግጡት እንደነበር በአንዳንድ ድርሳናት ተጽፎ ይገኛል (ባሕሩ 1999፣ 228)። አቶ ቅሩብ፣ የእነዚህ ማህበራዊ ስጋቶች መጨመር ያስከተሏቸው ጉዳቶች ሁሉም ነዋሪ ላይ መሆን፣ ማህበራዊ ቡድኑ ጠንክሮ እንዲከላከል፣ በጋራ እያሰበ እንዲጓዝና ችግርን በጋራ እንደተቀበለው ሁሉ ባላንጋራንም በጋራ እንዲያጠቃ ጥንካሬ ሆኖታል ይላሉ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። የአካባቢውን ሰው የሚገጥመው ችግሮች አንድ መሆን ችግሮችን ለመፍታት አንድ አይነት ዓላማ አስታጥቆታል። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስም በጋራ ተነሳስቷል ይላሉ።

በተጨማሪም፣ ራስ ገዝነቱን በማጥበቅ ወደ አካባቢው የሚጎርፉትን መጻተኞች ለመከላከልና ጦር ታጥቀው ለመዝረፍና ለመበደል የሚጎርፉትን ኃይሎች ለመመከት፣ በተለያዩ አካባቢዎች የተሰሩ ድልድዮችን የምሥራቅ ጎጃም አካባቢ ሰው ይሰብር ነበር ይባላል (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው፣ "ንጉስ ተክለሃይማኖት በተምጫ ወንዝ ላይ ድልድይ ለመስራት ሲሞክሩ አገሬው መቃወሙ ነው። የሰባራው ድልድይ ታሪክም የዚህ አስተሳሰብ ውጤት ነው ይባላል (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እነ ፊታውራሪ ታምራትም ፋሲለደስ የሠራውን የአባይን ድልድይ ቅባኑግ እየወቀጡ በድብደባ ብዛት እንዳፈረሱት ይነገራል"። መሸጋገሪያዎችን መስበሩ ከግራ ከቀኝ የሚነሳን የጥቅም ተጋሪ ለመከላከልና ወደ አካባቢው የሚመጣን ሰው ለመገደብ ነበር።

ይህንን ሁሉ ገደብ ጥሰው የመጡበትን ሰዎች ፈርቶና ተጠራጥሮ የባላይነት ስሜት እንዳያድርባቸውም ሳያስጠጋም ሳያርቅብም ያቆያቸው ነበር (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይህ ቀደምት ታሪኩ የራሱን እያቀረበ የራሱ ያልሆነውን እያራቀ እንዲሄድ አስገድዶታል ይላሉ።

አቶ ተዘራ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ በዚህ ምክንያት የጎጃም ሰው ከጎጃም ውጭ የሚመጣን ግዥ ባለፈው አይን እየተመለከተ ለመቀበል

ይቸገር ነበር ይላሉ። አካባቢውን ለማስተዳደር ከማዕከላዊ መንግስት ተሸመው የመጡት እንደ ደጃዝማች ከበደን፣ ደጃዝማች ፀሐይ እንቁ ሥላሴንና ከንቲባ ማተቤን የመሳሰሉ የሸዋ መስፍኖች እንደ ባዕድ ተመልክቷቸው እነሱም ጠልተውት፣ እሱም አምፆባቸው እነሱም በድለውት በመጨረሻ አሸንፎ እንዳባረራቸው በታሪክ ድርሳናት ውስጥ ተገልጸ ይገኛል (ባሕሩ ዘውዴ፣ 1999፣ 227) ።

የአካባቢው ህዝብ ከሌላ አካባቢ መጥተው የገዙ የመንግስት ባለስልጣናትን ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወሩ ያስደረገው በተባበረ አመጹ ነበር (ባሕሩ ዘውዴ፣ 1999፣ 228) ። ችግሮቹን ለመቅረፍ የወሰደው እርምጃና ያስገኘለት ውጤት በማጎበረሰቡ ጥንካሬ የመጣ ስለሆነ፣ ሌላ ማህበራዊ ችግር ቢያጋጥም በህብረት እንፈታዋለን ብሎ እንዲያስብ ብርታት ሆኖታል ማለት ይቻላል። Guetzkow (1957, 51) እያንዳንዱ የቡድን አባል፣ ከማህበራዊ ቡድኑ የሚያገኘው ጥቅም ከፍ ባለ ቁጥር በራሱ ማህበራዊ ቡድን ላይ የመተማመን ጥንካሬው መጨመሩ አይቀርም ።

ከማህበራዊ ቡድኑ የሚያገኘው ጥቅምና ፍላጎት በአስተማማኝ እየተፈታ ሲሄድ፣ ፍላጎቱን የሚያሟላበት ሁኔታ እየበዛ ስለሚሄድና ከሌላው የሚፈልገውን ነገር ስለሚያሳጣው በቡድኑ ላይ ያለው ውዴታና አንድነት ይጠነክራል። በውስጡ የሚነድልውን እያሟላ፣ መከላከያውን እያጠነከረ፣ ጠላቱን እየለየ በሂደ ቁጥር ተጠቃሚነቱን ያሳድግዋል፤ ይህ መንፈሱ አንድነቱ እንዲደረጅ ምክንያት ይሆነዋል (Guetzkow,1957,51)። የግለሰቦች ፍላጎትና እርካታ በማህበራዊ ቡድኑ አማካይነት መልስ እያገኘ በመሄዱም በመሠረተው ተቋም ላይ ያለው መተማመን ይጎለብታል። እነዚህ ሁኔታዎች በድምር ለማህበራዊ እሴቶች የሚሰጡትን ክበሬታና ውዴታ ያሳድጉታል።

ራስን መቻል

የምሥራቅ ጎጃም ሰው በባሕርይው፣ "የያዘውን ያጠብቃል፤ እንደሁኔታውና እንደነገሩ ራሱን እየቀያየረና እያስማማ መሄድን እንደ ሽንፈት፤ የነበረውን አጽንቶና አጠንክሮ መያዝን እንደቁምነገር ይቆጥራል" እያለ ይገልጹታል (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። "ራስን ዝቅ አድርጎ መግዛት ወይም ለታችኛው የሚመች ነገር ማድረግ አይሆንለትም" ። ያሰበውንና

ያወቀውን፣ የለመደውንና ያጸናውን ብቻ ማስቀጠል የእምነቱ አካል አድርጎ ከልቡ መያዝ ጠባዩ ነው ይሉታል። "እምቢ ባይነትና የተመኘውን ማስፈጸም የታላቅነት ምልክት አድርጎ ይቆጥረዋል በማለት አቶ ተዘራ ይገልጹታል። ይህ ድርጊቱ በታሪኩ ውስጥ የታየ ከመሆኑም በላይ በተለያዩ ጊዜዎች ዋጋ ያስከፈለው እንደሆነ ታሪካዊ ገጠመኞችን ጠቅሰው ይናገራሉ።

ከላይ ለተጠቀሰው ሐሳብ የእምባቦንና የጉር አምባን ጦርነቶች ምሳሌ አድርገው ይጠቅሳሉ (ተክለ ጻድቅ 1981፣ 126፤ ብላቴን ጌታ ኃሩይ 1999፣ 129)፤ "በእምባቦ ጦርነት ጊዜ የሸዋ ጦር ምሽግ ቆፍሮ መሬት ይዞ ሲዋጋ፣ የጎጃም ጦር ግን ምሽግን እንደ ሽንፈትና ፍርሃት ስለቆጠረው ቆሞ በመታኮሱ እንደ ገብስ ታጭዷል" እየተባለ እንደሚወራ አቶ ተዘራ ይናገራሉ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። "ንጉሱ ራሳቸው በዚያን ሰዓት፣ ዳር ሆነው ተዋጊዎቻቸውን ከፊት አሰልፈው እንደማዋጋት፣ ከጦሩ መሀከል ተወርውረው ገብተው በመታኮሳቸው፣ ቆስለው እንደተማረኩ" ታሪክ ይነግረናል (ተክለ ጻድቅ፣ 1982፣ 214፤ ብላቴን ጌታ ኃሩይ 1999፣ 130)። በሌላ የጦር አውድ ላይም፣ ለምሳሌ ከመሐዲስቶች ጋር በተደረገው የደንበያው ውጊያ የመጣው "በጎጃም ትዕቢት" ነው እያሉ የተከፈለውን ዋጋ ይተርካሉ (አቶ ቅሩብ፣ 2006ዓ/ም፣ ህዳር11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

ባላባቱ "ጦር አውርድልን" እያሉ ይጸልዩና ስለት ሁሉ ይሳሉ እንደነበር የአካባቢው አባቶች ይናገራሉ (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ፈጣሪም የልባቸውን መታበይ አይቶ ጦር አወረደላቸው። በጦርነቱ ላይ "ንጉሱ በችኮላ ሂደው ገቡ፣ ልጃቸውን አስማርከው፣ አምቻቸውን አስገደለው ሠራዊታቸውን በትነው ተመለሱ። ይኸ ሁሉ ጉዳት የመጣው በትቢት ነው" በሚል ሰው ይወቃቀሳል (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

ይህ የበላይ የመሆን፣ የአልሸነፍ ባይነት ስሜት መገለጫው ሆኖ እንዲጸና ያደረጉ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም፣ በአካባቢው ተፈጥሮ ላይ የሚነገሩ ሚቶችና አፈታሪኮች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ ይላሉ አቶ ቅሩብ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እነዚህ ተረኮች፣ "የአካባቢው ሰው ራሱን ከፍ አድርጎ

እንዲያይ፣ በተፈጥሮ ሀብቱ እንዲኮራ፣ ከእሱ በላይ የታደለና የተመረጠ ሰው እንደሌለ አድርጎ እንዲያስብ አስታብየውታል"። በወንዙና በመልክአምድሩ እንዲያመልክና እንዲኮፈስ ሰበብ ሆነውታል። በራሱ ምልዑ መሆን (self Sufficient) እና ከሌላው አካባቢ የሚፈልገው ነገር አለመኖር ይህን አስተሳሰብ ፈጥሯል የሚሉ ወገኖች አሉ።

እነዚህ ፀጋዎች ኩሩነትን፣ አትንኩኝና አትምጡብኝ ባይነትን መገለጫው አድርጎ እንዲያስብ አድርገውታል የሚል ነው። ራሱን መቻሉ ለሌላው አለማደርጉ፣ በራሱ መተማመኑ አለመሸነፍን አስተዋወቁት። ማነስን እንደ ጥቃት እየቆጠረ ላለመሸነፍና ላለማነስ መጣጣርን ተዋውቋል። መረታትን ጥቃት አድርጎ ስለሚያስብ መከራከርን የጠባዩ መገለጫ አድርጎ ያዘው ይላሉ (አቶ እውነቱ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

የምሥራቅ ጎጃም ማኅበረሰብ ባህሉ የሚፈቅደውን ምኞትና ፍላጎቱ የሚጠይቀውን ነገር በአካባቢው ለሚሟላት የሚቸገር አልነበረም። "በሁሉም ነገር ራሱን የቻለ ነው" (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ከሌላው አካባቢ የሚፈልገው ነገር የለም፤ ሁሉንም በራሱ አቅምና ተፈጥሯዊ ሃብት ማሟላት ይችላል። ይህ ተፈጥሯዊ ጸጋው ለሚቀሰቀሱ ፍላጎቶቹ ወደ ሌላው እንዳያይ አድርጎታል። ለሌላ አካል እንዳያድርና እንዳያንበድድ አቅም ሆኖታል። ባለው ተማምኖ በራሱ እንዲኮራና እንዲወስን የራስ መተማመን ፈጥረውለታል ይላሉ (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በአካባቢው የተለያዩ የመሬት አቀማመጦች፣ የስነምህዳር ዞኖች፣ ትላልቅ ጅረቶችና ስምጥ ሸለቆዎች ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ በውሃ መጠናቸው ከሚታወቁት ታላላቅ ወንዞች መካከል አንዱ የሆነው የዓባይ ወንዝ የሚገኘው በዚህ አካባቢ ነው። ለአባይ ወንዝ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ገባር ወንዞች መካከል ከፍተኛው ድርሻ የሚገኘው ከዚህ ዞን ከተለያዩ አካባቢዎች ከሚነሱ ጅረቶች ነው (አቶ አቻምየለህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

የአካባቢ ሰው ባለችው መሬት የሚያስፈልገውን ቀለብ ሁሉ እንዲያመርት የአየር ሁኔታው ያግዘዋል። ሁሉም የአየር ጠባይ አይነቶች በአካባቢ ስለሚገኙ ሁሉንም የእህል ዘሮች ለማብቀል አመቺ ነው። ስለዚህ፣ ነዋሪው ህዝብ ፈልጎ የሚያጣውና ተመኝቶት ወይም አምሮት የሚቀር ነገር ስለሌለ አካባቢው ራሱን የቻለ ነው። ማንኛውም ፍላጎቱ በአካባቢው መሟላቱ ወደ ሌላ አካባቢ አያሳየውም ወይም አያስመኘውም ይላሉ (አቻምየለህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

የመልክዐምድራዊ ገጽታ አስተዋጽኦ

በጎዛምን አካባቢ ሰው ማንነት ላይ ተጽእኖ የፈጠረው ሌላኛው ተለዋዋጭ፣ መልክዓ ምድራዊ ገጽታ ነው። መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች በሰዎች መካከል ያለን ግንኙነት ከሚወስኑ ተፈጥሯዊ ክስተቶች መካከል ይጠቀሳሉ (Daniels, 1993)። በምስራቅ ጎጃም ዞን ላይ ትልቅ መልክዓ ምድራዊ ጫና የፈጠረውና አካባቢውን ደሴት ተደርጎ እንዲታሰብ ምክንያት የሆነው ደግሞ የዓባይ ወንዝ ነው። ይህ ዞን በሰሜን ከደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅ ደቡብ ከደቡብ ወሎ፣ በደቡብ ከኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ ደግሞ ከምዕራብ ጎጃም ጋር ይዋሰናል።

በአራቱም አቅጣጫዎች የዞኑ ጠረፍ (boundary) በወንዝ፣ በተራራና በሸለቆ የተከበበ ነው። በስተምዕራብ ጠረፍ በ11.5 ኪ.ሜ. ርዝመት የተምጫ ወንዝ ያጥረዋል። ቢዚሁ አቅጣጫ 70 ኪ.ሜ የሚረዝመው አባያ ወንዝ ይገኛል። የምስራቅና የደቡብ ጠረፉ ደግሞ ታላቁ የአባይ ወንዝና ሸለቆ ሰርቶ አጥሮት ይገኛል። እንዲሁም፣ ከባህር ወለል በላይ 4000 ሜትር ርዝመት ያለው የጮቄ ተራራ ከዞኑ ዋና ከተማ ደብረማርቆስ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ሰፊ ቦታ ሸፍኖ ይዟል።

መልክአምድራዊ ሁኔታ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በስነልቦና እንዲቀራረቡ የራሱ አስተዋጽኦ አለው (Fischer, 1975)። የተወሰነ ዘይቤአዊ አገላለጾች እንዲኖራቸው፣ አንድ አይነት ባህልና ማህበረ ታሪክ እንዲጋሩ፣ የአብሮነት ስሜትና አስተሳሰብ እንዲያጎለብቱ ምክንያት ነው። አንድ አይነት ማንነት፣ የጋራ የሆነ ባህል ተመሳሳይ ቋንቋና ሃይማኖትን በማስገኘት በኩል ሚናው የላቀ ነው። ለምሳሌ፣ በጎዛም አካባቢ የሚኖረው ህዝብ 100%ቱ አማራ ነው። በቋንቋ በኩል

ያለውን ማስረጃ ስናይም አማርኛ ያልሆነ ቋንቋ የሚናገረው ሕዝብ የለም። ከሐይማኖት አንጻር 98.71%ቱ የጎዛምን ወረዳ ነዋሪ የኦርቶዶክስ ሐይማኖት ተከታይ ነው (CSA, 2007)።

ማህበራዊ ቡድኑ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በልማድ መቀራረቡ ተመሳሳይ አይዲዮሎጅ እንዲኖረው ያደርጋል(Guetzkow 1957, 57)። ባህላዊ ዳራቸው ተመሳሳይ በሆነ ቁጥር በመካከላቸው ያለው ግንኙነት የጠነከረ ይሆናል። መቀራረቡ በተራው በመካከል ያለ ልዩነት እንዲጠብ ምክንያት ነው። ልዩነት እየቀነሰ ሲሄድ፣ አንድ የሚያደርግ ነገር እየበዛ፣ የሚያለያይ ነገር እየቀነሰ ይመጣል። በአንድ ቋንቋ መግባባት መቻላቸው፣ በቋንቋ ምክንያት የሚፈጠርን ክፍተት ይደፍናል። ቋንቋው በሚሸከማቸው እሳቤዎች ዙሪያ ተመሳሳይ አረዳድ ያመጣል። አንድ አይነት የባህል እሴቶች ስላሏቸው አንድ አይነት የሞራል ኮድ ያስተዋውቃል። ስለዚህ፣ የሚገጥሟቸው ችግሮችና ችግሮቹን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ሁሉ ሊመነጩ የሚችሉት ከዚህ የጋራ ስነልቦናዊ ተሞክሮ ይሆናል።

መልክዓምድራዊ ገጽታው አካባቢውን አጥሮ ስለያዘውና የአካባቢው ሰው ከጎረቤት ወገኖቹ ጋር እንዳይገናኝ ስለገደበው ከሌሎች ማህበረሰቦች ባህልና የአኗኗር ልምድ ጋር እንዳይተዋወቅ ተፈጥሯዊ ክልል ፈጥሮበታል (አቶ ግርማ ሞገስ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በመሆኑም፣ የአካባቢ ሰው ከራሱ ውጭ ያለን ህብረተሰብ አኗኗር፣ ዕድገትና ባህርይ ተፈጥሯዊ ክስተቱ የመጋራቱን ዕድል ያጠበዋል ማለት ነው። ሰው በተወለደበት አድጎ ሌላ ነገር ሳያይ፣ ለሌላ የአኗኗር ባህል ሳይጋለጥና ሳይለማመድ ሊያልፍ ይችላል። የሌላውን አካባቢ አለማየት ለማንነት ግንባታ ያለው አስተዋጽኦ የተለየ ፍላጎትና ስሜት እንዳይቀሰቀስ ማስቻሉ ነው ይላሉ አቶ ግርማ ሞገስ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። አቶ ግርማ ከራስ ውጭ ያለን ነገር የማየት ዕድል በጠበበ ቁጥር ስሜትና ፍላጎት በአካባቢ ባለ ነገር ላይ እንዲወሰን ያደርጋል ይላሉ። ፍላጎት በአካባቢ ላይ ብቻ መገደቡ ደግሞ ያለን ነገር መውደድን የሌለን ነገር አለመናፈቅን ያመጣል በማለት ያስረዳሉ።

አቶ ግርማ ሞገስ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) ይህ አይነት ስሜት በሥራቅ ጎጃም አካባቢ እንዲፈጠር ያደረገው የአባይ ወንዝ ነው ይላሉ፡፡ ወንዙ ማህበራዊነትንና የስነልቦና መመሳሰልን ከማስገኘቱም በላይ አካባቢያዊ አምልኮን ያመጣ ትልቅ የአይዲዮሎጅ መፍለቂያ የሆነ ቦታ ነው ይሉታል፡፡ አካባቢው በዚህ መልክ እንዲታሰብ አፈ ታሪኮች አስተዋጽኦ አላቸው ይላሉ፡፡

እነዚህ አፈ ታሪኮች፣ "ኢትዮጵያ ማለት ጎጃም ናት" ብለው ይጀምራሉ፡፡ ማስረጃ ሲያጣቅሱም፣ "የኢትዮጵያ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲነሳ ያደረገው የአባይ ወንዝ ነው" በማለት ነው፡፡ በኦሪት ዘፍጥረት "ከኤዶም ፈሳሽ ውሃ ይወጣል እርሱ ለአራት ይከፈላል" ብሎ ሙሴ ሲጽፍ፣ "በኢትዮጵያ ምድር ዙሪያ ሁሉ የሚፈስ የግዮን ወንዝ" (ዘፍጥረት 2፣ 13) ሲል ጎጃምን መጥቀሱ ነው፡፡ ምክንያቱን ሲያቀርቡም፣ አባይ ጎጃምን እንጅ ኢትዮጵያን አይከባትም የሚል ነው፡፡ ስለዚህ፣ የኢትዮጵያ ውክልና ለጎጃም ነው" በማለት ለአካባቢው ከፍ ያለ ቦታ ለመስጠት ይሞክራሉ (አለቃ ተክለ-ኢየሱስ፣ በግርማ፣ 2003፣ 15)፡፡

ይህንን መነሻ አድርገው፣ ጎጃምን እንደ አውድማ ስለሚከባት፣ "አባይ የጎጃም መቀነቷ ነው፤ ሌላው ሁሉ የጎጃም ዘርፍ ነው" ይላሉ (አለቃ ተክለ-ኢየሱስ፣ በግርማ፣ 2003፣ 15) ፡፡ "የኢትዮጵያ ታሪክም ከተባለ የጎጃም ታሪክ ነው፡፡ ስለዚህ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ሲባል መነሳት ያለበት ከጎጃም ነው" በማለት ማንነታቸውን አተልቀውና አግዝፈው ለማሳየት ይጥራሉ፡፡ ሌላው ሁሉ ታሪክ መፍሰስ ያለበት ከዚያ ነው ብለው ደፍረው ይናገራሉ (አለቃ ተክለ-ኢየሱስ፣ ግርማ በተረጎመው፣ 2003፣ 15-16)፡፡ እነዚህ ታሪኮች የማንነት መገንቢያ ተረኮች ሆነው ተደጋግመው ስለሚቀርቡ በሰው ልቦና ሁነኛ ቦታ ይዘዋል፡፡

አቶ ቁሩብ፣ ይህ አስተሳሰብ እያደገ ሄዶ ጎጃምን ከሰማያዊው ዓለም ጋር ሁሉ አነጻጽሮ የመግለጽ ልምድ አመጣ ይላሉ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ መንግስተ ሰማይ የምትገኘው በብዙ ድካም ነው ይላሉ አለቃ ተክሌ (በግርማ፣ 2005፣ 25-28)፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ጎጃምም "ዳርዋ እሳት መሀሏ ገነት ነው"፡፡ "ዳርዋ እሳት መባሉ በዙሪያዋ ዓባይ በሚሄድበት ሁሉ በረሀና ረግጫ፤

ወደ መሀል ሲዘልቁ ግን በዙሪያው ያለው ሀገር ሁሉ አብራጃ እየሆነ ይሄዳል። በደብተራ ኦሪት 12ቱ ነገደ እስራኤል በዙሪያዋ ይሠፍሩ እንደነበረ ሁሉ በጎጃምም በዙሪያዋ 12ት ጎጃም የተባሉት አባቶች ሠፍረውባታል። ዘጠኙ ቅዱን የክርስቶስን ነገር ለማስተማር ባደረጉት እንቅስቃሴ "ደብረ ዘይት"፣ "ሳል"፣ "መንግስተ ሰማያት"፣ "ናዝሬት"፣ "ጌቴስማኔ"፣ ወ.ዘ.ተ... የሚባሉ ድንቃ ድንቅ ተአምር ተፈጽሞባቸው በዚያው ስም እስካሁን ድረስ የሚጠሩ ቦታዎች አሉበት (አለቃ ተክለየሱስ፣ በማርማ፣ 2005፣ 25-28)።

እነዚህ ሚቶች የራስን ባህልና ማንነት ጎልቶና ደምቆ እንዲታይ ሲያደርጉ፣ ለሌላው ደግሞ በአነሰ ለማሰብ ምክንያቶች ይሆናሉ። ከዚህ ቦታ መወለድን እንደ መባረክ በመቁጠር በራስ መኩራራትን ሲያሳስቡ፣ ከሌላኛው ማህበራዊ ቡድን ጋር መቀላቀል ይህንን ክብር ያሳጣሉ የሚል እምነትን ያመጣሉ። ስለዚህ፣ የራስን ቡድን ከሌላው ቡድን የበላይ አድርጎ ስለሚያሳስብ፣ ለልዩነት ዋጋ መስጠትን ትልቅ የማንነት መገለጫ መንገድ አድርጎ ያስይዛል። ይህ ደግሞ በተራው የራስን ትልቅና ትክክል አድርጎ መመልከት የሌላውን ስህተት አድርገን መቁጠርንና መፈረጅን ያሳስባል። የራስን ለይቶ መውደድና በራስ ባህልና ቡድናዊ መንፈስ መተማመን መልካም ቢሆንም፣ አንዳንድ ጊዜ ራስን የተለየ አድርጎ ለመቁጠር ምክንያት እየሆነ በሌላው ወገን በቅን እንዳይታሰቡ ሰበብ ሊሆን ይችላል።

4.4. ከጎጣምን አካባቢ ከተሰበሰቡ መረጃዎች የተገኙ እሴቶች[15]

የአንድን ህብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞችና ደህንነቶች ለማስከበርና ለማስጠበቅ የሚረዱ ልዩ ልዩ ዘዴዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል ዋናው አውራና ገዥ ጥቅሞችን እሴት አድርጎ በመያዝ ማህበራዊ ልምዶች በየትውልዱ አስተላሰብ ውስጥ እየገቡ የሚሰራጩበትን እና የሚሰርጹበትን ዘዴ ማመቻቸት ነው። እነዚህ ልምዶች ሰላማዊና የተረጋጋ ሥርዓትን በመፍጠርና አንድ የሚያግባባ ቋሚና የማይቀያየር ደንብ በማቆም ማህበራዊ ሚናዎች የሚጎለብትን መንገድ ማመቻቸት ይሆናል። የምሥራቅ ጎጃም ህብረተሰብ ከጋራ ልምዱ፣ ከታሪኩ፣

[15] እሴት በዚህ ጎጣቢው ከብዙ አማራጮች መካከል አንዱን ከሌላው በተለየ መርጠ በመያዝ የህይወት መመሪያ ማድረግ ነው።

ከገጠመኙና ከግንኙነቱ አንጻር ይጠቅሙኛል በሚል አራት ዋና ዋና እሴቶች[16] እንዳበጀ በ2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት ላይ ከተገኘ መረጃና በተናጥል ከተካሄዱ ቃለመጠይቆች ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ እሴቶች እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል።

መብዛትን ማክበር

"እንደ አባይ ተጋፉ፣ እንደዋርካ ስፉ"

በነዛምን ህብረተሰብ የምርቃት ባህል ውስጥ "ሀብት" ከመበርከት ጋር ተያይዞ ይገለጻል (አቶ ተዘራ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 10 የተደረገ ቃለመጠይቅ)። የሀብት ምንሪጮች ተደርገው የሚጠቀሱትና ምኞትና ምርቃት የሚደረግባቸው ደግሞ "ልጅ፣ ከብት፣ አዝመራ፣ ዕድሜ፣ ጤናና ሰላም ናቸው"። የምርቃቱ ምኞት እነዚህ ሀብቶች እንዲሞሉና እንዲበዙ፣ እንዲበረክቱና እንዲረቡ ነው። ከእነዚህ ምርቃቶች መካከል፣ "ሀብትና ንብረት ይስጣችሁ፤ ቤታችሁ የከብት ቤትና የልጅ ቤት ይሁን፣ በውሃ ይለቅ" የሚሉ ይገኙበታል (አቶ ተዘራ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 10 የተደረገ ቃለመጠይቅ)። የመባዛቱ ዋጋ ተክትቶ ለማለፍ፣ ራስን አስተዋሽ፣ ወግንና ልማድን አስቀጣይ ለማግኘት እንደሆነ ቀጥሎ ከቀረበው ምርቃት ለማወቅ ይቻላል። አባቶች፣ ወዳጅና ዘመድ በሰዎች ተግባር ሲደሰቱ "የእናት የአባት የቅድመ አያት ባድማ አስከባሪ ስም አስጠሪ ያድርጋችሁ፤ በቦታው ሽማግሌና የከብት አውራ ይውጣበት" ብለው ይመርቃሉ(አቶ ተዘራ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 10 የተደረገ ቃለመጠይቅ)። በእነዚህ የመልካም ምኞት መግለጫዎች ውስጥ ተተኪነት፣ ሰብሳቢነትና አስታዋሽነት ጎልተው ተንጸባርቀዋል።

አቶ ዘውዴ ገበየሁ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ በሰው ልጆችም ሆነ በዕፆች ተፈጥሮ መዋለድና መባዛት ባለበት ዘር ውስጥ መተካካት ተፈጥሯዊ ባህርይ ነው ይላሉ። ምክንያቱን ሲገልጹ፣ "በአባቸው ተፈጥሮ ውስጥ ማርጀት፤ ማፍጀት፣ መበስበስ፣ ማለቅና መክሰም የማይቀር በመሆኑ ነው" ይላሉ።

[16] የህዝቡ ባህላዊ እሴት በተለያዩ የመሬት ስሪትና በግብርና ላይ የተመሰረተ ነው።አማራው ዘሩን ሳይሆን ፣ ርስቱን ሀይማኖቱንና ሚስቱን መሰረት ያደረገ ብሔራዊ (ሐገራዊ) ጥሪ ሲደርሰው ወደኋላ አይልም(ባዬ 2001፣v)።

እያንዳንዱ ፍጥረት ዘሩን በመተካቱ ሂደት በስብሶ ያፈራል። የሚያፈራ ሁሉ ደግሞ ይበሰብሳል። ያፈራም ዕድሜው ሲደርስ ይከስማል። ስለዚህ፣ መበስበስ ለማፍራት ምክንያት የሚሆን የመተካኪያ መንገድ ነው። ዘርን መተኪያውና ራስን ማስቀጠያው መንገድ ደግሞ በመባዛት ወይም በመዋለድ ነው።

ስለዚህ፣ የማይጠበቀውና የማይፈለገው ሳይተካ ማፍጀት እንጅ አፍጅቶ ማለቅ አይሆንም (አቶ ዘውዴ ገበየሁ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በአካባቢው ሃብት፣ ስልጣንና ክብር በመወለድ የሚተላለፍ በመሆኑ ራሱን ያልተካ ይሽንን ክብር ስለሚያሳጣው ብዙ መውለድ እንዚህን ክብሮች ለመጨበጥ አይነተኛ መሳሪያ ነው። የስልጣንና የክብር ምንጩ ደግሞ መሬት[17] መሆን፣ አለመውለድ ይሽንን ሁሉ መብት ያሳጣል።

ሌላው ለመተካካቱ ቁም ነገር የሚሆነው ጉዳይ በሰው ልጅ ባህርይ ውስጥ "ሞት" የመኖሩ ምስጢር ነው ይላሉ። ሁሉም ፍጥረት ዘላለማዊ አይደለም። ስለዚህ፣ ገርያ የሚቀጥለው "በመዋለድ" ይሆናል። ማለቅና ማነስ ተፈጥሮ በሆነ ፍጥረት ውስጥ ጥቂት መውለድ ዋስትና አይሆንም ብለው ይናገራሉ (አቶ በቀለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። አቶ በቀለ፣ በመበርከት ውስጥ የተስፋፊነትና የተንሰራፊነት አቅም መኖሩን የሚጠቁምና ረጅምና ሰፊ አገልግሎት መስጠትን የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው ይላሉ። እያንዳንዱ ዘር ያፈራው ሁሉ ላይመረቅለት ይችላል። ከዘሮቹ መካከል ፈጥነው በቅለው ፈጥነው የሚጠፉ አሉ። በምድር ላይ ያላቸው አገልግሎትና የሚሰጡት ጥቅም አጭር ሆኖ የሚቀሩ ዘሮች ብዙዎች ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ ረጅም አገልግሎት ሰጥተው፣ ለመራባትና ለመባዛት ምቹ ሆነው፣ ራሳቸውን ከበቂ በላይ ተክተው የሚያልፉም አሉ። ስለዚህ፣ ከዚህ ሁሉ ችግር ነጻ የሚያወጣው የመውለድ ዕድልን ማስፋት ነው ይላሉ አቶ በቀለ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

የቀደመውን መጠበቅ (Originality)

"ፍጥረትና ዕውቀት በአንድ ቀን ነው"

[17] power and status are based on land in rural Amhara society (Koehn,1978, 42)

የንዛምን አካባቢ በአቅኝው ሃይል ቁጥጥር ውስጥ ከገባ በሁዋላ ሕዝቡ እንደየትውልዱና እንደዘር ሃረጉ በለመ· መሬት ላይ መተክሉን በታሪኩ ከቀረበው ክፍል አይተናል፡፡ ይህንን አሰፋፈሩን በሥርዓትና በሕግ ለመምራት የሚያስችለው የአስተዳደር ስርዓት፣ የመተዳደሪያ ደንብና የስልጣንና የኢኮኖሚውን አፈራርና አስተላለፍ ሕግ አጽንቶ የተረጋጋና የሰከነ መዋቅር ለመፍጠር መተዳደሪያ ሥርዓት እንደወጣ በተክለ-ኢየሱስ መጽሐፍ ውስጥ ተገልጿል (ተክለየሱስ፣ በግርማ ጌታቸን፣ 2003፣ 249-262)፡፡ በሥርዓቱ መሰረት እያንዳንዱ ግዛትና ውስን ሀብት ለባላባቱ፣ ለመኳንንቱ፣ ለጨዋውና ለቤተክርስቲያን ሰው ተከፋፍሏል፡፡ በመሆኑም፣ ዘግይቶ የመጣው የሚተክልበት ነጻ ወይም ትርፍ መሬት አይገኝም ማለት ነው፡፡

በአካባቢው በጊዜው ብቸኛው የሀብት፣ የክብርና የስልጣን ምንጭ የነበረው መሬት[18] ነው (Reminick,1976,752)፡፡ መሬት ደግሞ ውስን ተፈጥሮ የሆነ፣ የማይለጠጥ ወይም የማይባዛ ሀብት ሲሆን ቀድሞ በያዘው ወገን እጅ ገብቶ ለልጅ ልጅ ተከፋፍሏል፡፡ ክፍፍሉ አቅኝውን ባለሀገር አድርጎ የመጠቀም መብት ሲሰጠው ዘግይቶ ደራሹን መጤ አስብሎ መብት ያስነፍገዋል፡፡ ግዥው መደብ ይህንን ሃይል የደምና የአጥንቱ ክፋይ ለሆነው ወገኑ የሚያሳውቅበት ምልክት ማድረጊያው ነው (እቻምየለህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡

“ይህ መንግድ ዘግይቶ ለሚመጣው ዜጋ የመጠቀም መብትን ያሳጠል፡፡ ወደ አካባቢው በተለያዩ ጊዜ በፍልሰት፣ በጦርነትና በምርኮ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ዜጋ[19] ፈልሶ ገብቷል (አለቃ ተክለ-ኢየሱስ፣ ግርማ በተረጎሙት 2003፣ 32) ፡፡ ፈላሹ ወገን ዘግይቶ የደረሰ በመሆኑ ለአገሩ እንግዳ፣ ለደንቡ ባይታወር ነው፡፡ ስርዓት ከወጣና የሀብት ክፍፍል ከተደረገ በኋላ ወደ አካባቢው መምጣቱ “መጻተኞች” አስብሏቸዋል፡፡

---

[18] ባዬ አማራው ዘሩን ሳይሆን ጥቅሙን መሰረት ያደረገ አደረጃጀት አለው ይላሉ፡፡ በወንዝና በአገር ልጅነት ይሰበሰባሉ፡፡ በጎጃሜነት፣ በወሎየነት፣ በጎንደሬነት ወ.ዘ.ተ እየተደራጁ ሊረዳዱ ይችላሉ፡፡ ይህን ሲያደርግ ግን ዘርን ሃይማኖትን መሰረት አድርጎ ሊሎቹን አያገልም ይላሉ(ባዬ 2001፣ vii)፡፡

[19] በምሥራቅ ጎጃም አካባቢ የዜጋ እሳቤ ለባለመሬት ተገዥ የሆነ ሰው ማለት ነው (ግርማ ጌታቸን፣ 290)፡፡ ገባር ተገዥ፣ የሌላ ሰው ቅኝ (ደስታ ተክለወልድ፣ 479)

ሁሉም ነገር መልክ መልክ ከያዘና አቅኝው ወገን ኃይልና ጥንካሬ የሚያስገኝለትን ደንብ ካወጣና ከተለማመደው በኋላ የደረሱትም ቢሆን በቀናውና በረጋው ሥርዓት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ ቀድሞ ተገማች ነው፡፡ መጪው ወገን ወደ አካባቢው ሲያቀና ይዞት የሚመጣው የሃይማኖት፣ የባህልና የአስተዳደር ሥርዓት ይኖራል፡፡ ይህ ደንብና ሥርዓት ቀድሞ ገብቶ ከረጋውና ከጸናው ሥርዓት ጋር ሲገናኝ ከአቅኝው አካል ባህል ጋር መጋጨቱ አይቀርም፡፡ "የተጽእኖ መጠን የሚታረቀው፣ ቀድሞ ገብቶ ያቀናው አካል መሬቱን ተከፋፍሎ የተተከለበት በመሆኑ፣ ዘግይቶ ደራሽ ዜጋ የሚያርፍበት ኑሮውን መስርቶ የሚያቆይበት ቦታ እንዳይኖረው አድርጓል" (አቶ እውነቱ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ "በመጻተኞቹና በባላባቶቹ መካከል ያለው ግንኙነት አንዱ አንዱን በማፍለስ፣ በማግለልና በማራቅ እንዲሁም በግጭትና ባለመስማማት ላይ የተመሰረተ ነው" (አቶ እውነቱ ተገኘ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ አቶ እውነቱ የአንዱ መጠንከር የሌላውን መድከም፣ የአንዱ መተከል የሌላውን መነቀል ስለሚያስከትል በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለው ግንኙነት በዘላቂ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ባላንጋራነት ነው ይላሉ፡፡

በመሆኑም፣ መጻተኛነትና ባላባትነት የሁለቱ ወገኖች አይዶሎጂ የታነጸበት፣ የመደብ ቅራኔያቸው የቆመበት፣ አስተሳሰብ ይሆናል፡፡ የባላባቱ ወይም የባለርስቱ መደብ የያዘውና የተከለው ስርዓት ተጠብቆለት እንዲሄድ ይፈልጋል፡፡ ትክክል ብሎ አጽንቶና አስተካክሎ ያሰረጸው ልማድ ከተናጋባት ተጠቃሚነቱን ስለሚያሳጣው መብቱንና ጥቅሙን አሳልፎ ላለመስጠት ሲል ለመሰረተው ልማድ ባሪያ ይሆናል፡፡ አክብሮና አጽንቶ መሄድ ብቸኛው የመከላከያና የጥቅም ማስጠበቂያ መንገዱ ነው (አቶ እውነቱ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡

አቶ በቀለ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ "መጻተኛው ኃይል ተጠቃሚ የሚሆነው ትውፊታዊው ሥርዓት በአዳዲስ አስተሳሰብና እሱን በሚያቅፍና በሚያሳትፍ ስርዓት ከተተካ ብቻ ነው ይላሉ፡፡ መግቢያ መንገዱን ሁሉ የዘጋበትንና ማንኛውም ቀዳዳ ሁሉ የደፈነበትን ህግና ደንብ ካላናጋው በስተቀር ተስፋው ዝግ ነው፡፡ የተተከለው ስርዓት እንግዳ ክስተትንና አዳዲስ ለውጥን

እንዲያስተናግድ የሚናወጥበትን መንገድ ተበዳዩ ይናፍቃል በማለት ያስረዳሉ። በመሆኑም፣ የተተከለው ላልቶ አዲስ መሠረት እንዲቆም የጸናው መነቃነቅ አለበት። ያልተለመዱ ክስተቶች ተፈጥረው መደናገጥና መደናበር እንዲከተል ያስፈልጋል። የረጋውን ለማደፍረስና የጸደቀውን ለማናጋት የመፈንቀል መከራ መኖር አለበት። ነባሩ ደንብና ስርዓት እንዲናጋና እንዳይረጋ የሚደፈርስበትንና የሚናወጽበትን ሁኔታ መፈጠር አለበት።

ስለዚህ፣ አቅኝው ባለበት መቆየትን አጥብቆ እየወደደ ካወቀውና ከለመደው ውጭ አዲስ ነገር ተፈጥሮ እንዲነቅለው አይፈልግም። ነባሩ ለእሱ የሚያዳላ በመሆኑ ጥቅሙን በሌላ ነገር ለውጦ ሊያጣው አየፈልግም። በተከላቸው ባህላዊ ተቋማቱ ላይ የሚፈጠሩ ለውጦች የረጋውን ስለሚያደፈርሱና የተሰራውን ስለሚንዱ ለዘላቂነታቸው ዘብ ይቆማል። ግለሰቦች ወደ ማህበራዊ አኗኗር የሚቀላቀሉበትን ልማድ ስለሚያፋልስ፣ አዲሱ ክስተት ይዞት ከሚመጣው መልካም ነገር ይልቅ የሚያስከትለው ጦስ የማይገመት ኪሳራን ይወልዳል። ከለመደውና ከሚያወቀው ውጭ ሆኖ የተፈጠረ ወይም ያጋጠመ ነገር መልካም ነገርን አይጠራም ብለው ስለሚሰጉ ለማምለክ ይገደዳሉ።

አቶ ተዘራ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ "በአካባቢው የበሬ የብልቱ አንድ ፍሬ ጎድሎ ከተወለደ ይገፋል" አዲስ ነገር ማየት የአካባቢው ሰው ስለማይፈልግ ነው ይላሉ። ወይም "ጥርስ ከሚበቅልበት ቦታ ላይ ሳይበቅል ቀርቶ በሌላ በኩል ከወጣ ወይም አንድ ጤናማ ሰው ከሚይዘው ቅርጽ ጎድሎ ወይም አብዝቶ ይዞ የሚፈጠር ሰው ሲገኝ በጥሩ አይታሰብም ይላሉ። ምክንያቱም፣ አዳዲስ ነገሮች እንግዳ ነገሮች ለመምጣታቸው ምልክት ተደርገው ስለሚታሰቡ ነው።

ስለዚህ፣ በአካባቢው ከመንጋው የተለየ ነገር ይኖር ዘንድ አይፈቀድም። ወጣ ያሉና ያልተለመዱ ክስተቶች ተፈጥረው ሲታዩ የማህበረሰቡ ምላሽ የከፋ ነው። ማህበረሰቡ በሁለም ነገሩ በዜጎች መካከል ልዩነት እንዳይኖር ይሰራል። በትውፊታዊ ልማዱ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ግለሰባዊ ባህርይና አስተሳሰ ቢፈጠር ሊደርስ የሚችለውን ማህበራዊ ቀውስ ቀድሞ የገመተው ይመስላል። ሁሉም የማህበረሰብ አባል በእኩል ማህበራዊ ልማዱን ላይቀበልና ወጣ ያለ ባህርይ ሊያሳይ

ይችላል። ካሉት ውስጥ የሚያፈነግጡ በልማዱ የሚያምጹ ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ አንድነትን የሚያላላ ሁኔታ እንዳይፈጠር ወደ ወል አመለካከት ማስገቢያ መንገድ ይሆናል።

ይህን አስፈሪ ክስተት ማህበረሰቡ አርቆ ስለሚገምተው በጭራሽ እንዲመጣበት አይፈቅድም። በዚህ ምክንያት፣ ማህበረሰቡ ሳይወድ በግድ ባለው መኩራትን፣ አለመለወጥንና አለመቀየርን የጥንካሬው ምንጭ አድርጎ እንዲይዘው ይገደዳል። የያዘውን ተንከባክቦና አጠናክሮ ይጠብቀዋል። በያዘው መጽናትንና መኩራትን፣ በሌሎች አለመሸነፍንና ለማያውቁት እንግዳ ክስተት አለማጎብደድን የማንነቱ መገለጫ እያደረገ እንዲይዘው ያተጋዋል። ግትርነትና አልሸነፍ ባይነት የመጽኛ መንገዱ ይሆናል። በራስ መኩራትን፣ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግን የእሴቱ መጠበቂያና የጥቅሙ ማስከበሪያ ስልቱ አድርጎ ይተክለዋል።

የራስ ያልሆነን አለመፈለግ፣ ለመጤ አስተሳሰቦችና ባህሎች ቦታ አለመስጠት፣ ማንነትን ጠብቆ ማቆየት፣ እንግዳ የሆኑ ነገሮችን አለመቀበል፣ ባህል እንዳይበረዝ ማንነት እንዳይሸረሸር ማድረግ፣ ነባሩን አስጠብቆ ማስቀጠያና እንግዳውን አርቆ መያዣ ስልት ነው። በለመዱትና በሚያውቁት ነገር ብቻ ይገዛሉ። ከሚያውቁትና ከሚግባቡት ውጭ ላለ ነገር አይጓጉም። ሁኔታውን ለምዶና በስነ ባህርይው ውስጥ አስርጾ የኑሮ ዘይቤው አድርጎ ለመሄድ አይሞክርም። በመሆኑም፣ ለይቶና መርጦ ይጠቅመኛል በሚል የያዛቸው እሴቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ዘር መቁጠር

"የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ"

ከብዙ ዘውጌ ማህበረሰቦች በጋብቻና በስደት፣ በአቅኝነትና በተሰሪነት እንዲሁም በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ ምሥራቅ ጎጃም መጥተው የሠፈሩ ብዙ ወገኖች እንዳሉ በአካባቢው የሚነገሩ አፈ ታሪኮች ያስረዳሉ (ተክለየሱስ በግርማ፣ 2003፣ xiii)። በተጨማሪም በሕዝብ አሰፋፈር፣ የመሬት ይዞታ፣ የቦታ ስያሜ፣ ወ.ዘ.ተ...ላይ አስረጅ በመሆን በመጠሪያነት የሚያገለግሉ ማስረጃዎች አሉ።

“ትውልድ እየቆጠሩ፣ የዘር ሐረግን ወደላይ እየመዘዙ ማጥናትንና ማስጠናትን፣ የጎሣምን ሰዎች ይወዳሉ” ይባላል (አቶ በቀለ ውብሸት፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በየትውልዱና በየጋጡ ማን ከማን ጋር እንደሚዛመድ፣ አመጣጥና አካሄዱ ሁሉ እንዴት እንደሆነ ለልጅ ልጆቻቸው የማሳወቅ ልምዳቸው ጎላ ያለ ነው። ስም ሲያወጣ እንኳ ከአባት ከአያታቸው ጋር እንዲገጥምላቸው ይጨነቃሉ ይሏቸዋል (አቶ በቀለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይህ ነገረ ስራቸው ሰው ሥጋውን ከባዕዱ፣ ቅርቡን ከሩቁ ለይቶ እንዲያይ አድርጎታል ይባላል። ይህ ልምዱ አንድነቱን በማጠናከርና ግንኙነትን በማደስ በኩል በእጅጉ ጠቅሞታል።

ዘር መቁጠር በየትኛውም አካባቢ የተለመደ ሰዋዊ ባህርይ ነው። “የርስት ስርዓት በተስፋፋባቸው አካባቢዎች ግን የሀብት ማግኛ መንገድ ነው። በመሆኑም፣ ይህ አንድ መሰረታዊ እሴት ነው(አቶ ቻላቸው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በየስርዓቱ ዘርን ለመለየት ዋጋ ያሰጠው ነገር፣ “በአካባቢው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው አኗኗሩ ውስጥ መሬት የህልውና መሠረት የመሆኗ ምስጢር ነው”። መሬት፣ “በርስት የተያዘ ውስን ሀብት ነው”። የመሬት ባለቤትነት መሆንን የሚያመጣው ተወላጅነት ነው (Koehn,1978, 42)[20]። እያንዳንዱ ተወላጅ የመሬት ባለቤት የሚሆነው “ጋጥ እየቆጠረ” እስከ ሰባት ቤት ድረስ ከዘመዱና ከወገኑ በመካፈል ነው። በመሆኑም፣ ራስን ተጠቃሚ ለማድረግና የተጋሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ የሚገባውንና የማይገባውን አካል ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። “ተወላጁም ሆነ ወላጁ ዘሩን ጠንቅቆ በማወቁ በጥቅሙ ላይ የሚነሳን ተጋሪ ለመከላከል ይረዳዋል (አቶ ቻላቸው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

አቶ ቅሩብ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) ለዘር ቆጠራ ክብር እንዲሰጥ ያደረገው፣ “የአካባቢው ሰው ከጋብቻ ይልቅ ለዝምድና ክብርና ዋጋ

---

[20] በሃገር ሽማግሌዎች እምነት የዘር ሐረግ ቆጠራው ለአካባቢ ማህበረሰብ የሚሰጣቸው ጠቀሜታዎ አለ። የመጀመሪያው ጥቅሙ የርስት ጥያቄን ወይም በመሬት ይገባኛል የሚነሳ ግጭትን ለመፍታት ማን ቢወልድ ማን እየተባለ ሲሰራበት ቆይቷል። ሁለተኛው በዘመዳሞች መካከል ጋብቻ እንዳይፈጸም የዘር ሃረግ ቆጠራ ይከላከላል( )

መስጠቱ ነው" ይላሉ። ማህበረሰቡ፣ በዕዱን አርቆ ዘመዱን አቅርቦ መብቱንና ክብሩን በራሱ ወገን ለማስጠበቅ እንደሚፈልግ ይናገራሉ። ዝምድናውን ለማክበሩ አስረጅ ብለው የሚጠቅሱት፣ "እስከ ሰባት ቤት ደረስ ጋብቻ አለመፍቀዱን ነው"። በአካባቢው ሰባት ቤት ሳይሞላ ጋብቻ አይፈጸምም። ግንኙነቱን በጋብቻ ለማሰር የሚፈልገው፣ "በሥጋ መዛመድ ሲርቅና ቆጥሮ ማወቅ ሲሳነው ነው" (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በዚህ ጊዜ በክብሩና በማዕረጉ የሚመጥኑትን እየመረጠ የሚዛመድበትን ሁለተኛ አማራጭ ማለትም "ጋብቻ"ን ይይዛል እንጅ ከዝምድናው አያቀርበውም ይላሉ።

በአካባቢው ጋብቻ ወዳጅ እንዲበዛ፣ ክብር እንዲጨምር ይረዳል። ይህ ወዳጅነት ዝምድናን ያጠነክራል። ማህበራዊ ግንኙነቱን መልካም ያደርጋል። መተጋገዝንና መረዳዳትን ስለሚያመጣ ከጠላት ጥቃት ደጀን ይሆናል (አቶ ግርማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በአካባቢው ልማድ መሠረት ጋብቻን እስከ ሰባት ቤት ድረስ መቁጠር የተለመደ ነው። የዘር ሐረግ ቆጠራው የግለሰብ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የማህበረሰብን በርካታ ጥያቄዎችና ችግሮች የሚመልስም ነው። ከርስት፣ ከጋብቻና ከደም መመለስ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ከመፍታት በተጨማሪ ከየት መጣሁ አይነት የማንነት ጥያቄዎችን የሚመለሱት በዚሁ የቆጠራ ስልት ታግዘው ነው (ዮሴፍ፣ 1996፣ 10)።

ጅግናን ማክበር

"መርጠሽ አርሚው አሰንዳቦውን

ጓደኛ አርጎታል የጤፍ ዝርዝሩን።"

የምስራቅ ጎጃም አካባቢ ለግብርና ሥራ ያለው ምቾት፣ በጋብቻ እና በስደት፣ በአቅኚነትና በተሰሪነት በርካታ ማህበረሰቦች ወደ አካባቢው መጥተው እንዲሰፍሩ ምክንያት ሆኗል (አቶ አቶ እውነቱ ተገኘ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ፍልሰቱ ገደብ የለሽ በመሆኑ፣ በተበጣጠሰ ውስን ሃብት ላይ የሚመራውን ህይወት እንዲጎሳቆልና ማህበራዊ ግንኙነቱ እንዲረበሽ አድርጓል። ለምሳሌ፣ በጎዛምን አካባቢ የሚኖሱ አብዛኞቹ ግጭቶች መነሻቸው የርስትና የጉልት

ጠብ ነው። እንደ ጥቁር ደም፣ ስርቆት፣ ቃጠሎ፣ ድብድብና የመሳሰሉ የጸጥታ ችግሮች በአካበቢው መነሻቸው ውርስ ነው።

የአካባቢ መሬት በርስት አማካይነት በተወሰኑ ወገኖች እጅ መግባት፣ በአካባቢው ለምነት ተማርከው ኑሯቸውን በዚያ ለማድረግ ለመጡ ሌሎች አካሎች እንዳይመች አድርጎታል። ባለርስቶችም ከተተከሉበት መሬት ላይ ሌሎች ሃይሎች እንዳይተከሉ መሬትን በርስትና በጉልት የውርስ ማስተላለፊያ ስርዓት ገንዘብ አድርገውታል (Reminick, 1976, 752)። በመልክአምድሩ አማካይነት የተመሰረተው መቀራረብ፣ በወንዙ ከበባ የተነሳ የተፈጠረው መተሳሰር፣ በመሬቱ ምራታማነት ታግዞ የአካባቢው ማህበረሰብ ማንነት በዚህ ላይ ያለው እምነት እንዲጠነክር ሆኗል (አቶ አቶ እውነቱ ተገኘ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። "ይህ የተገኘው ሀብት እንዳይነጠቅ ጀግንነትን ባህል ማድረግ ያስፈልጋል(Reminick, 1976, 752)።

ይህ ጀግንነት ምልክት የሆነው እያንዳንዱ ጎጃሜ ጎጆ ቀልሶ፣ ጉልቻ ጎልቶ፣ መሬት ተካፍሎ ቤቱን ሲሰራ በቀጣይነት የሚያሚላው ነገር መሳሪያ መሆኑ ነው። "አንድ ጎጃሜ የምትፈልገው ቀዳሚ ነገር ምንድን ነው ተብሎ ቢጠየቅ በመጀመሪያ መሬት ይላል ቀጣይ ምርጫው ግን መሳሪያ ነው" (አቶ ቻላቸው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። መሳሪያው ከውጭ ጠላት ይመጣል ከሚል ስጋት አይደለም። ነገር ግን፣ የመጀመሪያው ራሱን የቻለ ነው። ሁለተኛው ሽፍትነት በከፍተኛ ሁኔታ የተስፋፋበት አካባቢ በመሆኑ ነው። ሽፍትነት ካለ የውጭ ወረራ የለም ማለት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የበላይነቱን አስጠብቆ የሚቆይበት መሳሪያው በመሆኑ ነው ይላሉ አቶ እውነቱ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

የጎጃምን ገበሬዎች ስነ ባህርይና አስተሳሰብ ለመረዳት ስለ መሬት ወይም ስለርስት፣ ስለ እርሻ በሬና የጦር መሳሪያ አስፈላጊነት፣ እንዲሁም ስለ ሚስት ያላቸውን የጠለቀና ሥር የሰደደ አመለካከት በልዩ ልዩ ዘዴዎች መመርመርና ማጥናት ያስፈልጋል ይላሉ (ጌቱ በባዬ፣ 2000፣ 2049) ። በመሬት ወይም በአባት ርስት የተነሳ ስንቱ ገበሬ ሞቷል፣ ተጋድሏል፣ ወይም ደም ተቃብቷል፣ ስንቱ ሽፍቷል፣ ስንቱ አገር ጥሎ ተሰዷል ይላሉ። የመሬት ይዞታ ዋስትና ለገበሬው ከሁሉም

የበለጠ ክብሩና ማዕረጉ ነው። መሬት ለገበሬው ህይወቱ፣ ጉሮሮው፣ ትዳሩ፣ ሃብቱ ማለት ነው። መሬቱን፣ ሃብት-ንብረቱን፣ ራሱን፣ ቤተሰቡንና ዘመዶቹን ነቅቶ ለመጠበቅና ከጠላት ለመከላከል ደግሞ እንደአካባቢውና እንደዘመኑ ባህላዊ ወይም ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ይይዛል ወይም ይታጠቃል (ጌቱ ገላዬ በባዬ ውስጥ፣ 2000፣ 2049)።

ጉብዝና፣ የጀብደኝነት ስሜት የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ መገለጫ ጠባይ ነው ብሎ መውሰድ ባይቻልም፣ በላጋራና ጥቅም ላይ ስጋት የሆነ አካል ባለበት አውድ ውስጥ ግን ብቸኛ መከላከያ መንገድ ነው (አቶ አቻምየለህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በመሆኑም፣ በጎጃም ለመሳሪያ ትልቅ ቦታ ይሰጣል። የጨዋ ቤተሰብ ሆኖ ለአካለ መጠን የደረሰ እና ለጎጆ የበቃ ከሆነ፣ መሳሪያ መታጠቅ በነበረው ሥርዓት ተገቢና ትክክለኛ መለኪያ ነበር። መሳሪያ በአካባቢው የትልቅ ሰው ዘር ቤተሰብ መታያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር (አቶ አቻምየለህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ሰዎች ለመሳሪያ ሲሉ ወታደር፣ የጥበቃ ሰራተኛ ሆነው ይቀጠራሉ እየተባለም ይነገራል (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

4.5. የዝምድና መፍጠሪያ መንገዶች

የጎዛምን ማኅበረሰብ የእርስ በርስ ግንኙነቱን ለማደስና ለማጠንከር ዝምድና የሚፈጥርባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉት። በጎጃም ያለውን የዝምድና አይነት Getie (1998,74) የሥጋ ዝምድና፣ የጋብቻ ዝምድና እና በሃይማኖት ስነሥርዓት የሚበጅ ዝምድና በማለት በሦስት ይመድበታል ። Guday (2005,) ግን ጌቱ በኃየማኖታዊ ስነሥርዓት የሚበጅ ዝምድና ብለው የመደቡትን በሁለት በመክፈል ኃይማኖታዊና ማህበራዊ በሚል ለያይተው ይገልጹታል ። በጎዛምን አካባቢ ያለው የሥጋ ዝምድና እስከ ሰባት ቤት የሚዘልቅ ሆኖ ምንጅላት፣ ቅማንት፣ ቅድመአያት፣ አያት፣ አባት፣ እናት፣ ልጅ በሚል የሚቆጠር ነው። የጎንዮሽ ዝምድና በቀጥተኛ መንገድ እህት ወንድም፣ አክስት፣ አጎት በሚል ይጠራል። በአንድ ወገን የሚወለዱ የአባት ወይም የእናት ልጆች ሲሆኑ የአባት ልጅ፣ የወንድም ልጅ፣ የእህት ልጅ የሚል ስም ይሰጠዋል።

በጋብቻ የሚመሰረተው ዝምድና ልዩ ልዩ መልክ ያለው ነው። ቤተሰብ መርጠና ፈቅዶ ወይም በልጆች ስምምነት ተወስኖ ሽማግሌ ተልኮ በይፋና በዕውቅና የሚጋቡ ሰዎች ባልና ሚስት ይባላል። አንዳንድ ጊዜ አግበተው ልጅ ወልደው፣ ቤታቸው ሞቆ ሳለ ከተጋቢዎች መካከል አንዱ ወንዱ በሞት ሲለይ ሀብት አይቶ የሚመሰረት ጋብቻ "ተከርችም" ይባላል። ወላጆች በፍቅር፣ በጓደኝነትና በተለያዩ ምክንያቶች ያዳበሩትን መቀራረብ በዝምድና ለማሰርና ለማጠንከር ሲፈልጉ፣ "ልጅህ ለልጄ" በሚል ቃል ተግባብተው ለአቅመ ጋብቻ ያልደረሱ ልጆች አብረው አድገው ለአካለ መጠን ሲደርሱ የሚመሰርቱት 'የማደጎ ጋብቻ' ይባላል (አቶ መ.ለ.ቀን፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)።

ለጋብቻው ይህን ስም ያሰጠው ዕድሚያቸው ከአሥር ዓመት በታች የሆኑ ልጆች አብረው አድገው እህቱ ወንድሜ እየተባባሉ ኖረው ሲደርሱ ጉልቻ ጎልተው ጎጆ ቀልሰው የሚኖሩ በመሆኑ ነው። በአካባቢው የተለመደ *"ገንፎ ቀቂ"* የሚባል ሌላ የጋብቻ ዓይነት አለ። ይኸ ጋብቻ ጸም ሊገባ አካባቢ በሚካሄድ ሠርግ የሚፈጸም ሆኖ፣ አንድ ሰው የሆነ ቤተሰብ ለምኖ፣ ተለማኙም ይሁንታውን ገልጾ፣ ተስማምቶ፣ ነገሩ መንገድ ከያዘ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ችግር ተከስቶ አንድርልህም ሲባል ወይም የሆነ ምክንያት ተፈጥሮ በሴት ቤተሰብ የተነሳ ጋብቻው እንቅፋት ሲገጥመው፣ ዝግጅቱ አልቆ፣ ወዳጅ ዘመድ ተጠርቶ፣ የሩቅ የቅርብ ዘመድ እህል ውሃ ሞኖ ከመጣ በኋላ ነገሩ ሲከሰት መ.ሽራው በመንገድ ሲሄድ ያገኛትን ጠይቆ ያገባል። መንገድ ላይ የተገኘችው ሴት የምትወሰደው ተስማምታ ነው። በዚህ የጋብቻ አይነት ውስጥ የሚሳተፉት የደሃና የሴተኛ አዳሪ ልጆች እንዲሁም አባትና ወንድም የሌላቸው ወገን አልባ ተገፊ ሴቶች ናቸው (አቶ መ.ለ.ቀን፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28 የተደረገ ቃለመጠይቅ)።

ይቺ ሴት በክብርና በማዕረግ የተመረጠች ሳትሆን፣ የተዘጋጀው ስርዓት እንዳይበላሽ በማሚያነት የተያዘች፣ ተፈልጋና ተለይታ፣ ታስባና ተጠንታ የተወሰደች ሳትሆን፣ በማነሷና ባለመፈለጓ ምክንያት የተጠየቀች የቀን ማሚያና የድግስ ማድመቂያ ሴት ነች። ስም የማውጣት ስርዓት ሲደረግ በዚህ መልክ ለተዳሩ ሴቶች የሚወጣላቸው "ድንጉቴ"፣ "አልታሰብሽ" ተብሎ ነው (አቶ መ.ለ.ቀን፣2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28 የተደረገ

ቃለመጠይቅ)። ከጀርባው አለመፈለግ፣ አጋጣሚ ያመጣው ድንገተኛ ጋብቻ እንዳለበት ይገለጽበታል። *ሾጭን ገረድ*' በቤት ውስጥ እየኖረች እንደ ሚስትም እንደ ሠራተኛም ሆና የምታገለግል ሴት ነች። በድሮ ጊዜ ከመኳንንቶችና ከመሳፍንቶች ጋር አብረው እየተንቀሳቀሱ ለጌታቸው በጉልበታቸውም ሆነ በግብረ ስጋ ግንኙነት አገልግሎት የሚሰጡ ነበሩ (አቶ ይልቃል፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ለዚህ ተግባር የሚመረጡ ሴቶች የጨዋው ወገን ያልሆኑ፣ ማህበረሰቡ ባሪያ ወይም አገልጋይ ብሎ የሚያርቃቸው ብዙም ክብር የሌላቸው የተገለሉ ቡድኖች ናቸው። እነዚህ ወገኖች ሃብትና ንብረት የሌላቸው በሰው ቤት ተቀጥረው በዕለት ሆድ እየተገዙ በጉልበታቸው የሚኖሩ ናቸው። በተክለሰውነታቸው ደህና የሆኑት በአሳዳሪዎቻቸው እየተመረጡ የጭን ገረድ ይሆናሉ። አኗኗሯቸውም ከዋናዋ ሚስት ጋር በአንድ ቤት ውስጥ ነው።

ይቺ ሴት ለእመቤቲቷ ስራ ትሰራለች፣ ትታዘዛለች። ለሰውዬውም የሚስት አከል ትሆናለች። ሁኔታው በምስጢር የሚፈጸም ሳይሆን፣ በሚስት ዕውቅናና ፈቃደኛነት የሚሆን ነው እየተባለ ይነገራል (አቶ ይልቃል፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሚስት አንዳንድ ጊዜ የጭን ገረዷን አጥባና አሳምራ ከባሏ ጋር እንድትተኛ ታደርጋታለች እየተባለ ይወራል። የጭን ገረዷን እንደ ባላንጋራ ሳይሆን በስራም ሆነ በአልጋ ላይ እመቤቲቱን አሳራፊ (sex partner) ነች። ማህበራዊ ደረጀዋ እመቤት ለመሆን ስለማያስችላት፣ ወንድዬውን ቤት ውስጥ በማዳከምና አማራጭ በማቅረብ ወደ ውጭ እንዳያይ ማድረጊያ ስልት አድርገው የቤት እመቤቶች ይጠቀሙባቸዋል እየተባለ ይነገራል።

"ቅምጥ" ግን በሚስት ላይ የተደረበች የድብቅ ሚስት ነች (አቶ ሙሉቀን፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። ይች ሴት እህል እየተሰፈረላት፣ ገንዘብ እየተቆረጠላት የምትወልድ የውጭ የሚስጢር ሚስት ነች። ለቅምጥ የሚመረጡ ሴቶች በማህበራዊ መደባቸው የሚመጥኑ፣ በዘራቸው ከጨዋውና ከባላባቱ ወገን የሆኑ ናቸው (አቶ ሙሉቀን፣ 2006ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። በአካባቢው በቀደመው ዘመን ከአንድ በላይ ቅምጠኞን መያዝና ማበጀት እንደ ክብር ይታይ ስለነበር ጉዳዩን እንደነውር ከማየት ይልቅ እንደ ጀግንነት፣ ብዙ መያዝን እንደ

ዕድለኛ ሁለ ያስቆጥር ነበር (አቶ መ.ለ.ቀን፣ 2006 ዓ/ም፣ ሀዳር 28 የተደረገ ቃለመጠይቅ)። በአሁኑ ጊዜ ቅምጥ ባይኖርም ከከተማ መስፋፋትና ከዘመናዊነት ጋር ተያይዞ ስሙ "ውሽማ" በሚል ይታወቃል (አቶ ይልቃል፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በቅምጥነት ወይም በውሽምነት የሚሰማሩ ሴቶች አግብተው የፈቱ፣ መካኖች፣ ባሎቻቸው የሞቱባቸውና መሰል ችግሮች የገጠማቸው ናቸው (አቶ ይልቃል፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በአካባቢው አንድን ወንድ በባልነት የያዙ ሁለት ሴቶች "ማውንቶሽ" ወይም "ጎባኖች" ይባላሉ (አቶ ይልቃ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ ባላንጣዎች ብዙ የሚያቀናቅናቸው ጉዳይ አለ። ሁለቱ አንድ የጋራ ባል አላቸው። ከዚህ ባል ሁለቱም የሚያፈሯቸው ልጆች ይኖሯቸዋል። በአካባቢ የገቢ ምንጩ ባል ስለሆነ ከአንድ ምንጭ የሚገኝን ገቢ ተካፋዮች ናቸው። በሁለቱ ሴቶች መካከል ያለው ልዩነት አንደ በይፋ የምትታወቅ ህጋዊ ሚስት ስትሆን፣ ሌላኛው በባል ምርጫ የተያዘች በሆነ መልካም ነገር የተመረጠች አካል መሆኗ ነው።

በዚህ አማካይነት የሚፈጠረው ጋብቻ ከተለያዩ ቤተሰቦች የሚወለዱ የአንድ አባት ልጆችን ስለሚያስገኝ በሀብት ክፍፍል ጊዜ ለሚፈጠሩ ቅራኔዎች ዋናው ስበብ ነው። ከተለያዩ እናቶች በሚወለዱ የአንድ አባት ልጆች መካከል የቤት ልጅና የውጭ ልጅ የሚል አከፋፈልና ለያይቶ ማየት በመኖሩ በልጆች መካከል ያለው ግንኙነት በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ነው። በአባት ንብረት ላይ የሃብት ተቀናቃኝነት ስለሚፈጥርና ከዝምድናው ይልቅ ለንብረቱ ቅድሚያ ስለሚሰጥ ወንድም ወንድሙን በመካድ፣ ተካፋዬ ነው ብሎ በመስጋት በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት በጥላቻ የተሞላ ያደርገዋል።

ከውጭ የተወለዱ ልጆችም መብታቸውን ለማስከበር ተወላጅነታቸውን ለማሳወቅ ወንድሞቻቸውን ከስሰው ለማሸነፍ ይተጋሉ። ይህ ሁኔታ ወንድም ወንድሙን እየከሰሰ፣ ከዝምድናው ይልቅ ሀብቱን እንዲወድ፣ ስጋኑን እየጠላ ለመገዳደልና ለመጠቃቃት ምክንያት እየሆነ በአካባቢው ችግር ሆኖ ይታያል። በሥጋ የማይዛመዱና በጋብቻም ያልተሳሰሩ ሆነው ዝምድና በሚፈልጉ ጊዜ አማራጭ ሆኖ

የሚመጣው ሌላኛው መተሳሰሪያ መንገድ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ የዝምድና ዘዴ ነው፡፡ በሃይማኖት የክርስትና አባትና እናት፣ የክርስትና ልጅ፣ የነፍስ አባት፣ የነፍስ ልጅ በሚል ይገናኛሉ፡፡ በማህበራዊ ዝምድና በኩል የጡት ልጅ፣ የጡት አባት፣ የጡት እናት በሚል ይዛመዳሉ፡፡

5. የክፉ ዓይን እሳቤና የማደሪያ አካሎች ምንነት

በዚህ ምዕራፍ በክፉ ዐይን ምንነት ላይ ህብረተሰቡ ያለው አመለካከት ምን እንደሆነ፣ ስለመንፈሱ ባህርት፣ ማደሪያ በመሆን ስለሚያገለግሉ ሰዎች አይነት መተላለፊያ መንገድ፣ ክፉ ስለሚባሉ እንስሳትና ተክሎች አይነትና ጠባይ ማብራሪያ ይሰጣል።

5.1. የክፉ ዐይን መንፈስ ምንነት

ከክፉ መንፈሶች መካከል አንዱ የሆነው ክፉ ዐይን በአካባቢው ማኅበረሰብ የሚታሰበው፣ "በአካል ውስጥ የሚቀመጥ ቀሳፊ ኃይል ተደርጎ ነው" (አቶ ቅሩብ፣ 2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። ይህ ኃይል እንደ ሰይጣን ያለ ፍጥረት ሆኖ በሰዎች ዐይን ላይ በማደርና በልቦናቸው ላይ በመተከል፣ ጤናን ያውካል፣ እንዲሁም አእምሯዊ ሚዛንን ያናጋል ይሉታል (አቶ ቅሩብ፣ 2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። ሰዎችን በማፍዘዝ፣ የተረጋጋ ሰብዕና በማሳጣት፣ አመዛዛኝ ህሊናና አስተዋሽ ልቦና በመንሳት፣ ከንቱነት የሚተክል ነው እያለ ይገልጹታል። የሰው ልጅ ማሰብ እንዳይችል ልቦናውን ጠልፈው በመያዝ የመመርመር፣ የማስተዋል ኃይልን በማስነፍና በማድከም፣ በኑሮ ላይ ግዴለሽና ብኩን አድርጎ ያስቀራል እያለ አቶ ቅሩብ ይገልጹታል።

ደስታ ተክለወልድ (1975፣ 152) ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በሚለው መጽሐፋቸው ክፉ ዐይንን፣ "ጋኔን፣ ዛር በ-ዳ፣ ዛር ጋኔን፣ ዐይነ ወርቅ፣ ዐይነ ወግ" እያለ ይገልጹታል። ይህ ኃይል አካል ላይ የሚሰለጥን ነው። ህሊና ላይ ተጠምጥሞ ቀልብን የሚቆጣጠርና ራስን የሚያስረሳ ነው። እያስለፈለፈና እያስቀባጠረ፣ እንደ ከብት አተላ እያስጠጣና እንደ ሸቦ እያስጎነበሰና እያስነከሰ፣ ሰውነትን በማስተው አውሬ የሚያደርግ ነው (ደስታ ተክለወልድ፣ 1975፣ 152) ።

አቶ ቅሩብ (2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) እንደሚገልጹት፣ "ባህሉ ከሚፈቅደውና ማህበራዊ ህይወት ከሚያዝዘው የወጣ ዐመልና ጠባይ ያስለምዳል"፣ ከባህልና ከማህበራዊ አኗኗር የተለየ አመል ያስይዛል ይሉታል። ከሚታወቀውና ሰው ከተቀበለው፣ ከሚፈቀደውና ከሚያደረገው የተለየና ፍጽም ያልተገባ የነውር

ሥራ የሚያስደርግና እንግዳ ነገርን የሚያስተዋውቅ ነው (ወ/ሮ ውዴ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 5፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በነዛም ሰው እሳቤ ውስጥ በምድር ላይ በሚንቀሳቀሱ ሁሉም ፍጥረቶች ባህርይ ውስጥ አራት ነገሮች አሉ ተብሎ ይታመናል (መርጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እነሱም ውሃ፣ መሬት፣ ነፋስና እሳት ናቸው። እነዚህ አራቱ ነገሮች በመዋሃድ የሚያስገኙትን አካል የሚጠራው 'ሥጋ' ተብሎ ነው ይላሉ። በሰው አሰራር ውስጥ በመጀመሪያ ቀድሞ የሚቆመው ይኸው አካል (ማለትም ሥጋው) ነው ተብሎ ይታመናል። አራቱ ግብራት ሥጋዎች በሰው አሰራር ውስጥ አካልን የሚፈጥሩ ወሳኞቹ አላባዎች ሆነው፣ የሰው ልጅ የተለያየ ጠባይና ልማድ እንዲይዝ ምክንያቶች የሚሆኑ ናቸው (መርጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በዚህ አካል ላይ የህይወት መሠረት የሆነችው "ነፍስ" ስትዘራበት ደግሞ "ሰው" የሚባል ፍጡር ይበቅላል ወይም የሚገኝ ይሆናል በማለት አመጣጡን ይተርካሉ። ይቺ ነፍስ በራሷ ሦስት ባሕርዮች ያሏት ስትሆን፤ ልባዊት፣ ነባቢትና ህያዊት በሚል ይታወቃሉ (መርጌታ፣ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ነብስ የሰውን ልጅ ከማዕዝ አካል ወደ ስብአዊ ፍጡር የምታሸጋግር ሆና፣ ሦስት ባሕርዮቿ የየራሳቸው አገልግሎት ይኖራቸዋል (መርጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)። የማሰብ መሰረት የሆነችው "ልባዊት"፣ የልሳን አካል የሆነችው፣ "ነባቢት"፣ የእስትንፋስና የህይወት ምንጯዋ ደግሞ "ህያዊት" በሚል የሚጠራ ነው። ስለዚህ፣ ሥጋና ነፍስ ሲዋሃዱ ሰብዕና የሚባለው ባህርይ የሚገኝ ይሆናል። ነፍስም ቁጥር በተሰጠው ሰው አካል ውስጥ ቦታ አግኝታ ስታድር የወል መጠሪያነቷን ትታ በአደረችበት አካል ስም የእከሌ ነፍስ እየተባለች መጠራት ትጀምራለች ይላሉ (መርጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እያንዳንዱ ሰውም የዚህ ባህርይ ያላት የነፍስ ክፋይ በሰውነቱ ውስጥ ይይዛል በማለት ያስረዳሉ።

በመሆኑም፣ ያ በነፍስና በሥጋ ውህደት በተፈጠረው ሰው አካል ውስጥ ራስን መግዛት ሲጠፋ ቀልብን መስብሰብ ይጠፋል ይላሉ መርጌታ አይነኩሉ። አዕምሮ

ሲሰንፍ፣ ማሰብ ሲፈዝና ማስተዋል ሲደክም ይህንን ክፍል የምተቆጣጠረው ክፍል ተለይታ ተመታች ይባላል (መርጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በዚህን ጊዜ ልባዊት ተጠልፋ ተያዘች እንላለን። የልባዊት መፍዘዝ ማሰብን ስለሚያጓድል፣ ነፈዝ፣ ሞኝ ወይም አላዋቂ፣ ሰነፍና እንስሳ የሚሆነው በዚህ ጉድለት ምክንያት ነው ይላሉ (መርጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)። የሰውን ልጅ ከእንስሳትና ከሌሎች ፍጥረቶች የምትለየው ይችው ክፍል ትሆናለች። ክፉ ዐይንም ይህንን ክፍል በመተካት በአካል ላይ በመንግስ ማህበራዊውን ሰው አውሬ፣ ባህል አልባና እንግዳ፣ ወግ የሌለውና ልምድን የናቀ ያደርገዋል (መርጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በአንደበቱ በሽታ ሲሞርበት ደግሞ መናገር ያቅተዋል፤ ልሳኑ ይተሳሰራል። በዚህ ጊዜ ነባቢት ተለጉማ፣ ያ ክፍል ብቻውን ተለይቶ በሽተኛ ሆነ ይባላል (መርጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በዚህ ጊዜ አፉ ዲዳ ይሆናል፤ ምኞትና ሃሳቡን መግለጽ ይሳነዋል። ልሳን ተዘግቶና አእምሮ ተሰውሮ በህይወት መኖር ይቻላል። የሰው ልጅ ሥጋና ነፍስ ሙሉ በሙሉ የሚነጣጠሉት እስትንፋስ ተመትታ ለሥጋ የምትሰጠውን አገልግሎት ስታቋርጥ ነው ይላሉ መርጌታ ዲበኩሉ። ክፉ ዐይን ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታሰበው ከነፍስ ክፍል ውስጥ የማወቅ ኃይል በሆነችውና የማሰብ መሰረት ናት ተብላ በምትታሰበው በ'ልባዊት' ላይ ነው (መርጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በመሆኑም፣ በዚህ ኃይል የተመታ ሰው፣ ዕውቀቱ፣ ማስተዋሉና መመርመሩ ስለሚጎድል የምናውቀው ሰው አይሆንም። እሱም የሚያደርገውን ልብ አይልም በማለት ይገልጹታል። ከሚታወቀውና ከሚታሰበው፣ ከተለመደውና ከተዘወተረው አሠራር የወጣ ነገርን ማድረግ ይለማመዳል። ሰውነቱን እያስረሳ የእንስሳ ግብር እየሰጠ፣ ማህበረሰቡ በሚጠላቸውና ክፉ ብሎ በሰየማቸው ፍጥረታት ግብር ያስጠራዋል ይላሉ (መርጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)። በዚህ መንፈስ የተጎዳ ሰው የሚያደርገውን ነገር ውዴ (2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 5 በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ሲገልፁ፣

ማህበረሰቡ ተጠቅሞና መጥጦ የጣለውን የተናቀውን አተላና ዐመድ ያስበላል። ራስን አስረስቶና በህሊናና በዕውቀት መመራት አስትቶ ወደ ሌላና የማይታወቅ እንግዳና አስፈሪ፣ ሰዋዊ ነገሩን የተወና የወጣ ጠባይ የሚያሳይ የአውሬነት ባህርይ ያለው ነገር ያስሆናል። እንደ ጅብ ያስጮኻል፣ ያስነክሳል፣ ያራምዳል። ይህ ኃይል ቀልብን ገዝቶ ህሊናን አስሮ በምትክ ስለሚነግስ ሰውን ከማህበራዊ ፍጡርነቱ አውጥቶ ወደ አልተለመደና እንግዳ ወደ ሆነ ጠባይ ይጨምረዋል።

እነዚህ ሰዎች፣ ይህ መንፈስ ከተጣባቸው በኋላ ጤነኛው ሰው የሚያደርገውን አያደርጉም። ወጥ ባህርይ ማሳየት ይቸግራሉ። በማያስቀው መሳቅ፣ በማያስኮርፈው ከንፈርን መጣል፣ ከመሬት ተነስቶ ማልቀስና መነጫነጭ ያበዛሉ ይሏቸዋል (አቶ ቅሩብ፣ 2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። መጨናነቅ፣ መቅበዝበዝ፣ በሃሳበ መወጠርና መረበሽ ሰሞነኛ ጠባያቸው ይሆናል። ሰውን ማየት ይጠላሉ፣ የሚያዋራቸው እና ትክ ብሎ የሚያያቸውን ሰው መመልከት ይፈራሉ። ብቸኝነት ያስወድዳቸዋል። መነጫነጭና መቀባጠር፣ ግራ ከተጋባ ነገር ላይ ይወድቃሉ። ቅልል ቅልል ማለት፣ መንከውከው፣ ጥርስን ማንቀራጨጭና ማፋጨት የሚያሳዩዋቸው የተለመዱ ምልክቶች ናቸው ይሏቸዋል። እነዚህ ነገሮች ምልክት ሆነው በሰዎች ላይ ሲታዩ፣ መንፈሱ በሰዎች ህሊና ውስጥ ለማደሩ ጠቋሚ ምልክት ይሆናል ይባላል።

የዚህን ኃይል ምንነት የገለፁት ሌላኛው የመረጃ አቀባይ ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ክፉ ዐይንን፣ "በሚንቀሳቀሱና በሚሳቡ ፍጥረቶች ላይ በመዋሃድ ህይወት ያለው ነገር ሁሉ እንዳይራባና እንዳይቀጥል የሚያደርግ ክፉ ፍጥረት" በማለት ነው። በሰው ልጆች ደምና አእምሮ እንዲሁም መንፈስ እየተሰራጨና እየተዘራ፣ ህሊናን እየሳበና አእምሮን እያሰረ ወደ ፊቀደው የሚመራ መራኄ ኃይል ነው ይለታል።

ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ ይህ መንፈስ ስለሚፈልገው ፍጥረት ጠባይ ሲገልጹ፣ "የሞተንና የደከመን፣ አቅም ያጣንና የደኸየን፣ ተስፋ የቆረጠንና የተጨነቀን ሰው፣ አፈንጋጭ ጠባይ ያለውን ተክል እና እንስሳን ይጠጋል በማለት ነው(2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ግራ በተጋባና በወላወለ አካል ላይ አርፎ የልብ

ABABA
LIBRARIES
O. BOX 11
ABABA

ፈቃድን በራስ ምኞትና ጠባይ ሊመራ ይፈልጋል ይሉታል። በማጣት የሚጠቀምና በሀዘን የሚከብር መልካም ያልሆነ መንፈስ በማለት ይገልጹታል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ምክንያቱን ሲገልጹም፣ ክፉ ዐይን የሚከብረው ስስት፣ ስግብግብነት፣ ራስን ወዳድነት ባለበት ሥጋ በሚከብርበት አጋጣሚ ነው ይላሉ።

በአካባቢው አንድ ሰው ሞተ የሚባለው ነፍስና ሥጋው ሲለያዩ ነው። ይህ የሚመጣው ደግሞ በነፍስና በሥጋ መካከል የባሕርይ መጣጣም ሲጠፋ ነው። ሥጋ በሚዛንና በመጠን አልገዛ ሲልና ለነፍስ የሚመች ነገር ማድረግ ሲያቆም ነፍስ ትለያለች(ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ አንድ ሰው የሚሞተው ነፍስ ስትለየው ነው ይላሉ። ነፍስ የምተለየው ደግሞ ሥጋ በሰብዕና ውስጥ በዝቶ ሲከብር ነው ይላሉ። የሥጋ ሥራ ተብለው የሚታሰቡት ደግሞ ስስት፣ ራስ ወዳድነት፣ ትዕቢት፣ ስርቆት፣ ውሸት፣ ዝሙትና የመሳሰሉት ፈቃዶች ናቸው። በመሆኑም፣ በመጎዳት የሚጠቀም፣ በደስታ ሳይሆን በሃዘን የሚደሰት ኃይል ነው ሲሉ ይገልጹታል ።

በመሆኑም፣ የዚህ ሃይል ተጠቃሚነት ከህይወት ሳይሆን ከሞት ነው። የሙት ሃሳብ ያላቸውን ቢከተልም፣ ሰው ደክሞ እስካልተሳሳተ ድረስ መንፈሱ ስለፈለግ ማንንም ሊያጠቃ አይቻለውም ይላሉ። መልካም ነገር ያለበት ቦታ የእሱ ስላልሆነ አይደርስም። እሱም ሆን ብሎ መጥፎ ነገር እንዲያደርጉ አያሳስትም በማለት ያስረዳሉ። የሰውን ውድቀት ጠብቆ የሚተክል እንጂ፣ ነፍስን በኃይል ነቅሎ የሚደላደል አይደለም በማለት ተጋላፊ፣ ራሱ ሰውዬው መሆኑን ይናገራሉ። ይሽን ሃሳብ የሚያስረዳ አንድ አፈታሪክ አጫውተውኝ ነበር (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

> ዓለም በቃኝ ብሎ የመነነ አንድ መነኩሴ ነበር። ይህ ሰው እንደሄደ የገዳም ህይወት በተለይ ርሃብ መቋቋም ይከብደዋል። አንድ ቀን ይርበውና ቢዞር ቢዞር የሚበላ ነገር ያጣል። በርሃ ለበረሃ እየተዘዋወረ ሲፈልግ የቆቅ እንቁላል ወድቆ ያገኛል። እሷን ይዞ ቤቱ ይገባና ክብሪት ለኩሶ ጧፍ ያያይዛል። ከዚያ እንቁላሏን በእጁ ይዞ በጧፍ መጥበስ ይጀምራል። በአጋጣሚ አለቃው ብቅ ይላሉ። ምነው ልጄ ምን እየደረግክ ነው ይሉታል

የሚያደርገውን አይተው፡፡ የኔታ ይቅር ይበሉኝ ጋኔል አሳስቶኝ ነው ይላል፡፡ ጋኔን ደግሞ መነምነኮቱን አይቶ በአምሮቱ ሊገባ ጥግ ይዞ ይሰማ ስለነበር የመነኩሴውን ምክንያት ሲሰማ ተቆጥቶ፣ "አባ ይቺን ጥበብ እኔም ዛሬ ነው ያየኋት" አለ ይባላል፡፡

በመሆኑም፣ ክፉ ኃይሎች በሰው ድክመትና ስህተት የሚገቡ፣ በመጋለጥ የሚጠቀሙ እንጅ የፈለጉትን የሚያጠቁ፣ ያሹትን የሚይዙ አይደሉም ይላሉ፡፡ ይኸ ኃይል፣ "ራሳችን ካልፈቀድንለት አይቀርበንም፡፡ የሚመቸውን ግብር ካላደረግን አይመጣብንም" ይላሉ፡፡ አንድ ጊዜ፣ ባልና ሚስት ተጣልተው ሲጨቃጨቁ ሁለት ክፉ መንፈሶች ቆመው ይሰሟቸዋል፡፡ ከዚያ አንዱ እንግባ ይላል፡፡ ሌላኛው ሳይጠሩን አንገባም ብሎት ቆመው ያዳምጣሉ፡፡ ጭቅጭቁ እየተባባሰ ሄዶ ሰውዬው ራሱን መቆጣጠር ያቅተውና፣ "እንግዲህ ሰይጣኔን አታምጪው" ሲላት፣ አሁን ጠሩን በል እንግባ አለ ይባላል(ሰዋገኝ[21]፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡

የአካባቢው ሰው ተክሎች ነቅዘው ሲያይ፣ እህል በርብሮ ማለቁን ሲመለከት፣ አዝመራው በረድ መትቶት መርገፉን ሲያስተውል ክፉ ዐይን አርፎበት ነው ብሎ ያስባል እያለ አቶ ቅሩብ አንተነህ ይናገራሉ (2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)፡፡ ከብቶቹን እየከተረበት አልረባ ብለው ሲቸገር፣ ጡታቸው ደርቆ፣ ሽላቸው ነጥፎ መምሰናቸውን ሲረዳ ክፉ ዐይን አድሮባቸው ነው ብሎ ያስባል ይላሉ፡፡ የሰው ልጅ አካሉ እየሰለለና እየመነመነ ሲሄድ፣ እራሱን እየጠላና እየናቀ ብቻ መዋልን ሲወድ፣ ይህ ክፉ ነገር ተጣባው ይላሉ፡፡ እንስሳት ሳር መጋጥ እየተው፣ እየነሰቆሉና እየከሱ ሄደው አደግድገው ሲሞቱ፣ ቁመኛ ተጣብቷቸው ነው ይባላል (አቶ ተዘራ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡

ይህ ኃይል ከህይወት ይልቅ በሞት የሚከብረው በጥንካሬ ውስጥ ነፍስ ስለምትበረታ ነው ይላሉ፡፡ ነፍስ ከተመቻት ለሥጋ ጤና ይሆናል፡፡ የነፍስ ምቾት ሥጋ በምጣኔ ተገርቶ ሲኖር ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ነፍስ በአካል ውስጥ ከሥጋ ጋር ያላት ዝምድና ጥብቅ ስለሚሆን ተጋላጭነት አይመጣም ይላሉ፡፡

[21] ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ የነገሩኝን የመነኩሴውን ታሪክ ሳጫውታት እንዲህም ይባላል እኮ በማለት ቤተ መጻሕፍት ተቀምጠን ያጫወተችኝ ነው፡፡

በድካም ውስጥ ግን ባዶነት ስላለ ገብቶ ለመንሳራፋት ከልካይ ስለማይኖር ክፉ ዐይኑ የነፍስን ቦታ ተክቶ ይደላደላል ይላሉ አቶ ቅሩብ (2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ የክፉ ዐይን የሚሆነው ነፍስ በተለየችው በባዶው አካል፣ በማይፈለገው፣ በተጠላውና ጥቅም በማይሰጠው በሞተውና በፈረሰው ነው። በቀናውና ሥርዓት በያዘው ክልል፣ ደግ በሚደረግበትና ደፍረው በሚኖርበት ቦታ ላይ አይጠጋም። ነስቂሎና ከስቶ፣ ሰንፎና አቅም አንሶት የታየውን መርጠው እንዳሻቸው ይሆኑበታል።

ለዚህ ዓላማቸው እንግዳና ያልተለመደ ነገር ይመቻቸዋል፤ ለወል ልማድ የማይገዙትና ስስትና ብቸኝነት፣ ትዕቢትና ማንአለብኝነት በሚያጠቃቸው ላይ ይበረታል (አቶ ተዘራ አስማረ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ። ይህ የሚሆነው እነዚህ ግብሮች ነፍስን ስለሚያቆሽሹ ነው ይላሉ። በመሆኑም፣ እንደሞት ያሉ አቅምን የሚነሱና ጉልበትን የሚያሳንሱ፤ እንደ ህመም፣ እርጅና፣ ድካምን የሚያመጡ ጠባዮች ለክፉ ዐይን ማደሪያ ይሆናሉ ይላሉ ውዴ(2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባሕርይውን በሚዛንና በምጣኔ ካላስኬደ፣ ለማህበራዊነት ካልኖረ፣ ስስትና ስግብግብነት ካበዛ፣ ትክክል ብሎ ማህበረሰቡ ያጸደቃቸውን ደንቦችና እሴቶች አጽንኦ ካልተጓዘ የመተዳደሪያ ልምዶች እንዳይከበሩና ዋጋና ጥቅም እንዳይኖራቸው ካደረገ ይኸ ነገር ይመጣበታል ይላሉ (ወ/ሮ ውዴ፣ 2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ።

ሊቀ ትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ ደግሞ ቀድሞ ለተገኘ ወይም ለጸና ልማድ ውዴታና አክብሮት በመንፈግ፣ በጸናውና በከበረው መጠቀምን በማደነቃቀፍ፣ ረብሻና ነውጥ በማቀጣጠል፣ ሥርዓቱን በማበስበስና በማርከስ በግሉ ሊጠቀም የሚፈልግ ሰው ሲገኝ ይህ ስም ይሰጠዋል ይላሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ አቶ ዮሴፍ (1997፣ 87) የተባለ በጥላትግን ወረዳ የግጭት አፈታት ላይ ሲያጠና ለሽምግልና የማይገዛ ሰው ከእሴቱ ያፈነገጠ ሰይጣን እንደሚባል ያቀረበው አንድ አፈ ታሪክ ይኸንን ሃሳብ የሚያጎለብት ነው ።

> ልጅ አልወልድ ብለው የሚጨነቁ አንድ ባልና ሚስት ነበሩ። ባልዬው ሚስቱ ባለመውለዷ እየተበሳጨ በየጊዜው ያገኘን ነበር። ሚስቱም መሀን ሆኜ ነው ያልወለድኩ እያለች

አብዝታ ትጨነቅ ነበር።።ብዙ ጊዜም ለታቦት ተስላ ሳትወልድ ትቀራለች።። ባሏ ደግሞ ሌላ የምትወልድ ሴት በድብቅ መፈለጉን ሰማችና ትቃጠል ጀመር።። እንግዲህ ለየታቦቱ ሁሉ ምን ተሻለኝ?" ብላ ስታስብ አንድ ነገር ትዝ አላት።። ለሰይጣን መሳል።። "ሰይጣን ልጅ የወለድኩ እንደሆነ ፈትዬ ጋቢ አስርቼ አለብስሃለሁ" ብላ ቃል ትገባለታለች።። ወዲያው ስለድ ሰመረላትና አረገዘች።። ባሏም ማርገዟን ሲያውቅ በስበብ ባስባቡ መጣላቱን ተወና ፍቅር ሆኑ።። ቀኗ ደርሶ በ9ኛ ወሯ ተገላገለች።።ታርሳ ስትወጣ ስለድን ለማድረስ ብትፈልግ ሰይጣንን የት እንደምታገኘው ግራ ገባት።። ሰውን ሁሉ ብትጠይቅ የሚገኝበት የት እንደሆነ ማወቅ ተቸገረች።። አንድ ሽማግሌ ግን የሚገኝበትን ቦታ ነገራት።።" ሰይጣንን የምታገኘው ሽምግልና ቦታ ነው።። ሰዎች ተጣልተው ከሚታረቁበት ቦታ ሂጂ።። ከዚያም ሽምግልናውን አፍርሶ አልታረቅም ብሎ የሚሄደው ሰው እሱ ሰይጣን ነው" ይሏታል።። ሴትዮዋም የሽማግሌውን ምክር ተቀብላ ሽምግልና ባለበት ቦታ ሁሉ እየሄደች አልታረቅም የሚል ሰው ትፈልግ ጀመር።። አንድ ቀን አንድ ሰው አልታረቅም ብሎ ሽምግልናውን አፍርሶ ሲሄድ ከኋላው እየሮጠች ተከትላው ሄደችና "ጌታው ፈልጌህ ነበር አለችው።። ሰውዬውም ቆም ብሎ "ለምን ፈለግሽኝ" አላት።። እሷም የስለድን ታሪክ ከነገረችው በኋላ ለማን እንደምትሰጠው ተጨንቃ ሰው ስትጠይቅ ከሽምግልና አልታረቅም ብሎ የሚወጣው ሰው እሱ ነው ሰይጣን ስላሉኝ እንካ ስለቴን ተቀበለኝ አለችው።። ሰውዬውም ተገረመና "እኔ ነኝ ሰይጣን?" በማለት ተመልሶ ሄዶ ታረቀ ይባላል (ዮሴፍ፣ 1997፣ 87)

በመሆኑም፣ ለነባሩ ልማድ ግዴለሽ መሆን፣ ለልዩነት ዋጋና ክብር መስጠት፣ ልዩ ሆኖ ለመታየት መሞከር አጋላጮች ይሆናል።። ዘግይቶ ደራሽና እንግዳ ነገር ከተለመደው የወጣ በመሆኑ ስመ ይኸው ነው።። በመሆኑም፣ የልምድ ማነስ ያለበት ቦታና አጋጣሚ መጉደልና ማጣት የበዛበት አውድ፣ በደልና ማለቅ የተስፋፋበት አውድ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል ይባላል።። ክፉ ኃይሉ ግራ ከተጋቡትና ካዘኑት ላይ አይጠፋም ይሉታል።። ማህበራዊ ተቋመ ሊፈታቸው ያልቻሉ ችግሮች ባሉበትና ለማፈንገጥ በሚሞክሩ ሰዎች፣ ተክሎች እና እንስሳት ላይ ይገለጣል ይሉታል።። ደካማ ጎንን አጥንቶ በዚያው ለመጠቀም ይጥራል።።

ከታሪኩ ለማየት እንደቻልነው ስለድን ልታስገባ ስትሄድ ታጠዋለች።። ግን ሰይጣን ተብሎ የተገለጸላት ደግሞ ማህበራዊ እርቅን ጠልቶ የሄደው ሰው ነው።። በመሆኑም፣

የክፉ ዐይን ስራ የነበረውንና የረጋውን በማደፍረስ ሥርዓት አልበኝነትን ማንገስ ነው። በተሰራው ልማድ መጽናትን የሚጠሉ፣ እምቢተኞች ራሳቸውን የሚያዳምጡና ለሌላው ክብር የሌላቸው ከራሳቸው ጋር የተጣሉ ስለሆኑ ማደሪያ ያደርጋቸዋል ይላሉ። በሌላ አካባቢም እንዲሁ በተመሳሳይ አንድ ታሪክ አለ።

> በተከለከሉ ቀናት ሳር እያጨደ፣ አጥር እያጠረ፣ እህል እያዘራ ደጋግሞ ሰንበትን እየጣሰ ያስቸገረ አንድ ሰው ነበረ። የንስሐ አባትዬው በመንደራችን በረድ ሊጠራብን ነው፣ መከራን ሊያመጣብን ነው ብለው ቢመክሩ ቢገስጹ አልሰማ ይላቸዋል። ከዚያም፣ በቤተክርስትያን አውድ አውግዘው በአደባባይ ይጥሉታል። ቢሞት በቤተክርስቲያኗ እንዳይቀበር፣ ከብት ቢወድቅበት ሰው እንዳያግዘው፣ ከሰንበቱ እንዲሰርዙት ደግሶ ቢጠራ ሰው ገብቶ እንዳይበላ ብለው ይገዝቱታል። ሁኔታው ያሳሰባቸው የሃገር ሽማግሌዎች በመሀከል ይገቡና የንስሐ አባትዬውን ይዘው አባቴ ከእሱ ጋር ብቻ እኮ አይደለም የተጣሉ፣ ከወገኑ፣ ከልጆቹ ከቤተሰቡና ከሃገርም ጭምር ነው። እባክዎ ይተውት ይፍቱት ይሏቸዋል። ከተወገዘው ሰው ዘንድ በመሄድም ለምን ይህን ስራ በበዓል ጊዜ አደረግክ? ብለው ቢጠይቁት፣ ሳር ያጨድኩ ላሜ ስለወለደች ነው። እኔ ባላጭድ እሷ መንጨረ መች ይቀራል። አጥር ያጠርኩ ሌባ ልከለክል ነው ምኑ ላይ ነው ሃጢያቱ። እያለ የሚያፈርስ ነገር እያመጣ ሲያስቸግራቸው እውነትም ይኸስ ጤነኛ ሰው አይደለም። ወሬውን ሃገር ከሰማው ብዙ ሰው ያበላሽብናል። ስለዚህ፣ እሱን ትተን አባታችን እንዲሸነፉ እናድርግ ብለው ይመክራሉ። ከዚያም ወደንስሓ አባት በመሄድ ይህ ሰው እውነትም ጤነኛ አይደለም። ንግግሩ ሁሉ የመልካም ሰው አይመስልም። ጌታዬ ሰይጣን ተጣብቶታል ይሏቸዋል። የሰይጣንን ክንፍ የሚሰብሩት ደግሞ እርስዎ ነዎት ይሸነፉና እንመልሰው ይሏቸዋል። የንስሓ አባትዬውም በሁኔታው ተስማምተው፣ በፆምና በስግደት ቀጥተው መለሱት ይባላል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

5.2. የክፉ ዐይን ባሕርይ

የዚህን ኃይል ባህርይ የአካባቢው ሰው የሚገልጸው፣ "እንደነፋስና እሳት ዐይነት ረቂቅ ተፈጥሮ ያለው መንፈስ" በሚል ነው (መሪጌታ አይነኩሉ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ፍጡሩን ረቂቅ ያሰኘው የሚዳሰስና የሚጨበጥ ሥጋዊ አካል አለመልበሱ ነው። አለመልበሱ ከሥጋ ለባሽ ፍጥረቶች የሚለየው ዋናው ነገር

ይሆናል። ሥጋ አለመልበሱ በሰዎችና በሌሎች ምድራዊ ፍጥረቶች የሚገኙ አንዳንድ ባሕርዮች በእሱ ውስጥ እንዲኖሩ ያደርጋል። ከእነዚህም መካከል የሥጋ ጠባይ የሆነው የዕድ አንቀጽ አንዱ ነው። ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ) ይህ መንፈስ ዕድዊ አንቀጽ ባለመያዙ እንደ ሰው እና እንደ እንስሳ በየጊዜው የሚባዛና የሚራባ አይሆንም ይላሉ። በተጨማሪም ህመምና ሞት የሥጋ ጠባዮች በመሆናቸው በእሱ አለመገኘታቸው ህልውናውን ዘላለማዊ ያደርገዋል። አንድ ጊዜ ከተፈጠረ በኋላ በየጊዜው እየቀነሰ የሚሄድ ወይም እየከሰመ የሚያልቅ ባሕርይ አያስይዘውም ማለት ነው ይላሉ። የባሕርይ ክፋዩ እየተጎረደ በተጠቂዎች አካል ውስጥ ባደረ ቁጥር ብዛቱ አይቀንስም። በአንዱ ቦታ ሲገኝ በሌላው አይጎድልም። ከሌሎች ጋር እየተዳቀለ እና እየተበረዘ የሚሄድ ስላልሆነ እንግዳ ነገር አይቀላቅልም በማለት ይገልጹታል (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ) ።

ሥጋ ለባሽ ባለመሆኑ፣ ህልውናውን በውስን ቦታዎች ላይ እንዲገደብ አያደርገውም (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ ኑባሬው በሁሉም ቦታና ጊዜ በማንኛውም ሰዓት ረብቦና ተሰራጭቶ እንዲገኝ ያግዘዋል። በተጨማሪም፣ የተለያዩ ተፈጥሯዊ መልኮች መከሰቱን እንዳይከለክሉት፣ መስረጹን አንዳይጋርዱት ይረዱታል። እንደ እንቅልፍ፣ ድካም መታከት የመሳሰሉ የሥጋ ባሕርያት በፍጥረቱ ውስጥ ስለሌሉ፣ በእይታው ላይ ገደብ አያርፍበትም። በባሕርይው መድከም፣ መታከትና መሰልቸት አይኖርበትም። ንቃቱ በሌላ ተጽእኖ ቁጥጥር ውስጥ አይወድቅም(መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይኸ ባሕርይው ከነፍስ ጋር በአቻ እንዲቀናቀን ያደርገዋል።

5.3. የክፉ ዐይን ወኪሎች

ይህ ክፉ ኃይል በዐይን አማካይነት የሚሳል መሆኑን ስለመንፈሱ በተሰጠው ገለጻ ተጠቁሟል። መንፈስ በመሆኑ የሥጋ ጠባይ እንደሌለውም ከላይ አይተናል። በመሆኑም፣ ባሕርይው ይገለጥ ዘንድ ማደሪያ የሚሆን አካል ይፈልጋል። በጎዛምን አካባቢ ባለው ማህበረሰብ እምነት መሰረት ይህ ፍጥረት ማረፊያ አድርጎ በዋናነት የሚጠቀመው ሰዎችን፣ እንስሳትን፣ ተክሎችንና ጉዑዛን ነገሮችን ነው (አቶ ቅሩብ፣

2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ አካሎች ለመንፈሱ ማደሪያ በመሆን የመንፈሱን ግብር የሚገልጡ ይሆናሉ።

መንፈሱ በሰው ልጆች አካል ውስጥ የሚያድረው የነፍስ ክፍል የሆነችውን ልባዊትን ተክቶ ነው ይባላል። ሁኔታዎች ሲመቹና ዕድሎች ሲያጋጥሙ ከተደበቀበት እየነቃና እየተቀሰቀሰ በተጠቂው አካል ውስጥ የአዛዥነት ሚና የሚጫወተው የማሰብንና የማስተዋልን ቦታ ተክቶ ነው። በዚህ ጊዜ በቡዳው ላይ ያደረው መንፈስ ካደፈጠበት በቅጽበት ተገልጦ በተጠቂው አካል ውሰጥ ያለከልካይ የሚገባበትን ዕድል ያስገኝለታል ይላሉ (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ ተገላጭነቱ ኢ-ተገማች በመሆኑ፣ ማደሪያ የሆኑ አካሎችን ወደ አካባቢው እንዳይጠጉ በማድረግ፣ የመጠቃት ዕድልን መቀነስ ይቻላል ይባላል።

5.3.1. ሰዋዊ የክፉ ዐይን ወኪሎች

የአካባቢው ሰው፣ "ከሰው በቡዳ ከከብት ጎዳ" እያለ ይመስላል። "ጎዳ በሬ" ቀንዱ የተዘለሰ ወይም የተቀለሰ፣ የሚወጋና የሚጎዳ ማለት ነው (ደስታ ተክለወልድ፣ 1972፣ 231)። እንደበሬው ሁሉ ሰዎችን በመውጋት፣ በማነቆር፣ ሥጋን በማጠውለግ፣ በማዛል ቀሳፊ ህመምን ለሚተክለው ኃይል ማደሪያ በመሆን የሚያገለግልን አካል የአካባቢው ሰው የሚጠራው "ቡዳ" ብሎ ነው። የቡዳ ወካይነት በዚህ አገባብ ለሰው ልጅ ነው። በዘፈንም "ጎጃሜ ቡዳ ነው ብለሽ ያወራሽው፣ ሰውን ሰው ሲበላው የት አባሽ አየሽው" ይባላል። በዚህ አገባቡ 'ጎጃሜ' ሲል በስመ ኃጎሪነት አቋቋሙና ውክልናው ለሰው ነው። "ቡዳ በላ" ሲልም ሰው ሰውን በላው እንደማለት ነው። ስለዚህ፣ የቃሉ ውክልና፣ በዚህ አድራጎት የሚጠረጠሩ ሰዎች ራሳቸው ጥቃት ያደርሳሉ ተብለው መታመኑን ያስረዳል።

አንዳንድ ሰዎች የቡዳን ምንነት ለማወቅ፣ ለቃሉ ፍቺ ትኩረት ሰጥተው ይመረምራሉ። የቃል መፍቻ መንገዱ ደግሞ አንድ መንገድን የተከተለ አይደለም። Kenneth Honea (1975, 1) ቡዳ የሚለው ቃል በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ አካባቢ በሚኖሩ የኩሽቲክ ቋንቋዎች እንደሚታወቅ ያስገነዝባሉ።

በአማርኛና በኦርምኛ 'ቡዳ'፣ በሶማሊኛ 'ቢዳ'፣ በአፋር 'ቡታ' እንደሚባልና በቃሉ ሥረዎ ምንጭ ላይ ግን እርግጠኛ መሆን እንደማይቻል ያስረዳሉ፡፡ በትዛምን አካባቢ የሚኖሩ አንዳንድ ሰዎች ግን ቡዳን "ባዳ ፣ ባዕዳ" ከሚለው ቃል የረባ ነው ብለው ይናገራሉ፡፡ 'ባዳ' ፣ "ባድ (ባዕድ) ማለት ነው፡፡ የዚህ ቃል ትርጉም ደስታ ተክለወልድ፣ "ባጋም በቀጋ የማይወለድ፤ ሌላ ልዩ እንግዳ መጤ የውጭ አገር ሰው" በሚል ይተረጉመዋል (1972፣ 124)፡፡ "ላገሩ እንግዳ፤ ለሰው ባዳ የሆነ፣ ወጉረ ልውጥ ሰው፣ በልምዱና በጠባዩ ከተሰሪው ጋር የማይመሳሰል፣ የተነጠለ፣ የራቀና የተገለለ ህዝብ" እንደ ማለት ነው፡፡ ኪዳነወልድ ክፍሌም (1972፣ 624) ፣ "እንግዳን" በቁመ ነግድ፣ ነገድ፣ መንገደኛ ስደተኛ፣ መጤ ባይታወር በሚል ይበይኑታል ፡፡ "ነገድ" ደግሞ ወገን ያንድ አባት ዘር፣ ልጅ፣ የልጅ ልጅ ዘመድ እንደ ንህብና እንደ ንግድ ገንዘብ እያበላ እያራባ አውራ እያበጀ የሚኼድ ማለት ነው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፣ 624)፡፡

ስለዚህ፣ እንግዳነቱ በተግባሩ፣ በስራው ጠባይ ልዩ መሆን፣ መለየትና ከብዙኃኑ ጋር አለመመሳሰ በሚል የሚተረጎም ነው፡፡ ይህ ወገን ሲመጣ አዲስ ሥርዓትንና ልማድን ይዞ ስለሆነና ያልተለመደን ነገር ስለሚያስተዋውቅ "ቡዳ" ወይም "ባዕዳ" አሰኘው የሚል ነው፡፡

ሌሎቹም እንዲሁ "በዳ" ከሚለው ቃል ጋርም ያያይዙታል፡፡ 'በዳ' ሲሉ፣ "በቁመ 'ባዶ' ፣ 'ወና' ማለት ነው ይላሉ (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ መርጌታ ዲበኩሉ፣ ደረቅና በረሓ የሆነ፣ ሰው የማይኖርበት ቦታ የሚጠራው 'ምድረ በዳ' ተብሎ ነው ይላሉ፡፡ ይህም ርስት ጉልት ሳይኖረው የመጣ በመሆኑ ባዶ፣ ያልነበረና የማይታወቅ መሆኑን ለመግለጽ ከፍጥረት የራቀ አድርገው በሞትና በደረቅ ነገር ይመስሉታል በማለት ያስረዳሉ፡፡ ምንም ነገር የሌለው ባዶ የሆነና የሌላውን ሃብት የሚሻማ በመሆኑ፣ የባዶና የወና ምሳሌ አድርገው ይገልጹታል፡፡ የተሰራውን ነባሩን፣ የጸናውንና የሚታወቀውን ነቅሎና አፍልሶ፣ የማይታወቅንና እንግዳን ስለሚተክል፣ በተሰራውና በሰለጠነው ላይ መጥተው የሚሰፍሩ፣ ቀዳሚውን የሚጠሉ አድርገው ስለሚቆጥሯቸው መጤ አሏቸው (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡

ሌሎቹም እንዲሁ ቃሉን ከሌላ ታሪካዊ ክስተት ማለትም 'ቡድሃ' ከሚለው የግለሰብ ስም ጋር በማመሳሰል ትርጉም ይሰጡታል። ይህ ሰው የህንዶችን፣ የሺኖችን፣ የጃፓኖችን ኃይማኖትና ምግባር ያደሰ፣ የህንድ ንጉሥ ልጅ ነው ይላሉ (ደስታ ተክለወልድ፣ 1972፣ 124)። እውነተኛ መናኛ፣ ግሩሥ፣ ባህታዊ ነበር እያሉ ይገልጹታል። "ህንዶች ቡድሃ ይሉታል" እንደሚሉት ደስታ ተክለወልድ ያስገነዝባሉ። ይህ ሰው ፈላስፋና ብልኅ፣ ዐዋቂ ብርሃናዊ ስለነበር ስሙ ከዚህ ጋር ተቆራኝቶ ቀረ በማለት ለስያሜው ማስረጃ ያቀርባሉ። በዚህ ስም የሚታመኑ ሰዎች የተሰማሩበት መ.ያ ደግሞ ዕደ ጥበብ ነው። የጠይብም ቡዳ የመባሉ ምክንያት ይኸ ነው ይላሉ ደስታ ተክለወልድ (1972፣ 124)።

ደስታ ተክለወልድ፣ ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በሚለው መጻሕፋቸው ቡዳን፣ "ጠይብ (ጠቢብ)፣ ቀጥቃጭ፣ ባለጅ፣ ዐዋቂ፣ ሠራተኛ፣ ጀን፣ ሽላሚ፣ አንጥረኛ ቀጥቃጭ፣ በጥቂት ብልሃት የሰውን ድካም የሚበላ፣ ፋቂ ሸማኔ" ብለው ይገልጹታል (1972፣ 124)። እንደ ቡድሃ ሁሉ የተለየ ችሎታና ወጣ ያለ ሥራ የሚሰሩ በጥበብ የላቁ ሰዎች ሲያገኙ በዚያው ስም ይጠሯቸዋል (Reminick,1974, 280) ። ይህ አበያየን መሰረት ያደረገው በዚህ ስም የሚጠረጠሩ ሰዎች የተሰማሩበትን መ.ያ በመግለጽና በመ.ያው ዙሪያ ያለው አስተሳሰብ በሰዎች መታሰብ ላይ ያስገኘውን ግንዛቤ ማስረዳት ነው።

የአካባቢው ሰው ህይወቱን የሚመራው በእርሻ ሥራ በመሆኑ፣ ለእጅ መ.ያ እንግዳ ጥበብ ነው (Reminick,1974, 280)። እነዚህ የህብረተሰቡ ክፍሎች በእርሻ ሥራ ለመሰማራት ቢፈልጉ እንኳ መሬት ቀድሞ በመጣው ወገን እጅ ውስጥ ገብቷል። የአካባቢው ሰው እነዚህን ሰዎች ይጠራቸው የነበረው "ዜጋ" ብሎ ነው (Habtamu, 2003, 13)። የዜጋ[22] ትርጉም፣ "ለባለመሬት ተገዥ የሆነ ሰው" ማለት ነበር (Habtamu, 2003, 13)። በሌላ አበባል ተተካይ ያልሆኑ ዘግይተው የመጡ ደግሞ ባይታወሮች ናቸው።

በአካባቢው ይህን ያልተለመደውን ሥራ እንግዳ አድርጎ ስለተመለከተው መ.ያውን እንደሚጠቅመው ከማሰብና ዋጋና ክብር ከመስጠት ይልቅ ፈርቶ እንዲያየው

[22] የመሬት ስርዓቱ በርስት በተያዘበት ጊዜ የነበረው ትርጉም ነው።

አድርጎታል። ሥራውን ከሚያውቁትና ከሚያስቡት በላይ ሆኖ ስላገኙት የብልጦችና የራስ ወዳዶች ተግባር አስደርጎ አስመልክቶታል። የዚህ ብልጣብልጥነት ምንጩ ደግሞ ሙያው ያለድካምና ያለእንግልት ቁጭ ብለው በቀላሉ የሚሰሩት ነው ብለው ከማሰባቸው የሚመነጭ ነው ይላሉ። ያላቸው መስለው አለመታየታቸው ለሁሉም እየሰሩ ገንዘብ ማከማቸታቸው፣ ደግሰው ሲያበሉ ስለማያዩዋቸው ነው በማለት ይናገራሉ (ወ/ሮ ጥሩዬ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 9፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

የቡዳ አይነቶች

ቡዳን ለመንፈሱ ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ማደሪያ ብሎ መከፋፈል ይቻላል። መንፈሱን ፈቅዶ በመዋረስና ያለፈቃድ አገልጋይ ከመሆን አንጻር የዘር ቡዳና የትምህርት ወይም የልምድ ቡዳ ብሎ ማወገን ይቻላል። ጥቃት በሚያደርሱባቸው አካሎች ዙሪያ ካለ ልዩነት ተነስተን የሰው፣ የእንስሳትና የእህል ቡዳ በሚል መከፋፈል ይቻላል። የቡዳ እሳቤ ከዘመን ጋር አብሮ እየተለዋወጠ የሚሄድ በመሆኑ በቅርጽ የሚያሳያቸው ልዩነቶች ብዙ በመሆናቸው 'ተንከባላይ'፣ 'ላሽ'፣ 'ወሳጅ' ወይም 'ብሉቱዝ' የሚል ስም ያላቸው የቡዳ አይነቶች መከሰት ለመጀመራቸው ልብ ይሏል። በአካባቢው የተከሰቱ ልዩ ልዩ ፖለቲካዊና ታሪካዊ ለውጦች ጽንሰ ሐሳቡ ቀደም ሲል ይዞት በነበረው ፍቺ ላይ የተለየ ለውጥ እንዲያመጣ ለማድረጉ ይህ መረጃ ዋቢ ነው።

በአጠቃላይ ሲታይ ግን፣ ይህ መንፈስ ወደ ሰዎች የሚጋባበትን ዕድል በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። በዘር ወይም በመወለድ በውል በማያውቁትና በማይለዩት ሁኔታ የሚሆኑት አንደኛው ሲሆን፣ ሌላኛው ግን ተምረው ወይም ለምደውት በውዴታና በፍላጎት ገንዘብና ሃብት ለማግኘት በማሰብ የሚሆኑት የቡዳ አይነት ደግሞ አለ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በእንስሳት ላይ የሚያርፈው የቡዳ አይነት በዚሁ ከፍል የሚታየው ነው። ከእነዚህ በተለየ በፍላጎትና በስሜት ግለት ነቅቶ በጊዜያዊነት ያርፍና ፍላጎትና ስሜት ሲረካ ወዲያው የሚለቅ የቡዳ አይነትም ይታወቃል። እነዚህን ነገሮች ታሳቢ በማድረግ በአጠቃላይ በጎላምን አካባቢ ሶስት የቡዳ አይነቶች አሉ ብሎ ማሰባሰብ ይቻላል። እነዚህ የቡዳ አይነቶች ቀጥሎ ተገልጸዋል።

የዘር ቡዳ

ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሂደ ቃለመጠይቅ) ማንም ሰው ሲወለድ ንፁሕ ነው ይላሉ፡፡ በርኩሰትና በሃጢያት የሚገኝ ፍጥረት የለም ብለው ይናገራሉ ፡፡ ፈጣሪ የሰውን ልጅ የፈጠረው በፀጋው አስውቦና ሰው አድርጎ፣ በሚታየውም በማይታየው፣ እሱን አስመስሎ በመሆኑ፣ ሁሉም ንጹህ ነው ይላሉ፡፡ እኒህ አባት የንጽሕናን አይነት ሁለት ያደርጉታል፡፡ አንደኛው የፈጣሪ ባሕርይ የሆነው የንጽሕና አይነት ነው፡፡ ሁለተኛውን ደግሞ፣ ከፈጣሪ የንጽሕና ባሕርይ እየፈሰሰ ለሰዎች የሚሰጠው የፍጡራን ንጽሕና ማለትም የፀጋ ንጽሕና የሚባለው ነው፡፡ በሁለተኛው ምድብ የተገለጸው የንጽሕና ዐይነት የተሰጠ በመሆኑ፣ ባግባቡ ሲኖር የሚከበር፣ ባግባቡ ሳይኖር ደግሞ የሚወሰድ ወይም የሚረክስ የራስ ያልሆነ ነው ይሉታል፡፡

በመሆኑም፣ የቡዳ መንፈስ ካደረባቸው ቤተሰቦች የሚወለድ ሕጻን፣ ምንም እንኳን በወላጆቹ ላይ ያደረው ክፉ ኃይል ባሕርይውን አርክሶ ልዩ ጠባይ ቢያስይዘውም፣ ሲወለድ ቡዳ ሆኖ አይመጣም የሚል ነው፡፡ እያንዳንዱ ሕፃን እስከ ሰባት ዓመት ድረስ ንጹህ በመሆኑ የመንፈሱ ጠባይ ሊገለጥበት አይችልም ይላሉ(ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሂደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ምክንያቱን ሲያስረዱ፣ ባሕርይ የአምላክ እንጅ ከወላጅ የሚወረስ አይደለም የሚል ነው፡፡ በፍጥረት ላይ ያለው ባሕርይ ከፈጣሪ የተገኘ በመሆኑ ንጹሕ ነው፡፡ መርከስ ግን፣ በተፈጥሮ ከተያዘ ባሕርይ የሚመጣ ሳይሆን ከተወለዱ በኋላ በሚያከናውኑት ያልተፈቀደ ነገር የሚለወጥ ነው ይላሉ፡፡

በመሆኑም፣ ሕጻናት እስከ ሰባት ዓመት ዕድሜያቸው እንኳን እጃቸውና እግራቸው ባሕርያቸው ሃጢያትን አያስበውም ይላሉ፡፡ እንኳን ከሚሰሩበት ከሚያስቡበት ደረጃ ላይ አይደሉም፡፡ በመሆኑም፣ ንጽሐ ማንነት አያድፍም እንደተጠበቀ ነው ይላሉ (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሂደ ቃለመጠይቅ)፡፡

በአካባቢ ሰው እሳቤ፣ ክፉ ሥራና ክፉ መንፈስ በትእምርት የሚወከለው በስስት፣ በንፍገት፣ በብልጣብልጥነት፣ በማታለልና በመሳሰሉት አሉታዊ የግለኝነት ጠባዮች ነው ይባላል (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሂደ ቃለመጠይቅ) ፡፡

ሰው የሌላውን ሲመኝ፣ የራሱን አብዝቶ ሲያከብር፤ ሰውን እየጠላ ለራሱ ማደርን ጠባይ ሲያደርግ፣ ማካፈልን፣ መተጋገዝን እየተው ወደ ራሱ ማየት ሲጀምር ክፉ ሆነ እንለዋለን በማለት ይናገራሉ፡፡ ሁሉንም ነገር ለራስ ለማስገዛትና ለማሳደር በማሰብ ሰብአዊነትን የመጨቆንና ግብታዊነትን የማስፋፋት የራስ ወዳድነት ችግሮች ውስኑን ሃብት በተወሰነ ሰው እጅ አስገብቶ አብዛኛውን ሰው የጨቆነ፣ ያልጠቀመና ያላማከለ ድርጊት መፈጸም፤ ደስታዎችንና መልካም ነገሮችን ሁሉ ሰብስቦና አከማችቶ በተናጥል መያዝ፤ በባህርይ ወሰጥ መታዛዘንንና መተባበርን ማሳነስና የመሳሰሉ የትብብርና የመካፈል መንፈስን የሚሸረሽሩ ሥራዎች ሁሉ የክፋት ሥራ ተግበሮች ናቸው፡፡

ስለዚህ፣ ንፅሕና ወይም ባሕርይ የሚበላሸው በስርቆት፣ በዝሙት፣ በሐሰት፣ በመግደል፣ በመሳሰሉት ክፉ ተግባሮች እንጅ ፍጥረቱ በያዘው ባሕርይ አማካይነት አይደለም፡፡ መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ (2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) የሰው ልጅ ቀዳሚ ባሕርዩን ይጠብቅ ሲባል በልክና በሚዛን፣ በማስተዋልና በምጣኔ ይኑር ማለት ነው ይላሉ፡፡ በመሆኑም፣ ይሽንን አከበረ ማለት ሰው ንፅሕናውን ጠበቀ ማለት ይሆናል፡፡ ያንን በሻረ፣ የተፈጥሮ ህግጋትን ባፈረሰ ቁጥር፣ ንጽሕናው ይረክሳል፤ ንጽሕናው በረከሰ ቁጥር ለዚህ መንፈስ ማደሪያ የመሆን ዕድል ይኖረዋል ይላሉ (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡

ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ) የአካባቢ ማህበረሰብ የሰው ልጅ ያለዘሩ አይበቅልም ይላል፡፡ “ስንዴ ዘሯን አትለቅም” የሚል አባባልም አለ፡፡ ሰባት ዓመት የሞላው ልጅ የዓለምን ሥራ አይቶ ይረዳል፡፡ ያየውንም ለማድረግ ይሞክራል፡፡ ከብዙ ነገሮች ጋር ይለማመዳል ይላሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ዓለም የሚያደርገውን ያስባሉ፡፡ ስርቆትን ያያሉ፣ መስጠትንና መቀማትን ይታዘባሉ፤ መያምንና መብላትን ይለያሉ፤ ማመንንና መካድን ይለማመዳሉ፡፡ እነዚህን እያዩና እያገናዘቡ በዐዕምሮ እየጎለመሱ ስለሚመጡ፣ ወደ ክፉ ለመሄድም መልካሙን ለመከተልም ዕድሜያቸውና አካላቸው ይበስላል፡፡ በአካባቢያቸው ያለውና በቤተሰብ ውስጥ የተለመደው በሚፈጠረውና በሚረባው ነገር ላይ አንሶ ወይም በዝቶ መንጸባረቁ

አይቀርም በማለት ክፉ ኃይል በመልመድ የሚጋባ መሆኑን ያስረዳሉ። በመሆኑም፣ ደግነትም ሆነ ክፋት ዘራቸውን አይለቁም ማለት ነው። መጥፎ ሥራም ሆነ መልካም ተግባር በመወለድ የሚገኝ ሳይሆኑ፣ ዘግይተን የምንማረውና በተሞክሮ ተለማምደን ገንዘብ የምናደርገው ጠባዮች መሆናቸው ነው።

የክፉ ዐይን መንፈስ በልቦናቸው ከተተከለባቸው ሰዎች የሚወለድ ልጅም መልካም ያልሆኑ ሥራዎች ሲደረጉ፣ ሃሳቦች ሲጸነሱ፣ በድርጊትና በንግግር ሲገለጹ እያየ ስለሚያድግ ከክፉ ስራዎች ጋር ይለማመዳል። ይህ መጥፎ ልማድ ቀስ በቀስ፣ በዘር ሐረግ ወይም በዚያ አካባቢ በሚያድጉ ልጆች ባሕርይ ውስጥ ቦታ እየያዘ ወደ ታች እየተሰራጨና እየተሸጋገረ የሚሄድ ይሆናል። "ዘሮቹ የያዙት ባሕርይ፣ ጠባይና መልክ በሚፈጠረውና በሚረባው ነገር ላይ ሁሉ ነጸበራቁ ስለሚታይ የአካባቢው ሰው "ለእባብ ልጅ ጉድጓዱ አይጠፋውም" ብሎ ይመስላል(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ስለዚህ፣ በዘር ሐረግ የሚተላለፈው የቡዳ መንፈስ በመውደድና በመጥላት የሚሆኑት ሳይሆን፣ አብረን በመኖርና ከባሕርይ የሚያስወጣንን ስራ በመለማመድ የሚመጣ ነው። ወደውና ፈልገው የሚይዙት ወይም ፈቅደው የሚዋረሱት ሳይሆን፣ ባላወቅነውና ባልገመትነው መንገድ የምንሆነው ነው ይባላል። በመልመድ ስለሚጋባ ለመሰራጨት ጸታን አይመርጥም ይሉታል (አቶ ቅሩብ አንተነህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። እንደ አቶ ቅሩብ ገለጻ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሴትም ሆነ ወንድ መንፈሱ ካለባቸው ወላጆች እስከተገኘ ድረስና የእነሱን ጠባይ ለምዶ፣ ሃሳባቸውንና ድርጊታቸውን ተለማምዶ እስከፈጸመው ድረስ ማደሪያ ከመሆን አያመልጥም ይላሉ። ከዘሩ መካከል የሚተርፍ ሰው አይኖርም። በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ ሳይጠና በተፈጸመ ጋብቻ ውስጥ ከወላጆች መካከል አንዱ ከጨዋው ሌላኛው ደግሞ በድንት ካለባቸው ቤተሰቦች ወይም ወገኖች በስህተት ጋብቻ ሊመሰርቱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ከልጆች መካከል የተወሰኑት የጨዋውን፣ የተወሰኑት ደግሞ መንፈሱ ያለበትን የወላጅ ምግባር ሊይዙ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል።

የጨዋ ቡዳ

ይህ የክፉ ዐይን ዐይነት ዘመናዊነትን ተከትሎ ብቅ ያለ በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያው ለውጦች ምክንያት የታየ አዲስ የቡዳ ዘር ነው። አቶ ተዘራ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ይሽንን ዐይነቱን የቡዳ ዘር፣ "ከነባሩ ልማድና እሴት ወጣ ያለ ባህርይ ላሳዩ የማህበረሰብ አባሎች የሚሰጥ በጎ ያልሆነ ስም ነው" ይላሉ። ለውጡን ተከትሎ በነዋሪው ሕዝብ መካከል የተፈጠረው የሃብት፣ የክብርና የስልጣን ልዩነት አዳዲስ ክስተቶች እንዲታዩና የተለመደው ማህበራዊ እሴት እንዲናቅ አድርጓል በማለት ይናገራሉ። ይህ ስም የሚወጣው ከተለመደውና ከሚታወቀው መንገድ ወጣ ብለው ሀብት ለሰበሰቡና እሴቱን የሚጫን ተግባር ለፈጸሙ ሰዎች ነው በማለት ያስገነዝባሉ።

አቶ ተዘራ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14 ፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) የዘራቸው ነው እንዳንል በትውልድ ግንዳቸው ውስጥ በክፉነት የሚጠረጠር፣ በልቶ ተለፈለፈ ተብሎ የሚታማ፣ ጉዳት አደረሰ በሚል የሚከሰስ ቤተሰብ የላቸውም። ዘራቸው ሲቆጠር ከጨዋውና ከባላባቱ ወገን ነው። ከዘራቸው ወጥተው ቡዳ ሲሆኑ፣ "የጨዋ ቡዳ" አንዳንድ ጊዜ ደግሞ "የትምህርት ቡዳ" እንላቸዋለን። የጨዋ ቡዳ ሲሉ በዘራቸው ሳይሆን የግል ጥቅም ለማግኘት አስበው ሲስገበገቡና የዘር ጠባያቸውን ሲለቁ የሚተክልባቸው ነው (አቶ ተዘራ አሥማረ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ አገላለጽ አዳሪው መንፈስ በቤተሰብ መለማመድ የመጣ አለመሆኑን ያመለክታል። ራሱ ተጠርጣሪው ፈልጎ የሆነው የግሉ ጠባይ መሆኑን ለመጠቆም የተሰጠ ስም ነው። የትምህርት ቡዳ ሲሉ ደግሞ፣ እያወቁ የሆኑት ወደውና ፈቅደው የተማሩት፣ የተቀበሉት፣ መንፈሱ እንደሚያድርባቸው እየተገነዘቡ የሆነ ጥቅሙን አስቀድመው መባሉን ንቀው ያመጡት መሆኑን ይጠቁማል።

እነዚህ ሰዎች በላብና በጥረታቸው ማግኘትን እየተው፣ ከራሳቸው አልፈው የሌላውን የመመኘት ጠባይ ሲያመጡና በቋሚነት ወደ ስስትና ስግብግብ ተግባር ሲሰማሩ፣ ይህ ነገር ጠባያቸው ሆኖ ይገለጥባቸዋል ተብሎ ይታመናል። ቡድኑም ይህንን ተግባር ተከትሎ የሚሆኑት ሆኖ፣ አንዴ ለዚህ መንፈስ ማደሪያ ሆነው ከተያዙ በኋላ በዘር ግንዳቸው ውስጥ በመለማመድ በተዋረድ እየተባባሩባቸውና እየተራባባቸው

እንደሚሄድ ይነገራል (አቶ ተዘራ አስማረ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ወቀሳውና ስሙ የመጣው በሕገ ወጥ መንገድ ለመክበር ክፉ መሆንን መርጠዋል ከሚል ክስ ነው። ማህበራዊ እሴቱን ንቀው ለተወሰነ ጥቅም ሲባል ከመጥፎ ሥራ፣ ሃሳብና ድርጊት ጋር ሲተዋወቁ የክፉ ዐይን ማደሪያ ይሆናሉ (መሪጌታ ይሄይስ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ ሰዎች ማህበራዊነትን ንቀው ግለኝነትን ሲያከብሩ፣ ሃብቱ ቢመጣም በውዴታ ግዴታ ቡድነትን ግብራቸው ያደርጉታል በማለት መርጌታ ይሄይስ ያስረዳሉ። በመሆኑም፣ ሰዎች ቡዳ የሚሆኑት፣ ሃብት ባልተገባ መንገድ ለመሰብሰብ፣ የተሻለ ሆኖ ለመገኘት፣ በአቋራጭ ለመክበር የተለያዩ ጥቅሞችን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረትና መከራ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ለሃብት የሚሆኑ ዕያችን ባለመ.ያዎች ሲቆርጡ ገቢሩን አስተካክለው ሳይፈጽሙ ሲቀር ዕፅዋ ቡዳ ታደርጋለች እየተባለም ይነገራል (አቶ ጥላሁን ውሃቤ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ ማለት ያ ሰውዬ ሲቆርጥ፣ ትዋሃደዋለች። ስትዋሃደው ፈጽማ አልተዋሃደችውም። የዚያን ሰዓት ያንን ግብር ሳያሳካላት ሲቀር፣ ከሁሉ ነገር ሁሉ እርቆ እያለ ቡድነትን ትተክልበታለች ይላሉ። እንደጠጣ ሰው ታክለፈልፈዋለች፣ መንፈሱን ትቀይረዋለች።

የአካባቢው ሰዎች ባልተጠበቀና ባልተገመተ ሁኔታ ድንገት በሃብት በልጽገው ሲገኙ፣ የተሻለ ሆነው ለመታየት ሲሞክሩና የሃብት ምንጫቸው ግልጽ አልሆን ሲል፣ 'ተንካባላይ' ሆነው፣ 'ላሽ ሆነው'፣ 'ወሳጅ ሆነው' ነው ይሏቸዋል (ወ/ሮ ጥሩዬ ይሁን፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ የተገኘ)። ተንከባላይ የቡዳ ግብር ሆኖ በእኩለ ሌሊት ራቁትን በመንታ መንገድ ላይ በመንከባለል የሰውን ወዝ ለመሰብሰብ የሚደረግ መከራ ነው (ወ/ሮ አዐደ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ የተገኘ)። ላሽ የባለቤቱን ወዝ ከቁልፉ ላይ በመላስ ሃብቱን ጠራርጎ በመውሰድ ለመክበር የሚደረግ ጥረት ነው(ወ/ሮ ጥሩዬ ይሁን፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ የተገኘ)። ወሳጅ ደግሞ፣ የተለያዩ ክፉ ሃይሎችን በአጋዥነት በማሰለፍ፣ ያልደከመበትን ሃብትና ንብረት በማጓጓዝ የራስ የማድረግ መከራ ነው (ወ/ሮ አዐደ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ)። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወሳጅ የሚለው ስም

'ብሉቱዝ' በሚል መጠሪያ ተቀይሮ እንደመጣ የአካባቢው ወጣቶች ይናገራሉ (ወ/ሮ ይደነቁ መኮንን፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ)።

ነባሩን ማህበራዊ ስርዓት ጠብቀው የሚሄዱት ንጽሕ የሚለውን ስማቸውን ይዘው ሲቀጥሉ፣ ከዚያ ልማድ ያፈነገጡት ደግሞ 'ቡዳ' በሚል ይገለጻሉ። እነዚህ ሰዎች ይኸ ስም ከተሰጣቸው በኋላ ከወገኖቻቸው ጋር አብሮ መብላት፣ መጋባት፣ ማህበር መመስረት፣ ሰላምታ መለዋወጥ ዘርን ስለሚያረክስ ይከለከላሉ (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)። በዘራቸው ውስጥ ይህን ነገር ያለማምዳል ተብሎ ስለሚታሰብ ያመረቱትን መግዛት፣ የሚነግዱትን መገብየት፣ በሞታቸው መሳተፍ ሁሉ እንዳተባባሪ ስለሚያስቆጥር ያስወግዛል ይላሉ።

ማህበራዊ ሥርዓቱ በተጠበቀ ቁጥር በማህበረሰቡ ውስጣዊ ሰላም ይነግሳል። በነዋሪዎቹ መካከል መስማማት ይመጣል። እኩል ተጠቀምጫ በሆኑ ቁጥር በመካከላቸው ያለው አንድነት ይጠነክራል። በመሆኑም፣ ውስጣዊ ኢ-ፍትሃዊነቶችን ለመታገል በዳዩን የሚያለዝብ በልማዱ ውስጥ ያሉትን ደግሞ ጠብቆ የሚይዝ አስነዋሪ ተረኮች ይወራሉ።። ለምሳሌ፡- ከባህሉ የፈነገጡ ሰዎችን ብንመለከት እነዚህ ሰዎች ጅብ ሲጋልቡ ታዩ፣ በውድቅት ጨለማ አውራ መንገድ ላይ ራቁታቸውን ሲንከባለሉ ተገኙ (ወ/ሮ ጥሩዬ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ)። የባንክ ቤትና የንግድ ተቋም መካዘኖችን ቁልፎች ሲልሱ ታዩ(ወ/ሮ አፀደ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ የተገኘ)፣ ሚስቱን በልቶ ገድሏት ሃገር ጥሎ ተሰደደ (ወ/ሮ አፀደ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15 በቃለ መጠይቅ የተገኘ)፣ የሚስቱን እህት በዐይኑ ወግቷት ቤተሰቡ ተጣልቶ ሚስት ሃብት አካፍለኝ ብላው ትዳሩ ሊፈርስ በቋፍ ላይ ነው፤ ወንድሙን በልቶት ሰውነቱ እየሰለለና እያለቀ ሄደ የሚሉ ሃሜቶች ጎልተው በአካባቢው እንደሚሰሙ አጸደ ይናገራሉ።

ቁመኛ

በአማርኛ ቁም ፣ "የቆመ የተገተረ፣ ደማዊት ነፍስ ያለችው የቤት እንስሳት ነው" (ደስታ ተክለወልድ 1975፣ 1036)። ቁሞች ሲልም፣ "ከብቶች እንስሶች" እንደ ማለት ነው። ቁመኛ ደግሞ፣ "አስማተኛ፣ ቡዳ፣ ዐይነ ወግ" የሚል ትርጉምና ፍቺ ያለው ነው (ደስታ ተክለወልድ፣ 1972፣1036)። የቁመኛ አካባቢያዊ ትርጉም፣

"እንስሳት አደግድገው፣ መንምነውና ከስተው እንዲሞቱ የሚያደርገውን ህመም ለሚተክለ ሰዎች መጠሪያ የሆነ ስም ነው" (አቶ ጤናው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ አጥቂዎች እንደ ቡዳ ሰዎች ሆነው ጥቃት የሚያደርሱት ግን በእንስሳት ላይ ብቻ ይሆናል። አቶ ተዘራ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ አንድ ሰው በሰውም በእንስሳም አይጠረጠርም ይላሉ። ቁመኛች ውዴታቸው የሚያርፈው በቤት እንስሳት ላይ ብቻ ነው በማለት ያስረዳሉ።

ከቤት እንስሳትም የሚመርጧቸው እንዳሉ ይናገራሉ። ቁመኛ የሚፈራው በቀንድ ከብቶች ላይ በሚያደርሰው ጉዳት ነው(አቶ ጤናው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ) ። በከብቶች ላይ ጉዳት የሚያደርሰውን የክፉ ዐይን መንፈስ የሚሸከመው አካል ወይም በሽታ ለሚያደርሰው መንፈስ አዳሪ የሆነው ሰው ተለይቶ "ቁመኛ"፣ ሰዎች ላይ የሚያርፈውን ህመም የያዘውን አካል "ቡዳ" ይሉታል (አቶ ጤናው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። የጥቃቱ ባህርይ አንድ ቢሆንም ጥቃቱ በሚያርፋባቸው አካሎች መለያየት የተነሳ አሰያየሙ የተለያየ ስያሜ ይዞ ይገኛል።

የቁመኛ ዐይን የሚያይለው ለሰው ልጅ በመሰረታዊነት በሚያገለግሉ የቤት እንስሳት ላይ ብቻ ነው። ከእንስሳት መካከል የቀንድ ከብቶችን ይመርጣሉ፣ ከቀንድ ከብቶች ደግሞ በጥጆች፣ በግልገሎች፣ በወላዶች፣ በወይፈኖች፣ ሰውነታቸው ሞላ ሞላ ባሉ እንስሰሶች ላይ ይጠናል (አቶ ጤናው ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። አቶ ጤናው፣ ካረጁት ይልቅ ልጆችን ይመርጣሉ። ከአባት በሬዎች በወይፈኖች፣ በጠቦቶች፣ በግልገሎች ላይ ይበረታሉ (አቶ ጤናው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። ለሽክም ከሚያገለግሉት ይልቅ ለምግብና ለግልቢያ ጥቅም በሚሰጡት ላይ ያርፋሉ በማለት ውዴታቸውን ይገልጻሉ።

ጠንፋፊ

ጠንፋፊነት በነባር ተሰሪዎች መካከል በሚፈጠር የፉክክርና የውድድር መንፈስ የሚመጣ መጠቃቃት ነው (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። ሁለንም የህብረተሰብ አባል ከአካባቢው ተፈጥሮና ከመልካም

ነገሮች እኩል ድርሻ ካለማግኘት የሚነሳ ነው። በውስጣዊው አደረጃጀት ውስጥ በአድልዎ፣ በማናሸር፣ በኢፍትሃዊነት ምክንያት፣ አንዱ የተሻለ ሊላው ያነሰ ቦታ ሲይዝ በጊዜያዊነት በሚቀሰቀስ ስሜት የሚደርስ ጥቃት ነው ይሉታል። አቶ ቅሩብ ጠንሳፊነት፣ በእኩል ከአለመታየት፣ መልካም ከሆነው ነገር ድርሻን ከማጣት፣ አንድን ነገር አጥብቆ ከመመኘት በጊዜያዊነት የሚሰማና የሚቀሰቀስ የንዴት ወይም የምኞት ስሜት ነው ይሉታል። ይህ ስሜት የጎደለንን ነገር የሚያስታውስ ሆኖ፣ ሲያጋጥመን የሚያምረን ወይም ስናየው የሚሰማን ነው በማለት ይገልጹታል።

ጉድለቱ የሚገለጽበት አውድ ሰዎችን ወደ ክፉ ስሜት ስለሚያስገባቸው፣ አጋጣሚው መንፈሱ የሚከሰትበን ሁኔታ አመቻች ያደርገዋል። እነዚህ አውዶች ሰዎች በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ይመለከቱበታል። ከመልካም ነገሮች ውስጥ የተወሰነ ድርሻ እንዳይዙ ያስባሉ። ይህ ስሜታቸው ውስጣዊ መናጋትን ስለሚያስከትል በጊዜያዊነት የቡዳ መንፈስ አገልጋይ አድርጎ የሚያሳጫቸው ይሆናል (ወ/ሮ ውዴ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 5፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሰዎች ካዩት ወይም ከሰሙት ተነስተው በአንድ ነገር ላይ የተለየ ፍላጎት አድሮባቸው ያንን ነገር የራሳቸው ለማድረግ ሲመኙ ሊያጡት ይችላል። ነገሩን አብዝቶ ከውደዱት የኔ በሆነ ስሜታቸው ያንን ነገሩን ሊመርዘው ይችላል(ወ/ሮ ውዴ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 5 የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ግላዊ ፍላጎቶች የሰዎችን የማመዛዘን ኃይል አዛብተው ወደ ስስትና ስግብግብነት በሚመሩበት ጊዜ በጎ ያልሆኑ ስሜቶች በጊዜያዊነት ይወለዳሉ። እነዚህ ስሜቶች ሰዎችን ለመጉዳት ክፋት ስለሚያሳስቡ ይሸንን አጋጣሚ በመጠቀም ሰዎችን የሚጎዱ የመንፈስ ዐይነቶች ጠንሳፊዎች ይባላሉ (አቶ ተዘራ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ14 የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ንዴትንና ብስጭትን በማጫር፣ ቅን ያልሆነ ስሜትና ሃሳብ በሰዎች ስሜት ውስጥ በመቀስቀስ፣ ለሰዎች ክፉ እንዲያስቡ በማደረግ ክፉ መንፈስ የሚራባበት መንገድ ነው። በዚህ የተነሳ መልካም ያልሆኑ ድርጊቶችን ለመፈጸም የሚያነሳሳና በእነዚህ ሰዎች መንፈስ ውስጥ በጊዜያዊነት ተተክሎ ሰዎችን ለመጉዳት የሚሞክር ኃይል ይፈጠራል።

እነዚህ ሰዎች ከንዴታቸውና በጎ ካልሆነ ምኞታቸው በጸጸትና ራስን በመውቀስ ወይም አቅልን በመግዛት ሲመለሱ ይህ ተናዳፊ ኃይል አጋጣሚውን ተጠቅሞ ይለቃቸዋል ይባላል[23] (አቶ ቅሩብ አንተነህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። በዚህ እሳቤው ሁሉም ሰው የዚህ መንፈስ አገልጋይ የሚሆንበት እኩል ዕድል እንዳለው የሚያስረዳ ነው። ነገር ግን፣ እንደሌሎች የቡዳ ዐይነቶች በቋሚነት ተተክሎ አይቀርም ይላሉ። አንድ ሰው ሚዛኑን ጠብቆ በልክና በመጠን ከኖረ መንፈሱ የሚቀርብበትን ዕድል ሲያጠበው፣ ከባሕርይ ከወጣ ደግሞ የመቅረብ ዕድሉን ያሰፋዋል።

በእርግጥ ልዩነትን በማጥበብ ወይም በማስተካከል ስሜቱን መቀነስ ወይም ማጥፋት ይቻላል። ነገር ግን፣ ኢ-ፍትሃዊነት እንከን አልባና ፍጹም ጤናማ በሆነ መልኩ የሚታከም ሳይሆን በከፊል ሊሚላ የሚችል ፍላጎት ነው። ምቀኝ[24] የሚይዛቸው ሰዎች እኩል ለመሆን ዋና ግብ አያደርጉም። ከዚያ ይልቅ ካጡት ነገር በመጠኑ ማግኘትን፣ ግለሰቦች ካሉበት ሁኔታ የተሻለ ሆኖ መገኘትን የሚያሳይ ከነበሩበት ሁኔታ ከፍ ብሎ የማዳር ስሜት ነው። ጥያቄው እኩል የመሆን ሳይሆን ያሉበትን ሁኔታ መጥላት ነው። ስለዚህ፣ ማህበራዊ መበላለጦች ሲሰፉና የማግኛው መንገድ በኢ-ፍትሃዊነት ሲከበብ የክፉ ሃይሎች የሚበረቱ ይሆናል።

5.3.2. የክፉ ዐይን ማደሪያ ተክሎች

[23] በጎጃም አንድ ሰው በሰዎች ላይ ቅን ያልሆነ ስሜት አድሮበት ሃሳቡን በንዴት ሲገልጽ፣ ለምሳሌ እሱንማ እገድለዋለሁ፣ አለቀውም እና የመሳሰሉ አይነት ዛቻዎችን ሲያሰማ ሰይጣን እንዳይሰማህ፣ ከአፍህ መጥፎ ቃል አታውጣ በል የተናገርከውን ትፋው ተብሎ ይገሰጻል። በልጅ ሳይቀር ሰዎች ተናድደው መራገም ሲጀምሩ በአጠገብ ያለ ሰው በምናወጣቸው ቃላት የሚገስጸን ለልጁ ሞራል በመጨነቅ ሳይሆን ሌላ ከአጠገብ ያለ ኃይል ሰምቶ በተናጋሪው ስሜት ውስጥ አድሮ ሊጎዳ ይችላል ተብሎ ስለሚፈራ ነው በማለት ቁስ እንስማ ነግረውኛል።

[24] ምቀኝነት ከመልካሙ ነገሮች ከፍተኛ የሆነ ድርሻ ይዟል ከሚል ስሜት የሚቀሰቀስ ሲሆን፣ የራስን ድርሻ አሳንሶ የባላጋራን (ተጋሪን) መጠን ደግሞ አብዝቶ የማየት አስተሳሰብ ነው። ቅናት ግን ከሌላው የጥቅም ተጋሪ አነስኩ ከሚልና መልካም የሆነው ነገር ከእነሱ እጅ ወጥቶ በተቀናቃኝ እጅ ሊገባ ይችላል ከሚል ፍርሃት የሚነሳ ነው።

መሪጌታ ዲበኩለ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ማንኛውም ፍጥረት የተፈጠረው በዓላማ ነው ይላሉ ። በመሆኑም፣ ህብረተሰቡ ተክሎችን ሲያቀርብ ወይም ሲያርቅ ይህንን ዓላማ ያስተውላል፤ ባሕርያቸውን ይመረምራል ይላሉ። የአካባቢ ሰው አባት ዛፎችንና የለመዱ ተክሎችን ያከብራል። በፍሬያቸውና በአበባቸው ለሰው ልጅች ጥቅም የሚሰጡ ተክሎችን፣ አዝርዕቶችን መርጦ ያረባል። በቆጣቢነታቸው፣ በመጣኝነታቸውና በጥንካሬያቸው የጎላ ረብ ያላቸውን መርጦ ያሳድጋል፣ ይተክላል ይላሉ።

ከዓላማው ጋር የማይዛመዱትንና ከእሴቱ ጋር የማይገጥሙትን ወደ ጓሮውም ሆነ ወደ ማሳው አያስጠጋም። ፈርቶና ተጸይፎ፣ አግልሎና አርቆ ይይዛቸዋል። አድራጎትና ተግባራቸውን እያየ እኩሎችን የክፉ ሊሎችንም የመልካም ምሳሌ እያደረገ ያስተምርባቸዋል። በመሆኑም፣ ተክሎች ውዴታውን፣ ፍርሃቱንና ጭንቀቱን ነጋሪዎች ናቸው። አንዳንድ ተክሎችን ክፉ የሚያስብላቸው የሚያሳዩት አፈንጋጭ ጠባይና መልካም ያልሆነ ዐመል ነው። እነዚህን ተክሎች ለዚህ ሃይል ያስመረጣቸው ነገር፣ በባሕርያቸው ውስጥ የሚከተሉት ጎጅ ጠባይ ነው ይላሉ። ከእነዚህ ጠባዮች መካከል አፍላሽነት አንዱ ነው።

አፍላሽነት

የአካባቢው ማህበረሰብ መፍለስን ከመነቀል ጋር ያዛምደዋል። በነባር ይዞታ ላይ እንግዳና መጤ ነገር መጥቶ ተተክሎ ነባሩ ተነቅሎ ሲመለከት ፈለሰ ይላል (አቶ ዜና፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። የቆዬው ጠፍቶ አዲስ ነገር መጣ ነባሩ ከቦታው ጠፋ ለማለት ነው። ቀድመው በቅለው የረቡት አዝርዕቶች፣ ፍራፍሬዎችና ቅጠላ ቅጠሎች የዕድገት ዘመናቸውን ጨርሰው ሊረግፉ ወይም ወደ መርገፉ ሲቃረቡ፣ መጤ ተክሎች ድንገት ተከስተው አካባቢውን ወርረው ይይዙታል። በአፍላሽ ባሕርይ ውስጥ መውረርና መስፋፋት ዋና ጠባዮች በመሆናቸው፣ ትንሽ ቦታ ካገኙ በአበባቸውና በግንዳቸው እየተሳቡ አካባቢውን በዘመቻ መልክ ፈጥነው ይቆጣጠሩታል (አቶ ዜና፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። ለዚህ ምሳሌ ሆኖ የሚጠቀሰው የዐዞ ሬሳ ነው። ይህ ተክል ባገኘው ነገር ላይ ተንጠልጥሎ የሚወጣ ራሱን የማይችል ልፍስፍስ ተክል ነው።

መሬት ለመሬት በመሳብና ባገኘው ላይ በመጠምጠም የሚስፋፋና የሚንሰራፋ ነው፡፡ አንድ ጊዜ እግሩን ከተከለ ስለማይነቀል ይፈራል፡፡

አቶ ጤናው ይኸ ተክል ሁልጊዜ የሚመጣው ተክሎች ቅጠሎቻቸውን በሚያረግፉበት ሰዓት ነው ይላሉ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)፡፡ መጤው ተክል በዚህ ቀዳዳ ሾልኮ የደከመውን ግፍቶ ጥሎ በቀናው ቦታ ላይ ራሱ ያደላድላል፡፡ በዚህ መልክ አካባቢው ለም የነበረው ቦታ ምድረ በዳና ባዶ እየሆነ ይሄዳል ይላሉ፡፡

የአካባቢው ሰው እንደዚህ አይነት ተክሎች ከግቢው በቅለው ሲያይ ይሰጋል ይላሉ (አቶ ዜና፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ) ፡፡ በመተከያው መሬት ላይ የማያውቀው እንግዳ ኃይል መጥቶ ተጠምጥሞና ወርሮ መያዙን ሲረዳ የሚያፈናቅለውና የሚያሳድደው መስሎ ይሰማዋል በማለት ስጋቱን ይገልጻሉ፡፡ ጠባየ ነገሩ እንደ ዐዞ ራሳ የሆነ "ስጉት" የተባለ ሌላ ዕጽም አለ፡፡ ይህ ዕጽ ሥሩን እንደተከለ ወዲያው ነጭ አበባ የሚያወጣ ዐመዳም የሆነ ጥቅም የሌለው ተክል ነው (አቶ ዜና ደለለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)፡፡ ይህ ተክል በአባባው ጊዜ የሚጥለው ፍሬ፣ በወደቀበት ቦታ ሁሉ ፈጥኖ የሚዘራ ነው፡፡ እንደተዘራ ፈጥኖ በመግስገስ ነባሩን ተክል ወርሮ ይዞ ምቾት በመንሳት ያደርቀዋል ይላሉ፡፡

ገስጋሽነት በአረም ዘሮች ውስጥ ያለ ጠባይ ነው፡፡ አረሞች ሲመጡ ድንገት ነው (አቶ ጤናው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)፡፡ አረም የሆነ ሁሉ ሥሩን አዝልቆ አይሰድም ይላሉ፡፡ ሥሩ ዘልቆ ባለመተከሉ ምግብ ለማግኘት ስለሚቸገር፣ ባገኘው ላይ መንጠልጠልና መከመር ይወዳሉ፡፡ በተሰራውና በለማው ላይ ተጠግቶ ያለፋበትን ይጠቀማል፡፡ ወደተለያየ አቅጣጫ ዘምቶ አዝርዕቶች መቆሚያና መገስገሻ ቦታ እንዲያጡ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም፣ ከገስጋሽነት ጋር ተያይዞ የሚመጣው ሌላው ጠባይ ተሻሚነት መሆኑ ነው፡፡ መሻማት የሌላን የመፈለግ ስሜት ነው፡፡ በመሆኑም፣ በተሻሚነት ውስጥ አግበስባሽነት አለ፡፡ ለራስን አብዝቶ ጠቅሞ ሌላውን ማራቆት ራስን ከመውደድ የሚነቃ ስሜት ነው፡፡ ይኸ ስሜት ራሱን ችሎ የሚኖርን ተክል ምቾትና ጤናማ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P.O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

አስተዳደግ የሚጎዳ ነው። በመሆኑም፣ የሌላውን የሚፈልግ ለራሱ የሚሳሳ ነውና እሱ ባለበት ቦታ ሁሉ የሚገፋና የሚፈናቀል ይኖራል። መስፋፋት የነበረ እንዲነቀል ስለሚያደርግ፣ የተደላደለው እየነገለ በመጨው ይተካል። አዲሱ እየተሰራ እንግዳው የሚገንና ነባሩና ቀዳሚው ማረፊያና መቀመጫ የሚያጣ ይሆናል። በዚህ የተነሳ፣ እነዚህ ተክሎች በአንድ ሰው ግቢ ውስጥ በቅለው ሲታዩ፣

"ሳይዘሩት ይበቅላል አረምና ጠላት
እሱን ቶሎ ቶሎ በየጊዜው ማጥፋት" ይባላል።

ንቀሏቸው፣ አርሟቸው፣ አፍልሷቸው ለማለት ነው ይላሉ አቶ ጤናው። እነዚህ ተክሎች ተንሰራፍተው ነግሰው በአንድ ግቢ ውስጥ ከታዩ፣ ለባለቤቶች መሞትና መነቀል ምልክት ተደርገው ይታሰባል። ባለቤቶቹ ሊሞቱ ነው ተብሎ ይታዘናል። ሰውዬውም በቁመ የመሞቻዬ ቀን ደረሰ እያለ በማሰብ ማዘንና መተከዝ ይጀምራል (2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመምጣቱ ክፉ ምልኪያ የደረግበታል።እንዲያውም ከእነ ግጥሙ፣

ይኸ የማን ቤት ነው ሐረግ የለበሰው
ያያ ከሌ ቤት ነው ዛሬ የፈረሰው። እየተባለ ሙሾ ሁሉ ይደረደራል በማለት አለቃ ደበበ ይናገራሉ።

አቶ ዘመኑ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ፣ "መሬት ሲያረጅ 'መቄ' ወይም 'እንግዶ' ያበቅላል" እየተባለ እንደሚተረት ያስታውሳሉ። መቄ፣ ኑግ የሚመስል ቢጫ አበባ ያለው ቅጠል ነው (ደስታ ተክለወልድ፣ 1972፣ 762) ። መቄ፣ መጨ ወይም የመጣ የሚል የቃል ፍቺ ያለው ሆኖ፣ ፍቺው በኋላ የሚመጣ እንደማለት ነው ይላሉ። ባዕድ የሆነ ካገሩ ወደ ባዕድ አገር ተሰዶ የመጣ ስደተኛ፣ ላገሩ እንግዳ የሆነ ባይታወር ሰው የሚጠራው መጠሪ ተብሎ ነው(አቶ ዘመኑ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እንደ ሰው ሁሉ የመሬትን መበላትና ማርጀት ተከትሎ የሚመጣን፣ በደከመና በተበላ መሬት ላይ የሚበቅልን ፍሬው የሚመር ጤፍ መሰል እንግዳ እህል የሚጠሩት "መቄ" ብለው ነው። ይህን የአረም

ዐይነት "መጭ" ያስባለው በድካም መብቀሉና መምጣቱ ነው። ይህን ነገረ ስራውን እያየ የአካባቢው ሰው ይሽንን ተክል የሚጠራው "ክፉ" ብሎ ነው።

አቶ ጤናው (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ) እንግዶም የግብስ ዘር ሆኖ ከፍሬው ገለባው የሚበዛ በደረቅና በተበላ መሬት ላይ የሚበቅል የችግር እህል ነው ይሉታል። መርጌታ አይነኩሉም (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ) "እንግዶ"፣ እንግዳ ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን፣ ለማዳ ያልሆነ ድንገት ደራሽ ማለት ነው ይላሉ። በድካምና በእርጅና ሰዓት አቅም ባነሰበትና ድካም በተጫጫነበት የሚበቅል ከፍሬው ገለባው የበዛ የግብስ ዘር ነው። እንደእነዚህ አይነት ተክሎች የመጥፎ አድራጎት ሁሉ ምልኪያ የሚሆኑት ቀን ጠብቀው የሚከሰቱ በመሆናቸው ነው (አቶ ጤናው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)።

መግፋትና ማድረቅ፣ መሰብሰብና ማግበስበስ ጠባያቸው የሆኑ ሌሎች ክፉ የሆኑ ተክሎችም አሉ። በእነዚህ ተክሎች ውስጥ ያለው ጠባይ ደግሞ የተለየ ነው። እነዚህ ተክሎች ከአጠገባቸው ያለን አዝርዕት በማክሰምና በማድረቅ የሚያፈልሱ ናቸው። ለማራቂያነት ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል ሥሮቻቸውን ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች በመስደድ የሌላውን ተክልና አዝርዕት ሥር መጥለፍ ነው(አቶ ጤናው ከብቴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። መልካም ተክሎች እግሮቻቸውን እንዳይሰዱና ተስተካክለው እንዳይቆሙ በማድረግ ምቾት መንሳት ነው። ቆልፈው በማሰር ምግብ ወደላይኛው የዕፀዋቱ ክፍል እንዳይተላለፍ ገድበው ያቆሙታል። ከዚያም የቆመው እንዲወድቅ፣ የጸናው እንዲንገዳገድ፣ የሚሰፋውና የሚስፋፋው እንዲሰበሰብ አድርገው ያሸማቅቁታል (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ተንኳሽነት

በክፉ ዐይን ማደሪያነት የሚፈረጁ አንዳንድ ተክሎች ደግሞ፣ በራሳቸውና በጎናቸው ባበቀሉት እሾህ አማካይነት ቀጥ ብለው የሚወጡትን ተክሎች እየወጉ፣ እያነቆሩና እያቀጨጩ የሚያደርቁ ናቸው (አቶ ዘመኑ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በእነዚህ ፍጥረቶች ጠባይ ውስጥ ያለው ዋነኛ ነገር፣ መመረዝ፣

መኮስኮስና መለብለብ ነው። ይህ ጠባይ አዝርዕቶች እንዳይበቅሉና እንዳያድጉ የሚረብሽና ጤና የሚነሳ ትንኮሳ ነው። ከዚህ ላይ አመዳም ቀለም ያለውና በሰው ልብስ ላይ የሚጣበቀው"የሽንጉግ" ተክል ምሳሌ አድርጎ መጥቀስ ይቻላል(ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ ይህ ተክል ዘሩ ሁለት መልክ ያለው ነው ይላሉ። አንደኛው ድቡልቡሉ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ እንክርዳድ የምትመስለ ፍሬ የሚያወጣውና ከወጋ በኋላ ተለቅሞ የማይጠራው የ"ሰይጣን መርፌ" የሚባለው ተክል ነው።

ሰፋፊ ቅጠል የሚያወጣውና ጫፍ ላይ መርፌ የምትመስል እሾህ የሚያበቅለው የእሾክ ዘር፣ "አሜካላ" ተመሳሳይ ጠባይ ያለው ነው ይላሉ ወ/ሮ ሰዋገኝ። የአሜካላ እሾክ ቀጭን በመሆኑ፣ ከወጋ በመርፌ ነቅሶ ለማውጣት ያስቸግራል ይሉታል። እሾኩ የሰረገበትን ቦታ ለይቶ የሚያበልዝና ቁስሉ ቂም ይዞ እንዲመረቅዝ የሚያደርግ ክፉ ተክል ነው። አሳብዶና አስክሮ የሚገድለውና በድን የሚያደርገው እሾኻማው የበረሐ ዛፍ በደኖንም በተመሳሳይ ይፈራል (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ።

ከእነዚህ ተክሎች ባሕርይ የተለዩ ግን ማህበረሰቡ የሚፈራቸው ሌሎች ተክሎችም አሉ። እነዚህ ተክሎች ቁመታቸው ረዘም ያለና ሸቅብ የሚያድጉ ሆነው፣ በግንዶቻቸውና በቅጠሎቻቸው ላይ እሾህ ያላቸው ናቸው። እሾሁ ከአጠገብ ያለን ተክል እየወጋ ጤና የሚነሳ ነው። እየገዘፈና እየሰፋ የሚሄደውን በማሽማቀቅና በማኮማተር ቅርጽ እንዲያጣ የሚያደርግ ነው ይሉታል (አቶ ይዘንጋው መኮንን፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ) ። በመሆኑም፣ አካባቢው ከእሱ ውጭ ሌላ ነገር እንዳይመች የሚያደርግ ነው። ከእነዚህ ተክሎች መካከል አጋም ይጠቅሳል። ከእነ ምሳሌው፣ "ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል" ነው።

አቶ ዜና ደለለ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ) በድብዳብ ቦታ የሚበቅሉ፣ እንደበርበሬ የሚለበልቡ የሚያንገበግቡ፣ ተንኳሽ፣ ኮስኳሽ፣ ጭረት ያላቸው እንደ ናጫና እንደ ቃጫ ገመድ የመሰሉ የክፉ ዐይን ማደሪያ የሆኑ ተክሎች እንዳሉ ይነገራል። እንደ አረም፣ ኩርንችት፣ አጋምና የመሳሰሉት እነዚህ ጥቅም አልባ፣ የማይፈለጉ ተክሎች ወይም ደካማ ዘሮች ወራሪ የሆነ ጠባይ ያሳያሉ

ይሏቸዋል። ይህ ጠባያቸው ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችን ለሚፈትኑ አፈንጋጮች ምሳሌ የሚሆን ነው። አለመጥቀማቸው እንዳለ ሆኖ ለመኖርና ለመራባት ሲሉ ምግብ መፈለጋቸውም ሌላው ጠባይ ነው። በአረባባቸውና በአመጋገባቸው ውስጥ ያለው ይህ ባህርይ መልካም ነገሮችን አብዝተው እንዲጠቀሙ የሚያደርግ ነው።

እነዚህ ተክሎች የመሬትን ወዝ በመምጠጥ አዝርዕቶችንና ፍራፍሬዎችን ያለምርት የሚያስቀሩ ናቸው። የለመለመውን አጠውልገውና ሥር የሰደደውን አጨናግፈው እህልን በአበባው የሚያስቀሩ ናቸው (አቶ ዜና ደለለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21 የተደረገ ቃለመጠይቅ)። አቶ ዜና ይህንን አረም የአካባቢው ሰው ይሰበስብና ዘሩ እንዳይስፋፋና እንዳይዛመት ይነቅለዋል ይላሉ። የጎዛምን ሰው ከአረም ሁሉ ክፉው አሰንዳቦ ነው ይላል (አቶ ይዘንጋው መኮንን፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። "አሰንዳቦ አንቺን በደቦ" እያለ ወንፈል የዋለው ሰው ያርመዋል። "ግላሎ" የሚባልም ከባድ አረም አለ። ነገር ግን፣ እንደ እንግጫ የከበደ አለመኖሩን ይናገራሉ። "እንግጫ አንቺን በእርግጫ" እያልን ባለበት ረጋግጠን እናጠፋዋለን ይላሉ አቶ ይዘንጋው። "መንቀል ስለማይቻል አናት አናቱን ጠቅጥቀን ባለበት ቦታ እናፈልሰዋለን" (አቶ ይዘንጋው መኮንን፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)።

የአካባቢው ሰው እነዚህን ተክሎች የሚመለከታቸው የክፉ ዐይን ምሳሌ አድርጎ ነው። ባገኘበት አጋጣሚና በተቻለው አቅም ሁሉ ወደ ግዛቱ ላለማስጠጋት ይሞክራል፤ በቅለው ሲያገኛቸው ይነቅላቸዋል። ለጠባያቸው የሚመችና እንዲራቡ የሚደግፋቸውን ነገር ከአካባቢያቸው ያርቃል። የሚመርዛቸውንና የሚያፈልሳቸውን ነገር ፈልጎ እንዳይጠፉት ይከለክላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በባህርይ የማይመስላቸውና በግብሩ የማይመቻቸው ሰው ሲያጋጥማቸው፤ በሃብታቸው፣ በጉልበታቸውና በሥልጣናቸው ተቀናቃኝ ተፈጥሮ ዝናቸውንና ተሰሚነታቸውን የሚነጥቃቸው ኃይል ሲመጣ በእነዚህ ተክሎች ይመስሉታል በማለት አቶ ዜና ይናገራሉ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)።

5.3.3. የክፉ ዐይን ማደሪያ እንስሳት

መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ (2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ከእንስሳት፣ ከአራዊቶችና ከነፍሳት መካከል ክፉ የሚባሉት ሞት የሚስማማቸው እና የሚያከብራቸው ፍጥረቶች ናቸው ይላሉ፡፡ እነዚህ ፍጥረቶች መራባትና መባዛት በደከመበትና እንቅስቃሴና ድርጊት በቆመበት ላይ የሚያርፉ በመሆናቸው፣ በመልካም ነገር የማይጠቀሙ ናቸው እያለ ያካባቢው ሰው እንደሚፈራቸው ይናገራሉ፡፡ ህልውናቸው የተመሰረተው ጥንብ በመብላት፣ በቀንድ ከብቶች ጉያ ተጣብቀው ደም በመምጠጥ፣ በአገዳ እህሎች ላይ በመጣበቅ ሰብሉን በማንቀዝ፣ የመስክን የቡቃያ ሥር በመመረዝ ነው ይሏቸዋል፡፡ አቁስለውና መርዘው ከገደሉ በኋላ በጥንብ ስለሚከብሩ፣ በአንበጣና በአተላ እንዲሁም አመድ በመሳሰለው በጉድፍ ላይ ስለሚውሉ ልማት ሳይሆን ጥፋት ያስደስታቸዋል ይሏቸዋል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)፡፡

ዲያቆን ብርሃኑ፣ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ) ከእኽል የሚፈጠር ባለክንፍ ተንቀሳቃሽና ከቅማል ከፍ የሚል፣ ጥሬ እኽልን የሚበላ ነቀዝ፤ ከእንጨት ባሕርይ የሚፈጠር ትል መሰል ፍጥረት፤ ወይራን፣ ጥድን፣ ኮሶን፣ ዋንዛን፣ ዝግባን የመሳሰሉ ዕንጨትችን በልቶ ዐመድ የሚያደርግ ተባይ፣ እህል እንዳያፈራ፣ አፍርቶም ውጤት እንዳይኖረው የሚያደርጉ ተምቾች በዚህ ስም እንደሚጠሩ ያስረዳሉ፡፡ ተናካሽ፣ ተቆናጣጭ፣ ሥጋና ቅባት ወዳጅ፣ ጥሬ እኽል ለቀለበ ወደ ጉድጓድ የሚያገባ፣ የሚከት፣ የሚጎዳጉድ ጉንዳን፣ በሽራቱ የሚነድፍ ባፉ የሚናከስ መርዛም ተንቀሳቃሽ የምድር አውሬ፣ እንደ ጊንጥ ያሉት መርዛሞች ሁሉ የክፉ ዐይን ምሳሌና አገልጋይ ናቸው ይሏቸዋል፡፡

ሰርቀውና ቀምተው የሚበሉ፣ በጉልበታቸው ተማምነው የሚኖሩ ፍጥረቶች አሉ የሚሉት ዲያቆን ብርሃኑ፣ እነዚህ እንስሳት ሸፍተው አምጸውና አንገዛም ብለው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ስለሚነጻጸሩ ክፉ ይሏቸዋል (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)፡፡ ምግባር ለሌላቸው የአማሊያን ምሳሌ እያደረጉ ይገልጿቸዋል፡፡ እነዚህ ፍጥረቶች የሚኖሩት ባልቀናውና ባልተገራው አካባቢ ነው፡፡ የቀና ሕግን ስላልያዙና ከሰው የመኖሪያ ክልል ርቀው በዱር ውለው የሚያድሩ

በመሆናቸው፣ ክልላቸው ጉልበተኛ የነገሰበትና ሞት ሆዱን ያሰፋበት ነው በማለት ይገልጿቸዋል። ሽብር መፍጠር ጠባያቸው ነው፤ የሚፈሩት ጌታ፣ የሚገዙበት ህግ የለም። ወዳጅ የላቸውም፤ ዘመዳቸው ሆዳቸው ነው ይሏቸዋል። ለዚህ ጠባያቸውና ተግባራቸው መገለጫ ይሆን ዘንድ "አውሬ" የሚል ስም አውጥተውላቸዋል በማለት ያስረዳሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)።

6. ተጋላጭነትና አጋላጭ አውዶች

በዚህ ምዕራፍ፣ ሰዎችን አጋላጭ ስለሆኑ የዕድሜ ክልሎች፣ አጋጣሚዎች፣ ተክሎች ጊዜዎች፣እንስሳት ለክፉ ኃይሎች ማደሪያ ስለሚያደርጋቸው ወቅት ተብራርቶበታል። ከቀን፣ ከሳምንትና ከወቅት የትኛው ሰዓት፣ ቀንና ወር አጋላጭ እንደሆነ ከነምክንያቱ ተገልጸበታል። እነዚህ ክስተቶች ከሌሎች ተለይተው ለምን አጋላጭ እንደሆኑ ምክንያቶቻቸው ተብራርቶበታል። በመሆኑም፣ እነዚህ በጎዛምን አካባቢ ባለው የክፉ ዐይን እምነት ውስጥ አጋላጭ አውዶች ናቸው በሚል የሚፈሩት ከሥርዓት ሽግግር ጋብቻ፣ ወሊድ፣ እርጅናና ሞት፤ ከጊዜ ጨለማ፣ አርብና ክረምት፤ ከተክሎች ህይወት የአመድ ዘመን፣ ከሰብሎች የዕድገት ወቅት የአውድማ ጊዜና የማዕድ ሥርዓት፣ ከእህል የአተላና የአምቡላ ጊዜዎች ናቸው ይላሉ።

እነዚህን ደረጃዎች አጋላጭ ያደረጋቸው ከፍጥረት ሥራቸው ወይም ከተፈጠሩበት ባሕርይ ርቀው ወይም ሸሽተው መገኘታቸው ነው ይላሉ። በመሆኑም፣ ከዚህ በመቀጠል የእነዚህ አጋላጭ አውዶች አይነትና ለምን በዚህ አጋላጭነት እንዳስከሰሳቸው ምክንያቱ ይቀርብበታል።

6.1. የሰብአዊነት አደካከም

አንድ ፍጡር ከተፈጥሮው ይበልጥ ሲርቅ፤ ባዶ፣ ጠፍ፣ ታካቹና ተገኝ ስለሚሆን የመከላከል አቅሙ ይደክማል ይባላል። ነገሮችና አካሎች ከፍጥረታቸው በዕድገት፣ በብስለትና ልዩ ልዩ ጠባዮችን በመልመድ እየሸሹ ሲሄዱ አቅማቸው እያነሰ፣ እያለቁ ሄደው፣ ባዶ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ተፈጥሯቸው ያከትማል ይሏቸዋል። በመሆኑም፣ በሰብዕና አደካከም ውስጥ የሰው ልጅ ተፈጥሮውን በቀዳሚነት የሚያጣው ድንግልናውን በሚለቅበት ደረጃ ላይ ነው። ድንግልና ፍጻሜ የሚያገኘው ጋብቻ ሲጀመር ነው። በመሆኑም፣ በመጀመሪያ የሰው ልጅ ከተፈጥሮው የሚሸሸው ሲያገባ ነው በማለት ይናገራሉ።

ጋብቻ

የጎዛምን ሰው ለድንግልና የሚሰጠው ዋጋና ክብር ከፍ ያለ ነው። ድንግልና በአካባቢው ትኩረት እንዲያገኝ ያደረገው ተፈጥሮ በሙሉ መልኳ የምትገኝበት

የንጽሕና ምልክት በመሆኑ ነው። የንጽሕና ምልክት ተደርጎ እንዲታሰብ ያስደረገውም ሳይዳቀሉና ሳይበረዙ እንዳሉ የሚገኙበት ስለሆነ ነው (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አንድ ዘር ከባሕሪው የሚደክመው እየተዳቀለና ከሌላው ወገን ጋር እየተዛመደ ሲሄድ ነው ይላሉ። መዳቀል የራስ ያልሆኑ ብዙ ጠባዮችንና ልምዶችን ያስተዋውቃል። የሌለን አመል ያስይዛል ይሉታል። አንድን ነገር መያዝ ትቶ ከዚህም ከዚያም ጋር መነካካትን ስለሚያስለምድ በድንግልናና በመታቀብ ያለ ጥብቀትና ጥንካሬ በጋብቻ ይላላል ይሉታል። ሁልጊዜም ከራስ መራቅ ቀድሞ ከነበረ ብርታት የሚያስጠፋ፣ ከንጽሕና የሚያስርቁ፣ የቀድሞ መልኩን የሚያስተው በመሆኑ፣ በመጋባትና በመነካካት ወጥነት ይበረዛል ይላሉ።

አንድ አካል ድንግልናውን ሲያጣ ከቀዳሚነቱ እንደራቀ ሁሉ፣ ያለው ግንኙነትና የማድረግ ልምዱ በሰፋ ልክ ደግሞ ተፈጥሯዊነቱ ይበልጥ እያዳከመና ብዙ ጠባዮችን እየተዋወቀ ይመጣል የሚል ነው። በመሆኑም፣ በልምዶች ይበልጥ መግፋት ባሕሪይን በፍጥነት ማሸሽ ነው ይሉታል። መውለድና መራባት ምድራዊ ናቸው የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው ይላሉ የአካባቢው ሰዎች። የዘሩ ጥበቀት እየኮሰመነና እየጫጨ፣ ስርጭቱም እየጨመረ ሄዶ ራስን ወደ ማጣትና መነሻን ወደ መርሳት፣ ወደመደበላለቅ ያስግባዋል (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ ግንኙነት በሰፋ ቁጥር መውረድ መዋረዱ፣ መበረዝና መከለስ፣ መውደቅና መስነፉ፣ ማነስና መራቅ መከተሉ አይቀርም በማለት ይናገራሉ።

አቶ ተዘራ (አቶ ተዘራ አስማረ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) በነዛምን የተፈጥሮና የማንነት ምልክት የሆነው ድንግልና ክብሩ ልዩ ስለሆነ፣ አስጠብቀው በያዙ ልጆች ላይ የክብር ምልክት ያደርጋሉ ይላሉ። ይህ የክብርና የመጠበቅ ምልክት የሆነው ኬላ ከተጣሰ በኋላ ግን ምልክቱ ይነሳል ይላሉ። ልጃገረዶች የልጅነት ጊዜያቸውን ጨርሰው የበግኝነት[25] ዘመናቸው ሲጀምሩ

[25] በነጃም ያላገባች ልጃገረድ ቁንጆ ያገባች ሴት "በገኝ" ትባላለች። የቁንጆና የበገኝ መለያ ከሆኑት ምልክቶች አንዱ መታጠቂያቸው ነው። የበገኞች መታጠቂያ "መቀነት" ሲባል የቁንጆዎቹ ደግሞ "ምሪ" የሚባል ጠፍር ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

መሻገሪያ በሆነችው የሠርግ ዋዜማ ላይ፣ የትዳር ህይወት 'ህ' ተብሎ ከመጀመሩ አስቀድሞ፣ የድንግልናቸው ምልክት የሆነው ሙሉ ጸጉር፣ በድስት ቅርጽ ልጭት ተቀይሮ 'ሰገን' ወጣች ይላሉ። በመቀጠልም የታጠቀችውን ከቆዳ የተሰራ 'ምሪ' የሚባል ጠፍር፣ ፈተው መቀነት ያስታጥቋታል። የ"ምሪ አፈታቱ" ሥርዓት[26] ዋና ዓላማ የድንግልና ምሳሌ የሆነውን የቆዳ መታጠቂያ በመፍታት፣ የባል ምሳሌ የሆነውን መቀነት በምትኩ እንድታስር ለማድረግ ነው። ይህ ሥርዓታዊ ልማድ ድንግልና ቀርቶ ወደ ዓለማዊ ህይወት መቀላቀልን አመልካች ነው(አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አንድ ሴት ምሪ ከፈታች እንደ ድንግል ሴት ብዙ አትከበርም። የዓለም ስራ ስለምታበዛ እየደከመች፣ ምድራዊ ነገር እየጎተታት ስለምትሄድ ውበቷም ወዟም ስለሚጠፋ፣ ጥንካሬዋም እየላላ ስለሚመጣ ያለ ዕድሜዋ ታረጃለች። በመሆኑም የምሪ መፍታት ሥርዓቱ ዓላማ የድንግልና ዘመን ማብቃቱን ወይም መሞቱን እና የዓለማዊ ጣጣ መጀመሩን ለማሳወቅ ነው ይላሉ።

ይህ አውድ ከተፈጥሮ ወደ ዓለም ሽግግር የሚፈጸምበት በመሆኑ፣ ሙሽራዋ የድንግልና ዘመኗን ጨርሳ የጋብቻ ምዕራፏን አንድ ብላ የምትጀምርበት ጊዜዋ ነው። ዋዜማ፣ ከተፈጥሮ ተሻግሮ ወደ ዓለማዊ ደረጃ መግቢያ ነው። ጋብቻው በዋዜማው ሳይሆን፣ በሠርጉ ዕለት የሚፈጸም በመሆኑ፣ አግባች የበገኝ ህይወት ጀመረች ብሎ ማሰብ አይቻልም። በመሆኑም፣ ዋዜማ ከተፈጥሮም ከዓለምም ሳይሆኑ መሃል ላይ በባዶው የቆሙበት አደናጋሪና ግራ አጋቢ ደረጃ ነው። ይህንን ቅጽር ፈጥነው ካልተሻገሩት ለክፉ ዐይን ያጋልጣል። ሽግግሩ እስኪፈጸም ድረስ ተሻጋሪው አካል መሻገር ወደ አንዱ ወገን ሲያሰልፍ መሃከል ላይ መቆም ግን አሳሳች ያደርጋል ይሉታል። ምክንያቱም፣ ተሻጋሪው አካል የነበረበትን ቦታ ቢተውም ወደቀጣይ ደረጃው ስላልተሻገረ፣ ይህ ያለበት ቦታ አሻሚና ግልጽነት የጎደለው ግራ አጋቢና አስጠቂ ይሆናል። ተሻጋሪው አካል ግራ መጋባት ውስጥ ያለ

[26] ይህ ሥርዓት የሚከናወነው ምሽት ላይ ሆኖ፣ የሙሽራዋ ጓደኞች በድንገት ልጅቱን በመክበብ ከጓዳ ወደ ሳሎን ይዘዋት ይመጣሉ። ከዚያም መሀከል ላይ ከቆመው ምሰሶ አጠገብ ላመነት ወይም ጀንዲ ያነጥፉና ከላይ መጠጊያ ወይም ትራስ በማድረግ እሷን ከዚያ ላይ ያስቀምጧታል። ያላገባች ሴት በወገቧ ላይ እንደመቀነት የምትታጠቀውን "ምሪ" የሚባለውን ጠፍር ልጃገረዶች ተመርጠው እንዲፈቱት ይደረጋል። ከዚያም የድንግልና ዘመኗን ለማጠናቀቋ ብሥራት ሆኖ ዘፈኑ ይቀልጣል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P.O. BOX 1176

በመሆኑ ያለበት ሁኔት አደገኛ ነው ይሉታል። እሱ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ያሉ ሌሎች አካሎችም ጭምር ተጋላጮች ይሆናሉ። አደጋውን ለመቆጣጠር ከነበሩበት ቦታ ወደ አዲሱ ቦታ በሚደረገው ሽግግር ላይ የሚፈጸሙ ክፉ ዐይንን የሚያርቁ ስርዓቶች አሉ።

የጋብቻዋ ዜና ይፋ ከሆነ ጀምሮ ከልጃገረድነት የሚያሻግሩ ሥርዓቶች ከተፈጸሙላት በኋላ ክፉ ዐይን እንዳያጠቃት ብቻዋን አትተውም። ይሽንን መጋለጥ ለመከላከል እኩለ ሌሊት ላይ ወደ ቤተክርስትያን ይዘዋት ሂደው ሆማ እንዲቆረጥላት በማድረግ ክፉ ዐይንን የመከላከል ዘዴ ይፈጸማል። ይህ ሥርዓት በዋዜማው ዕለት ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት የሚከናወን ሲሆን፣ ሚዜ ተመርጦ ሴቱ አታሞ እየመታ፣ ወንዱ ሽመል እየመከተ በሆታ፣ በጭፈራ ሙሽራውንና ሙሽራዋን ለየብቻ ተሸክሞ፣ ሁለት እንጀራ በድቁስ እንዲሁም ድፍድፍ በጥዋ በመያዝ ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ። 'ድፍድፍ'ና ድቁስ ከባለቤቱ በስተቀር ማንም እንዲነካቸው የማይፈቀድ የተከበሩ ምግቦች ናቸው (አቶ ተዘራ አስማረ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እንደዚያ እንደድፍድፉና እንደ ድቁሱ ተከብራ የቆየች ልጃገረድ ናት፣ እንደዚያ እንደድፍድፉ ተከበሮ የቆየ ጎረምሳ ነው ለማለት የሚያዙ ናቸው።

ሙሽራዋ፣ የሆማው ዛፉ ካለበት ቦታ ላይ ስትደርስ፣ ከድፍድፉና ከእንጀራው እንድትቀምሰው ይደረጋል። ይኸም፣ ጋብቻው ለመፈቀዱና በሥርዓትና በደንብ ለመፈጸሙ አዋጅ ይሆናል። ዛሬ በፈቃድ ክብረ ንጽሕናዋን ታስረክባለች፣ ወንድ ከሆነም ክብረ ንጽሕና ይገፋፋል የሚለው በይፋ ይነገራል። የመጣው ሁሉም ሰው በአዋጁ መሳተፉን በመቅመስ ይገልጸዋል። የተረፈው ወደ ቤት ሳይመለስ እዚያው ይቀራል (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ሙሽራዋ ከቀመሰች በኋላ ዛፉን እንድትቀባው ይደረጋል። ይህም ፈቃድ ለመግኘቱ ዜና ይሆናል። ከዚያም ጎረምሶች ከሆማው ዛፉ ላይ ወጥተው ቅጠል እየዘነጠፉ ይጥላሉ። ወርደውም ከድፍድፉም ከእንጀራው ቀምሰው የዘነጠፉትን የሆማ ቅጠል በመያዝ እየጨፈሩ ወደሙሽራዋ ቤት ይመለሳሉ። ከቤት እንደደረሱ ያመጡትን

የሆማ ቅጠል በወንፊት[27] አድርገው ከእናቷ ራስ ላይ በማስቀመጥ፣ ከመሀከል ገብታ እንድትጨፍር ይሆናል። ጭፈራው እንዳለቀ ቅጠሉ ተሰብስቦ በውሃ ውስጥ ይደረግና የመሸራዋ ገላ ይታጠብበታል። በአጠባው ጊዜም፣ ልጃገረዶች ገላዋን እያጠቡ

ሽንት አበባዬ ሽንት፣

ይበጃላሉ ለዓይነት በማለት ይዘፍናሉ።

በህገ ታጥሮ ተከልክሎ የነበረው በፈቃድ ለመጣሱ ምልክት ይሆናል። በግጥሙ ላይ እንደተጠቀመው በሆማ ቅጠል የምትታጠበው ዛፉ ክፉ ዐይንን ያርቃል ገርጋሪ አይነጥላን ይገፋል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

በትዛምን ያለው የጋብቻ ባህል በልጅነት ለመዳር ዋጋ የሚሰጥ ነው። ጋብቻ የክብር፣ የሃብትና የዝምድና መመስረቻ መሳሪያ ተደርጎ ስለሚታሰብ፣ ልጆች ለጋብቻ ሳይደርሱ ገና በልጅነታቸው ትልቅ ኃላፊነት ላይ እንዲቀመጡ የሚያደርግ ነው። በሰባትና በስምንት ዕድሜአቸው ክፉና ደጉን ባለዩበት የአበባ ዘመናቸው በማያውቁት ጉዳይ ለማያውቁት ሰው በቤተሰብ ስምምነት ተላልፈው ይሰጣሉ (አቻምየለህ ጌታነህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በመሆኑም፣ ተፈጥሯቸውን የሚያጡት ገና በልጅነታቸው ነው። በመሆኑም፣ በልጆች ላይ ክፉ ዐይንን የሚያበረታው የለጊዜያቸው ተፈጥሯቸውን ስለሚያሳጧቸው ስለመሆኑ ግልጽ ነው።

በተለይ የጋብቻው ፈቃድ በወላጆች ፈቃድ የሚፈጸም በመሆኑ፣ የፍቺው ቁጥርም ከፍተኛ ነው። አግብተው ምሪ ፈተው በክብረ ንጽሕናቸው የሚቀመጡ ልጆች ቁጥር ብዙ ነው። አንዳንዶች በጫጉላ ቤት እያሉ ልጅነታቸው ተጭኗቸው አልቅሰው አለተመቻቸውም ተብሎ ወደ ወላጆቻቸው የሚመለሱት ብዙ ናቸው። በመሆኑም፣ ማግባት መፍታት ይበዛል። አንድ ሰው በርካታ ሚስቶችን የማግባት ሰፊ ዕድል አለው። ከበርካታ ሰዎች ጋር የሚፈጸመው ጋብቻ ብዙ ልጆች ከተለያዩ

[27] የወንፊቱ ምሳ ዘርዘራ በመሆኑ ሌሎች ሴት ልጆች ስለሚኖሩ ለእነሱ ባል እንዳይመጣ ምልኪያ እንዳይሆን በገማ ዕቃ አያቀርቡትም

አባቶችና እናቶች እንዲወለዱ ስለሚያደርግ ማህበራዊ ቀውሱ ከፍተኛ ነው ይባላል፡፡ በተለይ በአካባቢው የሃብት ምንጩ መሬት ነው፡፡ መሬት ደግሞ በመወለድ በርስት የሚደለደል በመሆኑ፣ የተካፋዩን ቁጥር ስለሚያበዛው በዘመዳሞች መካከል ለሚነሳው ጠብ መንስኤው ይኸው ሰበብ መሆኑ ነው (አቻምየለህ ጌታነህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡

በሽግግሩ ጊዜ ግርግርና ትርምስ ስላለ ማህበራዊ ህጎች ሲጣሱ ይታያል፡፡ በአካባቢው በሕገወጥ ስራዎች ይተራመሳል፡፡ በዚህ አውድ ላይ በሚሳተፉት ሰዎች መካከል ድብድብ፣ ስርቆት ያይላል፡፡ የተቀቀለውን ክክ ይዞ መጥፋት፤ እንጀራውን መስረቅ፤ የወንድ ሚስት መድፈር፤ መቆንጠጥ ማሽኮርመምና መጠቃቀስ በዝቶ ይፈጸማል፡፡ በሠርግ ዕለት ደም ሳይፈስና የዱላ ምክክት ሳይደረግ ቤት አይገባም፡፡ ይህንን ለመከላከል ባለጉዳዮቹ፤ ሰው ወክለው የሠርገኛን ሽመል ቆጥረው እስከመረከብ ይደርሳሉ፡፡ ሙሽራዋን አጅበው የተመለሱት ቆነጃጅት ከወንዶች ልጆች ጋር እየዘፈኑ መገፋፋት መረጋገጥ፣ መቆነጣጥ መሽኮርመም፣ አብሮ መዝፈን አለ፡፡ ይህ ሁሉ ሥርዓተ አልበኝነትና ህገ ወጥ ሥራ ለክፉ ዐይን ስለሚያጋልጥ በሠርግ ቦታ የሚታመመውና የሚለከፈው ሰው ቁጥር ብዙ ነው ይባላል፡፡

እርግዝና

በጋብቻ የተወጠነ አብሮነት የሚባረከው በዘር ነው፡፡ አንድ ሴት ማህጸኗ ከተባረከላት በ"ህግ ቤት"[28] ትጸናለች ይባላል፡፡ በመሆኑም ጋብቻውን ተከትሎ እርግዝና መምጣቱ የግድ ነው፡፡ በጽንስ የተቋጠረ ዘር በመወለድ ወደ አዲስ ዓለም ስለሚሻገር በአካባቢው እርግዝና ራሱን የቻለ ዓለም ነው ይባላል (መርጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ በእርግዝና ዓለም፤ ዘር ወድቆ፣ ጽንሱ ተቋጥሮ፣ ሥጋ ነስቶ ወይም በቅሎ የማህጸን ውስጥ የኑሮ ዘመኑን ጨርሶ ወደ ሌላ የህይወት ዓለም ተሻግሮ የሚያልፍበት የራሱ የሆነ ዘመን አለው፡፡ በዚህ ዘመን እያንዳንዱ ለውጥ በመጸነሻ ወይም በመብቀያ፣ በማደጊያ፣ በማርጃና በማለፊያ ጊዜ የተመደበ ነው፡፡ ይህ የዕድገት መንገድ ከምድራዊው የሰው ልጅ

[28] የህግ ቤት የሚባለው ድንግልናዋን በመጀመሪያ የምታጣበት ቀን ነው፡፡

የህይወት ዘመን እና ከተክለሞች አስተዳደግ ጋር የጎላ ምስስሎሽ እንዳለው ይነገራል።

የጽንስ ዘመን እንደ ህፃንነት ጊዜ ርጋታና ስክነት የጎደለው ነው (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አንድ ሴት እንደጸነሰች ወዲያው የሚታየው ምልክት ማቅለሽለሽና አለመረጋጋት ነው። "የበላችው አልቀመጥ፣ የጠጣችው አልረጋ ይላታል" ይላሉ። ጸባይዋ አልያዝ አልጨበጥ እያለ ትቅበጠበጣለች። ውስጣዊ ሰላምና ዕረፍት ስለሚነሳት እንቅልፍ ታጣለች። የእህል ሽታ ያስጠላታል። ተረጋግታ አትትኛም፤ አርፋ አንድ ቦታም አትቀመጠም ይላሉ። ሰውነቷ እየሰለለና እየመነመነ፣ እየገረጣና እየቀለለ ይሄዳል። የጸናፂ አካል ይቀላል፣ ፊቷ ይገረጣል።

ቀስ እያለ ሥጋዋ ያልቃል። አብዝታ ትገረጣለች። ጽንሱ ሲረጋጋ ደግሞ ሰውነቷ ሞልቶ አምሮባት ትታያለች። ቀስ እያለ ጽንሱ እየገፋ ሲሄድ እየደከመች፣ በራሷ ማዘዝ እያቃታት፣ ሰውነቷ እየተሳሰረ ይመጣል። ከተቀመጠችበት መነሳት ይከብዳታል። አቅም እያነሳት ሄዶ ቆማ መቀመጥ፣ ተቀምጣ መነሳት ያስቸግራታል። አቅሏን ትስታለች። በዚህ ጊዜ ሰራዊ መንፈስ በክፍተቱ ሊገባ ይሞክራል ይላሉ አባቶች (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ከዚያም ጽንሱ የማህጸን ቆይታውን አጠናቆ ወደሌላ ዓለም የመሸጋሪያ ጊዜው ሲደርስ ለማህጸን ሞቶ፣ ለተጨባጩ ምድራዊ ዓለም ይወለዳል(መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ በመጸነስ የተቋጠረው ዘር በመወለድ ለማህጸን ሞቶ ለዚህ ዓለም ጀማሪ ልጅ ይሆናል ማለት ነው። የአራስን[29]ወቅት አጋላጭ የሚያደርገው ይሽን ተፈጥሯዊ ሁኔት ስለሚያስተናግድ መሆኑ ነው። በዚች ምድር ሞቶ ለዚያኛው ዓለም በአዲስ መወለድ እንዳለ ሁሉ፣

[29] ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅም ብትወልድ ሰባት ቀን ያክል የረከሰች ናት። እንደ ህመሟ መርገም ወራት ትረክሳለች። በስምንተኛውም ቀን ልጅዋ ከስጋው ሸለፈት ይገረዝ። ከደሟ እስክትነፃ 33 ቀን ትቀመጥ፣ የመንፃቷም ቀን እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰ ነገር አትንካ። ወደ መቅደስም አትግባ። ሴት ልጅም ብትወልድ እንደመርግሟ ወራት ሁለት ሳምንት ያክል የረከሰች ናት፣ ከደሟ እስክትነፃ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ (ምዕራፌ 12 ፣1-5)።

በማህጸን ሞቶ በዚህኛው ዓለም መወለድም አለ ማለት ነው። በመሆኑም፣ ክፉ ዐይን በተለይ በእንስሳትም ሆነ በሰዎች ህይወት ውስጥ በእርግዝና ጊዜ በተለይም በምጥ ሰዓት የሽግግር ጊዜ ስለሆነ፣ እንደ ሠርግ ዋዜማና እንደሞት ሁሉ አጋላጭ ነው ተብሎ ይፈራል። በወሊድ ጊዜ ምጥ ሲጠነክር ሰራቂ መንፈስ እንዳይገባ ጭስ የሚያጨሱትና ሌሎችን የመከላከያ ተግባሮች የሚፈጽሙት ሰራቂው መንፈስ ክፍተቱን እንዳይጠቀምበት ለመከላከል ነው ።

እንደ ጋብቻ ሁሉ እርግዝናም ግራ መጋባቶች የሚበዙበት ወቅት በመሆኑ፣ በተለይ ያለ ዕድሜ ጋብቻ በተስፋፋበቱ እንደ ጎዛምን ባሉ ቦታዎች የበለጠ አስቸጋሪና ግራ አጋቢ ነው። ያለ ዕድሜያቸው አግብተው በልጅነታቸው የልጅ እናት ስለሚሆኑ አጋላሚው ምጡን የሚያጠነክርና ወደ ተወሳሰበ ችግር የሚዘፍቅም ነው። በዚህ አካባቢ ለእናቶች ሞት ምክንያት የሚሆነው ወሊድ ነው። እናቶች ሆዳቸው ገፍቶ አቅም አንሷቸው የሚንቀሳቀሱ ሴቶችን ሲያዩ "በቀኝ ታቁምሽ" ወልዳ ሲያዩዋት "ሞታ ተነሳች" ይላሉ። ትሮጥ ትዘል የነበረች ልጅ ያለ ዕድሜዋ እጅ እግሯ ተሳስሮ ስትደክም ተፈጥሮዋ ያለጊዜዋ ስለሸሻት፣ ይህ አጋላሚ ከሁሉም ነገር በላይ ለክፉ ዐይን ያጋልጣል ይባላል። በመሆኑም፣ በአካባቢው ሴቶች ያለ ዕድሜያቸው ገና በጨቅላ ዘመናቸው ተፈጥሯቸው ስለሚጎድል ጋብቻን፣ እርግዝናንና ወሊድን የክፉ ዐይን መገለጫ ያደርገዋል ተብሎ ይታሰባል።

በሰው ልጅ አበዛዝ ውስጥ በመጀመሪያ የሚወለድ ልጅ ስሙ በኩር[30] ነው። የአካባቢው ሰው የበኩርን ልጅ የሚገልጸው፣ "የልጅ ሁሉ ራስ" ብሎ ነው (አቶ አሸብር፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ልጁ ከወጣ በኋላ በመጨረሻ ሰዓት ዘግይቶ የሚወጣውንና የእርግዝናን መጠናቀቅ የሚያሳውቀውን ደግሞ እንግዴ ልጅ ይለታል። እንግዴ ማለት እንግዳ ነው። እንግዳ መባሉም ልጅ ከተወለደ በሁዋላ እንደ ልጅ ከወላድ ማሕፀን በመጨረሻ የሚወጣ፣ የሚወለድ በመሆኑ ነው። የልጅ እንግዳ ለማለት "እንግዴ ልጅ" አሉት (ደስታ ተክለወልድ፣ 1962 ፣114)። የእንግዴ ልጅ እንደወጣ ሴት ከሆነች ከማጀት፣ ወንድ ከሆነ ከበር

[30] በኹር፣ መጀመሪያ ልጅ፣ ፍሬ፣ ቀዳሚ፣ ታላቅ፣ አለቃ፣ ሹም፣ አንጋፋ፣ ግንባር ቀደም፣ ፊት የተወለደ፣የበሰለ፣ መብሰል የፍሬ ነው። ልቅና ቅድምና (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፣ 270) ።

አካባቢ ከቤት ውስጥ ይቀብሩታል። ወሊድ ከእናትና ከህጻኑ አልፎ ቤቱን ጭምር የሚያደርገው እንግዴ ልጁ ከቤት ውስጥ ስለሚቀበር ነው። አራሷ ጸበል ስትረጭ ቤቱም አብሮ የሚረጨው ይኸንኑ ለማንጻት በማሰብ ነው።

መውለድ እየቀጠለ ሄዶ ማህፀን ሲደርቅና ማፍራት ሊበቃ ወይም ሊያርጥ ሲል በመጨረሻው የሚወለደውን ልጅ "መቂረጫ" ይሉታል (አቶ አሸብር ፀጋ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። መውለድ በበኩር ልጅ ተቀድሶ በመቂረጫ ልጅ ስለሚቋጭ፣ የነዛምን ሰዎች ከቀዳሚ ልጅ ይልቅ ዘግይቶ የመጣውን "ክፉና ብልጥ" ይሉታል። በኩሩን ልጅ ግን ንጹሕ አድርገው አስበው ገር፣ የዋህ፣ ደግ በማለት ይገልጹታል። ዘግይቶ የሚመጣ በጉልበቱ፣ በአሳቢነቱ፣ በጥንካሬውና በታዛዥነቱ እንደ ቀዳሚ ልጅ ስለማይሆን፣ ለክፉ መንፈስ ማደሪያ ይሆናል ብለው ይፈሩታል። በመሆኑም፣ ከልጆች ይልቅ አባቶች፣ ከተከታዮች በኩሩ፣ ከመጨው ተወላጅ በአካባቢው የሚከበረው ቀዳሚው ንጹሕ፣ መጨው ርኩስ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።

ከዘመድ ሁሉ ለአባት ቀዳሚ ወገኑ ልጅቱ መሆናቸው እውነት ነው። ዝምድና በልጅ ቀድሞ እየራቀና እየሸሸ ሲወርድ ሲወራረድ ቆይቶ ሰባት ቤት ላይ ሲደርስ ይሞታል ይባላል (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ከሰባት ቤት በኋላ ዝምድና ስለሚሞት ቢጋቡ ሥጋነት አይሰማቸውም። ሰውም አያነውራቸውም ይላሉ መሪጌታ ዲበኩለ። ከሥጋ በራቁ ቁጥር የሚያገናኛቸው ነገር ስለማይኖርና እንደ ባዕድ ስለሚያስቆጥራቸው አንዱ ሲጎዳ ሌላውን ስለማይሰማው በክፉ ያስተሳስባቸዋል ይሏቸዋል። ቀድሞ የተወለደ ዘግይቶ ከተወለደው፣ የልጅነት ዘመን ከሽምግልና ጊዜ፣ የተፈጥሮን ንጽህና በመያዝ ስለሚያበላልጣቸው፣ ቀድሞ የወጣው ዘግይቶ ከመጣው በተሻለ ጠንካራ በመሆኑ ለክፉ ዐይን አይጋለጥም ብለው ያሳባሉ።

ነዛምን ሽፍታ የተስፋፋበት አካበቢ እንደሆነ ይነገራል ። የሽፍታ አካባያዊ ፍቺ "ሰራቂ" ሳይሆን "ዘራፊ" በሚል የሚተረጎም ነው (አቶ እውነቱ ተግኘ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ዘረፋ በዚህ አካባቢ የጀግንነት ምልክት ተደርጎ የሚታሰብ ነው። ተደብቆና ጨለማን ተገን አድርጎ የሚወስድን ለይተው

የሚጠሩት "ሌባ" ብለው ነው። እየታየ በጀግንነት ሳይፈራ አስገድዶ አሻፈረኝ ብሎ የሚቀማን ጀግና ብለው ያሞካሹታል። ይህ አድራጎት እንዲስፋፋ ስላደረገው ነገር የአካባቢው ሰዎች ሲናገሩ፣ የአገሬው ሰው እያለ የማይታወቅ መጤ እየተሾመ ከልምዱና ከባህርይው ውጪ እንዲገዛው ስላደረጉት ነው ይላሉ (አቻምየለህ ጌታነህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። አድማሱ ኃይሉ፣ አባቱ ራስ ኃይሉ ታስረው በምትካቸው የሸዋው ሰው ከንቲባ ማተቤ ሲሾሙ፣ "ሸዋ ከሚበላው ያገሬ ሰው ይብላው" ብለው መካዘኑን ከፍተው ዝረፍ ብለው በማዘዛቸው የማርቆስን ሰው ያከበሩት እሳቸው ናቸው እየተባለ እንደ ዝና እስካሁን ድረስ ይነገራል።

ኃይሉ ተክለሃይማኖት የቁም እስረኛ ሆነው፣ ኃይሉ በለውን ወንድማቸውን መሾም እየቻሉ ለምንድን ነው ራስ ብሩን መሾም ያስፈለገው በሚል አገሬው ሸፍቶ ነበር ይባላል (አቻምየለህ ጌታነህ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። የጎጃም ገበሬዎች አመጽ እየተባለ የሚነገረው በብር ካምሳ ግብር ምክንያት የተቀሰቀሰ ሳይሆን፣ ደጃዝማች ዐሐዩ ሊያስተዳድሩ በመምጣታቸው የተቀጣጠለ ነው ይላሉ። አገሬው ባላባቱ እያለ እንዴት መጤ ይግዛን በሚል ለአመጽ የተነሳው ከመጤ ይልቅ ባላባትን ስለሚያከብር ነው ይላሉ (አቶ እውነቱ ተገኘ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

አንዳንድ ጊዜ በምሥራቅ ጎጃም የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ በወረዳ አከላል፣ በወረዳ ከተማ ምርጫ የሚነሱ ጠቦች መነሻ ይኸው ምክንያት ነው ይባላል። በጎጃም ውስጥ ያሉ የቦታ ስሞች በአቅኝዎች የተሰየሙ ስለመሆናቸው አፈ ታሪኮች ያስረዳሉ። የጎጃም አሥራ ሁለቱ ቤቶች በአባት በአባቶች የተከፋፈሉ ናቸው። ልጆቹ ደግሞ በተራቸው ለልጆቻቸው ድርሻቸውን ከፋፍለው እየሰጡ በድልድል እንደወረደ ይነገራል። የአሁኑ አስተዳደር አወቃቀር አከላለል ሌሎች መስፈርቶችን ታሳቢ ስለማያደርግ፣ አባቱን ትቶ ልጁን ወረዳ፣ ትላቱን ዘሎ ትናሽን ከተማ ሲያደርግ በአካባቢዎች መካከል ግጭቶች እየተነሱ ራሳችንን ችለን እንተዳደር፣ እኛን ትተው እነሱን አደረጉ የሚሉ ግጭቶች በርክተው ይሰማሉ። እነዚህ አንዱ ሌላውን አካባቢ በክፉ እንዲያይ፣ እንዲንቅ፣ እንዲጠቃቃ እያደረገ የአካባቢውን ሰው

በማክፋት መልካም ነገር እንዳያስብ ያደረገ ነው ይላሉ (አቶ ቅሩብ አንተነህ፣ 005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

እርጅና

የሰው ልጅ በልጅነት ዘመኑ እንደ ነፋስ ሮጦ፣ በእሳት ጊዜው ፍሬ አፍርቶና በስሎ፣ በውሃ ሰዓቱ እየደከመ፣ እየፈዘዘ ይሄድና ከመሬት ዘመኑ ላይ ሲደርስ ይሞታል ይሉታል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ነፋስ፣ እሳት፣ ውሃና መሬት በአራቱ ወቅቶች ልክ በሰው ህይወት ውስጥ የሚፈራረቁ፣ ሰውን ከልጅነት እስከ እርጅናው ይዘውት የሚሸጋሩና የሥጋን ባሕርይ የሚገልፁ ባህርያት ናቸው (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

መሪጌታ ዲበኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ልጅነት ለተፈጥሮ ቅርብ በመሆኑ፣ ሁሉም ነገር ከነፍጥረቱ ያለበት ነው ይላሉ። የልጅነት ባሕርይ የሚያረጀው በዓለም ሥራ[31] እየረከሰና እየጎደለ ሄዶ በመጨረሻ ሲደክም ነው። በመሆኑም፣ የእርጅና ዘመን የሥጋ ባሕርዮች ከሚገባው በላይ የሚዛበቡበት ዘመን ነው። የመሬት ጠባይ በበረታ ቁጥር የሰብዕና ማብቂያው ጊዜ ይሆናል ይላሉ። በመሆኑም፣ እርጅና በባሕርዮች መካከል የበዛ አለመጣጣምና አለመመጣጠን መኖሩን ጠቋሚ ነው። ሽምግልና ወደ ሙሉ ዕልቀት ታዛኝነትና ተገዥነት የሚመራ የዕድሜ ማለቅ ያለበት በመሆኑ፣ የማምሻ ዘመን አምሳል አድርገው ያስቡታል (አቶ አሸብር፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 22፣ ቀን በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የሰው ልጅ በዚህ ዘመኑ ሥጋ ስለሚከብደው ያጎነብሳል። እጅና እግሩ እየተሳሰሩበት ይጎትቱታል። የማሰብና የማስታወስ ኃይሉ ይደክማል። መርሳት፣ መዛልና መስነፍ አብዝቶ ይመጣበታል ይላሉ። ይህ አጋጣሚ የሥጋ መክበር የሚገለጥበት በመሆኑ፣ ለነፍስ አይመቻትም ይላሉ። በመሆኑም፣ ክፍተቱ ለክፉ ዐይን መንገድ ከፋች ነው በማለት መርጌታ ዲበኩሉ ያስረዳሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

[31] የዓለም ሥራ ሥጋን የሚያስደስት፣ ለራስ ምኞት የሚሰጥ፣ የዕውቀት ያልሆነ ተግባር፣ ድርጊትና ሃሳብ ለማለት ነው።

ለዚህ ሃሳባቸው ምሳሌ አድረገው የሚጠቅሷቸው መነኩሴዎችንና ሽማግሌዎችን ነው። እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ከልጅነት የራቁ፣ ወደ ሞት የተጠጉና ለመክሰምና ለመድረቅ የተቃረቡ ፍጡራን ናቸው። እርጅናቸው ለሥጋ ስላስገዛቸው ድካም የዘመናቸው ጠባይ ነው ይሏቸዋል። በመሆኑም፣ ይህንን ድካማቸውን ተጠቅሞ ክፉ ኃይል ሊያድርባቸው ይችላል የሚል ፍርሃት አለ (አቶ አሸብር፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይህ መድከምና መጠውለግ የእርጅና ዘመን ጠባይ ስለመሆኑ የሚያስረዱ በርካታ ነገሮች እንዳሉ አቶ አሸብር ይናገራሉ። ከሚለብሱት ልብስ ጀምሮ ሁሉም የሚገለገሉባቸው ዕቃዎች በሙሉ የመሬት ተጽእኖ ምልክት ያለባቸው ስለመሆኑ መስካሪዎች ናቸው።

ለዚህ ምሳሌ አድርገን "ወይባ" የሚባለውን የመነኩሴ ልብስ መጥቀስ ይቻላል። የመነኩሴ ልብስ "ወይባ" የተባለው ቀለም ቢጫ በመሆኑ ነው ይላሉ። ይህ መልክ በሰብሎች ላይ የሚወጣው በቅለው፣ አብበውና አፍርተው ሊደርቁ በሚቃረቡበት ወቅት ነው (አቶ አሸብር፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እንደሚታወቀው ሰብሎች ወይም ተክሎች ቢጫ አበባ ካወጡ በኋላ ወዲያው እየጠወለጉ፣ እየደረቁ ሄደው ይከስማሉ። ይህ ወቅት በሰዎችና በተክሎች ህይወት ውስጥ አቅም የሚያንስበትና ለመቆም የሚንገራገዱበት፣ እየፈዘዙና እየሰነፉ የሚሄዱበትና ምድራዊነት እየተሰማቸው ወደመርገፍ፣ መዝመምና ማለቅ የሚደርሱበት ነው በማለት ያስረዳሉ። ይህ ቀለም በአለባበሳቸው ላይ ምልክት ሆኖ መግባቱ፣ በቀላሉ የሚጠቁበትና ለመሸነፍና ለመውደቅ የሚንገዳገዱበት ጊዜ መሆኑን ለመጠቆም ነው። ስለዚህ፣ የሞትን መንገድ የጀመሩ ደካማ አካሎች አድርገው ይመለከቷቸዋል።

መሪጌታ ሞላ፣ መነኩሴዎች የሚደገፉበት መቋሚያ የሚሰራው በበረሃ ከሚገኝ "በትረ ሙሴ" ከሚባል ዕጽ እንደሆነ ይናገራሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በትረ ሙሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተገለጸው ሙሴ እስራኤላውያንን ከፈርኦን ግዛት ነጻ ሲያወጣ ቀይ ባህርን ለሁለት ከፍሎ ያሻገረበት "አስማታዊ" ዱላ ነው ይላሉ። ይህ ዱላ ባህሩን ለሁለት በመግመስ መንገድ የሠራው ባህሩን ከፍሎ አድርቆ ነው። በዚያን ጊዜ፣ ርጥብ በደረቅ ተሸንፏል።

ስለዚህ፣ በዚህ ዕፅ ተፈጥሮ ውስጥ የማድረቅ ሃይል እንዳለ ግልጽ ነው ይላሉ መሪጌታ ሞላ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

መሪጌታ ሞላ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ በጎዛምን መነኩሴና ሽማግሌ ከሌላው የዕድሜ እርከን ሁሉ በልጦ በተለየ ይከበራል። ለመከበራቸው መነሻው መፈራታቸው ነው ይላሉ። በሽምግልና፣ በምክር፣ በምርቃትና በእርግማን ላይ ከጉልበተኛ ሰው ይልቅ የእነሱ ይደመጣል። ቢራገሙ ያደርሳሉ፣ ቢመርቁ ከመጋለጥ ያደናሉ እያለ ሰው እንደሚያከብር እንደሚፈራቸው ይናገራሉ። እነዚህን የማኅበረሰብ ክፍሎች ያስከበራቸው ነገር በሳሳው ጉልበታቸውና አቅማቸው ውስጥ ክፉ ዐይን በቀላሉ ተስሎ ምኞታቸውን ሊያሳካ ይችላል የሚል ፍራቻ ነው ባይ ናቸው።

አባቶች እንደነገሩኝ "በአካባቢው ሰው ከቦታ ወደ ቦታ በመኪና ሲጓጓዝ፣ መንገዱ አልሰልጥ ካለውና የሚያደነቃቅፈው ነገር ከበዛ የሚጠይቀው፣ "መነኩሴ አለ?" ብሎ ነው ይላሉ (አቶ አሸብር፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 22፣ ቀን በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች መነኩሴ በገባበት መኪና አንሳፈርም ብለው እስከመውረድ እንደሚደረሱ ይናገራሉ። ይሽን የሚያደርጉት፣ ሞትን ይጠራሉ ብለው ስለሚፈሯቸው ነው (አቶ አሸብር፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) ።

መካንነት

መውለድ ያቆመ ወይም የነጠፈ ማህጸን ማፍሪያና መባጎ ካልሆነ ባዶ ነው። ማህፀን ማፍሪያ ስለሆነ ማፍራቱን ካቆመ ወይም የማያፈራ ጠፍ ቦታ ከሆነ ባዶ ይሆናል። ሰባት ቤት ላይ ደርሶ የቆመ ዝምድናም ቅርበት እየራቀና መተዋወቅ እየጠፋ ሄዶ ባዕድ ላይ የደረሰ በመሆኑ፣ መነመድ የቆመበት ወይም ያበቃበትና የተቆረጠበት ነው። በመሆኑም፣ ዝምድና በባዕድነት፣ መካንነት በወሊድ ባዶ ደረጃ ላይ የደረሱበት በመሆኑ አጋላጮች ናቸው ይሏቸዋል። ይሽ አጋጣሚ ለክፉ ዐይን ማደሪያ የሚሆን ክፍተት ነው ይሉታል። ብልቶች በቀዳሚነት ከያዙት ጠባይና ባሕርይ እየራቁ በሄዱ ቁጥር ኃይላቸው እየቀነሰ፣ እየወረደ መጥቶ መጥጥ ብሎ ያልቃል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARY

ይህ ዕልቀት በተፈጥሮ አካሎች መካከል ያለውን ግንኙነት ልል የሚያደርግና አጋልጦ ለሞት የሚሰጥ ነው ብለው ያስቡታል። ይህ ክፍተት ደግሞ በሞት ለሚበረቱ መንፈሶች መልካም ዕድልን አመቻች ያደርጋቸዋል ይላሉ። ሞት በአንድ አካል ላይ ሲሰለጥን፣ ይፈጽመዋል ተብሎ የሚታመነው መተካት፣ መርባትና መብዛት የሚችለውን አካል ያዳክምና ለዓላማው ፍፁም ታዛዥና አገልጋይ ማድረግ ነው (መሪጌታ ኪዳነ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በተለይ በአካባቢው፣ "ባዶ እንስራ ይዛ ውሃ ለመቅዳት ወደ ወንዝ የምትወርድ ሴት ስታቋርጣቸው ያገናለ" ይባላል (አቶ ተዘራ አስማረ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አንዳንዴ እንዲያውም የፍርድ ቤት ቀጠሮ ያለበት ወይም ለሁነኛ ጉዳይ መልካም ነገር ተመኝቶ የሚንቀሳቀስ ሰው እንደዚህ አይነቱን ገጠመኝ ለውሎው መጥፎ ምልኪያ ያደርገዋል (ቄስ እንስማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የማይቀርበት ጉዳይ ቢሆን እንኳ ይመለሳል ይላሉ። ያሰብኩት ይሳካል ብሎ በፍጹም ትንሽ እንኳ አይጠራጠርም። በተቃራኒው፣ "ውሃ ቀድታ እንስራዋን ሞልታ ቀድማ የምታልፍ ሴት ሲያይ ደግሞ በደስታ ሰክሮ በአጋጣሚው እየተደሰተ ይሄዳል" እያሉ ያወራሉ (ቄስ እንስማ ደለለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አንድ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ በልጅነቱ ከዚህ ሃሳብ ጋር የሚስማማ ታሪክ እንዳጫወተኝ ትዝ ይለኛል። የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያለን አብራን የምትማርና ከአጠገባችን የምትቀመጥ አንዲት ተማሪ ነበርች። ይቺ ልጅ ከእኛ ሰፈር ተከራይታ የምትኖር አንዲት መምህርት እህት ስለነበረቻት እሷን ለመጠየቅ ደጋግማ ወደ እኛ ሰፈር ትመላለስ ነበር። ይህ ልጅ ደጋግሞ በማየቱ ከዚች ልጅ ጋር የዐይን ፍቅር ይይዘዋል። ስለእሷም አብዝቶ ያስብ ያወራ ነበር። በዚህ መሀከል ህልም ያልማል። ህልሙም ለእህቷ "ከጉድጓድ ውሃ እየቀዳ እንስራዋን ሞላሁላት" የሚል ነበር። ይህን ህልም ለአባቱ ሲነግራቸው የፈቱለት፣ "እዚያ ቤት ዘር አለህ። እህል ውሃህ እዚያ ቤት ገብቷል" የሚል ነበር (ሳምሶን ብርሃኔ፣ 1982፣ ቀኑ በውል የማይታወቅ) ።

እንስራ እንደሚታወቀው የሴት ዕቃ ነው። በአካባቢው ወንድ ልጅ ውሃ በእንስራ ቀድቶ አይሸከምም፤ ጭቃ አቡክቶ ቤት ይመርጋል እንጅ ሸክላ አይሰራም (ወ/ሮ በየነች፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። የሰው ልጅ ስራቱ በሴት ነው። በአካባቢው ወንድ ልጅ ወደ ጓዳ ገብቶ ከእንስራ ውሃ አይጠልቅም። ቢጠማው ሴቶችን ውሃ ስጠኝ ብሎ ይለምናል እንጅ ራሱ ከፍቶ አይቀዳም። እነዚህ የሸክላ ዕቃዎች የሚቀመጡት ዘወር ካለ *"ማጀት"* ከሚባል ልዩ ክፍል ውስጥ ነው። ወንድ ልጅ ወደዚህ ክፍል አይገባም፤ ነውር ነው። "ሴት ልጅ ከባሏ ስትጣላና የሚመታት መስሎ ከታያት መደበቂያዋ ይቺው ክፍሏ ናት" ይላሉ (ወ/ሮ አካልነሽ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ነገሩ የሚያናድድ መስሎ ቢሰማው እንኳ ሊሳደብና ሊዝት ይችል ይሆናል እንጂ ወደ ማጀት ለመግባት አይሞክርም ይላሉ (ወ/ሮ በየነች 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

ውሃ ከህልሙ ትርጉም ለማየት እንደቻልነው 'ዘር' ነው። መርጠብ በአካባቢው ለህይወት ወሳኝ ሲሆን፣ እንስራው ውሃ ሲኖረው ለማህጸን መለምለም፣ ውሃ አልባነት ደግሞ ለመድረቅ ምሳሌ ይሆናል (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሂደ ቃለመጠይቅ)። በዚህ የተነሳ በቤት ውስጥ ባዶ እንስራ አይቀመጥም ይላሉ የጎዛምን እናቶች። የድቁስና የቅቤ ቅልም እንዲሁ ባዶ አይሆንም (ወ/ሮ የውብዳር፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ማዕድ ቀርቦ "ለስብዓት የሚሆን ተው" ይባላል። ይህን ባዶነት አጋላጭ ያደረገው ባዶ ቦታው ክፉ ኃይልን ሊጠራ ይችላል ብለው ስለሚፈሩት ነው (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። ክስተቱ ከቤት ውስጥ ባለ ልጆች፣ ከብቶችና ሰብሎች ላይ መልካም ያልሆነ ነገርን ይጠራል፤ ለጠላት ያጋልጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ይህ ክፍት መሆን አቅምና ጉልበት የማጣትና በቀላሉ ለመወረርና ለመያዝ ምቹ የመሆን ምልክት ነው። አጋላጭነቱ ባዶ የሆነውን ነገር ብቻ ሳይሆን፣ በአካባቢው ያለን ማንኛውንም ነገር ይጨምራል ።

አቶ ዜና (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ) ንብ አንቢዎች ማር ሲሸጡ፣ ገዥዎች እጆቸውን ከቅለ ወይም ከማሩ ዕቃ አስገብተው ሲጠርጉ እያዩ

አያነውሩም ወይም አይከለክሉም ይላሉ። በዕቃው ውስጥ ውሃ ጨምረው ለማለቅለቅ ሲከጅላቸው ግን ዝም በለው እንደማያልፉት ይናገራሉ። ሃብት ጠራርጎ ይወስድብናል ብለው ስለሚፈሩ ያስቆሟቸዋል። ባዶ ዕቃ አይመለስም ነውር ነው ይላሉ። በአካባቢው ወላድ ወይም ክበድ ላም እና በግ ከቤት ወጥቶ አይሸጥም፣ ነውር ነው። በተለያዩ ምክንያቶች ተነሳስተው ከብት ሲሸጡ፣ ከጭራው ነቅለው እንደሚያስቀሩ ይናገራሉ። እንስሳውን አሥረው የወሰዱበትን ገመድም ጥለውት አይመጡም። ሊሸጡት ያወጡት ከብት መንገድ ላይ ከሸና ግን ወዲያው ይመልሱታል። "እያየን ሲሳያችንን ከቤታችን አናስወጣም" ይላሉ (አቶ ዜና፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)።

የጎዛምን ሰው መሃላን ሲያስፈጽም በደረቅ፣ ሲመርቅ ደግሞ በርጥብ ነገር እየመሰለ ነው። የሰረቀን ወይም የቀጠፈን ሰው ሲያስምሉ ደረቅ የሆነ ነገር ያቀርባሉ። ከዚያም ድንጋይና ድንጋይ እያዋቀሩ ያፍዝዘኝ ይጫነኝ በል ይሉታል። ሰርዶ እያስነቀሉ ሥሬን ይንቀለው ከዚህ ያጥፋኝ በል ይሉታል። በእሳት ላይ ውሃ እየጨመሩ እንደዚህ ያጥፋኝ፤ ስለት ነገር እያስጨበጡ እንደዚህ ይውጋኝ ይላሉ። በረት እያስጠረጉ እንዲህ ያንጣኝ፣ ድንጋይ ላይ እያቆሙ እንደዚህ ያፍዝዘኝ እንደዚህ ያድርቀኝ በል እያሉ ያስጠነቅቁታል (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሲመርቁ ደግሞ በቁጤማ፣ በለምለም ዛፍና ብዙ በሚያፈራ እህልና ተክል እየመሰሉ መልካሙን ሁሉ ይመኙለታል። በደረቅ ውስጥ ክፉ ዐይን ስለሚሳል ክፉውን ለከፍው ኃይል የሚሰጡት ይሆናል ማለት ነው።

በጎዛምን አካባቢ መካን ሴት በአራስ እህል ዝግጅት አትሳተፍም። የነፍሰ ጡሮችና የአራሶችን ገላ መካን ሴት አታጥብም። በምጥ ጊዜ ከቤት ውስጥ ገብታ አብራ እንድትለማመን አይፈቀድላትም። የዚህ ክልከላ መነሻ፣ "ምጡ ይጠናል ወሳጅ ይስባል" ብለው ስለሚፈሩ መሆኑን ይናገራሉ። በመሆኑም፣ ከቤት ውስጥ "ደጅ ሆናችሁ አግዙን አለማምኑን" በሚል ከተወሰኑ ሰዎች ጋር ቀላቅለው ያርቋቸዋል (የውብዳር ጌታሁን፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። መካኖችም ይህ እንደሚባል ስለሚያውቁ፣ አንዳንዶች ስሜታቸውን ተቆጣጥረው ከውጭ ተቀምጠው የብስራቱን ዜና ይከታተላሉ። አንዳንዶቹ ግን እስክትገላገል

ድረስ ያልሰሙ መስለው ከቤታቸው ይቆዩና እልል ሲባል ገብተው ይቀመጣሉ። በዚህ ስሜት ውስጥ ሆነው የተወለደውን ልጅ ማየት ልጁንም ሆነ እመጫቷን ለአደጋ ያጋልጣል ብለው ስለሚፈሩ ሰው እንዳያይ መጋረጃ ይጋርዳሉ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ አይደለም ጨርሰው ያልወለዱ፣ ወልደው የሞተባቸው፣ ብዙ መውለድ ፈልገው ያልቻሉ ሰዎች ጭምር ልጅ በበዛበት ቤት ውስጥ ሲገኙ ዐይናቸው እንደሚፈራ ይነገራል (አቶ ተዘራ አስማረ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ልጆች እንዲደበቁ፣ ወደ ጎረቤት እንዲሄዱ፣ ከጓዳ ወይም ከምንጃ ቤት እንዲቀመጡ ያዝዟቸዋል። ከላይ ለማየት እንደተቻለው ባዶ የሆነና ወደ ማለቅ የተጠጋ ነገር ሁሉ፣ የሚያልፍ፣ የሚጠፋ፣ የሚነትብና የማይተካ ነገር መጥፎ ምልኪያ ያደርግበታል።

በእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ መድረቅ፣ መጠውለግ፣ አለማፍራትና አለመተካት ስላለ፤ የሚያፈራ፣ የሚተካና የሚያድግ ነገር ባለበት ነገር ውስጥ ተፈሪ ያደርጋቸዋል። በመምከን ውስጥ መውለድና መርባት ስለሌለ፣ በመውለድ የሚገኘውን ጥቅም መምከን የክፉ ዐይን ማደሪያ ሆኖ ሊያሳጣው ይችላል በሚል ይፈሩታል። ራስን መተካትና ማስቀጠል በሌለበት አጋጣሚ የማፍሪያ ቦታው የክፉ ዐይን ማደሪያ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል። በተወሰኑት መካከል ያለ በሌሎች ውስጥ ግን የታጣ የጎደለ ስለሆነ፣ በአላቸው ዘንድ ሲታይ ያጓጓል። በአንዱ ደርቆ በሌሎች ላይ በዝቶ ሲታይ በዕድል ይታዘናል። በመሆኑም፣ ክፉ ዐይን በምኞታቸው አድሮ ሌሎች እንዲጎዱ ምክንያት ይሆናል ይላሉ።

ይህ ንዴትና ምኞት ስለሚታወቅ የወለዱና የከበሩ ሰዎች መውለድ በማይችሉ ሰዎች መካከል ሲገኙ መታደላቸው ያስመኛል፤ ተሰጧቸው ያስቀናል፤ የእኛ በሆነ ኖሮ ብሎ ያስጎመጃል። እንደሚታወቀው፣ በሰዎች ተፈጥሮ ውስጥ ያለው የዘር አበዛዝ መንገድ አንድ አይደለም። ወላዶች የመኖራቸውን ያህል መካኖችም መኖራቸው እውነት ነው። ይህ ሁኔታ በአንዱ ያለውን ነገር በሌላው እንዳይኖር ያደርገዋል። ሁሉም ሰው የተሰጠው ነገር ቢኖርም ማህበረሰቡ ለጸጋዎቹ ያለው ቦታ ለተሰጥኦዎች ያለን አቀባበል ይለያየዋል። ሁሉም ተሰጥኦዎች እኩል ክብር

እንዳያገኙና ለአንዱ ልዩ ቦታና ግምት ለሌላው ደግሞ የወረደና የተናቀ አመለካከት እንዲያገኝ ያሳስበዋል።

ስለዚህ፣ ይህ የጎደላቸውን ነገር በሌላው ላይ ሲያዩት ማጣትና ማግኘት በልጁ አገኛኘት እየተሳለ መጥፎ መጥፎ ነገር ያስታውሳል። የአንዱ ማግኘት የሌላውን ማጣት ስለሚያሳስብ ነቂው አንቂውን ባዩ ቁጥር ጉድለቱን እንዲያሰላስል ያደርገዋል። እነዚህ ሰዎች በተገኙበት አካባቢ ልጆችን ይሆነኝ ብሎ የመሸሸግ ልማድ የሚታሰበው በአለመውለድ ስሜት ውስጥ ያለው ተጽእኖ በመታወቁ ነው። በዚህ ስሜታቸው ውስጥ ክፉ መንፈስ ተስሎ ሰዎችን ለመጉዳት ምክንያት ይሆናል በሚል ነፍሰ ጡሮችን እና ወላዶች በጨለማ ክፍል ውስጥ ያስተኟቸዋል። ሰው ገብቶ እንዳያያቸው በመጋረጃ ይከለላል።

ከዚህ ሃሳብ ጋር ተያያዥነት ያለው አንድ ገጠመኝ ያጫዎቱኝ ሰው ነበሩ። እኒህ ሰው እንደነገሩኝ፣ እህታቸው አይኖቿ ትልልቅ የሆኑ ሴት ልጅ ትወልዳለች። ከጎረቤታቸው አንድ መካን ሴት ነበረችና ልጅቷን ልይ ብላ ትገልጣታለች። ከዚያም "ወይኔ አይኗ ሲያምር" ብላ ትክዝ ትልባታለች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ልጅቷ አይና መቅላት፣ እንባ መቋጠር ጀመረ። አሁን አድጋ እንኳ አይኗ በትክክል አያይም፤ የተንሸዋረረ ነው (ወ/ሮ ውዴ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 5፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)

እነዚህ ሰዎች ይህን ክብር እንዲያጡ፣ ወላዶች ደግሞ ተገቢውን ቦታ እንዲያገኙ ያደረገው "ወላድነት" ነው (ወ/ሮ ቦሰና ፍካሬ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። የማትወልድ ሴት የሞቀ ቤትና የክብር ባል አይኖራትም። ደፋሪዋም ብዙ ነው። ለውሸምነት ካልሆነ አግብቶ በክብርና በወግ የሚይዛት አባወራ አታገኝም ይባላል። መጫዋቻና መላገጫ እየሆነች አክባሪ ታጣለች ። በእነዚህ ሰዎች ስሜት ውስጥ ንዴትና ብስጭት በቋሚነት ይይዛቸዋል። ትካዜ አይለያትም። የአካባቢው ሰው "አለመ·ን አየ" ሲል ወልዶ ድሮ ተደሰተ ማለት ነው። ስለዚህ፣ እነዚህ ሰዎች አለማቸውን የሚያዩ አይሆኑም።

ራስ ሃይሉ፣ "የመሃን ልጅ እኔ ነኝ" እያሉ ይወርሱ ነበር ይባላል። አንዲት ሴት መካን ልጃቸው ሞታባቸው ራስ ሊወርሱብኝ ነው ብለው ያስባሉ። " አቤቱ! አሮጊት

እናትዋ እያለሁ እንዴት ልጄ ትወረስ"፣ እያልሁ ብጮኽም አይሰሙኝም። ስለዚህ፣ በሚሄዱበት ሁሉ እየተከተልኩ መቆሚያ መቀመጫ አሳጣቸዋለሁ። ሲሰለቻቸው ይሰጡኛል ብለው በሄዱበት ሁሉ መከተል ይጀምራሉ። የዚያን ዘመን ጉዞ ይደረግ የነበረው በክብት ስለሆነ፣ ራስ ሃይሉ በበቅሎ ሆነው ሲሄዱ፣ ሴትዬዋ ደግሞ በእግራቸው ከኋላ ከኋላ እተየከተሉ ረፍት ይነሷቸዋል። 'ፈጣን ማዞሪያ' በሚባለው አካባቢ ሲደርሱ፣ አንድ ገበሬ ላም ጠምዶ ሲያርስ ራስ አይተው፣ "ለምን ነው አንተ?"፣ ሲሉ ይጠይቁታል። አራሹም፣ "ባትወልድ ነዋ! ጌታዬ" ብሎ ይመልሳል። ደጅ ጠኝዋ ይህን መልስ በሰሙ ጊዜ የሚከተለውን ለራስ ስለ ነገሩ ገንዘባቸው ተባርኮ ቤታቸው ተመለሱ ይባላል።

ዕዩት ያሳያችሁ የመካንን ጉድ

ጠምጥሞ ይገርፋታል እንደኔ ባትወልድ (አለማየሁ ሞገስ፣ 9)

በዚህ አፈ ታሪክ ውስጥ ላም ያለ ሥራዋ የበሬን ቦታ ተክታ እርሻ ላይ ገብታ እናያታለን። ይቺን ላም ያለ ቦታዋ እንድትገባ ያደረጋት ደግሞ አለመውለዷ ነው። በአካባቢው ሴት የሆነች ሁሉ ለእርባታዋ ካልሆነ በቀር ለሌላ ስራ አትሆንም። ይህንን የሴትነት ሚና አስነጥቆ ወደ ወረደና ተራ የጉልበት ስራና የጅራፍ ሲሳይ የዳረጋት መምሰኗ ወይም መምከኗ ነው። ስለዚህ፣ እንዲያፈራ ሆኖ ተፈጥሮ ዘር መተካት ካልቻለ ሁልጊዜም መገፋትና ማዕረጉን መተው የማይቀር ስለመሆኑ ከላይ የቀረበው ታሪክ ያስገነዝባል።

6.2. የጊዜ ዕልቀት አውዶች

ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ) በእያንዳንዱ ነገር ቀዳሚ የፍጥረት ዘመኑ ያለው ነገር እንደነፋስ ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነው ይላሉ። ያ ፍጥረት እያገለገለና እየሰራ ሄዶ ከተወለደበትና ከተፈጠረበት ዘመን ሲርቅ፣ ተቀዳሚ ተፈጥሮውን እያጣው ይሄዳል። ፍጥረቱ እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስና አገልግሎቱን ጨርሶ ሲያጠናቅቅ የሚቀረው ነገር የሚጠራው "ሙት" ተብሎ ነው። አካል በእርጅና ደክሞ በሞት እንደሚፈርስ ሁሉ ንጋት፣ የቀን ብርሃንና የዓመት ውልደት ሞት የሚሆነው በጊዜ ዕልቀት ማለትም በጨለማ፣

በአርብና በክረምት ነው ይባላል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። መርጌታ አይነኩሉ በበኩላቸው፣ "የብርሃን ሞቱ ወይም የቀን ዕልቀቱ በጨለማ፣ የሳምንት በአርብ፣ የበጋ ህልፈቱ ወይም ማለቂያው በክረምት ነው" ይላሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ የጊዜ ዕልቀት የሚገለጥባቸውና ለክፉ ዐይን የሚያጋልጡት ባዶ አውዶች ከዚህ ቀጥሎ ተዘርዝረው ቀርበዋል።

ጨለማ

የጎዛምን አባቶች፣ ራት ከበሉ በኋላ የሚመርቁት "እራትና መብራት አይንሳችሁ" ብለው ነው (ሰዋገኝ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። መብራት ብርሃን ነው። ራት የጨለማ ጊዜ ምግብ ነው። እራት እዚህ ላይ ውክልናው በዕለት የሚበላውን ብቻ ሳይሆን ዕድሜ ሲገፋ፣ ጉልበት በጊዜ ብዛት ሲደክም ወደ ማታ በእርጅና ዕድሜ ስላለው ስንቅ ማውራታቸው ነው። ሰዋገኝ ይህንን፣ "ዐይንህ በጠፋ፣ እግርህ በደከመ ጊዜ ችግር አይድረስብህ፣ አያጋጥምህ ብለው ሲመኙ ነው" ይላሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ሁለተኛው፣ እራት ያለ መብራት መብላት የሚለው አገላለጽ ምስጢር ያለበት ነው። በጨለማ ሲበሉ ምን እንደሚበሉ ከማን ጋር እንደሚበሉ አይታወቅም። የጨለማ መብል ከሰይጣን ጋር አብሮ ሞሶብ መሥራት ነው ይላሉ (ወ/ሮ የውብዳር ጌታሁን፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እራት እየተበላ እያለ መብራት ከጠፋ፣ ሊነርሱ ያነሱትን ያስቀምጣሉ። ሞሰቡን ከድነው ኩራዝ ሊለኩሱ ይሮጣሉ (ወ/ሮ የውብዳር፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በመሆኑም፣ ብርሃን እያለቀ መሸትሸት ሲል የተከፈተን ነገር መክዳደን፣ በርን መዝጋትና ማጥበቅ፣ ከውጭ ያለን ዕቃ ሁሉ ለቃቅሞ ማስገባት መጠንቀቅና መጠናቀቅ ይበዛል (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የእንጀራ ሞሰብ፣ የዱቄት ሽጉሾችን፣ የሊጥ በሃቃና ሌሎችም ለዕለትም ሆነ ለረጅም ጊዜ አዘጋጅቶ የሚጠቀምባቸውን ሁሉንም ምግቦችና የምግብ ማስቀመጫዎች የአካባቢ ሰው ይከዳድናል ። በሩን ያጠባብቃል፣ መስኮቱንም ይቆላልፋል። ሰዓት ዕላፊ ሞሰብ አይከፈትም። ሌሊት ቢርብ ማዕድ አይቀርብም።

ያለ ሰዓት ውሃ ቢጠማ አይጠጣም። ክፍቱን ያደረ ነገር የተጋለጠ ነውና ክፉ መንፈስ እንዳይለክፈው ይገጥመታል በማለት ወ/ሮ የውብዳር ያስረዳሉ።

ከመዘጋጋቱ ጎን ለጎን፣ በምሽት ወደ ውስጥ የሚገባ እንጅ የሚወጣ ነገር አይኖርም። የገባ አይወጣም፤ የመጣ ነገርም አይመለስም። ጎረቤታሞችም ሆነ ዘመዳሞች ከመሸ በኋላ ዕቃ አይዋዋሱም። እሳት አይጫጫሩም፤ ጨው ቢጎድል፣ ዘይት ቢያንስ እንጀራ ቢታጣ አበድሩን ብለው አይጠይቁም (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። የማታ ማሳረጊያ ጸሎት፣ "የማታ እንጀራ አታሳጣኝ" ነው ይላሉ። ከዚህ የምንገነዘበው፣ ከቀኑ ይልቅ ይህ ሰዓት ተፈሪ መሆኑን ነው።

አለቃ ደበበ (2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ በገጠር የሌላ ሰው ንብረት የሆኑ ከብቶች ተቀላቅለው ከሰው በረት ገብተው ቢገኙ አስወጧቸው አይባልም። ለከብቶቹ ባለቤት፣ "ከብቶችህ ከእኛ ከብቶች ጋር ናቸው እንዳታስብ ብለን መልዕክተኛ እንልካለን" ይላሉ (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከብቱ የባላጋራቸው ቢሆን እንኳ ሰረቀ ብሎ ያሳስረኛል፤ እኔን ሊጎዳ ሆን ብሎ ሰወረብኝ ብሎ ይከሰኛል የሚል ሥጋት አይገባንም ይላሉ። ባላጋራው ቢሰማም ልውሰድ ብሎ አይመጣም፤ ቢሞክር እንኳ እንግዳው ከብት የመጣባቸው ሰዎች ፈተው ለመስጠት አይፈቅዱም"። እንደዚህ አይነት ግጭት የተለመደ ባይሆንም ድንገት ተፈጥሮ ሽማግሌ ፊት ቢቀርብ፣ ጥፋተኛ ተደርጎ የሚወቀሰውና በጥብቅ የሚወገዘው የከብቱ ባለቤት ነው(አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በንግድ ሱቆች አካባቢ ምሽት ጥሩ የመገበያያ ጊዜ ተደርጎ አይታሰብም። አብዛኛው ነጋዴ አሥራ ሁለት ሰዓት ካለፈ ሱቁን ይዘጋል። አቶ ይልቃል፣ "ከመሸ በኋላ ዕቃ የሚገዛ ሰው ቢመጣ፣ የተሸጠውን ዕቃ ለገዥው አውጥተን አንሰጥም፤ እዚህ ይደርልህ ብለን እናግባባው አለን ይላሉ (2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።ልውሰድ ብሎ ገዥው ቢከራከር "ወሳጅ" ነው ብለው ይጠረጥሩታል። ነጋዴው ንብረቱን ለመሸጥ ቢስማማ፤ ገንዘቡን ተቀብሎ፣ ዕቃውን አስሮ፣ ለይቶ አስቀምጦ ጠዋት መጥቶ እንዲወስደው ያግባባዋል እንጅ አውጥቶ አይሰጠውም

ይላሉ፡፡ በጨለማ ገንዘብ ዘርዝሩልኝ ብሎ የሚጠይቅን ሰው በበጎ አናየውም ይላሉ፡፡

በጎዛምን አካባቢ ቤት ከመሸ በኋላ አይጠረግም፡፡ "ቢጠረግ እንኳ ቆሻሻው ከቤት ሳይወጣ ከበር አካባቢ አስቀምጣው ሲነጋ ያፈሱታል (ወ/ሮ አካልነሽ ታምሩ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ አውጥታችሁ ብትጥሉት ሃብታችሁ ይጠረጋል ስለሚባል እንፈራለን ይላሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ መልካም ሽታ ያላቸው ነገሮች ርኩስ መንፈስን ይስባሉ ተብሎ ስለሚታመን በማታ አይጨሱም፡፡ ዋሽንት አይነፋም፣ በገና አይደረደርም፣ ክራር አይገዘገዝም፡፡ ድምጽ አውጥቶ ማንጎራጎና ማፏጨት ነውር ነው፡፡ ሰዓት እላፊ ሁካታና ድንፋታ አይኖርም፡፡ ፀጥታና እርጋታ፣ አካባቢን ማዳመጥ፣ ማንቃቃት፣ መሳሪያን አዘጋጅቶ ማድፈጥ፣ ተኝቶ ሃጂ መጭውን መለየት ነው ይላሉ (ወ/ሮ አካልነሽ ታምሩ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ ሴቶችም ጸጉራቸውን ፈትተው፤ አይኳኳሉም፤ አይቀባቡም፡፡ ስትኳኳል፣ የታየች እንደሆነ፣"ያ መናጢ ይተናኮልሻል" እንላለን በማለት የጊዜውን ተፈሪነት ይገልጹታል፡፡

ወ/ሮ ቦሰና ፍካሬ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) እሳት ማታ አይጫርም ይላሉ፡፡ አብሽሎ እየተጋገረ ቁርጥ ዘመድ እንኳ መጥቶ ቢጠይቅ እሽ አይሉም፡፡ በርግጥ አብሽሎ እየጋገሩ መሆኑ እየታወቀ ደፍሮ የሚጠይቅ ሰው አይኖሩም፡፡ ነገርግን፣ ልማዱን ንቀው ቢሰጡ በአካባቢ ያለው ሰው፣ "እንግዳ ይጠራባችኋል" ይላል (ወ/ሮ ቦሰና ፍካሬ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ ሰው እሳት ሲጠይቅ አብሽሎ ነው ይላሉ፡፡ አረቂ ሲወጣ ደግሞ አይደለም እሳት የሰው ጥላ አይወድም ይባላል፤ ስለዚህ፣ ሰው ሲመጣ ጥላ እንዳትጥይብኝ ስንል መለሰ ይላሉ፡፡ አረቄው ሲጣድ ያልነበሩ ሰዎች አይገቡም፡፡ በጥላ ያደሩና የወር አበባ ያዩ ሴቶች ወደ አካባቢው ዘወር አይሉም፡፡ በአጠቃላይ ግን ከመሸ እሳት አይጫርም ብለውኛል (ወ/ሮ ቦሰና ፍካሬ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡

ቀን፣ በነፋስ ዕድሜው በጠዋት ሲወለድ የውሃ ያህል ይቀዘቅዛል(ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)፡፡ ቀስ እያለ

የመሩቱ ስሜት እየተሰማው ሄዶ ከረፋድ ዕድሜው ላይ ሲደርስ ለብ እያለ፣ እየበሰለና እየጋለ ይሄድና፣ ቀትር ላይ ሲደርስ ያቃጥላል ይሉታል ። በዚህ ሰዓት እሳት በቦታው ይተካል። እሳት እየጋለ ሄዶ እየደከመ፣ እየበረደ ይመጣና ሲደክምና ሲቀዘቅዝ ውሃው መጋረፍ ስለሚጀምር የውሃ ዘመን ይባላል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። የውሃው ሰዓት እየበረደ፣ እየፈዘዘ ሄዶ ሲጨልም የመሬት ሰዓት ይሆናል ይላሉ።

በዚህ ጊዜ ሁሉም ነገር እንደነፋስ መብረሩን፣ ከፍ ከፍ ማለቱን አቁሞ ይሰክናል። ጠዋት የወጣችው ፀሐይ ተወልዳ እየደመቀች እና እየፈካች ሄዳ፣ አቅም አጥታ አጨልሟላ ስትጠልቅና ብርሃኗ ሲከስም ቀን ብሩህነቷንና መፋጀቷን አቁሞ፣ እየቀዘቀዘችና እየፈዘዘች ሄዶ ማታ ላይ ፀጥ ስትል፣ ቀን ሞተ ይባላል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ይህ ጊዜ የመሬት ባሕርይ የሚሰለጥንበት ወቅት እንደመሆኑ፣ የመሬት ውክልናም የሥጋና የገላ አምሳል ነው። እርጋታው፣ ስክነቱና ፀጥታው የፍጥረቶች መሬታዊ ባሕርይው የሞት ምሳሌ ይሆናል (አቶ ተዘራ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አርብ

ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ፍጥረት የተጀመረው በእሁድ ነው ይላሉ። በእሁድ ተጀመሮ የተጠናቀቀው በአርብ እንደሆነ ቅዱስ መጻሕፍትን ምንጭ ጠቅሰው ያስረዳሉ። ስለዚህ፣ ፍጥረት የተባረከባት ቀን ሰንበት፣ ቅዱስ ቀን ተብላ በቀኖች ላይ ሁሉ ልቅና ልታገኝ ችላለች ይላሉ። ፍጥረት የተጀመረበቱ እሁድ ቅዱስ ከሆነ፣ ፍጥረት ሁሉ ተፈጥሮ ያለቀበቱ ቀን አርብ ደግሞ አልቆበታልና ባዶ ነች ይላሉ። ስለዚህ፣ የቀኖች ሁሉ ንጉስ ሰንበት ይሆናል። ቅዳሜ ደግሞ ፈጣሪ ሰርቶ ሰርቶ ያረፈባትና በአደረገው ነገር ሁሉ የተደሰተባት የማረፊያው ቀን ነች።

በመሆኑም፣ አርብ ፍጥረት የተጠናቀቀበት ቀን በመሆኑ የቀኖች ማለቂያ ያደርጋታል። ይሽንን እያሰቡ አንድ ነገር በመጨረሻው ደረጃ ላይ መሆኑን የሚገልጹት፣ "አንድ ሀሙስ የቀረው" በማለት ነው። በመሆኑም የአካባው ሰው

ADDIS ABABA UNIVERSITY

በአርብ የሚደላ ነገር አያደረግም። ቀኑ ያምና ዐሎት እንዲሁም ስግደት የሚዘወተርበት በዚህ የተነሳ ነው። ዲያቆን ብርሃኑ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቀኑ ሁለ የሞተው በዚችው ዕለት ነው ይላለ። መሪጌታ አይነኩለም (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)፣ ለእርቅም ሆነ ለጋብቻ ይች ቀን ስለማትመረጥ ሽማግሌ አይላክባትም። የቤት መሰረቱ ሲጣልም ይህ ቀን አይሆንም ይላለ። ሰው በአርብ ከቤቱ ወጥቶ ጉዞ አይጀመርም በማለት የቀኗን ጎደሎነት ያስረዳሉ (መሪጌታ አይነኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ) ።

በአካባቢው ሁሉም ቦታዎችና ሰዓቶች ሰታቴና ቀጥ ብለው የተዘረጉና የሚነጉዱ ተደርገው አይታሰቡም። ገደብ የተቀመጠባቸው፣ ምልክት የተደረገባቸው ብዙ ማረፊያ ቦታዎች አለ። በእንቅስቃሴ ላይ አካሄድን የሚያስቀይሩ፣ ስሜትን የሚቀሰቅሱ፣ አንዱ ከሌላው በዐይነቱ ልዩ ሆኖ እንዲሰማን የሚያደርጉ ምልክቶች ያረፉባቸው ናቸው። ከአንዱ ሰዓት ወደ ሌላኛው ሰዓት፣ ከአንዱ ቀን ወደሌላኛው ቀን በምንሻገርበት ጊዜ በአካሄድ፣ በአነጋገርና በአለባበስ ላይ ሁሉ ለውጦች አለ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። እነዚህ ምልክቶች፣ "በቦታዎቹ መካከል የመቆራረጥ፣ የመከፋፈልና የመለያየት ስሜት እንዲሰማን የሚያደርጉ ናቸው" (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ መቆራረጦች አንድን መንገድ ብቻ ተከትለን እንዳንሄድ፣ ቆም ብለን እንድናስብ እንዳንዘናጋና እንዳንረሳ ሁሉ ያስታውሳሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ የሰው ልጅ እንዲሰራ፣ ማንኛውንም የሥጋ ነገር ሁሉ እንዲያከናውን የተሰጠው ጊዜ አለው ይላለ። ለግሉ የሆነ ነገር ሲሰራ ሲለፋ ሲደክም ይቆይና የተወሰኑ ሰዓቶችና ቦታዎች ላይ ሲደርስ ጥንቃቄ፣ ርጋታ፣ ስክነት ያደርጋል። በእነዚህ ክልክል ቀናት የሚሰሩት አብዛኞቹ ተግባሮች ደንብ የሚገለጽባቸው፣ ምግባር የሚሰበክባቸው፣ ማህበራዊ ትስስር ማጠናከሪያ የሚሆኑ ሥራዎች የሚከናወንባቸው ዕለቶች ናቸው። አቶ ይዘንጋው (2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)፣ ስንሮጥና ስንባክን ለግል ጥቅምና ለሥጋ አምሮት ስንሰራ እንቆይና በሰንበት በሽተኛ እንጠይቃለን፣

የታመመን እንንበኛለን፣ የሃይማኖት ትምህርት እንማራለን ይላሉ። ይህንን የተቀደሰና መልካም የሆነ ሥራ ከተለመደውና ከተራው አኗኗር አውጥቶ ወደ ተቀደሰ ነገር የሚያስገባን ዓለማዊነትንና መንፈሳዊነትን አመጣጥነን እንድንመራ የሚያደርገን ነው። በሥጋ ስራ የረከሰው ሥጋ በየጊዜው እየተስተካከለ ካልሄደ ለክፉ ዐይን ማደሪያ ስለሚያደርግ ማስተካከሉ ሰብዕናን ለማረቅ ይጠቅማል።

መሪጌታ ዲበኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ በተለመደውና በዚህ በተራው ህይወት ውስጥ በሰዓቶች፣ በቀኖች መካከል መበላለጥ የለም ይላሉ። ያለው ሩጫ፣ ጥድፊያ ነው በማለት ይናገራሉ። ቦታዎችና ጊዜዎች ልቅ ከተተው የሰው ልጅ ለህይወቱ ማሰቢያ ጊዜ ያጣል። ሥጋዊ ፍላጎቱ እንደመራው መንጎድ፣ ልብ እንደፈቀደ መስራት፣ ሥጋ የፈለገውን ማድረግ ይበዛል ይላሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ለግል ፍላጎት ሲሮጡ ደግሞ ነፍሱን ይጨቁናል። እንድንደነግጥና እንድንጠነቀቅ የሚያደርገን ከፉጫ የሚገታን ነገር በአካባቢው አያጋጥመንም። በመሃከል ሰንበት ሲመጣ ቆም ይባላል።

የአካባቢው ሰው ቅዳሜን ለመገበያያ እሁድን ደግሞ ማህበራዊ ስራዎችን ለማከናወን ይመድባል። በመሆኑም፣ ዓርብ ሲደርስ የሰንበት ውሃ ይቀዳል፤ የሰንበት ቡና ይቆላል። በመረዳጃ ማህበራት እየተሰባሰበ የሞተን ይቀብራል። የተቸገረን ይጠይቃል። በዕቁብና በሌሎቹ አደረጃጀቶች እየተቧደነ አንድነቱን ያጠናክራል፤ ይተዋወቁባቸዋል። ሰንበት የታመመን መጠየቂያ ቀን ነው። በሞት የተጎዳን ቤተሰብ መድረሻ ነው(መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እሁድ የቀኖች ልደት በመሆኑ በምግባር ሥራ ይከብራል።

ስለዚህ፣ ይህ የመለያ ቅጽር በሁለቱ ዓለማት መካከል ያለውን ድንበር ለይቶ የሚያሳይ ነው። የእነዚህ መገለጫዎች መኖር የሰው ልጆች በዕለት ተዕለት ህይወቱ እንቅስቃሴውና አኳኋኑ ምን መምሰል እንዳለበት እንዲያገናዝብ፣ በየትኛው የምግባር ኮድ መመራትና መገዛት እንደሚገባው እንዲያስብና እንዲረዳ ይማርበታል። ሰዎች በየጊዜው በሚፈጽሙት ወይም በሚያከናውኑት ተግባር ውስጥ ማድረግ ስለሚገቧቸውና ስለማይገቧቸው ነገሮች አውቀውና ተጠንቅቀው እንዲንቀሳቀሱ የሚያነቁ ማህበራዊነትን ማግኛ መንገዶች ናቸው።

ማህበረሰቡ በእነዚህ ተጨባጭ ቅርጾች አማካይነት ደንብን ይማራል። ዓውደ ቅጽሮቹ ሲዘለቅ አንዱን ዑድን ንቆ ከሌላው ጋር መወገኑን ያሳውቅበታል። እነዚህ ቅጽሮቹ በልዩ ልዩ መልኮች የሚገለጹ ናቸው። በእነዚህ ቀናት ማህበራዊ ሕግን ስለማክበር፣ ስረዓትን ስለመማር፣ መተጋገዝንና መረዳዳትን ስለማክበር ይማርበታል። እነዚህን ቀናት ሲጥስና ከማክበር ሲያፈነግጥ ረከሰ ተላልፎ ሲገኝ ከክፉ ሥራ ጋር ተዋወቀ ይባላል። ለክፉ ሥራ የመጋለጥ ዕድላቸው በሰፋ ቁጥር በክፉ ዐይን የመጠቃት አጋጣሚውን ስለሚያሰፋ በሰንበት ላይ ክልከላው ሰፊ ነው።

ክረምት

የጎዛምን ሰዎች፣ "ሸሸትህ በክረምትና በጨለማ አይሁን" ይባባላሉ (ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ወቅቱ የተጠላው ለመንቀሳቀስና ለመጓጓዝ እንደልብ የማይመች በመሆኑ ነው። በክረምት ጭቃውና ረግረጉ እንደልብ አያራምድም። የወንዙ መላት መስኩን ስለሚያጥለቀልቀው ከቤት አያስወጣም። የጨለማ መንገድም እንደዚያው አሻሚና አደናጋሪ፣ ግልጽ ያልሆነና የሚያስፈራ አስጠቂ ነው ይሉታል። ክረምትን በሞት ስለሚመስሉት ጋብቻ አይፈጸምበትም ይላሉ። ዘመድ ለመጠየቅ፣ በዓላትን ለመክበር፣ የሞቱን ለመቅበር ያስቸግራል (አቶ ይዘንጋው መኮንን፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ) ።

መሪጌታ ዲበኩሉ፣ ዓመት በነፋሻው መስከረም አብቶ ባጅቶ የሚሞተው በመዓቱ ነሐሴ ነው ይላሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ የአዲስ ዓመት ሥር፣ እንቁጣጣሽም ወይም የዘመን መለወጫ (መስከረም አንድ ቀን) ወይም ቅዱስ ዮሐንስ የበዓል ኹሉ ራስ፣ አንደኛ መኾመሪያ በዓል ይሆናል። የእንቁጣጣሽ ምስጢር፣ "ወላድና ክረምት ሲጣሉት ያከብር" እንዲሉ ምድር ጭቃ ከኾነች በኋላ ብዙ ዐይነት ቡቃያና ተክል ማስገኘቷን ያሳያል በማለት ይገልጻሉ። ከዚያም እህሉ እያዘረዘረ፣ እያፈራ ሄዶ በፀሐይ ዘመን እየቀላና እየበሰለ ይመጣል። ምድር ጸጉሯን ተላጭታ ያለልብስ ርቃኗን ከነቆረኗ ተገምሳ ትቆያለች (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከዚያም፣ በክረምት ማዕቱ ወርዶ ምድርም ጨቅይታ ያንን የደረቀውንና የተራቆተውን አርሳና አበስብሳ፣

አጥባና አለቅልቃ ስታነጻው በዚህ ጊዜ ዓመት ይሞትና ዘመን እንደገና ውልደቱን በአዲስ ዘመን መስከረም ላይ ያደርጋል ይላሉ (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ ፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)።

ክረምት በሐምሌ አቦ ተሸሞ በጥቅምት አቦ ስልጣኑ ይነሳል እየተባለ ይነገራል (አቶ ተዘራ አስማረ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በዚህ ጊዜ ሰውን የመብላት፣ ከብትን የመውሰድ ስልጣን ይሰጠዋል ይላሉ። እስከ ዘመን ንጋት ድረስ ባለው ጊዜ ወንዞች ከብረው ይቆዩና መስከረም ሲያብት መጉደልና መቀነስ ይጀምራሉ። ስልጣናቸው እየቀነሰ ሄዶ፣ የብርሃኑ ዘመን ሲያብት መስከረም ይገባል። ከዚህ በኋላ፣ "ባልና ሚስት አብሮ ይተኛል" ይባላል (አቶ ተዘራ አስማረ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የክረምት እሳቤ ግን እንደ ጨለማ ነው ይላሉ መሪጌታ አይነኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)።

በመሆኑም፣ በክረምት የሞተ ሰው ዕድለኛ አይደለም፣ የተረገመ ነው እየተባለ ይታዘንለታል። መሬቱ ያረገርጋል፣ መቃብሩ ሲቆፈር ይመነጫል። ገጠር አካባቢ ወንዝ አቋርጠው መሄድ ስላለ ወገን አይቀብረውም። መታሰቢያ ዝክሮች ሁሉ ስለሚሻገሩ በቀኑ አይታወስም። ሠርግም ሆነ የንግስ በዓላትም የሉም ይላሉ መርጌታ አይነኩሉ።

የክረምት ወቅት የዓመቱ መጨረሻ እንደመሆኑ ሁሉም ነገር እየቀነሰና እየሳሳ የሚሄድበት ጊዜ ነው ብለው ይናገራሉ (አቶ ዘውዴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። ይህ ወቅት የዘር በመሆኑ፣ የሚበላና የሚቀመስ ነገር አይገኝበትም። በዚህ ወቅት የተዘራ እህል የሚደርሰው በበጋ ነው። የክረምት ወቅት አዝርዕቱ ሁሉ የሚተከሉበት እንጅ የሚያፈሩበት ባለመሆኑ

ሰኔን በዘራዘር፣

ሐምሌን በንመንዘር፣

ነሐሴን በምን ባላ ይሻገሩታላ (አቶ ዘውዴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ) እየተባለ ያንጎራጉራሉ ይላሉ። ወቅቱን "የጎተራ ጸጋና በረከት ይሸሸዋል፣ ርሃብንና ችጋርን የሚያመጡ በርካታ ውስብስብ ጸባይ ያላቸው

ነገሮች ይታዩለ" (አቶ ዘውዴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። በዚህ ወቅት ተዘርተው የሚደርሱት ጎመንና ድንች ናቸው። ሁለቱም ተክሎች በክረምት ስለሚበቅሉ፣ ፀሎተ በረድ[32] ደጋሚ ሰው አይበላቸውም። ሃብት ሲመጣ ይደፍናሉ፣ ይከለክላሉ እያለ ከወቅቱ ጋር እያያዙ ያናንቁ ይፈሯቸዋል(መሪጌታ ይሄይስ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ማጠጥና ማለቅ የወቅቱ ሁነኛ መገለጫዎቹ በመሆናቸው፣ በወሮቹ ችጋርና አጸባ ይበዛል። ወንዞቹ ስለሚሞሉና ዝናቡም ስለሚጠነክር የሰዎች እንቅስቃሴና ግንኙነት ይገደባል። እንደ ልብ ወጥቶ ለመግባት ስለሚያስቸግር ማህበራዊ ግንኙነት ደካማ ነው። ሁሉም በየቤቱ ሆኖ በአቅሙ ቤት ያፈራውን ይበላል። በበጋው ያመረተውን ከጎተራው እያወጣ ይመገባል። ከነአበባለ፣

አገመገመ ሰኔና ግንቦት፣

ያለው ሊበላ የሌለው ሊሞት፣

እንግዲህ ጀመረ ሰኔ አቆለቆለ፣

በግማሽ እንጀራ ጎመን ተቆለለ ይባላል (እማሆይ ማናዬሽ ፍካሬ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27 የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ።

በዚህ ወቅት የማህበራዊ አገልግሎቶች አፈጻጸም ደካማ ነው። የጋብቻ፣ የጽዋ ማህበራት፣ የሰንበቴና ሌሎቹም ድግሶች በብዛት አይወጡም። የታመመ ለመጠየቅ፣ የሞተን ለመቅበር፣ የናፈቀን ለማየት ያስቸግራል። የውሃውን መላት ፍራቻ ከብቶች የሚውሉት ከመንደር ነው። መስኩ በውሃ ስለሚሸፈን ለከብቶች ቀለብ ይቸግራል። ሰው የወደደውን አያይም፣ የታመመን አይጠይቅም፣ የናፈቀውን አይጎበኝም። ያለው ይነፍጋል። ቀን የሚያወጣ ዘመድ ከሌለው ወቅቱ ከባድ ነው ይላሉ። የሌለው ባለው ላይ ክፉ ያስባል። ቀምቶና ዘርፎ ወቅቱን ሊያልፈው የሚሞክረው ሰው ብዙ ነው ይባላል። በመሆኑም፣ ከወሮቹ ሁሉ ይህን ወቅት ሌባ

---

[32] አዝመራው በቅሎ ፍሬ በሚይዝ ወቅት በረዶ ወርዶ የደረሰውን እህል እንዳይመታው ደብተራዎች ዕፅ ደግመው ጠንካራ ለሆነ አንድ የአካባቢ ሰው መርጠው ይሰጡታል። ይህ ሰው ዕፁ እንዳይረክስ ከምግብና ከአንዳንድ ግንኙነቶች ይታቀባል።

ይወደዋል ይላሉ፡፡ ቀማኛው ይበረታል እየተባለ ይነገራል፡፡ የሚበላው ያጣ አውሬ ደጅ ለደጅ ይልከሰከሳል፡፡ አቅም ሲደክም አይቶ የሚመጣው ብዙ ስለሆነ፣ ወንጀለኞች የሚበዙበት፣ ብቀላዎች የሚበራከቱበት ወቅት በመሆኑ ክፉ ዐይንም በዚህ ዘመን ይበረታል ይላሉ፡፡

ሐምሌ ድንጋይ ይዟል፣

ነሐሴም ጦር ይዟል፣

መስከረምም ካራ፣

ሰው ሊገሉላችሁ፣

አትገላግሉም ወይ ያላችሁ ያላችሁ፡፡ ይባላል (እማሆይ ማናዬሽ ፍካሬ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27 የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ፡፡

አዲሱ ዓመት በተራው ሁሉም ነገር የሚታደስበት ነው፡፡ በወቅቱ፣ አዝርዕቶችና ሰብሎች ፍሬ በመያዝ ይለመልሙበታል፡፡ የተዘራው ዘርገሮ፣ የዘረዘረው አብቦ፣ አዳዲስ ተክሎች ብቅ ብቅ ማለት ይጀምሩበታል፡፡ አሮጌው በአዲስ ሰብል ይተካል፡፡ ሜዳውና ጋራው በልምላሜ ያጌጣል፤ ታስረው የከረሙ እምቦሶች ተፈተው ስለሚለቀቁ ይቦርቃሉ፤ የከብቶች አካል በለመለመው ሳር መሙላትና መጠገን ይጀምራል፤ ተግድቦ የነበረው የሰዎች ግንኙነት ይመለሳል፡፡ በመሆኑም፤ በወቅቱ ጤና፣ ደስታ፣ ብልጽግናና ሀብት ሁሉ በአዲስ ይሞላል፡፡ ያ፣ አሰፈሪና አስቸጋሪ ወቅት እንደጦር ተፈርቶ ያልፋል፡፡

መስቀል ጠባ ዛሬ፣

በሸዋ በትግሬ

እኔም ወጣሁት በጎመን ብዛት

በሚስቴ ብርታት

በልጅቼ ጉልበት

ባንድ ላም ወተት ይባላል።

ጎመኗን የሚበሏት በቅቤ በመሆኑ "ባንድ ላም ወተት" የሚለው ጥቆማ የመጣ ለዚያ ነው ይላሉ። ከመስቀል በኋላ በቆሎውም ሊላውም ነገር ስለሚደርስ ተስፋ ይነሰራራል። የጎዛምን ሰው የዚያን የችግር ጊዜ ማለፍ አይቶ። ይህ ባህርያቸው ለዘሩና ለትውልዱ መጨመርና መንሰራፋት ጥሩ ምልኪያ ስለሚሆኑ እንዲመረጡ ያደርጋቸዋል። ክብርንና ባለፀግነትን ለማስገኘት ለመፍትሄነት በሚዘጋጁ አደራረጎች ውስጥ በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉ ዕፆች ተመራጭ ይሆናሉ። በሃብት ለማደግ፣ ለመበልጸግ፣ ለመላቅና ለመብለጥ በሚል ለሚደረጉ ማናቸውም ሥራዎች እነዚህን ዕፆች ይፈለጋሉ። ይህ ጠባያቸው ለተለያዩ አገልግሎቶች ስለሚያስመርጣቸው የአካባቢው ሰው ከጓሮው አያጠፋቸውም። በማሳው ውስጥ ይዘራቸዋል።

6.3. የሰብሎችና የተክሎች አከሳሰም

እንደሰዎች ሁሉ ተክሎችም የሚዘሩበት፣ የሚበቅሉበት፣ የሚያብቡበት፣ የሚያፈሩበትና የሚረግፉበት ጊዜ አላቸው። ከተክሎች የዕድገት ዘመን አጋላጭ ነው ተብሎ የሚታመን ክፍል አለ። ከተክሎች መካከል የማይነቅዙና የማይበሰብሱ እንዳሉ ሁሉ፣ ጠንካራ ያልሆኑ በቀላሉ የሚበሰብሱና የሚነቅዙ አሉ። በተክሎች የክፉ ዐይን መጋለጥ ወይም መከላከል ላይ መሰረቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ፣ ተቋቋሚነት፣ ተካፋይነትና የመሳሰሉ ጠባዮች ላይ ይሆናል። የተክሎች የአጋላጭነት ሁኔታ በሚከተለው ክፍል ተገልጿል።

የእህል አደካከም

በጎዛምን እህል ተዘርቶ፣ በቅሎ፣ አፍርቶ፣ ታጭዶ ሲወድቅ ወይም ሲታጨዱ "መጉ እህል" እንዲሁም፣ ተፈጭቶ፣ ተቦክቶና ተጋግሮ ተበልቶ በእዳሪ መልክ ሲወጣ "ሰገራ" ብለው ወዳቂውን ክፍል ይጠሩታል (አቶ ይዘንጋው፣2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። ሞት በእህል ውስጥ የሚታሰበው፣ "ጥሬነት በሌለው፣ ተዘርቶ በማይበቅል፣ ተፈጭቶ በሚቦካ፣ ተጋግሮ በሚበላ፣ በሞሰብ ላይ በቀረበ በማይተካ ነገር ነው (እማሆይ ማናየሽ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ

ቃለመጠይቅ)። ለመብል የተዘጋጀን ወይም በስሎ መብል ይሆን ዘንድ የቀረበው እህል፣ ለማፍራትና ለመተካት አስተዋጽኦ ስለሌለው 'የሞተ እህል' እንለዋለን ይላሉ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከቀብር መልስ፣ "እንደ ሰውዬው የሞተ እህል አለና ሳትቀምሱ እንዳትሄዱ" የሚለው አነጋገር ይሸንኑ የሚያስረዳ ነው (ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

እህል በፍሬው ለዘር ካልሆነ መጨረሻው ለእሳት ሲሳይ መሆን ነው። እሳት ከነካው ወይም አንዴ ከተጋገረ በኋላ ከመበላት ውጭ ለሌላ አማራጭ ስለማይውል የሞተ ብለው ይጠሩታል። የሞተ እህል መባሉም የበሰለ ስለሆነ ነው።

በአካባቢው እህል "በቁመ እንጅ ከሞተ አይጠበቅም" የሚል አባባል አለ (አቶ ተዘራ አስማረ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እህል በቁመ የሚጠበቀው ማሳ ላይ እያለ ነው። ማሳ ላይ አዕዋፋት እንዳይጠረጥሩት፣ እንስሳት እንዳይበሉት፣ ዝንጀሮና ጦጣ እንዳይፈለፍሉት፣ ጃርት እንዳታፈልሰው ነው። እህል ሞተ የሚባለው በራሱ ቆሞ ራሱን መርዳት ሲያቆም ወይም ደርቆ ሲታጨድ ነው። "በቡቃያ የተወለደ ሰብል ሞቱ በአጨዳው ነው" ይላሉ። ፍሬ በዘር ካልቀጠለ፣ እንደ "መካን" ሁሉ ሳይተካ ቀርቶ ከተቀቀለ፣ ከተፈጨና ከተጋገረ ግን እሱም ሙት ነው በማለት ይገልጹታል። ይህ ከሆነ በኋላ ያ ምግብ፣ ሊቀመጥ፣ ሊቆጠብ፣ እድሮና ውሎ ሊበላ ስለማይችል፣ ለዘር አይሆንም ይሉታል (ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ደረቅ፣ ጠፍ፣ ጥሬነት የሌለው (ማለትም ለፍሬ የማይሆንና ተዘርቶ የማይበቅል) ፣ ተፈጭቶ ተበክቶ፣ ተጋግሮ፣ በሞሰብ ያለ ወይም እገበታ ላይ የቀረበ እንጀራ ሁሉ ምሳሌነቱ የሞት ነው (ደስታ ተክለወልድ፣ 1975፣ 755) ። ምክንያቱም፣ ቢቆርሱት፣ ቢጠቀልሉት፣ ቢፈረፍሩት፣ ቢያኝኩት ቢያላምጡት ፍጹም ታዛዥ በመሆኑ ነው ይላሉ። ከአንዳንድ ሰው ቤት ሄደው ምግብ ሲከለክሏቸው "የሞተ እንጀራ ነሳችኝ" ይላሉ (ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እንጀራ የሞተ የተባለው ሌላ እንጀራን መተካት ስለማይችልና ለሌላ እንጀራ መገኘት አስተዋጽኦ ስለማይኖረው ነው። በውስጡ ምንም አቅምና ጉልበት የለም።

የሚያፈራውና የሚተካው ከቤት ሲወጣ ምልኪያውን ይፈራሉ እንጅ ከማይተካው ፍቅር የላቸውም።

ለምሳሌ፡- ማንኛውም የእህል ዘር ከተፈጨ በኋላ ለዘር አይሆንም። መብል ይሆን ዘንድ በስሎ የቀረበ ምግብ ከመበላት ውጭ ለሌላ አማራጭ ስለማይሆን የመከነ ነው ይሉታል። የበሰለ በመሆኑ ለመላመጥ ታዛኝ ነው። ቢቆርሱት ይታዘዛል፣ ቢቆረጥሙት ይደቃል፣ ቢያኝኩት ይፈጫል።ኃይልና ጉልበቱ በእሳት ስለደከመ የዝንብ ማረፊያ፣ የሁሉ ነገር መራቢያ በመሆኑ ሙት ነው (አቶ ተዘራ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ ለመመረዝ የተጋለጠና እንደ አስከሬን ሁሉ አደጋ አምጭ ተሸናፊ ክስተት ነው።

በአካባቢው ባቄላ ተነክሮ ከመሃከል ሳትበቅል የቀረችውን 'ጻድቃን' ብለው ይጠሯታል (ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከዚህ በመነሳት፣ "ከባቄላ ቅርጣን የሚያወጣ አምላክ" እያሉ ያመሰግናሉ። የጻድቅ ትርጉሙ፣ የሚጸድቅ፣ ሥር እየሰደደ የሚለማ የሚለመልም፣ የሚያቆጠቁጥ፣ ቅጠል የሚያወጣ፣ ከመድረቅ የራቀ፤ ደግ፣ ቅን፣ ገር፣ እውነተኛ የሆነ ሰው በምግባሩ የቀና በህይማኖቱ የጸና ማለት ነው (ኪዳነወልድ ክፍሌ 1948)። ከብዙ ሃጢያን መካከል አንድ መልካም ሰው ሲገኝ፣ ማህበረሰቡን ከመከራና ከጉድ የሚያወጣ፤ በምግባሩ የጠነከረ ማህበራዊ ልማዱን የጠበቀ ጠንካራ በዓላማ የጸና ሰው ሲኖር በዚህ ይመስሉታል (ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ይቺ ፍሬ በመከራ ተፈትና የጸናችና የበሰለች ነች። ከባቄላዎች መካከል ተለይታ አልሞተችም። በመሆኑም፣ በቀላሉ ለሚሸነፉት፣ በፈተና ለሚወድቁት አምሳል አትሆንም። ይህ ተግባሩ በአንድ በኩል ሙት አያስብላትም። ተነክሮ የዘረዘረው ግን በችግርና በመከራ በቀላሉ ለሚጠቃውና ለሚወረረው፣ ለሚጋለጠውና ለሚሸነፈው እንዲሁም እጅ ለሚሰጠው ሁሉ አምሳል ይሆናል። በመሆኑም፣ ሙት ይሉታል። ይህ አካል ለፈተና የማይጸና ተሸናፊ የሆነ የሚያፈራ አካል ነው።

በመሆኑም፣ አጋላጭና አስጠቂ ነው። የደካማ፣ የተሸናፊና የምርኮኛ ምሳሌ አድርገው ይገለገሉበታል። እንደጣፈጡና እንዳማሩ፣ እንደከበሩና እንደጸኑ የሚቆዩት ግን

ህያዋን ናቸው። የማያበቅለው ወይም ታሪክ ያልሰራውን፣ ዕድሜውን በመብልና በጨዋታ የጨረሰው ህያው ፍሬ ስላልሆነ የሙት ምሳሌ ነው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)።

ማዕድ

በጎዛምን እንደ አስከሬን ሁሉ ለማዕድ ልዩ ክብርና ጥበቃ እንደሚደረግለት አቶ ዘውዴ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ) ይናገራሉ። ማዕድ ጥብቅ የምግባር ጥበቃዎች፣ ሥርዓትና ደንቦች ይተላለፉበታል፤ ስግብግብነትና ችኩልነት፣ ስስትና ራስ ወዳድነት ይነወሩበታል" (አቶ ዘውዴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። ተካፍሎና ተሳስቦ የመኖር ጥበብ በአውዱ ላይ እንዲፈጸም ይመከራል። በቤተሰብ አባላቱ መካከል መከባበርና መተጋገዝ፤ ትንሽ ለትልቁ፣ ልጅ ለአባትና ለእናቱ ዝቅ ብሎ የሚገባበት ቦታ ነው (አቶ ዘውዴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። ይህ ክብር በሞሰብ ስሪትና በመብል መቀዳደም የሚገለጽ ነው። ትልቅ ሲበላ ትንሽ ይጠብቃል። አባቶች ባንድ ሲሰሩ ልጆች ደግሞ ለብቻ ራሳቸውን ችለው ይቀርባሉ።

በማዕድ በአንድ በኩል ያማረና የሞላ በሌላ መልኩ ያነሰና ያጠጠ ነገር ይቀርብበታል" (አቶ ዘውዴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የራበውና የጠገበው እኩል ይሰራበታል። በመብሉ ሰዓት አሳላፊና ተሰሪ፣ ጠባቂና ቀዳሚ ሆኖ መቅረብ ስላለ ቀድሞ ቀማሽና ዘግይቶ ጎራሽ ይኖራል። በቦታው ክብርና ስርዓት ስለሚደረግበት፣ ሁሉም በእኩል ላይስተናገድ፣ ሁሉም በፍትሃዊነት ላይካፈል ይችላል ይላሉ አቶ ዘውዴ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)።

አቶ በቀለ (2006 ዓ/ም፣ ጥር 14፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) የአማረው ነገር ለሁሉም በእኩል የማይዳረሰው፣ በአመጋገቡ ጊዜ ዕድሜ፣ ማህበራዊ ክብርና ጸታ ልዩነት ስለሚደረግባቸው ነው። በዚህ ምክንያት፣ አብዝቶ ጠግቦ የሚበላና ቀምሶና አንሶት የሚቀር፤ ሲበሉ የሚሸተውና የሚጠብቅ፣ ጠግቦ የሚያገሳና ቁንጣን የሚይዘው ይኖራል በማለት አጋጣሚውን ይገልጻሉ። በዕደላው ሰዓት በዛ ተደርጎ የሚከመርለትና ሳሳ ተደርጎ ተቀንሶ የሚቀርብለት አካል አለ። ከዋናው የሚያገኝና

ከመናኛው የሚቀምስም አይጠፋም። (አቶ በቀለ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 14 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ ይላሉ አቶ በቀለ እነዚህ ልዩነቶች መግፋትና መቅረብ፣ መከበርና መናቅ የሚታይባቸው፣ ያለውና የሌለው በሚል ወገንተኝነት የሚገለጽባቸው ቦታዎች ናቸው ይላሉ። መጠቃቀምና መጠቃቀስ ይበዛበታል።

ሞሰብ ቀርቦ እስኪነሳ ድረስ ቀልድና ዋዛ አይነገርም፤ እንደሳቅና ዘፈን፣ ቀልድና ክርክር፣ ዘለፋና ትግል የመሳሰሉ ተግባሮች በዙሪያው አይከናወኑም (አቶ በቀለ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 14፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ፀያፍ የሆኑ የምግብ ፍላጎትን የሚዘጉና የሰውን ስሜት የሚረብሹ ነገሮች በዚህ አውድ ቦታ የላቸውም በማለት ይናገራሉ። "ክፉ ልማድ ያስርቃል ከማድ" ይባላል። በአጎራረስ፣ በአለማመጥ፣ በአዋዋጥ ዙሪያ የአመጣጠን ስርዓት አለ። የአቆራረስ ደንብና የጉርሻ አለካክ ደንብ እና ልማድ አለው።

ይህ ልዩነት ባለበት አውድ ውስጥ ቶሎ ቶሎ መብላት፣ በትልቁ መጉረስ አቅምና ጉልበት በሌለው ሙት እህል ውስጥ ክፉ መንፈስ ተስሎ ሊጎዳ ይችላል ይላሉ (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከአቆራረስ እስከ አጎራረስ ባለው ሁኔታ በሰዎች ዘንድ ግምትን ያሰጣል ተብሎ ይነገራል። ሞሰብ ቀርቦ ከራስ ፊት ያለውን ማንሳት ትቶ ከሰው ፊት የሚደርስ ድንበር ዘላይ የሞሰብ ተሻጋሪ ሲገኝ፣ አበላሉም ሥርዓት ሲያጣ አጎራረሱ አላምር ሲል ይተቻል። ሲጎርስ የሚያዝረከርክና መሰብሰብ የማይችል ሰው ሲያጋጥም ርቦት የሚበላን ሰው የምግብ ፍላጎት ስለሚያጠፋ "ወስፋቴን ዘጋው" በሚል በዐይን ያስመታል። በማዕዱ ላይ ምንም ሳያስቀሩ ሲበሉ አዋይዋን አስቆጣ ለስብሐት እንኳ ሳያስቀር እንዳለ ጎረሰው ተብሎ ያስገምታል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)

አመድ እና አተላ

መሪጌታ ዲበኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ተክሎችም እንደ ሰው ሁሉ በአበባቸው አዘርዝረው፣ ነፋስ ሲያስደንሳቸው ይቆይና እሳት እንዲያፈሩ ያደርጋቸዋል ይላሉ። ከዚያም እየደረቁ እየጠወለጉ ሄደው መጨረሻ ላይ ወደ ትቢያና አመድ ይቀየራሉ። ለምሳሌ፦ ጠላና ጠጅ በጥንስስ ደረጃቸው እየፈሉ፣

እርስ በርሱ እየተብላሉ ይቆዩና ሲበስሉ እንደልብ የሚጠጡበት፣ የሚጣፍጡበት ጊዜ ይሆናል (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እማሆይ ማናዬሽ፣ ይህ ብስለታቸው እየላላና እየለሰለሰ ሲሄድ፣ የውሃው እጅ በዝቶ ቅራሪ ይሆናል። ቅራሪው ሲያልቅ ዘቅጠ የሚቀረውና የማይጠቅመው አላቂ ክፍል የሚጠራው በቅደም ተከተል "አተላ" እና "አምበላ" ተብሎ ነው (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ ጠላና ጠጅ በነፋስ ዘመናቸው ተጠንስሰው፣ በአፍለኝነታቸው በስለው፣ በቅራሪነታቸው ለስልሰው ሞታቸውን በዝቃጩ፣ በአተላና በአንበላ ያደርጋሉ ማለት ነው። ክፉ ዐይንም አመደንና አተላን ማደሪያ የሚያደርጋቸው ባዶ ስለሆኑ ነው።

በዕፀዋት ህይወት ውስጥ አንድ ተክል ማበብና ማፍራት ሲያቆም ወይም በተባይ እየተቦረቦረና እየተበላ ሄዶ በርብሮ ሊወድቅ ሲል ሰዎች ይቆርጡና ማገዶ ያደርጉታል። የደካማ ተክል መጨረሻ አመድ መሆን ነው (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)። የማይነቅዝና ብል የማይበላው እንጨት ግን ተመርጦ ለቤት ምሰሶ፣ ለታቦት፣ ለእርሻ ዕቃ ይሆናል (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። መልካም ተክልን እሳት አይበላውም። "ከሰው መርጦ ለሸመት፣ ከእንጨት መርጦ ለታቦት" የሚባለውም ለዚያ ነው ይላሉ መርጌታ አይነኩሉ። ለማንኛውም ዕፅ ማርከሻውም ማንገሻውም የሚሆነው የቀንድ ካራ እና የወይራ አንካሴ ነው እየተባለ ይነገራል (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የወይራ ዛፍን የአካባቢው ሰው ቆርጦ ማገዶ አያደርገውም። ዛፉም ጠንካራ እንጨት ነው ይሉታል። አቅራሪታ ሲያቅራራ፣

ጎራው ብለህ ጠምደህ፣ ጀሎ ብለህ መልስ፣

ቂምና ወይራ እንጨት ቶሎ ማይበሰብስ ብሎ ነው (አቶ ተዘራ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ።

ወይራ ጠንካራ ተክል ነው። እንኳን በቂሞ ተቆርጦም አይበሰብስ። ሞቶና ወድቆ አይነቅዝም። ጠንካራ በመሆኑ ቤተክርስቲያን ሲሰራ ርብራብ የሚሆኑት ጥድና

ወይራ ናቸው። በመሆኑም፣ በእነዚህ ዛፎች የተሰሩ ነገሮች ለዘመናት ለልጅ ልጅ ልጅ ያልፋሉ። ነገር ግን፣ እንደ ቁልቋል ያሉ በጣም ቀላል ተክሎች የሙት ምሳሌዎች ናቸው (አቶ ዘመኑ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ቁልቋል የሚሆነው ለሬሳ ሳጥን ብቻ ነው ይላሉ መሪጌታ አይነኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)። እህል ተወቅቶ ሲያዘሩ ለማጣረቢያነትም ይጠቀሙበታል። ሙት ጠባቂ ያደረገው እንደ አመድ ሁሉ ምስጥ ስለማይወደው ነው ይላሉ እኚሁ መላኸ። ደረቅና ቀላል የሆነ በውስጡ ምንም ምግብ የሌለው ውሃ የማይገዝ መርዛማ ዛፍ ነው በማለት ይገልጹታል (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ቆሞም የሞተ ወድቆም የሞተ እያሉ በሬሳ ይመስሉታል።

በመሆኑም፣ ለአቅኝ ዛፎችና ለአባት ተክሎች ክብደትና ክብር ይሰጣል። ቀላሎችና አቅመ ቢሶች፣ ባዶዎችና ጠፎች ግን ተመርጠው ይጣላሉ። ከመክበድና ከመጠንከር የመራቅ የማነስ ምልክት ተደርጎ ይታሰባል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ዐመድ ለሚማገዱትና ፍሬ ለሌላቸው ለጠፎች አምሳል የሚደረገው በዚህ ስሌት ነው። ለመስዋይት የሚቃጠል አመድ ግን የተመረጠ ዛፍ በመሆኑ አክብረው ሰውነታቸውን ቀብተው ለፈውስ ያደርጉታል።

ይህ ደካማነቱ አስጠቂ ነገር ሆኖ ስለሚታሰብ አመድ በተደፋበት አካባቢ ክፉ መንፈስ አይርቅም እያሉ የአካባቢ ሰዎች ይመሰክራሉ (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እንዳያጋልጣቸው እየፈሩ አመድን የሚደፉት በጠዋት ተነስተው ነው። በሰንበትና በበዓላት ቀን አፍሰው በዕቃ ያስቀምጡታል እንጅ ከውጭ አይጥሉትም። ሰዓት ካለፈ በኋላም አመድን መድፋት ለአደጋ ያጋልጣል ይባላል (ወ/ሮ የውብዳር፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እንዲያውም ቀትር አለቀትርና ማታ ላይ ያ ሰዓት አመድ በተደፋበት አካባቢ መንቀሳቀስ ይፈራል (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እንደ አስከሬን የእንጨት ሞት የሆነበት ስለሆነ ከንቱና ተልከስካሽ ነገር ይወደዋል እያሉ ይገልጹታል (ወ/ሮ የውብዳር ጌታሁን፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

አመድ ከቡዳ ጋርም ተያይዞ ይነሳል። ብዙ ጊዜ ቡዶች ሲለፈልፉ ቤታቸው ውስጥ አመድ ይነሰንሳሉ፤ በአመድ ላይ ይንከባለላሉ ይሏቸዋል። ጅብም አመድ ይወዳል እየተባለ ይነገራል። ቡዳ ለፍልፎ ሲለቅ 'ምስህ' ምንድን ነው ሲሉት፣ አመድና አተላ ይላል (ወ/ሮ ውዴ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 5፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ይህ የክፉ ዐይን ቀለብና ማደሪያ የሆነው ሙት ክስተት ቤት ውስጥ ሲያድር ብዙ ጊዜ እንዳያጋልጥ፣ የእሳት ማዳፈኛ አድርገው ያሳድሩታል። በጋመው እሳት ላይ ኩበት ያደርጉና አመዱን ከባዶነት ይጠብቁታል። የጉንዳን ዘር የሆነው "ቀይ ዘመሚት" የሚባላቸውን እንደ አሪቲ፣ ጠጅሳርና ጤናዳም የመሳሰሉ ተክሎችን ሥር አመድ ያስታቅፋሉ። ሌላው ቀርቶ ጉንዳን ወደቤት እንንዳይገባ አመድን ማጠሪያ ያደርጉታል። ጉንዳን የተከመረውን አመድ አልፎ አይሄድም። ደረቅ ስለሆነ ርጥብ ነገርን የሚፈልግ አይቀርበውም ይሉታል።

7. የክፉ ዐይን መከላከያ መንገዶች

በዚህ ምዕራፍ ከክፉ ዐይን ጥቃት ስለምንጠበቅባቸው፣ ሰብዕናን ስለምናስከብርባቸው፣ በተፈጥሯዊነት ምንነት፣ ስለተፈጥሮ ሥሮችና ምንነታቸው ገለጻ ቀርቧል። በተጨማሪም ቀድሞ በመከላከል ከክፉ ዐይን ጥቃት እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል ስላለው ማኅበራዊ አረዳድ ገለጻና ትንተና ተሰጥቷል።

7.1. ፍትሃዊ መሆን

በትዛምን ማኅበረሰብ የፍጥረት አስተሳሰብ ውስጥ የፍጥረት ሥራቱ ከአራት ነገሮች እንደሆነ ይታመናል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከእነዚህ አራት ነገሮች ውጭ ሊፈጠር የሚችል ወይም የተፈጠረ ፍጥረት አለ ተብሎ አይታሰብም። የእነዚህ ፍጥረቶች ሥር ጥቅል መጠሪያ ባሕርይ ሲባል፣ ስማቸውም ነፋስ፣ እሳት፣ ውሃና መሬት ነው። ነፋስ ፍትሃዊነትን፣ እሳት ኃይልንና ጥንካሬን፣ ውሃ ንጽሕናን፣ መሬት ደግሞ ታዛዥነትን ወክለው የሚገለጡ ናቸው።

በእያንዳንዱ አካልና ነገር ውስጥ ያለው ይህ ባሕርይ ከፈጣሪ የተሰጠና ቀድሞ የተገኘ በመሆኑ፣ ከምንም ነገር በላይ ልዩና የተመረጠ ነው ይላሉ። እነዚህ የሥጋ ባሕርዮች የዚያ ተፈጥሮ እውነተኛ መልኮችም በመሆናቸው ንጹሕ ናቸው ተብሎ ይታመናል። ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ በፍጥረት አገኛኘትና የህይወት ዘመን ውስጥ እነዚህ አራት ባሕርዮች የሚሰለጥኑባቸውና ጎልተው የሚወጡባቸው የየራሳቸው ዘመን አላቸው ይላሉ። የእያንዳንዱን ፍጥረት የህይወት ዘመንም ለአራቱ ባሕርያት እኩል ተከፍሎ ይተዳደራል። ይህ ማለት ግን አንዱ ሲገን ሌሎች ይደቃሉ ማለት አይደለም።

በመሆኑም፣ በእያንዳንዱ ፍጥረት የቀዳሚ ዕድሜ ሰልጥኖ የሚገኘው ንጽሕ ባሕርይ የነፋስ ባሕርይ ነው ይላሉ (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በዘመን ደረጃ ሲታይ የንጋት፣ የጽንስ ጊዜዎች በህይወት ውስጥ በማበብ ውስጥ ያለው የአበባ ወይም የፀደይ ዘመን፣ ምድር

በየአይነቱ ልዩ ልዩ ተክሎችን የምታበቅልበት፣ ዕፀዋቱ የሚለመልሙበት፣ ጽጌያት አበባ የሚያወጡበት፣ ሜዳው የሣር ልብሱን የሚለብስበት ጊዜ ሁሉ አመኑ የነፋስ ነው። በሰው ልጅ የህይወት ጉዞ ልጅነት የሚካተተው በዚህ ክፍል ነው። ልጆች የሚቦርቁበት፣ የሚዘሉበት፣ የሚጫወቱበት ሁሉም ነገራቸው በአዲስ ስለተሞላ የሚያምሩ የሚደምቁበት የንጽሕና ዘመናቸው የነፋስ ዘመን ነው እያለ አባቶች የዕድሜ እርከኑን ይገልፁታል።

መርጌታ ዲበኩሉ፣ ይህ ዘመን በነፋስ የተመሰለው በነፋስ ባህርይ ውስጥ ቀላልነት በመኖሩ ነው ይላሉ (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይህም በፍጫ፣ በዝላይና በፈንጠዝያ የሚገለጽ ሆኖ፣ በሰው ልጆች የዕድሜ ዘመን እስከ ሃያ ዓመት ያለው በዚህ የሚታሰብ ነው ይላሉ ። የሰው ልጅ በዚህኛው ዘመኑ ስለዓለም ነገር ስለማያውቅ አያዳላም ይሉታል። እንደ ነፋስ እየነፈሰ፤ አካሉ ቀሎት እየሮጠና እያበደ ወደ መሬት የሚጥተው ሳይኖርና የሚከብደውና የሚያስረው ነገር ሳይታይ ከፍ ከፍ እንዳለ እንደተጫወተ ይኖራል በማለት ዘመኑን ያስረዳሉ። ምደራዊ ሥጋው ሳይከብደው ወደላይ ለመመንጠቅና ለመንሳፈፍ፣ ከመሬት ለመነሳት ሲፈልግ ያሻውን እያደረገ ሲፈጽም ይቆያል። ሰውን እንዲዘል፣ እንዲራመድ እንዲነሳ እንዲቀመጥ፣ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርገው ደግሞ የሰውነቱ ቅለት ነው ይላሉ (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

ጥጆች እንዲቦርቁና እንዲዘሉ፤ ተክሎች እንዲወዛወዙና እንዲንቀሳቀሱ የሚያነቃው ኃይል፤ ጽንስን የሚራውጠው፤ ጥንስስን የሚያፈላውና የሚያንተክትከው ይኸው የነፋስ ባሕርይው ነው በማለት መሪጌታ አይነኩሉ ያስረዳሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። መቀመጥንና መርጋትን እየጠላ፣ ምድር ላይ ማረፍንና መርጋትን እየሰለቸ እንደበረዱ እንደበረገገ ያሳልፈዋል ይላሉ። በምድር መታሰር በአካባቢው በዓለም ስራ መተብተብ ስለሆነ ከፍ ከፍ ማለትን የንጽሕና ምልክት አድርገው ያስቡታል። የሰው ልጅ ወደ መብሰል ደረጃ ላይ ደርሶ በማስተዋልና በማገናዘቡ መኖር ሲጀምር ለዓለም ጣጣ መግዛት ይጀምራል ተብሎ ይታሰባል። ልጅነት ግን ስሜቱ እንደመራውና ፍላጎቱ እንዳመላከተው መጓዳትን

ሳያስብ ሲነጉድ፤ እርጋታንና ስክነትን አሳጥቶት ማስተዋልን እያጎደለበት ዘመኑን ባለማወቅ ሲያሳልፍ፤ መቀመጥና መርጋት እየተሳነው መክለፍለፍ እያናወጠው፤ ደጉን ከክፉ፣ ቀዝቃዛውን ከሙቁ፣ ጎጅውን ከጠቃሚው፣ እየሞከረና እያግበሰበሰ ሳይለያቸው ይቆይና ዘመኑ ሲያልፈበት አደብ ይገዛል በማለት ነፍስ በወቅቱ ላይ እንዴት እንደሚገለጽ ያስረዳሉ፡፡

መሪጌታ አይነኩሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) በሰውና በእንስሳት ተፈጥሮ ውስጥ ቀድመው የሚገኙ አካሎችም የነፍስ ባህርይን ይዘው የሚገኙ ናቸው ይላሉ፡፡ የሰውነት እራስ የሆኑት ፀጉርና ቀንድም የቀለሉት የነፍስ ክልል ውስጥ ስላሉ ነው፡፡ "ለላም ቀንዷ አይከብዳትም" የሚባለው ለዚህ ነው ይላሉ አባባሉን ሰቅሰው፡፡ ይህ የነፍስ ባህርይ፣ እድሜ እየጨመረ ከቀዳሚነት እየራቀ በሄደ ቁጥር መከርከር፣ መጠንከር፣ መከርደድ ይጀምራል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ መጠንከርና አለመታዘዝ፣ እንደልብ አለመነሳትና አለመቆም የሚመጣው የነፍስ ዘመን ሲያበቃ ይሆናል፡፡ ተክሎች ቀስ እያሉ አበባቸው እየጠወለገ በምትኩ ፍሬ እያወጡ እንደሚሄድ ሁሉ፣ ልጆችም የነፍስ ዘመናቸው እያለቀ ሲሄድ እየበሰሉና እያወቁ ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ሰዓት የነፍስ ባሕርያቸው እያለቀ ስለሚሄድ፣ እንደልብ መውደቅ መነሳቱ፣ መዝለል መጨፈሩ እየከበዳቸው ይመጣል ይባላል፡፡

በመሆኑም፣ በሥጋ ባሕርይ ውስጥ ያለው ነፍስ ወካይነቱ ለፈታሒነት መሆኑ ነው (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) ፡፡ ነፍስ ገለባን ከፍሬ እንደሚለይ ሁሉ የርክሰትን ዕድፍ አንስቶ በንጽሕና የሚያኖር በአግባብና በሥርዓት መኖርንና ማደግን የሚፈቅድና የሚያስተምር የመለኪያ ሚዛን ነው ይሉታል፡፡ ይህ አስተሳሰብ በፍጥረቶች ቀዳሚ ህይወት ውስጥ የተወከለው በገራምነት፣ በታዛዥነት፣ በቀናነትና በለጋነት ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ የሰው ልጅ በነፍሳዊ ባሕርይው አስቦ ስለማይበድል፣ አዛብቶ ስለማይጠቅም ንጽሕናው የሚገለጸው በዚህ ነው ይላሉ፡፡

በሥጋ ባህርይ ውስጥ ያለው ነፍስ በባህርይው ውስጥ ቅለት ስላለ ከፍ ከፍ ያደርጋል፡፡ ይኸ ደግሞ በተራና በወረደ፣ በዘቀጠና ባነሰ ሥራ ላለመገኘት አምሳል

ነው ይላሉ መሪጌታ ዲበኩሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ከፍ ከፍ ማለትን የሚያነድፈውና የሚጫነው በሃሳብ፣ በድርጊትና በንግግር የሚያሳንስ ነገር ሲሰሩ ነው። በመሆኑም፣ የነፋስ ክልሉ ከአየር ውስጥ ነው ይባላል። ነፋስ በቀላልነት የሚወከለው በመንሳፈፍና በመሮጥ ነው። ይህን ቅለትና ከፍ ከፍ ማለት በሥጋ ጎድሎ በዕውቀት ለመክበድ ምሳሌ ስለሆነ፣ የሃሳቦች መግኛና መምጫ መንገድ ከአየር ላይ ነው ተብሎ እንዲታሰብ ያደርጋል በማለት ያስገነዝባሉ። አየር እንደ ትንፋሽ የሚታይ የእስትንፋስ መሠረት ነው። ምርምር፣ የሃሳብ ምጥቀትና አጠይቆት የነፋስ ተግባሮች መሆናቸው ነው። ቀኑን ሙሉ ሲያስብ ሲያልምና በምናብ ሲጓዝ የዋለ ሰው አእምሮው በሰማይ ላይ ያለ ነው ይሉታል። ይኸን ሰው ምዳራዊ ሥራ አይማርከውም። ሁልጊዜም በተራና በረከሰ፣ በቀነሰና በወረደ ሃሳብ፣ በክፉ ድርጊትና ተግባር አይሰማራም ይሉታል።

ይኸ ባሕርይ በፍጥረት ውስጥ ምልክት የተደረገው ክንፍ በሚባለው የአካል ክፍል ነው (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በራሪ ፍጥረቶች ወደላይ ለመውጣትና ከፍ ብለው ለመንሳፈፍ የሚረዳቸው ክንፋቸው ነው። ምድርን ለቀው ወደአየር የሚመጥቁት በዚሁ የአካል ክፍል አማካይነት ነው። በአየር ላይ መብረር ወይም ክፍ ማለት ከተለመደውና ከተራው ኑሮ ለመላቀቅ፣ ከክፉ ሥራና ምግባር ለመራቅ ምሳሌ ነው(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ለላቀና ለተመረጠ ዓላማ መመረጥ ነው። ክንፍ አልባነት ደግሞ ዘውትራዊ አካሄድን መከተልና አንሶና ወርዶ የመገኘት፣ በተናቀና በተጠላ መልካም ባልሆነ ሥራ ውስጥ ለመዘፈቅ ምልክት የሚሆን ነው።

የሰው ልጅ በአመለካከቱ፣ በአስተሳሰቡና በኑሮው እንደ እንስሳ መሬት እንደያዘ መቅረት የለበትም ብሎ ሲያስተምር ነው ይላሉ ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ሰውን ወደ መርዳት ወደ መውደድ፣ ወደ አለማድላት፣ እንደዚያ ወደ ሆነ ነገር መውጣት የተለመደ አኗኗርን ከመምራት መደመለየት፣ ወደ ተሻለና የተመረጠ ምግባር መቀየር እንዳለብን ሲመክር ነው

በማለት ሁኔታውን ያብራሩታል። ለክፉ ሥራና ለጥላቻ ከሚያጋልጡና ከሚያስከስሱ ሥራዎች የመራቅ አስተሳሰብ ነው።

እንደ እንስሳቱ ሁሉ ሰዎችም እንደ ድንጋይ ከመረገጥና ከመስመጥ ወጥተው፣ ከፍ ወዳለና ወደተሻለ፣ ልዩ ሆኖ ወደመታየት፣ ወደ መወደድና መመረጥ እንደሚገቡ የሚያስገነዝብ ቁምር ነው ይላሉ። በሃሳብ፣ በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት ወደላይ መውጣት፣ ተውጦ አለመቅረትን ይጠቁማል። ይህ መውረድ በሰብዕና ላይ መርከስን ስለሚያስከትል ለክፉ ኃይሎች ያለው አጋላጭነት ከፍተኛ ነው። ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ) ሰጥመው የሚቀሩ፣ ሠርገው የሚጠፉ፣ የበታችና ተገዥ ለሚሆኑት ባልተገባና በነውር ተግባር ላይ ለሚልከሰከሱ አካሎች አምሳል ናቸው በማለት ይገልጿቸዋል። ስለዚህ፣ እንደዚህ አይነቱን አትብላ ማለት "ከእነሱ ዓለም፣ ሃሳብና መንገድ ተነጥል፣ መንገድህን አስተካክል፣ ከፍ ላለና ለተለየ ዓላማ ራስክን አስገዛ፣ ሰብዕናህን ጠብቅ፣ ሰውነትህን አስከብር ማለት ነው" በማለት ይገልጹታል።

ምድራዊ አትሁን፣ አታግበስብስ፣ ያንንም ይህንንም እየሰበሰብክ አካልህ አይክበድህ ማለት ነው ይላሉ። አትብላ ሲልም እነሱን ማህበርና ጓደኛ አታድርጋቸው፣ ከሥጋህና ከደምህ አታዋህዳቸው ሲል ነው (ዲያቆን ብርሃኑ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። በዚህ የተነሳ ከአሣ ዘሮች መካከል እንዲበሉ የተፈቀዱት ቅርፊትና ክንፍ ያላቸው ብቻ ናቸው (ዘሌ 11፣9)። ቅርፊትና ክንፍ የሌላቸውን ተግባራቸው አጋላጭና አስጠቂ በመሆኑ እንዲርቋቸው ይመክራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ሳይዘራ የበቀለውን አትጨድ ካልተገረዘው የወይን ተክልህ ፍሬ አተሰብስብ" ይላል (ዘሌ 25፣ 5) ። ይህንን ጠቅሰው ትርጉሙን ያብራሩት መርጌታ ዲበኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ "አርሰህ ዘርተህ፣ ጥረህ ግረህ በላብህ ያላገኘኸውንና ያንተ ያልሆነውን ነገር አትመኝ ማለት ነው" ይላሉ ። ይህም ከማግበስበስና ያንንም ያንንም ከመለቃቀም መጠበቅ እንዳለብን የሚያስተምር የሰብዕና መግሪያ ቃል ነው በማለት ሃሳባቸውን ያጠናክራሉ ።

ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ) በተፈጥሮ ውስጥ ልኬታና ምጣኔ አለ ይላሉ ። አንድን ፍጥረት ንጹሕ የሚያደርገው በዚህ የተፈጥሮ ህግ መመራቱ ነው። የሰው ልጅ ከዚህ ከተሰጠው ስፍር ሲያልፍና በምኞቱ እየተነዳ ውስን ተፈጥሮውን ሲጥስ ማለትም አታድርግ ከተባለው ገቢሩ ተላልፎ ሲገኝ የነፋስ ተፈጥሮው ስለሚጠፋ ማሰብና ማስተዋሉ ይነድልበታል ይላሉ።

ለምሳሌ፡- ዝሙት አብዝቶ ሲፈጽም፣ ስረቆት ሲጀምር፣ እንደሐሜት፣ ውሸት፣ አለባልታ፣ አድማና ምቀኝነት የመሳሰሉ ጠባዮችን ሲለማመድ ምድራዊነት እየተጫነው ስለሚሄድ ከፍ ከፍ ማለቱ፣ ለተሻለ ቁምነገር መታጨቱ እንደሚቀርበት ይናገራሉ። ከእነዚህ ጠባዮች ጋር ፍጥረት የሚተዋወቀው በምጣኔ መኖር በተቸገረበት ጊዜ ነው ይላሉ (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ በባህላዊ እምነቱ ውስጥ ትርፍና የራሱ ያልሆነ ነገርን መያዝ ለዚህ ችግር እንደሚያጋልጥ ያስረዳል።

ከብት ሲታረድ፣ 'ሥብ'ና "ደም" እንዳይበላ በመጽሐፍ ቅዱስ የተከለከለውን የኅብምን አካባቢ ሰው ለይቶ ሲያከብረው ይታያል (ዘሌ 4፣2)። ደም የህይወት ምሳሌ ስለሆነ አትብላ ሲል "ነፍስ አታጥፋ" ማለቱ እንደሆነ ይታወቃል (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህንን ሕግ የሚተላለፉ ግለሰቦች አልፎ አልፎ አይከሰቱም ማለት አይቻልም። ከላይ ከቀረበው ሃሳብ ጋር ተያይዞ የቀረበው ግን የሥብ ጉዳይ ነው። ሥባ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በአካባቢ የያዘው ትርጉም፤ "ወፈረ፣ ደለበ፣ ደነደነ ማለት ነው" (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በአካል ውስጥ ሥብ የሚመጣው ሲደልቡና ከሚገባው በላይ ተጨማሪ የሥጋ ክምችትን ሲይዙ ነው። ይህ ሥጋ ተገቢ ላልሆነና በስግብግብነትና በመሻማት ለተገኘ፣ በፍትሃዊነት ላልመጣና የራስ ያልሆነ ሃብት ምሳሌ ነው።

በአካል ውስጥ ሥጋ ሲበዛ በሥጋ ባሕርያት መካከል ያለውን ምጣኔ ያዛባዋል። የሰው ልጅ የመሬት ጠባዩ እያየለ የማሰብ ሃይል የሆነው ነፋሳዊ ጠባዩና የመመርመር ችሎታውና ማፍራት አቅሙን የሚያስገኝለት እሳታዊ ግብሩ ሁሉ

ሳይቀር ይፈላል (መሪጌታ ዲበኩለ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሌሎቹም ግብሮቹ ሁሉ እየጎደለ ይመጣሉ። በሌላ አገላለጽ የተወሰነው ባሕርይው በተመጠነና በተደለደለ መልኩ አካሉ ውስጥ አለማገልገሉን ጠቋሚ ነው። ሰውነት ሌሎቹን ባህርያት ሲያጣ፣ ሰው ሆነን የተገነባንባቸው ነገሮች ስለሚጎድሉ ሰው መሆን ፈተና ውስጥ ይወድቃል (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ።

በመሆኑም፣ የተወሰነው ባሕርይ በተመጠነና በተደለደለ መልኩ አካሉ ውስጥ አለማገልገሉ የአጠቃቀም ችግር መኖሩን ነጋሪ ነው ይላሉ። ይህ ደግሞ ሰብአዊነትን የሚጫን ሆኖ ይታሰባል። እንደዚህ ያሉ የህይወት ልምዶች አግበስባሽነትንና ግለኝነትን የሚተክሉና የሚያነግሱ አብሮ መኖርን የሚፈትኑና የማያመጣጥኑ አበላላጭ ሁነቶች ናቸው ብለው ያስቧቸዋል። ማሰብንና ማገናዘብን የሚጫኑ የሰውን ልጅ ወደግብታዊነት፣ ደመነፍሳዊነት፣ ራስ ወዳድነትና ስግብግብነት የሚከቱ ፀረ ሰብአዊ ተግባሮች ናቸው በሚል ይረዷቸዋል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። በመሆኑም፣ ይሽንን ሲያደርግ አካሉ ከብዶት ስለማይታዘዘው የዕውቀትና የማመዛዘን ምሳሌ የሆነችው ነፍሱ ስለምትጎድል፣ ሥጋ የሚያከብረው ክፉ ዐይን ገብቶ እንዲደላደል አጋጠሚዎችን ይፈጥራሉ በማለት ዲያቆን ብርሃኑ ይናገራሉ።

የጎዛምን አርሶ አደሮች የዘሩትን ሲያጭዱ በወሰን አካባቢ ያለውን እህል ለይተው ይተውታል። 'አውድማ ሲጣል' የኔ ቢጤ ስለሚመጣ ከዚያ አጭደህ ውሰድ ይባላል (አቶ ይዘንጋው ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። ለይታችሁ ሳታጭዱ የምትተውት ለምንድነው? ተብለው ሲጠየቁ፣ "ስንዘራ ነፍስ የኔን ዘር ወስዶ ወደእሱ፣ ከእሱ አምጥቶ ወደኔ ማሳ ሊጥለው ይችላል። ስለዚህ፣ ወሰናችን አካባቢ ያለው የራሳችን አላባ ስላልሆነ እኔም ሆንኩ እሱ ዳር ዳሩን አናጭደውም። የራሴ ያልሆነውን ዘር ከእኔ ጋር አልቀላቅለውም። የኔ ሃብት አይደለም" በማለት የሰው ሃብት ያጠፋል የሚለውን አካባቢያዊ ብሂል በተግባር ይገልጹታል (አቶ ይዘንጋው፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። ለፍተውና ደክመው፣ አርሰውና ቆፍረው ያመረቱትን የላባቸውን ዋጋ ብቻ ይፈልጋሉ። በመሆኑም፣ አንዱ

ARABA UNIVE
ANTES
x 1170

ሥጋዊ ባሕርይን የምናመጣጥንበት መንገድ የራስ ያልሆነን ነገር ባለመመኘት ወይም ባለመፈለግ እንደሆነ ከላይ ከቀረበው ምሳሌ ማረጋገጥ ይቻላል።

አቶ ይዘንጋው (2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ) አንዳንድ ጊዜ ዘመን ሰጥቶ አዝመራው ከመጠን በላይ ሲሆን፣ አለልክ በቀለ እያልን ከመደሰት ይልቅ እናዝናለን ይላሉ። ወቅት ሰጥቶት ለቆው ሲያምር ምርቱ ሽጋ ሆነ ብለን አንኩራራም። ከዚያ ይልቅ ምን ሊያመጣብኝ ነው ብለን እንፈራለን። ከብቶች ሰውነታቸው ሲፋፋና ሞላ ሞላ ሲል፣ እንደዚህ ሆነው ያማሩ ለኔ ብሏቸው ነው? ሊሞቱብኝ እንዳይሆን እያልን እንሰጋለን። የፈራሁት አግኝኝ የምንልበት ሰዓትም አለ በማለት ከልክ ያለፈ ሃብት የሚያጠፋና ጎጅ ሆኖ የሚታሰብ መሆኑን ያረጋግጣሉ (አቶ ይዘንጋው፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ) ።

ሁልጊዜ አንድ ነገር ከመጠኑ ሲያልፍ አይመጥንም፤ ይገፋል ይላሉ። አንድ ሰው አካሉ ሞላ ሞላ ብሎ ሰው ተመችቶሃል ካለው፣ ሊወስደኝ ነው መሰል ብሎ ስጋቱን ይገልጻል (አቶ ዘመኑ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ ሰው መልካም ብሎ የሚቀበለው በልክ መኖርን፣ በተመጠነ አኳኋን ህይወትን መምራትንና ትርፍ ነገር አለመያዝን ነው። በልክ ውስጥ ፍትሃዊነትና ሚዛናዊነት ስላለ ተፈጥሮን በማክበር ከልዩ ልዩ ስጋቶች መጠበቅ ይቻላል ብለው ያስባሉ።

ይህ የልክኝነት አስተሳሰብ በአካባቢው እንስሳትን የሚበሉና የማይበሉ ብሎ ለማወገን ዋነኛ የመምረጫ መስፈርት ሆኖ ይታሰባል (ዲያቆን ብርሃኑ፣2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሰዎች የሚመገቧቸውን እንስሳት የሚበሉና የማይበሉ ብለው ሲመርጡ በአበላል ሁኔታቸው ላይ መስፈርት ሆኖ የሚመጣው የአበላል ምጣኔአቸው ነው (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በዚህ ጥናት ክልል ሥጋ በል የሆኑ እንስሳት ምግብ አይሆኑም። ግር በል ከሆኑ እንስሳት መካከል ትኩረት የሚደረግባቸው የማያማበሰብሱት፣ ሁሉን ነገር መለቃቀምና መክተት የማይወዱትና በልክና በአግባብ የሚኖሩት ናቸው (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ከአዝርዕት መካከል መልካም የሆነውን ለይተው የሚበሉ እንስሳትን ይወዳል። በምግብ ዝርዝሩ ውስጥ ሥጋ በል የሆኑ እንስሳትን አያስገባም። በአካባቢው የአመጋገብ ባህል ውስጥ ሽኮናቸው ክፍት የሆኑት ሲበሉ፣ ክፍት ያልሆኑት ደግሞ ርኩስ ተብሎ ይገፋሉ (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አምስኳ መሆን በእንስሳት ህይወት ውስጥ ልክንና መጠን ነጋሪ ጽንሰ ሐሳብ ነው።

ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ማምስኳን፣ "እያመላለሱ መፍጨት" በሚል ይገልጹታል። የሰው ልጅ የሚነገረውንና የሚማረውን ሁሉ መልሶ መላልሱ ለማብላላቱ፣ ለማጤኑ፣ ለማጥናቱ፣ ለማገናዘቡ፣ ለማስተዋሉና ልብ ለማድረጉ የሚሆን ምሳሌ ነው በማለት ይገልጹታል (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ደግሞ ደጋግሞ ማየት መመርመር፣ ማመላለስ፣ ከዚያ አብዝተህ መማር ማወቅ መቻል መጥፎውን ከጥሩ ለማጥራት፣ ክፉውን ከመልካሙ ለማንጠርጠር ፍሬውን ከገለባው ለመለየት የሚረዳ የዕውቀት መንገድ መሆኑን አሳይ መሆኑ ነው። የሚያመሰኩት ካገኙት መካከል መርጠውና ለይተው ስለሚጠቀሙ፣ የበሉትንም እድቅቀውና ፈጭተው እንዲመጥን ስለሚያደርጉ መጣኞች ናቸው ይሏቸዋል (ዲያቆን ብርሃኑም፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አምስኳ ከፍ ከፍ ከማለት ጋር የሚያገናኘው ሌላው እሳቤ ከማግበስበስ እርቆ፣ ከመመጠን ጋር ስለሚያወዳጅ ነው(መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ማግበስበስ ሳያጣሩና ሳይለዩ እንዳለ መክተትን፣ ማጠራቀምን፣ መጎስጎስንና መውሰድን የሚመለከት ነው። ያገኘውን ሁሉ ይከታል፤ ሳይመርጥ ያከማቻል። ወዳጁን ከጠላቱ፣ ክፉን ከደግ እንዲሁም እኩዩን ከመልካም አይለይም ይሉታል። የነገሩትን ሁሉ የሚቀበለው፣ ሳያመዛዝንና ሳያገናዝብ ነው። የሚወስደው፣ የሚጠቅመውን ከሚጎዳው ሳይለይ ነው። እንደነዱት የሚነዳ እንደገፉት የሚያዘነብል አቋማና ዓላማ የሌለው ሰው በዚህ ይመስሉታል። በሌላ በኩል ይህ አይነት አስተሳሰብ በአካባቢው የሆዳምነትና የአግበስባሽነት መገለጫም ነው። ይህ ሁነት ካለማስተዋል፣ ካለማወቅና ካለመብሰል የሚመጣ ነው በማለት

ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም፣ ለግል ፍላጎት ብቻ እንደ እንስሳት መገዛትን የሚነግር በመሆኑ ነው፡፡

ዲያቆን ብርሃኑ(2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ የሚያመስኩ እንስሳት የበሉትን ሁሉ አምሽከው የሚጨርሱ አይደሉም ይላሉ፡፡ በጠባያቸው ለመምረጥ ዋጋ ይሰጣሉ፤ በማግበስበስና በመሰብሰብ ያገኙትን ሁሉ መልቀምና መክተት አይገልጣቸውም ይሏቸዋል፡፡ መመጠንና በልክ ማድረግ ጥሩውን ከመጥፎ መለያ ዘዴ ነው፡፡ ጎናቸው ሲያርፍና ጊዜው ሲጨልም ያንን የቆጠቡትን እያወጡ ቀስ እያሉ እየፈጩና እያደቀቁ ምሽቱን ያነጉበታል፤ ቀን ይወጡበታል ይላሉ፡፡ ይህ ቆጥቦ የመጠቀም ልማድ፣ መርጦ የመብላት አስተሳሰብና ጠባይ የአስተዋይነት ምልክት ነው በማለት ተፈጥሯቸውን ይተረጉሙበታል፡፡

እንደ ፈረስና አህያ ያሉ ፍጥረቶች ግን፣ በልተው የማይጠግቡና የማይመርጡ አግበስባሾች ናቸው ይሏቸዋል፡፡ በመሆኑም፣ ይህ ጠባያቸው ይጋባብናል ብለው ስለሚፈሩ ጉልበታቸውን ካልሆነ ሥጋቸውንም ሆነ የአካባቢው ማኅበረሰቦች አይገለገሉበትም፡፡ አይደለም ሊበሏቸው፣ ሲወልዱ የሚያጣፍሯቸው ሰዎች እንኳ ሳይቀር ፈሳሾቻቸው ሲነኳቸው ረክሰናል ብለው ወደ ቄስ በመሄድ ይባረካሉ (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ፡፡

በጎሣሞን፣ ሰው ከሚያገኘው መካከል ቀድሞ በማካፈል ተፈጥሮውን ሊያከብር ይሞክራል፡፡ ነገሮች በቀዳሚነት ለነበራቸው ተፈጥሯዊ ሚዛንና ምጣኔ ወዴታና አክብሮት ያሳያል፡፡ በዚህ ልምዱ የቀደመውን ነገር ማክበርና ጠበቆ መያዝ እንዴት እንደሚቻል እየተማረበት ይሄዳል፡፡ የአካባቢው ሰው ባህርዩን ከፈጣሪ በስጦታ ቀድሞ እንዳገኘው ሁሉ በላቡና በጉልቡቱ ቀድሞ ያገኘውን እሱም በመስጠት ሊከብርበት ይሞክራል፡፡ በመሆኑም፣ መስዋይት ሲያቀርብ ካሉት ውስጥ የሚመረጡት በመጀመሪያ የተገኙት ናቸው፡፡ የከብትም ሆነ የበግ የመጀመሪያ ልጅ ገበያ ወጥቶ አይሸጥም፡፡ አባቶች በቀደመው ዘመን የመጀመሪያ ልጃቸውን ካህን እንዲሆን ለቤተክርስትያን ይሳሉ ነበር ይባላል (ቄስ እንስማ፣ 2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡

“ላሞች ሲወልዱ የመጀመሪያውን ወተት ማለትም እንባሩን ሰብስቦ ይንጥና የወጣውን ቅቤ ሸጦ ጧፍና እጣንቶ በመግዛት ለቤተክርስትያን መባ ይሰጣል። አሁን አሁን ደግሞ እንባሩን በተለየ ዕቃ ያጠራቅሙና ጎረቤት ሰብስበው ያበላዋል (ወ/ሮ የውብዳር፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይሽንን ባህል ንቆ ለጥጃው ቢሰጥ ፀጉሯ ይመለጣል” እየተባለ ይነገራል። ይህ የወተት አይነት ላሚ እንደወለደች ቀድሞ የሚወጣ በመሆኑ፣ ዘግይቶ ከሚታለበው የተሻለ ጣዕም፣ ውፍረት፣ ጥንካሬና ኃይል አለው ይላሉ (ቄስ እንስማ፣ 2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

እመጫቶች እንደወለዱ የጡታቸውን ወተት ለተወለደው ሕጻን ከመስጠታቸው በፊት ከመሬት ያፈሱታል (ወ/ሮ የውብዳር፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይህንን ወተት ልጆች ቢጠቡት አፋቸው ይቆስላል ይላሉ። እናቶች ለጠላ የሚሆነውን ቂጣ ሲጋግሩ ሰው ከመቅመሱ በፊት ቀድመው ቆርሰው የሚያቀምሱት ለውሻ ነው። ውሻ የበሰለ እህል ሲሸተው አይኑን ተክሎ ስለሚያይ ትኩስ እንጀራም ቢሆን ለእሱ ተቆርሶ ሳይሰጥ ሌላ ሰው አይቀምስም ይባላል። ከውሻው ቀድሞ ሰው ቢቀምሰው እንደሚታመም ይናገራሉ (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። የውሻ አፍንጫ ከሩቅ ስለሚያሸት ነገረኛ ነው ይሉታል።

በእህል ዙሪያ ያለውም እምነት ተመሳሳይ መሆኑን የሚገልጹት አቶ ይዘንጋው (2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ) ገበሬው አምርቶ፣ አጭዶ ሲከምር፣ ከተከመረው ነዶ መካከል ከላይ ያለውን ለብቻ ያዘራና ከጠራው መካከል ቀድሞ ‘ማሪያም ባርኪ’ ብሎ መገበሪያ ይሰፍራል ይላሉ። በቤት ውስጥ በና ሲፈላ ቀድሞ የተቀዳውን በስኒ አድርገው ሳይቀምሱ ያስቀምጡታል (ወ/ሮ ንግስቴ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በአንዳንድ ቦታ ደግሞ ቀድመው ምድር ላይ ያፈሱና አስክትለው የቀዱትን ለቤተኛው ሰው ያድላሉ።

እንደተልባና ኑግ ያሉ የቅባት እህሎች ተቆልተው ሲወቀጡ፣ ሰው ከመቅመሱ በፊት ቆንጥረው ለመሬት ያቀምሳሉ (ወ/ሮ በየነች፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በበዓል በግ ሲታረድም በመጀመሪያ የሚፈሰውን ደም መሬት ሳይፈስ አስቀድመው በዕቃ ይቀበሉታል። ከዚያም ከድነው ለሶስት ቀን ያኸል

ያስቀምጡና ጉድጓድ ቆፍረው ይቀብሩታል። በአዲስ ዓመት፣ በህዳር፣ በጥርና በሰኔ ሚካኤል ምሽት ላይ በሚከናወን የበሶ መብል ባህላዊ ሥርዓት አለ። ለሥርዓቱ ምግብ ይሆን ዘንድ የሚቆላውን ገብስ ቀድሞ ሰው እንዳይቀምሰው፣ "ከበላችሁ አፋችሁ ይጣመማል" እያሉ እናቶች ያስፈራራሉ (ወ/ሮ በየነች፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በሶው ተበስብሶ እንደቀረበ ሰው ከመቅመሱ በፊት ሥርዓቱ አምልኮውን የሚመራው ሰው እየቆነጠረ በአራቱ አቅጣጫ ይረጫል። ይህን የሚሆነው በአካባቢው ተነስንሰው ለሚገኙ ህቡዓን ኃይሎች ለማቅመስ ነው ይላሉ።

በመሆኑም፣ የአካባቢው ሰው ከሚያገኘው ላይ መጀመሪያ ቀንሶ ሳይሰጥ ለራሱ አይወስድም። በመስጠት ስስትን፣ ስግብግብነትንና የኔ ባይነትን ያርቅበታል። ከሰጠ በኋላ የላቡ ዋጋ እንዲባረክለት ይፈልጋል። የእሱ ከሆነው መካከል ቀንሶ በመስጠት ነፈሱን ያስደስታል። ሳያቀምስ ተስገብግቦ ለራሱ ሊያደርግ አይሞክርም ይላሉ መሪጌታ ዲበኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ትርፍ ነገር ግን ያጠፋኛል፣ ያስቀስፈኛል ብሎ ስለሚሰጋ የሰው ሀብት እንዳይገባበት ይጠነቀቃል ይባላል።

የሚሰጠውን ሰጥቶ ለእሱ የሚሆነውን ወደቤቱ ሊያስገባ ሲል በላቡ ያገኘው፣ በበሬዎቹ ጉልበት ያመረተው የግሉ መሆኑን ባርከውና መርቀው ውሰድ እስኪሉት ድረስ ይጠብቃል። ሕብረተሰቡ አምኖ ያንተ ነው ብሎ ይሁንታውን ሳይሰጠው ቢያስገባው በረከት አጣበታለሁ ብሎ ይፈራዋል በማለት አቶ ተዘራ አስማረ ይናገራሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የእሱ ላብ ለመሆኑም በአደባባይ ይምላል። በንዛምን አካባቢ በራይ ተበራይቶ ካለቀ በኋላ ገበሬው ከማሳው ላይ ሠርዶና የአባሎ ቅጠል እንዲሁም የራሱ ከሆኑት በሬዎች ላይ ጭራ ነቅሎ በአንድነት ይይዛል። እነዚህን በአንድ ላይ "አጉማስ" ይላቸዋል።

ከዚያም የበሬዎችን ማፈኛ ይፈታና፣ በሬዎቹን እያዞረ፣ "ተባረክ በሬዬ፣ ማር ውሃ ይምጠንህ፣ ያልገዛ አይንዳህ፣ ከቁልቁለት ከሶማ ዳገት ያድንህ" በማለት በሬውን በአጉማሱ ይመርቅበታል (አቶ ተዘራ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ያንን አጉማስ ከምርቱ ውስጥ ያደርግና የተሰበሰበውን ሰው፣

"ተዋሰኝ ለአምሳ ጫን" ይላል። ወንፈል የዋለው ሰው ሁሉ አዋሳለሁ ይላል። የእሱ ስለመሆኑ እማኝ ሆነው፣ ፈቅዶ ውስድ ብሎ ሰጠው ማለት ነው። ይህ ሳይባል እህል ውሃ አይቀመስም። ይህን አጉማስ ጤፉን ሲያዘራ (ማለትም በንፋስ ሲለይ) ከምርቱ አይለየውም። ሲጭን አብሮ ከእህሉ ውስጥ ያስቀምጠዋል፤ ከጎተራ ይከተዋል። ሚስቱ እህል ለማስፈጨት ስታወጣ ከወጣ መልሳ ትከተዋለች። እንዲህ እያለ የየዓመቱን በጎታው ያስቀምጠዋል (አቶ ተዘራ አስማረ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ከዚህ የምንረዳው ሰርዶን ከባድማው ውስጥ ነቅሎ የአጉማሱ አካል አድርጎ የመያዙ ትርጉም ነው። አቶ ተዘራ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ይህን ልማድ፣ "ሃብቴን ለሰው አትበለው፤ በበሬዎቼ ለፍቼ፣ መሬቴን አርሼ፣ በላቤና በወዜ ያገኘሁትን ንብረት ለሌላ አትስጥብኝ ብሎ ሲማጸን ነው" ይላሉ። ስለዚህ፣ ሰርዶ የዘር፣ የትውልድ፣ የራስ ወዝና ላብ ለሆነ ለተተከለ ሃብት ምሳሌ ነው። በላቡና በወዙ ያመረተውን፣ አርሶና አጭዶ የሰበሰበውን ሌላ ተጋፊ ኃይል እንዳይወስድበት መመኛው ነው ይላሉ። ያልተፈቀደለትን ሲወስድ፣ የማይገባውን ሲነካ ያልተፈቀደለትን ሲያደርግ እንደሚጥለው ያስባል። ለክፉ ኃይል አሳልፎ እንደሚሰጠው ያምናል።

በትግሞን አካባቢ ያለው ህብረተሰብ እንግዳና አዳዲስ የሆኑ ክስተቶችንና ዘግይቶ ደራሽና መጤ ልምዶችን ለመልመድና ለማቅረብ ይቸገራል ይሉታል። ሁልጊዜም ቢሆን የሚያውቀውንና የለመደውን ብቻ ነው የሚመርጠው (አቶ ቻላቸው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ለቀደመው ነገር የሚሰጠው አክብሮትና ጥበቃ የተለየ ነው። ለመጀመሪያ ተፈጥሮው፣ ሁኔታውና ገጽታው ሁሉ ክብርና ሞገሱ ልዩ ነው። በእያንዳንዱ አካል፣ ነገርና ተፈጥሮ ውስጥ ቀድሞ የተገኘ፣ የወጣ ወይም የተፈጠረ ከምንም ነገር በላይ ተለይቶ ይያዛል። እንግዳውን፣ ዘግይቶ መጪውንና ደራሽን ይፈራዋል።

ቀዳሚዎችን እንዲያከብር ያደረገው በነባሩ ውስጥ ጥንካሬ፣ ፍትህና ንጽሕና ስላለ ነው (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በመሆኑም፣ ከልጆች መካከል በእግሩ ቀድሞ የሚሄደው የበኩር ልጅ ነው። ይህንን ያየ ሰው፣

“የቁብ ልጅ ሆኖ ነው” ይላሉ። የቤተሰብ አባላቱ ሰውነታቸውን ሲቆረጣጥማቸው፣ አካላቸው እየደቀቀ ሲልፈሰፈስ የበኩር ልጅ ሲያሽ ይለቃል ይባላል። ስለዚህ፣ ቀድሞ መገኘት የተሻለ አስደርጎ የሚያስገምትና ዋጋ የሚያሰጥ ነው። ቀድሞ ላቀናው ባለመብትና ባለክበር ስለሚያደርግ የቀደመው ሳያገባ ተክታዩ አይዳርም።

የቤተሰብ አባላት በአንድ ሞሰብ ሲቀርቡ በራኬም ሆነ ምርቃት የሚሆነው በታላቅ ነው። ታላቅ እያለ ታናሽ ተነስቶ ለመስዋዕት ወይም ለእርድ የቀረበን የከብት አንገት አይባርክም። ባራኪው ደግሞ ለልቅናው ዋጋ እንዲሆነው የበሬው ራስ ይሰጠዋል (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። አቶ ቅሩብ ለመከባበርና ለመስማማት መስፈርቱ ዕድሜ የሚሆነው ለቀደመ ነገር የሚሰጠው ቦታ ትልቅ በመሆኑ ነው ይላሉ። ቀዳሚነት ክብርንና ተሰሚነትን ሲያስገኝ፣ ቀዳሚነትን ማጣት ደግሞ መብትንና ክብርን ያስነፍጋል ይላሉ። ምክንያቱም፣ ከቀዳሚነት መሸሽ መጉደል፣ መቀነስ፣ ማነስ ስላለበት አጋላጭነቱ ከፍተኛ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።

ካለው ፍጥረት ሁሉ በተለየ በእነዚህ እንስሳዎች ላይ ይህ ህግ ሊጸና የቻለው፣ እነዚያ ፍጥረቶች በእሴቱ ውስጥ ትክክል ተብሎ ከተያዘ ልማዱ ጋር የማይስማማ ነገር ስለሚይዙ ነው። ፍጥረቶች እንዲገለሉ ምክንያት የሆነው ነገር፣ ከተለመደውና ከሚታሰበው የዝርያ ባህርይ ያፈነገጠ ጠባይ መያዝና ወጥነት የጎደለው ተፈጥሯዊ መልክና ቅርጽ ማሳየት ነው። ለምሳሌ፡- በአፈጣጠር ዙሪያ ያለውን ልማድ ብንመለከት፣ የሚበሩት አብዛኞቹ የወፍ ዘሮች ጅራት ያላቸው ናቸው። በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶች ደግሞ “ላት” ወይም “ጭራ” ያላቸው ናቸው። የወፍ ወገን የሆኑ ፍጥረቶች የሚራቡት ከእንቁላል የሚፈለፈሉ ናቸው። አጥቢዎች ግን በመዋለድ የሚራቡ ናቸው ይላሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)።

ከተፈጥሯዊ ዝርያቸው አፈንግጠው፣ ከፍጥረታቸው ተለይተው የተገኙ እንቁላል ጣይ ሆነው ጭራ፣ አጥቢዎች ሆነው ጅና ያላቸው አሉ በማለት ያስረዳሉ(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። እንደዚህ አይነት ፍጥረቶች ምድባቸው ከእንቁላል ጣይም ከአጥቢም ያልሆኑ ግራ አጋቢዎች ናቸው ይሏቸዋል። ወገናቸው ከወፍ ሆነው የሚያጠቡ አሉ። ለዚህ የሌሊት ወፍን ምሳሌ

አድርጎ መጥቀስ ይቻላል ይላሉ (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅም)። ይኸ ፍጥረት ከሌላው ፍጥረት ተለይታ የቀን ዳፍንታም የማታ ዐይናማ ነች ይሏታል። ይህንን ማፈንገጥና የጠባይ ለውጥ እያየ የአካባቢው ሰው የሌሊትን ወፍ ዙረትና ጥላ ይፈራዋል። እሷ የዞረችውን ምግብ የበላ ወይም የዞረችበት *"ጉበቱ አብጦ፣ አይኑ ቢጫ ሆኖ ይሞታል"* ይላሉ (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ፍጥረቷ ከወገኖቿ ተለይታ ይኸንን ጠባይ ልታሳይ የቻለችው ከፍጥረቷ በመጉደሏ ወይም በመነጠሏ ነው። በመሆኑም፣ ከፍጥረቱ የተነጠለውን ክፉ ዐይን እንደሚጠጋው አሳይ ነው።

እንስሳቱ በመኖሪያ ቦታ ምርጫቸው የሚያሳዩት አፈንጋጭ አፈጣጠር ወይም ከዝርያቸው የሚያስወጣ ያልተለመደ አኗኗርም በተለየ እንዲታሰቡ የሚያደርግ ሌላው አጋጣሚ ነው። ሥጋ በል የሆኑ ፍጥረቶች በአካል ቅርጻቸው፣ በቆዳ ሁኔታቸውና በጥርሳቸው አይነት ከሳር በል እንስሳት በእጅጉ የሚለዩ ናቸው። በእንስሳቱ ዝርያ ያሉ አንዳንድ ጠባዮቻቸው ወጥነት ባለው መልኩ ለምሳሌ፡- ሥጋ በል የሆኑ እንስሳት፣ ሳር በል ከሆኑ እንስሳት የተለየ ጠጉርና ጥፍር የያዙ አሉ ይላሉ ዲያቆን ብርሃኑ። እንቁላል የሚጥሉ ፍጥረቶች በክንፋቸው እንዲበሩና ሁለት እግር ያላቸው ሆነው የተፈጠሩ ናቸው። ጡት አጥቢዎች ደግሞ አራት እግር ያላቸውና በየብስ ላይ የሚንቀሳቀሱና የሚድኹ ናቸው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ይህ የአፈጣጠር ሥርዓት በአንዳንድ ፍጥረቶች ላይ ወጥ አይሆንም። ሲጓደልና የተዘበራረቀ ቅርጽ ሲይዝ ይታያል። ለምሳሌ፡- እንቁላል የሚጥሉ ዝርያዎች እግራቸው ሁለት ሆኖ ሳለ፣ እንደ ኤሊ ያሉት ደግሞ አራት እግር ያላቸው ናቸው። በሌላ በኩል ጡት አጥቢዎች ሲፈጠሩ ባለ አራት እግር ሲሆኑ፣ እንደ የሌሊት ወፍ ያሉት ሁለት እግር ያላቸው ሆነው አጥቢና በራሪ የወፍ ዘሮች ናቸው። የሌሊት ወፍ እንደ አጥቢዋ አይጥ ጥርስ እንደ ዕንቁላል ጣይዋ ወፍ ደግሞ ክንፍ አላት። ስለዚህ፣ የዚች ፍጥረት ምድብ አሻሚ ነው። ሥርዓት አልበኝነት ተፈጥሮን የመልቀቅና ያለማክበር ምልክት ነው ይላሉ። አፈንጋጭነት ፍጥረትን መለቀቅ በመሆኑ የጎጅ ምሳሌ ሆኖ ይመጣል።

ከመኖሪያ ቦታ ምርጫ አኳያ ያለውን የፍጥረት ሁኔታ አስመልክቶ፣ ሁሉም ፍጥረት ሊኖር የሚችለው አንድም በየብስ አልያም በባህር ነው (ዲያቆን ብርሃኑ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከዚህ ውጪ መኖሪያ ሊሆን የሚችል ቦታ በነባረ ተፈጥሮ[33] ውስጥ የለም ብለው ያስረዳሉ። ነባር ግን፣ ከዚህ በተለየ አንዳንድ ዝርያዎች ሁለቱንም የመኖሪያ ክልሎች የመንቀሳቀሻ ቦታ አድርገው ይጠቀማሉ። እነዚህ ዝርያዎች አንድ ጊዜ ወደ ባህር ሌላ ጊዜ ወደ የብስ የሚመላለሱ ናቸው። የእባብ ዘር የሆኑትን ፍጥረታት ሁሉ ለዚህ ምሳሌ አድርጎ መጥቀስ ይቻላል በማለት አስረጅ ይመላሉ። ለምሳሌ፡- እባብ ውሃ ውስጥ ሲገባ መርዙ ይረክሳል፤ የብስ ላይ ሲያርፍ ደግሞ አድብቶና ጠብቆ ሰውን ይጎዳል ይሉታል። ሰው ሲያየው ራሱን መሬት ላይ ቀብሮ ያደፍጣሉ። ከተዘናጋ ደግሞ ተወርውሮ መጥቶ ይተናኮላሉ። ይህን ጊዜንና ሁኔታን አይቶ ማደሩን እያዩ ብልጥ ይሉታል። ራሱን ከጊዜና ከሁኔታዎች ጋር ማስማማት በአካባቢው ከብልጠት ጋር የተገናዘበ ትርጉም ያለው ነው።

ይህ ባሕርይ የሚገለጥባቸው ከፍ ብለው ከሚንቀሳቀሱት ይልቅ ምድር ለምድር በሚሳቡት ፍጥረታት ላይ ነው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በአካባቢው በብልጠት የሚጠቀሱት እንደእባብና ምስጥ ያሉት ፍጥረቶች ለመሬት ቅርብ የሆኑና መሬት ላይ የተነጠፉ ናቸው። ምስጥ የሰበሰበውን ሳይጠቀምበትና ለማንም ሳይሰጥ ያበሰብሰዋል። እንደ 'ግዴ'፣ 'ጉጉት' እና የመሳሰሉ የወፍ ዘሮች ከፍጥረታቸው ተለይተው በምሽት የሚመጡ በመሆናቸው የመጥፎ ገጠመኝ መልዕክተኞች ያደርጓቸዋል። ጉጉት ድመት መሳይ የሌሊት አሞራ ነች። ሌሊቱ ቀን፣ ቀኗ ሌሊት የሆነባት አፈንጋጭ በራሪ ፍጥረት ነች። ስትጮኽ ጎትት ትላለች ይላሉ። እሷ ከጮኸች በአካባቢው ሰው ይሞታል ይባላል(ደስታ ተክለወልድ፣ 1962፣ 228)።

በመሆኑም፣ እንደዚህ ያሉ ቅርጽ አልባና ለህግ የማይገዙ፣ ከአንደ ወገን የማይታሰቡ እንስሳት በብዛት አደገኛና ልዩ ሃይል ያላቸው ፍጥረቶች ተደርገው የሚታሰቡ ናቸው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ

[33] Cosmology የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚተካ ቃል ነው።

መቀያየርና አንዱን መርጠ አለመያዝ በፍጥረታቱ ጠባይ ውስጥ ያለመርጋትና ያለመጽናት አመል ተድርጎ ይታሰባል።

አንዱን ነገር አጥብቆ አለመያዝና በአንዱ ቦታ ላይ ረግቶ አለመኖር፣ ከዚያም ከዚህም ማለት በማኅበረሰቡ እሳቤ ውስጥ የወላዋይነት፣ የተጠራጣሪነትና የአቋም አለመስተካከል ምልክቶች ናቸው። እንደጊዜውና እንደሁኔታው ማደር የጽናት ችግር በመሆኑ፣ ክብርንና ጥቅምን የሚያስነጥቅና አድርባይ የሚያስብል አድራጎት ነው። ይህ ጠባይ ካለባቸው ፍጥረቶች ጋር መቀራረብ የተከለከለው ጠባያቸው እንዲወደድና አመላቸው እንዲከበር፤ መነካካቱም ከማህበረሰቡ ተጠይ እሴት ጋር እንድንላመድ ሊያበረታታ ይችላል የሚል ፍርሃት ያስተጋባል (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በመሆኑም፣ ነዋሪው ሰው አይጥ እጁን በድንገት ስትነካው ወዲያው ምንም ነገር ሳያደርግ የነካውን እጁን አንከርፍፎ እየሮጠ ከቄስ ዘንድ በመቅረብ ይባረካል። ሳይባረክ ሰው ሰላም አይልም። እህልም አይቆርስ (ቄስ እንስማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመነካካት የመጣ ንኪኪ በመታጠብ እንዲርቅ ከተባረከ በኋላ እጁን በአመድ ይታጠባል። አህያ ወይም ፈረስ ካዋለዱና ካጣፈሩ በኋላ ወዲያው ልብሳቸውንም ገላቸውንም በውሃ ያጥባሉ። ሰባት ቀን እስኪሞላቸው ወደ ቤተክርስትያን አይሄዱም። ሰው ሲያገኙም አይጨብጡም፣ እህል ባርከው ለሰው ቡራኬ አይሰጡም (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በመሆኑም፣ ልከኛ መሆን እንጅ መጉደልም ሆነ መትረፍ ተጠይ ሁነት ነው። ትርፍ መያዝ በአካባቢው ለውስጣዊ ጥንካሬ መላላትና አለመጠንከር ምሳሌ የሚሆን ተነዋሪ አመል ነው። ይህንን ጠባይ በዓላማና በመንፈስ አንሶና ሳስቶና ሳይጠነክሩ ለመታየት ምልክት አድርገው ይገልጹታል (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። መሟላት ወይም ልከኛ መሆን ግን ጠንካራ ሆኖ ከመቅረብ ጋር እየተገናዘበ የሚታሰብ ነው። ከአካላዊ ሁነት በሚታየው ተነስቶ ወደማይታየው፣ ከረቂቁ ወደ የማይጨበጠው እንድንሄድ ማሳያ ክስተት ሁሉ ይሆናል። በሐዲስ ኪዳን እንደዚህ አይነት ሰዎች በቤተክርስትያን እንዳይሾሙ

ስለመደንገጉ ይነገራል(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። እጅ እግሩ የጎደለ፣ ዐይኑ ማየት እንዲሁም ጆሮው መስማት የማይችል ለመስዋይት አይቀርብም በማለት ሁኔታውን ገልጸውልኛል። እንደዚህ አይነት ሰዎችን ቢወረውሩ አይስቱም፣ ክፉ ቢመኙ ያደርሳሉ እያለ ይፈሯቸዋል።

በነባሩና በተሰራው ህግና ምግባር ላይ ማመጽና አለመገዛት አካል አጓዳይ፣ ሰብዕና አቃዋሽ፣ ጤናን አዛቢ ነው። እጁ ወይም እግሩ የሰለለና ጎባጣ ወይም ድንክ ማንኛውም ዐይነት የዐይን እንከን ያለበት በተስተካከለውና ስርዓት በያዘው ዓለም ለረጋው ተቃራኒ፣ ለተሰራው አፍራሽ ነው ተብሎ ይታሰባል። የቀናው ንጹሕና ምርጥ ዘር መሆንን የሚጠቁም ሲሆን፣ ይህ ጉድለት ይህንን መልካም ነገር አሳናሽና ቀናሽ፣ አበላሽና መራዥ ተደርጎ ይታሰባል። ለምሳሌ፡- በቅሎ መክና የቀረችው በትቢታ ነው ይላሉ ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። እባብ እግሩን አጥቶ በልቡ የሄደው በተንኮሉ ነው። የጅብ አንድ እግሩ ያጠረው እንዲሁም የሌሊት ወፍ ከመሰሎቿ ተለይታ በምሽት የምትንቀሳቀሰው በእርግማን ነው። በመሆኑም፣ ጅብ የነከሰው፣ አይኑ የጠፋና የሚያነክስ እንዲሁም ጆሮው የማይሰማ ከብት ለእርድ አይሆንም። ይህ የሚባልበት ምክንያት የረከሰው ስለለከፈው፣ ተለካፊውም የረከሰ ተደርጎ ስለሚያዝ ነው።

ስለዚህ፣ የእንግዳ ክስተትን ወይም ያልተለመደን ነገር አከሳሰት ዝም ብሎ የተገኘ ነገር ነው አይልም። ክስተቱን ለመቀበል ያንገራግራል። እንግዳነት አንድም በአካልና በሁኔታ ካለው ጋር አለመመሳሰልና በጠባይና በመልክ አለመግጠም ነው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። እንዲሁም ከሚያውቁትና ከሚያስቡት ውጭ የሆነ ሥራን በማከናወን የሚከተል ሆኖ በመፈጠርና በመገኘት የሚመጣ ነው በሚል ይረዱታል። ሕግና ሥርዓት በያዘ፣ ርጋታና ስክነት ባለበት ቦታ ውስጥ ሥርዓት አልባ ሆኖ መገኘት እንግዳ ገጠመኝ ነው። ሰው ሁለት ዐይን ያለው ሆኖ በተፈጠረበት ዓለም ውስጥ ዐይን ይዞ አለማየት፣ እግር እያለው አለመሄድ፣ ጆሮ እያለው አለመስማት በአጠቃላይ ጎዶሎነት እንግዳ ክስተቶች ያደርጋቸዋል። በዚህ የተነሳ የአካባቢው ሰው፣ "አንድ

የብልት ፍሬ ያለው በሬ ከተወለደ ሊገፋኝ ነው፤ የልጁ ጥርስ ቀድሞ ባልተለመደው ቦታ ሲወጣ ምን ጉድ ሊመጣ ነው" እንደሚል ይነገራል (ቄስ እንስማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

7.2. መከላከልን ማጥበቅ

መሪጌታ ዲበኩለ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ፣ በሰዎች ሥጋዊ ባሕርይ ውስጥ በሁለተኛው ደረጃ የሚቀመጠው፣ እሳት ውክልናው "በሃይልና በጥንካሬ ነው" ይላሉ። ፈጣሪን ከሃሊነቱ ካልያዘው ትልቁንም ትንሹንም፣ ክፉውንም መልካሙንም አንድ ጊዜ ላጥፋ ቢል አያቅተውም ይላሉ። እሳትም ይህ የመለኮት ባህርይ በፍጥረቱ ውስጥ ምሳሌ ሆኖ የተገለጸበት ስለሆነ፣ ውሃ ካልከለከለው ቆላውንም ደጋውንም፣ እርጥቡንም ደረቁንም ልብላ ቢል ይቻለዋል። በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ማፍራት፣ መጎምራት፣ መጎርመስ፣ መጥናት፣ የልጅነት ማለቅ፣ መጋመር፣ መጎልመስ፣ መዳበር፣ በእሳት የሚወከል ነው (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ዘር ለመቀበልና ለማርገዝ የደረሰች፣ የጠናች፣ ልጅነቷ ያለቀ፣ ምኞት በሰውነት ውስጥ እየተቀጣጠለና እየጋለ ሄዶ አድጎ ብስለት ላይ ሲደርስ፣ ከእሳት ደረጃ ላይ ደረሱ ይባላል።

እሳት ብቅ ብቅ በማለት፣ በመውጣት፣ በመብቀልና በመዘርዘርና በማጎጥጎጥ የሚታይ ነው። ጉንስስ ሃሳብና ፈጠራ በነፋስ ውስጥ ተዘርቶ፣ በተስፋ ተጸንሶ፣ በምኞት ተወጥኖ በእሳት ተግባራዊ የሚሆን ነው (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ ሃይል ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የሚረዳ አቅም ነው ይሉታል። ጥሬን ያበስላል፣ ዘርን ያበቅላል፣ ምኞትንና ስሜትን ይቀሰቅሳል። ከየትኛውም መከራና ችግር ጋር ተጋፍጦ ለማሸነፍ የሚረዳ ጉልበት ነው በማለት ባህሪውን ይገልጹታል (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሊቀትጉሃን እሳት፣ "ውሃን ያፈላዋል፤ ነፋስን ያሞቀዋል፤ መሬትን ያቃጥለዋል" ይላሉ። በመሆኑም፣ ይህ ተፈሪና ተከባሪ የሆነው ኃይል በሥጋዊ ባሕርይ ውስጥ አንዱ ወሳኝ አካል እንደመሆኑ ህልውናው

በእያንዳንዱ ፍጥረት ውስጥ በልዩ ልዩ መንገድ ምልክት ሆኖ በቀዳሚነት ሲመላክት የሚታይ ነው።

የነዛምን አካባቢ ሰው ምልክትና ድንበር ባበጀለት፣ አቅንቶና አሰልጥኖ በያዘው፣ የመንቀሳቀሻ ቦታዬ ብሎ በሚጠራው በግዛቱ ውስጥ ይጠቅመኛል ብሎ ለምግብነት በሚመርጣቸው እንስሳት፣ ሰብሎች፣ ተክሎች፤ ለመድሃኒት በሚገለገልባቸው ዕፆች ውስጥ መሸፈኛ፣ መከላከያና መተግኛ ነገር አለባቸው ብሎ ይናገራል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። እነዚህ መከላከያዎች የአካል ክፍሎቹ በሚፈጠሩ፣ በሚወለዱና በሚበቅሉ ጊዜ ቀድመው በመውጣት አካባቢን የሚያቀኑ ሲሆኑ፣ በያዙት ጥንካሬና ኃይል ፍጥረቱን ጠብቀው የሚይዙ ናቸው። ከእነዚህ የአካል ክፍሎች መካከል ቀንድ፣ ፀጉር፣ የፊት እግር፣ ጥፍር፣ ቆዳ ወይም ቆርበት እና ቅርፊት ይገኙበታል። እነዚህ የአካል ክፍሎች ባሉበት ቦታ ክፉ ነገር አይቀርብም ይባላል። ክፉ ዐይን ያደረበትን አካል ለመፈወስ ወይም ለመከላከል በሚደረጉ መከራዎች ዋነኛ መድሃኒቶች ሆነው የሚመረጡት እነዚህ የሰውነት ክፍሎች ናቸው። የእነዚህ አካል ክፍሎች ምንነትና እሳቤ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ቀንድ

"ቀንድ በእንስሳትና በአራዊት ራስ ላይ እንደ ሰው ፀጉር የበቀለ መጋጫ የአካል ክፍል ነው" በማለት ይገልጹታል (መሪጌታ አይነኩሉ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እንደ ሥጋ ልል ያልሆነ ጠንካራ አጥንት ሆኖ ቀድሞ የሚወጣ ነው። ተደብቆ ቆይቶ ቀስ እያለ የሚያድግና ቀጥ ብሎ እንደ ጦር የሚቆም ጠንካራ አካል ነው። ይህ የሰውነት ክፍል፣ ፍጥረቱ ራሱን ከተለያዩ ጥቃቶች የሚጠብቅበት መሳሪያው ነው። ይህ አገልግሎቱ በብዛት የማሸነፊያ፣ የድል ማድረጊያ፣ የመታመኛና የመጠጊያ ምልክት አስደርጎ ያሳስበዋል። በዕውቀት የቀደሙ፣ በጠላት ላይ ድልን የተቀዳጁና ከአጋንንት ኃይል ራሳቸውን ነጻ ያወጡ ሲገኙ በቀንድ ይመስሏቸዋል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አቶ ተዘራ (2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) የእንስሳት ትልቁ መከላከያ ቀንድ መሆኑን ጠቅሰው፣ የሰው ቀንዱ ራሱ ስለሆነ፣ ሲጣላ የሚጋጨው

በእሱ ነው ይላሉ፡ በግና በግ፣ ፍየልና ፍየል፣ በሬና በሬ ሁሉ ሲጣሉ የሚገጥሙት በቀንዳቸው ነው፡፡ በሬ ሲጎፈላ በቀንዱ መሬት ይወጋል፤ በእግሩ ይቆፍራል በማለት የአካል ክፍሉን አገልግሎት ይዘረዝራሉ፡፡ የአካባቢው ሰው ጥንቃቄ በሚሹና መከላከል በሚፈልጉ አውዶች ውስጥ ይሽንን ኃይል በመጠበቂያነት ይጠቀምበታል፡፡ ያጋልጣሉ ተብለው በሚያሰጉ አጋጣሚዎች በተለያዩ መንገዶች ያስገባዋል፡፡

ለምሳሌ፡- ለመድሃኒት የሚያገለግሉ ዕፆች የሚቆረጡት በቀንድ ካራ ነው (መሪጌታ ሞላ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3 የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ልጆች በሚገረዙ ጊዜ ወደ አካባቢው ክፉ ዐይን እንዳይቀርብ የሚከላከሉት ቀንድ በማጨስ ነው (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ አውድማን ሰላቢ ይገባዋል ተብሎ ስለሚሰጋ፣ አባቶች 'በራይ ሲጥሉ' ክፉ ሃይሉን ለመከላከል ፈጦ ይረጫሉ፡፡ ፈጦ የሚቀርበው በቀንድ ዋንጭ ነው (አቶ ተዘራ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡

በትዛምን በተለይ በገጠሩ አካባቢ የሴት ሚዜ አይታወቅም፤ ሙሽራዋን የሚያጅቧት ወንዶች ብቻ ናቸው (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ሙሽራዋ በወንዶች ስለምትከበብ ብቸኝነት እንዳይሰማትና ተፈጥሮዋ ሲጠይቃት ፈርታ እንዳትቸገር የሚመራትና የምታማክረው እንድ ወንድም የሚሆን ሚዜ ያስፈልጋታል ይላሉ፡፡ ይህንን ሃላፊነት የሚረከብ አንድ ሰው ከሚዜዎች መካከል በሙሽራው አማካይነት ይመረጣል፡፡ ይሽ ልጅ ምስጢር የሚደብቅና የልቧን የሚፈጽም ስለሆነ፣ ቀረቤታው የእናትና የወንድም ያህል ነው ይባላል፡፡ በገለጠዋ ቀን እህቱ ብሎ ሊማት[34] ይዞ እንደሚቀርብም ይነገራል፡፡ ይሽ ሰው ሃላፊነት የሚቀበለው በመሀላ ተገዝቶ ነው፡፡

እምነቱን በቃለ መሃላ እንዲያስር ሲደረግ ማስማያ ሆኖ የሚመጣው የቀንድ ዋንጫ ነው (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ልጆች ክርስትና ሲነሱ የክርስትና አባት "ከልጄ ብለያት ወይም ብለየው ወንጌል ያጥፋኝ" ብሎ መሃላ የሚፈጽመው የልጁን አውራ ጣት እንደ ቀንዱ ይዞ ነው ይባላል (ቄስ

[34] ለስድሳ ሰው የሚበቃ መጠጥና ምግብ አዘጋጅተው በሥርግ ድግስ ላይ ከሰርጉ ባለቤት ጎን የሚቆምወገን

እንስማ፣ 2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ቄስ እንስማ ቀንድ እንደዚህ እንዲከበርና አገልግሎቱ እንዲበላ ያደረገው የኃይልና የጥንካሬ አምሳል ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው ይላሉ።

ይህ የሰውነት አካል በወሊድ ጊዜ ከሰውነት ብልቶች ሁሉ ቀድሞ የሚወጣ ወይም የሚገኝ ነው። ከብቶች ሲወለዱ ከአካል ክፍሎቻቸው ሁሉ ቀድሞ የሚወጣው የፊት እግራቸውና ራሳቸው ነው (አቶ ተዘራ፣2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከራስ ቀንዱ፣ ከእግር ደግሞ ጥፍሩ በአንጻራዊነት መቀዳደሙን ይመራሉ። ይህ ቀዳሚነት ከሁሉም የአካል ክፍሎች ፈጥኖ አዲሱን ዓለም የሚተዋወቅና የሚባርክ በመሆኑ፣ በተለየ በእሱ ላይ ጠንካራ አቅምና ጉልበት ያለ ሆኖ እንዲታሰብ አድርጓል። በፍጥረት ጊዜ ቀድሞ መምጣቱ በተከላካይነቱ አቻ የሌለው ያደርገዋል። ነገር ግን፣ ይህ የአካል ክፍል ተጣሞና ጦሮ ከወጣ የክፉ ዐይን ምሳሌ ያደርጉታል። በመሆኑም "ከከብት ጎዳ፣ ከሰው ቡዳ" ይባላል። ጎዳ በሬ ማለት ቀንዱ የተዘለሰ የሚዋጋ ለማለት ነው።

ራስ

በእንስሳትና በሰው አገኛኘት ከመቀመጫና ከኋላ እግር ሁሉ ቀድሞ የሚመጣው ራስ ነው። ይህንን ምስስሎሽ በማስተዋል ይላሉ አቶ ተዘራ አስማረ (2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ በዓለማዊው የመንግስት አስተዳደር በነበረው የሽመት ሥርዓት ውስጥ ቀዳሚውን ቦታ የሚይዙ ባለስልጣኖች ይጠሩ የነበረው ራስ ተብለው ነው ። በሃገራችን ታሪክ ራስና ንግሥና ትስስራቸው የቆዬ ነው። የንግስና ምልክት የሆነው ዘውድ የሚቀመጠው በራስ ላይ ነበር (2006 ዓ/ም፣ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ራስ የሚለው ቃል በሥልጣን የንጉሥ አቻ ነው። ርዕሰ ርዑሳን ሲባልም፣ በራስ ላይ ሌላ ራስ (ማለትም ቀንድ መትከል) ነው። ራስ ውክልናው በብዛት ከስልጣን ጋር ነው ይላሉ (2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህን አካል ሸፍኖ የሚይዘው ፀጉርም በኅብምን አካባቢ ተፈሪና ሃይል ያለበት አካል ተደረጎ የሚታሰብ ነው። ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948፣ 344) ፀጉርን፣ "የገላ ግር፣ የሥጋ ቡቃያ" ብለው ይበይኑታል።

የሰው ልጅ ሲወለድ እንደ ሰብል ሁሉ ቀድሞ የሚወጣው ፀጉሩ በመሆኑ ቡቃያ አለት፡፡ አንድም ራስ ላይ በመብቀሉ አንድም በማልበሱ ነው፡፡ ቀንድ ራስ ላይ በቅሎ እንደሚከላከል ሁሉ፣ የፀጉር አገልግሎትና ሥራ ሁሉ እንደዚያው ነው፡፡ መሬትን ማር ሸፍኖ እንደሚይዛት ፀጉሩም ራስን አልብሶ ይጠብቀዋል፡፡ ይኸ ክፍል ራስን ተግኖ በመከለሉ የራስ ጦር ወይም ቀንድ አስብሎታል (አቶ ተዘራ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ይኸን የራስ ጦር ሲላጩት[35] የመከላከል አቅም እየደከመ፣ ከተፈጥሯችን እየራቀንና እየሸሸን እንሄዳለን በማለት ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም፣ ተፈጥሮ በፍጥረት ላይ ያስቀመጠችውን መከላከያ እየተውን ከአንዱ የህይወት እርከን ወደሌላኛው የህይወት እርከን ሽግግር ስናደርግ ከቀዳሚነት የሚያሸሽ ሥራ እየፈጸምን እንሄዳለን፡፡ አንዱን ደረጃ አጠናቅቀን ሌላኛውን ስንጀምር ተፈጥሯችንን ለመምሰል ሁሉም ነገር በአዲስ እንዲበቅልና እንዲወጣ፣ ህይወት በአዲስ ኃይልና ጉልበት እንዲጀምር ለማድረግ እንሞክራለን ይላሉ፡፡ በመሆኑም፣ ሊተካ ሲል ቀሪው ለማለቁ መጨው ለመጀመሩ ምልክት የሚደረገው በፀጉር ልጭት ነው፡፡ ጥፍርና ፀጉር እየተቆረጠ መሬት ሲወድቅ የሚኖረው የሙታን የሚያቀጠቅጠው ደግሞ የትንሳኤ ሙታን ምሳሌ ይሆናል ይላሉ፡፡

ይኸ ሃሳብ በእጅጉ የጸና መሆኑን የምንረዳው እያንዳንዱ ሰው የነበረበትን ደረጃ ሲለቅ ፀጉሩን የሚላጨው የነበረበት ቦታ ማርጀቱን ወይም ማለቁን ለመጠቆም ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በአዲስ የሚበቅለው ፀጉር ለዚያ ደረጃ ጀማሪ መሆኑን የሚያሳይ ይሆናል፡፡ ስለዚህ፣ እየተላጨን በሄድን ቁጥር ከቀዳሚነታችን ለመራቃችንና ለየደረጃው ጀማሪ መሆናችንን ጠቋሚ ምልክት ነው (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡

በጎባምን ህፃን ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ፀጉሩን የሚላጨው በተወለደ በሰባተኛው ቀን ማለትም በመገረጥው ዕለት ዋዜማ ላይ ነው (ወ/ሮ ጥሩዬ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 9፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ኃይሉንና ጉልበቱን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያጓድለው በሚገረዝ ጊዜ ነው፡፡ ከተፈጥሯዊ ሰውነቱ ወጥቶ ባህላዊ ሰው

[35] በጎጃም ይህ የራስ መከላከያ የሆነው ጸጉራቸው ከርዳዳና የማያድግ ኩርንችት ከሆነ፣ እነዚህን የሰው ዘሮች ባርያ ይላቸዋል፡፡ ወገኑ አድርጎ አያያቸውም፡፡

መሆን የሚጀምረውም በዚህ ጊዜ ነው። የነበረበትን ደረጃ ለማጠናቀቂና አዲሱን እርከን ለመጀመሩ ቀድሞ የለበሰውን የራስ ልብሱን በልጭት አውለቆ አዲስ በማብቀል ይጀምራል። ክርስትና ሊነሳ ሲል በድጋሚ በዋዜማው ስለሚላጭ አዲስ የሚበቅለው ፀጉር ክርስትናን ለመቀበሉ ምልክት ይሆናል[36] (ወ/ሮ ጥሩዬ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 9፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ልጃገረዶች ሲያገቡ "ሳዱላ" ወይም "ድስት ቅርደ" ተብሎ የሚታወቀውን የልጭት አይነት ይላጫሉ (ወ/ሮ ጥሩዬ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 9፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሳዱላው ወይም ድስት ቅርዱ ድንግልናን ለማጣት ምልክት፣ ወደ 'ሰገን' ለመግባት መነሻ ነው ይላሉ አባቶች (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ምክንያቱም፣ ሳዱላ ከወጣች በኋላ ድንግል ናት ተብሎ ስለማይታሰብ ነው። በአካባቢው፣ ሰው የመሞቻው ቀን ደርሶ ሲደክም ቀድመው የሚላጩት ፀጉሩን ነው። በመሆኑም፣ በዚህኛው ዓለም ያለውን ጉዞ የመጨረሻው ነገር ፀጉሩን በመላጨት ይጠናቀቃል። ከዚህኛው ዓለም አልፎ ወደዚያኛው ዓለም የሚሻገረው ያለፀጉር ባዶውን ይሆናል። የሰው ልጅ ከተፈጥሯዊ ሰውነቱ እየወጣ፣ ወደተለያዩ ደረጃዎች ሲሻገር ምልክት የሆኑትን እነዚህ የየርከን ማስታወሻዎች ካወለቃቸው በኋላ ዝም ብሎ የትም አይጥላቸውም። የፊተኛው ወልቆ ወይም አልቆ በአዲስ ሲተካ፣ የኋለኛውን አንስቶ በክብር ያስቀምጣል።

ራሱን ከተላጨና ጥፍሩን ከተቆረጠ በኋላ ፀጉሩን ለቅሞ ከማገር ላይ ይሸጉጠዋል። ጥፍሩን ሰብስቦ ከሰው ሰውሮ ይቀብረዋል (አቶ ዘውዴ፣ 2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። አቶ ዘውዴ ይኸ የሰውነት ክፍል ጥንካሬውና ኃይሉ ያለበት፣ ሰብዕናው የተወጠነበት፣ የተፈጥሮ ባሕርይው ሥር ያለበት በመሆኑ፣ ሥር ጠምዛዦች ካገኙት ክፉ ነገር ይሰሩበታል እየተባለ ይነገራል በማለት ባህሉን ያስታውሳሉ (2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። በተለይ በቡድነት የሚለፈለፉ ሰዎች ፀጉርና ጥፍር ከተገኘ፣ የተጠቃውን ሰው አቃጥለው ቢያጥኑበት ያድናል ይባላል (አቶ ዘውዴ፣ 2004 ፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)።

---

[36] ከእናቴ ማኅፀን ጀምሬ ለእግዚአብሔር የተለየሁ ነኝና በራሴ ላይ ምላጭ አልደረሰም የራሴንም ጠጉር ብላጭ ኃይሌ ከእኔ ይሄዳል። እደክማለሁ እንደ ሌላም ሰው እሆናለሁ ብሎ የልቡን ሁሉ ገለጠላት (መጽሐፈ መሣፍንት፣)16፣ 17

በመሆኑም፣ በአካባቢው በቡድኑት የሚጠረጠር ሰው ካለ እንደምንም ብሎ የአካላቸው ወገ ያረፈበትን ልብስ፣ ጥፍርና ፀጉር ለማግኘት ሙከራ ይደረጋል (መርጌታ ሞላ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ነገር ግን፣ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮችን ነዋሪው ሰው አውጥቶ የትም አይጥላቸውም። ሰው ወደማይደርስብትና ማይንቀሳቀስበት ቦታ ዘወር አድርገው ይቀብሩታል። አንዳንዶችንም ይጥላቸዋል። ለምሳሌ፡- የወተት ጥርስ ቀድሞ የሚወጣ በመሆኑ፣ ወልቆ ለእህል ጥርስ ቦታ ሲለቅ፣ ወለቀ በቃ ብለው የትም አይጥሉትም። ጥርሱን አይጥ ወድቆ አግኝታ ከበላችው ተመልሶ አይበቅልም ስለሚባል፣ ማንም ከማይደርስበት ወይም ሊያገኘው ከማይችል ስፍራ አርቀው ይደብቁታል (ልጅ ስራዬ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 10፣ የነገረችኝ)። ልጆች ሲገረዙ፣ ከላይ የሚቧጠጠውን ሽለፈት ውሃ ባልነካው እራፊ ይጠቀልሉና ከቤት ውስጥ ጉበን ላይ ያንጠለጥሉታል። በአንዳንድ ቦታ ደግሞ በእበት ቀብተው ግርግዳ ላይ ይለጥፉታል (አቶ ዘመኑ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከብት ታርዶ ሥጋው ከመቀመሱ በፊት የምላሷን ጫፍ ቀድመው ቆርጠው ይቀብሯታል ይባላል። ፈሷ ከተቀበረች በአካባቢው ጭልፊት ዘወር አይልም ብለው ያምናሉ (አቶ ዘመኑ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ የአካባቢው ሰው ለአቅኝ ክብርና ውዴታ እንዳለው ጠቋሚ ነው። አረጀ ብሎ አይገፋውም፣ አገልግሎት መስጠት አቆመ ብሎ አውጥቶ የትም አይጥለውም።

የፊት እግር

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ 203) የፊት እግርን የግላ ክንፍ፣ መሥሪያው መሣሪያው፣ የግላ ቅጥያዎች፣ እድ፣ የእንስሳትና የአራዊት በማለት ይገልጹታል። አለቃ ደበበ (2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ሰኮናቸው[37] ድፍን የሆኑ እንስሳትን የኅብምን ሰው የሚያስባቸው ርኩስ አድርጎ ነው ይላሉ። ርክሰታቸው እነዚህን እንስሳት ከብዙ ተግባር ያርቃቸዋል ይላሉ። አርሶ

[37] በኅብምን ተልባን፣ የከብት የፊት እግርን፣ ጎመንን ጸሎተ በረድ ደጋሚ አይበላቸውም ይባላል። ጸሎተ በረድ የሚደግሙ ሰዎች ሙቀጫ ላይ አይቀመጡም። ወርችም አይበሉ (ጥላሁን ውሃቤ ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አደሮች አውድማ ላይ ወግዝ አያደርጓቸውም። በተለያዩ የእርሻም ተግባሮች አይሰማሩም።ሥጋቸው ለምግብ፣ ቆዳቸው ለማንኛውም ጥቅም፣ ጭራቸውን ለጅራፍ አያገለግልም (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሲወልዱ የሚወጣቸው ፈሳሽ ስለሚያረክስ፣ የነካው ሰው ለሰባት ቀን ከሰውም ከቤተክርስትያንም ይገለላል በማለት የሚጠሉ መሆኑን ያስረዳሉ።

ሰኮናቸው ክፍት የሆኑት ግን ወተታቸው ይጠጣል፣ ሥጋቸው ይበላል። በቆዳቸው ይተኛል። በእርሻ አገልግሎት ውስጥ አጋዥ ሆነው ይገባሉ። ሰኮናን የንጽሕናና የርክሰት መለያ ሆኖ እንዲመጣ ያደረገው መቆሚያና መተኪያ በመሆኑ ነው ይላሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ክፍት መሆንና አለመሆኑ የምረጫ መስፈርት የሆነው ለመተከል ወይም ለመንሸራተት፣ ተረጋግቶ ለመቆም ወይም ለመወላወል፣ ለመጽናት ወይም ለመንገራገጭ ምክንያት ስለሚሆን ነው።

ሰኮናቸው ክፍት የሆኑ እንስሳት በቆመበት ላይ ረግተው የሚጸኑና ቆንጥጠው የሚረግጡ በመሆናቸው አይወላውሉም፣ ቢገፏቸውም አይወድቁም በማለት ይገልጿቸዋል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ቆንጣጭነት በአቶ ብርሃኑ ገለጻ፣ "በአለበት ቦታ ለመተከል የሚረዳ ጉልበት በሚል ይተረጎማል። መተከል ወይም ባለበት መርጋት በሕግና በሥርዓት ለመግዛት ያለን ንጽሕና የሚጠቁም ነው። ሰኮና የቆመበት ቦታ አዳልጦ እንዳይጥልና ተደላድሎ ለማረፍ የሚያግዝ እንዲሁም ጸንቶ ለመራመድና ተተክሎ ለመግፋት አቅም የሚሆን ኃይል ነው(ዲያቆን ብርሃኑ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ ተግባር በአለበት ለሚረጉና ተፈጥሯቸውን እንደያዙ ለሚቀጥሉ አምሳል ነው ይባላል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ።

ሰኮናቸው ድፍን የሆኑት ግን ረግተው ለማይቆሙት፣ እዚያም እዚህም ለሚሉትና ለሚወላውሉት፣ በሥርዓትና በልማድ ለመገዛት ለማይጠነክሩትና ለማይተጉት ለሰነፎችና ለክፉዎች አምሳል ያደርጓቸዋል። በሰለጠነውና በለማው ባልደከመበትና ባልለፋበት ለመጠቀም ለሚስገበገቡት ምሳሌ የሚሆኑ ናቸው በማለት

ይገልጿቸዋል። ከማህበራዊ እሴቱና ልማዱ ፈቀቅ የማይሉትና ለወግና ለባህላቸው ተገዥ የሆኑት የተወከሉት በተሰነጠቀው ሰኮና ሲሆን ወላዋዮችና ግራ አጋቢዎች ደግሞ በድፍኑ ተመስልዋል(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ።

ሰኮናቸው የተሰነጠቁት ሳይወላውሉ በአቋማቸው ለሚጸኑት፣ በቀላሉ ተገፍተውና ተታልለው ወደ ሌላ ለመሄድ ለማይሞክሩት ሰዎች ምሳሌ ያደርጓቸዋል። መንሸራተት፣ ከዚህም ከዚያም ጋር አብሮ መንሳድ፣ ጸንቶ አለመኖር ተነዋሪና ተጠይ ባህርይ በመሆኑ፣ አለመብላትና መጸየፍ ከጠባዩ መሸሽ እንዳለብን በነውር አስተሳሰብ ተገልጸ ቀርቧል። በመሆኑም፣ የሰው ልጅ በተፈጠረበት ክልል መተከል እንዳለበት በአካባቢው አንጽሮተ ዓለም ውስጥ መኖሩን ይነግራል። አብዛኛው የኅብምን አካባቢ ህዝብ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ እንደመሆኑ የሚበላውና የማይበላውን የሚለየው ከመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝት ጋር አገናዝቦ ነው። ነገር ግን፣ ለክልከላውና ለፈቀዳው ትርጉምና ፍቺ የሚሰጠው ከራሱ ማህበራዊና ባህላዊ ልምድ ጋር አስማምቶ ነው።

ነገር ግን፣ ከሰውነት ክፍል ሁሉ መርጦ በእግር፣ ከእግርም መካከል ለይቶ ሰኮናን ለምን መስፈርት አደረገ የሚለው ጥያቄ ትኩረት የሚሰጠው ነው። በአንድ አካል ውስጥ ነገሮች ወይም አካሎች በአገኛኘታቸውና በአፈጣጠራቸው ጊዜ የሚኖራቸው መቀዳደም አንዱን ኃይለኛ፣ ጽኑና ጠንካራ ሌላኛውን ደግሞ ደካማ፣ ወላዋይና አቅመ ቢስ አድርጎ የማየት ልምድ በባህሉ ውስጥ የሚደጋገም ነው።

በአካባቢው እንደ ብኩርና ሁሉ ቀድሞ የተገኘ፣ የበቀለ፣ የተሰራ፣ የተፈጠረ፣ ከፊት መሆኛና መከበሪያ መንገድ ነው። በርግጥ በአገኛኘት ወይም በአመጣጥ ውስጥ ያለው መቀዳደም አንጻራዊ ነው፣ ለምሳሌ፡- ከሰውነት ራስ እንደቀደመ ሁሉ ከራስ ደግሞ ፀጉር ከፊት ይሆናል። ከክብት እግሮች የፊተኛው ሲቀድም ከእግሩም ሰኮናው፣ ከሰኮናውም ጥፍሩ በአንጻር ከፊት ሲሆን ይታያል። በመሆኑም፣ ምልክቶች ያሉባቸው ጫፎች፣ አቀማመጦችና ቅርጾች የባህሉ ፈርጦች ናቸው። በእነዚህ ነገሮች ላይ ክብርና ውዴታ እንደሚያርፍ በማሰብ ለእነሱ አምሳል ለሆኑ ነገሮች ሁሉ ልዩ እንክብካቤ የማድረግ ልማድ አለ።

እንስሳት በሚወለዱ ጊዜ ራስ የሚወጣው በፊት እግር ተሸፍኖ ነው (አቶ ተዘራ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይኸ የአካል ክፍል ከሌላው ሁሉ ቀድሞ አዲሱን ዓለም እንደ ራስ ሁሉ የረገጠ በመሆኑ አቅኝ ነው። በዚህ መልክ ከመጡት ፍጥረታት መካከል የተለየ ቅርጽ ያላቸው እነዚህ እንስሶች ንጹሕ ያደረጋቸው ስክነታቸውና ጽናታቸው ነው። ከአዲሱ ዓለም ጋር ቀድሞ ከሚተዋወቀው ከእንስሳቱ የእግር ከፍሎች መካከል እንደ ጸጉር ሁሉ ቀድሞ የታየው ደግሞ ሰኮናው ነው። ይህ የአካል ክፍል በሁሉም እንስሳት ላይ ያለው ቅርጽ ተመሳሳይ አይደለም። የቅርጽ ልዩነቱ እንስሳቱ ለሰው ልጆች የጠባይ ማስተማርያ ቅርጽ ያደርገዋል(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

መምረርና መጣፊጥ የጥንካሬና የጽናት ማሳያ

እማሆይ ማናዬሽ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ፣ "አባቶች በልጆቻቸው ላይ መልካም ያልሆነ ነገር ሲያልሙና መጥፎ ነገር ያጋጥማቸዋል ብለው ሲፈሩ፣ በሌሊት ይነሱና ግራዋ ዘንጥፈው ህልም ያለሙበትን ልጅ በተኛበት ይጠበጥቡታል" ይላሉ። መሪጌታ ሞላ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ ግራዋ የመጋኛ ጥሩ መድሃኒት ነው ይላሉ። ጠላ ሲጠነሰስ፣ ዕቃው ጣዕሙን እንዳይቀይረው መጠንሰሻውን ዕቃ በግራዋ ያጥቡታል (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ።

የጎጃም አምላክ ነው የሚሉት 'ሳምሴ' ኮስታራና ተቆጭ ነው ይባላል (ወ/ሮ ካሰች፣ 2004 ዓ/ም፣ ታህሳስ 29፣ ቀን የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ካሡ ሳምሴ ያዘዘውን ካልፈጸሙለትና ካላሚለለት፣ "እጅንና እግርን ይቆራርጣል፤ አስሮና ቀፍድዶ ያስቀምጣል፤ ውኃት ይተክላል፤ አጋልጦ ይሰጣል" እያሉ ይገልጹታል። ሳቅና ጨዋታ አይወድም ቁጡና ኮስታረ ነው ይሉታል። የጎዛምን ሰው "ሳቅና ቅዘን ቤት ያበላሻል" እያለ ይተርታል (ወ/ሮ ካሰች፣ 2004 ዓ/ም፣ ታህሳስ 29፣ ቀን የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በአካባቢው ቁምነገር እንጅ ቀልድ የጉብዝና መለኪያ ተደርጎ አይታሰብም። ይህ የሃገር አምላክ ለፍርድ ሲወርድ ቀድሞ የሚጋተው ግራዋ ነው። ፍርድ የሚጀምረው፣ "ሽምጥጦ ጠጥቶ ገረር ሲልለት ነው" ይላሉ። ከዚያ ያሻውን

ይናገራል። ቢለምኑት ይሰማል፣ ቢጠይቁት ይመልሳል እያሉ ይገልጹታል (ወ/ሮ ካሰች፣ 2004 ዓ/ም፣ ታህሳስ 29፣ ቀን የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ወ/ሮ ካሰች (2004 ዓ/ም፣ ታህሳስ 29፣ ቀን የተካሄደ ቃለመጠይቅ) የጎዛምን ሰዎች፣ " ለስላሳና ጣፋጭ የሆኑ ምግቦችንና መጠጦችን ሲመገብ ያዩትን ወንድ እንደሚንቁ ይናገራሉ። በምግቡ ውስጥም ኮስተር የሚያደርግ፣ የሚለበልብ ነገር እንጅ የሚለሰልስና አልጫ የሆነ፣ ሲጠጣ ወይም ሲበላ የታየ ሰው "ሴት ይመስል"[38] ይባላል። እንደ "አልጫ" እና "ገንፎ" ያሉ ምግቦችን ወንድ አይመገባቸውም። ጣፋጭ የሆኑ፣ ምላስን የማይዙ ከሆኑ የሴት ናቸው።

ምግብ እየበላ ውሃ የሚጠጣ ሰው ሲገኝ ፈተናን የማይቋቋም በቀላሉ የሚንበረከክ አድርገው ያስቡታል። አባቶች ይሽን ሲያዩ፣" ወንድ ልጅ የሚያጋጥመው አይታወቅም እንደዚህ አትልመድ" ይላሉ። በምግቦቻቸው ውስጥ እንደ ስናፍጭ፣ በርበሬ፣ ሚጥሚጣ፣ ጨውና የመሳሰሉ ኮስተር የሚያደርጉ ማጣፈጫዎችን እንደሚቀላቅሉ ትናገራለች። ጥሬ ሥጋ ሲበላ በሃሞት እንዲሁም ጥራጥሬ ሲቆረጠም በስናፍጭ ይለውሱታል። በምግብ ውስጥ ወጥ አይበዛም፣ ደረቁን ይበላል። አቶ ዜና (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ) አንዳንዴ እንዲያውም አባቶች ደፋር እንድትሆኑ የበግ ሃሞት ጠጡ ሁሉ ይሉን ነበር በማለት ያስታውሳሉ። እኛም ልጆቻችንን እንደዚሁ እያልን እናሳድጋለን በማለት ያስረዳሉ። በመሆኑም፣ በራስ ተፈጥሮ ለመከላከል እንጅ በሌላ መሣሪያ መታገዝን አይፈልጉም ይሏቸዋል።

መሳቅ መጫወት፣ ማማር መፈንጠዝ፣ መለሳለስና መሳሳት ብርታትን አጓዳይ፣ አዘናጊና አታላይ ሁነቶች ናቸው ይሏቸዋል (አቶ ይልቃል፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አቶ ይልቃል እንደሚሉት፣ የአካባቢው ሰው ልብስ ሲገዛ የደረጀውንና የሻከረውን ይመርጣል። ዕድሜ ያለ በጠንካራውና በሸካራው ውስጥ ነው ብለው ስለሚያስቡ የሳሳውንና የለሰለሰውን ግዥ አይፈልግውም ይላሉ። አቶ ቁሜም (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 21፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ኮስታራነትና አደብ

[38] ሴት በዚህ አባቢው ፈሪ፣ ድፍረት የሌለው አቅመ ቢስ የሚል ፍቺ ያለው ነው።

መግዛት የወንድነት፣ የንቃትና የማስተዋል መግለጫ ተደርጎ ይታሰባል ይላሉ። ምኞት ልፍስፍስ ያደርጋል ይላሉ።

መከራን ለመጋፈጥና ውጣ ውረዱን ለማለፍ ርሃብን መቅመስ፣ ውሃ ጥምን ማወቅ፣ መማረርንና መከፋትን ሁሉ ቀድሞ መለማመድ ያስፈልጋል ተብሎ ይታመናል በማለት ያስረዳሉ። በአካባቢው፣ መከራና ፈተና አከሳሰታቸው ድንገት ስለሆነ፣ ሁልጊዜ ንቁ መሆን ያስፈልጋል የሚል ፍልስፍና አላቸው። እነዚህ ችግሮቹ ሁሉ የሚወከሉት ደግሞ በሚመር፣ በሚለበልብና በሚቆመጥጥ ነገር ነው። ማህበረሰቡ ይህንን እሴቱን መመሰያ አድርጎ የሚያቆመው እንደ ግራዋ ባሉ መራራ ተክሎች ነው (አቶ ቁሜ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 21 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በአካባቢው ፍርሃት በጅብ ይመሰላል። ጅብ ጀግናና ደፋር ባለበት ቦታ አይቀርብም በማለት ጀግንነትን ለወንድ ይሰጣል። ጅብ በምሽት ከርቀት ሰው ሲመጣ ወንድ ከሆነ ይሸሻል፣ ሴት ከሆነች በጠረኗ ለይቶ ይተናኮላታል ይላሉ (አቶ ዜና፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። የሰውን ዖታ ከርቀት የሚለየው ደግሞ በሽታ ነው ይላሉ። "ወንድ ከሆነ ብረት ብረት፣ ሴት ከሆነች ማበለቻ ማበለቻ ትሸተዋለች" እያሉ ይናገራሉ። የጎመን ዘርን ለሴት፣ ብረትን ደግሞ ለወንድ ወላይ አድርጎ ያቆመው ባህላዊ እሳቤ ከፍርሃትና ከጀግንነት ጋር የተያያዘ እንደሆነ አቶ ተዘራ አስማረ ይመሰክራሉ (አቶ ተዘራ፣2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። "ማበለቻ" እናቶች ለምጣድ ማሰሻነት የሚገለገልበት ከጎመን ዘር የሚዘጋጅ የቅባት እህል ነው።

ይህ የእህል ዘር ለስላሳ፣ ተንሸራታችና ተሸለኽኪኪ ባሕርይ ያለው ነው (አቶ ይልቃል፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ ጠባይ በአካባቢው የአዳሪነትና የተልመጥማጭነት መለኪያ ተደርጎ ይታሰባል። ከነስድቡ፣ "የተልባ ስፍር" ይባላል። ጥንካሬንና ጽናትን የሚፈትኑ፣ ባለበት መርጋትንና ባመነበት መቆምን የሚያላሉ ክስተቶች ሲፈጠሩ መጠሪያቸው ይኸው ነው (አቶ ይልቃል፣2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ይህ ጠንካራነት፣ እንደሁኔታውና እንደነገሩ አለመሆን፣ ተለማማጭና የአዳሪነት ጠባይ አለመያዝ፣ ተብረክራኪነትንና በቀላሉ ተጣጣፊነትን ባህርይ አለማድረግ የጀግናና የወንድ መለኪያ ሆኖ ይወሰዳል (አቶ በቀለ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 14፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ጽናትና ወላዋይነት፤ ርጋታና አለመደላደል፤ ተንሸራታችነትና መካችነት እርስ በርስ እየተነጻጸሩ የሚሄዱበት መንገድ ነው። እንደተልባ ያሉ ለስላሳ ሰብሎች ግን ለማይፈለጉ ጠባዮች ወካዮች ናቸው።

ይህ የጥንካሬና የጽናት ባሕርይ የሚወከለው ደግሞ በ"ብረት" ነው። ብረት ይህንን ውክልና በመያዙ የጀግንነት አውድ ባለበት አብዝቶ ይገኛል። ጥቃትንና ፍርሃትን ስጋት በሆነባቸው አውዶች ውስጥ ተመራጭ ነው። ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ልጆች ክፉ ዐይን እንዳይቀርባቸው፣ ከተለያዩ የነሐስና የብረት አይነቶች የሚሰሩ ቀለበቶችና አምባሮች አልቦዎችን ከማተባቸው ጋር፣ በእግራቸውና በእጃቸው ያጠልቁላቸዋል። በአራስ ቤት ቢለዋ፣ ማጭድ፣ ወስፌ መጠበቂያ በማድረግ ትራስ ውስጥ ይቀመጣሉ። እንዲሁም በቀለበት መልክ እየተዘጋጁ በጣት ላይ ይጠለቃሉ። በእህል ጎተራ ውስጥ ሰላቢን ለማራቅ ከእህል መሃከል ይሸጎጣሉ (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ቆዳ ወይም ቁርበት

የራስ ማር ወጉር እንደሆነ ሁሉ፤ ቆዳ፣ ቆርበትና ቅርፊት ደግሞ ተፈጥሯዊ የግላ ልብሶች ናቸው (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ወጉር የሰውን፣ ቀንድም የከበቶችን ራስ እንደሚጠብቅ ሁሉ እንደ ቅርፊት፣ ቆዳና ቆርበት ያሉ ውጫዊ ልብሶች አካልን ከብርድ፣ ከሙቀትና ከቅዝቃዜ የሚከላከሉ መሸፈኛዎች ናቸው። ይህንን እያሰበ የአካባቢው ሰው ልብሱንና መኝታውን ሁሉ ቆርበት ያደርጋል ይላሉ። ሲንቀሳቀስ በእግሩ ጫማ አያደርግም። ቅዝቃዜ ሲሰማው የበግ ለምድ ይደርባል። የሚተኛው በጀንዲ (በላም ቆዳ) ነው (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ከሰው ሰራሽ ይልቅ በተፈጥሮ ልብስ መከላከል ይወዳል ይላሉ።

በጎላምን ያላገባች ሴት በወገቧ "ሚሪ" የሚባል ጠፍር ታስራለች። በድንግልና ያለች ሴት በሕግ መጠበቋንና በተፈጥሮዋ ያለች መሆኗ የሚታወቀው ይኸንን ስታደርግ

ነው። ተድራ ልጃገረድነቷ ሲቀር የድንግልና ምልክት የሆነው ሚሪ ይፈታና በምትኩ ሽማኔ የሰራውን መቀነት ትታጠቃለች (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። የአካባቢው ሰው፣ "መቀነት ባል ነው" የሚለው በዚህ ምክንያት ነው። አባቶችና እናቶች ዓለምን ንቀው ለመሰብሰብ ሲፈልጉ በቆብ ይደነግላሉ ይባላል (አቶ ተዘራ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በዚያን ጊዜ እንደ ደንግሎች ሁሉ እነሱም መቀነታቸውን ይፈቱና በምትኩ "ሰቅ" ወይም "አጽቅ" የሚባል ከጠፍር የሚዘጋጅ ቀበቶ መሰል ነገር መልሰው ይታጠቃሉ (አቶ ተዘራ አስማረ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በአካባቢው ድንግልና የቀዳሚነት መልክ ያረፈበት ያለመደፈርና እንዳለ የመቆየ መንገድ በመሆኑ ምልክት የሚሆነው በተፈጥሮው ልብስ ቆዳ ነው በማለት አቶ ተዘራ ይገልጹታል። በአካባቢው እንደ ድንግልና ያለ ፍጹም ንጽሕናና ክብር የለም ይባላል። በድንግልንዋ ያለች ሴት ተፈጥሮዋን ጠብቃ የምትገኝ በመሆኗ፣ የጥንካሬ መግለጫ መንገድም ነው። የንጽሕና ምልክት ተደርጎ እንዲታሰብ ያደረገው በቀዳሚ መልክ ሳይዳቀሉና ሳይበረዙ እንደነበሩ የሚገኙበት በመሆኑ ነው (አቶ ተዘራ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 17፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ጸታዊ ግንኙነቱ ሰው የያዘውን ንጹህ ሰብዕናና ተፈጥሮ የሚያቆይበት፣ ወደ ምድራዊ መባዛት፣ መዳቀልና መቀላቀል የሚገባበት፣ ተፈጥሮውን አክብሮ የሚያቆይበት መንገዱ ይሆናል። ቆዳን ከሥጋ፣ ልብስን ከገላ፣ ክዳንን ከጣራ፣ የሚለይ፣ የሚገፍና የሚነጥቅ ሰው የአራቆች፣ የገፋፊ፣ የቀማኛ፣ የወንበዴ አምሳል ተደርጎ የሚታሰበው በዚህ ነው (ደስታ ተክለወልድ፣ 1972፣ 296)፣ ክፉ ዐይን ይህንን መራቆትና መከፈት ተከትሎ ስለሚገባ አጋጣሚው አስጠቂ ነው ይሉታል ።

በመታቀቡና ጸታዊ ግንኙነትን በመጠበቁ ክብርንና ራስን በቀደመው ሁኔታ እንዲያቆይ፣ ራስን ሳይበርዝና ሳይከልስ እንዲሄድ የሚረዳ ዐይነተኛ መንገዱ ነው (አቶ ቅሩብ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። በአካባቢው፣ "እረከሰ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ፍቺ፣ ጠብቆና አክብሮ ይዞት የነበረውን ሰውነቱን አጓደለው" ማለት ነው (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ በፍጥረቱ

ውስጥ የነበረው ድንግልና ሲታጣ፣ ተፈጥሮው ከነበረው ቀዳሚ ጥንካሬና ብረታት ስለሚርቅ በክፉ ዐይን የሚጠቃበትን ዕድል የሚያሰፋው ይሆናል።

የአካባቢው ሰው ከጋብቻ ይልቅ ለዝምድና ዋጋ ይሰጣል ይባላል (መርጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)። ከጋብቻ ይልቅ ለምን ለመወለድ ክብር ትሰጣለህ ብለው ሲጠየቁት ባላባትነቴን ስለሚያስከብርልኝ ነው ይላል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)። ጋብቻ ቀስ በቀስም ቢሆን ከሌላ ጋር እየተቀላቀለ መሄጃው ስለሆነ፣ ዘሩ የያዘውን ጥንካሬ እንደሚሸረሽረው ያውቃል በማለት ያስረዳሉ።

የሰው ልጅ ተፈጥሮውን በመጀመሪያ የሚያጣው በጋብቻ ጊዜ ህጉን ሲያስደፍር ነው። በወሊድም ሲበክር ቆይቶ ደግሞ በመጨረሻ ይቆርጣል። ዝምድና የሚሞተው ግን ሰባት ቤት ላይ ሲደርስ ነው (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ግንኙነቱን በጋብቻ የሚያጠብቀው በሥጋ መዛመዱ ሲርቅበትና ቆጥሮ ማወቅ ሲሳነው ነው። በዚህ ጊዜ በክብሩና በማዕረጉ የሚመጥኑትን እየመረጠ በልዩ ልዩ መንገድ ዘመድ ያደርጋቸዋል። በዚህ የተነሳ ቅርበን ከሩቁ፣ ሥጋውን ከባዕዱ ይለይበታል። በትውልድ ሐረጉ ማን ከማን ጋር እንደሚዛመድ እያጠና ወገን ወገኑን እየለየ መያዝን ያከብርበታል።

መሪጌታ አይነኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ) ኃይልና ጥንካሬ አለ ተብሎ የሚታሰበው በቀዳሚ ተፈጥሮ ውስጥ በመሆኑ፣ ዕውቀትና ክብር ከትንሾች ይልቅ በዕድሜ በገፉ አባቶች፣ ከልጅ ደግሞ በወላጅ ይገኛል ይላሉ። በመሆኑም፣ ልጆች ዕድሜያቸው ለጋብቻ ሲደርስ የሚሆኗቸውን መርጠው የሚድሯቸው እንዲሁም፣ እንዲያርሱ ሲያደርጉም ቀድመው የሚተልሙላቸው እነሱ ናቸው በማለት ይናገራሉ። ካለ ወላጆች ምርጫ የሚታሰብ ምንም ነገር አይኖርም። አባቶች የሚመስላቸውን እንጅ ልጆች የሚወዱትን ማድረግ "ልጅ ለእናት ምጥ አስተማረች" ይሆናል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ መባረክ በመሬትም ሆነ በሚስት በአባቶች ነው። ልጆች ያውቃሉ ተብሎ ስለማይታመን አባቶች ሁልጊዜ ይመሯቸዋል።

ይህ ድንግልና በፍጥረቶች ውስጥ የጥንካሬና የኃይል ምልክት የሚሆነው በቆዳ፣ በቆርበትና በቅርፊት አማካይነት ነው፡፡ እነዚህ የገላ ልብሶች የተፈጥሮ ምልክቶች ናቸው፡፡ ይህ ተፈጥሯዊ ሃይል ሳይጣስና ሳይበሳ ወደ ውስጥ ስለማይዘለቅ ድንግልና በቆዳ ወይም በቆርበት ምሳሌ ይደረጋል (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4 ፣በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ይህ አካል ሲገሰስ ቀዳሚ አስገኝ የሆነችው ሴት ቀዳሚዋ ተከባሪ ስትሆን፣ መጀመሪያ የተወለደው በኽር ልጅ ከተከታዮቹ ቀድሞ በመገኘቱ እሱም ከተፈጥሮ ቀድሞ የተገኘው ይሆናል፡፡

በመሆኑም፣ ያ ፍጥረት ከተገኘ በኋላ ያንን ክፍል በመቆረጥ፣ በመላጨት፣ በመገፈፍና በመሳሰሉት መንገዶች ሊያነሳቸው ሲፈልግ፣ የዚያ አካል ጥንካሬና ብርታቱ እንደቀደመው አይሆንም፡፡ አብሮ እየቀነሰ፣ እየጠፋና እያጠጠ ይሄዳል ይላሉ መርጌታ አይነኩሉ፡፡ ተፈጥሯዊ ጉልበቱን በመውለድና በተለያዩ የሥጋ ፈቃዶች እያጣው ይሄዳል፡፡ ይኸ ደግሞ በደከመና በአጠጠ ነገር ኃይልና ጉልበት ለሚኖራቸው ክፉ ኃይሎች አጋላጭ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በድንግልናዋ ያለ ፍጥረት ከተፈጥሮ ባሕርይው የሚያስወጣ ነገር እሳካልፈጸመ ድረስ ለክፉ ዐይን ሊጋለጥ አይችልም፡፡ ነገር ግን፣ አንድ ሴት ክብረ ንጽሕናዋን ካጣች ከእርግዝናዋ ጀምሮ ወልዳ እስከምትነሳ ባለው አጋጣሚ ሁሉ በዚሁ መንፈስ የመያዝ ዕድሏ ሰፊ ነው፡፡

በመሆኑም፣ በድንግልናዋ ያለች ሴት ክፉ ዐይን እንዳይቆራኛት ከቤት ውስጥ ሊጥ አቡክታ፣ ከጓሮ ሄዳ የበቆሎ እሸት ሽልቅቃ[39]፣ የቅቤና የጨው[40] ቅል ከፍታ

---

[39] ለመስክ ሥራ ወደ ደብረማርቆስ ስሄድ የማርፈው ከእናትና ከአባቴ ቤት ነበር፡፡ እንደደረስኩ እንኳን በሰላም መጣህ ብለውኝ ምሳ ከበላን በኋላ ከጓሮ ሂጄና እሸት ሽልቅቅሽ አምጪና ጥበሽለት ተብላ ከወደ ቆላው የመጣች አንድ የዘመዳችንን ልጅ እናቴ ታገዛት አለች፡፡ ልጅቱ አይኔ ጓሮ ገበቹ ቦቆሎ አልሸለቅቅም ብላ ለእናቴ ትመልስላታለች፡፡ ከዚያም ፣ እናቴ ተናድዳ አንቺ ሂጅ ምን ያደርግሻል ብትላት፣ እማማ ልጅ ቦቆሎ አይቆርጥም ብላ አሻፈረኝ ትላለች፡፡ ከዚያ ምስጢሩ ገባኝና፣ እንዴ ተያት፣ የአንቺን የቅቤ ቅል ልጆችሽን ታስከፍቻለሽ፣ ስላት እህ እንደዚያ ነገሩ ብላ ሳቀች፡፡ ከዚህ የተረዳሁት በነገሮች መካከል ያለው የቅርጽ መመሳሰል አንድ ሆኖ ሳለ እያንዳንዱ የማህበረሰብ አባል የሌላውን ጠቅልሎ አለመረዳቱን ነው፡፡ በአንዱ አካባቢ ይበልጥ የሚከበር ሲኖር በሌላው አካባቢ ደግሞ ትርጉም የማይሰጠው አለ፡፡ ልጅቱ ቆለኛ ስለሆነች ከቦቆሎ ጋር ያላት ቅርበት እሴቱ ላይ ያላትን ዕውቀት እንዲያጠናክረው ሲያደርግ፣ እኛ ያደግንበት አካባቢ ደጋ በመሆኑ ይህንን ይዘት የምናውቀው በሌሎች ቅርጾች ነው፡፡

[40] ጨው በትህምን አካባቢ የበርበሬ ድልህ ነው፡፡ በመደበኛው አማርኛ ውስጥ ያለው ‘ጨው’ በዚህ አካባቢ የሚታወቀው ‘አሻቦ’ ተብሎ ነው፡፡

አታወጣም ወይም አታመጣም (ልጅ ስራዬ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 10፣ የነገረችኝ)። ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ልጅ መሬት አይባርክም (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ልጃገረድ የድፍድፍ ዕቃ አትከፍትም (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ የሚፈራው የልጆች ተፈጥሮ በምድራዊ ሥራዎች እንዳይረክስ ለመከላከል ነው ይላሉ። መባዛትና መራባት ባለባቸው ነገሮች አካባቢ እንዲገኙ በማድረግ ንጽናቸውን እንዲጓደል፣ መሬታዊ የሆነ ነገር እያታለላቸው ድንግልናቸውን እንዲያጡ ሊያተጋ፣ ሥጋዊ ነገር እንዲያታልላቸው ከዓለም ጋር እንዲለማመዱ ሊያበረታታ ይችላል ብለው ስለሚፈሩት ነው በማለት አቶ ተዘራ አስማረ ያስረዳሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ነገር ግን፣ የካህንንና የመነኩሴን ፀጉር ለመላጨት፣ ለመድሃኒት የሚሆኑ ዕፆችን ለመቁረጥና ሌሎች መንፈሳዊ ሥራዎችን ለማከናወን ከድንግል የሚመረጥ የለም ይባላል (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የአካባቢው ሰው ልጆችን ያልተጋነናቸው በሚል የሚገልጻቸው በዚህ ምክንያት ነው።

ከላይ ለቀረበው ማብራሪያ ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ቅርፊትን ማየት ይቻላል። በጎዛምን በውሃ ውስጥ ከሚኖሩ ፍጥረቶች መካከል ምግብ የሚሆኑት ቅርፊት ያላቸው ብቻ ናቸው። ዲያቆን ብርሃኑ ቅርፊት፣ "ፍጥረቱን ከቅዝቃዜ፣ ከብርድና ከመበስበስ የሚከላከል፣ ውጫዊ የአካል መሸፈኛ ጠንካራ ልብስ ነው" በማለት ይበይኑታል(አቶ ተዘራ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ይህ መከላከያ ያላቸው ፍጥረቶች ከሌላቸው በተሻለ ራሳቸውን ከጥቃት ይከላከላሉ ተብሎ ይታሰባል። በመሆኑም፣ የአካባቢው ሰው ለምግብ የሚሆኑ ፍጥረቶችን ሲመርጥ መከላከል ወደ እሚያበዙት ምርጫ ያደርጋል ይላሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።


ይህ የሆነው እያንዳንዱ ሰው ራሱን ሁልጊዜ ጠብቆና ተከላክሎ፣ ሚዛኑን ተቆጣጥሮና አስተውሎ መሄድ እንዳለበት የሚማርበት በመሆኑ ነው ይላሉ ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት መካከል ይበላቸውና የአካልና የሰውነት አጋር አድርጎ ይይዛቸው ዘንድ

የተፈቀዱለት ባለቅርፊቶቹ ብቻ ናቸው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ ጥበቃ፣ ከተለያዩ መርዛማ ነገሮች፣ ከክህደት፣ ከኑፋቄ፣ ከሃጢያት ራስን ጠብቆ፣ ሳይዘናጉና ሳይሰንፉ ተከላክሎ በመኖር ራሱን እንዲት ማቆየት እንደሚቻል የሚያስተምር ነው። እነዚህ ነገሮች ሰብዕናን አርክሰው፣ ከሰው ተራ አስወጥተው ለክፉ መንፈስ የሚያጋልጡ በመሆናቸው በአበላለ ሳይቀር ወጥ በሆነ መልኩ ሕጉን አክብሮ እንዲኖር ይማርባቸዋል ይላሉ።

መሪጌታ ሞላ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) በተክሎች የመከላከል ተፈጥሮ ውስጥ የመዳኛ መንገድ ሆኖ የሚታሰበው ራስን ከሚያጋልጡ ነገሮች መጠበቅ የሚለው ነው ይላሉ። በተክሎች ተፈጥሮ ውስጥ ራስን ማጋለጥ የሚመጣው በዕያዝ የፍሬ አያያዝ መንገድ ላይ ነው። ፍሬ የተክሉ ዘር የሚቀጥልበት በመሆኑ ፍሬው ለአደጋ ያለው መጋለጥ ፍጥረቱ እንዳይቀጥል በማድረግ በኩል ሚናው ላቅ ያለ ነው (መሪጌታ ሞላ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ተክሎች ፍሬያቸውን የሚይዙበት መንገድ መለያየቱም ጸንተው ለመገኘታቸው አስረጅ ነው።

ከተክሎች መካከል አንዳንዶቹ ፍሬያቸውን በግንዳቸው ላይ የሚቀጥሉ ናቸው። አንዳንዶቹ እንዲሁ ፍሬያቸውን ሳይሸፍኑና ሳይከልሉ ከላይ ከቅርንጫፎቻቸው ላይ በግልጽ አጋልጠው የሚተው ናቸው። በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ "የዘር ፍሬን ደብቆ መያዝ ወይም አጋልጦ መስጠት፣ ከሚያጠፉና ስጋት ላይ ከሚጥሉ ክፉ ኃይሎች ከመጠበቅ ወይም ከመጋለጥ ጋር ተያይዞ የሚተረጎም ነው በማለት መሪጌታ ይሄይስ ያስረዳሉ (2004 ዓ/ም፣ ጥር 17፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ይህ አቀማመጥ በአተረጓጎምና በአመሳሰል ሂደት ውስጥ ቁልፍ ነገር ነው። ሰዎች ተክሎችን መርጠው ሲይዙና ለይተው ለተለያዩ አገልግሎት ሲጠቀሙ ምርጫ የሚያደርጉት በዚሁ ክፍል ላይ ነው። "ፍሬያቸውን በሥሮቻቸው ደብቀው የሚይዙ ተክሎች፣ ከማንኛውም ጥቃትና ትንኮሳ ራሳቸውን ጋርደውና ተከላክለው ለሚይዙ ሰዎች ወይም ማኅበረሰቦች አምሳሎች ናቸው (መሪጌታ ይሄይስ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የዕያቸው ህይወት የመክሰም ወይም የማበብ፣ የመፍለስ ወይም የመራባት ቀጣይነቱ በዘሩ ላይ የተወሰነ በመሆኑ፣ ይህንን ዘር አስጠብቆ



በመሄድና አጋልጦ በመስጠት በኩል ያለ ጥንካሬ ወይም ክፍተት ጎልቶ መውጣትና መድከም ራስን ከማቆየትና በመንፈሶች ከመጠቃት ጋር ተጎጻጽሮ የሚገለጽ ነው።

በመሆኑም፣ ዘራቸውን ከተለያዩ መከራዎችና ችግሮች ተከላክለው፣ ህልውናቸውን የሚያስቀጥሉት ረጅም ዕድሜ ያላቸው ናቸው (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ምክንያቱም፣ ከሌላ ወገን የሚሰነዘር ጥቃት በቀላሉ ያጠቃቸዋል ተብሎ ስለማይታሰብ ነው። ዘራቸውን ለማፍለስና ህልውናቸውን ለማቋረጥ አቅደውና አልመው ለሚንቀሳቀሱ አካሎች ያላቸው ተጋላጭነት ዝቅተኛ ነው። ከአካል ክፍሎቻቸው ውስጥ ቀድሞ የሚገኘው ቀዳሚው አካሉ ስለሆነ፣ አካሉ ተጎድቶ ቢደርቅ እንኳ ዘሩ ስለማይጠፋ መተካካቱና መራባቱ ላይ ያለው ተጽእኖ ዝቅተኛ ነው። ስለዚህ፣ ይህ የተክሎች ባህርይ በማህበረሰብ በኩል ለመመረጥ ምክንያት ይሆናል።

የዘር ፍሬያቸውን አጋልጠው የተው ተክሎች ለተለያዩ አእዋፋት ራሳቸውን ያጋለጡ ናቸው ተብሎ ይታመናል (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ ተክሎች፣ "ራሳቸውን፣ ሃብታቸውንና አላባቸውን ሁሉ ለጠላት የተው ስለሆኑ፣ ዘራቸው አይረባም፣ ደፋሪያቸው ብዙ ነው" ይሏቸዋል። ጥሪታቸውን ስለማይሰበስቡና ሃፍረታቸውን ስለማይሸፍኑ ፍሬያቸው በተለያዩ አካሎች እየተጠረጠረ ስለሚባክን ለዘር አይበቁም። ለዘር ሳይተርፉና ራሳቸውንም ሳይተኩ የሁሉ መጫዎቻና ማላገጫ ሆነው ለሚቀሩ የብኩንና የከንቱ ፍጡሮች ምሳሌዎች ያደርጓቸዋል። ክፉ ዐይን ማደሪያ አድርጎ የሚጠቀምባቸውም እንደዚህ አይነት ተክሎች ናቸው(መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

የአካባቢው ሰው ልጆቹን፣ ከብቶቹና አዝመራው ለክፉ ዐይን እንዳይጋለጥበት በተቻለው አቅም እንደተክሎች ፍሬ ዘሩን መክተት፣ መደበቅና መሰወር ይወዳል (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አዝመራና ቡቃያው አፍርቶ ለምርት በሚደርስበት ጊዜ ከሰው ዐይን ከገባ ጫጭቶና በርብሮ ያልቃል፣ ፍሬ ሳይሰጥ መክኖ ይቀራል ተብሎ ስለሚፈራ ይሸሸጋል። በዚህ ምክንያት ደብቆና ከልሎ መያዝ ሲያቅተው ለዐይን ማረፊያ የሚሆን ነገር ከማሳው ውስጥ ይተክላል

ይላሉ። አሳሳችና አስቀያሽ የሆነ ምልክት በማድረግ ከጥቃት ሊጠበቀው ይሞክራል። የሰው ቀልብና ስሜት በእህሉ ላይ አርፎ እንዳይጎዳው በማሰብ ከአዝመራው መሃከል ረዘም ካለ እንጨት ላይ ሳቢ ህብር ያላቸውን ቀይ ሰማያዊና ነጭ ጨርቆች ይሰቅላሉ። ልጆቹን ሳቢና ማራኪ ቀለም ያላቸው ልብሶች ያለብሳል። በጥጆች አንገት ቃጭል ያንጠለጥላል ይላሉ።

7.3. ንጽሕናን ማክበር

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "እንስሳህ ከሌላ ዓይነት ጋር እንዳይደባለቅ በእርሻህ ላይ ሁለት አይነት ዘር አትዝራ"። ከሁለት ዐይነት ነገር የተሰራ ልብስ አትልበስ ይላል(ዘሌ፣ 19፣19)። የዘራኸው ዘርና ከወይኑ የወጣው አንድ ሆነው እንዳይጠፋብህ በወይንህ ቦታ ላይ ሁለት ዓይነት ዘር አትዝራ ይላል (ኦሪት ዘዳግም፣ 22፣ 9)። በነዛምን ደግሞ፣ "በሬና አህያ በአንድ ላይ ጠምደህ አትረስ" የሚል አባባል አለ (አቶ ዜና ደለለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 21፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። እርስ በርሱ የማይስማማንና የማይገናኝን ነገር መቀላቀልና መበረዝ፣ መከለስና መደባለቅ በዘር አበዛዝ ላይ ጥንካሬን ነሽና በረከትን አጓዳይ ነው ይላሉ። ለዚህ ምሳሌ ተደርጋ የምትጠቀሰው በቅሎ ነች። በቅሎ፣ ከአህያና ከፈረስ በመዳቀሏ መከነች እያሉ ይናገራሉ (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14 የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በአካባቢው ያለው የንጽሕና እሳቤ በዘር ጥራት ላይ ያለን ልማድ የሚነግር ነው። ነገሮች የራሳቸው ካልሆነ ጠባይ ጋር ሲነካኩ፣ ሲጨምሩ ወይም ሲዳቀሉ በቀዳሚነት ከያዙት መልክና ጣባይ እየራቁ፣ እየሸሹ ሄደው ወደመነባትና ያልተለመደና አጥፊ የሆነ አመልን ወደ መያዝ ይመጣሉ የሚል ነው። ለምሳሌ፦ ሰውን ከፈጠሩ ሥጋዊ ባህርያት መካከል አንዱ ውሃ እንደሆነ አባቶች ይናገራሉ(ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ውሃ እድፍን ከአካል፣ አካልን ከእድፍ የሚለይ መንጽሒ ነው ብለው ይገልጹታል። ከፍጥረት መካከል እንደውሃ የጠራና ንፁህ የሆነ ዘር የለም በማለት ያስረዳሉ። ውሃን ንጹሕ ያስባለው፣ ከመቀላቀል የጸዳና ያልተነካካ ተፈጥሮውን ጠብቆ የያዘ በመሆኑ ነው ይላሉ። በውሃ ውስጥ ሽታም ሆነ ጣዕም የሌለው በውስጡ የቀላቀለው ነገር ስለሌለ ነው (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ይህ የንጹህና ባሕርይ በቀዳሚነት ከያዘው ጠባይ የሚደክመውና እያደፈና እየቆሸሸ የሚሄደው እንደራሱ ካልሆነ ወገንና በደል ከተሞላበት ክፉ ዘር ጋር እየተቀላቀለ ሲሄድ ነው ይላሉ (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመቀላቀል የሚገኘው ክልስ ጠባይ ወይም "ዲቃላ" ዘሩ ሌላ ግብር እንዲይዝ ስለሚያደርግ፣ በውሃ የነበረው ጥራት እየተጓደለና እየተበረዘ ሄዶ ራሱን እንዲያጣ ሌላ ጠባይ እንዲይዝ ያደርገዋል የሚል ነው። እንደዚህ ያለው መቀላቀል ዘሩ ልዩ ጠባይ እንዲወርስ የሚያደርግና የተፈጥሮ ነገሩን የሚያስተው ነው ተብሎ ይታመናል።

በዚህ ጊዜ ዘሩ የነበረውን ጥንካሬና አቅም ስለሚያሳጣው ለተባይና ለአረም እንዲሁም በበቀለውና ባፈራው ላይ ህይወታቸውን ላደረጉት መጤ ተክሎች የሚያጋልጠው ይሆናል ብለው ያምናሉ። በዘር ውስጥ ያለውን ጥንካሬ በማላላት ዘሩ ሌላ ባዕድ ነገር እንዲጠጋው ያደርጋል። ይህ መነካካት ልዩ ጠባይ ተሳይ በመሆኑ፣ ተነዋሪና ተፈሪ ነው። ይህ እምነት፣ "የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ" በሚል መሀላ በአካባቢው ሲገለጽ ይሰማል (አቶ ዘመኑ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አለመቀላቀል

የአካባቢው ህብረተሰብ ግቢውን ሲያጥርና ከጓሮው ችግኞችን ሲተክል አጥር የሚያደርገው ስሚዛን (ሰንሰልን) እና ቦዝን ነው። ስሚዛና ቦዝ በሥራቸው ወይም በፍሬያቸው ሳይሆን በግንዶቻቸው የሚያቀጠቅጡት ተክሎች ናቸው (አቶ ይልቃል፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከግንዳቸው እየቆረጡ ሲተክሏቸው ይጽድቃሉ። በግንዶቻቸው የሚራቡት ሁሉ ሥራቸውም ዘራቸው አንድ ነው። ከአንዱ ሥር በተገኙ ግንዶች አማካይነት የሚረቡና የሚጸድቁ ናቸው ይሏቸዋል (አቶ ጫኔ፣ 2003 ዓ/ም፣ ሰኔ 5፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ በዘራቸው ውስጥ ሳይቀላቅሉ በአንድ ሥር ላይ እየበቀሉ ቀጥ ብለው ወደላይ ከፍ ከፍ የሚሉ እና መሬት ሳይስባቸው ወደ ላይ የሚያድጉት የቀላልነት ባህርይ የተላበሱትን የንጹሕ ዘሮች ምሳሌዎች ያደርጓቸዋል። እንደዚህ ቀጥ ብለው ያደጉት

ሌላ ባዕድ ነገር ሳያስገቡ በራሳቸው ጠባይ የሚኖሩ በመሆናቸው ነው በማለት ይናገራሉ።።

በመሆኑም፣ ሌላን ሥር ወይም ተተካይ ሳያስገቡ በራሳቸው ወገን በአንጓቸውና በአጽቃቸው ተቆርጠው እየጸደቁ፣ እየተባዙና እየተስፋፉ በአንድ እግር የሚራቡ ከተፈጥሯቸው ያልራቁ የዘራቸውን ይዘው የሚሄዱ ተክሎች አምሳል እያደረጉ ይገልጿቸዋል (አቶ ጥላሁን፣ 2003 ዓ/ም፣ ሰኔ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ዘሩ ካልተቀላቀለና ካልተበረዘ የራሱ ባህርይ ጠርቶ ስለሚወጣ ግብሩን የሚለቅ አይሆንም። የእነዚህን ተክሎች ምሳሌነት መርጌታ አይነኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ) ሲያስረዱ፣ የምድሩ ነገር የማይማርካቸው፣ ሰማያዊ ሃብት የሚገዛቸው፣ ከፍ ከፍ ማለት ለሚወዱ ምሳሌ ይሆናሉ ይላሉ።። ግንዳቸው ቀላልና ቀጭን ቅጠሎቻቸው ለስላሳና ስስ ስለሆኑ ከፍ ብለው ይወጣሉ።። በክረምት ቅጠላቸውን አርግፈው በበጋ የሚያቀጠቅጡ ለምለሞች ናቸው።። ጣዕማቸው የሚመር አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ዕውቀትን ይገልጣሉ እየተባለ ከሌሎች ዕፆች ጋር ተቀላቅለው የሚጠጡ ናቸው በማለት ጥቅማቸውን ይገልጹታል ።።

የዚህ ሃሳብ ዋና ቁምነገር፣ ተክሉ የሚጸድቀው በዘር ፍሬው ሳይሆን በግንዱ መሆኑ ነው።። ግንዱ ያንድ ወገን ከሆነ ጠባዩን አይለቅም። እነዚህ ተክሎች አፍርተው ሊያረጁ ሲል ነጭ አበባ ያወጣሉ።። አበባውን ተከትሎ ድርቀት ይከተላል።። ሊደርቁ ሲል አበባ ማውጣታቸው፣ ከደረቁ በኋላ ደግሞ መልሰው ማቆጥቆጣቸው ከአካባቢው ማህበረሰብ አንጽሮት ጋር የሚስማማ ትርጉም ይይዛል።። ከሞት በኋላ (ነጭ አበባ የማውጣት ምስጢሩ) ህይወት መኖሩን፣ ረግፎና በስብሶ አለመቅረትን ምሳሌ የሚያደርግ ነው (መርጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አንድም ነጭነት ራስን ተክቶ ዘላለም ህያው ሆኖ ለመኖር ምሳሌ ይሆናል።።

ስለዚህ፣ ምርጥ ዘር በሆኑ ነገሮች ውስጥ ይህ የቀዳሚ ንጽሕና ምልክት የርቀትና ከፍ ከፍ የማለትን ምስጢር ተላብሶ ለሚገኘው ነፍስ መኖሩ አሳይ ነው።። ሁሉም ዘር ቀዳሚ ከሆነው አካሉ በያዘው እርሾ ስለሚለያይ ሁሉም ፍጥረት እኩል ክብደትና ክብር ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም። በአንዱ የእህል ዘር ውስጥ እንኳ

በዘሩ መለያየት የተነሳ አንዱ በገዙ ሊመረጥ ሌላው ደግሞ ተመርጦና ተለይቶ ሊጣል ይችላል። ስለዚህ፣ ከዘሩ መካከል የተሻለውን መምረጥና መለየት የተለመደ ነው።

ለምሳሌ፣ በጤፍ ውስጥ ያለውን ልማድ ብናይ በዘሩ ውስጥ በልዩ ልዩ ስሞች የሚታወቁ የተለያየ መልክ፣ አበባዝና አፈራር የሚያሳዩ እንደ "መሪ"፣ "መርጅ"፣ "ዝንጅርዬ"፣ "ዳቦ"፣ "ድብል አብሸ"፣ "አፈሳ"፣ "ዳዋ" እና የመሳሰሉ የዘር አይነቶች አሉ። ከእነዚህ መካከል "መሪ" የሚባለው የጤፍ ዘር በማሳ ውስጥ ከሌላው ሁሉ በተለየ ከፍ ብሎ የሚታይና ፍሬው ጎላ ጎላ ያለ ቀላል የእህል ዘር ነው። ይህ የጤፍ ዘር ከሌሎች በተለየ እንዲያድግ ያደረገው፣ "ዘሩ በተለየ በጥንቃቄ ተይዞ የሚጠበቅ በመሆኑ ነው" ይላሉ (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የአካባቢው ሰው በማሳው ውስጥ ይህንን ዘር በቅሎ ሲያገኘው፣ ለዘር ይሆናል ብሎ አጭዶ ለብቻ ያስቀምጠዋል። ያንን ዘር በመሬቱ ላይ እያባዛ ያራባዋል (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህን ዘር በተለየ ያስመረጠው ነገር ደግሞ ፍሬ እያያዙና ቁመናው ነው። ከሌላው የጤፍ አይነት ሁሉ ጎለቶና ቀድሞ ከፍ ብሎ በመገኘቱ ነው።

በእርግጥ አንዳንድ ማሳዎች በተለየ የሚፈልጓቸው የዘር አይነቶች አሉ። ሁሉም ማሳ ለሁሉም ዘር የትኛውም ቦታ በእኩል ላይመች ይችላል። ለተወሰነው "ዘር" ብቻ የሚሆን መሬት እንዳለ ሁሉ ለተወሰነ መሬት የሚሆንም "ዘር" አለ (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ "የመሬቱ ኮክብና የዘሩ ኮክብ" እንዲገጥም አድርጎ በማጋባት የዘሩን ንጽሕና አስጠብቆ ማስኬድ ላይ ጥንቃቄ አለ። ዘሩ አምሮ ለዚያ ቅንጣት የሚሆን ምቹ ዘር ተቀባይ እስካላገኘና ያረፈበት ቦታ እስካልተመቸው ድረስ ዘሩን ላያወጣ ይችላል ይላሉ። መሬቱም ምን የለማና የፋፋ ቢሆን፣ የሚመቸውን ዘር እስካላገኘ ድረስ ላይበቅል ይችላል። ለነጭ፣ ለዳቦ፣ ለሠርገኛ ጤፍ የሚሆነው መሬት ልዩ ልዩ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው ይባላል (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በመሆኑም፣ የአካባቢው ሰው የመሬቱን ጠባይ እያየ የሚዘራውን ዘር አስቀድሞ ይለያል። ከአመረተው ላይ የዘሩን ቀንሶ ሰቅሎ ቀሪውን ለፍጆታው ያደርጋል።

ነገር ግን፣ "ምን ቢቸግረው ዘሩን አይሸጥም፣ ለዘር ያለውንም አይበላም" ይሉታል (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ። ከእነ ተረቱ "ዘር በዱቄት ነው" (እማሆይ ማናዬሽ፣ 2004 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በጣም የሚያከብረውና የሚወደው ከሆነ ግን ሊያበድረው ይችላል። በዓመቱ ግን ተመሳሳዩን ዘር ይተካለታል እንጅ ወስዶ አያስቀርበትም። ይሽን ቢያደርግ፣ በመዳቀሉ የተነሳ አቅምና ጥንካሬ እያጣ ስለሚሄድ፣ ከነበረው ተፈጥሮ እያሸሸው ይሄዳል፣ ከሌላ ጠባይና አመል ጋር የሚተዋወቅ ይሆናል። ይህንን መድከም ተከትሎ የሚመጣው ደግሞ ክፉ ዐይን ነው።

ከመዳቀል ጋር ተያይዞ ይሽንን ጉዳይ በምሳሌ ለማብራራት ቀጥሎ የሚቀርበውን ማስረጃ ማየት ይቻላል። የአካባቢው ሰው ሲሰረቅ፣ ሲጣላ፣ ሲበደል የፍትህ ችግሩን የሚቀርፉለት ዛሮች ናቸው ይባላል (ወ/ሮ ካሰች፣ 2004 ዓ/ም፣ ታህሳስ 29፣ ቀን የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ መንፈሳዊ ሃይሎች፣ "የተጣላን ያስታርቃሉ፤ የዋሸን ያሳምናሉ፤ የሰረቀን ያጋልጣሉ" እያሉ ያከብሯቸዋል። ነገር ግን፣ ከፍትህ አሰጣጥ ልማዳቸው እየተነሱ ዛሮችን፣ ዲቃላና አባት ብለው ይመድቧቸዋል (ወ/ሮ ካሰች፣ 2004 ዓ/ም፣ ታህሳስ 29፣ ቀን የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ዲቃላ የሚሏቸው ከግዛቱ ውጭ የሚመጡትን፣ የበረሃዎችን ነው። እነዚህ ዛሮች የመጡበት ስለማይታወቅ አይታመኑም ይሏቸዋል (አቶ ጫኔ፣ 2003 ዓ/ም፣ ሰኔ 5፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። "በፍርድ ሰዓት ይዋሻሉ፤ ይቀላብዳሉ። ፌዝና ቀልድ ይቀላቅላሉ። ርዝራዦች ጭማቂዎች ናቸው" እያሉ ይንቋቸዋል። አባታቸው አይታወቅም። መሰረት መሰረቶች ግን በአንደበታቸው ሀሰት አይነገርም። ቀልድና ፌዝን ይጠላሉ እያሉ ያሞካሿቸዋል (አቶ ጫኔ፣ 2003 ዓ/ም፣ ሰኔ 5፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አንዳንዶቹ እንዲያውም "የእነ እገሊት ዘሮች፣ ቀጥ ያልን ባላባቶች" ነን እያሉ ይናገራሉ ይባላል (ወ/ሮ ካሰች፣ 2004 ዓ/ም፣ ታህሳስ 29፣ ቀን የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ ቢዋሹ ዘራቸውን ያሰድባሉ፤ ቢያጠፉ ወገኖቻቸውን ያስወቅሳሉና ለውክልናቸው ይጨነቃሉ (መሪጌታ ሞላ፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ። የጠራ ዘር ካለው ለማህበረሰቡ ደንብና ሕግ ተገዥ ነው። በፍርድ ሰዓት ሲቀላምድና ሀሰት ሲያወራ ከአንጋገሩ ለይተው ክብርና አመኔታ

ይነፍጓቸዋል። ከዚያ በኋላ ሰርቀው ቢይስፈራራቸው አያምኑለትም፣ ገድለው ከፊቱ ይክዳሉ። አያውቅም ብለው ይንቁታል፤ ምንም አያደርገኝም ብለው ይደፍሩታል (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ። በእነሱ ፍርድ ሰው ከሰው ይጋደላል። ክፉዎች፣ ውሸታሞችና ቀላማጆች የክፉ መንፈስ ዘሮች ናቸው ይሏቸዋል።

የእናት አባት አምላክ ያረፈባቸው ሰዎች በንግስ ቀናት መንፈሱ በሚወርድበት ቀን ቁጭ የሚሉት ቀይ ጃኖ ጥለት ሸማ፣ መቀነት፣ ወይም ቀሚስ ለብሰውና ደርበው ነው (ወ/ሮ ንግስቱ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 10፣ ቀን የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ የክብር ሸማ ሲሰራ ብዙ ጥንቃቄ ተደርጎ ነው። እንደተራ ልብስ ማንም አይሰራውም፣ ያላረጠች ከባላባት ወገን የሆነች ሴት የፈተለችው ተመርጦ፣ ድርና ማጉ እርስ በርሱ መሆኑ ተረጋግጦ ነው። ከፋብሪካ የሚገኘው ድር የአገሬው ስላይደለ አይመረጥም። ለመስዋይት የሚሆነው ዶሮ ባለ ድርብ ኩተቱ መሆን አለበት። ነጠላ ኩተቱን መጪ ነው፣ ያገሬው አይደለም ይሉታል። ነጣላነት ወይም አለመደረብ በአባት ወይ በእናት የጎደለ መሆኑን ስለሚያሳስብ ነው (ወ/ሮ ንግስቱ ሙሉቀን፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 10፣ ቀን የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ ሁሉም ነገር ከሌላ ነገር ጋር ሳይቀላቀልና ሳይበረዝ እርስ በርሱ በሆነ ነገር እንዲመራ ጥንቃቄ ይደረጋል። በመሆኑም፣ ንጽሕናውን የሚጠብቁት ከሌላ ጋር እንዳይቀላቀል በማድረግ ነው። በዚህም ክልሱ ጠባይ የሚያስከትለውን ድክመት በመከላከል ክፉ ዐይን የሚመጣበትን ዕድል ለማጥበብ ይሞክራሉ።

የዕፅ እግር የሚያውቁ ባለሙያዎችም ዕያችን ከቆረጡ በኋላ ከሙቀጫ ላይ አይቀመጡም። የተቆረጠው ዕፁም ከቤት አይገባም። ሁለቱም የመድሃኒቱን የፈዋሽነት ኃይል ያሳጣሉ ይባላል (መሪጌታ ይሄይስ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በሙቀጫ የማይወቀጥ የእህል ዘር ስለሌለ እያንዳንዱ እህልም በዘሩ ውስጥ ልዩ ልዩ ጸባይ ስለሚኖር መነካካቱ ይቀይረዋል በሚል ነው። የዕፁ ዘር በተለየ ቁጥር ባህርይውና ጠባዩም በዚያው ልክ ይበዛል ከሚል ስጋት ነው(መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ከማይፈለጉ ኃይሎች ጋር በመነካካት የሚፈጠርን መርከስ መጠበቅ የሚቻለው ከዚያም ከዚያም ጋር ማቀላቀሉንና ማነካካቱን በማስቀረት ብቻ ነው (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ)። ለምድራዊ ሃብት በሚደረግ ገቢር ውስጥ የመንፈሳዊ ኃይል ወኪል የሆነውን ማነካካት አንዱ ሌላውን ስለሚያሰንፈው፣ ተፈላጊውን ውጤት ማግኘት አያስችለውም።

የጎዛምን ደብተራዎች ዕያችን ከተቆረጡ በኋላ የበሰለ እህል ካለበት ቤት ውስጥ አያስገቧቸውም። ለንስሐ የሚያገለግለው ጠበልም እንዲሁ እህል ከሚበስልበት ቤት ውስጥ አይገባም። ሰዎች ጠበል ወደ ቤት ሲያመጡ የሚያስቀምጡት ከጥግ ነው(መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አንድ አስከሬን ፍትሃት ከተደረገለት በኋላ መልሶ ከቤት ውስጥ ሲገባ፣ ማጠብ ማቆሸሽ ነው ይላሉ (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ቤት የዓለም ምሳሌ ነው ይላሉ። ዕፅ ቆራጩም ሲቀምም እህል አይቀምስም። መድሃኒቱን የሚወስደው ታካሚም የሚጠጣው በባዶ ሆዱ ነው። ይህን የሚያደርገው የዕፁን ጥንካሬና በቀዳሚ ባህርይው ውስጥ ያለውን ግብሩን ጠብቆ ለማቆየት ነው ይላሉ መሪጌታ ሞላ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እያንዳንዱ ነገር ሌላ ተፈጥሮ ካለው ነገር ጋር በተቀላቀለ ቁጥር እንደ ነፋሱ ሁሉ ከቀዳሚነት ጠባዩ እያራቀው ስለሚሄድ የፈዋሽነት አቅሙ ይዳከማል። ለክፉ ነገርም ያጋልጣል ይላሉ።

በዚህ አውድ ውስጥ ቆረጣው ዋነኛ ሆኖ ለመቁረጫነት የሚውለው ነገር ብረት የመሆኑ ጉዳይም ከዚሁ ጋር አብሮ ተያይዞ የሚታሰብ ነው። በእያንዳንዱ ንዑሕ ዘር ውስጥ ሌላ ተፈጥሮ ያለው ነገር በተቀላቀለ ቁጥር ያ ፍጥረት የያዘውን ሃይልና ጥንካሬ፣ ጠባይና መልክ እያጣ እንደሚሄድ አሳይ ምልክት ነው። ስለዚህ፣ ዘሩ በንዑሕ ጠባዩ ማንጻቱን እንዲፈጽም ከሌላ ጋር ከመነካካት መጠበቅ ይኖርበታል። ይህ ንጽህና የሚገኘው በዘሩ ቀዳሚ ጠባይ ውስጥ ነው (ሊቀትጉሃን፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ የተገኘ)። ነገሮችና አካሎች የያዙት ቀዳሚ ነገርና ባሕርይ ዘግይቶ ከሚመጣው የተሻለ ልምድ ያለው ተደርጎ ስለሚታሰብ፣ የዘገየው ደግሞ ሃይልና ጉልቡቱ በንጽጽር ያነሰ ሆኖ የሚገመት በመሆኑ፣ ዘሩን አጥርቶ

በመያዝ ላይ ምልክት አለ። ለውጥ በብዛት ከተፈጥሮ መራቅ በመሆኑ፣ በቅርጽ፣ በጥንካሬ፣ በመጠንና በአይነት መቀነስና መጉደል ይከተላል። ስለዚህ፣ ቀዳሚነት የማንኛውም ነገር ወይም ተፈጥሮ እውነተኛ መልኩ ነው። ለቅድሚያ ዋጋ በሚሰጠው በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ ንጽሕና የሚገኘው የፊቱን በማክበር ነው።

7.4. ታዛዥ መሆን

በኑዛዜን ሰዎች ቀዳሚ ባህርይ ውስጥ ያለው ሌላኛው ነገር ታዛዥነት ነው። በአካባቢው፣ "ለመገራት፣ ለመቅናት፣ ለመልዘብና ለመልመድ ያለ ምቾት የሚገለጸው በታዛዥነት ነው"። መታዘዝ የተወከለው ደግሞ በመሬት ነው (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። መሬት የሰጧትን ሁሉ የምትቀበል፣ የዘሩባትን የምታወጣ ነች (ቄስ እንስማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ሁሉንም በየዓይነቱ ታበቅላለች። ሁሉም ነገር ለምልሞና አብቦ፣ በሥሩም፣ በግንዱም እንደየወገኑ ዘሩን ይዞ ይበቅልባታል። በዚህ የተነሳ መሬትን በዱላ ወይም በጅራፍ ሰው ሲገርፍ ሲያዩ ይገስጻሉ። መሬትን ለመቆፈር ሲዘጋጁም ሳይባርኩ አይጀምሩም። ያለ ሰዓትም ተነስተው ለመቆፈር አይሞክሩም (አለቃ ደበበ፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 21፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በመታዘዝ እሳቤ ውስጥ "ለጋ" መሆንና አለመጠንከር ዋና ጉዳይ ነው። የእነዚህ እሳቤዎች መነሻ ራስን ከማህበራዊ ጥቅምና ከጋራ እሴት ዝቅ አድሮ ከማስገዛት ጋር ተነጻጽሮ የሚታሰብ ነው። የግልን ምቾትና ደስታ መጥኖ ከማስኬድ ጋር ተስማምቶ የሚቃኝ ነው (አቶ ጋሼ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 7፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። ይህን እሳቤ የአካባቢው ሰው "ቀና" ወይም "ገር" መሆን በሚል ይገልጸዋል። ገርነት ወይም ቀናነት አንድም በዚህ እሳቤው ለወዳጅና ለወገን መቆርቆርን፣ አስቦና አቅዶ ለመጉዳት አለመዘጋጀትንና ቂምን ቋጥሮ ለማጥፋት አለመሞከርን ሁሉ ያስታውሳል (አቶ ጋሼ ህብስቴ፣2006 ዓ/ም፣ ህዳር 7፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)።

ለጋነት በኑዛዜን አካባቢ የታዛዥነት መገለጫ ነው። በለጋነት ውስጥ ገራምነት አለ። ገራም የሆነ ሰው የጠየቁትን የሚያደርግና የነገሩትን የሚቀበል ነው። ለትብብርና ለመተጋገዝ አለመወላወል፣ ሲጣመም ለመቅናትና ሲዘም ለመገራት

ምቹ መሆን በሚል ይገለጻል። ሰው አሜን ብሎ ሲቀበል፣ የሰጡትን ሳያንገራግርና ሳይጠይቅ ሲፈጽም ታዛዥና ትሁት ሆነ ይላሉ (አቶ ፈንታሁን፣ 2004 ዓ/ም፣ ነሐሴ 25፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የተጠየቀውን የሚፈጽም፣ ሰው የሚለውን የሚሰማ፣ የዘሩበትን የሚያበቅል "ሲጠሩት አቤት፣ ሲልኩት ወዴት" የሚል፣ የሚጠበቅበትን ግዳጅ ሳይጠይቅ የሚፈጽም ለፈለጉት ጉዳይና ተግባር የቀና፣ ያልገነገነ፣ ያልጠነከረ፣ ለሰው ሃሳብ የሚያድር፣ ለምን ብሎ የማያትት፣ የራሱን ጥቅም የማያስቀድም፣ በራሱ መንገድ የማይጓዝ፣ የነገሩትንና ያዘዙትን የሚቀበል ሆኖ ሲገኝ፣ ትሑት፣ ታዛዥ ቅን ይሉታል። ለዚህ ታዛዥነት የሚሰጠው የክብር ስም ደግሞ የዋህ ወይም ቻይ የሚል ነው (አቶ አሸብር ፀጋ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 22፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አቶ አሸብር (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 22፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) የዋህነት በውስጡ ለሌላው ማህበራዊ አባል አስጊ ሆኖ አለመታሰብ ነው ይላሉ። ቂም አለመያዝና ለማጥቃትም ሆነ ለመበደል አስቦ አለመንቀሳቀስ በመሆኑ፣ በውስጡ ንጽሕናን ይዟል በማለት ያስረዳሉ። ንጽሕና በህብረተሰቡ እሳቤ ከማህበራዊ ደንብና ከሕግ ጋር ያለን ጥብቅ ትስስር የሚያመለክት ነው። ለልማድና ለባህል ያለን ታማኝነት የሚስመሰክር ነው። ማህበራዊ እርቅን ለማምጣት፤ በአባላቱ መካከል መስማማት ለመፍጠር፣ ጤና እንዲበላ፣ ህመም እንዲርቅ፣ ሰላም እንዲነግስ ጥላቻ እንዲጠፋ፣ ተፈጥሮ የተለመደ ስራዋን ሳታጓድል እንድትቀጥል፣ ልማዶች ጸንተው ሳይሸራረፉ እንዲጠቅሙ ሲታሰብ ከበራዎች ያዘጋጃል። ከበራዎች የሚዘጋጁበት ዋና ዓላማ ሰላም፣ ፍቅር፣ ጤናና ዕድገት እንዲሰፍን ነው። በዚህ ሥርዓት ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ መስዋይት የሚሆኑት የተቀደሱትና ለማህበራዊ ልማዱ ታማኝ የሆኑት ማለትም፣ ገራሞች፣ ቀናዎች፣ ታዛገሮችና የዋሆች ተመርጠው ነው።

በመሆኑም፣ የአካባቢው ሰው በክብረ በዓላቱ ላይ ግብር የሚሆኑ ነገሮችን ሲመርጥ መመዘኛ የሚያደርገው ታዛዥነትን ነው። በዚህ አውድ ላይ ለመሰዋት የመምረጫ መስፈርት ሆነው የሚቀርቡት ለማህበራዊው ልማድ ቅን አገልጋይ የሆኑትን ነው። ይህ መታዘዝ የሚወከለው ለጋ በሆነና ባልበሰለ፣ ባልገነገነና ባልገነተረ ነገር ነው (አቶ አሸብር፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 22፣ ቀን በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ለምሳሌ፡- በክብረ በዓሉ ላይ ለመስዋይትነት የሚመረጠው ከብት ከሆነ፣ "ቀንበር ያላረፈበት፣

ቀንዱ ያልከረከረ፣ ፀጉሩ ያላረረ፣ ሥጋው ያልግነተረና ለስሪያ ያልደረሰ ወይፈን ነው። በግ ከሆነ ደግሞ ግልገል ወይም ጠቦት ነው። ለመጠጥ የሚሆነው ጠላም አፍለኛ፣ ለጋ የሆነ ጎሽ ጠላ ነው" (ቄስ እንስማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ለሥርዓት ማጀቢያ በመሆን አዘውትረው የሚገቡት ገብስና ማር የሚመረጡትም በጠባያቸው ውስጥ ለስላሳነት፣ ለጋነት መልካምነት ስላለ ነው በማለት አቡሃይ አባቱ ይናገራሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 19፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ። ገብስ ቢቆላ ፈጥኖ ይበስላል። ቢሸፈሽፉት ገለባው ሳያስቸግር ይለቃል። ከነአባባሉ፣ "እከሌ ገብስ ነው" ሲባል ትርጉሙ የዋህ ማለት ነው። ገብስ በአካባቢው፣ "የእህል ንጉስ፣ የእህል አውራ" እንደሚባል የተናገሩት አቶ ቁሜ ናቸው (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 21፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ንጉሥ መባሉ ራሱ ላይ እንደ ቀንድ ጦር፣ እንደ ዘውድ ምርቅ መድፋቱ ነው። ይህም ዘሩን ጠብቆና ከልክሎ ለመያዝ ይረዳዋል። ስለዚህ፣ የእህል ዘር አንድ አባት የነገሩኝ አንድ ታሪክ አለ።

> "በድሮው ጊዜ አንድ ባላባት ክፉ ሥራ ሠርቶ ይታሰርና ከእህል ዘር አንዱን ብቻ መርጦ እንዲመገብ ይፈረዱበታል። የተፈረደበት ሰው አዋቂ ነበረና ሲመርጥ ገብስ ይላል። ገብስን የመረጠበት ምክንያት፣ ታካቹር እህል በመሆኑ ነው። ታካቹርነቱም ቢርብ እንጀራ፣ ቢጠማ ጠላ ቢሸፈሽፉት በሶ፣ ቢቆሉት ቆሎ፣ ቢያገነፉት ገንፎ ይሆናል። የማይሆነው ነገር የለም፣ ለፈለግነውና ለወደድነው ነገር እናውለዋለን ይላሉ (አቶ ቁሜ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 21 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ቄስ እንስማ፣ "ማር ከሁሉም የበለጠ ጣፋጭ ነው ይላሉ። ከመልካም ነገር ሁሉ ተቀስሞ የተዘጋጀ ጣፋጭ እንጀራ ነው"(2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ቢበሉት መድሃኒት፣ ቢመገቡት ምግብ ይሆናል። ቢበርዙት ይዋሃዳል። በእህል ዘር ላይ ሲገባ መልካም ቃናና ጣዕም ይጨምራል። እንዳረጉት ይሆናል። ይህ ገርነት ሳያስቸግርና ሳይጠነክር እንደልብ ለመዋሃድና ለመቀላቀል፣ በገባበት ቦታ ሁሉ ለመምጠን ያለው ምኞት፣ ለፈለጉት ነገር ለመመዋልና አቅሙንና ጉልበቱን አሟጥጦ ለመስጠት ያለው ለጋስነት የሚያስረዳ ነው(ቄስ እንስማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በቀላሉ ተዋህዶና

ተስማምቶ ለሚፈለገው ዓላማ ለመዋል ያለውን ልዝብነት ያሳያል። ሳያስቸግርና ሳይጠነክር ለሚፈለገው ዓላማ በቀላሉ ገዝ መሆንን ይነግራል። ማር ቂም አይዝም ቢታጠቡት ይለቃል ይሉታል።

መሪጌታ ሞላ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ አባቶች ለቡና መድሃኒት የሚሆነውን ዕፅ የሚያስቆርጡት ለአቅም ባልደረሱ፣ ክፉና ደጉን ባለዩ ልጆች ነው ይላሉ። በመስታውት መናፍስትን አቅርበው የሚያናግሩ ሰዎች መልዕክት የሚያገኙት በሕሣናት አማካይነት ነው ይባላል (ቄስ ዕድሜአለም፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ። እነዚህን ልጆች 'አልተጋነናቸውም' ይሏቸዋል። አለመጋነን ማለት፣ "ለሌላ ሃሳብና ስሜት ተገዥ አለመሆን ወይም ከትዕቢትና ከትምክህት ጋር አለመደመር ነው" (ቄስ ዕድሜአለም፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በዚህ አገባቡ ሌላ ሃሳብ ተብሎ የተገለጸው ከማህበረሰቡ እሴት ውጭ አለመሆንን የሚገልጽ ቃል ነው። እንደዚህ አይነት ሰዎች የክፉ ዐይን ማደሪያ የሚሆኑ ናቸው።

ከነተረቱ፣ "ልጅን መቅጣት በልጅነት፣ ዛፍን ማረቅ በለጋነት" ይባላል። ልጆች የነገሯቸውን ይሰማሉ (ቄስ ዕድሜአለም፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በውስጣቸው ክፉት የለባቸውም። ዕድሜያቸው ለጋ በመሆኑ የዘሩባቸውን ያበቅላሉ። ይህም አምነውና አክብረው የሚኖሩት አሳዳሪያቸውን ወይም ገዥያቸውን ነው። የሚሰጣቸውን የሚቀበሉ የሚነግራቸውን የሚያዳምጡ በሂደት እየበሰሉና እየጠነከሩ የሚሄዱ ናቸው (አቶ ይልቃል፣ 2003 ዓ/ም፣ ግንቦት 17፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። መታዘዝን እንጅ ማዘዝን ማህበራዊ መደባቸው ስለማይፈቅድላቸው የነገሯቸውን ይሰማሉ፤ እንዲሁም ያዘዟቸውን ይፈጽማሉ። እንደገሪውና እንደአሳዳጊው ፍላጎትና ዓላማ እንዲመቹ ሆነው ያድራሉ። የሚጠበቅባቸውን ማህበራዊና ባህላዊ ሚና አክብረው ታርመውና ተኮትኩተው ያድጋሉ። አሳዳጊው ሕፃናትን አዝዞና መርቶ፣ በሚፈልገው መልኩ ገርቶና አሰልጥኖ ለማሳደግ ስለሚመቹት በለጋ፣ ለስላሳ በሆነ፣ ባልጠነከረና ባልገነገነ ነገር ይመስላቸዋል። 'አይ ልጅ ገብሱ' እንዲሉ።

ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ይህ ታካችነት ሁልጊዜ የሚፈተነው ራሳን በመቻልና አንዱ ከሌላው የሚያገኘውን ጥቅም በሚያጣበት ጊዜ ነው ይላሉ፡፡ ይህ ሲሆን በአካባቢ በ'ሁለት እግሩ ቆመ'፣ 'ጎጆ አቁሞ፣ ጉልቻ ጎልቶ፣ የራስ ሞሰብ ሠርቶ መኖር ጀመረ' ይባላል ፡፡ በራስ መቆም በራስ ከመወሰን ጋር ተነጻጽሮ የሚገለጽ ነው፡፡ ራስን ችሎ መቆምና ማሰብ ደግሞ ከመደርጀት፣ ጠንክሮና በርትቶ ከመግኘትና በዕድሜና በልምድ ከመጥናትና ከመብሰል ጋር የሚተሳሰር አቻዊነትን የሚያስገኝ አሰላለፍ ነው፡፡ እምቢተኝነት የሚመጣው በራስ ማዘዝና በሌላው እንደልብ አለመመራት ሲመጣ ነው፡፡ የበሰለና የገነተረ ጊዜ የመታው ነው፡፡ ክፉና ደጉን መለየት በውስጡ ይዟል፡፡ እንደዚህ ሲሆን፣ ሲነግሩት ይለዝባል፣ ሲያዝዙት ይጠነክራል፡፡ ከልቡ አልታዘዝ ይላል፡፡ እንዲህ ያለውን ክፉ ዐይን ይወደዋል፡፡ በትዕቢቱ ገብቶ ያጠፋዋል፡፡ በጥንካሬው ገብቶ ይሰብረዋል ይላሉ ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡

መታመንና ማመጽ በእንስሳት

በእንስሳቱ ምርጫ ገራምነት ወይም ለማዳነት እንዲሁም ቀናነት እንስሳቱን በመልካም የሚያስቆጥርና አቅርቦ ለማስለመድ መነሻ የሚሆን የማቅረቢያ መስፈርት ነው (አቶ ነብይ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 21፣ በተደረገ ቃለመጠይቅ)፡፡ በአንዳንድ እንስሳት ጠባይ ውስጥ የታማኝነት፣ የሞኝነት፣ የደግነት፣ የአካፋይነት፣ የቆጣቢነትና የአጋችነት ሃሳብ አለ ይላሉ፡፡ ይህ ጠባይ እንስሳትን ለሰዎች ምሳሌና አገልጋይ አድርጎ ለማቅረብ ሁነኛ የመምረጫ መስፈርት ነው፡፡ በሰዎችና በእንስሳት መካከል ያለውን ግንኙነትና ስነልቦናዊ ዝምድና ጭምር ጠቋሚ ነው (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ከለማዳዎቹ መካከል አንዳንዶቹ ለአገልግሎት አንዳንዶቹ ለመብል አንዳንዶቹ ደግሞ ለተለያዩ ጥቅሞች ሆነው እንዲገዙ ማህበራዊ ሥርዓቱ ወስኖባቸዋል፡፡ ይህን አገልግሎትና ጥቅም እያሰበ የአካባቢው ሰው ገርቶና አላምዶ ከመጠቀሙ አንጻር ለእንስሳቱ ባሕርይ ስም ይሰጣል፡፡

እንስሳቱን ለራስ ፍላጎት በማስገዛት ሂደት የታለፉ ረጅም ታሪካዊ ክንውኖች ቢኖሩም፣ በመግዛቱ ሂደት በተመራጭነት የማላመጃ ዘዴዎች ሆነው የገቡት ማካፈልና በጥቅም ማሰር ወይም መደለል ናቸው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። እነዚህ ዘዴዎች እንደ እንስሳቱ አይነትና እንደሚፈለጉበት ተግባር ከሰዎች ጋር ቅርበት መመስረቻና መላመጃ ዘዴዎች ሆነው ስለማገልገላቸው አባቶች ይመሰክራሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ማሰልጠን (መግራት) እንስሳቱን ለሸክም፣ ለግልቢያና ለአንዳንድ ስራዎች እንዲመቹ ማድረጊያ የማግባቢያ ተግባር ነው። ለእርሻ፣ ለግልቢያና ለማጓጓዣነት እንዲጠቅሙ አድርጎ የማስገዛት ስልት ነው። ለምሳሌ፣ ወይፈንን ብንመለከት ጫንቃው ላይ ቀንበር ሳያርፍና ሳይለማመድ ከሚዳ ተነድቶ አያርስም። በቅሎና ፈረስ ሳይገሩ መጋለብና መጫን አይቻልም። ሁሉም እንስሳት ለመልመድና ለመገራት አይመቹም። ነገር ግን፣ በእንስሳቱ ግብር ውስጥ ያለው ደግነት፣ ሞኝነትና ሆዳምነት እንስሳቱን አዳሪ አድርጎ ሊያስገዛቸው ይችላል።

ለዚህ ለዓላማው የሚመቹትንና በቀላሉ ሰልጥነው ለአገልግሎት የሚደርሱትን የአካባቢው ሰው ሞኝ፣ ቅን፣ ደግና አዳሪ እያለ ስም ይሰጣቸዋል። ቅንነት በእንስሳት ህይወት ውስጥ የያዘው አካባቢያዊ ትርጉም፣ ሳይቃወሙና ሳያንገራግሩ፣ ለራስ ሳይሆን ለሌላው ማገልገልን፣ መገዛትን፣ ራስን አሳልፎ ለሌላው ጥቅም መስጠትን የሚያመለክት ነው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ለምሳሌ፡- በአካባቢው፣ "እገሌ በሬ ነው፤ በግ ነው" ይባላል። ይህን ሲሉ ሞኝ ነው፣ ገር ነው፣ የዋህ ነው፣ አላዋቂ ነው ማለታቸው ነው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ገር መሆን እና ሞኝነት በአካባቢ ያለው እሳቤ ሳይሰስቱና ሳይለግሙ ጉልበትን፣ ሃብትንና ማንኛውንም ጥቅም ለማህበራዊ ጥቅም ማዋል፣ ሳያንገራግሩና ሳይቃወሙ የታዘዙትን መፈጸም፣ ለወገን ቅን መሆን፣ ራስን አሳልፎ ለማህበራዊ ደህንነት መስዋይት ማድረግና ማካፈል በመሳሰሉ አረዳዶች የሚገለጽ ነው።

አንዳንድ እንስሳት በባሕርያቸው ቁጡዎችና ተናካሾች ናቸው። ይህንን ባህርያቸውን ለመግራትና ለሰው ልጅ እንዲመቹ ለማድረግ ሲፈለግ የሚረዱ ዘዴዎች አሉ። የማላመዱ ሂደት መሰረት የሚያደርገው የሚያውቁትንና የሚቀርቡትን የሚጠብቁ፤ የማያውቁትንና እንግዳ የሆነውን የሚናከሱና የማያስቀርቡ ናቸው። ከእንደዚህ አይነት እንስሶች ጋር ለመቀራረብ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለው አብዝቶ መገናኘት፣ መለማመድና የሚወዱትን በመስጠት ማቅረብና አዳሪ ማድረግ ነው። ለምሳሌ፣ ውሻ ከሰው ጋር አብሮ የሚኖር ለማዳ እንስሳ ነው። ሃብትና ንብረትን በታማኝነት ይጠብቃል። ታማኝ ያስባለውም ጌታውን ወይም አሳዳሪውን በሌላ ነገር አለመለወጡ ነው። በአካባቢው ይህ ታማኝነት፣ "ያበላውን እጅ የማይነክስና የበለጣትን ወጪት የማይሰብር" በሚል እንደሚገለጽ አቶ ጤናው ከብቱ ያስረዳሉ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)

> ላም ሆነ በሬ፣ በግም ሆነ ፍየል የገዛቸውን፣ ጌታቸውን ያውቃሉ። አህያ ገለባ የሚቅምበት ቤት አይጠፋውም። ማንኛውም ገዝ የሆነ ሁሉ ከዋለበት ሲመሣ ከብዙ መንጋ ተለይቶ ወደ ቤት ይሄዳል። መልመድን የሚያመጣው መብላትና መጠጣት፣ ማደርና መዋል ጌታው የመሳሰሉ መለማመዶችና መደጋገሞች ናቸው። በአካባቢው ሰዎች እንግዳን ለማላመድ፣ ዘመድ ለማድረግና በታማኝነት ለማቆም የሚሞክሩት በማብላትና በማጠጣት ነው።

የጎላምን ሰው አብሮ የበላ ሰው ሲከዳ፣ "ያበላሁበት እጄ ተነከሰ ይላል። ሰጥተው አልመሰገን፣ አድርገው እንዳላደረጉ ሲታሰበ ደግሞ፣ "እጄ አመድ አፋሽ ሆነ" ይላሉ (ሻሸቱ፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 7፣ የነገሩኝ)። ወዳጅ ዘመድ ሞቶ ሲለቀስ የቅርብ የሆነ ሰው ከሚች ቤት ገብቶ ለማልቀሻነት አንዳንድ የመመገቢያ ቁሳቁሶችንና የመጠጫ ዕቃዎችን በመያዝ፣ ደረቱን በዋንጫው እየመታ፣ "የበላሁበት የጠጣሁበት ቤት ፈረሰ" ብሎ ያለቅሳል። ይህ ሁሉ የሚደረገው አብሮ መብላትና መጠጣት ብቸኛው መተማመንንና ወዳጅነትን መፍጠሪያ መንገድ በመሆኑ ነው። "አብሮ የበላን ቅዱስ ዮሐንስ አይሸረውም" የሚለው አባባልም አለ።

ሰዎች ሲማማሉ፣ "እስኪ እጄን ጥፋው" ይባባላሉ (ወ/ሮ ሻሸቱ ፣2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 7፣ የነገሩኝ)። እጅ የሚጠፋፉት፣ "የተናገርከው እውነት ካልሆነ ያበላህ እጄ ይጣልህ/ይጣልሽ፤ ጤና አይሁንህ/አይሁንሽ ያጥፋህ/ ያጥፋኝ" ለማለት ነው ይላሉ ወ/ሮ

ሻሸቱ፡፡ በእርቅ ስርዓት ላይ የገዳይና የሟች ወገኖች ጠበንጀ ዘቅዝቀው ከታረቁ በኋላ፣ በአንድ መዓድ ላይ ተሰርተው የሚበሉትና የሚጠጡት አብሮ የበላ አይከዳዳም፣ እርቁም ይጸናል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ቄስ እንስማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ቄስ እንስማ የተጣሉና ቂም የተያያዙ ሰዎች ሲታረቁ ከልብ መቀበላቸው የሚረጋገጠው በአንድ ማዕድ ላይ ቀርበው አብረው ሲበሉ ነው ይላሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት፣ "ውሻ በበላበት ይጮኻል" ይላሉ (ወ/ሮ በየነች ምናሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ የነገሩኝ)፡፡ የውሻ ዘመዱ ያበላውና ያጠጣው ነው፡፡ ውሻ የሚጮኸው በማያውቀው፣ ባላበለውና ባላጠጣው ሰው ላይ ነው፡፡ ውሻ የጌታውን ቤት የሚጠብቀው ጌታው ስለሚንከባከበው፣ ስለሚያበላውና ስለሚያጠጣው ነው፡፡ ስለዚህ፣ በማለማመዱ ሂደት ማብላትና ማጉረስ ትልቁ ግንኙነትን ማደሻና ታማኝነትን መግዣ መንገድ ነው (አቶ ጤናው ከብቴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)፡፡

8. ሥርዓተ ንስሐ፤ የመፈወሻ መንገድ

በዚህ ምዕራፍ በሥጋ ባህርዮች መጣላት የተነሳ የተከሰተውንና በፍጥረት ውስጥ የመጣውን መዛነፍ እንዴት በሥጋ ባህረያት ግብሮች አማካይነት አስታርቆ፣ ሰዎችን ከክፉ ዐይን ጥቃት ማዳን ወይም መፈወስ እንደሚቻል፣ የመፈወሻ ዘዴዎችስ የትኞቹ እንደሆኑ፣ ስለምንነታቸውና ስለፋይዳቸው፣ በመፈወስ ስርዓቱ ጊዜ ስለሚያገለግሉ ቴክኒኮችና ስለ ባህላዊ ፍቻቸው ምንነት እንደሚከተለው ተብራርቶ ቀርቧል።

8.1. ሥርዓተ ንስሐ

ንስሐ የበደለን ሥጋ በመቅጣትና በማስተካከል ነፍስን ወደቦታዋ የመመለስ መንገድ ነው (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህ መስተካከል የሚመጣው የሥጋን ልጓም አልባ ጉዞ በመግታትና የሰበሰበውን ጠባይ በማሳጣት ለክፉ ሥራና ሃሳብ ማደሪያ ከመሆን በመዳን ነው። ማለትም ልብላ ልብላ፣ ልጠጣ ልጠጣ፣ ልውደቅ ልውደቅ፣ ልቀማ ልቀማ፣ ልግደል ልግደል የሚለውን ጠባዬ ሥጋ ገርቶ፤ ልፀም ልፀም፣ ልስጥ ልስጥ፣ ላካፍል ላካፍል፣ ላስብ ላስብ፣ በሚል ውስን ጠባይ የመተካት አስተሳሰብ ነው። የሥጋን ባሕርይ መግዛት የሚቻለው ደባልና ትርፍ ጠባዩች እንዳይመጡ በማገድ ነው።

ንስሐ ሰው ለሆነ ሁሉ የሚገባ አይደለም ይላሉ አባቶች። ተፈጥሮውን አክብሮ ለኖረ ሰው በዕድሜም ይሁን በመንፈሳዊ ብቃቱ፣ በሆነ ነገር ኃጢያት ያልገዛው፣ ከተሰጠው ግዴታ ያልወጣና በሕግ ለኖረ ንስሐ የግዱ አይደለም (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ፈውስ የሰውን ልጅ ከሕግ መተላለፍ አውጥቶ ወደ ቀደመ የባሕርይና የሰብዕና ማንነት መመለሻው ስለሆነ፣ የሚገሠጸው መተላለፍ ሲመጣ ነው።

እንድ ሰው ከተፈጥሮውና ከተበጀለት የባሕርይ መጠን አልፎ ሲገኝ ወይም የተሰጠውን የሰብዕና ልክ ጥሶ ሲያልፍ ረከሰ ይባላል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ጠባዩን ገርቶና ከአእምሮው ጋር ታርቆ ማደር ሲያቅተው፣ ከቀዳሚ ባሕርይ እየወጣ ሄዶ ሌላ ጠባይ ሲለማመድ

ንጽሕናውን አጎደፈ ይባላል። ሰዎችን ለጥቃት የሚያጋልጣቸው ይኸ መተላለፋቸው ነው።

አንድ ሰው በንጽሕናው ሆኖ መልካም ነገር ሲሰራ ደግሞ ንጹሕናውን አስከበረ ይሉታል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ ንጽሕና ከሕግ ጋር የተያያዘ መጠበቅን የሚሰብክ ጽንሰ ሐሳብ መሆኑ ነው። ራስን በተገደበና በተመጠነ የሥጋ ባሕርይ አስገዝቶ ወይም ጠብቆ ማኖር መቻል ነው። መተላለፍን ከሚያለማምዱና ስሜትን ከሚቀሰቅሱ ጠባዮች አሳርፎ ወይም አቅቦ ማቆየት ነው።

በመሆኑም፣ አንድ ሰው የተፈቀደለትን በሚያደርግ ጊዜ ከንጽሕናው፣ ከፈጣሪው፣ ከህብረተሰቡ፣ ከአፈጣጠሩና ከሰብዕናው ጋር ይኖራል። የተከለከለውን ሲያደርግ ወይም የተፈቀደለትን ሲተው ደግሞ ያ፣ ንጽሕናው ማለትም በቀዳሚነት የተሰጠው ባሕርይ የሚወሰድበት ይሆናል (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ንጽሕና ከተወሰደ ቦታው በርኩሰት ስለሚተካ፣ ነፍስ ደግሞ ርኩሰት ስለሚያሸሻት ባዶው ቦታ ተለይቶ የክፉ ዐይን ማደሪያ ይሆናል።

በዚህ ጊዜ በዚህ በክፉቱ ቦታ ክፉ ዐይን የሚያድር ይሆናል። የሰው ልጅ ከነፍሱ ተጣልቶ ቦታውን ክፉ ዐይን ሲያድርበት፣ ንጹሕ የነበረው ፍጡር ክፉ ተብሎ ከፈጣሪው፣ ከመንጋው፣ ከሰብአዊነቱና ከተፈጥሮው የሚለይ ይሆናል። ባሕርዩ ሰብዕን እየተወ ጠባዩ እንስሳን ገንዘብ ያደርጋል። ከጠባዩ እንስሳ እየከፋ ወደ ጠባዩ አራዊትም እየተሻገረ ይሄዳል(ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

እነዚህ የሰብዕና ኪሳራዎች የሚከተሉት እያንዳንዱ ፍጡር ተፈጥሮን ስቶና ከልክ ወጥቶ ከሌላ ጠባይ ጋር እየተዋወቀና ማንነቱን እየናቀ ሲሄድ ነው። ከዚህ በኋላ በፍጥረቱ ሰው ቢሆንም፣ በጠባዩና በሥራው ሌሎች ፍጥረቶችን እየመሰለ፣ ራሱን እየተወና ከሰብአዊነቱ እየራቀ መሄድ ይጀምራል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይኸ ነገር፣ ማንኛውም ፍጥረት

በቀዳሚ ዘመኑ ምንም አይነት እንከን የሌለበት መሆኑን የሚጠቁም ነው። ይህንን ሃሳብ ሊቀ ትጉሃን እንዲህ በማለት ያስላምሱታል፡-

> ማንም ሰው ሲወለድ ንፁሕ ነው። ሲፈጠር ንፁሕ ነው። በርኩሰትና በሃጢያት የሚፈጠር ምንም ዐይነት ፍጥረት የለም። እግዚአብሔር ሲፈጥር በፀጋው አስውቦና አስተካክሎ ሰው አድርጎ አምላክን የሚመስል፣ በሚታየውም በማይታየውም፣ ፈጣሪውን የሚከተል አድርጎ ነው። ይሽን ንጽሕና ከጊዜ በኋላ ልናስወስነው ወይም ልናረክሰው የምንችለው እኛው ባለቤቶቹ ነን።

የሰው ልጅ በራሱ ተፈጥሮ ውስጥ የፈለገውን የማድረግ ነጻ ፈቃድ ቢኖረውም፣ በተፈጥሮው ውስጥ ያለበት ምጣኔ ከልክ እንዳያልፍ ያስገድደዋል። ነጻነቱ መልካሙን ከጥሩ በራሱ ፈቃድ እንዲመርጥና እንዲያገዝ እንጅ እንዳሻው እንዲሆን ልቅ የሚተወው አይደለም። ነገር ግን፣ ተፈጥሮን ሲያከብር በጤና፣ በሰላምና በፍቅር መኖርን ሲያሸልመው፣ ሲጥስ ደግሞ በህመም፣ በመረበሽና በሁከት ያሰቃየዋል። ኢ-ሰብአዊ ተግባር የሚያስፈጽሙ ኃይሎች እንዲያዝዙበት ያጋልጠዋል። ይሁን እንጅ፣ ፈጣሪ ህመምን ያለ መድሃኒት አልፈጠርም ይላሉ ሊቀ ትጉሃን (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ። ይህ ህመም ወይም በህግ መተላለፍ የመጣው መርከስ የሚነጻው፣ ርኩስ ያደረገውን ጠባይ በማከም ወደ ቀደመና ትክክለኛ ባሕርይው በመመለስ ነው።

ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ "የሥጋ መርከስ ሙሉ በሙሉ አይነጻም ይላሉ። ሃጢያትን ሊያስወግድ የሚችል እኩል የሆኑ ዋጋም የለም" በማለት ያስረዳሉ። "መቶ ብር ለሰረቀ ሰው ተመሳሳይ ዋጋ ያለው ነገር እንዲከፍል በማድረግ መቅጣት ይቻል ይሆናል። ነገር ግን፣ ክፍያው ለተወሰደው ንብረት አቻ ግምት እንጅ የስርቆቱን ሥር አይቀጣውም ወይም አይገስጸውም" በማለት ቅጣት በብዛት የተወሰደውን በማስመለስ ላይ እንጅ እንዲወስድ ምክንያት የሆነውን ነገር በመገሰጽ ላይ እንደማያተኩር ይናገራሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በንዛምን ባሕል ውስጥ ዋናው የሃጢያት ዋጋ የሚሆነው የስርቆቱን ስሜት መገሰጹ ላይ እና ሰራቂው በድርጊቱ ተጸጽቶና ራሱን ወቅሶ ሁለተኛ እንዳይደግመው

አስተምሮ በመመለሱ ላይ ነው ይላሉ (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ የሃጢያቱ ሥር እንዲሁም ለመርከሱ ምክንያት የሆነውን ነገር ካላከምነው ከመሠረቱ እንደተስተካከለ ተቆጥሮ ወደ ባሕርይው መጣ ብለን መናገር አንችልም ይላሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በመርከስ ሂደት የሚታከመው አጋላጭ የሆነው ጠባይ ሲሆን፣ ነጻ የሚባለው ደግሞ ወደ ተፈጥሮው መመለሱ ነው። ስለዚህ፣ የረከሰው የሚነጻበት፣ የወደቀው የሚነሳበት፣ የተወሰደው ጸጋ የሚመለስበት፣ የተሰበረው ማንነት የሚጠገንበት፣ የተጣላው ሰብዕና ክብር የሚያገኝበት ትልቁ መድሃኒት "ንስሐ" ሆኖ ተሰርቷል ይላሉ(መርጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ሊቀትጉሃን (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) ንስሐን፣ "ሃጢያትን ደምስሶ ሰው የሚያደርግ ነው" በማለት የሚገልጹት ይሽንን በማሰብ ነው። የረከሰው መንጻት፣ የወደቀው መነሳት ብቻ ሳይሆን ወደ ማንነት መቅረቢያም ነውና።

8.2. የባሕርይ ማስታረቂያ ግብሮች

ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) በመርከስ ምክንያት ለክፉ ዐይን የሚያጋልጠውን ነገር የገለጹት "የባሕርይ ሥሮች መጣላት" በሚል ነው። በፍጥረት ውስጥ ይህ መዛባት የሚፈጠረው አራቱ ባሕርያት በአካል ውስጥ ያላቸው ተፈጥሯዊ ድርሻ አልመጣጠን ሲል ወይም ተፈጥሯዊ መሠረታቸውን ለቀው አንዱ ሌላውን ሲጫነው ነው። ሥጋ በተመጠነላት ባሕርይ ስትኖር ከነፍስ ጋር ወዳጅነቷ ይከብራል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በባሕርዮች መካከል ያለው መመጣጠን ሲዛባ ከነፍስ ጋር ያለ ግንኙነት ልል ይሆናል። መጣላቱና መለያየቱ የሚመጣው፣ አንዱ ባሕርይ ተለይቶ በዝቶ ሌሎች አንሰው አልመጣጠን ሲሉ ነው።

ስለዚህ፣ ሰው ከነፍሱ ጋር ፍጹም ውህድ የሚሆነው በፍጥረቱ ልክ ሆኖ ሲገኝ ነው ይላሉ። የሥጋ ባህርያት በተናጥል ስለማይሰሩ፣ ሰብዕና ይኖር ዘንድ ሥጋ የግድ ለነፍስ የሚመች እንዲሆን ይጠበቅበታል። በእርግጥ በሥጋ ባህርይ ውስጥ ያሉት

እያንዳንዳቸው አላባዎች ራሳቸውን ችለው ወይም አውቀው የሚንቀሳቀሱ አይደሉም ይባላል (ዲያቆን ብርሃኑ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ዲያቆን ብርሃኑ፣ "እሳት እሳትነቱን፣ ነፋስም ነፋስነቱን፣ ውሃ ውሃነቱን፣ መሬትም መሬትነቱን አውቆ አይሰራም ይላሉ። ግን ባሕርዮቹ መኖራቸው ይታያል። ባሕርያችን ከእነዚህ መምጣቱን እንድናውቅ እንድንረዳ ነው እንጅ የተደረገው፣ እነሱ በራሳቸው እንደዚያ የሚያደርጉበት ጠባይ የላቸውም" ይላሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በተወሰነ ሰዓት አንዳንድ ባሕርዮች ግንነው ይወጣሉ ወይም ይሰለጥናሉ። ነገር ግን፣ ሌሎቹ አይሰሩም ወይም የሉም ማለት አይደለም።

እነዚህ ባሕርዮች እርስ በርስ በግብር እንዲታረቁ፣ እንዲስማሙና እንዲመጣጠኑ ተደርገው የተፈጠሩ ናቸው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አንዱ ሲጨምር በሌላው ግብር እየተገደበ እንዲሄድ፣ አንዱ ሲያንስ ወደ መጠኑ እንዲደርስ የሚሆንበት መንገድ ይዟል። ይህ ዘዴ ባህርያቱ እንዳይጣሉና እንዳይጋጩ ማድረጊያ የሰብዕና ሚዛን ማስጠበቂያ ስልት ነው። አንድ ፍጥረት በእሳታዊ ባሕርይው ቢግል በውሃዊ ባህርይው እየበረደ፣ በውሃ ባህርይው እጅጉን ቢቀዘቅዝና እጅግም ስሜቱ ቢወርድ፣ በሰውነቱ ውስጥ መነሳሳትን አጥቶ በረዶ ቢሆን፣ በእሳታዊ ባህርይው አማካይነት እንዲነቃቃና እንዲግል እየሆነ፣ ነፋሳዊ ባህርይው በዝቶ ቀለል ቀለል እያለ ቢያስቸግር በመሬታዊ ባህርይው እንዲከብድና እንዲረጋ እየተደረገ፣ በመሬታዊ ባህርይው በዝቶ ቢረጋና ቢደክም በነፋሳዊ ባህርይው እየተስማማና ራሱን በግብሩ እያረቀ ህይወት ባሕርይዋን ጠብቃ እንድትሄድ የሚደረግበት መንገድ አለው ይላሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አንዱ በዝቶ ሌላው ሲጎድልና መሸናነፍ ሲመጣ የሚገኘው መዛባት መርከስን ወልዶ ለክፉ ዐይን የሚያጋልጥ ይሆናል። ይህ መርከስ ካልተመለሰ ለነፍስ ስለማይመች ጎጅ ኃይል ይሆናል። ይህ ሁሉ እውን የሚሆነው የሰው ልጅ የንስሃን መድሃኒት አምኖ ሲቀበል ብቻ ነው ይላሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ስለዚህ፣ የሰው ልጅ ሲያጠፋ የሚመለስበት የባሕርይ መታረቂያ መንገድ ያለው ቢሆንም፣ ጠባዩን የሚያወጣው ግን በራሱ ፈቃድና መቀበል ይሆናል

(ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እንደተሳሳተ አምኖ ለመቀየር እንዲሁም ያለፈን ማንነት ለማግኘት መሻት በሰብዕናው ውስጥ መፈጠር አለበት። ለዚህ መጀመሪያው ደግሞ፣ ራስህን በመክሰስ የራስህን ጥፋት ማመን ነው በማለት የጠባይ ማከሚያ ሥሩ ራስን መውቀስ እንደሆነ ያሰምራሉ።

እነዚህ አራቱ ባህርያት የሚስማሙባቸው ብቻ ሳይሆን፣ እርስ በርስ የሚጣሉባቸውና የሚሸናነፉባቸው ሁኔታዎች አሏቸው ይላሉ (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ለምሳሌ፡-እሳት ገደቡን ሲያልፍ ውኃን ያፈላዋል ማለትም የታመቀውንና የታፈነውን ከውስጥ ተደበቆ የሚብሰለሰለውን ነገር ያፈነዳዋል ይላሉ። ውኃ ደግሞ ሲበረታ እሳትን ያጠፋዋል። ነፋስ መሬትን ይበትነዋል፤ ይዘረዝረዋል። መሬትም ነፋስን ይገድበዋል፤ ይጋርደዋል። ነፋስ ውኃን ይመታዋል፤ ያማታዋል እንደ ከበሮ ያስመሽዋል (አክሲማሮስ፣ 14)። ስለዚህ፣ እነዚህን አራቱን ባህርያት ለማስታረቅ ለማዛመድ ሦስት ሦስት ግብር ያላቸው ተደርገው ተፈጥረዋል (ኩፋ 2፣ 17)። ዋናው ነገር ሁሉ ሁሉ በምስጢር መገኘታቸው ነው ይላሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ።

8.3. የንስሐ አይነቶች

በሥጋ ባሕርያት መካከል በሚፈጠር አለመመጣጠን የሚመጣን መጋለጥ ማከም የሚቻልበት ዘዴ "ንስሐ" ነው። እነዚህ ዘዴዎች ፍጥረቱን ከክፉ ዐይን ጥቃት ለማላቀቅ የሚያግዙ ሲሆኑ፣ የፈውሱ ዘዴ የሚያተኩረው ጠባይ ያመጣውን ሥጋ ማከም ላይ ነው። ፍጥረቱ በተፈጥሮው ይዞት ወደነበረው ግብር በመመለስ እንዲጋለጥ ያደረገውን ችግር ለማከም ዓላማ ያደርጋል። የሰውን ልጅ ለክፉ ዐይን ያጋልጣል ተብሎ የሚታመነው ሥጋ በመሆኑ፣ ሁሉም ማስተካከያዎች የሚያነጣጥሩት "ሥጋ" ላይ ነው። በመሆኑም፣ በሥጋ ባህርይ መጣላት በተፈጠረው መርከስ የገቡትን የክፉ ዐይን መንፈሶች ለማስወጣት የመፈወሻ መሳሪያዎች ሆነው የሚያገለግሉት አራት የንስሐ አይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

ምጽዋት

ለክፉ ዐይን አጋላጭ የሆነው ዋነኛ ችግር፣ ከሌላ ድንበር ገብቶ መበደል ነው ይላሉ (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። ከሌላ ድንበር መግባት ሲባል፣ የራስ ያልሆነን ነገር አሻግሮ ማየትንና ለራስ ለማድረግ መመኘትንና ማድረግን ሁሉ ያጠቃልላል። ለሌላው አለማሰብና ለራስ ፍላጎት ብቻ መገዛት ሲመጣ፣ ሁሉንም ለኔ ማለትና መሰብሰብና ማጠራቀም ይከተላል። በመሆኑም፣ የክፉ ዐይን ዋነኛ መግቢያ የሚሆነው በስጋ መጎምጀትና በስስት መኖር ናቸው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። የስስት አንዱ መገለጫ ደግሞ መስገብገብና መጓጓት ነው በማለት ምንነቱን ያብራሩታል።

በጠባያቸው ማጠራቀምን የሚወዱ ማውጣትን ደግሞ የሚጠሉ ሰዎች አሉ። መካፈልንና አብሮ ማደግን የሚያነውሩ ንፉግና ክፉ የሆኑ አካሎች ብዙ ናቸው። ማጠራቀም፣ ማከማቸት መሰብሰብ ሁሉንም ነገር ወደ ውስጥ የማቆት ልምድ በመሆኑ፣ እንዲህ አይነት ጠባይ ያለው ሰው ክፉ ዐይን እንደሚወደው ይነገራል። ከሰው ጋር ተካፍሎ መብላትን የሚጠላ፣ ያንንም ይህንንም ማግበስበስ የሚወድ፣ መክተትና መደበቅ ባህርይው የሆነ፣ እያወቀ አላዋቂ የሚመስል ዝግተኛና ልዝብ የሆነ ሁሉንም በልቡ የሚያጉርና የሚከት ቂመኛና ክፉ ሰው ነው ይሉታል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)።

አባቶች፣ እንደዚህ አይነት ጠባይ የሚመጣው ከባሕርይ ሥሮች መካከል አንዱ የሆነው ውሃ ሲበዛ ነው ይላሉ (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። መርጌታ ኮከብ በሰውነታችን ውስጥ ያለ ማንኛውም ፈሳሽ በደም፣ በላብ፣ በእንባ፣ በወተት መልክ የሚገለጸው ሁሉ ባሕርይው የ"ውሃ" ነው ይላሉ። ውሃ በሰው ልጅ ውስጥ ውክልናው በስሜት ነው። ወደ ውስጥ የሚንቦለቦሉ ስሜቶች፣ ቦታ ይዘው የሚቀመጡ ጥልቅ ሃሳቦች፣ በእሳት ብርሃን የማይታዩ በጨለማ ውስጥ ገብተው የተሰወሩ ምስጢሮች፣ እንደ ጨረቃ ብርሃን ጭላንጭል የሚረጩ፣ ቦግ ብግ የሚሉ ሽሽግ የሆኑ ሁሉ አምሳላቸው የዚህ ናቸው ይላሉ (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ፊት ለፊት የማይታዩ፣ ለሰው ግልጽ ያልሆኑና በውስጥ የሠረጸ፣ የተቋጥረ፣ የተቀበረ፣ የተቀመጠ ምስጢር የሆነ ነገር ሁሉ የዚህ ባሕርይ አምሳል ነው (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ምክንያቱን ሲያስረዱ፣ የውሃ ጠባዩ ማቋት ስለሆነ የሚፈሰው ወደ ውስጥ ነው ይላሉ። ገብቶ የሚከተት፣ ውስጥ ለውስጥ የሚሰማ እንጅ የማይወጣ፣ ውስጠትን የሚሰረስርና የሚቀዘቅዝ ነው ይላሉ (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በእሳት ውስጥ ያለው ግን ወደ ውጭ የሚንቦገቦግ፣ የሚፈነዳ፣ የሚታይና የሚገለፀ ነው። በመሆኑም፣ ውስጣዊ የሆነ ዕውቀት፣ የማይገለጥና በምስጢር የተያዘ፣ ድብቅ የሆነና ገሃድ የማይወጣ ውስጥ ለውስጥ መሄድ፣ የክፉ ዐይን ጠባይ ነው ይሉታል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)።

በመሆኑም፣ ምድራዊ ሃብትን አብዝተው የያዙና የበለጸጉ፣ ትርፍ ነገር ሁሉ ያላቸው በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገቡ ናቸው። በመሬት ከርስ ውስጥ የተደበቁ ሃብቶችና ተከማችተው የተቀመጡ ነገሮች ከማቆት ጋር የተያያዙ ስለሆኑ፣ ማቆት ከብዷቸው የዘቀጡ ናቸው ይሏቸዋል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ብዙ የወለዱ፣ የለመለሙና ብዙ ቅርንጫፍና ፍሬ የያዙ ዛፎች በውስጣቸው የበዛ ውሃ ስለሚይዙና ስለሚከብዳቸው ምድር ይስባቸዋል ይሏቸዋል። የለመለሙና አካላቸው የደለቡ እንስሳት፣ ብዙ ፍሬ የሚያፈሩና ከበጋ እስከ ክረምት እንደለመለሙ የሚኖሩ ዕፀዋት ሁሉ የውሃ መጠናቸው በዝቶ የሚገንባቸው ናቸው (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እነዚህ ፍጥረቶች ምደራዊ ሃብት ስለተጫናቸው የማሰብና የመመርመር ምልክት የሆነችው ልባዊት የጎደለችባቸው ስለሆኑ፣ በቦታው ክፉው መንፈስ ይተክልባቸዋል ይላሉ።

አቶ አሸብር (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ በጎዛምን ሙሽሮች የሚመረቁት፣ "ውለዱ ክበዱ" ተብለው ነው ይላሉ። ሠርግ አሠርጎ፣ ማህበር አውጥቶ ወይም ክርስትና አስነስቶ ያበላንና ያጠጣን ደጋሽ፣ የበላው ሰው፣ "የጤፍ ዘር፣ የእንቧይ ፍሬ ያድርጋችሁ" ብሎ ይመርቃል። ሙሽሮችን አባት እናት ወዳጅ ዘመድ ይሰበሰብና፣ "ውለዱ ክበዱ" ይሏቸዋል። መክበድ በዓለም መክበር

ነው። ጤፍም ሆነ እንቧይ የተመረጡት በፍሬያቸው ብዛት ነው። በመሆኑም፣ በጠፋ ይተካ ማለታቸው ነው። ሁለቱም የለምለም ተክሎችና እህሎች ምሳሌዎች ናቸው። መክበድም የልምላሜ ውጤት ነው።

የበላ ውሃ በውስጡ ያለበት ነገር አካሉ ስለሚከብደው መሬት ይይዛል(መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በንብረቱና በሃብቱ ምክንያት በአካባቢው ይታሰራል። ሰው በሀብት በበለጸገ፣ ገላ በገዘ፣ ንብረት ባፈራ ቁጥር የሚተከለው ባለበት ነው፤ መንቀሳቀስ ይጠላል። ዓለም ይገዛዋል። ጌትነት ተጭኖት፣ ድሎት ከብዶት፣ ክብር አስሮት እንደልብ ለመዘዋወር ይቸገራል። ምድራዊ ጠባዩ አይሎ ስለሚጫነው እንደልብ አያንቀሳቅሰውም ይላሉ።

ስለዚህ፣ በመብዛት፣ በመክተትና በመቋጠር ውስጥ ያለው ቅለት ሳይሆን ክብደት በመሆኑ፣ ከፍ ከፍ ማለት እየቀረ መዝቀጥና መስረግ ስለሚመጣበት "ውለዱ ክበዱ" ይላሉ። በዚህ ጊዜ ነፍስ እየተበደለች ሥጋ እያበጠች ለመምጣቷ አሳይ ነው። በመብዛት፣ በመክተትና በመቋጠር ውስጥ ያለው ቅለት ሳይሆን ክብደቱ በመሆኑ፣ በመክበድ ውስጥ ደግሞ ያለው ክፉ ኃይል በመሆኑ ከፍ ከፍ ማለት እየቀረ መውረድና መስረግ ስለሚመጣ ይህ አካሄድ ለሌላ ኃይል የሚያሳጭ ይሆናል።

ዲያቆን ብርሃኑ፣ ልምላሜ የሚገኘው ብዙ ፈሳሽ ባለበት ውስጥ ነው ይላሉ። በለመለመ ውስጥ ከልኩ ያለፈ ውሃ ስላለ ጠባዩ የተለየ ይሆናል በማለት ያስረዳሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) ። ይኸን ቋጣሪነትና አቋሪነት ደግሞ የራስ ያልሆነን ነገር ሰብስቦ ከሚገባው በላይ አብዝቶ ለመያዝ ምሳሌ ያደርጉታል። በአንድ አካል ውስጥ ውሃ በበላ ቁጥር ከፍ ከፍ እንዲል የሚያደርገውን ቅለት ፈሳሽ ይጫነዋል ማለት ነው። እንደልብ ለመራመድና ለመሮጥ የሚያስችለው የነፋስ ባሕርይ አነሰ ማለት ነው (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ነፋስ የዕውቀት አምሳል ስለሆነ፣ ለህሊናው ማደርን እየተወ ለሆዱ የሚያድር ይሆናል። ሰው ሆዱን ሲወድ ነፍሱን ይረሳል እንዲሉ፣ ነፍሱን ሲንቅ ማንኑቱን ይጥላል። ማንኑቱን ሲንቅ ክፉ ዐይን የሚያስተዳድረው ይሆናል። በዚህ የተነሳ

አባቶች የውሃን አቅጣጫ በምዕራብ ያደርጉታል (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ፀሐይ በምዕራብ እንደምትጠልቅ ሁሉ የነፍስና የሥጋ መለያየት ብሎም ወደ ሞት መሄድ በዚህ የሚመሰል ነው በማለት ያስረዳሉ(መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በዚህ ጊዜ ከሚደርስ አደጋና መተላለፍ ለመውጣት ምህረት አምጪ መንገድ ሆኖ የሚመጣው ከአካል ውስጥ ያለውን ፈሳሽ መቀነስና ወደ ልከኛ የባሕርይ መጠኑ ላይ ማድረስ ነው ይላሉ (መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይህ መንገድ ዋነኛው የማካፈያና የማቻቻያ፣ የማመጣጠኛና እኩልነትን የማምጫው ዘዴ ነው በማለት ይገልጹታል (ሊቀ ትጉሃን 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህንን የባሕርይ መጣረስ ማከም የሚቻለው "በምጽዋት" ቴክኒክ ነው።

ምጽዋት ለሰው በጎ መሆንን የሚጠቁም የርህራሄ መንገድ ነው በማለት ዲያቆን ብርሃኑ ይገልፀዋል (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ዲያቆን ብርሃኑ አክለው እዚህ ላይ ማሰብ ያለብን ሃጢያትን ወይም ከሕግ መተላለፍን በገንዘብ መክፈል ማለት አይደለም ይላሉ። ለሌላው ሰው በማሰብ ማካፈልን እንዲለምድ ለማድረግ ነው ይላሉ። በስስት የተያዘና ፍቅረ ንዋይ ያየለበት ሰው የውሃ ጠባይ በውስጡ ያደረበት ቋጣሪና ሰብሳቢ ሰው ነው ይላሉ። የውሃ ባሕርያችን ማቋት በመሆኑ፤ ይህ ጠባይ የያዛቸው ሰዎች ማጠራቀምና መክተት ያበዛሉ። እሱን ማስተካከል የምንችለው በመስጠትና በማነቃነቅ ነው በማለት ያስገነዝባሉ።

አራቱ የቅጣት አይነቶች አራቱን የሥጋ ባሕርያት እንዲመጣጠኑና እንዲመቻቹ እና እንዲያስተካክሉ ሆነው የተሰጡ ናቸው። በዚህ ውስጥ ተጠቃሚ የምትሆነው ነፍስ ነች (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በስስት የተቋጠረው ገንዘብ በመመጽወት ሲስተካከል፣ በመልካምነት የምትደሰተው ነፍስ ወደ ቦታዋ እንድትመለስ አድርጎ፣ የንፍገት አባት የሆነው ክፉ ዐይን እንዲወጣ የሚያስገድደው ይሆናል ይላሉ። ለአንተ ይቅርታ እንዲደረግልህ፣ ምህረትን ከፈለግክ፣ ለሌላው ማድረግን መለማመድ ይኖርብሃል የሚለው የክርስትና መፈክር ከዚህ አስተሳሰብ የሚነቃ ነው ይላሉ ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር

30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በጉልበቱ ወጥቶ ወርዶ ያፈራውን ለሌሎቹ፣ ባካፈለ ጊዜ የክፉ ዐይን ይቀላል፣ ነፍስ ግን በእጅጉ ትደሰታለች በማለት ያስረዳሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

የራሱ የሆነውን ነገር በማሳጣት፣ ከራሱ ላይ እንዲሰጥና እንዲወሰድበት በማድረግ ግንዘብ በመሰብሰብና በማቆት የመጣውን ልዩ ጠባይ፣ በማደልና በመበተን እንዲታረቅ ይደርጋል (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በዚህ ውስጥ መንፈሳዊ ህይወት ያድጋል። መንፈሳዊ ህይወት ሲያድግ ንጽሕና ይመለሳል፣ ቅድስና ይመጣል፣ እርቅ ከነፍስ ጋር ይሆናል (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የጎዛምን ሰው ሰውነቱን ለማክበርና ክፉ ዐይን እንዳይጠጋው ለመከላከል ከሚበላው ያካፍላል። ከብት በታረደበት ቤት የመጣ ሰው ሥጋ ሳይቀምስ አይወጣም። ላሞች ሲታለቡ የደረሰ ሰው ወተት ሳይቀምስ አይሄድም። ገበሬው አርሶ ካገኘው ፍሬ ማርያም ባርኪ ብሎ ይሰፍራል። ስረቆት በሚጀምርበት ጊዜ ግን ንጽሕናውን ያጣል። በማጠራቀም የተገዛ ሰው በመበተን ሲቀጣ አይኑ ደም ይለብሳል(አቶ ዘመኑ ከፋለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በዚያን ጊዜ ነፍሱ ስትደሰት ሥጋው ትታመማለች በማለት ካለን በማካፈል ክፉ ዐይንን ማራቅ እንዲሁም ሰብዕናን ማስተካከል እንደሚቻል ያስረዳሉ።

ጾምና ስግደት

በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ እሳት የምኞትና የፍላጎት ወኪል ነው ይሉታል። ምኞት በሰውነት ውስጥ እየተቀጣጠለ፣ እየጋለ ሄዶ የሚፈነዳ አንድን ነገር ካላገኘና ካላሳካ የማይቆም ገደብ አልባ ጠባይ እንደሆነ አድረገው ይገልጹታል (መሪጌታ ዲበኩለ 2005 ዓ/ም ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ምኞት የመሻት ምልክት በመሆኑ፣ የሥጋ ምኞት ሲበዛ፣ ነፍስ ትቆስላለች ሥጋ ገደቧን አልፋ በጥጋብ ትረክሳለች ይላሉ። ክፉ ዐይን ሰዎችን ሁልጊዜ የሚቀርበው ሥጋ ለነፍስ ባሕርይ ተገዥ አልሆነ ስትል ነው። ሥጋ ሃይል የሌለው ልጓም አልባ ፈረስ ነው የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው። ልጓም እንደሌላቸው እንደ ፈረስና በቅሎ ራሳቸውን አትልቀቁት ይላሉ አባቶች (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በሰው ልጅ የዕድገት ዘመኑ ውስጥ ወንዶችና ሴቶች የአካል ለውጥ የሚያሳዩት በእሳት ዘመናቸው ላይ ነው (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ለምሳሌ፡- ወንዶች በተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸው ፀጉር ያወጣሉ። ድምጻቸው ይጎረንናል። ጠረናቸው ይቀየራል። አካላቸው ይፈረጥማል። ለመታዘዝ የሚያስቸግሩበት፣ ለድብድብ የሚጋበዙበት ወቅት ነው ይባላል (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ሊቀ ትጉሃን ሴቶችም በዚህ ጊዜያቸው የወር አበባ ያያሉ፤ ጡታቸው ያጎጠጉጣል፣ ዳሌአቸው ይሰፋል። ሁሉ ነገራቸው ወጣ ወጣ ማለት ይጀመራል።

በተክሎች የህይወት ዘመን የሚያፈሩበት ወቅት የሚመሰለው በእሳት ነው። ይህንን ጠባዩን ከቀትር፣ ከሙቀት፣ ከብሩህ ጊዜና ከበጋ ጋር ያያይዙታል። ይሽን እያሰቡ አንዳንድ የባህሉ ዕውቀት ያላቸው አባቶች፣ ነፋስን በዘር እንዲሁም በቃያን በእሳት ሲመስሉት ይታያል (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እሳት በዋናው ዘር ውስጥ አድሮ ሃይል ሲሆን ለዘሩ ምቾት ሆኖ እንዲበቅል ያደርጋል ይላሉ። በመሆኑም፣ አእምሮው ብሩህ የሆነ፣ ሃይለኛና ደፋር፣ የአንደበት ስጦታዎች ያሉት፣ ከፍ ያለ ሃሳብ ያለው ሰው ሲሆን፣ የእሳት ባሕርይው የበዛ ነው እንለዋለን በማለት ያስረዳሉ (ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በብዛት በጣም የሞቀው፣ የብርሃን ጊዜ፣ የቀትር ሰዓት እንዲሁም ወር በዚህ የሚወከል ነው። የሃሳብ ሆነ የነገሮች መጠንሰሻው ነፋስ ሲሆን፣ የበሰለ ነገር ደግሞ የእሳት ነው (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ነፋስ በዘርነቱ ብቅ ብቅ በማለት፣ በመውጣት፣ በመብቀል፣ በመዘርዘር ሲገለጽ፣ በአብሳይነቱ በማፍራት፣ በማሸት፣ በማጎጥጎጥ ይታወቃል። የተጠነሰሰ ሃሳብና ፈጠራ በነፋስ ውስጥ ተዘርዶ የሚቀመጥ ሲሆን፣ ተስፋና ፍላጎትን ካላገኘ ለፍሬ የማይደርስ ይሆናል።

መሪጌታ አይነኩሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ "እሳት ለዋጭ ሃይል ነው፤ አሮጌውን አቃጥሎ ልዩ የሆነ ነገር እንዲመጣ ያደርጋል" ይላሉ። ጥሬውን ያበስላል። በቃያውን ፍሬ፣ ርጥቡን ደረቅ፣ ለጋውን ብስል፣

ጥሬውን ልዝብ፣ ለጋውን ጠንካራ ያደርጋል። ጥሬ ሥጋ እሳት ሲነካው ጣፋጭ እንደሚሆን ሁሉ ልጅነት አልፎ ወጣትነት ሲተካ፣ በዕውቀትና በማስተዋል ይበስላል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም ፣ ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ ተክሎች ቢጫ ወይም ብርቱካናማ ቀለም ላይ ሲደርሱ፣ ፍሬው ወደ ቀይነት፣ እሸቱ ወደ ፍሬ ሲሸጋገር የእሳት ዘመኑ ነው፣ በሰለ ይላሉ።

በዚህ ጊዜ የሥጋ እሳታዊ ባህርይ ልዩ ልዩ ፍላጎቶች እንዲቀሰቀሱ ያደርጋል ይላሉ (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይህ ሁሉ ተፈጥሯቸውን የሚያነቃንቀው፣ የሚያሳድገው፣ መፈለግ እንዲመጣ የሚፈልጉትን ነገር እንዲያገኙ የሚያደርገው አበጅቶ ነው ይላሉ (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። የሥጋ አምሮት ገደቡን ሲጥስ ባለ ብዙ ምኞት ይሆናል። ዝሙት ያምረዋል፣ አብዝቶ መብላት ማግበስበስ ያስደስተዋል። ይኸ ፍላጎት ካልተገደበ ስሜት እየጋለ፣ ምኞት እያየለ እንዲሄድ ያበረታታል። ሁሉን ልያዝ፣ ሁሉን ልቅመስ ይመጣል። ሰው በዚህ ዘመኑ በጉልበቱ ይበድላል፤ በአንደበቱ ያስቀይማል። እምቢተኝነትና የትዕቢት ጠባይ ይጫነዋል። እያንዳንዱ የሰውነት ብልት ሁሉ በሃይል ስለሚሞላ ጥፋት ለመስራት ይገፋፋዋል ይላሉ መርጌታ አይነኩሉ (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ክፉ ዐይን በሰዎች ውስጥ ለማደር የሚረዳው ትዕቢትና የሥጋ አምሮት ነው።

ሊቀትጉሃን ሃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ ሰዎች ዝሙት እንዲሰሩ የሚያነሳሷቸው ነገሮች ይኖራሉ ይላሉ። ሥጋ እስከበላ እስከጠጣ፣ ድረስ ሰውነቱ እየጎላ፣ እየጎለመሰና እየፋፋ እንዲሁም መውጣት እየተሰማው ይሄዳል። ስለዚህ፣ መንፈሳዊ ህክምና የሚሆነው ወደዚህ የመራውን ነገር በማድረቅ የሥጋውን ጠባይ ማስተካከል ነው። መጥኖ በመብላት ሥጋዊ ስሜትን በተወሰነ መልኩ መቆጣጠር ይቻላል። መጥኖ መብላትን በክርስትና የመጀመሪያው አስተምህሮት እንደሆነም ያስረዳሉ።

ስለገተገኘ ብቻ ሁሉን ነገር መለቃቀም አይገባም። ተፈጥሮ በራሷ መጠን አላት። ከተፈጥሮ መጠንም እስኪደርሱ አይነሰንስም፣ ከዚህም በላይ ራሱ መመጠን

የሚችልበት አእምሮ ተሰጥቶታል። ያን ማድረግ አለበት። እንዲንሸራሸርና እንዲስማማው ክፍት ቦታ መተው ይገባዋል ይላሉ(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይኸ ከጽድቅ ጋር አይየያዝም። ጤነኛ ሆኖ ለመኖር እንደዚያ ማድረግ ይኖርበታል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከዚህ ጭብጥ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ የሰነዘሩት ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ የሚከተለውን ብለዋል (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

> አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጅ በጥጋብና በስካር ከሰው ተራ እየወጣ ማህበራዊ ሕግን ሲጥስ፣ ጉልበተኛ እየሆነ ሰውን ሲያስቀይም፣ ስርዓት አለበኛ እየሆነ ሲሄድ ማህበራዊ መረጋገት እየጠፋ ሃገር በሥርዓት አልበኝነት ይታመሳል። ይኸ ትኩስ አቅም በአግባቡ ካልተመጠነ፣ አካልን ሥጋዊ ፍትወት እየተጫነው ከመጣ፣ አካላዊ ፍላጎቱን ለማርካት ሲል ያሻውን ሁሉ ማድረግ ካበዛ ፍትወቱ ይበልጥ እየጋለ፣ እየጨመረ፣ እያቃጠለና እየተፋጀ የሚሄድ ይሆናል። ይህ ያልተመጠነ ስሜት ገደቡን ሲጥስ ያንንም ያንንም መመኘት አልገደብ ሲል አካል ባህርይውን አጥቶ ጠባይ ሆኗልና ሰውነቱን ይስታል።

በመሆኑም፣ የሰው ልጅ የሚያንገበግበውና የሚደክመው፣ ወደ ምድር ዝቅ ዝቅ ማለት የሚጀምረው የምድራዊ ምኞትና የዓለማዊ ደስታ ምልክቶች የሆነው መሬት እየተጫነው ሲሄዱ ነው ይላሉ (ቄስ እንስማ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ሆድን ጥጋብ ሲጫነው እንደ ድንጋይ ይከብዳል። መሬት ሊይዝ ይወዳል። መንቀሳቀስን ይጠላል ይላሉ። በልጅነት ውስጥ ያለው ዋነኛ ባህርይ የነፋስ በመሆኑ በመክነፉ ውስጥ ቀላልነት እንዳለ ልብ ይሏል። ያገኘውን መብላት፣ ያዩትን መነካካት፣ መንቀሻቀሻ፣ አለመረጋጋትና በአንድ ቦታ ላይ አርፎ አለመቀመጥ የሚታይባቸው ለዚያ ነው ይሏቸዋል (ቄስ እንስማ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በቀላልነት ውስጥ አለመብሰል ስላለ ማስተዋልንና ስክነትን የነፋስ ግብር አያደርጋቸውም። በነፋስ ውስጥ ከቀላልነት በተጨማሪ የጀማሪነት ባሕርይም ይኖራል። በመሆኑም፣ መነሳት፣ መውጣት፣ ብቅ ማለት፣ መብቀል መወለድ፣ መብራት መታየት፣ መግለጥ፣ መባት፣ መግባት፣ መቸርመር፣ መፍላት፣ መብቀል፣

ሥር መስደድ፣ መለምለም፣ ማፈጥፈጥ፣ በዚሁ ይመሰላሉ (ቄስ እንስማ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በመሆኑም፣ ብሩሁን የሚያጨልም፣ ብቅ ብቅ ማለትን የሚደፍቅ፣ መሮጥ መቦረቅን የሚያስር፣ መቅለልን የሚያከብድ የሚያቆሽሽና የሚያሳድፍ ነገር ሲያርፍበት ነው። በዚህ ጊዜ ያ፣ ይፈነጥዝ፣ ያብድ፣ ይከንፍ፣ የነበረው አካል የሚዘቅጥ፣ የሚደክምና የሚሰንፍ ይሆናል(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከዕለት ወደ ዕለት የነፋስ ንፁሕ ባሕርይ እየደፈረሰና እየቆሸሸ ሄዶ መዝቀጥን፣ መዛልንና መስነፍን ባሕርይው ያደርጋል።

በነፋስ ባህርይ ውስጥ የነበረው ለመንሳፈፍ የሚያስችለው የቀዳሚነት የቀላልነት ባህርይው ላይ የጥቁርነት ነቁጥ ሲያርፍበት ነፋስ አፈር ሲጎርስ ይከብዳል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከፍ ከፍ እንዳይል እየተጫነውና እየንተተው ያደክመዋል። እንደልብ ከፍ ብሎ ለመብረር፣ ተነስቶ ለመሮጥ ያስቸግረዋል። ሥጋ ሲበዛ አእምሮ ይቀጭጫል፤ ይጫነዋል።

ይህ ጠባይ ሰዎችን አርክሶ ህመም ሲመጣ፣ አካል ሲደክም መድሃኒት የሚሆነው ጾም ነው ይላሉ (አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣ 122) ። አባ ጎርጎርዮስ ጾምን፣ "ሰውነት ከሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ መከልከል መወሰን ነው" በማለት ይገልጹታል (1991፣ 122)። ይህም ለሰውነት የሚያምረውን የሚያስጎመጀውን ነገር መከልከል ነው። አባ ገብረሥላሴ (ገብረሥላሴ ብርሃኑ፣ 72-73)፣ ጥንቱንም ጾም የተሠራው እንስሳዊ ባህርይ ላደረሰባቸው፣ ዘውትር በለስላሳ ምግብ ለሚማግጡ ሰዎች ወይም ለማይሰሩ በዘኔዎች ትርፍ ሥጋ እንዳይሸከሙ ተብሎ፣ ስለ ሰው ጤና አጠባበቃቸው ለሚያስቡት ሰነፎች ነው እንጂ ጾም ጽድቅን ሊገዛበት የተሰራ አይመስልም በማለት ሃይማኖታዊ ጥቅሙን አሳንሰው ለሰብአዊነት ያለውን ጥቅም አድምቀው ያስረዳሉ።

በመሆኑም፣ በጥጋብ የሚመጣን ሃጢያት መከላከልም ሆነ ማከም የሚቻለው በማስራብ ይሆናል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ሲያም የሚራበው ሥጋ ነው። ሆዳምን፣ አግበስባሽን፣ በልቶ የማይጠግብን ጠጥቶ የማይረካ ሲሆን በዚህ ይቀጣሉ። ያም በዚህ እሳቤው ከምግብ

ብቻ መቆጠብ አይደለም፣ ሁሉም ስሜቶች አድርግ አድርግ ከሚሉ ምኞቶች እንዲቆጠብ ማቀቢያ ዘዴዎች ናቸው። ይኸውም ዐይን ክፉ ከማየት፣ ጆሮ ክፉ ከመስማት፣ ምላስ ክፉ ከመናገር መከልከል ነው። ወሬ እንዲጠማው፣ ብርድ እንዲያቃጥለው ማድረግ ነው። ከምግብም፣ ከምኞት፣ ከንግግር፣ ከድርጊት፣ ሁሉ ራሱን እንዲያቅብ ማድረጉ፣ ያጣው ሰብዕና እንዲመለስ ያግዛል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በመሆኑም፣ ሰው ሲያም ላምሮትና ለቅንጦት የሚበሉ ወይም ለመንፈሳዊ ኃይል ተቃራኒ የሆነ ፍትወትን የሚያበረታቱ የአልኮል መጠጦች፣ ሥጋንና ቅቤን ፣ ወተትንና እንቁላልን እንዲያርቅ ታዟል (አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣ 122) ። ይህንን የቆጠበውንም ለማጠራቀም፣ ለማቋት የሚሆን ከሆነ ሌላ ጠባይን ስለሚያመጣ፣ ጠመኛው ለምሳው ወይም ለራቱ ያለውን ነዲያንን እንዲረዳበት ይታዘዛል (መርጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ብዙ ልብስ ካለው አንዱን አስቀርቶ ሌላውን እንዲሰጥ፣ የሚመካበትን ነገር ሁሉ ከእጁ እንዲያርቅ በማድረግ፣ በሀብትና በጌጣጌጥ አምሮና ደምቆ፣ ተውቦና ተሞሽሮ መቅረብን በመከልከል ምላሄን እንዲለማመድ በቅንጦት እንዳይጠፋ ይጠበቅብታል። ሥጋን በማድከምና በማቅለል የነፋስነት ባሕርይውን በመመለስ ሃጢያትን የማቅለያ መንገድ ያደርገዋል።

በቤቱ ውስጥ ካለው የራሱ ከሆነው ከመብላት ስትከለክለው፣ ሌሎቹን ሰዎች እየከለከለ መብላት፣ መቀማት ክፉ እንደሆነ ይረዳል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። በዚህም ይቀጣል። ይህንን ያህል ወር፣ ይህንን ያህል ሰዓት፣ እስከ ቀኑ እስከ ሰዓቱ ተሰፍሮና ተለክቶ የቅጣት ውሳኔ ይሰጠዋል። የሚበላው ልክና አይነት ሁሉ ይወሰናል። እነዚህ ሁሉ ተባብረው የሚያመጡት ውጤት የበደለውን ሥጋ ቀጥቶ ማስተካከል ነው። ይህም ነፍስን ወደቦታዋ በመመለስ፣ ለነፍስ ሃይል በመስጠት፣ ሥጋ እንዲገዛ ማድረግ ይቻላል።

ፀሎት

ደመናው ተገፎ ፀሐይ ስትወጣ የፍጥረት ባሕርይ ከሆኑት መካከል ቀድሞ የሚሰለጥነው ነፋስ እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል። መምሸት፣ ሠርክ መኸን፣

የሚችልበት አእምሮ ተሰጥቶታል። ያን ማድረግ አለበት። እንዲንሸራሸርና እንዲስማማው ክፍት ቦታ መተው ይገባዋል ይላል(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይኸ ከጽድቅ ጋር አይየያዝም። ጤነኛ ሆኖ ለመኖር እንደዚያ ማድረግ ይኖርበታል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከዚህ ጭብጥ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ የሰነዘሩት ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ የሚከተለውን ብለዋል (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

> አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጅ በጥጋብና በስካር ከሰው ተራ እየወጣ ማህበራዊ ሕግን ሲጥስ፣ ጉልበተኛ እየሆነ ሰውን ሲያስቀይም፣ ስርዓት አለበኛ እየሆነ ሲሄድ ማህበራዊ መረጋገት እየጠፋ ሃገር በሥርዓት አልበኝነት ይታመሳል። ይኸ ትኩስ አቅም በአግባቡ ካልተመጠነ፣ አካልን ሥጋዊ ፍትወት እየተጫነው ከመጣ፣ አካላዊ ፍላጎቱን ለማርካት ሲል ያሻውን ሁሉ ማድረግ ካበላ ፍትወቱ ይበልጥ እየጋለ፣ እየፋመረ፣ እያቃጠለና እየተፋጀ የሚሄድ ይሆናል። ይህ ያልተመጠነ ስሜት ገደቡን ሲጥስ ያንንም ያንንም መመኘት አልገደብ ሲል አካል ባህርይውን አጥቶ ጠባይ ሆኗልና ሰውነቱን ይስታል።

በመሆኑም፣ የሰው ልጅ የሚያጎነብሰውና የሚደክመው፣ ወደ ምድር ዝቅ ዝቅ ማለት የሚጀምረው የምድራዊ ምኞትና የዓለማዊ ደስታ ምልክቶች የሆነው መሬት እየተጫነው ሲሄዱ ነው ይላሉ (ቄስ እንስማ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ሆድን ጥጋብ ሲጫነው እንደ ድንጋይ ይከብዳል። መሬት ሊይዝ ይወዳል። መንቀሳቀስን ይጠላል ይላሉ። በልጅነት ውስጥ ያለው ዋነኛ ባህርይ የነፋስ በመሆኑ በመክነፉ ውስጥ ቀላልነት እንዳለ ልብ ይሏል። ያገኘውን መብላት፣ ያዩትን መነካካት፣ መንቀዥቀዥ፣ አለመረጋጋትና በአንድ ቦታ ላይ አርፎ አለመቀመጥ የሚታይባቸው ለዚያ ነው ይሏቸዋል (ቄስ እንስማ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በቀላልነት ውስጥ አለመብሰል ስላለ ማስተዋልንና ስክነትን የነፋስ ግብር አያደርጋቸውም። በነፋስ ውስጥ ከቀላልነት በተጨማሪ የጀማሪነት ባሕርይም ይኖራል። በመሆኑም፣ መነሳት፣ መውጣት፣ ብቅ ማለት፣ መብቀል መወለድ፣ መብራት መታየት፣ መግለጥ፣ መባት፣ መግባት፣ መዥመር፣ መፍላት፣ መብቀል፣

ሥር መስደድ፣ መለምለም፣ ማፈጥፈጥ፣ በዚሁ ይመሰላሉ (ቄስ እንስማ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በመሆኑም፣ ብሩሁን የሚያጨልም፣ ብቅ ብቅ ማለትን የሚደፍቅ፣ መሮጥ መቦረቅን የሚያስር፣ መቅለልን የሚያከብድ የሚያቆሽሸና የሚያሳድፍ ነገር ሲያርፍበት ነው። በዚህ ጊዜ ያ፣ ይፈነጥዝ፣ ያብድ፣ ይከንፍ፣ የነበረው አካል የሚዘቅጥ፣ የሚደክምና የሚሰንፍ ይሆናል(ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከዕለት ወደ ዕለት የነፋስ ንፁሕ ባሕርይ እየደፈረሰና እየቆሸሸ ሄዶ መዝቀጥን፣ መዛልንና መስነፍን ባሕርይው ያደርጋል።

በነፋስ ባህርይ ውስጥ የነበረው ለመንሳፈፍ የሚያስችለው የቀዳሚነት የቀላልነት ባህርይው ላይ የጥቁርነት ነቁጥ ሲያርፍበት ነፋስ አፈር ሲጎርስ ይከብዳል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ከፍ ከፍ እንዳይል እየተጫነውና እየጎተተው ያደክመዋል። እንደልብ ከፍ ብሎ ለመብረር፣ ተነስቶ ለመሮጥ ያስቸግረዋል። ሥጋ ሲበዛ አእምሮ ይቀጭጫል፤ ይጫነዋል።

ይህ ጠባይ ሰዎችን አርክሶ ህመም ሲመጣ፣ አካል ሲደክም መድሃኒት የሚሆነው ጾም ነው ይላሉ (አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣ 122) ። አባ ጎርጎርዮስ ጾምን፣ "ሰውነት ከሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ መከልከል መወሰን ነው" በማለት ይገልጹታል (1991፣ 122)። ይህም ለሰውነት የሚያምረውን የሚያስጎመጅውን ነገር መከልከል ነው። አባ ገብረሥላሴ (ገብረሥላሴ ብርሃኑ፣ 72-73)፣ ጥንቱንም ጾም የተሠራው እንስሳዊ ባህርይ ላደረሰባቸው፣ ዘውትር በለስላሳ ምግብ ለሚማግጡ ሰዎች ወይም ለማይሰሩ ቦዘኔዎች ትርፍ ሥጋ እንዳይሸከሙ ተብሎ፣ ስለ ሰው ጤና አጠባበቃቸው ለሚያስቡት ሰነፎች ነው እንጂ ጾም ጽድቅን ሊገዛበት የተሰራ አይመስልም በማለት ሃይማኖታዊ ጥቅሙን አሳንሰው ለሰብአዊነት ያለውን ጥቅም አድምቀው ያስረዳሉ።

በመሆኑም፣ በጥጋብ የሚመጣን ሃጢያት መከላከልም ሆነ ማከም የሚቻለው በማስራብ ይሆናል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ሲያም የሚራበው ሥጋ ነው። ሆዳምን፣ አግበስባሽን፣ በልቶ የማይጠግብን ጠጥቶ የማይረካ ሲሆን በዚህ ይቀጣሉ። ያም በዚህ እሳቤው ከምግብ

ብቻ መቆጠብ አይደለም፣ ሁሉም ስሜቶች አድርግ አድርግ ከሚሉ ምኞቶች እንዲቆጠብ ማቀቢያ ዘዴዎች ናቸው። ይኸውም ዐይን ክፉ ከማየት፣ ጆሮ ክፉ ከመስማት፣ ምላስ ክፉ ከመናገር መከልከል ነው። ወሬ እንዲጠማው፣ ብርድ እንዲያቃጥለው ማድረግ ነው። ከምግብም፣ ከምኞት፣ ከንግግር፣ ከድርጊት፣ ሁሉ ራሱን እንዲያቅብ ማድረጉ፣ ያጣው ሰብዕና እንዲመለስ ያግዛል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

በመሆኑም፣ ሰው ሲያም ላምሮትና ለቅንጦት የሚበሉ ወይም ለመንፈሳዊ ኃይል ተቃራኒ የሆነ ፍትወትን የሚያበረታቱ የአልኮል መጠጦች፣ ሥጋንና ቅቤን ፣ ወተትንና እንቁላልን እንዲያርቅ ታዟል (አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣ 122) ። ይህንን የቆጠበውንም ለማጠራቀም፣ ለማቋት የሚሆን ከሆነ ሌላ ጠባይን ስለሚያመጣ፣ ጠመኛው ለምሳው ወይም ለራቱ ያለውን ነዲያንን እንዲረዳበት ይታዘዛል (መርጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ብዙ ልብስ ካለው አንዱን አስቀርቶ ሌላውን እንዲሰጥ፣ የሚመካበትን ነገር ሁሉ ከእጁ እንዲያርቅ በማድረግ፣ በሀብትና በጌጣጌጥ አምሮና ደምቆ፣ ተውቦና ተሞሽሮ መቅረብን በመከልከል ምጣኔን እንዲለማመድ በቅንጦት እንዳይጠፋ ይጠበቅበታል። ሥጋን በማድከምና በማቅለል የነፍስነት ባሕርይውን በመመለስ ሃጢያትን የማቅለያ መንገድ ያደርገዋል።

በቤቱ ውስጥ ካለው የራሱ ከሆነው ከመብላት ስትከለክለው፣ ሌሎቹን ሰዎች እየከለከለ መብላት፣ መቀማት ክፉ እንደሆነ ይረዳል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ የተወሰደ)። በዚህም ይቀጣል። ይህንን ያህል ወር፣ ይህንን ያህል ሰዓት፣ እስከ ቀኑ እስከ ሰዓቱ ተሰፍሮና ተለክቶ የቅጣት ውሳኔ ይሰጠዋል። የሚበላው ልክና አይነት ሁሉ ይወሰናል። እነዚህ ሁሉ ተባብረው የሚያመጡት ውጤት የበደለውን ሥጋ ቀጥቶ ማስተካከል ነው። ይህም ነፍስን ወደቦታዋ በመመለስ፣ ለነፍስ ሃይል በመስጠት፣ ሥጋ እንዲገዛ ማድረግ ይቻላል።

ፀሎት

ደመናው ተገፎ ፀሐይ ስትወጣ የፍጥረት ባሕርይ ከሆኑት መካከል ቀድሞ የሚሰለጥነው ነፋስ እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል። መምሸት፣ ሠርክ መኾን፣

መውረድ፣ መዘቅዘቅ፣ መግባት መጥለቅ፣ ድግዝታ፣ ጭልምልምታ፣ የመዓልት ጫፍ፣ የሆኑት ሁሉ የሌሊት ሥሮች በመሆናቸው ምሳሌነታቸው የመሬት ነው(ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። መሬት ፍጹም ለተገዛ ወይም ግዝ ለሆነ አካል አምሳል እነደሆነች እንዲሁ ቀደም ሲል ከቀረበው ገለጻ ለመረዳት ተችሏል። አርሰው ቢዘሩባት፣ ዘለው ቢረግጧት፣ ሆዷን ወግተው፣ ገላዋን ምሰው ያሻቸውን ቢፈጽሙባት ስለምትችልና ስለምትታዘዝ፣ የተማረከች ምርኮኛ፣ በጌታዋ ዐሳብ ዐዳሪ፣ በራሷ ማዘዝ የማትችል ባለመከራ ነች አስብሏታል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ስለዚህ፣ በቁሙ ሙት የሆነ፣ የማይላወስ፣ የማይንቀሳቀስ፣ የፈዘዘ፣ የተገነዘ፣ ባዶ የሆነ በመሬት የሚመሰለው በዚህ መነጽር ነው።

ይህ ዓለም የገዛቸውና የማረካቸው፣ ለዝናና ለጥቅም የሚሮጡ፣ ለሃብትና ለምኞት የሚደክሙ በዚህ ይመሰላል (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ራሱን የማይቆጣጠር፣ በራሱ የማያዝዝ፣ ጠፊና ቀሪ የሆነን ተግሯ ይሉታል። የተገዛ ከሙት ቁጥር ስለሆነ፣ ሙት የሆነ ደግሞ ተስፋ ቢስ በመሆኑ፣ ይህ ሃሳብ መሬት ቀሪና ጠፊ፣ አላፊና ከሳሚ፣ ንጋት ደግሞ የመታደስና የመነሳት አምሳል ይሆናል። ክረምት የክፉ መንፈስ ማደሪያ በመሆኑ መሬትን ስለሚያረክሳት፣ የረከሰ ዘመን የሚባረከው የፀሐይ መውጫና መሸጋገሪያ በሆነ ጊዜና ወቅት ላይ ነው (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። መላና ምክር፣ ዕውቀትና ጥበብ የሚገኘው ራስን ገዝቶና ከፍ አድርጎ በማስተዳደር በመሆኑ፣ ነፋስ ደግሞ ከፍ በሚል የሚገለጽ ስለሆነ፣ ዕውቀት የሚገኘው በዳመና፣ በሰማይና በአየር ክልል ውስጥ ይሆናል (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

ይህ አስተሳሰብ የሥጋ መክበሪያው ምድር፣ የዕውቀት መገኛዋ ደግሞ አየር ነው እንዲባል አስደርጓል። ነገር ተርጓሚ፣ የሰው ልብ ገማች፣ መርማሪ፣ ምስጢር አዋቂ፣ የሆነ ምድራዊውን ንቆ ለዕውቀትና ለጥበብ የሚጨነቀው ነው። አእምሮው ብሩህ የሆነ ሰው መጭውን ነገር ለመተንበይ የሚችል ሁሉ በዚህ ክልል የሚኖር ነው ተብሎ እንዲታመን ያደርጋል።

ህልምን የመተርጎም፣ እንቆቅልሽን የመፍታትና የተሰወረውን የመግለጥ ልዩ ችሎታ ቀላል ባሕርይ ባለው በነፋስ ይመሰላል። ነፋስ በብዛት ተዛምዶ የሚታየው ከሰማይ፣ ከአየር እና ከደመና እንዲሁም ከሁሉም የወፍ ዘሮች ጋር ነው። በጣም ወደ ሰማይ የሚመነጠቁና ከፍ ብለው የሚበሩ ከሆኑ የነፋስ አምሳልነታቸው ትልቅ ሲሆን፣ ከመሬት ወይም ከውሃ አካል ብዙም ርቀው የማይሄዱ ወደ መሬት የሚቀርቡት ደግሞ ዝቅተኛ የነፋስ ሃይል ያላቸው ናቸው (ዲያቆን ብርሃኑ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ በሰዎች ህይወት ውስጥ ነፋስ ከዕውቀትና ከማሰብ ጋር ተያይዞ የሚገለጥ ነው ይላሉ። በመሆኑም፣ የሃሳቦች መግኛና መምጫ መንገድ ከአየር ላይ ሆኖ እንዲታሰብ ያደርገዋል። ነፋስን ደግሞ መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፣ እንደ ትንፋሽና ሽታ ባሉ የማይጨበጡ ሰርሳሪ ስሜቶች የሚገለጥ ይሆናል። ምርምር፣ ምናብ፣ በሃሳብ መመንጠቅ ሁሉም የነፋስ ተግባሮች በመሆናቸው፣ ቀኑን ሙሉ ሲያስብ ሲያልምና በምናብ ሲጓዝ የዋለ ሰው አእምሮው በሰማይ ላይ ያለ ይሆናል(መሪጌታ ኮከበ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ተግባር ምድራዊ ሲሆን ሃሳባዊነት የነፋስ ጠባይ ነው።

ነፋስ ከጠዋትና ከፀደይ ጋር ስለሚያያዝ፣ በንጋትና በመጀመሪያ ውስጥ ያለው አየር፣ ፀሐይ የምትወጣበቱ አቅጣጫ ማለትም ምስራቁ፣ መግኛ ይሆናል። ዘር የሁሉም ፍጥረት መነሻውና መጀመሪያው በመሆኑ፣ ምድቡ በነፋስ ነው። የሥጋ በሕርይ በሆነው ነፋስ ውስጥ ያለው ዋነኛ ግብር ቀላል ነው ያስባለው ከፍ ስለሚል ነው። ቀላልነት ደግሞ ሳይቀላቀሉና ሳይበረዙ የራስን ጠባይ ብቻ በልክና በመጠን ይዞ መግኛ ይሆናል። ይህ ቀላልነት እሳት ሲነካው እየሞቀ፣ ውሃ ሲጨመርበት እየተጨባበጠ፣ መሬት ሲጫነው ደግሞ እየተሰባበረና እየተዋጠ የሚሄድ ይሆናል።

እንደ ሜድ፣ ግለባና የመሳሰሉ ቀላል ነገሮች አብነት የሚሆኑት ለነፋስ ነው ይላሉ መሪጌታ አይነኩሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እሳትን ገለባ አብዝቶ ከነበኘው ይበላዋል። ይህ የሚሆነው በሁሉቱ ባህርያት ውስጥ የጋራ የሆነ የመቀት ግብር ስላለ ነው ይላሉ። ነፋስንና ውሃን የሚያዋድዳቸው ቅዝቃዜ

በመሆኑ፣ የተከመረን ገለባ ውሃ ሲገባው ይጨባበጥና ይተኛል ይላሉ መርጌታ አይነኩሉ።።

በመሆኑም፣ ጭድ ቀላልነቱን የሚያጣው የመክበድ ባህርይ ያለው ነገር እየተጫነው ከሄደ ነው።። ከጭቃ ጋር አቡክተው ቤት ቢለስኑበት መክነፉን ትቶ ጭቃውን ከጭቃ ያዋድድ እና እሱም ይዋጣል።። ጭድን ጭቃ በዝቶ ሲበላው የሚጠፋ ይሆናል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።። ነፋስን የበዛ እሳት ያሳርረዋል፣ ልከኛ እና የተመጠነ ሲሆን ያነቃቃዋል።። ይህ የቀላልነት ግብር ከልተመጠነ የውሃ ግብር ጋር ሲገናኝ የበራሪነት ጠባዩ ጠፍቶ የሞተ ያህል አደብ አስገዝቶ ያስተኛዋል።። የራሱ የሆነው ግብሩ እያነሰ ሌሎች የራሱ ያልሆኑ ትርፍ ነገሮች ሲጨመሩበት ያ ብሩህ፣ በራሪ፣ ከፍ ከፍ ባይና ተመንጣቂ እንዲሁም ዘላይ የነበረው ፍጡር ተሳስሮ ይወድቅና ይቀበራል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።።

በግልጽነት፣ በንጽሕና ውስጥ ማወቅ፣ ማሰላሰል ሲጨመርበት ሩጫ ሰክን እያለ እንደሚሄድ ሁሉ፣ በተመጠነ ዕውቀትና ማስተዋል ቅንነት ገራምነት ሲጨመርበት ይህ የሚሞቅ ነገር ልከኛ ሆነ ይላሉ መርጌታ አይነኩሉ።። ነገር ግን፣ የእሳት ግብሩ አይሎ በነፋስ ላይ ካደረ ያሳብደዋል።። እሳት ከልከኛ ባህርይው ወጥቶ ሌላ ጠባይ ሲይዝ የሚበላ፣ የሚለበልብ የሚያቃጥል ይሆናል።። እሳት በማወቅ፣ በፍሬ፣ በማሰብና በማሰላሰል ስለሚመሰል፣ ይህ መጠን ልኩን አጣ ማለት ከአቅም በላይ በሰለ፣ አረረ፣ ልቆና መጥቆ ሄደ ማለት ነው።። በዚህ ጊዜ ያንን የተመጠነውን ንጽሕናና ገራምነት ውጦን ሃሳብና ዘር እያቃጠለው፣ እያሳረረው ይሄዳል።። አድርቆ፣ አሳርሮ ጠባዩን ያስለቅቀዋል።። በዚህ ጊዜ ከጥቂረቱ እየተላቀቀ ሄዶ ብሩህ ጠባዩን ይይዛል።። ከጠነከረ ግን አፍልቶ አሙቆ አቃጥሎ ያደርቀዋል።።

ነፋስን ውሃ በቀዝቃዛ ግብሩ ከእብደቱና ከድንፋታው አቀዝቅዞ ሊመልሰው ይችላል።። መክለፍለፉን አስትቶ ሊያሰክነውና ሊያረጋው ይችላል።። ሲያግበሰብስ የሰበሰበውን የእሱ ያልሆነውን ባህርይ አጥቦና አንጽቶ ጥቂረቱን በብሩህነት ባህርይው ሊያበራው ይችላል።። በርጥብ ባህርይው እጅጉን አግሎ ውሃ ያደርገዋል።።

በመጀመሪያው፣ የነፋስ ዘመኑ የሰው ልጅ አፈጣጠር በንጹሕ ስለመሆኑ አይተናል። የሕጻንነት ዘመን ለሃጢያት የተጋለጠ አይደለም ይባላል። ሕፃናት በዚህ ዘመናቸው፣ እንኳን እጃቸውና እግራቸው፣ ባሕረያቸው ሃጢያትን አያስበውም ይላሉ አባቶች (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እንኳን የሚሰሩበት የሚያስቡበት ጊዜያቸው እንዳልሆነ ይነገራል። ህጻናትን ንጹሕ ያስባላቸው ክፉ ነገሮችን ለማሰብና ለመስራት ጊዜያቸው ገና በመሆኑ ነው ተብሎ ይታሰባል። ባልና ሚስት ከልጆቻቸው ጋር ይተኛሉ። ሕጻናት ግን ባልና ሚስት እንኳን አብረው ለምን እንደሚተኙ አያውቁም። የትኛው ወንድ የትኛው ሴት እንደሆነ፣ ማን ለማን ምን ያደርጋል የሚለው ለእነሱ፣ ገና ያልደረሱበት ጥበብ ነው(ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ይኸን ማወቅ ሲጀምሩ ወደ መብሰል፣ መለየትና ማስተዋል እየተሸጋገሩ ለመሆናቸው ምሳሌ ይሆናል። በመሆኑም፣ ሕጻንነት በሃሳባም፣ በገቢርም፣ በነቢብም ንጹሕ በመሆኑ ድንግል ናቸው ይባላል።

ባሕርያቸው ሃጢያትን ስለሚከላከል ፆም፣ ፀሎት፣ ስግደትና ንስሐ የሚባሉ ነገሮች እስከ ሰባት ዓመት ድረስ ያሉ ሕጻናትን አይመለከትም (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ከሰባት ዓመት በኋላ ግን ወደዚህ ነገር ሃሳብ ስለሚመጡ ዓለምን ማየት፣ ማስተዋልና ማሰብ ስለሚጀምሩ፣ በማወቅ ይረክሳሉ። በመሆኑም፣ ከዚህ ጊዜ በኋላ እነዚህን የንስሐ ጥበቦች እንዲያስቡ ይታዘዛሉ።

ይኸ አመለካከት፣ የሰው ልጅ ወደ ኃጢያት የሚገባው ማወቅና መመርመር ሲጀምር ለመሆኑ አሳይ ነው። ሃጢያትን ዕውቀቱን፣ ፍሬውንና ውጤቱን በሚገባ በመጠቀምና ባለመጠቀም የሚመጣ ይሆናል። ምኞት፣ ስሜትና ፍላጎት እንደመራን መኖርን ዕውቀታችን ካለማመዳን የሥጋ ባህርያችን እየጨመረ፣ እየጠነከረና እየበሰለ የሚሄድ ይሆናል። ምኞት ተግዥ አድርጎን ሥጋዊ ምኞት ለፈቃደ ሥጋው አሳድሮ ታዛዥ ያደርገናል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

አንዳንዶቹ ራሳቸውን ገዝተው፣ የስሜት ፈቃዳቸውን ተቆጣጥረው ዓለምን ንቀው ሊመንኑ ይችላሉ፡፡ ሰው ራሱን እንዲገዛና እንዲቆጣጠር ሆኖ የተፈጠረ በመሆኑ፣ በራስ ላይ የበላይነትን ማግኘት ከቻለና ስሜቱንና ምኞቱን እንዳሻው የሚያዝዝበት ከሆነ ከርክሰት ይድናል (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ በመሆኑም፣ ርኩሰትን የሚያመጣው ማናለብኝነትና ከማን አንሳለሁ የሚል ትዕቢት መሆኑ ነው፡፡ ዕውቀት ራስን መግዛም ማንነትን አርካሽም ሊሆን ይችላል፡፡ ያ፣ ጠባያችን ተለውጦ ንጽሕናችንን እንዳያሳጣን፣ ንጽሕናችን ረክሶ ቅድስናችንን እንዲያበላሽብን ምኞትን መግደብ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ የተነሳ፣ የሰው ልጅ ማንኛውንም ለዕለት ጉርሱና ለቀን ልብሱ የሚሆኑ ነገሮችን በላቡና በጥረቱ ብቻ እንዲያሟላ ታዝዟል ይላሉ (መሪጌታ አይነኩሉ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ ነገር ግን፣ ሁሉንም ሰዓቶችና ቀኖች ለሥጋ ፍላጎት ማሳኪያ ብቻ እንዲጠቀምባቸው አልታዘዘም ይላሉ፡፡ ግማሹን መንፈሳዊ፣ ግማሹን ዓለማዊ ሥራ እንዲሰራባቸው ተሰፍሮ ተሰጥቶታል፡፡ ለግሉ የሆነ ነገር ሲሠራ፣ ሲለፋና ሲደክም ይቆይና የተወሰኑ ሰዓቶችና የተወሰኑ ቦታዎች ላይ ሲደርስ ጥንቃቄ፣ ርጋታ፣ ስክነት ያደርጋል፡፡ ቆም የሚለውም አብዛኞቹ ደንብ በሚገለጽባቸው፣ ምግባር በሚሰበክባቸው፣ ማህበራዊ ትስስርን ለማጠናከር በሚውሉ ቀኖች፣ ሰዓቶችና ወቅቶች ላይ ነው (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡

ከእነዚህ መከካል ሰንበት ዋናው የተከበረውና የተቀደሰው ቀን ነው፡፡ ይህን የዕረፍት ጊዜ እያንደንዱ የማህበረሰቡ አባል የታመመን እየጎበኘ፣ የተጎዳን እያስተዛዘነ፣ ዘመድ ወገኑን እየጠየቀ በምግባርና በመልካም ሥራ እንዲያሳልፈው የታዘዘበት ቀን ነው፡፡ ይህ ቀን በተለየ ተመርጦ ለዚህ የዋለው፣ ስንሮጥና ስንባክን ለግል ጥቅምና ለግል ስኬት ስንሰራ፣ ስናጠራቅም፣ ስንሰበስብ ቆይተን በዚያው እንዳንጠፋ ገደብ ለማበጀት ነው በማለት ያስረዳሉ (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ በዚህ በተለመደው ሥራ ውስጥ በሰዓቶች፣ በቀኖች መካከል መበላለጥ በማድረግ፣ በየጊዜውና በየሰዓቱ የሰው ልጅ ሰውነቱን እንዲያከብርባቸው፣ ሰብአዊነትን እንዲማርባቸው የተመረጡ ቀኖችና ሰዓቶች

ተሰጥተውታል። ቦታዎች ልቅና የማይገቱ ሆነው ስላልተፈጠሩ፣ በማንኛውም እንቅስቃሴ ባሕርያቱን የሚያመጣጥንባቸው ይሆናሉ (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

አቶ ይዘንጋው፣ (2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20 ከተደረገ ቃለመጠይቅ)፣ "ሰንበት ሲጣላ ከአርብ ሮቡ ይብሳል" ይባላል ይላሉ። ማንኛውም የማኅበረሰብ አባል፣ በሰንበት እንዲያድርግ የታዘዘው የታመመ እንዲያይባት፣ የሞተ አልቅሶ እንዲቀብርባት፣ የበረደውን እንዲያለብስባት፣ የተራበን እንዲያበላባት ነው ይላሉ። በሰንበት ትጥቅ አትታጠቁባት ይባላል(አቶ ጫኔ፣ 2003 ዓ/ም፣ ሰኔ 5 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ቤተክርስትያን ሳመሳት፣ የታመመ ጠይቁባት፣ ያጣ መጥውቱባት፣ የተጣላ አስታርቁባት እየተባልን ነው ያደግን ይላሉ። እማሆይ ማናዬሽ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27 የተካሄደ ቃለመጠይቅ) በሰንበት ውሃ ተቀድቶ በሊጥ ቡሃቃ እይገባም። ሰው ሞቶ ለቀብር ወንዝ ተሻግረው ቢሄዱ፣ ግብዓተ መሬት እንደተፈጸመ ወዲያው ሳይቀመጡ በቁማቸው፣ እህል ሳይቀምሱ ተመልሰው ይመጣሉ እያለ ያስረዳሉ። የሚበላ ጠፍቶ ምግብ ተዘጋጅቶ ቢበላ እንኳ አያድርም። ለእለት ፈጭተው ቢበሉ ከእህል ጋር አይቀላቀልም በማለት በሰንበት የሚደረገውን ጥንቃቄ ይናገራሉ።

በመሆኑም፣ ከሰኞ እስከ አርብ የተሰራ የዓለም ስራ ሁሉ በዚህ ቀን በፀሎት፣ ከፍ ከፍ የሚያደርግ የምግባር ሥራ በመሥራት የሚታደስ ይሆናል። ከፈጣሪ ምህረትን በመለመን፣ ለታመመ ምህረትን በመጠየቅ፣ ራስህን ደግሞ እየከሰሱ ጥፋትን በማስታወስ የኃጢያትን ዕድፍ ያነጥባታል (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2005 ዓ/ም ነሐሴ 8፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የራስን ጥፋት ተቀብሎ ለመመለስ ከልብ መከጀል ይገለጽባታል።

አቶ ተዘራ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ "በጎዛምን ጻጉሜ ስትመጣ ልብሳችሁን እጠቡ፤ ማሳችሁን ደቅድቁት ይባላል። በዚህ ቀን ገበሬው ሁሉንም ማሳውን ያዳርሰዋል። ሁሉንም ልብሱን ያጥበዋል። ማዳረስ ካልቻለ በውሃ ይረጨዋል። የሩፋኤል ዕለት ውሃ ቀድተው በቡሃቃ ይጨመራሉ። የሩፋኤል ዕለት ከዘነበው ዝናብ ቀንሶ በማስቀመጥ በደመራ ዕለት ለሚጎተተው ዳቦ የሊጥ ማቡኪያ እንዲሆን እናቶች ያስቀምጣሉ። ይኸ ሁሉ የሚደረገው ክረምት ያረከሰው ሁሉ

ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P.O. BOX 2170

በሩፋኤል ጠበል ስለሚባረክና ስለሚነጻ ነው በማለት ሊቀትጉሃን ያስረዳሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

እናቶች እቤት ያደረውን የየቀኑን ቆሻሻ ወይም አመድ፣ አውጥተው የሚደፉት በ ሌሊት ነው (ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ወ/ሮ ሰዋገኝ ሴቶች ጠዋት ተነስተው የበሉበትን ዕቃ ያጣጥባሉ፤ ክፍቱን ያደረ መብል ወይም መጠጥ ካለ አውጥተው ይጥላሉ ወይም ይደፉታል። በጠዋት ተነስተው ወደ ቤተክርስትያን ይሄዳሉ። የጠዋት ጸሎት ያደርሱና ከቁስ ቀርበው ተባርከውና ቤተክርስትያን ተሳልመው ይመለሳሉ ይላሉ። እንደ ቡሃ ዕቃና ጉድ ጓድ ያሉ ነገሮች ሳይከደኑ ካደሩ ግን ከተቀደሰበት ጠበል አምጥተው ይጨምሩበታል ይላሉ (ወ/ሮ ሰዋገኝ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 28 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ቁስ እንስማ፣ "በጳጉሜ፣ ትንሽ ትልቁ ወንዝ ወርዶ ገላውን ይታጠባል። ልብሱንና ዕቃውን ሁሉ ያጥባል። በዓመት ሞት ምክንያት የረከሰውን የነካ ዕቃ፣ ያደፈ ገላ አዲስ ዓመት ነግቶ ሽግግር ከመሆኑ በፊት ቀድመው በሩፋኤል ዕለት በተባረከው ውሃ ታጥበው ይነጻሉ" ይላሉ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። ሰውም በማህበርና በቤተሰብ እየሆነ ደመራ ደምሮ እርድ ፈጽሞ ዘመኑን በምስጋና በጸሎት ለመቀበል ይሞክራል። ከደመራው እሳት ችቦ በመለኮስ መቃብር ቦታዎችን፣ የእህል ማሳዎችን፣ የማብሰያ ዕቃዎችን፣ የእህል ጎተራዎችን ሁሉ 'እንኩሮ ገባሽ' እያሉ ልጅ አዋቂው የመባረክና የመሻገር ሥርዓት ይፈጽማል (ቁስ እንስማ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። በጳግሜ አክርማ ቀጭተው እየጎነጎኑ በእጃቸው እንዳአምባር ያሰሩትን "አጥንቢላ" የሚባል ጌጥ ደመራው ሲለኮስ አውልቀው ያቃጥላሉ። "ቁርጥማትና ደዌ ተቃጠል" ይላሉ። ጠዋት ፌጦ ፈትፍተው ይቀምሳሉ፤ ቀበርቾ አጭሰው አካባቢውን ያጥናሉ። አሮጌውን ጥለው በአዲስ ልብስ ይንፈላሰሳሉ (አቶ ዘመኑ ከፋለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 24፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

አቶ ተዘራ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፣ ጳጉሜ ክረምትንና በጋን የምታገናኝ ድልድይ ነች ይላሉ ። ክረምት ተብላ ከነሐሴ ወይም በጋ ተብላ ከመስከረም ስለማትደመር፣ ራሷን ችላ የቆመች መሻገሪያ ወር ነች። በዚች

የመሸጋገሪያ ጊዜ የባሕርይ ሥሮች በአዲስ ስለሚታደሱባት፣ የዕጽ እግር የሚያውቁ ባለሙያዎች የዓመቱን መድሃኒት የሚቆርጡት ዘመን በታደሰባትና በረከት በሆነባት ቀን ላይ ነው (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ዕጽም የሚነግሰው በዚች በጸልኦት በተባረከች ቀን ሲቆረጥ ነው ይላሉ አቶ ተዘራ።

ዕፅ የሚቆረጠው ክፉና ደጉን ባለዩ፣ ባልተጋነናቸው ሕጻን ልጆች ነው። ልጅ ሲታጣም ሱባኤ ገብተው፣ ከሴት ርቀው፣ ጸልኦት አድርሰው ነው። ንጽሕናቸውን ሳይጠብቁ የሚሰሩት ሥራ ሁሉ ውጤቱ መልካም እንደማይሆን ይታወቃል። ወደ መቁረጥ ሲሄዱም እህል አይቀምሱም። በመሆኑም፣ የባሕርይ ግብራቸው እንዳይፋለስ ይጠነቀቃሉ። ዕፅዋ ከተቆረጠች በኋላም እህል ውሃ ከሚደረግበትና የተለያዩ ዓለማዊ ስራ ከሚፈጸምበት ቦታ ያርቁታል። የታመመው ሰው ወይም ግለሰብ መድሃኒቱን የሚጠጣው በባዶ ሆዱ ሆኖ ነው (መሪጌታ ይሄይስ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይኸ ሁሉ የሚሆነው በመቀላቀል የሚመጣውን የባሕርይ መድከም ለመከላከል ነው።

ወ/ሮ በየነች ምናሉ፣ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) ምጥና ጣዕረ ሞት አንድ ናቸው' ይላሉ። በምጥ ሰዓት ጉልበት ይከዳል፣ ልቦና ይዘነጋል፣ አካልን ማዘዝ ይሳናል፣ ቀልብን መሰብሰብ ያስቸግራል። በተለይ አንዳንድ ወላዶች ምጥ ይጠናባቸዋል። ትንፋሽ እያጠራቸው፣ ገላቸው እየቀዘቀዘና እየበረደ ይሄዳል። በዚህ ጊዜ የወላዷን የመገላለገል ብስራት ቀርበው የሚከታተሉ ሰዎችን፣ "ቀበቶ ፍቱ፣ መቀነት አላሉ" ይባላሉ (ወ/ሮ በየነች፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 24፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)። እናቶች ተንበርክከው ማርያም ማርያም ይላሉ።

ይች ሴት የመሬት ባሕርይዋ በሥጋዋ ውስጥ እየከበደ፣ መንፈሳዊነቷ እየቀነሰ ወደ መውደቅ፣ መድከም፣ መስነፍና ፀጥ ወደማለት እየገባች ለመሆኗ አሳይ ነው። በዓለም ትዳር ለመታሰራቸው ምልክት የሆነውን ቀበቶና መቀነት ወንዶችና ሴቶች ፍቱ መባሉም፣ በዓለም የመታሰር ምልክት የሆነውን ነገር በመተው፣ ዓለማዊ ነገርን ንቀው ላቅ ላለና ለተመረጠው መንፈሳዊ ዓለም ተገዥ እንዲሆኑ ለማሳሰብ ነው። የዓለም ነገራቸውን እርግፍ አድርገው ትተው ለፈጣሪያቸው ለመገዛታቸውና

ሥጋቸውን ለመናቃቸው ምሳሌ የሚሆን ነው (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

ድካሙ ከጠነከረና ማስተዋልና ማገናዘብ እየራቀ ከመጣ፣ "ቀዘቀዘች፣ ልቧ ቆመች" እያለ ይጨናነቃሉ። ይህንን መደንዘዝና መፍዘዝ ለመመለስ የአካባቢው ሰው ፈጥኖ የሚያደርገው በአደጋ ላይ ያለችውን ነፍሰ ጡር ከገባችበት ድብርትና ሰመመን እንድትነቃ ዘመድ አዝማድ እንዲሁም ጎረቤት ተሰብስቦ ኃይልና ጉልበት ያለውን ነገር በአጠገቧ በማከናወን ቀልቧ የሚመለስበትን ዘዴ ያፈላልጋሉ። ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ፣ እሳት ያነዳሉ። ቤቱ ቀዘቀዘ አሙቂት ይባባላሉ (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

የመጀመሪያው መከራ፣ ከፍተኛ የሆነ ብርሃን ወደ ቤት እንዲገባ ማድረግና ከፍተኛ የሆነ ድምጽ በማውጣት የምትነቃበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። ለእነዚህ ድርጊቶች አጋዥ የሚሆኑት ብረት ምጣድ መደብደብ፤ ከፍተኛ ድምጽ ሊያወጡ የሚችሉ ዕቃዎችን ወደ ነፍሰ ጡሯ ጆሮ በማስጠጋት ማንኳኳትና እሳት ማንደድ ናቸው (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ደም እየፈሰሰ ከሆነ ደግሞ ቀዝቃዛ ውሃ በአካሏ ላይ መቸለስ ይኖራል። ከፍ ባለ ድምጽ ስሟን እየጠሩ መቀስቀስ እንድትነቃ መነቅነቅ መገፋት፣ ማሻሸት ሁሉ ያደርጋሉ። እነዚህ ዘዴዎች አቅላቸውን የሳቱ ሰዎች ከገቡበት ሰመመን እንዲቀሰቀሱና እንዲነቁ የሚረዱ መፈወሻ መንገዶች ናቸው በማለት አቶ ተዘራ አስማረ ይገልጹታል (አቶ ተዘራ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ14፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ከላይ ለመመለሻነት ያገለገሉትን ዘዴዎች ዲያቆን ብርሃኑ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) የጸሎት አምሳሎች ናቸው ይሏቸዋል። ሁኔታውን ሲገልጹ፣ ጸሎት ከድካም ያበረታል፣ ከጭንቀት ያረጋጋል፤ ከሀዘን ያጽናናል በሚል ነው። የሚጸልይ ሰው ኃይልን ያገኛል። ፈቃደ ነፍስ በሥጋ ላይ ኃይል እንድታገኝ ከሚረዷት ኃይሎች መካከል ጸሎት አንዱ ነው (ዲያቆን ቃኘው፣1994፣ 6)። ጸሎት የራስን ስሜት ለመግዛት አጋዥ ነው ይላሉ። ከነፍሳችን ጋር፣ ከልቦናችን ጋር የምንነጋገርበት መንገድ ነው። ራስን መግዣና መጠየቂያ የሆነ ነው።

መንፈስ ጠላፊው የቡዳ ሃይል ወደ ሰዎቹ አካል እንዲገባ የረዳው የባሕርይ መጣረስ ነው፡፡ በሰው ልጅ የጥንካሬ ዘመን ጉልበትና ኃይል የሆኑት በእንቅስቃሴ የሚገለጠው ነፋስና በዕውቀትና በልቦና የሚመሰለው እሳት ናቸው፡፡ ይኸው መንገድ በተራው የወጣችውን ነፍስ ወደቦታዋ እንድትመለስ ለማድረግ የባሕርያቱን መዛባት ለማስተካከል የሚጠቅም ዘዴ ይሆናል፡፡ በድንጋጤ የወጣችው ነፍስ ራስን በማወቅ ተመልሳ ቦታዋን ስትይዝ ችግር ውስጥ ገብቶ የነበረው አካል ማስተዋልን በምትሰጠው የነፋስ አካል አማካይነት አቅልን ገዝቶ ወደ ነበረ ሰላሙ ይገባል የሚል ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ቡዳ የበላው ሰው መንፈሱ የሚቀሰቀሰው በሞቅታ፣ በጨዋታ፣ በሀሳታና በልቅሶ ጊዜ ነው ይባላል (ወ/ሮ ውዴ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 5 የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ በልተው ጠጥተው ሲጠግቡና ሲሰክሩ አንዳንዶቹ ያለቅሳሉ፣ አንዳንዶቹ ይጮኻሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ይስታሉ፡፡ ሞቅ ሲል በጫዋታ መካከል ብዙ ሰዎች ይለፈልፋሉ፡፡ ግርግር ባለበት ቦታ መንፈሱ ፈጥኖ ይነቃል ይባላል፡፡ ቡዳዎች ሲለፈልፉ፣ ጥምቀትና የመሳሰለ በዓላት በሚከበሩበት ላይ፣ ለየት ያለ ነገር በሚያከናውኑ ጊዜ ነው አይኔ ውስጥ የገባ ይላሉ፡፡

እናቶች እብድ ሲያዩ ውሃ ድፉበት ይላሉ፡፡ ቀልቡን ስቶ ላበደ ለከነፈ ውሃ መድሃኒቱ ነው ይባላል (ወ/ሮ ውዴ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 5፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡ ዝናብ ጠብ ጠብ ሲያደርግ ቆይቶ ነፋስ ከነፈሰ ሊያባራ ነው ይላሉ (ቄስ ዕድሜአለም፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ በመሆኑም፣ ነፋስና ውሃ እንዲሁም እሳትና ውሃ እርስ በርስ የሚደካከሙ መሆናቸው ነው (መሪጌታ አይነኩሉ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)፡፡ አውድማ ውስጥ ማለትም ፍሬው ከገለባ በሚለይበት ቦታ ውሃ አይገባም ይላሉ፡፡ አበራይተው ሳይጨርሱ ሰዎች እጅና እግራቸውን አይታጠቡም (አቶ ጤናው፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)፡፡ ተኝቶ ሳለ እየቃዠ አልነቃ ካለ ፊቱን ውሃ ያስነኩታል፡፡ ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ (2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት) ፀሎትን እንደ ውሃ ብንወስደው ለእሳታዊ ባህርይ አስፈላጊ ነው ይላሉ ፡፡

እሳታዊ ባህርይን ለማስተካከል ፀሎትን በውኃነት መጠቀም ይቻላል። እሳት ላይ የጸሎት ውሃ ሲከለበስ የስሜት ግለት ለዘብ ይላል። በፀሎት ውስጥ ያለው መድሃኒት ብዙ ነው። ፀሎት ውስጥ ብዙ ማዕድናት አሉ ይላሉ አባቶች። ጠባዬ እሳትን መግደል የሚችሉት የሚገኙት ከእነዚህ ከእነዚህ መካከል ነው በማለት ይናገራሉ (ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 11፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት)።

ፀሎት በንጹሕ ልብ፣ በተሰበረ መንፈስ፣ በተመስጠ ሆኖ የሚካሄድ ነው። ልቦናን ለመልካም ነገር መክፈት ነው። በንዘን ልቡናን የሚያቃጥል የሚያናድድ ንስሐ ነው። ምላስ ቢያፍር፣ አፍ ቢከላተፍ፣ ቢንተባተብና መናገር ቢያዳግተው ልብ በዕንባ ልሣንነት ርቱዕ ሆኖ ይናገራል (ዲያቆን ቃኘው፣1994፣ 15) ። ዕንባ የተሰበረ ልብና የንጹሕ ሕሊና ፍሬ በመሆኑ የእውነተኛ ስሜት መገለጫ ነው (ዲያቆን ቃኘው፣1994፣ 15)

8.4. የማስፈጸሚያ ስልቶች

አንድ የተዛባ ባሕርይ የመስተካከያው መጠኑ እስከምን ነው? ልከኛ የሚሆነው ምን ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው? የሚሉትን የሚመልስልን የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው። የባሕርያቱን ትክክለኛነት ከአቅጣጫ፣ ከመጠንና ከልክ አንጻር እንዴት ይመዘን ሲባል በግልጽ የተቀመጡ መመጠኛ መንገዶች አሉ። ለዚህ ማስተካከያነት የሚያገለግሉት ደግሞ ቁጥሮችና አቅጣጫዎች ናቸው።

8.4.1. ቁጥሮች መጠንን ግላጭ ማስተካከያዎች

በነዛምን ማኅበረሰብ ህይወት ውስጥ የተወሰኑ ቁጥሮች ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለማስፈጸም ተደጋግመው ይመጣሉ። እነዚህ ቁጥሮች በነዋሪው ሰው ህይወት የማይገቡበት የኑሮ ዘይቤ የለም ይባላል (አቶ በቀለ ውብሸት፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 14 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። መጠንን፣ ልክን፣ ስፍርን በመለካትና፤ በሃሳብ፣ በባህርይና በድርጊት መልክ ለሚገለጹ ነገሮች የመስፈሪያ አሃድ በመሆን፣ ተደጋግመው ይመጣሉ። ነገሮች ወይም ሁነቶች በምን ያህል እርቀት ቢደረጉና ቢባሉ፣ በምን

ያህል ብዛት ቢዘጋጁና ቢፈጸሙ ይሳካሉ? በሃሳብ፣ በባህርይና በድርጊት ፍጹም የሆነ ጥምረት፣ መስማማትና መዋሃድ እንዴት ይመጣል? ልከኛ መጠን ላይ የሚደረሰው በምን ያህል መጠንና ልክ ሲከናወን ወይም ሲደረግ ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ የሚያሰገኙና አስተሳሰብን የሚመሩ ናቸው። በተለያዩ የልኬት ሚዛኖች ውስጥ መመጠኛ ሃይሎች በመሆን፣ የመብሰልንና የመብቃትን፣ የመድረስንና ምልዑ የመሆንን ደረጃ ሁሉ የሚነግሩ፣ ትክክለኛ የሆነ የጣዕምና የቃና ስሜት እንዲፈጠር ምክንያት በመሆን የሚመረጡ ናቸው።

ይህንን ነጥብ ታሳቢ በማድረግ፣ በህብረተሰቡ የዕለት ከዕለት ህይወት ውስጥ ቁጥሮች ካላቸው ቁልፍ ሚናና አገልግሎት አንጻር 7 ቁጥር በንስሐ ላይ ባላት ጥቅም ተመርጣ እንደሚከተለው ተተንትናለች።

የ7 ቁጥር ሚና

በማኅበረሰቡ ህይወት ውስጥ ልዩ አገልግሎትንና ጥቅምን አላቸው በሚል በተለያዩ አሰራሮችና አደራረጎች ውስጥ ተደጋግማ ከሚጠቀሱ ቁጥሮች መካከል 7 ቁጥር ዋነኛዋ ነች። ቁጥሯ መለኮታዊ ሀይል ይዛ የምትገኝ በመሆኑ፤ ወደስኬት፣ ትክክለኛነትና ወደመታደስ ከሚያደርሱ እሳቤዎች ጋር በእጅጉ ተያይዛ የምትታሰብ ነች (መሪጌታ ይሄይስ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። የሞተ ሰው ከወጣበት ቤት ያሉ ሰዎች በሰባተኛው ቀን ጠራርገው ሁሉ ይላጫሉ፣ ራሳቸውንም ጢማቸውንም ቅንድባቸውንም፣ የገላቸውን ጠጉር ሁሉ ይላጫሉ። ልብሳቸውንና ገላቸውን በውኃ አጥበው ንጹሕ ይሆናሉ(ዘሌዋ፣ 14፣ 9)።

አንድ ሰው ንጽህናውን በሚያጓድልና ሰብዕናውን በሚያራክስ ሥራና ሁኔታ ውስጥ ሊገባ ይችላል። በጸጸትና በንስሀ ራሱን አስተካክሎ ወደነበረበት ሁኔታ ለመመለስ በሚያደርገው መከራ በግልም ሆነ በቡድን ምህረትንና መንጻትን ለማግኘት ሲጥር ሰባት ቁጥር ወደቀደመ ባሕርይ መላሽና የማንጫ ኃይል ሆና ትመጣለች ይላሉ (መሪጌታ ይሄይስ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። አንድ ነገር የነበረ መልኩንና ክብሩን ለማግኘት በሚያደርገው ጥረት ውስጥ አጋዥ ሆና የምትመጣም እሷ ነች። ለምሳሌ፡- ሴት ልጅ የወር አበባው ከመጣ

የቤተክርስቲያንን ቅጽር ትረግጥ ዘንድ አይቻላትም። የወር አበባዋ መጥቶ በጠራ በሰባተኛው ቀን ላይ ብትገባ ግን ነውር የለውም (እማሆይ ማናዬሽ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 27፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ።

እንደአህያና እንደፈረስ ያሉ የቤት እንስሶችን ያዋለደና ያጣፈረ ሰው፣ ምግብ ከመብላቱና ሌላም ዕቃ ከመንካቱ በፊት እጅና እግሩን በውሃ ይጠብ፤ ልብሱንም አለቅልቆ በቄስ ይባረካል ይባላል (ቄስ እንስማ ደለለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18 ፣የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ቄስ እንስማ፣ ተባርኮም ቢሆን እርክሱቱ የሚለቀው በሰባተኛው ቀን ላይ በመሆኑ እስከዚህ ቀን ድረስ ወደቤተክርስትያን አይገባም ይላሉ። እነዚህ እንስሳት የእግር ጥፍራቸው የሚጣፈረው በተወለዱ በሰባተኛው ቀን ላይ ነው (አቶ ቄሜ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 21፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህን ቀን ካለፉ ግን ጥፍራቸው ስለሚጠነክር ለመቁረጥ ያስቸግራል፤ ካልተቆረጠ ደግሞ ይጃለፋል በማለት አቶ ቄሜ ይናገራሉ። በዳ የበላው ሰው መንፈሱን ለማባረር የሚጠመቀው አንድ ሰባት ነው፤ ካለቀቀው ሁለት ሰባት፣ ሶስት ሰባት እያለ ይጠመቃል (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። መርጌታ ሞላ፣ ሰባት ሳይሞላ ጀምሮ መተው ነጻ አያደርግም ይላሉ።

ቄስ እንስማ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) የአካባቢው ሰው፣ አውራ ንብ እየበረረ እንዳያስቸግረው ቅፍጠን ውስጥ ለአንድ ሳምንት ማለትም ለሰባት ቀን አስቀምጡት ይላሉ። "ሰባት ቀን ከቆየ ይለምዳል። ንቡም የትም አይሄድም፤ ይረጋል ይላሉ። ሳምንት ሳይሞላ ለምዷል ብለው ከፍተው ከለቀቁት ግን ንቡን ይዞ ይጠፋል" ይላሉ (ቄስ እንስማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ። አንድ ንብ እስከሰባት ጊዜ ይወልዳል የሚሉት ቄስ እንስማ፣ በጋ የከረመውን "ነባር"፣ ሳምንት ጠብቆ የሚረጋውን ደግሞ "ዲቃላ" ብለው ይጠሩታል። ዲቃላው ፈጣን ነው። ተናካሽ ነው፣ ጠባይ የለውም። ከዚያ አዲሱ ሲወለድ ነባሩ እየለቀቀ እስከ ሰባት ጊዜ ይቆያል (ቄስ እንስማ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18 የተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በልጆች "የሰኞ ማክሰኞ" የጨዋታ ሜዳ ላይ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ባሉ የቀናት መደቦች ውስጥ የጨዋታው ደንብ በአንድ እግር እየዘለሉ እንዲጫወቱ ያዝዛል

(ወ/ሮ አፀደ መኮንን፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ የተገኘ)። በአንድ እግር እያነከሱ ስድስቱን ቤቶቹ ካለፉ በኋላ፣ ከሰባተኛው ቤት ማለትም እሁድ ላይ ሲደርሱ፣ በሁለት እግር እንዲያርፉ ይፈቅዳል። ትንሽ አርፈው ትንፋሽ ከሰበሰቡ በኋላ፣ ከሄዱበት መንገድ ሲመለሱ፣ ሌሎቹን ስድስት ቤቶች እንደገና በአንድ እግር እየዘለሉ በመሻገር ዙሩን ያጠቃልላሉ (ወ/ሮ አፀደ መኮንን፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ የተገኘ)። ማኅበረሰቡ ከሰኞ እስከቅዳሜ ያሉትን ቀናት በሥራ ካሳለፈ በኋላ፣ ቀሪውን አንድ እሁድ በሽተኛ በመጠየቅ፣ ዘመድ በመጎብኘት፣ የተጣሉትን በማስታረቅ፣ ጋብቻ በማስፈጸምና ሌሎችን መንፈሳዊ ተግባሮች በማከናወን የሥጋ ያልሆኑ የምግባር ተግባሮችን እየሠራ ቀኑን ያከብራል፤ በማረፍም ያሳልፋል (አቶ ይዘንጋው መኮንን፣ 2006 ዓ/ም፣ ታህሳስ 20፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)።

በታላቁ መጽሐፍ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰው፣ ፈጣሪ የስድስቱን ቀናት የፍጥረት ስራ አጠናቅቆ ያረፈው በሰባተኛው ቀን ላይ ነበር። ስራውን ሁሉ ፈጽሞ፣ በሰባተኛው ቀን ላይ ስለማረፉ ተገልጸ ይገኛል (ዘፍ 2፣2)። በዚህ የተነሳ፣ ይህ ቀን የተባረከና የተቀደሰ ዕለት ተደርጎ በክርስትና አማኞች ዘንድ ይታመናል። ምክንያቱም፣ አንደኛው ፈጣሪ ሲያከናውን የነበረውን ስራ ጨርሶ ያረፈበት ጊዜ በመሆኑ ነው። ሌላኛው ደግሞ በፈጠረው ፍጥረት በእጅጉ የተደሰተበትና ያለምንም እንከን ሰርቶ በማጠናቀቁ የሰራውን ስራ በማየት ከመደሰት ውጭ በሰራው ነገር ላይ የመጨመርም ሆነ የመቀነስ፣ የማሻሻልም ሆነ የመቀያየር ተግባር አለማከናወኑ ነው (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በመሆኑም፣ በስድስቱ ቀን የፈጠረው ነገር ሁሉ እጅግ ያማረና ምንም አይነት እንከን ያለወጣለት ፍጹም ስራ ስለነበር ሰባተኛዋ ቀን እጅግ የተባረከች ሆነች ይላሉ መሪጌታ ዲበኩሉ።

የሰው ልጅ የተፈጠረው በስድስተኛው ቀን ነው (ዘፍጥረት 1:24-31) ። የሰው ልጅ ስድስት ቀን ሰርቶ በሰባተኛው ቀን እንዲያርፍ፤ ስራም እንዳይሰራባት ታዝዟል

(20፣ 8-11) [41]። በስድስት ቀን የሰራው ሁሉ በዚች ቀን ይባረክለታልና። ሙሴ ወደሲና ተራራ በወጣ ጊዜ አምላኩን እንዳያገኘው ደመና ለስድስት ቀን ያህል ሸፍኖት ቆይቶ ነበር። ደመናው ተገልጦ ከአምለኩ ጋር የተገናኘው በሰባተኛዋ ቀን ላይ ነበር (ዘፅአት 24፣ 15-16) ።

በተጨማሪም፣ ከክፉ ስራና ሃሳብ ታቅቦ፣ ስጋን ከሚያስደስቱ ነገሮች ሁሉ እርቆ፣ በጸም በጸሎት እንዲወሰኑ የሚደረግበት ስርዓት አለ። ይህ ስርዓት ሱባዔ[42] በሚል ይታወቃል። ለምሳሌ፣ ፈጣሪ በሰባተኛው ቀን ስነ ፍጥረትን ከመፍጠር ማረፉ፣ ለጸሎት የሚተጉ ምእመናን በቀን ለሰባት ጊዜ ማመስገናቸው የሰባት ቁጥርን ፍጹምነት ያመለክታል (ዘፍ.2.2፤ መዝ.118.164)። ከዚህ አንጻር አንድ ሰው ለሰባት ቀናት ቢጸም «አንድ ሱባዔ ጸመ»፣ ለ0ሥራ አራት ቀን ቢጸም «ሁለት ሱባዔ ጸመ» እያለ እየጨመረ ይሄዳል (መሪጌታ ዲበኩለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

ለቅዱሳን ሐዋርያት የማርያም የዕረፍትና የዕርገት ምስጢር የተገለጠላቸው በሱባዔ እንደሆነ ይነገራል። ለዮሐንስ ተገልጣ ለእኛ ሳትገለጥ ብለው በነሐሴ አንድ ሱባዔ ገቡ። ሁለተኛው ሱባዔ ሲፈጸም በ14ኛው ቀን መልአክ ሥጋዋን አምጥቶ ሰጥቷቸው ቀብረዋታል። በሶስተኛው ቀን ነሐሴ 16 ቀን ተነስታ ዐርጋለች (ተአምረማርያም፤ ስንክሳር ነሐሴ16 ቀን)። ጻድቁ ሔኖክ፣ የያሬድ ልጅ ሲሆን፣ በትውልድ ከአዳም ሰባተኛ ነው። እርሱም በሕይወቱ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ቤት ንብረቱን በመተው በሱባዔና በትምሕርት እግዚአብሔርን አገልግሏል።

ቅዱሳን በየራሳቸው ያዩት የራእይ ምስጢር ሲከደንባቸው የራእዩም ምስጢርና ትርጉም እንዲገለጥላቸው ያግዘናል ብለው የፈጸሙት ሱባዔ መግባት ነው። እግዚአብሔርም በንጽህና ሆነው የገቡትን ሱባዔ ተመልክቶ ምስጢር

---

[41] የሰንበትን ቀን ቅዱስ አድርገህ አክብር። ስድስት ቀን ትሰራለህ፣ ስራህንም ሁሉ አከናውን። ሰባተኛው ቀን ግን ለአምላክ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው። በዕለቱ አንተም ሆንህ ወንድ ልጅህ ወይም ሴት ልጅህ፣ ወንድ አገልጋይህ ወይም ሴት አገልጋይህ፣ ወይም እንስሳትህ፣ ወይም ሴት አገልጋይህ፣ ወይም እንስሳትህ፣ ወይም በግቢህ ያለ መጻተኛ ምንም ስራ አትሰሩም (ዘፀአት 20፣ 8-9)።

[42] ሱባዔ በሰዋስው ትርጉሙ "ሰባት" ማለት ነው። ሱባዔ በመንፈሳዊ አተረጓጎም አንድ ሰው ከዚህ ቀን እስከዚህ ቀን በጸሎት ከፈጣሪዬ እገናኛለሁ ብሎ የሚያቅደው መንፈሳዊ ስራ ነው (ማህበረ ቅዱሳን)።

ገልጠላቸዋል። ለምሳሌ፡- ነቢዩ ዕዝራ የመጻሕፍትን ምስጢር እንዲገልጥለት ሱባዔ ገብቶ የጠፉትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዳግም መልሶ ለመጻፍ ችሏል (መዝ፣8፣1) ።።

መሪጌታ ይሄይስ (2004 ዓ/ም፣ ጥር 17፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) በአስማት አደራረግ እያንዳንዱ ተግባር የሚመራው በስርዓት ነው ይላሉ።። በአደራረጉ ሂደት ላይ የሚፈጠር ትንሽ ስህተት ስራውን መና ያሰቀረዋል በማለት ያስረዳሉ።። ለአስማት ሥራ የሚውሉ ቁሳቁሶችን መርጠን ስለያዝን፣ ለአደራረጉ አስፋላጊ የሆኑ ዕያችን ወይም እንስሳትን ሁሉ አሟልተን ስላቀረብን፣ በአጠቃላይ በአደራረጉ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ሁሉ ስላካተትን ብቻ ስራው ለስኬት ይበቃል ማለት አይቻልም (መሪጌታ ይሄይስ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 17፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)። በአደራረግ ጊዜ የሚፈጸም ማንኛውም ጥቃቅን ስህተትና በመጠን ወይም በልክ አሰፋፈርና አወሳሰን ምክንያት የሚመጣ ለውጥ ወይም ግድፈት በውጤት ወይም በስኬት ላይ በጎ ያልሆነ ተጽእኖ ያስከትላል ይላሉ።።

ለምሳሌ፣ ስኪቱ (ብልቱ) የሞተበት ወይም የሰነፈበት ሰው፣ የዕሬት ስርን በቅቤ ለውሶ እንዲቀባ የሚያዝዙ ደብተራዎች አሉ (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ነገር ግን፣ እነዚህን ገቢሮች ብቻ አሟልቶ መፈጸም ችግሩን አይፈታውም ይላሉ።። ከገቢሩ ጎን ለጎን "እግዚአብሔር ቆመ"ን መድገም ይገባል።። የ"እግዚአብሔር ቆመ" ድግምት ዕፅዋ የምታሳካው ጉዳይ ምን እንደሆነ በግልጽ የሚነግር ቴክስት ነው።። ይኸ ቴክስት ወደስኬት የሚሸጋገረው ድግምቱና ገቢሩ ሳይቋረጡ ለሰባት ተከታታይ ቀኖች ከቀረቡ ብቻ ነው (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ይህንን ልማድ ጠብቆ አስኪዶ ለውጥ ካልታየ፣ በድጋሚ ሌላ ሰባት ይታዘዛል።። ነገር ግን፣ ድግምቱን ከ7 አሳንሶ ወይም ጨምሮ መድገም የሚቻል አይሆንም።።

የጎዛምን አካባቢ ሰዎች መከራና ችግር እንዳይቀርባቸው፣ ለእነዚህ መጥፎ አጋጣሚዎች መከሰት ምንጭ የሚሆኑ ረቂቅ ርኩሳን ፍጥረታት ወደአካባቢያቸው እንዳይመጡ የተለያዩ የማራቂያ ልማዶችን ይፈጽማሉ (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3 የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ ልማዶች በድግምት መልክና

በተለያዩ አድራጎቶች የሚከናወኑ ሲሆን፣ ድግምቱም ሆነ ድርጊቱ የሚዘጋጁት ከ7 ቁጥር ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ጉንዳንን ብንወስድ፣ ይች ፍጥረት በአካባቢው ህብረተሰብ የእምነት ስርዓት ውስጥ የእርኩስ መንፈስ ወኪል ወይም ማደሪያ ተደርጋ ትታሰባለች፡፡

አንዳንድ የዕፅን መንገድ የሚያውቁ ሰዎች ሊቆርጡ በሚሄዱበት ሰዓት የሚፈልጓትን ዕፅ ጉንዳን ወይም ቁጫጭ ከብቧት ካገኙ ለመቁረጥ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡ ጉንዳን ከቤት ውስጥ ሲገባም ምቀኛ መጣብኝ ይላሉ፡፡ ስለዚህ፣ የዚችን ፍጥረት አመጣጥ በምንም መልኩ ከበጎ ነገር ወይም አጋጣሚ ጋር አያዛመዱትም፡፡ የአካባቢው ሰዎች ይቺን ወኳይ ኃይል ከቤታቸው ለማስወጣት ሲፈልጉ በመናፍስቱ ላይ ሀይልና ስልጣን ያላቸውን ኃይሎች ስም 7 ጊዜ ደጋግመው ይጠራሉ፡፡ ከዚያም ቤቱን ውሃ ሲረጩት ቤቱን ለቆ ይሄዳል ይላሉ፡፡

ሰዎች በህዝብ ዘንድ ግርማ ሞገስ አግኝተው ውዴታን ለማትረፍ ይሻሉ፡፡ ተወዳጅና ቅን ተደርገው እንዲታሰቡ ይመኛሉ፡፡ ከሰዎች ጋር ውል ሲዋዋሉ ነገሩ ቀና መንገድ እንዲይዝ ይፈልጋሉ፡፡ በመሃከል ችግር ተፈጥሮ መደነቃቀፍና መሰነካከል እንዳያጋጥም ይፈራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁኔታውን ምቹ ለማድረግ ያስችላሉ በሚል የሚጠሩ ህቡዕ ስሞች አሉ፡፡ የእነዚህ ስሞች መጠራት የሚረባው የመለኮትን ፈቃድ ለማግኘት ነው፡፡ አጠራሩ ግን በዘፈቀደና በተዘበራረቀ ሁኔታ የሚፈጸም አይሆንም፡፡ ጉዳዩን ለመፈጸም ከመጀመራቸው በፊት ቀድመው እያንዳንዱን ስም 7 ጊዜ ደጋግመው መጥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሰባት ቁጥር የተበላሸ ነገርን ለማስተካከል፣ የተመሰቃቀለንና መልክ ያልያዘን ጉዳይ ስርዓት ለማላበስ እንደምትረዳም በአካባቢው ከሚፈጸሙ ከአንዳንድ ባህላዊ ተግባሮች ያስረዳሉ (ቄስ ዕድሜአለም፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) ፡፡ ለምሳሌ፣ ሰዎች በመካከላቸው አለመግባባት ሲኖር እንዲስማሙ፣ የኔ ሀሳብ ይበልጣል በሚል ፉክክር ውስጥ ሲገቡ እንዲደማመጡ፣ አለመግባባቱና መናቆሩ ቆሞ፣ ትሕትና እንዲማሩ፣ አዲስ ማስተዋልን በሕይወታቸው ውስጥ

እንዲተገብሩ ታስችላለች በሚል 7 ቁጥር ትመረጣለች (ቄስ ዕድሜአለም፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 29፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)።

በፍቅረኞች መካከል አለመግባባቶች ሲመጡ፣ አንደኛው ወገን የፍቅረኛውን ስም እየጠራ በሚሮን፣ በቅብአ ቅዱስ፣ በሰውነት ዘይት በቀን ሰባት ጊዜ እየደገመ መቀባት ወይም ስምንና የፈለጉትን ሰው ስም በአዲስ ቅጠል ጽፎ መታጠን በመካከል ያለ ልዩነት እንዲጠብ ያደርጋል ይባላል። ከጠላንና ከናቀን ሰው ጋር ለመስማማትና ለመቀራረብ፣ ክብር እንዲሰጠንና በእኛም ላይ ውዴታ እንዲያድርበት ለማድረግ ስንፈለግ፣ የፈላጊውንና የተፈላጊውን ስም አንድ ላይ በማንሳት የሚደገም ጸሎት አለ። ይህ ጸሎት ለፍጻሜና ለውጤት የሚበቃው 7 ጊዜ ተደጋግሞ ከተጠራ ብቻ ነው።

የቁጥር መረጣው ታሳቢ ከሚደረገው ውጤት ጋር ተዛምዶ የሚታይ ሆኖ፣ ኃይሉ ወደተፈለገው ውጤት ለማሸጋገር፣ ቃላቱ ወይም ሐረጋቱ ከተፈለገላቸው ልክ በላይ እንዳይባሉ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ። አንድ ቃል ወይም ሐረግ ይባል ዘንድ የሚፈለግበት ልክ አለ። ከዚያ መጠን በላይ አልፎ ወይም አንሶ ቢጠቀስ፣ ድግምቱ ያሳካዋል ተብሎ በሚጠበቀው ውጤት ላይ ተጽእኖ እንደሚፈጥር የሚታመን ይሆናል። ስህተቱ ቁጥሮች በምስጢር ደብቀው የያዙትን ኃይልና ጉልበት ያሳጣቸዋል የሚል ነው።

አንድን ድግምት ወይም ገቢር ድግምትና ገቢር የሚያደርገው ተገቢነት ያላቸው የቃሎች ወይም የሐረጎችና የድርጊቶች መረጣና የአደራረግ ሁኔታ ብቻ አይደለም፤ ከእነዚህ እሴቶች በተጨማሪም እያንዳንዱ ቃል ወይም ሐረግ እንዲሁም ድርጊት በምን ያህል ጊዜና መጠን ይደገም ወይም ይደረግ የሚለው ቁምር ነው። በመሆኑም፣ በእያንዳንዱ ድግምት ውስጥ ያለ ቃልና ሐረግ የሚጠራበት ልክና የሚቆይበት የቀን ብዛት ቁጥሮቹ ከያዙት ተአምራዊ ሃይል ጋር አብሮ የሚናበብ ይሆናል።

የቁጥሮችን ምስጢር ተረድቶ ሊያሳካው ለሚፈልገው ነገር አስተዋጽኦ የሚሆኑ ነገሮችን መርጦና አሟልቶ ለዚያ ጉዳይ ማሳኪያነት አስማታዊ ሀይል ያለውን ቁጥር

ይዞ ተገቢውን ሥራ ካከናወኑ ጉዳዩ ይሰምራል ይላሉ፡፡ በአደራረጉ ሂደት አዎንታዊ ውጤትን ለማምጣት ታሳቢ በሚደረግ ተግባር ውስጥ፣ የቁጥሮቹን አገባብ ከዚያ አስተሳሰብ ጋር እየታየና እየተገናዘበ አገባብ ላይ ይውላል፡፡ በተቃራኒው ለአሉታዊ ተግባር ስንጠቀምበት ደግሞ ለዚያ አስተሳሰብ የሚመቹ ተግባሮችን መርጠንና ለይተን መጠቀም ግድ ይሆናል፡፡ ስለዚህ፣ ለእያንዳንዱ ቁጥር አብይ ፍቺና ልዩ ትርጉም ሰጥተንና የተገባ የምስጢር ትርጓሜ አስይዘን ካልመራነው የመሳካቱ ጉዳይ ጥያቄ ላይ የሚወድቅ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ 7 ቁጥርን ጠብቆ የሚሰራ ማንኛውም ክንውን ከሚፈራው ነገር እንደሚዳን፣ በስርዓት ሆኖ ቢጠቀመባት የጠሉት እንደሚርቅ፣ የወደዱት እንድሚቀርብ፤ የአሰቡት እንድሚፈጸም፣ ህመም እንደሚቀንስ፣ ለነገርም ከሆነ ተሰሚነት እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

የ3 ቁጥር ሚና

ሦስተኛዋና በጣም ተደጋጋሚዋ ተአምረኛ ቁጥር 3[43] ነች፡፡ ይቺ ቁጥር የማትገባበትና የማትነካው የኑሮ አይነት የለም ይሏታል፡፡ እሷ ያልገባችበት ዝግጅት፣ ያልባረከችው ድግስ ውጤቱ ብኩን ነው (መሪጌታ ኪዳነ ጽባሕ፣ 2006 ዓ/ም፣ ጥር 9፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ፡፡ የዚች ቁጥር ፋይዳና ባህላዊ እሳቤም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

ይቺ ቁጥር ከሁሉም በተለየ የስፍርን ልከኛ ቅርጽ በመመጠን በኩል ወሳኝ አገልግሎት አላት፡፡ ከልኬታ ጋር ተያይዞ መብዛትንና ማነስን ወይም ትክክለኛ መጠን ላይ መገኘትን በመንገሩ በኩል ተመራጭ ነች፡፡ በመለኪያዎች መካከል ያለው ግንኙነት፣ ልዩነቱ በስርዓት የሚጓዝበት ሁኔታ የሚመሰረትባት የምስጢር ቁልፍ ናት፡፡ ከትንሽ እስከትልቁ መለኪያ ድረስ አንዱ ከሌላው የሚገናኝበት፣ የጭነቱ ክብደት የሚመጠንበትና በግብይይትና በልውውጥ ቦታ ያለው የሂሳብ ስሌት የሚሳለጥባት ቁጥር 3 ነች፡፡

---

[43] በዓለማችን ውስጥ ባለ በአብዛኛው ባህል ውስጥ ከ1 እስከ12 ያሉ ቁጥሮች ተአምረኛ የሆነ ፋይዳ እንዳላቸው ይነገራል፡፡ ነገር ግን፣ 3 ቁጥር በሁሉም ቦታና አካባቢ በመገኘትና ተደጋግሞ በመከሰት ተወዳዳሪ አይገኝላትም (ሊሴ፣ 56)

በስፍር ዙሪያ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ለምሳሌ፣ "አንድ ድርብ ሦስት ላዳን ነው። ሦስት ድርብ ደግሞ አንድ አቆማዳ ነው። ሦስት አቆማዳ አንድ ጭነት ነው። በአካባቢው ክምር የሚለካው በጭነት ብዛት ነው" (ቂስ እንስማ ደለለ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 18 የተካሄደ ቃለመጠይቅ) ። እህሉ ስንት ጭነት ሆነ? ተብሎ ይጠየቃል። "የመንሽ ጣቱ ሦስት ነው። ጤፍ ሲወቃ የሚበረበረው በዚሁ መሳሪያ ሲሆን፣ በጉርቦራውም የሚደጋገመው ለሦስት ጊዜ ነው"። ያልተገለበጠ ሲያጋጥም እየለዩ ያበራዩታል። ከውስጥ አውጥተው በእጅ እያራገፉ ያፍታቱታል። ከዚያ ደቃቃው ሲደርስ በነፋስ ያዘሩታል እንጅ ከሦስት አልፈው አይቦረቡሩትም።

ሦስት ቁጥር ጥሩ ጣዕም አመንጪ ሀይል ሆና በመግብና በመጠጥ የአመጣጠን ስርዓት ውስጥ ባህላዊ ቃናን ለማስገኘት ደጋግማ ትገባለች። ይቺ ተአምረኛ ቁጥር አንድ ነገር በሰለ የሚባለው ምን ያህል ቀን ወይም ሰዓት ሲቆይ ነው? ልከኛ ቃና ወይም ጣዕም እንዴት ይፈጠራል? የሚሰራው ነገር የትኛውን የጣዕም መልክ እንዲይዝ ይፈለጋል? አንድን ነገር ለመስራት በሚደረግ ጥረት ውስጥ በየደረጃዎቹ መካከል ያለው ርቀት በምን ያህል ይሁን? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመለስና በመወሰን ትልቅ ባህላዊ ግልጋሎት ትሰጣለች። አንድ መጠጥ ወይም ምግብ ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ የሚያልፍባቸው የተለያዩ ደረጃዎች ይኖሩታል።

በእያንዳንዱ ደረጃ ውስጥ ያንን እርከን ብቁ የሚያደርጉ የተለያዩ አላባዎችን ያካትታል። እነዚህ አላባዎች በምን ያህል መጠን ይዋሃዱ? ተዋህጆቹስ ምን ያህል ይሁኑ? የተዋህጆቹ የርስበርስ ሚና ምን መሆን አለበት? ለሚሉት ጥያቄዎች መልሱን የምታስገኘው 3 ቁጥር ነች። ውጤቱ በመጨረሻ ሊያስገኘውና ሊያሳካው የሚችልን ግብ ከዝግጅቱ ጋር በማስማማት ስለሚጠበቀው ነገር ቁጥሯ ወሳኝ ኃይል ነች ።

በመጠጥ ዙሪያ ያለው አሰራር በዚሁ አስተሳሰብ የተካተተ ነው። የጠላ ጠመቃ ዝግጅት ተጀምሮ ለመጠጥ እስኪበቃ ድረስ በተለያዩ ደረጃዎች ያልፋል። በጠመቃ ስርዓቱ ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ "ጥንስስ" ይባላል (ወ/ሮ አፀደ፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ የተገኘ)። ጥንስሱ የሚዘጋጀው ከሦስት ነገሮች (ማለትም ከብቅል፣ ከጌሾና ከውሃ) ነው። ያለ እነዚህ ተዋቃሪዎች ጥምረት ጥንስስ የሚገኝበት

ሌላ መንገድ የለም ይላሉ ወ/ሮ አጸደ። ወይም አንዱ ጎድሎ ወይም በሌላ ነገር ተተክቶ ቢዘጋጅ፣ ሙከራው ተጠነሰሰ አያስብልም። በመሆኑም፣ ጠላን ለመጥመቅ ባለቤቶቹ ወይም ጀማሪዎች እነዚህ ሶስት አካሎች ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው።

ነገር ግን፣ በአጠነሳሰሱ ሂደት የተዋቃሪዎቹ ድርሻ ምን ያህል ይሁን? ውህደቱ በምን አግባብና የማዋሀጃ ልክ ይመጠን ለሚለው ሥርዓት አለ ይላሉ ወ/ሮ አጸደ (2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ የተገኘ)። ጠላ ለመጥመቅ ምን ያህል ብቅል ወይም ምን ያህል ጌሾ ያስፈልጋል? የሚለውን የሚወስነው የዝግጅቱ ፍላጎት ቢሆንም፣ ጠንሳሾቹ (ብቅሉ፣ ጌሾውና ውሃው) በምን ያህል ድርሻ ወይም ተመጥኖ ተሰፍረው ጥንስሱን ያስገኙ ለሚለው ዋናውና የጥንስሱን ስኬት የሚያስገኘው ስሌት የሚገዛው ቁጥሮቹ በያዙት ጥልቅ ትርጉም እንደሆነ በዝግጅቱ ሂደት ከሚታለፍባቸው ሁኔታዎች መረዳት ይቻላል። ቁጥሮቹ በተለያዩ የልኬታ ሚዛኖች ውስጥ መመጠኛ ሀይሎች በመሆናቸው፣ የመብሰልንና የመብቃትን፣ የመድረስንና ምልዑ የመሆንን ደረጃ ሁሉ ይናገራሉ። ትክክለኛ የሆነ የጣዕምና የቃና ስሜት የሚገኝበትን ጊዜ ምልክት ያደርጋሉ።

የጥንስሱ ቃና እንዳይበላሽና ተፈላጊውን የጣዕም ደረጃ ይዞ እንዲገኝ የሚያደርገው ጥምረቱ የሚፈጠርበት መንገድ ነው። እያንዳንዱ ጠንሳሽ ማለትም ብቅል፣ ጌሾና ውሀ የሚዋሀዱት ሁለት እጅ ከብቅሉ እንዲሁም አንድ እጅ ከጌሾው (2+1) በመሆን ነው (ወ/ሮ በየነች፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ የነገሩኝ)። ሁለቱን በመቀላቀል (+) ወይም በመዋሀድ ማለትም አንድ እንዲሆኑ በማጣመር በኩል ሦስተኛ አላባ ሆኖ የሚመጣው ውሃ ነው። ስለዚህ፣ ጠላን ለመጠንሰስ ሦስት ነገሮች እንዳስፈለጉ ሁሉ፣ እነዚህ ጠንሳሾች ጥንስሱን ሲፈጥሩ የሚኖራቸው የምጥን ድርሻም ከዚሁ ልክ ጋር እንዲስማማ ይሆናል። ጠላ በተጠነሰሰ በአራተኛው ቀን "አብሸሎ" ወይም የጠላ ቂጣ ይገባበታል (ወ/ሮ በየነች፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ የነገሩኝ)። ከተጠነሰሰ በሰባተኛው ቀን ወይም "አብሸሎው" በገባ በሦስተኛው ቀን ላይ "ደረቆት" ገብቶ ይደፈደፋል ይላሉ ወ/ሮ በየነች። ከዚያም ከሦስት ቀን በኋላ ማለትም በአስረኛ ቀኑ ላይ ውሀ እንዲገባበት ተደርጎ "ሙሊት" ይፈጸማል (ወ/ሮ በየነች፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ የነገሩኝ)።

ጥንስሱን የሚፈጥሩት ሦስቱ ነገሮች ጥንስሱን በመስራቱ ሂደት የየራሳቸው ፋይዳና አገልግሎት ቢኖራቸውም፣ እያንዳንዱ ተዋቃሪ የያዘው እሴት ከሌላው ተዋቃሪ ጋር ሲገናኝ በውህደቱ ግንኙነት የተነሳ የሚገኘውን ተጨማሪ እሴት እንዲያምርና እንዳያምር የሚያደርገው ቅልቅሉ የተመራበት የምጥኑ ሥርዓት ነው። ይህ እሴት በጠላው ማማር ወይም አለማማር፣ መጣፈጥ ወይም መምረር፣ አዲስ መሆን ወይም መሬጮር ላይ የራሱ ተጽእኖ ይኖረዋል። የልስላሴውን ወይም የጥንካሬውን ደረጃ (ማለትም ኃይል) በመወሰን ተግቢው ልኬታ ላይ መድረሱ የሚታወቀው በእነዚህ ተአምረኛ ቁጥሮች መለኪያነት ነው። እንዲሁም፣ የብስለት ደረጃውን እንደያዘ ረጅም ጊዜ እንዲቆይ ወይም ፈጥኖ እንዲያጣ በማድረጉ በኩልም የግንኙነቱ ስምረትና የምጣኔውና የስፍሩ ትክክለኛ መሆን ወሳኝ ሚና ይኖረዋል (ወ/ሮ በየነች፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30 የነገሩኝ)።

በመሆኑም፣ የስፍሩን ወይም የቅልቅሉን ሁኔታ ቀያይሮና አዛብቶ በሌሎች ቁጥሮች ተክቶ መጠቀም ማህበረሰቡ ትክክል ብሎ የተቀበለውን የጣዕም ጠባይ ያበላሸዋል (ወ/ሮ በየነች ምናለ፣ 2006 ዓ/ም፣ ህዳር 30፣ የነገሩኝ)። መጠጡ በማህበረሰቡ ዘንድ ተለይቶ የሚታወቅበትን የቃናና የብስለት ሁኔታ ያሳጣዋል። በአጠቃላይ፣ መጠጡ የያዘውን እሴትና ስውር የማስደሰትና የማርካት አቅም ይነሳዋል። ወይም ያልተለመደ የጠላን ባህርይ ስለሚያስተዋውቅ የተዘጋጀውን ነገር "ጠላ" ብሎ ለመጥራት ባህላዊ እሳቤው አይፈቅድም። እህል ተፈጭቶ፣ ተቦክቶ፣ ተቀጥኖ እስኪጋገር ድረስ ባሉ ሂደቶች ውስጥ የብስለት ደረጃው የሚለካው በእነዚሁ ቁጥሮች አማካይነት ነው። "በእንጀራ አሰራር ሂደት ውስጥ አብሲት የሚገባው ሊጡ በተቦካ በሦተኛው ቀን ላይ ነው" (ወ/ሮ አፀደ መኮንን፣ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 15፣ በቃለ መጠይቅ የተገኘ) ።

መሪጌታ ይሄይስ (2004 ዓ/ም፣ ጥር 17፣ ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) የቁጥሯን ምስጢር ተረድተው ለድግምትና ለዕፅ ማንገሻነት የሚጠቀሙ ደብተራዎች አሉ ይላሉ። እነዚህ ዕፆች ፍጹም ጥምረት ፈጥረው አንድነት መስርተው፣ በመካከላቸው ነፋስ ሳያስገቡ፣ አንድ ሆነው ከቆሙ እህልን ለመስለብ የሚመጡ ልዩ ኃይል ያላቸው መናፍስቶች ይርቃሉ ይላሉ። በሰዎች ዙሪያ የሚደረግን ምክር ለመበተን፣ ወደእነሱ

የሚወረወርን ነገርና ጉዳይ ለማስቀየስ፣ በነዋሪዎቹ መካከል መስማማትና መፈቃቀር ያመጣሉ በሚል የሚደረጉ የተለያዩ "መድፍነ ፀሮች"[44] አለ፡፡ የእነዚህ አደራረጎች የመከላከያ መንገድ ከጠላት የሚወረወረው ማንኛውም ጥቃት በተቀናቃኙ ሃይል ላይ አርፎ ጉዳት እንዳያደርስ ማናቸውንም ማለፊያ መንገድና የማሳኪያ አጋጣሚ የሚከሽፍበትን ሁኔታ ማዘጋጀት ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ከሌሎች ገቢሮች ጋር በማድረግ፣ "በእኔ በእከሌ ላይ የሚነሱትን የጠላቶቹን ልብ ድፈን፣ ጉሮሯቸውን ዝጋ፣ አይናቸውን ጋርድ፣ አፋቸውን ጠርቅም" በማለት የሚጸልዩት 3 ጊዜ ነው በማለት ምሳሌ ይጠቅሳሉ፡፡ሌላኛው መንገድ ጉዳት አደርሳለሁ ብለው እንዳያስቡና ሌሎቹንም አስተባብረውና አሳድመው ከራስ ጎን በማሰለፍ የሚጠሉትን አካል ለመጉዳት ጉልበትና ተሰሚነት እንዳያገኙ ለማድረግ ሲፈልጉ ይቺ ቁጥር መልካም ናት ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ 3 ቁጥር በሀሳብ፣ በባህርይና በድርጊት ፍጹም የሆነ ጥምረት፣ መስማማትና መዋሀድ እንዲፈጠር ሀይል ያላት ቁጥር ነች፡፡ በነገሮች መካከል የሚፈጠርን ክፍተት የምትደፍን፣ ልዩነቶችን የምታጠፋ፣ ፍጹም የሆነ መዋድን የምትፈጥር ተአምረኛ ቁጥር ተደርጋ ትታሰባለች፡፡ ይህ እሳቤዋ ደግሞ ቀዳሚነትን፣ ነፃ መሆንን፣ ራስ መቻልን፣ ፍጹም መሆንንና እንከን አልባ ለሆኑ እሳቤዎች ወካይ ቁጥር ሆና እንድትገባ አድርጓታል፡፡ በአጠቃላይ ፍጹም ውህደት፣ ጥምረትና አንድ መሆን ሲታሰብ ይቺ ቁጥር በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ተፈላጊ ነች፡፡

8.4.2. የቀኝና ግራ እሳቤ

አቶ ቅሩብ አንተነህ (2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ) የአካባቢው ሰው ቀኝን የሚረዳው "ቅን" በሚለው ፍቺው ነው ይላሉ፡፡ ቅን የሚለው ቃል ሲፈታም፣ "የተለመደና የታወቀ" የሚል ትርጉም ይይዛል፡፡ "ቅን መሆን" ወይም "ቀና መሆን" ማለት ባወቁትና በለመዱት ነገር መገዛት ማለትም ነው ብለው ይፈቱታል፡፡ ጽንሰ ሐሳቡ መገዛትን፣ መታዘዝንና የኔ በሚነ ብሎ መመኘትን ሁሉ ጠቅልሎ የሚያቅፍ ሃሳብ ነው፡፡ ግራ፣ የሚለው ቃል ደግሞ፣ "ችግርንና ቁንቁትን የሚጠራ ነው፡፡ ጽንሰ ሐሳቡ ያለመለመድና የእንግዳ ክስተት ወካይ እሳቤ ነው"

[44] ጠላትን የሚከላከል፣ ለባላንጋራ የማያጋልጥ እንደ ማለት ነው፡፡

(አቶ ዘውዴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 14፣ ከተደረገ ቃለመጠይቅ)። በተለያዩ አውዶች ውስጥ የዚህ ቃል አጠቃቀም፣ "ጠማማና ቀናነት ለጎደለው፣ ለማያገዙበትና ለማይገዙበት ወጣ ያለ ሀሳብ መገለጫ ሆኖ የሚጠቀስና ገድ ለሌለው ነገር ምሳሌ ተደርጎ የሚወሰድ" ነው በማለት አቶ ዘውዴ ያስረዳሉ።

የሰው ልጅ ከሚኖርበት ከዚህ ከደልዳላው፣ ዝርግ ከሆነው ለማዳው መሬት ዝቅ ብለው ያሉት ዘብጦች፣ ረባዳዎች፣ ዋሻዎች፣ የገደል ሥሮች፣ በተለያዩ ምክንያቶች የመንቀሳቀሻ፣ የመኖሪያና የመስሪያ ቦታዎች ስላይደሉ እንደሌላ ዓለም ቆጥረዋቸው "ግራ" ይሏቸዋል (መሪጌታ ሞላ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 3፣ የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። እነዚህ ቦታዎች የሰው ልጅ እንቅስቃሴ የተገደበባቸው በመሆናቸውና በተፈጥሮ የያዙትን ነገር አስጠብቀው በደኖች፣ በጫካዎችና በዱሮች ተሸፍነው ስለሚኖሩ በውስጣቸው ያለው ነገር ይፈራል። በዚህ ቦታ ውስጥ ተደብቀው፣ አካባቢን ማደሪያ አድርገው የሚኖሩትም ከሰው ልጅ ጋር ያልተላመዱ ፍጥረቶች ናቸው። ተናዳፊ፣ ተናካሽ፣ አስፈሪ የሆኑ ፍጥረቶች መገኛቸው በዚህ አካባቢ ነው።

በአንዳንድ አጠቃቀሞች "ግራ አጋባ፣ ግራ አግቢ" የሚሉት ፈሊጦች አጠቃቀም ከላይ በቀረበው እሳቤ የተገራ ትርጉም ያለው ነው። የእነዚህ ቃሎች አጠቃቀም ከሌሎች ቃሎች ጋር ሆኖ የፈጠረው ጥምረት፣ "አስቸጋሪ፣ አዋኪ ዕረፍት ነሽ የሚሉ ፍቺዎችን የያዘ ነው"(ደስታ ተክለወልድ፣ 1956፣ 302)። "ግራ ገባው" ሲሉም፣ "ተቸገረ የሚያደርገውን አጣ፣ ታወከ፣ ተጨነቀ እንደማለት ነው" (ደስታ ተክለወልድ፣ 1956፣ 302)። ከዚህ አጠቃቀም በመነሳት "በግራው የሚበላ ሰው ሲያጋጥም አይጠግብም፣ በግራ ጎኑ የሚነሳም እንዲሁ አይቀናውም" ይላሉ (አቶ ጤናው ከብቴ፣ 2005 ዓ/ም፣ ሐምሌ 20፣ የተደረገ ቃለመጠይቅ)። አንዳንድ ጊዜ፣ የግራ እጅ መሀል መዳፋችንን ሲያሳክከንና የግራና የቀኝ ጆሯችንን ሲበላን ወይም የግራና የቀኝ አይኖቻችን ሲርገበገቡ የሚሰጠው ትርጉም ከዚህ ጋር በመያያዝ የመልካምና የመጥፎ ዕድሎች ምልክት እያደርግን እንደምንጨነቅና እንደምንጓጓ ይናገራሉ።

በተለይ ሁለት ሁለት ሆነው በተፈጠሩ የሰውነት ብልቶች ውስጥ እነዚህ ጽንሰ ሐሳቦች ከተለያዩ ነገሮች ጋር በተገናኘ አቅጣጫ ይዘው ሲገቡ ያላቸው ፍቺ ከዚህ

ጋር እየተነጻጸረ አካባቢያዊ ትርጉም ያገኛል፡ ፡ ለምሳሌ፡- ከአበላል ጋር ተያይዞ ያለውን ፍቺ ስናይ ሁኔታው ምን ያህል የተወሰነ ቅጥአምባርን (ፓተርንን) ይዞ እንደገባ ያስገነዝበናል፡፡ በአካባቢው (ይህ እሳቤ ምናልባትም ሀገራቀፋዊና ዓለማቀፋዊ ተመሳስሎ ይኖረዋል) እህል የሚበላው በቀኝ እጅ ነው፡፡ ማንኛውንም ዓይነት ስራ ለማከናወን ማለትም ዕቃ ለማንሳት፣ ለመቀበልና ሰላምታ ለመለዋወጥ ተመራጩ ቀኝ እጅ ነው፡፡ በአውድማ ውስጥ፣ "በሬዎች ተግባራቸውን ሲጨርሱ አውድማውን ለቀው ከመውጣታቸው በፊት ወደ ግራ ሲዞሩ ቆይተው ከሆነ ወደ ቀኝ እንዲዞሩ ተደርጎ ይመራቃሉ፡፡ ምረቃው ሲያበቃ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አውድማውን ለቀው እንዲወጡ ይሆናል" (ማሞ፣ 2002፣ 52)፡፡

በእነዚህ የአቅጣጫ መጠቆሚያዎች አማካይነት መልካሙ ከመጥፎው፣ አልሚው ከአጥፊው ጋር እንዳይቀላቀሉና እንዳይዋሃዱ ሲል በመካከላቸው ልዩ የሆነ የተፈጥሮ ባህርይ እንዲኖራቸው አድርጓል ይላሉ መሪጌታ ዲበኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ይህ ክፍፍል ሃይሎችን ከመከፋፈል በተጨማሪ ለፍጥረቶች ሁሉ ገደብ ያለው ነጻ አእምሮ እንዳላቸው አንዱ ከሌላው እንደሚበልጥ ለመጠቆም ጭምር የቀረበ ማሳወቂያ መንገድም ነው፡፡

ግራ በብዛት ለተለመደ ነገር ምልክት ተደርጎ ስለማይወሰድ፣ ምንጊዜም ወጪን ለሚያመጣና ከእጅ ለሚያመልጥ፣ ለድንገተኛ፣ ላልተገመተ፣ ላልታሰበ ፍጹም ላልተጠበቀ ገጠመኝ ደራሽ ምሳሌ የሚሆን ነው (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ መርጌታ ዲበኩሉ፣ የአካባቢው ሰው የግራ አይን ሲርገበገብ እንግዳ ሊመጣ ነው ይላል በማለት ይናገራሉ ፡፡ ሰዎች በቀን ውሏቸው ያልጠበቁት ነገር ሲያጋጥማቸው፣ ለምሳሌ ከሚወዱት ሰው ጋር ሲጣሉ፣ ያላሰቡት በጎ ያልሆነ ነገር ሲደርስባቸው "በግራ ጎኔ ተነስቼ ነው" ይላሉ (መሪጌታ ዲበኩሉ፣ 2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 4፣ በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ከእንቅልፋቸው ነቅተው ጸሎት ካደረሱ በኋላ ፈጣሪያቸውን የሚለምኑት "ቀኝ አውለኝ" ብለው ነው፡፡ ያልለመድኩትን አታሳየኝ፣ መከራውን አርቅልኝ፣ ክፉን ወደእኔ አታቅርበው ለማለት፣ አባቶችና እናቶች አራስ ጠይቀው ሲወጡ፣ "በቀኝ ያቁምሽ" ብለው ይመርቃሉ በማለት መርጌታ ዲበኩሉ ያስረዳሉ፡፡

የክፉ ሥራ መግኛና ማረፊያ ያልቀናውና ያልተገዛው፣ መባዛትና መበርከት የሌለበቱ፣ በምርትም ሆነ በወሊድ ሰዎች የማይራቡበትና የማይኖሩበት የማይታወቀው ዓለም ነው በማለት የሚገልጹት ደግሞ መሪጌታ አይነኩሉ (2005 ዓ/ም፣ ነሐሴ 8፣ በተካደ ቃለመጠይቅ) ናቸው። በቀኙ ካረፈ ይንሰራፋል፣ የረጋውን ሊያናውጥ፣ የሰከነውን ሊያደፈርስ፣ የተተከለውን ሊነቅል ይችላል ተብሎ ስለሚሰጋ ክፉ ዐይንን ለማስለቀቅ ሲሞከር ይህ አቅጣጫ ታሳቢ ይደረጋል ይላሉ። በወደደውና በፈለገው ቦታ በቀኝ ማረፍን ተመኝቶ ከሰዎች ጋር ሲጣባ አንፈልግም ብለው አርቀው ወደነበረ ቦታው መልሰው በመጣል ለእሱ ክብር የማይመጥን መሆኑን ያሳውቁበታል በማለት መርጌታ አይነኩሉ ያስረዳሉ። መንፈሱ ከሰውዬው ከተነጠለ በኋላ ለተለካፊው ሰው ተገቢው የፈውስ ስርዓት ተፈጽሞለት ወደ ነበረበት ቦታ ማለትም የረጋውና የቀናው ማህበራዊ ዓለም ይቀላቀላል በማለት ልዩነቱ በመንፈሱ አወጣጥና ሰውዬውን ወደ ቀናው በመመለስ አቅጣጫው የያዘውን እሳቤ ያስረዳሉ።

ቡዳ የበላው ሰው በሃሳቡና በሁኔታው ሁሉ በቀናው ቦታ ያለው ሰው የሚያከናውነውን ነገር እየተወ ያልተለመደና እንግዳ ጠባይ የሚያሳይ ነው (ወ/ሮ ውዴ 2004 ዓ/ም፣ ጥር 5 የተካሄደ ቃለመጠይቅ)። ወ/ሮ ውዴ ቡዳ የበላው ሰው ከሰው ጋር ማውራት ይጠላል። መሸፋፈንና ራሱን መደበቅ ይመርጣል ይላሉ። መንፈሱ ይህንን ሰው ስርዓትና መልክ ከያዘው ከቀናው መንገድ አውጥቶ ግራ ወደሚያጋባና ያልተረጋጋ ስክነት ውስጥ ይከተዋል። ይህንን ሰው ወደ ነበረበትና ወደ ድሮው ሁኔታው ለማምጣት ወይም ወደ ቀናው ለመመለስ በሚደረገው የፈውስ ስርዓት ውስጥ ለማስለፈለፍ በሚሞከርበት ጊዜ መድሃኒቱ ለታማሚው እንዲሸት የሚደረገው በግራው የአፍንጫው ቀዳዳ ነው ይላሉ። ወዝ በሌለው በደረቅ፣ አዲስ እራፊ መድሃኒቱን ይጠቀልሉታል። የግራ እግሩንና እጁን አውራ ጣት ይይዛሉ። ከዚያም በግራው የአፍንጫ ቀዳዳ እያሸተቱ ማንነቱን ይጠይቃሉ። በሰዎች ላይ የሰፈረ አጋንንት በጠበል ለፍልፎና ተገዝቶ እንዲለቅ ሲደረግም ቃለ መሃላ የሚያስገቡት በሸተኛውን በግራ ጎኑ ሶስት ጊዜ እየወደቀ እንዲነሳ በማድረግ ነው። በመሆኑም፣ ቀኝን ለዚያ መንፈስ የተገባ ቦታ አያደርገውም።

9. ማጠቃለያና ይሁንታ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ጠቃሚ ሃሳቦች ተመርጠው ይቀርበበታል። ጥናቱ በሂደት ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያለፈባቸው ደረጃዎችና በመጨረሻ የደረሰበት ነገር ተጠቃሎ ቀርቧል። በመቀጠልም፣ በቀጣይ ሊጠኑና ሊዳሰሱ ስለሚገቡ ጉዳዮችና ርዕሶች፣ ቢመረመሩ ጠቃሚ ነገሮች ይገኙባቸዋል በሚል የሚታሰቡ ሃሳቦችና የመተንተኛ ስልቶች ይጠቁማል።

9.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት እንዲካሄድ መነሻ የሆነው ጉዳይ፣ የክፉ ዐይን እምነት በጎዛምን ሰዎች የማንነት አቀራረጽ፣ የባህል ግንባታ፣ የአስተሳሰብ ሁኔታና ልምድ፣ የተፈጥሮ እሳቤ፣ በአጠቃላይ ህይወት ውስጥ ተጽእኖው ከፍተኛ መሆን ነው። ክስተቱ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ፣ ዕውቀት፣ ክህሎትና ባህርይ ውስጥ ያለውን ቦታ ለማወቅ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ይዞ የመረመረ ነው። ይህንን መነሻ ጭብጥ በመያዝ፣ የክፉ ዐይንን ምንነት፣ ባሕርይና የያዘውን ባህላዊ ፍቺ በበቂ ሁኔታ መግለጽ፤ የክፉ መንፈስ ወኪል በመሆን ስለሚያገለግሉ ፍጥረቶች ምንነትና ባህርይ ማስረዳት፤ ክፉ ዐይን የሚከሰትባቸውን አውዶችና የመጠቂያ አጋጣሚች መተንተን፣ የክፉ ዐይን መንፈስን ለመከላከል ስለሚያገለግሉ ዘዴዎች ማሳየት፣ በክፉ ዐይን የተያዙ ፍጥረቶችን ለመፈወስ ስለሚያገለግሉ የማንጫ ስልቶች መመርመር ተችሏል።

ይህ ጥናት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከሚገኙ አሥራ አንድ የዞን መስተዳድሮች መካከል አንዱ በሆነው በምሥራቅ ጎጃም ዞን የተካሄደ ሆኖ፣ በዞኑ ከሚገኙ 18 የወረዳ አስተዳደሮች መካከል አንዱ በሆነው፣ የጎዛምን ወረዳ ውስጥ የተጠና ነው። የጎዛምን ወረዳ በአጠቃላይ በ25 የገጠር ቀበሌዎች፣ በአንድ ንዑስ ታዳጊ ከተማ እና በአንድ የከተማ አስተዳደር የተዋቀረ የአስተዳደር ክልል ሲሆን፣ ጥልቀት ያለው የኢትኖግራፊክ ጥናት ለማካሄድ ያመች ዘንድ በወረዳ ውስጥ የሚገኙ ሰባት ቀበሌዎች ማለትም የጥጃን፣ ሽበልማ፣ ወንቃ፣ እነራታ፣ ቀቢ፣ የቦ አርጀ፣ የጋግናና ጭምቦርድ እንዲሁም አንድ የከተማ አስተዳደር ተመርጧል።

ጥናቱ መግቢያውንና ማጠቃለያውን ጨምሮ በአጠቃላይ በዘጠኝ ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ ለጥናቱ ዳራዊ ዕውቀት የሚሆኑ መረጃዎችን የያዘው የመግቢያ ክፍል፤ በሁለተኛው ምዕራፍ ትውራዊ አቀራረቦች፣ ተዛማጅ ጥናቶች፣ ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፎችና የመተንተኛ ሞዴሌቹ የተብራሩበት፤ ሦስተኛው ምዕራፍ፣ ለምርምሩ መረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችና የአጠናን ዘዴዎቹ የተገለጹበት፤ በአራተኛው ምዕራፍ ደግሞ፣ የጥናት አካባቢው መልክዐምድራዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች በስፋት የተዋወቁበት ነው። ከምዕራፍ አምስት እስከ ምዕራፍ ስምንት ባሉት ክፍሎች ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑበት ሲሆን፣ ምዕራፍ ዘጠኝ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ ይሁንታና አስተያየት ተገልጸበታል።

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል። የኢትኖግራፊክ መረጃው የተሰበሰበው በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይትና በቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ሆኖ በአጠቃላይ 15 ሴት 32 ወንድ በድምሩ 47 ሰዎች ተሳትፈውበታል። መረጃውን ለመሰብሰብ በአራት ዙር ምልልስ የስምንት ወር ቆይታ ተደርጓል። የመረጃ አቀባዮች ምልመላ ሲካሄድ፣ ለአካባቢው ባህልና ቋንቋ ያለ ዕውቀት፣ በማህበራዊ ተቋማቱ የሚያደርጉት ተሳትፎ፣ የህይወት ልምድ፣ ለመረጃው ያለ ቀርበት ታሳቢ ተደርጓል።

ከተጠኝው ማህበረሰብ አባላት መካከል በጥናቱ የተሳተፉ ሰዎች የተመረጡት በዓላማ ተኮር (purposive sampling) ፣ በቅብብል ምሬት ንሞና (Snowball Sampling) እና አልፎ አልፎ በአመች ንሞና (Convenience Sampling) ስልቶች ነው። ለእነዚህ ሰዎች ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ (Semi structured Interview) እና ኢመደበኛ ቃለ መጠይቆች (Informal interviews) ቀርበውላቸዋል።

ቃለ መጠይቁ በዲጅታል መቅረጸ ድምጽ የተቀረጸ ሲሆን፣ በድንገት የተገኙ አስተያየቶች በማስታወሻ ደብተር ተገልብጠዋል። የመረጃ ሰጪዎች ፎቶ ግራፍ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በዲጅታል ፎቶ ካሜራ ተይዟል። በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትክክለኛነት በመስክ ላይ በተካሄደ ምልከታ፣ ከቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ጋር በተደረገ ውይይት እንዲሁም በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት ከተደረጉ የጋራ

ውይይቶችና መግባባቶች በመነሳት ትክክለኛነታቸው ተመዝኗል። በአጠቃላይ ሦስት ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምድብ ሰባት በሦስተኛው ደግሞ ስምንት ሰዎች ተሳትፈዋል።

የንዛምን ሰው በዓለማቱ አደረጃጀት፣ በፍጥረቶች አመጣጥና አገኛኘት ዙሪያ የያዘው እምነት፣ ሥርዓት ስለመጣበት መንገድ ያለው ዕውቀት፣ በማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወት ውስጥ ነጸብራቁ ከፍ ያለ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል። የማህበራዊ ህጎችና የትውፊታዊ ስርዓቶች ምንጭ ከዚሁ አስተሳሰብ የተቀዳ ስለመሆኑ ለመረዳት ተችሏል። በንዛምን ሰው የፍጥረት እሳቤ ውስጥ ዋና ሆኖ የቆመውና የርዕዮቱ ምንጭ በመሆን ሥርዓት የሆነው ግዥ ነገር፣ "ሁሉም ፍጥረት በጣም በተመጠነ አኳኋንና በልክ ተወስኖ ተፈጥሯል" የሚለው ሃሳብ ነው። ይኸ ማዕከላዊ ሃሳብ የተንዛዛና የተትረፈረፈ ነገር ለክፉ ዐይን እንደሚያጋልጥ ስለሚያስረዳ ከመጠነ በላይ መያዝ እንዲነወር፣ መሰብሰብና ማጠራቀም እንዲጠላ በማድረግ ለተፈጥሮ ሚዛንና ለባሕርይ መክበር እንዲያስብ የሚያስችል ባህል እንዲፈጠር አድርጓል።

ይኸንን ባህላዊ ሕግ መተዳደሪያ ተደርጎ ሲያዝ፣ ተረዳድቶ በመኖር፣ የተረፈውን ለጎደለበት በመለገስ፣ በራስ ወዝና ላብ በማመንና የሰውን ባለመመኘት እሴቱ እንዲጠነክር አስተምሮታል። ከበዛው ነገሩ ላይ ቀንሶ የጎደለውን ሲሞላ፣ መስጠትን የማመጣጠኛ ዘዴ አድርጎ ተፈጥሮውን እንዲያከብር አሳስቦታል። ሥጋዊ ፍላጎትና መንፈሳዊ ህይወት ከክፉ ዐይን የሚጠበቁትና ጤናማ አኗኗር የሚኖረው በተመጠነ ኑሮ ውስጥ መሆኑ ተገልጸበታል። ወደግብታዊነት፣ ደመነፍሳዊነት፣ ራስ ወዳድነትና ስግብግብነት የሚመሩ ዐረ ሰብአዊ ተግባሮችን መጥላትንና መጸየፍን የምግባሩ አካል አስደርጎታል። ሰውን ወደ መርዳት፣ ወደ መውደድ፣ ወደ አለማድላት፣ እንደዚያ ወደ ሆነ ሥራና የምግባር ተግባር ውስጥ በመግባት ራስን መጠበቅ እንደሚገባ አስተምሯል። የተለመደን አኗኗር ከመኖር በመለየት፣ ወደ ተሻለና የተመረጠ ሥራ ለመቀየር ይጥራል።

በመጠን፣ በልክና በሚዛን መክበር አዋቂ፣ ጠቢብና አስተዋይ እያደረገ ሲያከብር፣ በተቃራኒው መሆን ደግሞ ለክፉው መንፈስ የሚጋላጥ መሆኑ ተረጋግጧል።

ፍትሃዊነት በፍጥረት ህይወት የተወከለው በዕውቀትና በማሰብ፣ በመመርመርና በማገናዘብ እንዲሁም በማስተዋልና በአጠይቆት ሆኖ፣ ህይወትን በማመዛዘንና በልክ እንዴት ማስኬድ እና ማኖር እንደሚቻል የሚያስረዳ ነው፡፡ ፍላጎትን ለወል ልምድ በማስገዛትና በተመጠነና በልክ በመምራት ሰብአዊነትን ማስከበር እንደሚቻል መንገሪያ ነው፡፡

ሁለተኛው ከክፉ ዐይን መጠበቂያ የሆነው መንገድ ተፈጥሮውን አክብሮና ጠብቆ በመያዝ የጥንካሬውና የብርታቱ አምሳል አድርጎ ሊይዘው ይገባል የሚለው ነው፡፡ እውነተኛ ነገር ያለው በተፈጥሮ ውስጥ ነው ተብሎ ስለሚታመንና፣ ተፈጥሮ ደግሞ ከሁሉም በፊት የሚገኝ ተቀዳሚው ነገር በመሆኑ፣ የነዛምን አካባቢ ሰው ምልክትና ድንበር ባበጀለት፣ አቅንቶና አሰልጥኖ በያዘውና የመንቀሳቀሻ ቦታዬ ብሎ በሚጠራው 'ግዛቱ' ወይም 'ቅናቱ' ውስጥ በምግብነት በሚገለገልባቸው እንስሳት፣ ሰብሎች ተክሎች፣ ለመድሃኒት በሚጠቀምባቸው ዕፀዋት ላይ ሁሉ፣ ቀድመው የተወለዱና የተገኙ የሰው ዘሮች፣ ልጆች፣ አባት ዛፎች፣ የህል ንጉሦች፣ ፍጥረት የተጀመረባት ቀን፣ ንጋት የተበሰረባትን ጊዜ፣ ዘመን የነጋበትን ወር፣ እህል የበቀለባት፣ መቅደም የሆነበት ሁሉ ቀዳሚ ተፈጥሮዎች በመሆናቸው ለእነሱ ክብረና ውዴታ እንዲሰጣቸው የሚመክረው ነው፡፡

እነዚህ በአፈጣጠር ጊዜ የቀዳሚነት ምልክት የተደረገባቸው ክፍሎች፣ ፍጥረቶቹ በሚወለዱና በሚበቅሉ፣ በሚወጡና በሚታዩ ጊዜ ቀድመው የሚታዩ በመሆናቸው ከሌላው ሁሉ ተለይተው የመክበሪያ ምልክት ተደርገው መያዝ እንዳለባቸው ያሳስባል፡፡ ቀድሞ የመጣ ወይም የነበረ ከዘግይቶ ደራሽና ከእንግዳው በፍትሃዊነቱ፣ በኃይሉና በጥንካሬው፣ በንጽሕናውና በታዛዥነቱ የተሻለ ሆኖም እንደሚታሰብ ይነግራል፡፡ ተፈጥሯዊነት የፈጣሪ የባሕርይ መገለጫ ሲሆን፣ ከተፈጥሮ መውጣት የሰው ልጅ በራሱ ፈቃድ የሚጨምረው ጠባይ ነው፡፡ ተፈጥሯዊነት ሰውን ሲያከብረው ስልጣኔና ዕድገት ሰው በፈቃዱ ያመጣው መጥፊያው መንገዱ ነው ብሎ እንዲያስብ እንዳደረገው ጥናቱ ያሳያል፡፡

በእንስሳትና በአራዊት ራስ ላይ እንደ ሰው ፀጉር ሁሉ የሚበቅለውና ሥጋዊ ጦር የሆነው ቀንድ፣ በእንስሳትና በሰው አገኛኘት ቀድሞ የሚመጣውና የሥልጣንና

የሸመት ምልክቱ ራስ፤ ሣር መሬትን ሸፍኖ ከመጠረግ እንደሚያድናት ሁሉ፣ የሥልጣንና የበላይነት ምልክት የሆነውን ራስ ከጥቃት የሚጠብቀውና የራስ ጠሩ በመባል የሚጠራው ፀጉር፤ ለመተከል፣ ጸንቶ ለመቆም፣ ለመግፋትና ለመጋፋት የሚያገለግለው የፊት እግር፤ ተንሸራቶው እንዳይወድቁ ምርኩዝ የሚሆነውና ለመራመድና ተተክሎ ለመግፋት አቅም የሚሆነው ሸኮና፤ ሰውነትን ከብርድና ከሌሎች ጎጅ ኃይሎች ጠብቆና ተከላክሎ የሚያኖረው የንጽሕናና የተፈጥሮው አምሳል የሆነው የግላው ልብስ ቆዳ ወይም ቆርበት፤ ሁሉ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑ ናቸው፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ቀዳሚነቱን የሚያከብሩ በመሆናቸው፣ ሲጠፉ አስጠቂ ሲኖሩ ደግሞ የክፉ ዐይን መከላከያዎች እንደሆኑ ይጠቁማል፡፡

ሶስተኛውና የማንነቱ መገለጫ አድርጎ የያዘው ነጥብ፣ “ሳይዳቀሉና ሳይበረዙ ንጽሕናን ጠብቆ መጓዝ ለክፉ ዐይን ከመጋለጥ ያድናል” የሚለው የህይወት መመሪያው ነው፡፡ ንጽሕና ሳይዳቀሉና ሳይበረዙ እንደነበሩ መግኛ ሁነት ነው፡፡ ተፈጥሮን ጠብቆና አክብሮ ሥሩን ሳይለቁ መጓጎ ስልቱ ነው፡፡ አንድ ዘር እየተዳቀለና ከሌላው ጠባይ፣ ግብርና ሃሳብ ጋር እየተላመደ በሄደ ቁጥር ከቀዳሚነቱ እየራቀ፣ የያዘውን ጥንካሬና ጥራት እያጣና ተፈጥሯዊ ጠባዩን ሁሉ እየሳተ እንደሚሄድ በጥናቱ ታይቷል፡፡ የንጽሕና ባሕርይ በቀዳሚነት ከነበረው ጠባይ እየደከመ፣ እያደፈና እየቆሸሸ የሚሄደው የራሱ ካልሆነ ነገር ጋር ሲቀላቀል እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

እርስ በርሱ የማይስማማንና አብሮ የማይሄድን ነገር ለመቀላቀልና ለመበረዝ መሞከር እንግዳ የሆነ ክስተት እንዲፈጠር ምክንያት ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ በዘር አበዛዝ ላይ ጥንካሬንና አለመታዘዝን የሚያስከትል ድርጊት ነው ተብሎ እንዲታመን አድርጓል፡፡ ነገሮች የራሳቸው ካልሆነ ጠባይ ጋር ሲነካኩ፣ በመጨመር ወይም በመዳቀል የሚይዙት ተጨማሪ ዐመል በቀዳሚነት የያዙትን ባሕርይ ያስተዋል፡፡ ከባሕርይ እየሸሸ መሄድ የሰብዕና መናጋትንና ያልተለመደና አጥፊ የሆነ አመልን ወደ መያዝ ይመራል፡፡ በመሆኑም፣ ከማይፈለጉ ሃይሎች ጋር በመነካካት የሚፈጠርን መርከስ መጠበቅ የሚቻለው ከዚያም ከዚያም ጋር ከመቀላቀልና ከመነካካት በመታቀብ እንደሆነ መረጃዎቹ ጠቁመዋል፡፡

አራተኛው የማንነት ማሳያው ነጥብ፣ "መታበይንና ትምክህትን አስወግዶ ለተፈጥሮ ሕግ ታዛዥና ተገዥ መሆን ይገባል" የሚለውን እሴት ያደርጋል። በጥናቱ መሰረት፣ ታዛዥነት ለመገራት፣ ለመቅናት፣ ለመልዘብና ለመመለስ ያለ ምቾት ነው። የነገሩትን የሚሰማና የታዘዘውን የሚፈጽም በጎዛምን ታዛዥ ያስብላል። በመታዘዝ እሳቤ ለጋነት ወይም አለመጠንከር ዋናው ነው። በዚህ አስተሳሰብ ለመቀየርና ለመለወጥ የተነገሩትን ለመፈጸምና ተግባር ላይ ለማዋል ያለን ፈቃደኝነት ያስረዳል። የእነዚህ እሳቤዎች መነሻ ከግል ፍላጎትና ስሜት ይልቅ ለማህበራዊ ጥቅሞችና ለጋራ እሴቶች ራስን ዝቅ አድሮ ማስገዛት እና የግልን ምቾትና ደስታ መጥኖ ለማስኬድ ተባባሪ መሆን ይገባል የሚል ነው። በመሆኑም፣ ለወል ፍላጎትና አስተሳሰብ ለመገዛት ያለን ውዴታ ይገልጻል።

የታዛዥነት ማህበራዊ እሳቤ፣ ለትብብርና ለመተጋገዝ ቅን ከመሆንና አጥፍቶ ለመመለስ በድሎ ይቅር ለማለት ገራም መሆን ነው። አምኖ መቀበልና አለመጠራጠር፣ የሰጡትን መፈጸም የታዛዥነትና የትህትና ምልክት ነው። ለፈለጉት ጉዳይና ተግባር የቀና፣ ያልገነገነ፣ ያልጠነከረ፣ ለራሱ ሃሳብ የማያድር፣ ለምን ብሎ የማያትት፣ የራሱን ጥቅም የማያስቀድም፣ በራሱ መንገድ የማይጓዝ፣ የነገሩትንና ያዘዙትን የሚፈጽም ወይም የሚቀበል ሆኖ ሲገኝ፣ ትሑት፣ ታዛዥ ቅን ይሉታል። ሸፍተው፣ አምጸውና አንገዛም ብለው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር አነጻጽረው ይገልጹታል። ከእነዚህ አራት የማንነት መገለጫዎች በሰው ልጆች ሰብዕና ውስጥ የተወከሉት በነፋስ፣ በእሳት፣ በውሃና በመሬት ናቸው። ነፋስ ፍትሃዊነትን፣ እሳት ኃይልና ጥንካሬን፣ ውሃ ንጽሕናን መሬት ደግሞ ታዛዥነትን ወክለው ይገኛሉ። እነዚህ አራቱ ባሕርያት የፍጥረት ሥሮች ተብለው ይታወቃሉ።

አንደኛው በዚህ ጥናት አካባቢ ለውጥ ሁለት መልክ ያለው ነው። የመጀመሪያው ተፈጥሯዊ የሆነ ሲሆን፣ ሁለተኛው በአቋራጭ የሚከሰት ነው። ለውጥ ማንኛውም ከተፈጥሮ የሚያወጣ ነገር በመሆኑ አጋላጭ ነው። ነገር ግን፣ ተፈጥሯዊው ለውጥ ለመተካካት፣ ለመኖር፣ በተመጠነ ልክ ለመዝለቅ መሰረት የሆነ ነው። ተፈጥሮ ራሱን እያደሰችና ህልውናዋን እያስከበረች የምትዘልቅበት መንገድ ነው። ሁለተኛው ግን ከተፈጥሮ አካሄድ በመውጣት ወደ አልተገባ መንገድ ለመግባት

ምክንያት ስለሚሆን፣ የተፈጥሮን ሥርዓት የሚያዛባ ነው። ያልተለመዱ ክስተቶች፣ እንቅስቃሴዎች በማህበረሰቡ የተወገዙ አስተሳሰቦች በመሆናቸው ማህበረሰቡ እንደ ጥፋት ይመለከታቸዋል። እንደዚህ አይነቱን ለውጥ ማህበረሰቡ አስፈላጊ እንዳልሆነ ያምናል። አጋላጭና አጥፊ፣ አዛቢ አቃዋሽ ነው ብሎ ያስባል። የለውጥ እሳቤው ከተፈጥሮው መራቅና ተደርጎ ይታሰባል። ይበልጥ መራቅ የድካም፣ የንጽሕ ጉድለት አድርጎ ያስበዋል። በተፈጥሮው መጠበቅ፣ እንግዳ ነገር እንዳይቀርብ፣ መጪው ቦታ እንዳያገኝና በፈጣሪ ባሕርይ ተግዝቶ ከመኖር ጋር ተያይዞ ይገለጻል። ለውጥ አቅምና ጉልበትን ይነሳል። ጥንካሬንና ብርታትን ይነፍጋል ብለው ይፈረጁታል። ለለውጥ ምክንያት የሚሆነው ነገር ከስጦታ ወጣ ብሎ ለመታየት መሞከር፣ ከፈጣሪ ይልቅ የሰው ልጅ በራሱ ዕውቀት ለመኖር ማሰብ ነው። ምኞትንና ድሎትን መፈለግ፣ ለሥጋ ክብርና ውዴታ መስጠት ነው።

እያንዳንዱ ፍጥረት፣ የተፈጥሮን ሕግ በመጣስ አልጣበትም ብሎ ሲያፈነግጥ፣ ከተፈጥሮ ውጭ የሆነ ከልክ ያለፈ አድራጎት ሲሰራ፣ ባሕርያቱ እርስ በርስ ይጣላሉ። እነዚህን ተፈጥሮዎቹን በመላጨት፣ በመቆረጥ፣ በመገፈፍ፣ የትም በመጣል፣ አክብሮት በመንፈግና በመሳሰሉት መዛባቶች ሲያቃልላቸውና በስስትና በንፍገት ሲያዛባቸው የመከላከል አቅማቸው እየደከመ፣ ከተፈጥሮ እየራቀ፣ ከጥንካሬው እየሸሸ ይሄዳሉ። ጥራቱን እያጣ በሄደ ቁጥር ክብሩ እየቀነሰ፣ ቀድሞ የነበረው ጥንካሬ እየጠፋ፣ ከንጽሕናው እየወጣ፣ ዓለማዊነት እየገዛው፣ መንፈሳዊነት እየራቀው መክበድ መውለዱ እያደከመው፣ የቤቱ ጣጣና ነገር ሁሉ እያሳሰረው ስለሚሄድ፣ የቀድሞ መልክና ባሕርይ ይጠፋል። ተፈጥሯዊ መልክን ጠብቆና አክብሮ መጓዝ ይከብዳል። የባሕርዮች መጣላት እና መለያየት የሚመጣው፣ አንዱ ባሕርይ ተለይቶ በዝቶ ሌሎች አንሰው ሲገኙ ነው። ስለዚህ፣ ሰው ከነፍሱ ጋር ፍጹም ውህድ የሚሆነው በቀዳሚ ተፈጥሮው ውስጥ ሲገኝ ነው።

በመሆኑም፣ በኀጣን በባሕርይ መዛባት ድካም፣ ዕልቀት፣ ባዶነትና ሞት ሲመጣ ምልክት የሚሆኑት አውዶች ከጊዜ ጨለማና ክረምት፣ ከሽግግር ሥርዓቶች ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት፣ ከዕድሜ ሽምግልና እና እርጅና፣ ከተክለሮች ህይወት የአመድ ዘመን፣

ከሰብሎች የዕድገት ወቅት የአውድማ ጊዜ ይጠቀሳሉ። ማዕድ፣ እርግዝና፣ ህመምና ምጥ የድካም ጊዜዎች ናቸው ይባላል።

በመሆኑም፣ እርጅና፣ ማለቅና ማብቃት ነገሮቹ ከተፈጥሮ መንገዳቸው ሲወጡ የሚኖራቸው ጠባይ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያሳያል። በፍጥረቶች ቀዳሚ ዘመን ላይ ዘግይቶ የሚመጣው አመል ያለጊዜው ከቀደመ፣ ተከታዩም ቦታውን ለዘገየው ካስረከበ የፍጥረቱ ባህርይ ስለሚዛባና የተፈጥሮ መንገዱን ለቆ ጠባዩን እየተወ ስለሚሄድ መንገዱን ይስታል። በመሆኑም፣ ሞት በፍጥረቶች ላይ የሚመጣው የመከላከልና የመመከት አቅም ፍጹም ሲያልቅና ተፈጥሮው ከሰብዕና ውስጥ ሲሟጠጥ ይሆናል። አካሎቹ በእርጅና ከተፈጥሮ እየሸሹ በሄዱ ቁጥር በመካከላቸው ያለው ትስስር ልል እየሆነ ሄዶ ይሰንፍና አልታዘዝ ይላል። አቅም ማጣት ደግሞ ለመያዝና ለመወረር ምቹ መደላድል ይፈጥራል። ይህ አቅመቢስነትና አለመከላከል ፍጹም የሚሆነው፣ ተፈጥሮን ሙሉ በሙሉ በምናጣባት፣ በሞትና 'በባዶነት'፣ ውስጥ ነው።

በመሆኑም፣ እያንዳንዱን ፍጥረት ለክፉ ዐይን የሚያጋልጠው ከተፈጥሮው መራቁና መሸሹ ሲሆን፣ የሚያስጠብቀው ተፈጥሮውን ማክበሩ ነው። ከባሕርይ ሥር ይበልጥ እየራቁ መምጣት አቅምና ጉልበት የሚያሳጣ በመሆኑ አጋላጭነቱ ፍጹም ነው። ወደቀዳሚነት መቅረብ ግን ይህን የመጋለጥ መጠን ለመቀነስና ጥንካሬን ለማግኘት የሚረዳ ራስን መግዣ መንገድ ነው። በልጅነት፣ በመብቀል፣ በመውጣት፣ በጥንስስ፣ በመንምራት፣ በመጸነስ ውስጥ ሁሉም ነገር በአዲስና በአግባብ የሚገኝ በመሆኑ፣ በአዲስ የተፈጠረና የተሞላ ሃይል ይኖረዋል።

ብልቶች በቀዳሚነት ከያዙት ጠባይና ባህርይ እየራቁ በሄዱ ቁጥር ሃይልና ጥንካሬያቸው በተፈጥሮ አካሎች መካከል ያለውን ዝምድና ልል የሚያደርግና ወደ ሞት የሚያስጠጋ ይሆናል። በመሆኑም፣ በፍጥረቶች ቀዳሚ ዘመን ላይ ዘግይቶ የሚመጣው ባሕርይ ያለጊዜው ከቀደመ፣ ተከታዩም ቦታውን ለዘገየው ካስረከበ የፍጥረቱ ባህርይ ስለሚዛባና የተፈጥሮ መንገዱን ለቆ ጠባዩን እየተወ ስለሚሄድ መንገዱን የሚስት ይሆናል። በቀዳሚነቱ መጥፋት ምክንያት በዚያ አካል ላይ የሚመጣው የቅርጽ መዛባት በሞትና በመድከም ለሚጠቀሙ ሃይሎች ለመሰልጠን

አጋጣሚን ይፈጥራል። በመሆኑም፣ በአመድ የሚከብሩ በተክሎች በሞት ይደሰታሉ። በአስከሬን፣ በጥንብ፣ በአተላ፣ በአምቡላ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ሞት ወይም ፍፁም ተገዥነት በፍጥረቶች ላይ የሚመጣው የመከላከልና የመመከት አቅም እየተዳከመ፣ እየፈዘዘ፣ ጥቅም መስጠቱን እያቆመ፣ ቀዳሚ ጉልበቱና አቅሙ እያነሰና እያጠጠ ሄዶ ዝምድናው ወደ መረሳት፣ አገልግሎቱ ወደ ማለቅ፣ አካል ወደ አለመታዘዝ፣ ነገሩ ወደ አለመጥቀምና አለመፈየድ ሲሄድ ነው። ሥጋ ደካሚ አካል በመሆኑ፣ በውስጡ የነበረው አንቀሳቃሽ፣ ሃይል ሰጪና ፈሳሾች እየተሟጠጡበት ሄደው ባዶውና ቀፎው አካል ስለሚቀር፣ በቀላሉ ለመያዝና ለመወረር ምቹ ይሆናል። ይህ አቅመ-ቢስነት የሚመጣው ከላይ ለማየት እንደተሞከረው፣ ከቀዳሚ ሁነቶቻችን በምንርቅባቸውና ተፈጥሯዊ ባህርዮቻችንን አጥተን ባዶ በምንቀርባቸው ወቅቶች ነው።

እያገለገለና እየሰራ ሄዶ ከተወለደበትና ከተፈጠረበት ዘመን እየራቀ መጥቶ ተቀዳሚ ተፈጥሮውን የሚያጣው መሬታዊ ባህርይው ሲከብደው ነው። እያንዳንዱ ፍጥረት እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ አገልግሎቱን ጨርሶ ሲያጠናቅቅ የሚቀረው ነገር ሙት መባል ነው። እያንዳንዱን ፍጥረት ለክፉ ዐይን የሚያጋልጠው ከተፈጥሮው መራቁና መሸሹ ሲሆን፣ የሚያስጠበቀው ደግሞ የጥንካሬው ምንጭ የሆነውን ተፈጥሮውን ማክበሩ ነው ይላሉ። ይበልጥ እየራቁ መምጣት አቅምና ጉልበት በፍጹም የሚያሳጣ በመሆኑ አጋላጭነቱ ከፍተኛ ነው። ወደቀዳሚነት መቅረብ ግን ይህን የመጋለጥ መጠን ለመቀነስና ጥንካሬን ለማግኘት የሚረዳ ራስን መግዣ መንገድ ነው።

በተፈጥሯቸው ውስጥ ገፊነት፣ ተሻሚነት፣ መራዥነት፣ አፍራሽነት ያለባቸው፣ የሚወላውሉና የማይጸኑ፣ ድካም ያለበትን የሚወዱ፣ ደረቅና በረሓ የሚያከብራቸው፣ የተሰራውን ነባሩን፣ የጸናውንና የሚታወቀውን ነቅለውና አፍርሰው የማይታወቀውንና እንግዳውን የሚተክሉ፤ በተሰራውና በሰለጠነው ላይ መጥተው የሚሰፍሩ፣ ቀዳሚውን የሚጠሉ፣ መጤንና ባዕዱን የሚወዱና የሚያስተዋውቁ ናቸው ይሏቸዋል።

በቀንድ ከብቶች ጉያ ተጣብቀው ደም የሚመጡ ክፉ ተባዮች፣ በአገዳ እህሎች ላይ የሚጣበቁ ቀጫጭን ትሎች፣ ጥንብ አንሳዎች፣ ኑግ የሚመስል ቅጠል ያላቸው

ትላትሎች፣ የመስክንና የቡቃያን ሥር የሚበሉ መርዛማነት ያላቸው ዕንጨቶች፣ ፍጥረታትን አስክረው የሚገድሉና በድን የሚያደርጉ እሾኻማ የበረሐ ዛፎች፣ እንስሳትን አቁስለውና መርዘው ገድለው በጥንባቸው የሚከብሩ፣ አንበላና አተላ እንዲሁም አመድ ቀለባቸው የሆኑ ፍጥረቶች ሁሉ የዚህ መንፈስ ማደሪያዎች ናቸው።

ንስሐ የሰውን ልጅ ከባሕርይ መተላለፍ አውጥቶ ወደ ቀደመ የተፈጥሮ ሚዛን እና የሰብዕና ስፍር መመለሻና ማስተካከያ መንገድ ነው። የባሕርይ መዛባትን ደምስሶ ሰው የሚያደርግ፣ የረከሰ ማንነትን የሚያነጻ፣ የወደቀውን በማንሳት ወደ ማንነት የሚያቀርብ ነው። በመርከስ ሂደት የሚታከመው ተጋላጭ ባሕርይ ሲሆን፣ ደህንት የሚሆነው ወደቀደመ ተፈጥሮ በመመለስ ነው።

እነዚህ ባሕርዮች እርስ በርስ በግብር እንዲታረቁ፣ እንዲስማሙና እንዲመጣጠኑ እየተደረገ አንዱ ከባሕሪው አልፎ ሲገኝ፣ በሌላው ግብር እየተገደበ፣ አንዱ ሲያንስ ወደ መጠኑ እንዲመጣ የሚሆንበት የማቻቻያ መንገድ ንስሐ ይባላል። ይህ ዘዴ ባህርያቱ እንዳይጣሉና እንዳይጋጩ ማድረጊያ የሰብዕና ሚዛን ማስጠበቂያ ስልትም ነው። በመሆኑም፣ ሥጋን በመቅጣትና በማስተካከል፣ ነፍስን ወደቦታዋ ለመመለስ በሚደረገው ሥርዓት ውስጥ አራት ዘዴዎች አሉ። እነሱም ጸሎት፣ ምጽዋት፣ ጾምና ስግደት ናቸው። የእነዚህ አራት ቴክኒኮች ዋና ተግባር ሥጋ የሰበሰበውንና ያጠራቀመውን የሚበትኑ፣ የሚቀንሱ፣ የሚጠርጉና የሚያራቁቱ፣ በዳይ በጸጸት፣ ራስን በመውቀስ ፈቅዶና ወዶ ወደራሱ ነባር መምጫው መንገዱ ነው።

ስለዚህ ፀሎት ራስን መክሰሻና መውቀሻ፣ ውስጥን መመርመሪያና ጥፋትን ማወቂያ መንገድ ነው። ጥፋትን ከልብ ተቀብሎ ለመመለስ የሚደረግ ይቅርታም ማግኛ ነው። ግብታዊነትን፣ ስስትን፣ ስሜታዊነትን ከህሊናችን አስወግደን በአጠይቆትና በምርምር፣ በማሰብና በማስተዋል ነገሮችን እንድንመረምር የተሰወረው እንዲገለጥልን፣ ያላስተዋልነው እንዲታየን ቀልብንና ስሜትን ሰብስቦ አንድን ነገር በአስተውሎት እንድናይ የሚያደርግ የመመርመሪያ መሳሪያ ነው።በማቆት የመጣው ልዩ ጠባይ በማደልና በመበተን እንዲታረቅ ምጽዋት ዋነኛ ዘዴ ይሆናል።

በመጥገብና በመስከር የረከሰውን፣ በማስራብና በማስጠማት ለማንጻት መሞከር ነው። ለትግልና ለልፊያ የሚሆንን ጉልበት በስግደት በማድከም፣ ዘዋዊነትን በታዕቅቦ በመግራት ልቅ ፍላጎትና ወሰን አልባ እርካታ የሚያመጣውን ጥፋት በእነዚህ ዘዴዎች አማካይነት በመግታት ባሕርይን ለመመለስ መከራ ይደረጋል።

9.2. ይሁንታ

በመስክ ላይ ከተገኘው ልምድና መረጃ በመነሳትና በቃለመጠይቅና በተኩላሪ የቡድን ውይይት ላይ መረጃ ሰጪዎቹ ያነሷቸውን ጠቃሚ ነጥቦች በመመርመር በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ቀጣይ ጥናት ቢደረግ መልካም ነው እላለሁ።

በዚህ ጥናት ውስጥ በክፉ ዐይን ዙሪያ የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን የማያ መነጽር ሆኖ ያገለገለው "ተፈጥሯዊ ሞዴል" አጠቃላይ በባህሉ ውስጥ ያሉ የፎክሎር ነገሮችን፣ የአካባቢን ርዕዮተ ዓለምና ማንነት እንዲሁም የአስተሳሰብ ሁኔታ ለመተንተን የሚያግዝ የፍልስፍና ማጠንጠኛ ነው ብዬ አምናለሁ። ይህንን ቁምነገር በአጠቃላይ ለባህል ዘርፍ ጥናት የመተንተኛ ሞዴል አድርጎ ለመመርመር ቢታሰብ መልካም ነው እላለሁ። በተለይ የክርስትና ባህል ያላቸውን ማኅበረሰቦች አስተሳሰብ ለመመርመር ይረዳል የሚል ግምት አለኝ። በመሆኑም፣ ይህ ጉዳይ ተመርምሮ ሞዴል ተቀርጾለትና አጠቃላይ አላባዎችን ባጠቃለለ መልኩ ማዕቀፉ ቢዘጋጅ የሚል አስተያየት አለኝ። በሞዴሉ ላይ ሰፋ ያለ ጥናትና ምርምር ተደርጎ ክፍተቶቹ ተሞልተው እንደ አንድ የመተንተኛ ማዕቀፍ ሆኖ የሚያገለግልበት መንገድ ቢመቻች መልካም ነው እላለሁ።

በአካባቢው የወረዳ አስተዳደር አወሳሰን፣ የወረዳ ከተማ ምርጫና ማስተዳደር ላይ የሚነሱ ቅራኔዎች፣ አባት አባት ከተሞች እያሉ አዳዲሶችና በቅርብ የተቋቋሙ ቀበሌዎችና ከተማዎች ለምን የመንግስት የመስተዳድር አስተዳደር ምርጫዎች ሆኑ፣ አባቶች እያሉ ልጆች ለምን መሩን፣ አባት አባት ከተሞችን ፈጠፍልቀውና የእኛን አባት ንቀው ሌላውን አባት ዋና ከተማ አደረጉት የሚሉ፣ ከዚሁ የቀዳሚነት መንፈስ የሚነቃ እሮሮ በጎ ያልሆነ ስሜት ነው። በአካባቢው ባሉ የወረዳ ሕዝቦች መካከል ያለው ግጭት ሊፈታ የሚችለው በዚህ መንገድ ስለሆነ፣ በተለይ ማንኛውም የአስተዳደር፣ የልማትና መሰል ስራዎች ሲሰሩ ይህ ነገር ታሳቢ ቢሆን።

እንስሳትን፣ ዕፀዋትንና አንዳንድ ግዑዛን ነገሮችን ለሃብት፣ ለዝናና ለክብር፣ ለጤና ማከሚያና ለመከላከያነት በሚመረጡ ጊዜ ታሳቢ የሚሆነው አባት ዛፍ መሆን አለመሆኑ፣ ከፍ ከፍ ብሎ ማደጉና ቁልቁል መዝለቁ፣ ቀጠኖ መውጣቱና ወደ ጎን መስፋቱ ስለሆነ፣ በተለይ በሃገረሰባዊ መድሃኒት ጥናት በኩል ይኸ አስተሳሰብ ትኩረት ተደርጎ ቢጠና መልካም ነው እላለሁ፡፡

በአካባቢው አዳዲስ ቴክኖሎጅዎች እየተዋወቁ በመሆናቸው፣ ከዘር ምርጫ፣ ከአዳዲስ የሥራ ፈጠራዎች፣ የሰብል ትውውቆች፣ እንግዳ ሰዎችን ከማሳተፍና ከማቀፍ ጋር ያለው እምነት ሁሉ ማጠንጠኛው ይኸ ነጥብ በመሆኑ፣ እንግዳ አስተሳሰብንና ሰውን ከአካባቢ ጋር ለማላመድ የሚያስፈልጉ ቴክኒኮችና ስትራቴጅዎች ቢዘጋጁ መልካም ነው እላለሁ፡፡

በአካባቢው የማህበራዊ አባላቱ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ፣ የአካባቢው ሰው ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር የሚገናኘው ነገር መንገድ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚህ ምክንያት ነባሩ ነገር ሁሉ በእጅጉ የተፈተነ ይመስላል፡፡ እነዚያን ፍላጎቶች የሚያስተናግድ ስርዓት ባልተፈጠረበት ነባሩም ልምድ በአዲስ ባልተቀየረበት ሁኔታ የችግሩ መጠን ማየሉ አይቀርም፡፡ በተለይ በአካባቢ የስርቆት፣ የግድያ፣ የድብድብና ሌሎም ሕገወጥ ስራዎች እየመጡ ያሉት በነባሩና በአዲሱ አስተሳሰብ መካከል በተፈጠረ ግጭት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በመሆኑም፣ ማህበራዊ ሥርዓቱ ሁለቱን አስተሳሰቦች በእኩል እንዲያገለግል፣ የፍትህ ተቋማት፣ የቁጥጥርና የክትትል ስራዎችን ነጻ አድርጎ በመሄድ ላይ የሚሰራውን ስራ ትኩረት ሰጥቶ ማከናወን ተገቢ ነው እላለሁ፡፡ አዲሱ ከነባሩ ጋር ተጣጥሞ ከዘመን እና ከአዳዲስ አስተሳሰቦች ጋር አብሮ የሚያድግና መፍትሄ የሚሆን ስርዓት ለመፍጠር የሚያስችል ማህበራዊ ህግ አውጪ አካል አለመኖር፣ ለአዳዲስ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች በነበረው አስተሳሰብ መፍትሄ ለመፈለግ መሞከር፣ ከነባሩ ጋር አልገጥም ሲሉ ጠልፎ ለማስቀረት በሚደረግ ጥረት የተነሳ በአዲስ አስተሳሰቦችና በነባሩ መካከል ግጭት እየተፈጠረ ስለሆነ፣ በዚህ ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ቢደረግ ለበርካታ ችግሮች መፍትሄ ይገኛል ብዬ አስባለሁ፡፡

በአካበባው እየተካሄደ ያለው ቁሳዊ ልማት ሲሆን፣ በባህሉ ውስጥ ያለው መንፈሳዊ ልማት ነው፡፡ ቁሳዊው እና መንፈሳዊ ልማት ሳይጋፉ፡ ተጣጥመው የሚሄዱበት መንገድ ቀድሞ ካልተጠነ የተሳለጠ ነገር ይኖራል ብዬ አላምንም፡፡ አዳዲስ አስተሳሰቦች ከማህበራዊ ልምዶች የፈለቁ ሳይሆኑ፣ ከውጭ ከሌላ ባህል የተቀዱ በመሆናቸው ከነባሩ ጋር ያላቸው መጣጣም ሳይጠና በግድ ለማስተሳሰር የሚደረገው መከራ ቅጥአምባር እያበላሸ ስለሆነ፣ ሌላ ማህበራዊ ችግር ከመፍጠሩ በፊት ተስማምተው የሚሄዱበት ነገር በተመራማሪዎች ቢታሰብበት መልካም ነው ብዬ እጠቁማለሁ፡፡

ከአመጋግብ ጋር በተያያዘ የሚመጣውን የጤና ችግር ለመፍታት የአካባቢው ሰው የዘየደው መላ ለጤና ፖሊሲ ግብዓት ሊሆን የሚችል በመሆኑ ሰፋ ያለ ጥናት ቢደረግበትና ከመከላከል ፖሊሲው ገር ተጣጥሞ የሚጓዝበት መንገድ ትኩረት ቢሰጠው እላለሁ፡፡

ዋቢ መጻሕፍት

መ.ሉቀን ዘውዱ፤ በባህርዳር አካባቢ በወንዞች ዳር የሚፈጸሙ የአምልኮ ሥርዓቶችና ክዋኔያቸው፤ትስስር፤ አ.አ.ዩ. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ዲማጽ፣ 2001 ዓ/ም።

መልአከ ገነት ሃይለማርያም ፈንታሁን፤ *መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ*፤ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1999 ዓ/ም።

መሪራስ አማን በላይ፤ መጽሐፈ ብሩክ ጐንሽዋ ቀዳማዊ፤አዲስ አበባ (የህትመት ቦታ ያልተገለጸ)፤ 2000) ዓ/ም።

መኮንን ባይህ፤ በምሥራቅ ጎጃም ዞን በቢቡኝ ወረዳ የገነቱ ማርያም ቀበሌ የባህላዊ ማቅ አሠራር፤ ጠቀሜታና ባለሙያዎች ከሙየው ጋር ያላቸው ትስስር፤ አ.አ.ዩ. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ዲማጽ፣ 1998 ዓ/ም።

ማሞ ተፈራ፤ በመኸር ወቅት የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳና የቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና በዳንግላ ወረዳና አካባቢ፤አ.አ.ዩ. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ዲማጽ፣ 2002 ዓ/ም።

ቅዱስ ኤፍሬምና አባ ሕርያቆስ፤ (ቀ.የ)፤ *ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፤ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ።

በምስራቅ ጎጃም ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የተዘጋጀ ሪፖርት፤ (ያልታተመ)፤ 2004 ዓ/ም ።

ባሕሩ ዘውዴ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983፤ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 1999 ዓ/ም።

ተክለ-ጻድቅ መኩሪያ፤ ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት፤ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1981 ዓ/ም።

----------፤ ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፤ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1982 ዓ/ም።።

----------፤ ዐፄ ሚኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት፤ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1983 ዓ/ም።።

ተክለየሱስ ዋቅጅራ፤ የጎጃም ትውልድ በሙሉ ከአባይ እስከ አባይ፤ግርማ ጌታቸን እንዳዘጋጀው፤ አዲስ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 2003 ዓ/ም።።

ጎሩይ ወልደሥላሴ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፤ አዲስ አበባ፤ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣1999 ዓ/ም።።

ጎሩይ ወልደ ሥላሴ፤ የልቅሶ ዜማ ግጥም፤ አዲስ አበባ፤ ኮምፒዮግራፊ አታሚዎች፣ 2001 ዓ/ም።።

እምሩ ኃይለ ሥላሴ፤ ካየሁት ከማስታውሰው፤ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ፕሬስ፣ 2002 ዓ/ም።።

አስረስ የኔሰው፤*የካም መታሰቢያ፡ የኢትዮጵያ ፊደል መሰረትነት መታወቂያ*፤ አሥመራ፤ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት፣ 1951ዓ/ም።።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ(አለቃ)፤ *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፤ አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ/ም።።

ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፤ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣1990 ዓ/ም።።

ደስታ ተክለወልድ፤ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ/ም።።

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ።። የአማራ ሕዝብ ባህልና

ቋንቋ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲ አበባ፣ 2001 ዓ/ም፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሐፍ፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1980 ዓ/ም፡፡

ዮሴፍ ጌትነት፤ "ባህላዊ እርቅ በምሥራቅ ጎጃም መስተዳድር ዞን በደባይጥላትማን ወረዳ"፤ ኤ.አ.ዩ. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲግጽ፣ 1998 ዓ/ም፡፡

ዘሪሁን አስፋው፤የስነጽሁፍ መሰረታውያን፤ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1998 ዓ/ም፡፡

Alan Barnard, Jonathan Spencer. *Encyclopedia of Social and Cultural Anthropology.* New York: Routledge, 2002.

Barnard, Alan. *History and Theory in Anthropology.* Cambridge: Cambridge University Press, 2004.

Berry, Veronica. "Neapolitan Charms against the Evil Eye." *Folklore*, 1968: pp. 250-256.

Blek, Wolf. *Witchcraft, Gossip adn Death: A social Drama.* 1976.

CSO. 1966. Imperial Ethiopian Government Central Statistical Office: Report on A survey of Gojjam Province. Addis ababa

Coss, Richard. "Reflections on the Evil Eye." *Human Behavior* , 1974: 3:16-22.

Daniels, S. *Daniels S (1993) Fields of vision: landscape and national identity i.* England : Polity Pres, 1993.

Dawson, Catherine. *A Practical Guide to Research Methods.* Spring Hill House: howtobooks, 2007.

Douglas, Mary. *Purity and Danger.* LONDON: Routledge & Kegan, 1966.

Douglas, M. *Natural Symbols Explorations in cosmology.* London: Barrie &

Rockliff, 1970.

-----. *Thirty years after Witchcraft, Oracles and Magic, in M. Douglas (ed.) Witchcraft Confessions and Accusations.* London: Tavistock, 1970.

Douglas, M. (1963) 'Techniques of Sorcery Control', in J.Middleton and E.H.Winter (eds) *Witchcraft and Sorcery in East Africa,* London: Routledge and Kegan Paul

Druckman, Daniel. "Nationalism, Patriotism, and Group Loyalty: A Social Psychological Perspective." *Mershon International Studies Review*, 1994: 46.

Dundes, Alan. "Folk Ideas as Units of Worldview." *The Journal of American Folklore*, 1971: pp.93-103.

-----. *Wet and Dry, The Evil eye: An Essay in Indio-Europian and Semitic Worldview.* 1971.

Dundes, Alan. *Interprating Folklore.* Bloomington: Indiana University Press.,1980.

Eller, Jack David. *Introducing Anthropology of Religion Culture to the Ultimate.* New York,: Routledge, 2007 .

Erikoson, Erik H. *Toys and Reasons: Stages in the Ritualization of Experience.* New York: Norton, 1977.

EVANS-PRITCHARD, E. E. *Witchcraft, Oracles and Magic among the Azande.* Oxford: Clarendon Press , 1937.

Fetterman, D. M. *Ethnography: step-by-step.* Los Angeles: SAGE Publications, Inc., 2010.

Finneran, Niall. "Ethiopian Evil Eye Belief and the Magical Symbolism of Iron Working." *Folklore*, 2003: pp. 427-433.

Geertz, Clifford. *The Interpretation of Cultures.* New York: Basic Books, Inc,

1973.

Geertz, Clifford. "Ethos, World-View and the Analysis of Sacred Symbols." *The Antioch Review*, 1957: pp. 421-437.

----. *THE Interpretation of Cultures.* New York: Basic Books, Inc., 1973.

Getie, Gelay. "Semantic Analysis of Amharic Kinship Terms in Gojjam: An Anthropological Approach." *Africa: Rivista trimestral di studie documentazione dell'Istituto italiano per l'Africa e l'oriente*, 1998: pp. 71-92.

Glesne, C., & Peshkin, A. *Becoming qualitative researchers: An introduction.* New York: Longman, 1992.

Gluckman, Max. *Politics, Law and Ritual in Tribal Society.* Oxford: Basil Blackwell and Mott,ltd, 1965.

Gluckman, M. *Custom and Conflict in Africa.* Oxford: Basil Blackwell, 1956.

Gluckman, M. (1944) 'The logic of African science and witchcraft', Human Problems in Central Africa 1: 61—71. "The logic of African science and witchcraft." *Human Problems in Central Africa* (Gluckman, M. (1944) 'The logic of African science and witchcraft', Human Problems in Central Africa 1: 61—71.), 1944: 1: 61—71.

Green, M. *Shaving witchcraft in Ulanga', in R. Abrahams (ed.) Witchcraft in Contemporary Tanzania.* Cambridge: Cambridge African Studies Centre, 1994.

Guetzkow, Harold. "Isolation and Collaboration: A Partial Theory of Inter-Nation Relations." *Conflict Resolution,*, 1957: pp. 48-68.

Harrell, Stevan. "The Concept of Soul in Chinese Folk Religion." *The Journal of Asian Studies*, 1979: pp. 519-528.

Herzfeld, Michael. "Meaning and Morality: A Semiotic Approach to Evil Eye Accusations in a Greek Village." *American Ethnologist*

(American Ethnologist, Vol. 8, No. 3, Symbolism and Cognition (Aug., 1981), pp. 560-574), 1981: pp. 560-574.

Herzfeld, Michael. "Honour and Shame: Problems in the Comparative Analysis of Moral Systems." *Man (NS)*, 1980: 15: 339-351.

Hoelscher, S. D. 2003. Making Place, Making Race: Performances of Whiteness In the Jim Crow South. Annals of the Association of America Geographers 93 (3): 657-68), 2003: 93 (3): 657-68

Homans, George C. "Anxiety and Ritual: The Theories of Malinowski and Radicliff-Brown." *American Anthropologist*, 1941: pp. 164-172.

Kearney, Michael. "World View Theory and Study." *Annual Review of Anthropology*, 1975: pp. 247-270.

Koehn, Peter. "Land Tenure among the Amhara of Ethiopia: The Dynamics of Cognatic Descent by Allan Hoben." *ASA Review of Books*, 1978: pp. 41-44.

Koehn, Peter. "Land Tenure among the Amhara of Ethiopia: The Dynamics of Cognatic Descent by AllanHoben." *African Studies Association*, 1978: pp. 41-44.

Krige, J. D. "The Social Function of Witchcraft." *Theoria*, 1947: PP. 8-21.

Kluckhohn, C. *Navaho Witchcraft.* Boston: Beacon Press, 1944.

Lease, Emory. "The Number Three, Mysterious, Mystic, Magic." *Classical Philology* (Lease, Emory. B. 1919. "The Number Three, Mysterious, Mystic, Magic". Classical Philology. pp. 56-73), 1919: pp. 56-73.

Lienhardt, Godfrey. "Some Notions of Witchcraft among the Dinka." *Africa: Journal of the International African Institute*, 1951: pp.303-318.

Luhrmann, T. *Persuasions of the Witch's Craft.* Oxford: Blackwell, 1989.

Malinowski, BRONISLAW. *The Dynamics of Culture Change an Inquiry*

into Race Relations in Africa. New Haven: Yale University Press,1945.

Malinowski, Bronislaw. "The Group and the Individual in Functional Analysis." *American Journal of Sociology*, 1939: pp. 938-964.

Marwick, M. G. "The Social Context of Cewa Witch Beliefs." *Africa: Journal of the International African Institute*, 1952: pp.120-135.

Marwick, M. G. "The Social Context of Cewa Witch Beliefs." *Africa: Journal of the International African Institute*, 1952: pp.120-135.

Marwick, M.G. *Sorcery in its social setting:A study of the Northern Rohdesian cewa.* Manchester: Manchester Universty Press, 1965.

Mayer, P. *Witches', in M. Marwick (ed.) Witchcraft and Sorcery.* Harmondsworth: Penguin Books, 1970.

McGee, R. and Warms, Richard L . Anthropological Theory. New York: McGraw-Hill, 2008.

Meyerowitz, Eva L. R. "Concepts of the Soul among the Akan of the Gold Coast." *Africa: Journal of the International African Institute*, 1951:pp.24-31.

Middleton, John. *Lugbara Religion Ritual and Authority Among An East African Peole.* London: Oxford Universwity ress, 1960.

Middleton, John, and E. H. Wintereds. *MiddletoWitchcraft and Sorcery in East Africa.* London: Routledge and Kegan Paul, 1963.

Miller, Arthuri. *Deciphering the Cosmic Number.* United States of America: Nortorn and Company led., 2009.

Moore, H. L. *Magical Interpretations, Material Realities.* London: Taylor & Francis e-Library, 2004.

Nadel, S. F. "Witchcraft in Four African Societies: An Essay in Comparison." *American Anthropologist* (American Anthropologist, New Series, Vol. 54,

No.1 (Jan. - Mar., 1952), pp. 18-29), 1952: pp. 18-29.

Quinton, Anthony. "The Soul." *The Journal of Philosophy*, 1962: pp. 393-409.

Radcliffe-Brown, A. R. "On the Concept of Function in Social Science." *American Anthropologist*, 1935: pp. 394.

Rawls, Anne Warfield. *Epistemology and Practice Durkheim's The Elementary Forms of Religious Life.* Cambridge: Cambridge University Press, 2004.

Reminick, Ronald A. "The Evil Eye Belief among the Amhara of Ethiopia." *Ethnology*, 1974: pp. 279-291.

Reminick, Ronald A. "The Symbolic Significance of Ceremonial Defloration among the Amhara of Ethiopia." *American Ethnologist*, 1976: pp. 751-763.

Sanders, Henrietta L. Moore and Todd. *Magical interpretations and material realities An introduction in Henrietta L. Moore and Todd SandersMagical Interpretations,Material Realities Material Realities occult in postcolonial Africa.* London: Routledge, 2001.

Schoeck, Helmut. "The Evil Eye: Forms and Dynamics of a Universal Superstitions." 1955: 11:153-61.

Schubert, Hermann Amborn and Ruth. "Soul and Personality as a Communal Bond." *Anthropos*, 2001: pp. 41-57.

Schubert, H. A. "Soul and Personality as a Communal Bond." *Anthropos*

Schubert, H. A. (2001). Soul and Personality as a Communal Bond. Anthropos , pp. 41-57.), 2001: pp. 41-57.

Shiner, L. E. "Sacred Space, Profane Space, Human Space." *Journal of the American Academy of Religion* (Shiner, L. E. (1972). Sacred Space, Profane Space, Human Space. Journal of the American Academy of Religion , pp. 425-43), 1972: pp. 425-43.

Spencer, Alan Barnard and Jonathan. *ENCYCLOPEDIA OF SOCIAL AND CULTURAL ANTHROPOLOGY.* London: Routledge, 2002.

Spooner, Brian. *Anthropology and the Evil Eye. In the Evil Eye, edited by Clarence Maloney, pp. 279-85.* New York: Columbia University Press., 1976.

Strathern, PAMELA J. STEWART and ANDREW. *Witchcraft, Sorcery, Rumors,and Gossip.* New York: cambridge university press, 2004.

Summer, William Graham. *Folkways.* New York: Mentor, 1960.

Taddese, Tamrat. "The Process of Ethnic Interaction and Integration in Ethiopian History, the Case of the Gafat." *Journal of Ethiopian Studies*, 1988: pp.140-141.

Taddesse, Tamrat. "Ethiopia in Miniature: The Peopling of Gojjam." *Proceedings of the Twelfth International Conference of Ethiopian Studies.* Michigan: Michigan State University. , 1994. pp.959-960.

Toelken, Barre. *The Dynamics of Folklore.* Logan: Utah State University Press, 1996.

Toit, Brian M. du. "Some Aspects of the Soul-Concept among the Bantu-Speaking Nguni-Tribes of South Africa." *nthropological Quarterly*, 1960: pp. 134-142.

Turner, V. *Schism and Continuity in an African Society: A Study of Ndembu Village Life.* Manchester: Manchester University Press., 1957.

Turner, Victor W. "Witchcraft and Sorcery: Taxonomy versus Dynamics." *Africa: Journal of the International African Institute,*, 1964: pp.314-325.

VALLÉE, JACKY. *21st century anthropology: a reference handbook.* London: SAGE Publications, Inc., 2010.

Vansina, Jan. *Oral Tradition As History.* Madison: The University of Wisconsin

Press, 1985.

Yihenew Jenbere. 1996. "Ageneric Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam." M.A. Thesis, SGS, AAU.

1. አባሪ

1.1. በቃለመጠይቅ የተሳተፉ አባላት ግላዊ መረጃ መዘርዝር

ተ.ቁ	ስም	ዕድሜ	ጾታ	የትምህርት ደረጃ	የትውልድ ቦታ	አጠቃላይ መረጃ
1	አቶ አቻምየለህ ጌታነህ	56	ወ	12+6	ደ/ማርቆስ	• ነገሌ ቦረና፣ አዲስ ዓለም፣ ደብረማርቆስ ያገለገሉ • የአማርኛ የቋንቋ መምህር
2	አቶ ቅሩብ አንተነህ	53	ወ	12+6	ደ/ማርቆስ	• ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም ዞን ያገለገሉ • የቤተክህነት ትምህርት ያላቸውና የእንግሊዘኛ መምህር
3	አቶ ዘውዴ ገበየሁ	54	ወ	12+6	ደ/ማርቆስ	• ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም የማስተማር ልምድ ያላቸው • የእንግሊኛ መምህር
4	አቶ ተዘራ አስማረ	53	ወ	12+6	አዲስ ቅዳምን	• መተከልና ደብረማርቆስ ያገለገሉ።። • የአማርኛ ቋንቋ መምህር፣ በተለያዩ ሃላፊነት ቦታዎች ያገለገሉ
5	አቶ እውነቱ ተገኘ	56	ወ	12+6	ባህርዳር	• አሥመራ፣ አሙኑኤል፣ ደብረማርቆስ ያገለገሉ • የታሪክ ትምህርት መምህር፣ በጎጃም አካባቢ ላይ ምርምር ያካሂዱ
6	አቶ ቻላቸው አንዳርጌ	54	ወ	12+6	ቀይ/ማርያም	• ምስራቅ ጎጃም
7	አቶ ግርማ ሞገስ ይታየው	50	ወ	12+4	ሞጣ	• ምስራቅ ጎጃም
8	አቶ በቀለ ውብሸት	50	ወ	12+3	ደ/ማርቆስ	• ምስራቅ ጎጃም
9	አቶ ቅሩብ አንተነህ ተበጀ	52	ወ	12+6	ሞጣ	• ወሎና ምስራቅ ጎጃም

10	መርጌታ አይነኩሉ	58	ወ	መርጌታ	ዳሊገው ዮሐንስ	• የቅኔ መምህር፣
11	መርጌታ ሞላ	63	ወ	መርጌታ	እንድማማ ኢየሱስ	የሃገር ባህል መድሃኒት አዋቂ፣
12	እማሆይ ማናዬሽ ፍካሬ	83	ሴ	የለም	የብራኔ ሐዋርያት	• ጠላ በመኸማሪ፣ በጉሊት ንግድ፣ በእርሻ ሥራም ሰፊ ልምድ ያላቸው። ከመነኩሱ 10 ዓመት የሆናቸው። መረጃ የማስታወስ ችሎታቸው ከፍተኛ የሆነ፣ ቀልድ የሚያውቁ
13	ወ/ሮ በየነች ምናሉ	54	ሴ	የለም	የብራኔ ሐዋርያት	• በሽቀጣ ሽቀጥ ንግድ የተሰማሩ፣
14	ወ/ሮ የውብዳር ጌታሁን	58	ሴ	መሠረተ ትምህርት	አብማ ማርያም	• የቤት እመቤት፣ ከብት እያረቡ ወተት በመሸጥ የሚተባበሩ። የመተረት ችሎታቸው ከፍተኛ የሆነ •
15	ወ/ሮ ቦሰና ፍካሬ	60	ሴ	የለም	የብራኔ ሐዋርያት	• አርሶ አደር፣ ሙሾ ደርዳሪ
16	አቶ ጤናው ከብቴ	69	ወ	የለም	ጨምቦርድ	• በአካባቢ በእርሻ ሥራ የተሰማሩና በሙያቸውና በምግባራቸው ሰው ሁሉ የሚያመሰግናቸው። መራቂና አስታራቂ ይሏቸዋል።
17	አቶ ዜና	71	ወ	መሠረተ ትምህርት	የጥጃን	• አርሶ አደር ናቸው። በድምጽም በውዝዋዜም በአካባቢ ተስተካካይ እንደሌላቸው የሚነገርላቸው፣ ተጫዋችና ሰው የሚወዱ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።
18	ቄስ እንስማ	74	ወ	ቄስ	የጥጃን	• በወንቃ ጊዮርጊስ ቤተክርስትያን በቅዳሴ የሚያገለግሉ፣ በስብከት፣ በሽምግልና ሰፊ ልምድ ያላቸው፣ በተጨማሪም በእርሻ ሥራ ተሰማርተው የሚገኙ ናቸው።
19	አቶ ዘመኑ ከፋለ	40	ወ	12+4	ደብረማርቆስ ከተማው	• የስነህይወት መምህር ሆነው ለ15 ዓመት ያገለገሉ። አሁን ደግሞ በርዕሰ መምህርነት በደብረማረቆ ከተማ በማገልገል ላይ ያሉ። የእርሻውን ሙያ በሚገባ የሚያውቁ።
20	አባሆይ አባተ ፍካሬ	85	ወ	የለም	የጥጃን	• ልብስ ሰፊና አርሶ አደር የነበሩ፣ አሁን ግን ጉልበታቸው ደክሞ፣ መንኩሰው ቤት የዋሉ።
21	አቶ አሸብር ፀጋ	72	ወ	12+1	አብማ ማርያም	• መምህር ሆነው ሲያገለግሉ የቆዩና በጡረታ የተሰናበቱ። በኢህአፓ አባልነታቸው ተፈርዶባቸው በጨለማ ክፍል ውስጥ ሶስት ዓመት በሥር ያሳለፉ።

22	ወ/ሮ ጥሩዬ	40	ሴ	12 ክፍል ያጠናቀቁ	የቦ	• በደብረማርቆስ ከተማ በሆቴል አገልግሎት ተሰማርተው የሚገኙ፡፡ ባል አግብተው የፈቱ፡፡ አቀንቃኝና ሙሽ አውራጅ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል
23	ወ/ሮ አካልነሽ ታምሩ	58	ሴ	መሰረተ ትምህርት	አብማ መርያም	• የቤት እመቤት፡፡ መ.ያቸው የሚነገርላቸው፡፡ በጠላቸው፣ በእንጀራቸው፣ በድቁላቸው ሁሉ ላይቀር የሚመሰገኑ፡፡
24	ወ/ሮ ሻሸቱ ተሰማ	60	ሴ	መሰረተ ትምህርት	አብማ ማርያም	• የቤት እመቤት
25	ቄስ ዕድሜአለም	53	ወ	የክህነት ትምህርት	የቦ	• የሃገር ባህል መድሃኒት አዋቂ፣ መቀሰሱን ትተው በዓለማዊ ሥራ የተሰማሩ
26	ወ/ሮ ካሰች	44	ሴ	የለም	የቦ	• የባህል ዘፈን አቀንቃኝ፣ ባለውቃቤ፣ ቀልደኛና ተጫዋች፣ አግብተው የፈቱ፣ ልጆች ያሏቸው • ሠርግና ለቅሶ ባለበት ቦታ ከፊት የሚመሩ አንደበተ ርትዑ፣ ምስጢር አዋቂ
27	ወ/ሮ ንግስቴ መ.ሉቀን	36	ሴ	የለም	የቦ	• የቤት እመቤት፣ ጠላና አረቄ አውጥተው በመሸጥ የሚተዳደሩ፣ ተጨዋች
28	ወ/ሮ ውዴ	45	ሴ	12+1	የመቃ አቦ	• በደብረማርቆስ መምህራን ኮሌጅ የቤተመጻሕፍት ሰራተኛ፣ ባህላቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ
29	አቶ ቀረዓለም መ.ሉቀን	33	ወ	8	የቦ	• የልጅ አዋቂ፣ የማስታዎስ ችሎታቸው ከፍተኛ የሆነየአካባቢ ወጎችን የሚያውቁ፣ መስከረም 16፣ 2007 ዓ/ም ህይወታቸው ያለፈ፡፡
30	አቶ ቢያድግልኝ	51	ወ	የለም	የብራጌ	• በሽመና ሥራ የሚተዳደሩ
31	ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ	57	ወ	የትርጉም መምህር	የጥጃን	• በአብማ መርያም ቤተክርስትያን የትርጓሜ መምህር፣ የሃገረስብከቱ የስብከተ ወንጌል ሃላፊ • ከPhilology Department የ M.A ተማሪ
32	ዲያቆን ብርሃኑ አድማሴ	43	ወ	12+6	አብማ ማርያም	• በመርቆስ ደብር የስብከት ወንጌል ሃላፊ፡፡ •
33	አቶ ይልቃል መለሰ	50	ወ	12 ክፍል ያጠናቀቁ	አብማ ማርያም	• በንግድ ሥራ የተሰማሩ፣ አንደበተ ርትዑ፣ ሽምግልና ቦታዎች ላይ በብዛት የሚሳተፉ፣ ነጋዴውን በመወከል በተለያዩ ቦታዎች የሚሳተፉ
34	መርጌታ ኮከበ ጽባሕ	45	ወ	የትርጉም መምህር	አብማ መርያም	• በአብማ ማርያም ቤተክርስትያን የትርጉም አስተማሪ

ADAMA UNIVERSITY LIBRARIES P.O. BOX 1176 ADAMA

35	አቶ ይዘንጋው መኮንን	65	ወ	የለም	አሽመን ኢየሱስ	አርሶ አደር የነበሩ። አሁን ደግሞ በከተማ ዘበኝነት ተቀጥረው የሚሰሩ። በሰርግና በደስታ ቦታ ሁሉ አቀንቃኝ ናቸው
36	ልጅ ስራዬ	16	ሴ	3	የቦ	• እናት አባቷ ሞተው በሰው ቤት ያደገች። • የገጠሩን ህይወት በልጅነቷ ጠንቅቃ የምታውቅ
37	ወ/ሮ አፀደ መኮንን	36	ሴ	12+2	አብማ ማርያም	• የፖሊስ አባል።በሴቶችና ሕፃናት ወንጀል መርማሪ
38	አቶ ቁሜ	67	ወ	የለም	የብራዬ ሐዋርያት	• በንግድ ሥራ የተሰማሩ። የገጠሩን ህይወት ከከተማው አስማምተው የሚኖሩ። በርካታ ቦታዎችን በንግድ ያዩ
39	መርጌታ ይሄይስ	48	ወ	የቅኔ መምህር	እንድማማ ኢየሱስ	• በእንድማማ ኢየሱስ የስብከት መምህር። ጥሩ ቅኔ አዋቂ
40	አቶ ጫኔ	74	ወ	የለም	የቦ	• አርሶ አደር። የዛር ፍርድ ሥርዓት ልዩ ተሞክሮ ያላቸው። ድፍትርናውን የሚሞክሩ
41	አቶ ጥላሁን ውሃቤ	42	ወ	12 ክፍል ያጠናቀቁ	አብማ ማርያም	• የቤተክርስትያን ስዕል አዋቂ። ባህሉን የሚተርክ። በምሥራቅ ጎጃም ወረዳ አብዛኛውን ቤተክርስትያን ስዕል የሳለ። ታሪክ የሚያውቅ
42	መርጌታ ህሩይ	77	ወ	የትርጉም መምህር	የጥጃን	• በወንቃ ጊዮርጊስ ሰባኪና የመጽሐፍ ትርጉም አስተማሪ
42	አቶ ነብይ ደለለ	68	ወ	አርሶ አደር	የጥጃን	• አርሶ አደር፣ ዘፋኝና ተጫዋች።
42	አቶ ጋሼ ህብስቴ	70	ወ	12+1	የጥጃን	• በመምህርነት ያገለገሉ። የአካባቢውን ባህልና ታሪ የሚመዘግቡ። ገጠመኞቻቸውን ማስፈር የሚወዱ።
43	ጥሩዬ ይሁን	38	ሴ	12+2	አብማ ማርያም	• የአንደኛ ደረጃ መምህርና በተለያዩ የወረዳው ክፍለች ያስተማሩ። ጨዋታ የሚያውቁና ተግባቢ።
44	ይደነቁ መኮንን	28	ሴ	12+2	አብማ ማርያም	• በጥብቅና ሙያ ያገለገሉ። አሁን በንግድ ሥራ ተሰማርተው ያሉ።
45	ወ/ሮ ሰዋገኝ	44	ሴ	የጊ.ኤች.ዲ.ተማሪ	አብማ ማርያም	• የፎክሎር አስተማሪና ተማሪ • ረጅም ጊዜ በማስተማር ያገለገሉ።
46	አለቃ ደበበ	68	ወ	• ቅስና	የቦ	• በሽምግልና ያገለገሉ። ታሪክ የሚያውቁ
47	አቶ ሙሉቀን ካሳሁን	43	ወ	• 12+2	ደብረማረቆስ	• አቃቤ ህግ

1.2.በአካባቢው እሴቶች፣ የዝምድና መፍጠሪያ ስልቶችና ታሪኮች ላይ በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሳተፉ

ተ ቁ	የአባላት ስም ዝርዝር	የውይይት ቀን
1	አቻምየለህ ጌታነህ፣	ሐምሌ 11፣ 2005 ዓ/ም
2	አቶ ቅሩብ አንተነህ፣	
3	አቶ ዘውዴ ገበየሁ	
4	አቶ ተዘራ አስማረ፣	
5	አቶ እውነቱ ተግኘ	
6	አቶ ቻላቸው አንዳርጌ	
7	አቶ ግርማ ሞገስ ይታየው	
8	አቶ በቀለ ውብሸት	

1.3. በሽሽግግር ሥርዓት ልማዶች ውስጥ ስለተከለከሉና ስለተፈቀዱ ነገሮች ከሴቶች ጋር የተደረገ የተተኳሪ የቡን ውይይት

ተ ቁ	የተሳታፊ አባላት ስም	
1	እማሆይ ማናዬሽ ፍካሬ	
2	ወ/ሮ በየነች ምናሉ	ህዳር 24፣ 2006 ዓ/ም
3	የውብዳር ጌታሁን	
4	ወ/ሮ ቦሰና ፍካሬ	
5	ወ/ሮ አካልነሽ ታምሩ	
6	ወ/ሮ ሻሽቱ ተሰማ	
7	ወ/ሮ ንግስቲ መሉቀን	

1.4. በንጽሕና፣ በርክሰት፣ በነፍስና ሥጋ ባሕርይ፣ በመፈወሻ ዘዴዎች ዙሪያ

ተ ቁ	የተሳታፊ አባላት ስም	ህዳር 11፣ 2006 ዓ/ም
1	መርጌታ ዲበኩለ	
2	ሊቀትጉሃን ኃይለጊዮርጊስ፣	
3	ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ	
4	መርጌታ ኮከበ ጽባሕ፣	
5	አቶ አሸብር ፀጋ፣	
6	(መርጌታ አይነኩለ	
7	ቄስ እንስማ ደለለ	

1.5. መዳዬ ቃላት

ለቆ ምርት፣ አላባ

ላሽ የሱቆችን የቁልፍ ወዝ የሚመጥና የሚለስ ወሳጅ

ሌማት

መካን የማትወልድ ሴት፣ ብትወልድም የማይባረክላት የሚያድግላት

መርከስ ሃጢያት ሰራ፣ ባሕርይውን ለቀቀ፣ አደፈ ጎደፈ ማለት ነው።

ሚሪ ልጃገረዶች እንደመቀነት በወገባቸው የሚታጠቁት ጠፍር፣ የድንግልና ምልክት፣ ሲያገቡ የሚያወልቁት።

ማዕድ በገበታ ላይ ያለ መብልና መጠጥ። የሞተ እህል የሚቀርብበት ገበታ

ራስ የሰውነት ቀንድ፣ የሁሉም የበላይ፣ ቁንጮ፣ የአካል አቅኝ

ሳዱላ ድንግልናን ለማጣት ምልክት፣ ወደ ሰገን ለመግባት መነሻ የሆነ የልጭት አይነት፤ ቅርጹ ድስት ስለሚመስል አንዳንድ ጊዜ ድስት ቅርጹ ይሉታል። ጉልቻ ለመጎለቲ ምሳሌ ሲያደርጉ

ስሚዛ፡- ሰንሰል፣ ግንዱ ተቆርጦ የሚጸድቅ ተክል፣ ድንበር ላይ ተተክሎ አጥር የሚሆን፣ ወሰን ላይ ስለሚተከል፣ ስም ይዛ የቆመች አሉት፣ ድንበር ለይ በመሆኑ


ቁመኛ እንስሳት አደግድገው፣ መንምነውና ከስተው እንዲሞቱ የሚያደርገውን ህመም የሚያመጡ ሰዎች መጠሪያ ነው

ቀንድ በእንስሳትና በአራዊት ራስ ላይ የሚበቅል ሥጋዊ ጦር፣ የድል ማድረጊያ፣የመታመኛና የመጠጊያ ምልክት የሆነ


ቅርፊት	ፍጥረቱን ከቅዝቃዜና ከመበስበስ የሚከላከል፣ የውሃ ውስጥ ፍጥረቶች የአካል መሸፈኛ ጠንካራ ልብስ ነው
ቆዳ	ተፈጥሯዊ የገላ ልብስ፣ ገላን ከልዩ ልዩ ጥቃቶች የሚጠብቅ መከላከያ
በኩር ባለሃገር፣	የልጅ ሁሉ ራስ፣ የመጀመሪያ ልጅ፣ ማህጸን ከፋች፣ ግንበር ቀደም፣ ባላባት ባለመሬት፣ ተወላጅ፣ ተቆጣሪ የሆነ
ባላንጣ	የጥቅም ተጋሪ፣ አምጣ ባይ፣ ተካፋይ
ባሕርይ	የፍጥረት መሠረት፣ ሥር፣ ምንጭ፣ መውጫ፣ መፍለቂያ፣ መገኛ፣ ማለት ነው፡፡
ተንከባላይ	የቡዳ ግብር ሆኖ በእኩለ ሌሊት ራቁትን በመንታ መንገድ ላይ በመንከባለል የሰውን ወዝ ለመሰብሰብ የሚደረግ ሙከራ ነው
አርብ	የመጨረሻዋ የፍጥረት ቀን፣ ፍጥረት ያለቀባት
ክረምት	ወቅቶች የሚሞቱበት ጊዜ፡፡ ምድር የምትጨቀይበትና የምትታጠብበት ወቅት
ወንፈል	ሲበራይ ለማገዝ የተሰበሰቡ ሰዎች፣ ደቦኛ ለማለት ነው፡፡
ወርች	የፊት እግር፣ መተከያና መጽኛ በመሆኑ የገላ ክንፍ ይሉታል፡፡
ዘር ቡዳ	በዘራቸው በቡድነት የሚታመሙ ቡድኖች፣ ወገኖች
ዜጋ	ለባለመሬት ተገዥ የሆነ ሰው"
ገለጣ	ሙሽራ በጫጉላ ቤት ተደብቃ ቆይታ ለሕዝብ ይፋ የምትሆንበት ሥርዓት
ጉልቻ	ከሸክላ፣ ከድንጋይ የተበጀ የድስት፣ የምጣድ የማሰሮ የጋን መጣጃ
ግንፎ ቀሞ	በሠርግ ዋዜማ የሴት ወገን በጋብቻው አለመስማማቱን ድንገት ሲልክ ማታውኑ ተፈልጋ የድግስ ማሞቂያ የምትሆን ሚስት

ገዴ	የአሞራ ወገን፡፡ የዶሮና የወፍ ጠላት፡፡ ምልኳ በስትጓላ ቅጠልያ፣ በስተፊት ነጭ የኾነ፣ ዕድል፣ ክፍል፣ ዕጣ ትነግራለች በሚል ማሚረቻ የሆነች
ጉጉት	የሌሊት አሞራ፣ በፊቼኽቷ ጎትት የምትባል፡፡ እሷ ከሬሞኽች በአካባቢው ሰው ይሞታል ተብሎ ይመለካል
ጋሜ	ድስት ቅርጽ ቁርጥ፣ ልጃገረዶች በሰርጋቸው ዋዜማ የሚላፊቱት የፀጉር ቁርጥ
ግራዋ	ጣዕመ መራራ የሆነ በቅርንጫፉ የሚያፈራና ነጭ አበባ የሚያወጣ ለምለም ዛፍ
ጎባን	የሰው ሚስት ያገባ ወይም የሰው ባል ያገባች ጣውንት፣ ተጋሪ የሆነች ወይም የሆነ ባላንጋራ ማለት ነው
ጠባይ	ሰው ወዶ የሚያመጣው ዐመል፣ ከባሕርይው ሲወጣ የሚከተለው ነገርና ለመርከስ የሚያጋልጥ
ጨለማ	የቀን ማለቂያውና ማብቂያው ሰዓት፤ የብርሃን መድከሚያውና መሞቻው ጊዜ
ጨዋ	በርስት በጉልት የተተከለ፣ ተራ ሰው
ጨዋ በዳ	ከዘራቸው ተለይተው በዳ ለሆኑ ሰዎች መጠሪያ የሆነ፡፡
ጫቅማ	ጉሎ፣ ፍሬ ብዙና ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ ለምለም ዛፍ
ፀጉር	የራስ ልብስ፣ እንደ ሰብል ሁሉ ቀድሞ የሚወጣ የገላ ቡቃያ

1.6. የአማራ ክልል ካርታ



1.7. የምሥራቅ ጎጃም ዞን ካርታ



ማረጋገጫ (Declaration)

ተፈጥሮን መናቅና ሥጋን ማክበር፤ ለክፉ ዐይን አጋላጭ ክስተት በምሥራ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማኅበረሰብ እምነት በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ካሁን በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ፣ ለማንኛውም ተቋም ያልቀረበና የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን፤ የጠቀስኳቸው ድርሳናትም በትክክል በዋቢነት ያገለገሉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ዋልተንጉሥ መኮንን ፊርማ [signature] ቀን 29/07/2007 ዓ/ም

ADAMA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADAMA